# ክፍል አስራ አምስት

# ትምህርትና ስልጠና

## ሀ/ ትምህርት አስተዳደር

### አዋጅ ቁጥር 260/1976 ዓ.ም

### የትምህርት ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ለማጠናከር የወጣ አዋጅ

**«ኢትዮጵያ ትቅደም»**

ከኢትዮጵያ አብዮት አላማዎች አንዱ ኅብረተሰብአዊ የትምህርት ስርአት እንዲበለጽግ ንድፈ ሀሳብንና ተግባርን በማዋሀድ የማምረትና የመመራመር ችሎታ እንዲዳብር ትምህርትን ከሰፊዉ ህዝብ ኑሮ ጋር ማዛመድ በመሆኑ፤

እነዚህን አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ከተወሰዱት ርምጃዎች አንዱ የትምህርት ቤቶች አመራርና አስተዳደር በሰፊዉ ህዝብ ተሳትፎ ጭምር እንዲካሄድ ማድረግ በመሆኑ፤

ሰፊዉ ህዝብ በትምህርት በቶች አመራርና አሰተዳደር ባደረገዉ ተሳትፎ ማይምነት ድል እንዲመታ ኋላ ቀር ባህሎች ተወግደዉ በተራማጅ ባህሎች እንዲተኩ መንገድ በመክፈት የረዳ ቢሆንም የትምህርት አላማዎችን አስተማማኝ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ማጠናከር በማስፈለጉ፤

የጊዜያዊ ወታደራዊ አሰተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ስልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ.ም በአንቀጽ 5/6/ መሰረት የሚከተለዉ ታዉጅዋል፡፡

## ክፍልአንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ አዋጅ "የትምህርት ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 260/1976 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠዉ ካላስፈለገ በቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፡-

   1. "የመንግስት ትምህርት ቤት" ማለት የአንደኛ፣ የመለስተኛ ወይም የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤትን ወይም ሚኒስትሩ የሚሰይማቸዉን እነኝህን የመሳሰሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶችን ነዉ፤

2. "የህዝብ ትምህርት ቤት" ማለት የግል ትም/ቤቶችን የህዝብ ሀብት ለማድረግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 54/1968 ዓ.ም በአንቀጽ 3/1/ መሰረት የህዝብ ሀብት የሆነ ወይም ከዚያ ወዲህ በህዝብ የተቋቋመ ትምህርት ቤት ነዉ፤

3. "ወላጅ" ማለት በመንግስት ወይም በህዝብ ትምህርት ቤት የሚማር የቤተሰብ አባል ያለዉ ሰዉ ነዉ፡፡

4. "የዉስጥ ገቢ" ማለት ከስራ ትምህርት፣ ከማታ ትምህርት፣ ከቲያትር፣ ከምርት ሽያጭ ወይም ከመሳሰሉት የሚገኝ ገቢ ነዉ፤

5. "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነዉ፡፡

3. **የተሻሩ ህጎች**

1. ትምህርት ቤቶችን በሰፊዉ አርሶ አደርና የከተማ ኗሪ ህዝብ ቁጥጥር ስር ለማድረግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 103/1969 ዓ.ም. ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

2. የግል ትምህርት ቤቶችን የህዝብ ሀብት ለምድረግ በመጣዉ አዋጅ ቁጥር 54/1968 ዓ.ም ዉስጥ የተመለከቱት አንቀጽ 5፣6፣7፣8 እና 9 ተሽረዉ በዚህ አዋጅ ተተክተዋል፡፡

4. **የአፈጻጸም ወሰን**

ይህ አዋጅ ሚኒስትሩ የዉጭ ኮሚኒቲ ወይም የሚሲዮን ት/ቤት በሚለዉ፤ በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ሥር በሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፤ በቴክኒክና በሙያ ትምህርት ቤትና በሌላ የመንግስት ወይም የግል መስሪያ ቤት ስር በሚተዳደር ትምህርት ቤት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5. **ለኮሚቴ አባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች**

ለመንግስት ት/ቤት ኮሚቴ ወይም ለህዝብ ት/ቤት ኮሚቴ አባል መሆን የሚችል መልካም ጠባይ ያለው፤ ቢያንስ ማንበብ፤ መፃፍና ማስላት የሚችል፤ ለትምህርት ጥራትና መስፋፋት አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለመንግስት ትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር

6. **ስለኮሚቴ መቋቋም**

1. እንዳንዱ የመንግስት ትም/ቤት የራሱ የሆነ የመንግስት ት/ቤት አመራርና አስተዳደር ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) ይኖረዋል፡፡
2. የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ሚኒስቴሩ ለሚወክለዉ አካል ይሆናል፡፡

7. <u>የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር</u>

የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ የሚከተለዉ ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. ሚኒስትሩ በሚሰጠዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ትምህርት ቤት በስነ ስርዓትና በሚገባ መካሄዱን በበላይነት ይቆጣጠራል፤
2. የሰፊዉ ህዝብ ተራማጅ ባህል በትምህርት ቤቱ ተኳዳኝ ትምህርት ፕሮግራም እንዲንፀባረቅ ርእስ መምህሩ በሚያወጣዉ ፕሮግራም መሰረት ትምህርት ቤቱን ያማክራል፤ይረዳል፤
3. ለትምህርት ቤቱ ከሚኒስቴሩ የሚሰጠዉን ድጋፍ ወይም በጀት ሚኒስትሩ በሚያወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ስራ ላይ መዋሉን በበላይነት ይቆጣጠራል፤
4. ትምህርት ቤቱ በዉስጥ ገቢ እንዲዳብር የሚደረገዉን ጥረት ያበረታታል፤ ያስተባብራል፤ ገቢዉም ሚኒስትሩ በሚያወጣዉ ድንብ ወይም መመሪያ መሰረት ለትምህርት ቤቱ ጥቅም መዋሉን አጠቃላይ ቁጥጥር ያደርጋል፤
5. ንድፈ ሀሳብን ከተግባር ጋር ለማዋሀድ የትምህርት ቤቱ ርእስ መምህር የሚያወጣዉን የትምህርት ፕሮግራም ለማስፈጸም የአካባቢዉን ህዝብና ትምህርት ቤቱን ያስተባብራል፤ በአካባቢዉም የሚገኙትን ባለሙያዎች ጠቃሚ ጥበብ እንዲያስተምሩ ያደርጋል፡፡
6. የትምህርት ቤቱ ንብረት በሚገባ እንዲጠበቅና ንብረቱም ለትምህርት ስራ ለሆነ ተግባር ብቻ እንዲዉል በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡
7. ርእስ መምህሩ ተግባሩን በሚገባ ሳይፈጽም ቢቀር ለአካባቢዉ የትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ መ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

8. <u>የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ አባሎች</u>

1. የመንግስት ትም/ቤት ኮሚቴ የሚከተሉት አባሎች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የትምህርት ቤቱ ርእስ መምህር የሚኒስቴሩ ወኪል በመሆን፤

ለ/ የት·ም/ቤቱ መምህራን ወይም የአስተዳደር ሰራተኞች ያልሆኑ እንደአግባቡ በት·ም/ቤቱ አቅራቢያ የሚገኙ የገበሬ ወይም የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ተወካዮች፤

ሐ/ የመምህራን ማህበር ተወካይ ወይም ይህ በሌለ ጊዜ በት·ም/ቤቱ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች የሚመረጥ አንድ መምህር፤

መ/ የአኢወማ ተወካይ ወይም ይህ በሌለ ጊዜ በመለስተኛ ወይም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎች የሚመረጥ በችሎታዉና በጠባዩ እንዲሁም በዕድሜዉ ብስለት ያለዉ አንድ ተወካይ ተማሪ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት አባሎች ብዛት በአንደኛ ደረጃ ትም/ቤት ከ9 በመለስተኛ ወይም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤት ከ11 አይበልጥም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተዉ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአባሎች ብዛት እንደሁኔታዉ ሚኒስትሩ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ሊወሰን ይችላል፡፡

9. <u>የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ አባሎች አመራረጥ</u>

1. የከተማ ነዋሪዎች የገበሬ ማህበራት ተወካዮቻቸዉን የሚመርጡት በሚከተለዉ አኳኋን ይሆናል፡፡

ሀ/ ትም/ቤቱ የሚገኝዉ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር በተቋቋመበት ከተማ እንደሆነ አባሎቹን የመወከል ስልጣን የአጠቃላይ ማህበሩ ይሆናል፡፡ ሆኖም አገልግሎቱን የሚሰጠዉ በከፊል ለገጠሩ ነዋሪ ህዝብ ከሆነ በት/ቤቱ አካባቢ የሚገኝዉ የወረዳ የገበሬዎች ማህበርና የአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር እያንዳንዳቸዉ ከሶስት የማያንሱ ተወካዮች ይመርጣሉ፤

ለ/ ትም/ቤት የሚገኝዉ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ባልተቋቋመበት ከተማ ዉስጥ የሆነ እንደሆነ የአዉራጃዉ ወይም የወረዳዉ የገበሬ ማህበርና የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር እያንዳንዳቸዉ ሶስት ሶስት ተወካዮች ይመርጣሉ፤

ሐ/ ት/ቤቱ የሚገኝዉ የቀበሌ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ብቻ በተቋቋመበት ከተማ ዉስጥ ከሆነ የወረዳዉ የገበሬ ማህበርና የቀበሌዉ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር እያንዳንዳቸዉ ከሶስት የማያንሱ ተወካዮች ይመርጣሉ፤

መ/ ት/ም/ቤቱ የሚገኘዉ በገበሬ ማህበራት ክልል ዉስጥ ብቻ እንደሆነ በት/ም/ቤቱ አካባቢ የሚገኙት የቀበሌ የገበሬ ማህበራት እያንዳንዳቸዉ ቢያንስ አንድ አንድ ተወካይ ይመርጣሉ፤

ሠ/ የገበሬ ማህበራት ወይም የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ባልተቋቋሙበት ቦታዎች ከሆነ የወላጆች ተወካዮች የኮሚቴዉ አባል በመሆን ስራዉን ያካሂዳሉ፤

2. አጠቃላይ ወይም ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ወይም የአዉራጃ ወይም የወረዳ የገበሬ ማህበራት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተዉ መሰረት የኮሚቴ አባሎችን በሚወክሉበት ጊዜ ተወካዮች ትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኙት የከተማ ነዋሪዎች ወይም የገበሬ ማህበራት የተዉጣጡ መሆናቸዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ፡፡

10. **<u>የስራ ዘመንና አመራር</u>**

1. የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ አባሎች የስራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባሎች በተከታታይ እንደገና የመመረጥ መብት ይኖራቸዋል፡፡
2. የኮሚቴዉ ሊቀ መንበር ከከተማ ነዋሪዎች ወይም ከገበሬ ማህበራት ወይም ከወላጆች ተወካዮች መካከል ይመረጣል፡፡
3. የትምህርት ቤቱ ርእስ መምህር የኮሚቴዉ ም/ሊቀ መንበር ይሆናል፡፡

11. **<u>የመሰብሰቢያ ጊዜ</u>**

1. የመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡
2. የኮሚቴዉ ሊቀመንበር ወይም ጸሐፊዉ ወይም ከኮሚቴዉ አባሎች ከአምስት በላይ ከጠየቁ ኮሚቴዉ እንዲሰበሰብ በማናቸዉም ጊዜ ጥሪ ሊደረግ ይችላል፡፡
3. ከኮሚቴ አባሎች ከግማሽ በላይ በስብሰባዉ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ ሆኖም የከተማ ነዋሪዎች ወይም የገበሬ ማህበራት ወይም የወላጆች ተወካዮች ከተሰበሰቡት አባሎች ቁጥር በልጦ መገኘት ይኖርበታል፡፡
4. ማናቸዉም ዉሳኔ የሚተላለፈዉ በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡ አባሎቹ የሚሰጡት ድምፅ እኩል በእኩል ሆኖ ለሁለት የተከፈለ እንደሆነ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
5. ኮሚቴዉ የራሱን የዉስጥ የስነ ስርአት ደንብ ያወጣል፡፡

12. **<u>የመንግስት ት/ቤት ርእስ መምህር ስልጣንና ተግባር</u>**

1. የመንግስት ትም/ቤት ርእስ መምህር የሚከተለዉ ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

ሀ/ ሚኒስትሩ በሚያወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት የት/ቤቱን መምህራንና ሰራተኞች ይመራል፤ ያስተዳድራል ይቆጣጠራል፡፡

ለ/ ከሚኒስትሩ በሚተላለፍለት ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት የት/ቤቱን ቴክኒክ ነክ ፕሮግራም ያስተባብራል፤ በስራ ላይ ያዉላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ርእስ መምህሩ በሰጠዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታዉን በት/ቤቶች የዉስጥ አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት በየደረጃዉ ለተቋቋመዉ የሚኒስቴሩ መ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የህዝብ ትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር

13.<u>የህግ ሰዉነት</u>

እንዳንዱ የህዝብ ት/ቤት የህግ ሰዉነት ይኖረዋል፡፡

14.<u>ስለኮሚቴ መቋቋም፤</u>

1. እያንዳንዱ የህዝብ ት/ቤት የህዝብ ትም/ቤት አመራርና አስተዳደር ኮሚቴ (ከዚህ በኃላ "የህዝብ ትም/ቤት ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) ይኖረዋል፡፡
2. የህዝብ ት/ቤት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ሚኒስትሩ ለሚወክለዉ አካል ይሆናል፡፡

15.<u>የህዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር፤</u>

የህዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ የሚከተለዉ ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1. ሚኒስትሩ በሚያወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ትምህርት ቤቱ በስነ ስርአትና በሚገባ መካሄዱን ያረጋግጣል፡፡
2. የሰፊዉ ህዝብ ተራማጅ ባህል በትምህርት ቤቱ ተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም እንዲንጸባረቅ ርእስ መምህሩ በሚያወጣዉ ፕሮግራም መሰረት ትምህርት ቤቱን ያማክራል፤ ይረዳል፤
3. ከሚኒስትሩ በሚሰጠዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ለትምህርት የሚከፈለዉን ዋጋ ይወስናል፤
4. የትምህርት ቤቱ ንብረት በሚገባ እንዲጠበቅና ንብረቱም ለትምህርት ስራ ለሆነ ተግባር ብቻ እንዲዉል በበላይነት ይቆጣጠራል፤

5. ንድፈ ሀሳብን ከተግባር ጋር ለማዋሀድ የትም/ቤቱ ርእስ መምህር የሚያወጣዉን ፕሮግራም ለማስፈጸም የአካባቢዉን ህዝብና ትምህርት ቤቱን ያሰተባብራል፤ በአካባቢዉም የሚገኙትን ባለሙያዎች ጠቃሚ ጥበብ እንዲያሰተምሩ ያደርጋል፤
6. ሚኒስትሩ በሚያወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ዕርዳታ ወይም ስጦታ ይቀበላል፤
7. ሚኒስትሩ ስለርዕሰ መምህራን፤ ስለመምህራንና ስለ አስተዳደር ሰራተኞች የሚያወጣው የሕዝብ ትምህርት ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ደንብ ወይም መመሪያ በሥራ ላይ እንዲውል ይረዳል፡፡ በዚሁ መሠረት መምህራንና ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ከሥራ ያሰናብታል፡፡

## 16.<u>የሕዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ አባሎች</u>

ኮሚቴው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት አባሎች ይኖሩታል፡፡

1. ከወላጆች የሚመረጡ የትም/ቤቱ ተቀጣሪዎች ያልሆኑ 6 ተወካዮች፤
2. ት/ቤቱ ከሚገኝበት የቀበሌ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ወይም የቀበሌ የገበሬ ማህበር 2 ተወካዮች፤
3. የመምህራን ማህበር ተወካይ ወይም ይህ በሌለ ጊዜ በት/ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች የሚመረጥ 1 መምህር፤
4. የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፤
5. ከኢአ.ወማ ወይም ይህ በሌለ ጊዜ በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚመረጥ በችሎታና በጠባዩ እንዲሁም በእድሜው ብስለት ያለው አንድ ተወካይ ተማሪ፡፡

## 17.<u>ስለሕዝብ ትም/ቤት ኮሚቴ ሊቀመንበር</u>

የህዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ሊቀመንበር፤

1. ሚኒስትሩ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት የሕዝብ ት/ቤትን ርዕሰ መምህር ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፡፡
2. ትም/ቤቱ በሚከስ ወይም በሚከሰስበት ጊዜ ት/ቤቱን ይወክላል፡፡

## 18.<u>የሥራ ዘመንና አመራር</u>

1. የህዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ አባሎች የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም አባሎቹ በተከታታይ የመመረጥ መብት ይኖራቸዋል፡፡
2. የኮሚቴው ሊቀመንበር ከወላጆች ተወካዮች መካከል ይመረጣል፡፡
3. የሕዝብ ት/ቤት ርዕሰ መምህር የኮሚቴው ም/ሊቀመንበር ይሆናል፡፡

19. <u>የመሰብሰቢያ ጊዜ</u>

1. የሕዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡
2. የኮሚቴው ሊቀመንበር ወይም ጸሐፊው ወይም ከኮሚቴው አባሎች ከአራት በላይ ከጠየቁ ኮሚቴው እንዲሰበሰብ በማናቸውም ጊዜ ጥሪ ሊደረግ ይችላል፡፡
3. ኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ በስብሰባው ሲገኙ ይሆናል፡፡ ሆኖም የወላጆች ተወካዮች ቁጥር ከሌሎቹ መብለጥ ይኖርበታል፡፡
4. ማናቸውም ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ አባሎቹ የሚሰጡት ድምጽ እኩል ሆኖ ለሁለት የተከፈለ እንደሆነ ሊቀ መንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
5. ኮሚቴው የራሱን የውስጥ የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

20. <u>የሕዝብ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ሥልጣንና ተግባር፤</u>

የህዝብ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ከሕዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ የሚሰጠውን አጠቃላይ መመሪያ በመከተል፤

1. ሚኒስትሩ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት የትምህርት ቤቱን መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
2. ከሚኒስትሩ በሚተላለፍለት ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት የትም/ቤቱን ቴክኒክ ነክ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፤ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

21. <u>ለግልግል ዳኛ ስለመምራት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው በሕዝብ ትምህርት ቤት የሠራተኞች ጉዳይ ደንብ ላይ የሚነሱ ክርክሮች ለአንድ ወይም ከአንድ ለበለጠ የግልግል ዳኞች መመራት ይኖርበታል፡፡

22. <u>የግልግል ዳኞች አመራረጥ</u>

1. የግልግል ዳኛ ወይም ዳኞች በተከራካሪ ወገኖች ይመረጣሉ፡፡ ሆኖም የግልግል ዳኞቹ ቁጥር ከሶስት መብለጥ አይኖርበትም፡፡
2. በግልግል ዳኛ ወይም ዳኞች አመራረጥ ላይ ተከራካሪ ወገኖች ያልተስማሙ እንደሆነ ሚኒስቴሩ ይመርጥላቸዋል፡፡

23. <u>የግልግል ሥነ ሥርዓት</u>

የግልግል ሥነ ሥርዓት የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ በተደነገጉት አጠቃላይ ደንቦች መሠረት ይሆናል፡፡

24.<u>ውሳኔ</u>

የግልግል ውሳኔ ለተከራካሪዎቹ ወገኖች በጽሑፍ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

25.<u>አቤቱታ</u>

1. በግልግሉ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በሠላሳ ቀኖች ውስጥ ለሚኒስቴሩ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ የግልግሉን ውሳኔ ሊያጸድቀው፤ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>መሸጋገሪያና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

26.<u>ከኪራይ ነጻ ስለመሆን</u>

የሕዝብ ትም/ቤቶች የህዝብ ሀብት ከሆኑበት ቀን ጀምሮ ከቤት ኪራይ ክፍያ ነጻ ናቸው፡፡

27.<u>ስለንብረት መከበርና መሸጥ</u>

ለትምህርት መስጫ የሚያገለግሉ የሕዝብ ት/ቤት መሣሪያዎችና ዕቃዎች በዕዳ ምክንያት አይከበሩም፤ አይሸጡም፡፡

28.<u>መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ</u>

በአዋጅ ቁጥር 103/1969 እና 54/1968 ዓ.ም መሠረት ተቋቋመው የነበሩት ኮሚቴዎች መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው እንደሁኔታው አግባብ ላለው ለመንግስት ትምህርት ቤት ኮሚቴ ወይም ለህዝብ ትምህርት ቤት ተላልፏል፡፡

29.<u>የቀድሞ ኮሚቴ ኃላፊነት</u>

በአዋጅ ቁጥር 103/1969 እና 54/1968 ዓ.ም መሠረት የተቋቋሙት ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 እና 14 መሠረት ኮሚቴዎቹ እስኪቋቋሙ ድረስ ሥራውን በነበረው አሰራር መሠረት የማካሄድ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

30.<u>የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት</u>

ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 64/1968 ዓ.ም በሕዝብ ትምህርት ቤት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

31.<u>የሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሚኒስትሩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1. ስለየዓመቱ የትምህርት ወቅት፤ በየትምህርት ወቅት መሸፈን ስላለበት የትምህርት መጠን፤ ስለትምህርት ቤቶች ለእረፍት መዘጋት፤ ትምህርት በፈረቃ ስለመስጠት፣ ስለፈተና፣ ስለትምህርት ቤቶች አደረጃጀትና አስተዳደር እና በአጠቃላይ ስለስርዓተ ትምህርቱ መሪያዎች ያወጣል፤ ለመንግስትና ለሕዝብ ትምህርት ቤቶች ያስተላልፋል በሥራ መተርጎማቸውን ይቆጣጠራል፤
2. ስለትምህርትና ትም/ቤቶች መስፋፋት ደንብና መመሪያ ያወጣል፤ ከመንግስትና ከሕዝብ ትም/ቤት ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ሐሳቦች አጥንቶ ይወስናል፡፡
3. ተጠሪነቱ ለትምህርት አመራርና አስተዳደር ኮሚቴ የሆነ የወላጆች ኮሚቴ እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡
4. የመንግስት ወይም የሕዝብ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ሥራውን በሚገባ ያላከናወነ እንደሆነ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
5. ይህን አዋጅ በሚገባ ስራ ላይ ለማዋል ደንብ ወይም መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡ ደንቡ ወይም መመሪያው በሥራ ላይ መዋሉን በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

32.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

የከተማ ነዋሪዎች ወይም የገበሬ ማህበራት፤

1. በክልላቸው ውስጥ ያሉትን የትምህርት ቤቶች ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙና ሥራቸውም እንዲቀላጠፍ በመርዳት፤
2. በአካባቢያቸው ትምህርት በጥራት እንዲስፋፋ የበኩላቸውን ጥረት በማድረግ፤
3. ትምህርት ቤቶች በተግባራዊ ትምህርት ፕሮግራም በሚያደርጉት ጥረት አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት፤
4. ለትህምርት ቤቶች ለሰውነት ማለማመጃ እና ለተግባራዊ ለትምህርት በቂ መሬት መከለሉን በማረጋገጥ፤
5. የትምህርት ቤቱ የውስጥ ገቢ እንዲዳብር በማስተባበር፤

አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

33.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 5 ቀን 1976 ዓ.ም**

**ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ**

## ደንብ ቁጥር 206/1987 ዓ.ም

## ስለግል የትምህርት ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የግል ትምህርት ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 206/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "የግል ትምህርት ተቋም" ማለት በግል ባለሀብት የሚካሄድና መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ወይም ሥልጠና በማንኛውም ደረጃ የሚሰጥበት ተቋም ሲሆን፤ አጸደ ሕፃናትን ይጨምራል፤
   2. "መደበኛ ትምህርት" ማለት በተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት የሚመራና በዕድሜ በጊዜና በዘመን ተተምኖ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ያለውን የትምህርት ሥርዓት የሚያመለክት ሲሆን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ያጠቃልላል፤
   3. "መደበኛ ያልሆነ ትምህርት" ማለት አብዛኛውን ጊዜ በዕድሜ ያልተገደበ ሆኖ ትምህርት ላልደረሳቸውና ላቋረጡ ሕፃናትና ወጣቶች እንዲሁም የትምህርት ዕድል ላላጋጠማቸው ጐልማሶች የሚሰጥ ትምህርት፣ የተለያየ ሥልጠናና የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን የሚያካትት ነው፤
   4. "አጸደ ሕፃናት" ማለት ዕድሜያቸው ከ4-6 ዓመት የሆኑ ሕፃናት በአካል፣ በአዕምሮ፣ በሥነልቦና፣ በስሜትና በማኅበራዊ ኑሮ እየታነጹ የሚያድጉበትና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚዘጋጁበት ተቋም ነው፤

5. “የከፍተኛ ትምህርት ተቋም” ማለት ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ትምህርት የሚሰጥበት ተቋም ነው፤
6. “ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን” ማለት እንደ አግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር የትምህርት ቢሮ ነው፤
7. “ሚኒስቴር” ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፣
8. “የውጭ አገር ባለሀብት” ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር በወጣው አዋጅ ቁጥር 15/1984[1] የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን፣**

ይህ ደንብ የውጭ ኮሚኒቲ፣ የሕዝብ፣ የሚሲዮን፣ የቤተክህነት፣ የመስጊድና ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ትምህርት ቤቶችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለፈቃድ አሰጣጥ

4. **ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን፣**
1. ለግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችና በውጭ አገር ባለሀብት ለሚካሄድ ማናቸውም የትምህርት ተቋም ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡
2. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በስተቀር በአገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች ለማካሄዱ ሌሎች የትምህርት ተቋሞች ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች የትምህርት ቢሮዎች ይሆናል፡፡

5. **ስለፈቃድ አስፈላጊነት**

የትምህርት ተቋም ለማቋቋም ወይም በመካሄድ ላይ ያለ የትምህርት ተቋም ደረጃ ለማሳደግ የሚፈልግ ማንኛውም የግል ባለሀብት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

6. **ፈቃድ ለማውጣት ስለሚቀርብ ማመልከቻ**
1. የትምህርት ተቋም ፈቃድ ለማውጣት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም በትምህርት ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ አግባብ

[1] ይህ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ በ18/63 (2004) አ. 769 አንቀፅ 2(6) ተመልከት፡፡

ያላቸው መረጃዎችን የያዘ ማመልከቻ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

2. አመልካቹ የውጭ አገር ባለሀብት ከሆነ ወይም ከብር 250ሺ.ህ ያላነሰ የኢንቨስትመንት ካፒታል ኢንቨስት የሚያደርግ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር በወጣው አዋጅ ቁጥር 15/1984 መሠረት የተሰጠ የኢንቨስትመንት ሠርተፊኬት አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

7. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት የትምህርት ተቋሙ የወጣውን ስታንዳርድ የጠበቀ መሆኑን ገምግሞ ብቁነቱን ሲያረጋግጥ የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የቀረበለትን ማመልከቻ ያልተቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሑፍ በሶስት ወር ውስጥ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

8. <u>የማስፋፋትና የማሻሻል ፈቃድ፣</u>

1. የትምህርት ተቋሙን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚፈልግ ባለፈቃድ በቅድሚያ ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን ማስፈቀድ አለበት፡፡

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የትምህርት ተቀሙ የተወሰነለትን ስታንዳርድ ጠብቆ የሚስፋፋ ወይም የሚሻሻል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ማስፋፋቱ ወይም ማሻሻሉ እንዲደረግ በጽሑፍ ይፈቅዳል፡፡

9. <u>ፈቃድ ስለማደስ፣</u>

1. የግል ትምህርት ተቋም በየሁለት ዓመቱ እየተገመገመ አዲሱ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት ፈቃዱ መታደስ አለበት፡፡

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲቀርብለት የትምህርት ተቋሙ የተወሰነለትን ስታንዳርድ ጠብቆ እየሠራ መሆኑን አረጋግጦ ፈቃዱን ያድሳል፡፡

3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄውን ያልተቀበለው ከሆነ፣ ያልተቀበለበትን ምክንያት አዲሱ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ ከ3 ወር በፊት ለአመልካቹ በጽሑፍ ያስታውቀዋል፡፡

10. <u>ስለፈቃድ ክፍያ</u>

1. ለግል የትምህርት ተቋም ፈቃድ ለማውጣትና ለማሳደስ እንዲሁም ለማስፋፊያና ማሻሻያ ፈቃድ የሚደረገው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡
2. በሰንጠረዡ ላይ ለመደበኛ ትምህርት ተቋም የተመለከተው የፈቃድ ክፍያ በተመሳሳይ ደረጃ ለሚገኙ የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ተቋማትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

11. <u>ምትክ ፈቃድ ስለመስጠት፣</u>

1. የተሰጠው የግል ትምህርት ተቋም ፈቃድ የተበላሸበት ማንኛውም ባለፈቃድ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት አመልካቹ የተበላሸውን ፈቃድ እንዲመልስ ካደረገ በኋላ ምትክ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
3. የተሰጠው የግል ትምህርት ተቋም ፈቃድ የጠፋበት ማንኛውም ባለፈቃድ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ፈቃዱ እንዴት እንደጠፋ የሚገልጽ ራሱ የፈረመውን መግለጫ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
4. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተገቢው መግለጫ ሲቀርብለት አመልካቹ ፈቃድ የጠፋበትና ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀ መሆኑን የሚገልጽ የጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣ ካደረገ ከአንድ ወር በኋላ ምትክ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

12. <u>ፈቃድ ስለመሠረዝ፣</u>

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የግል ትምህርት ተቋም ፈቃድን ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊሠርዝ ይችላል፤

   ሀ/ ፈቃዱ የተሰጠው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

   ለ/ ባለፈቃዱ የትምህርት ተቋሙን ስታንዳርድ ባለመጠበቁ ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ባለማክበሩ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በማስጠንቀቂያው በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ያላስተካከለ እንደሆነ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተወሰደ ፈቃድ የመሠረዝ እርምጃ ተፈጻሚ የሚሆነው የተጀመረው የትምህርት ዘመን ሲያበቃ ይሆናል፡፡

13. <u>ፈቃድ ስለመመለስ፣</u>

1. ፈቃዱ የተሠረዘበት ወይም ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን መመለስ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ባለፈቃድ የትምህርት ተቋሙን ደረጃ አሳድጎ አዲስ ፈቃድ ለማግኘት የቀድሞውን ፈቃድ መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. <u>የግል ትምህርት ተቋሞች ስለሚከተሉት ሥርዓተ-ትምህርት</u>

1. የአፀደ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃና መደበኛ የሆነ የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ተቋም ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ያወጣውን ሥርዓተ ትምህርት የመከተልና ብሔራዊ ፈተናዎች በሚሰጡባቸው ክፍሎች ተማሪዎች እንዲፈተኑ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
2. የግል ከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ይዘት ሚኒስቴሩ ያወጣውን ስታንዳርድ የተከተለ ይሆናል፡፡
3. የግል ትምህርት ተቋም ሚኒስቴሩ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት ማስረጃ ይሰጣል፡፡

15. <u>ስለግል ትምህርት ተቋም መምህራን ብቃት</u>

የማንኛውም መደበኛ የሆነ የግል ትምህርት ተቋም ርዕሰ መምህርና መምህራን ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት ለደረጃው የሚመጥን ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

16. <u>ስለሪኮርዶችና ሰነዶች</u>

ማንኛውም የግል ትምህርት ተቋም የተማሪዎችንና የመምህራንን ሪኮርዶችና በጥንቃቄ መያዝ አለበት፡፡

17. <u>የትምህርት ክፍያን ስለማሳደግ፣</u>

1. በማንኛውም የግል ትምህርት ተቋም የሚሰበሰብ የትምህርት ክፍያ በትምህርት ዘመን መካከል የማሳደግ ለውጥ ሊደረግበት አይችልም፡፡
2. ባለፈቃዱ የክፍያ ጭማሪ ለማድረግ ከወሰነ፣ የተያዘው የትምህርት ዘመን ከማብቃቱ ቢያንስ ከ3 ወር በፊት ተጠቃሚዎች እንዲያውቁት አድርጎ አዲሱን

ተመን በሥራ ላይ የሚያውለው በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ይሆናል፡፡

18. <u>መረጃ ስለማቅረብ፣</u>

1. የግል ትምህርት ተቋም የሚያካሂድ ማንኛውም ባለ ፈቃድ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ ሲጠይቅ ስለሥራው እንቅስቃሴ ተገቢ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የቀረበለትን መረጃ በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በምሥጢር ይጠብቃል፡፡

19. <u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

1. በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የተመደበ ተቆጣጣሪ ማንኛውም የግል ትምህርት ተቋም የወጣለትን ስታንዳርድ ጠብቆና የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን አክብሮ እየሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ በሥራ ሰዓት ወደ ትምህርት ተቋሙ ለመግባትና ለመቆጣጠር ይችላል፡፡
2. ተቆጣጣሪው የተሰጠውን የሥልጣን ማረጋገጫና የመታወቂያ ወረቀት ቁጥጥሩ ለሚካሄድበት የትምህርት ተቋም ባለቤት ወይም ለወኪሉ ማሳየት አለበት፡፡

20. <u>የወላጆችና የሕብረተሰቡ ተሳትፎ</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ በሚያካሂደው የትምህርት ተቋም አመራርና ቁጥጥር ወላጆችና ኅብረተሰቡ ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡
2. በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የተመደበ ተቆጣጣሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 መሠረት ቁጥጥር ሲያደርግ ወላጆችና ኅብረተሰቡ በትምህርት ተቋሙ አመራር ያላቸውን የተሳትፎ ደረጃ ይመረምራል፡፡

21. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ያለፈቃድ ሲካሄድ የተገኘ የግል ትምህርት ተቋምን መዝጋት ይችላል፡፡

22. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የተቋቋመ የግል ትምህርት ተቋም በማካሄድ ላይ ያለ ማንኛውም የግል ባለሀብት ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማመልከቻውን አቅርቦ በዚህ ደንብ መሠረት ማውጣት አለበት፡፡

23. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩና የክልል የትምህርት ቢሮዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን እንደአግባቡ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

24. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 27 ቀን 1987 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት**

**ጠቅላይ ሚኒስትር፣**

**<u>ጠንጠረዥ</u>**

**<u>የፈቃድ ክፍያ</u>**

| ተ.ቁ | የትምህርት ተቋሙ ዓይነት | ደረጃ | ለፈቃድ ማውጫ (ብር) | ለፈቃድ ማሳደሻ (ብር) | ለማስፋፊያ ማሻሻያ ፈቃድ (ብር) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አፀደ ሕፃናት | - | 250 | 200 | 200 |
| 2. | የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተቋም | 1-8 | 400 | 300 | 300 |
| 3. | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም | 9-10<br>11-12<br>9-12 | 750<br>1000<br>1000 | 500<br>750<br>750 | 500<br>750<br>750 |
| 4. | ከአፀደ ሕፃናት እስከ መጀመሪያ ደረጃ ያለውን የሚያጠቃልል ተቋም | አፀ-8 | 650 | 500 | 500 |
| 5. | ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የሚያጠቃልል ተቋም | 1-12 | 1250 | 1000 | 1000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6. | ከአፀደ ሕፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የሚያጠቃልል ተቋም | አፀ-12 | 1500 | 1100 | 1100 |
| 7. | የከፍተኛ ትምህርት ተቋም | - | 3000 | 2000 | 2000 |
| 8. | መደበኛ ያልሆነ የትምህርት ተቋም | - | 1200 | 800 | 800 |

## ደንብ ቁጥር 154/2000 ዓ.ም

## የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995 አንቀጽ 56(3) እና አንቀጽ 99 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

   1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
   2. "ተቋም" ማለት በመንግሥት አካል ሥር የሚተዳደር ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ትምህርት የሚሰጥበትና በማንኛውም ክልል፣ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ከፌደራል መንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ተቋም ነው፤
   3. "አሰሪ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመራቂን ቀጥሮ የሚያሠራ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ወይም ዓለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ድርጅት ሲሆን በሙያው በግሉ ሥራ የተሰማራ ሰውን ይጨምራል፤
   4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
   5. "ተጠቃሚ" ማለት ማንኛውም በመንግሥት ተቋም ለመማርና የሚፈለግበትን ወጪ ለመክፈል ከተቋሙ ጋር ውለታ ገብቶ የከፍተኛ ትምህርት ወይም ሥልጠና የሚከታተል ተማሪ ነው፤
   6. "ወጪ መጋራት" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚና መንግሥት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ የሚጋሩበት ሥርዓት ነው፤

7. "ከምረቃ በኋላ ከገቢ ተከፋይ" ማለት ማንኛውም ተጠቃሚ በገባው ውለታ መሠረት የሚጋራውን የወጪ መጠን ከወርሃዊ ገቢው በታክስ መልክ እየቀነሰ የሚከፍልበት ሥርዓት ነው፡፡

3. <u>የደንቡ ተፈጻሚነት</u>

ይህ ደንብ 1996 የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ከነበሩበት ዓመት ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>የተጠቃሚው ድርሻና አፈጻጸም</u>

   1. መንግሥት ለምግብና ለመኝታ የሚያወጣውን ወጪ ሙሉ በሙሉና፣ ለትምህርት ከሚወጣው ወጪ ለመነሻ 15 ፐርሰንት ያላነሰ ተሰልቶ ተጠቃሚዎች እንዲጋሩ ይደረጋል፡፡ ይህም ድርሻ በየተቋሙና በየመርሐ ግብሩ በሚወጣው ወጪ ላይ ተመስርቶ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በቅድሚያ ለተጠቃሚው መገለጽ አለበት፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸውን መጠን ለመክፈል እያንዳንዱ ተጠቃሚ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከተቋሙ ጋር የጽሑፍ ውል በማድረግ፣ ትምህርቱን እንዲከታተል ይደረጋል፡፡ ይህ የውለታ ሰነድ በሕግ ፊት የጸና ይሆናል፡፡
   3. ተጠቃሚው ትምህርቱን ካቋረጠ ወይም ካጠናቀቀ መክፈል የሚገባውን መጠን የሚያሳይ መረጃ በተቋሙ ይሰጠዋል። ይህ መረጃ የተጠቃሚውን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ፎቶና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን የያዘ ይሆናል፡፡
   4. ለተማሪው ትምህርትና ሥልጠና የሚወጣው ወጪ መጠን ቢያንስ በየሶስት ዓመቱ የሚከለስ ይሆናል፣ ለዚሁም ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል።
   5. በታሳቢ ተምሮ ከምረቃ በኋላ ከገቢው ተከፋይ በሆነ መልክ እየተቀነሰ በገንዘብ ወይም በአገልግሎት የሚከፍል ተጠቃሚ በዜግነት ኢትዮጵያዊ መሆን ይኖርበታል።

5. <u>ግበረታቻዎች</u>

   1. በየዓመቱ የሚፈለግባቸውን መጠን ሙሉ በሙሉ በቅድሚያ ወይም እስከሚመረቁ ድረስ የሚፈለግባቸውን በጠቅላላ በቅድሚያ ወይም በየዓመቱ መጨረሻ ላይ ለዓመቱ የተማሩበትን የወጪ መጋራት ክፍያ በግል ወይም በድርጅቶች ድጋፍ

ለሚከፍሉ ተጠቃሚዎች የሚደረግላቸው ቅናሽ እንደ ጊዜው የገንዘብ ዋጋ እየታየ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

2. አገልግሎት ለመስጠት ውል የገቡ ተጠቃሚዎች በድህረ ምረቃ የትምህርት እድል አሰጣጥ ላይ ቅድሚያ ያገኛሉ።

6. <u>የወጭ ድርሻ አከፋፈል</u>

1. ተጠቃሚው ከምረቃ በኋላ ሥራ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ወይም ከምረቃ በኋላ ከአንድ ዓመት በኋላ የሚፈለግበትን ክፍያ ተቀጣሪ ከሆነ ከወር ገቢው በየወሩ ቢያንስ አሥር በመቶ ከገቢ ተከፋይ በሆነ መልክ እየቀነሰ ወይም በሙያው በግሉ የተሰማራ ከሆነ ከዓመት ገቢው በዓመቱ የሚፈለግበትን መጠን ተሰልቶ መክፈል አለበት፡፡

2. ተጠቃሚው የሚፈለግበት ጠቅላላ መጠን የአገልግሎት ክፍያ ወይም ወለድ የሚከፈልበት ሆኖ ውለታ በተገባበት ወቅት በሀገሪቱ የሚሠራበት የተቀማጭ ወለድ መጠን ይሆናል፡፡ የወለዱ ክፍያ የሚታሰበው ተጠቃሚው ከተመረቀ ከአንድ ዓመት የእፎይታ ጊዜ በኋላ ነው፡፡ የወለዱ መጠንም ውለታ የተፈጸመባቸው የትምህርት ዘመናት የተቀማጭ ገንዘብ አማካይ የወለድ ምጣኔ ይሆናል፡፡

3. ተጠቃሚው ያለበትን የክፍያ ግዴታ እንደ ትምህርት መርሃ ግብሩ ርዝመትና ዓይነት ከ15 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ማጠናቀቅ ይኖርበታል።

4. ተጠቃሚው ትምህርቱን ሳይጨርስ በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥም እስካቋረጠበት ጊዜ የሚፈለግበትን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል። ሆኖም ትምህርቱን ያቋረጠው በሀገራዊ ጥሪዎችና ተልዕኮዎች ከሆነ ክፍያው መሰረዝ ይኖርበታል።

5. ተጠቃሚው ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን ክፍያው በአሠሪው አማካኝነት በየወሩ ከደመወዙ እየተቀነሰ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ይህ ተቀናሽ በማናቸውም ጊዜ ተጠቃሚው በዚህ ደንብ በአንቀጽ 8(1)(ሐ) መሠረት ክፍ ካላደረገው በስተቀር ከገቢ ተከፋይ ተቀናሹ መጠን ከተጠቃሚው የወር ደመወዝ 1/3ኛ ሊበልጥ አይገባም፡፡

6. ተጠቃሚው በውጭ ቅጥር ወይም በግል ሥራ ምክንያት በውጭ ሀገር የሚኖር ከሆነ፣ ክፍያው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፡፡

7. <u>የአሰሪዎች ግዴታ</u>

1. ይህ ደንብ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት የተከታተለን ሰው የሚቀጥር ማንኛውም አሠሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

ሀ/ ተቀጣሪው ከተማረበት ተቋም የተሰጠውን የሚፈለግበትን ክፍያ መጠን የሚገልጽ መረጃና በየወሩ ከደመወዙ እየተቀነሰ ገቢ ሊደረግ የሚገባውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የተሰጠ ማስረጃ እንዲያቀርብ የመጠየቅ፤

ለ/ የተቀጣሪዎችን ዝርዝር በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጽሑፍ የማሳወቅ፤

ሐ/ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በቀረበለት መረጃ እና በዚህ ደንብ በአንቀጽ 8(1)(ሐ) መሠረት ከተቀጣሪው ደመወዝ በየወሩ እየቀነሰ የማስተላለፍ፣

መ/ ተቀጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተጠቀሰውን መረጃ ወይም ከእዳ ክፍያ ነፃ መሆኑን የሚገልጽ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ መረጃ ካላቀረበ የተቀጣሪውን የወር ደመወዝ 1/3ኛ በመያዝ ሁኔታውን የማሳወቅና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያገኘው መግለጫ መሠረት ከሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መፍትሄ መስጠት ይኖርበታል፤

ሠ/ ማንኛውም ተጠቃሚ ሥራ በሚለቅበት ወቅት የወጪ መጋራት ክፍያ ስለመክፈሉ ወይም በአገልግሎት ስለመወጣቱ በመልቀቂያ ወረቀቱ ላይ ማረጋገጥ አለበት፣

ረ/ በአገልግሎት ግዴታቸውን እንዲወጡ ከተመደቡ በኋላ ግዴታቸውን ያልተወጡትን ተጠቃሚዎች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም አሠሪ ሳይሰበሰብ በቀረው ክፍያ መጠን እና ባልተከፈለባቸው ወራት በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

8. <u>የተጠቃሚው ግዴታ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6(1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀጣሪው በማናቸውም አሠሪ ተቀጥሮ ሲሠራ የሚከተለው ግዴታ ይኖርበታል፤

ሀ/ የሚሰራበትን ሙሉ አድራሻ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት በሌላ ቦታ ሠርቶ ከሆነ ይህንኑ መረጃ ለአሠሪው በመስጠት በአሠሪው አማካኝነት ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የማሳወቅ፤

ለ/ የሚፈለግበትን ክፍያ በየወሩ ከምረቃ በኋላ ከገቢ በተከፋይ መልክ ተቀናሽ በማድረግ መክፈል የመጀመር፤

ሐ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4(2) የገባውን የውለታ ሰነድ ለአሠሪው የመስጠትና አሠሪው ተገቢውን መጠን በየወሩ እየቀነሰ ለመንግሥት እንዲያስገባ የማድ ረግ፣ ይህ መጠን በዚህ ደንብ አንቀጽ 6(1) ከተገለጸው ማነስ አይችልም፤

መ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4(2) እና አንቀጽ 8(1)(ሐ) መሠረት የተደረገ ስምምነት ቢኖርም በጤናው ዘርፍ የሰለጠነ ወይም በመሰልጠን ላይ የሚገኝ ተጠቃሚ ግዴታውን በአገልግሎት ብቻ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም መስክ ገንዘብ በመክፈል ለመሰልጠን የተገባ ግዴታ ወደ አገልግሎት፣ በአገልግሎት የተገባ ግዴታ ደግሞ ወደ ገንዘብ ክፍያ እንዲለወጥ ሚኒስቴሩ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፤

ሠ/ ማንኛውም በግል ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም ያለሥራ የተቀመጠ ተጠቃሚ ተመርቆ ከወጣ አንድ ዓመት የእፎይታ ጊዜ በኋላ በአቅራቢያው በሚገኝ የግብር አስገቢ መሥሪያ ቤት ተመዝግቦ መረጃ የመያዝ ግዴታ አለበት፤

ረ/ የአገልግሎት ግዴታውን ያልተወጣ ማንኛውም ተጠቃሚ ትምህርቱ የፈጀውን አጠቃላይ ወጪ እና የዚህኑ ወጪ ሃምሣ በመቶ መቀጫ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ (6) የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም ተጠቃሚ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

9. <u>ዕዳን ስለመሰረዝ</u>

ተጠቃሚው በሙሉ መሠረት ግዴታውን ሳያጓድል ክፍያውን ሲፈጽም ቆይቶ ጠቅላላ ክፍያው ከመጠናቀቁ በፊት በጡረታ ቢገለል ወይም ቢሞት ቀሪው ብድር ይሰረዛል፡፡

10. <u>የትምህርት ሚኒስቴር ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተለው ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

1. ይህ ደንብ ሥራ ላይ መዋሉን የመከታተልና የማረጋገጥ፤
2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከተጠቃሚዎች የሚጠይቁትን የክፍያ ተመን የማጽደቅ፤
3. ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት፤
4. የውለታ ሰነዶችን ይዘት የመወሰን፤
5. የወጪ መጋራቱ ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልግሎት የሚፈጸምበትን መስኮችና ዝርዝር መመሪያዎች የማውጣት፡፡

11. <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ኃላፊነት</u>

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

1. ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈለገውን መጠንና ወርሀዊ ክፍያውን ጭምር ለተጠቃሚውና ቀጣሪዎች የማሳወቅ፤
2. አጠቃላይ ክፍያውን የመሰብሰብ ፣ የመከታተልና የመቆጣጠር፤
3. ለዚሁ ተፈጻሚነት አስፈላጊውን ሥርዓትና ድርጅት የመፍጠርና ተግባራዊ የማድረግ፤
4. የሚፈለግበትን ክፍያ ላጠናቀቀ ተጠቃሚ ተገቢ መረጃ ወይም ሠርተፊኬት የመስጠት፤
5. ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ የግብር ክፍያ መለያ ቁጥር የመስጠት፤
6. በክልሎች ውስጥ ከሚቀጠሩ ተጠቃሚዎች የሚፈለገው ተቀናሽ መጠን ለመንግሥት ገቢ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
7. የክልሎችና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮዎች ከተጠቃሚዎች የሚፈለገውን የወጪ መጋራት ክፍያ እንዲሰበስቡ ውክልና የመስጠት፤
8. የወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ በሚፈለገው ሁኔታ እንዲከናወን በልዩ ልዩ መንገዶች ቅስቀሳ የማካሄድ፡፡

12. <u>የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤

1. የወጪ መጋራት ሥርዓቱን ተፈጻሚነት የመከታተል፤
2. በየትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ተጠቃሚው እንዲጋራ የሚጠበቅበትን ወጪ አስልቶ የመግለጽ፤ ተጠቃሚውን በተመለከተ ተገቢውን መረጃ አደራጅቶ የመያዝ፤
3. ከተጠቃሚዎቹ የሚፈለገውን ወጪ አጠናቅሮ ተጠቃሚው ከተቋሙ ሲለቅ አስፈላጊ መረጃ የመስጠት፤
4. የወጪ መጋራትን ሥራ የሚከታተል የሥራ ክፍል ማደራጀት፤
5. ተቃሚዎች የሚፈጽሙትን የቅድሚያ ክፍያ በመሰብሰብ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ፤
6. በየትምህርት ዘመኑ ተመራቂዎችና ያቋረጡትን ተጠቃሚዎች ዝርዝር፣ ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈለገውን የወጪ መጋራት መጠን በመግለጽ ለጉምሩክ አግባብ ላላቸው አካላት የማሳወቅ፤
7. በአገልግሎት እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸውን ተጠቃሚዎች የአገልግሎት ግዴታቸውን እስኪወጡ ጊዜ ድረስ፣ በገንዘብ ግዴታ የገቡ ተጠቃሚዎች ክፍያ እስኪያጠናቅቁ ወይም ለክፍያው ዋስትና እስኪያቀርቡ ድረስ ጊዜያዊም ሆነ ዋናውን የትምህርት ማስረጃና ትራንስክሪፕት (ኦፊሻሉንም ጨምሮ) በጥንቃቄ የማስቀመጥ፣ ለተጠቃሚውም ሆነ ለማንኛውም ሦስተኛ ወገን መረጃ እንዳይሰጥ የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ፡፡

13. <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሥልጣንና ሀላፊነት</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ክፍያ አፈጻጸም ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን የመምራት የመከታተልና የማስተባበር፣ እና
2. ከክፍያ አሰባሰብና አፈጻጸም ጋር በተያያዘ መመሪያዎችን የማውጣት፡፡

14. <u>ከሥልጠና በኋላ አገልግሎት የሚፈፀምባቸው መሥሪያ ቤቶች ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

ወደፊት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሌሎች የሥልጠና መስኮች እንደአስፈላጊነቱ እየታየ የሚወሰን ሆኖ በትምህርትና በጤና ሙያ ሰልጣኞች ግዴታቸውን በአገልግሎት ብቻ የሚወጡ ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶችም የሚከተለው ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤

1. ከመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ባለሙያዎች ከሰለጠኑበት ዓመት ሳልበለጠ ጊዜ በፌደራልና በክልል ተቋማት ውስጥ ተደልድለው አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
2. በሀገር ውስጥ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ባለሙያዎች በፈጻሙት ውለታ መሠረት አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ፣ ግዴታቸውን እስካልተወጡ ድረስ በማንኛውም ሙያ የሥራ ዘርፍ እንዳይሰማሩ የሙያ ፈቃዳቸውን የመሰረዝ ለአፈጻጸሙም መመሪያ የማውጣት፤
3. አገልግሎታቸውን ባልተወጡ ባለሙያዎች ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለትምህርት ሚኒስቴር የማሳወቅ፡፡

15. <u>የቅድሚያ ክፍያን ተመላሽ ስለማድረግ</u>

የወጪ መጋራት ክፍያ አስቀድሞ የፈጸመ ተጠቃሚ ትምህርቱን ቢያቋርጥ በተቋሙ ለቆየበት ጊዜ የሚፈለግበት ሂሣብ ተቀናሽ ተደርጎ ቀሪው ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

16. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

17. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ልዩ መመሪያ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሙያው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበትን ተመራቂ አገልግሎቱን ማጠናቀቁን ሳያረጋግጥ እንዲሁም ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የገባ ክፍያውን ሳያጠናቅቅ ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀበል የለበትም፡፡
2. ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

18. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/1995 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

19. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 650/2001 ዓ.ም

## የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ

በኢትዮጵያ ህዝቦች የዕድገት ፍላጎትና ዓለም አቀፋዊው ትስስር መሰረት ተቋማት አስተማማኝ የማስፈፀም ዓቅም ግንባታ ዓቅሞች እንዲሆኑ የሚያበቃ ተቋማዊ ለውጥን እንዲያረጋግጡ ለማስቻል ሕጋዊ ስርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ተቋማት አንገብጋቢ በሆኑ የትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት ጥያቄዎች ላይ በማተኮር የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሰላም፣ የዲሞክራሲ እና የልማት ፍላጎትን ለማሳካት አስተዋፅኦዋቸውን በብቃት እንዲያበረክቱ የሚያስችል ሕጋዊ ማዕቀፍን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት እየተስፋፋ ባለበት ሁኔታ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተቋም ነፃነትና ለመንግስትና ለህዝብ ጥቅም ባጠቃላይ ባለው ተጠያቂነት መካካል ተገቢው ሚዛን እንዲጠበቅ በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የተቋማት የአስተዳደር ስርአት በሕገ-መንግስቱ መሠረት፣ በአመክኖአዊነትና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መርህ ላይ በተመሰረተ መመራመር የሚመራ የአካዳሚክ ማሕበረሰብን ሕይወት የሚያራምድ እንዲሆን ሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ባጠቃላይ በደረሰበት የእድገት ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን ሕጋዊ አቅጣጫና አመራር በመሻቱ እና በተለይ በግል ተቋማት የሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት በትምህርት አግባብነትና ጥራት የሚጠበቅበትን አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችል አቅጣጫን የሚያስይዝ ስርዓት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "አካዳሚክ ማሕብረሰብ" ማለት በተቋም ውስጥ በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት በመማር ፣ በማስተማር እና በምርምር ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችን ያቀፈ ነው፤
   2. "አካዳሚክ መኮንን" ማለት የምርምርና ህትመት መኮንን፣ ሬጂስትራር እና የመሳሰሉትን መኮንኖች ማለት ነው፤
   3. "የአካዳሚክ ሰራተኛ" ማለት በማስተማር እና/ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ የተቋም ሰራተኛ ሲሆን ሴኔት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛ ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ የተቋሙ ባለሙያንም ይጨምራል፤
   4. "የትምህርት ክፍል" ማለት የአንድ ተቋም አካል የሆነ ኮሌጅ፣ ፋካልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢንስቲትዩት፣ ማዕከል ወይም ዲፓርትመንት ነው፤
   5. "የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር፣ የቢዝነስ አመራር፣ የፋይናንስና የሂሳብ ሥራ፣ የምግብ አገልግሎት ማቅረብ፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናውን የተቋም ሰራተኛ ነው፤
   6. "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው፤
   7. "ማዕከል" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የትምህርት ስትራቱጂ ማዕከል ነው፤
   8. "ከፍተኛ ትምህርት" ማለት በስነጥበብ፣ ማሕበራዊ ሳይንስና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ ፕሮግራሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ሥር በተመለከቱት የትምህርት አግባቦች የሚሰጥ ትምህርት ነው፤
   9. "ተቋም" ማለት የመንግሥት ወይም የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

10. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ሲሆን የፌዴራል መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን በሚመለከት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤[2]
11. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
12. "የግል ተቋም" ማለት በአንድ ግለሰብ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥር ባላቸው ሰዎች ባለቤትነት ወይም ዓላማቸው ለትርፍ ባልሆነ ማሕበራት ወይም በሕብረት ስራ ማህበራት ወይም በንግድ ማሕበርነት የተመሠረተ ወይም በውጭ አገር የተመሠረተና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤
13. "የመንግስት ተቋም" ማለት እንደ አግባብነቱ በጀቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤
14. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
15. "የቴክኒክ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ያልሆነና የመማር ማስተማርንና የምርምር ሥራን ለማገዝ የተቀጠረ ሰራተኛ ሲሆን በማስተማርያ ሆስፒታሎች ውስጥ የተቀጠረ የአካዳሚክ ሰራተኛ ያልሆነን ባለሙያንም ይጨምራል፤
16. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተቋም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሃይማኖት ተቋም ሥር ባለና ዓላማውና የትምህርት ሥርዓቱ ኃይማኖት ነክ በሆነ ተቋም ላይ እንዲሁም የዲፕሎማ እና የሰርተፊኬት ስልጠና ብቻ በሚሰጥ ተቋም ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

---
[2] ይህ ንዑስ አንቀፅ በ20/60 (2006) አ.861 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

4. <u>የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች</u>

የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አገሪቱ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችሏት በእውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የታነፁ ምሩቃንን በአገሪቱ ፍላጎት መሠረት በተገቢ የሙያ መስኮችና የትምህርት ዓይነቶች ማፍራት፤
2. በአገሪቱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ትኩረቱ በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የሆነ ምርምርን ማራመድና ማጎልበት፤
3. ትምህርትና ምርምር በአመክኖአዊነትና ተቀባይነት ባለው የሃሳብ ልውውጥ መርህ ላይ የተመሰረተ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ ነፃነትን የሚያጎለብት መሆኑንና ከማንኛውም አድሎ የፀዳ መሆኑን ማረጋገጥ፤
4. በአገሪቱ የዕድገት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የማሕበረሰብና የማማከር አገልግሎትን ማበርከት፤
5. ተቋማዊ ነፃነትን ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥ፤
6. በተቋማት አስተዳደር የቁልፍ ባለ ድርሻዎች ተሳትፎን ማረጋገጥ፤
7. በተቋማት እንቅስቃሴ ፍትህን፣ ፍትሃዊነትንና የሕግ የበላይነትን ማራመድና መጠበቅ፤
8. ዴሞክራሲያዊ ባህልን ማሳደግና የማሕበረሰቡ የባህል ብዙህነትን መጠበቅ፤
9. የመንግስት ተቋማት ስርጭት ሚዛናዊ መሆኑን ማረጋገጥና የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎን የአገሪቱ ፍላጎትንና ፍትሃዊነትን መሠረት በማድረግ ማስፋፋት፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለተቋማት፣ የተቋማት ሠራተኞች እና ተማሪዎች</u>

### <u>ንዑዕ ክፍል አንድ</u>

### <u>ስለተቋማት</u>

5. <u>መቋቋም</u>

1. በፌዴራል መንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይቋቋማል፡፡
2. በክልል መንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም በክልሉ በሚወጣ ሕግ መሠረት ይቋቋማል፡፡ ሆኖም በክልል መንግስት የሚወጣው ሕግ የዚህን አዋጅ

ድንጋጌዎችና ሌሎች የፌዴራል አነስተኛ የጥራት መመዘኛዎችን ሳይነካ መሆን ይኖርበታል፡፡

3. አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የግል ተቋም እንደ አግባብነቱ በማሕበራት፣ በንግድ ማሕበራት፣ በሕብረት ሥራ ማሕበራት ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ይቋቋማል፡፡
4. ማንኛውም ተቋም የሚቋቋመው፣ የሚለወጠው ወይም ማሻሻያ የሚደረግበት የሚከተሉትን ባካተተ የፕሮጀክት እቅድ ላይ በመመሥረት ይሆናል፡-
   ሀ/ ማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸው የተቋም ዓላማዎችን ያስቀመጠ፤
   ለ/ የተቋሙ ደረጃና ዋና ዋና አካዳሚክ ክፍሎች ዝርዝር እና የትምህርት ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን ያካተተ መግለጫ፤
   ሐ/ የተቋሙን አካዳሚክ ሰራተኞች፣ የትምህርት መገልገያዎችና የገንዘብ ምንጭን የሚገልፅ መረጃ፤
   መ/ ትምህርትና ምርምርን በብቃት ለማካሄድ የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዓት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤
   ሠ/ የአገሪቱ አነስተኛ የጥራት መመዘኛዎችን የሚያከብር ስለመሆኑ የፅሁፍ ማረጋገጫ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ሥር የተመለከቱትን በሚመለከት ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡
6. የግል ተቋምን ለማቋቋም የሚቀርበው የፕሮጀክት እቅድ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) ስር ከተመለከቱት መረጃዎች በተጨማሪ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጉዳዮች ካካተተ የመመስረቻ ፅሁፍ ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡-
   ሀ/ የተቋሙን ተግባራት ወሰን፤
   ለ/ ተቋሙ የሚገለገልባቸውን ንብረቶችና የወጪ መሸፈኛ ምንጭ፤
   ሐ/ የተቋሙን የአመራር አካላትና ወኪሎች፡፡
7. ስለተቋም መቋቋም፣ መለወጥ ወይም መሻሻል የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ በውጭ ሀገር በተቋቋመ ተቋም ወይም የተቋሙ ቅርንጫፍ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

6. <u>ሕጋዊ ሰውነት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ ይችላል፡፡

7. <u>የተቋማት መሪ እሴቶች</u>

ተቋማት ለተልእኳቸው መሳካት የሚያራምዱዋቸውና የሚጠብቋቸው መሪ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡

1. እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለፅ ነፃነት፤
2. በተልዕኮ ስኬት ላይ የተመሰረተ ታዋቂነት፤
3. አካዳሚያዊ ተወዳዳሪነትና በትብብር ላይ የተመሰረተ ዝምድና፤
4. የተቋም ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር፤
5. አሳታፊ አስተዳደርና የሕግ የበላይነት፤
6. ፍትህና ፍትሃዊነት፤
7. ሙስናን የመታገል ባህል፤
8. ጥራትንና ቀልጣፋነትን ያቀናጀ አገልግሎት መስጠት፤
9. ቆጣቢ የሃብት አጠቃቀምና ውጤታማ የንብረት ክብካቤ፤
10. ለምስጉን ሰው እውቅና መስጠት፤
11. ዴሞክራሲና የባህል ብዙህነት፡፡

8. <u>የተቋም ሃላፊነት</u>

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ተቋም የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና የተቋማት መሪ እሴቶችን የማክበር፣ የትምህርትና ምርምር ተቋም መሆኑን የማረጋገጥ፤
2. የትምህርት ፕሮግራሞችን የመቅረፅና የከፍተኛ ትምህርትን የመስጠት፣ በአገሪቱ ፍላጎት ላይ በመመሥረት በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የታነፁ ምሩቃንን የማፍራት እና በፕሮግራሞቹ መሠረት የተለያዩ የትምህርት ማሰረጃዎችን የመስጠት፤
3. በሃገራዊ የትኩረት አቅጣጫ መሰረት አግባብነት ያላቸው የጥናት፣ ምርምር እና የማሕበረሰብ አገልግሎትን ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሃገራዊና ከባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የማካሄድና ግኝቶቹንም ተገቢ በሆነ አግባብ የማሰራጨት፤ እንደ አስፈላጊነቱ

ከአገር ውስጥና ከውጭ ተቋማት እና ከሌሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመተባበር አካዳሚያዊና የምርምር ፕሮጀክቶችን የማካሄድ፤

4. በዚህ አዋጅና ተፈፃሚነት ባላቸው የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች መሰረት ሰራተኞቹን የመቅጠርና የማስተዳደር፤ የተቋሙን ገንዘብና ንብረትም የማስተዳደር፤
5. በዚህ አዋጅ መሰረት የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈፀም፤
6. የተቋሙን ዕቅድ፣ በጀትና አደረጃጀት የማዘጋጀትና የመተግበር፤ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሰረት ያፈፃፀም ሪፖርቶችን የማቅረብ፤
7. በተልኮው ላይ በመመስረት ከኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነቶችን የመመስረት፤
8. ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ወይም ለህብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦች እውቅና ወይም ሽልማት ወይም የክብር ዲግሪዎችን የመስጠት፤
9. ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እገዛ ማድረግና እንደአስፈላጊነቱ ለመሰናዶና ለቴክኒክ ሙያ ትምህርት ቤቶች እገዛ ማድረግና ከነሱ ጋር መተባበር፤
10. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት አመታዊና የቀደምት አመታት የትምህርት ግብአትና ውጤት እንዲሁም የፋይናንስ ገቢና ወጪ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሳተም፤
11. በዚህ አዋጅና በማቋቋሚያው ሕግ ወይም በመመስረቻ ሰነድ የተሰጠውን ሌሎች ሃላፊነቶች የመወጣት፡፡

## 9. <u>ስለተቋም ደረጃ</u>

ማንኛውም ተቋም ቀጥሎ ከተመለከቱት በአንዱ መቋቋም ይችላል፡-

1. ዩንቨርስቲ፤
2. ዩንቨርስቲ ኮሌጅ፤
3. ኮሌጅ፤
4. ኢንስቲትዩት፡፡

## 10. <u>ስለትምህርት ደረጃ</u>

በዚህ አዋጅ ስለተቋማት ደረጃ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በማንኛውም ተቋም የሚሰጥ ሥርዓተ ትምህርት፡-

1. በባችለር (ቢ.ኤ/ቢ.ኤስ. ሲ) ዲግሪ፤

2. የሕክምና ዶክተር (ኤም.ዲ.) ወይም የእንስሳት ሕክምና ዶክተር (ዲ.ቪ..ኤም) ዲግሪ፤

3. የማስትሬት ዲግሪ (ኤም.ኤ እና ኤም.ኤስ.ሲ) ወይም የሕክምና ወይም የሌላ ሙያ ስፔሻሊስት፤

4. የዶክትሬት (ፒ.ኤች. ዲ) ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ፣ ወይም

5. በሴኔት የተወሰነ ማንኛውም ሌላ ዲግሪ፣ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

11.<u>የዩንቨርስቲ ደረጃ ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም ተቋም "ዩኒቨርስቲ" የሚለው ስያሜና ደረጃ በሚኒስቴሩ የሚሰጠው የሚከተሉትን መመዘኛዎች ሲያሟላ ይሆናል፡-

ሀ/ በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ 2,000 እኛ ከዚያ በላይ ተማሪዎችን ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ ፕሮግራሞች የማስተማር አቅም ሲኖረው ወይም በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ 2,000 እና ከዚያ በላይ ተማሪዎችን ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ አራት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ የማስተማር ዓቅም ሲኖረው፤

ለ/ በዩኒቨርስቲ ኮሌጅነት ወይም በኮሌጅነት ወይም በኢኒስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለአራት ተከታታይ አመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ ሲሆን፤

ሐ/ አግባብነት ባላቸው የተለያዩ መስኮች ምርምር የሚያደርግ፣ የምርምር ውጤቶቹን ያሳተመ እና የምርምር ግኝቶችን ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍባቸውን መንገዶች ያመቻቸ ሲሆን፤

መ/ በሚኒስቴሩ የወጣ ሃገራዊ አነስተኛ የደረጃ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ደረጃውን የጠበቀ ስርዓተ ትምህርት፣ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ በዚህ አዋጅ የተደነገገውን ተቋማዊ የአስተዳደር አደረጃጀት፣ የማስተማሪያ ክፍሎች፣ ቤተመፃሕፍትና ቤተሙከራዎች ያለው እና ሌሎች ለየትምህርት መስኩ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ያሟላ ሲሆን፤ እና

ሠ/ ሌሎች በሚኒስቴሩ የተቀመጡ አነስተኛ የደረጃ መመዘኛዎችን ሲያሟላ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ተቋም የዩኒቨርስቲ ስያሜና ደረጃ ይዞ

እንዲቋቋም ታስቦ ከሆነና ያለው የሃብት አቅርቦትና ተቋማዊ አቅድና ራዕይ ሲታይ የታሰበው ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተቀመጡትን መመዘኛዎች ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያሟላ ይችላል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን ተቋሙ ዩኒቨርስቲ ሆኖ መቋቋም ይችላል፡፡

3. በመደበኛና በርቀት ትምህርት ላይ ወይም በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ የተመሰረተ ተቋም የዩኒቨርስቲ ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ የራሱን ጥናት በማድረግ ወይም መልካም ዓለም አቀፍ ተሞክሮን በመጠቀም በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል።

## 12.ዩንቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃን ስለመስጠት

1. ማንኛውም ተቋም ከሚኒስቴሩ "ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) ከተመለከቱት በተጨማሪ፡-
   ሀ/ በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ ቁጥራቸው ቢያንስ 2,000 የሆኑ ተማሪዎችን ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ የማስተማር አቅም ያለው፣ እና
   ለ/ በኮሌጅነት ወይም በእንስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለሶስት ተከታታይ አመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ፣

   መሆን አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ተቋም ያለው የሃብት አቅርቦት፣ ተቋማዊ እቅድና ራዕይ ሲታይ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተቀመጡትን መመዘኛዎች ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያሟላ ይችላል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን ተቋሙ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሆኖ መቋቋም ይችላል፡፡
3. በመደበኛና በርቀት ትምህርት ላይ ወይም በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ የተመሰረተ ተቋም የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ የራሱን ጥናት በማድረግ ወይም መልካም ዓለም አቀፍ ተሞክሮን በመጠቀም በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል።

## 13.የኮሌጅ ደረጃን ስለመስጠት

አንድ ተቋም በሚኒስቴሩ "ኮሌጅ" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) እና (ሠ) ከተመለከቱት መመዘኛዎች በተጨማሪ ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆነ አንድ የትምህርት ክፍል በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል።

14.<u>የኢንስቲትዩት ደረጃን ስለመስጠት</u>

አንድ ተቋም ከሚኒስቴሩ "ኢንስቲትዩት" የሚለውን ስያሚና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) እና (ሠ) ከተቀመጡት በተጨማሪ፡-

1. ቢያንስ በአንድ የትምህርት መስክ ወይም አይነት ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችል፣ እና
2. በሚሰጠው የትምህርት አይነት በዲግሪ ደረጃ ትምህርት የመስጠት አቅም ያለው፣ መሆን ይኖርበታል።

15.<u>አዲስ መንግሥታዊ ተቋም ስለማቋቋም</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 እና 12 ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አዲስ መንግስታዊ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በዩኒቨርስቲ ወይም በዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃ ሊቋቋም ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ አዲሱ መንግስታዊ ተቋም ከደረጃው የሚጠበቁ መመዘኛዎችን በሙሉ ማሟላቱን ያረጋግጣል።

16. <u>ስለአካዳሚያዊ ነፃነት</u>

1. ማንኛውም ተቋም በተቋሙ ተልዕኮና በአለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት አካዳሚያዊ ነፃነት ይኖረዋል።
2. ማንኛውም ተቋም ማሕበረሰቡ የአካዳሚያዊ ነፃነቱን ሲያራምድ የማሕበራዊ ሃላፊነት ባሕልን እንዲያበለፅግ ማድረግ ይኖርበታል።
3. ማንኛውም ተቋም በዚህ አዋጅና በዓለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት የአካዳሚያዊ ነፃነት አተገባበር በሥርዓት እንዲመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

17. <u>የመንግስት ተቋማት ነፃነት</u>

1. ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ተልእኮውን ለማስፈፀም ይችል ዘንድ በዚህ አዋጅ ተቋማዊ ነፃነቱ ተረጋግጧል።

2. በዚህ አዋጅ የተደነገጉት የቦርዱና የሚኒስቴሩ ሃላፊነት እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት ተቋማት ነፃነት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ አግባብነት ያላቸውን የሥርአተ ትምህርትና የምርምር ፕሮግራሞች ማዘጋጀትና ማካሄድ፤ አዳዲስ ፕሮግራሞችን መክፈት ወይም ነባሮችን መዝጋት፤ አደረጃጀቱን መወሰንና የውስጥ ደንብንና መመሪያዎችን ማውጣትና መተግበር፤

ለ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የአካዳሚክና ሌሎች ሰራተኞቹን መቅ ጠርና ስለሥራ አፈፃፀም ብቃት ባስቀመጣቸው መመዘኛዎችና በሚሻው ውጤት መሰረት ኃላፊነታቸውን መወሰን፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ተፈፃሚነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መርሆዎች መሰረት የሰው ሃይሉን ማስተዳደር፤

መ/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ፕሬዚዳንቱን፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና የቦርድ አባላትን በእጩነት ማቅረብ፤ የትምህርት ክፍሎች መሪዎችን መምረጥና መሾም፤

ሠ/ በዚህ አዋጅና ተፈፃሚነት ባላቸው ሊሎች ሕጎችና ደንቦች መሠረት የገንዘብ ሃብቱንና ንብረቱን ማስተዳደር።

3. ማንኛውም የመንግስት ተቋም ነፃነቱን ሲያራምድ ሕጋዊነት፣ ውጤታማነት፣ ግልፅነት፣ ፍትህና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ መሆን ይኖርበታል።

## 18. <u>ስለመንግስታዊ ተቋም የአካዳሚክ ክፍሎች ነፃነት</u>

1. ማንኛውም ተቋም አሳማኝ በሆነ የትምህርት ዓይነቶች ወይም የትምህርት ዓይነት ቅርንጫፎች መጣመር ላይ የተመሰረቱ አስፈላጊ አደረጃጀት ያላቸውና ተገቢው ስያሜ የተሰጣቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ይኖሩታል።
2. የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም አካዳሚክ ክፍሎች ተቋሙ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚያወጣቸው ድንጋጌዎች፣ መመዘኛዎችና ያፈፃፀም ስርአት መሰረት በአስተዳደር፣ በፋይናንስና በአካዳሚክ ጉዳዮች ነፃነት ይኖራቸዋል።
3. የተቋማት ፕሬዚዳንቶች የአካዳሚክ ክፍሎች ባላቸው ነፃነት ሃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ አስፈላጊው ተቋማዊ ድጋፍ፣ አመቺ ሁኔታዎችና በቂ ሀብት እንዲኖራቸው ማስቻል ይኖርባቸዋል።

## 19. <u>ስለትምህርት ፕግራሞች</u>

1. በተለየ ሁኔታ ካልተቋቋመ በስተቀር የማንኛውም ተቋም ቁልፍ ተግባር በመደበኛ ፕሮግራሞች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ ምርምር ማካሄድና ለማሕበረሰብ አገልግሎት መስጠት ይሆናል፡፡
2. ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ማንኛውም ተቋም በተጨማሪ በሚከተሉት መንገዶች ትምህርትና ስልጠና መስጠት ይችላል፡-

   ሀ/ ተከታታይ ትምህርት፤

   ለ/ የርቀት ወይም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዝ ትምህርት፡፡
3. ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ማንኛውም ተቋም በተጨማሪ የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት ወይም በአንድ የተወሰነ የሙያ መስክ እውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት ተገቢውን ሰርተፊኬት መስጠት ይችላል፡፡

20. <u>**የማስተማሪያ ቋንቋ**</u>

1. በሌሎች ቋንቋዎች ትምህርት መስጠት ወይም ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የማንኛውም ተቋም የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ለአጫጭር ስልጠና እና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መምህራን ማዘጋጃ የሚፈፀም ሙያዊ ሥልጠና በተፈላጊው ቋንቋ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
3. መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት በምልክት ቋንቋ መሰጠት ወይም መደገፍ ይኖርበታል።

21. <u>**ሥርዓተ ትምህርት**</u>

1. በማንኛውም ተቋም የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ ትግበራና የምዘና ዓላማ ተማሪው ተገቢው ሳይንሳዊ ዕውቀት፣ በነፃነት የማሰላሰል ክህሎት፣ ሃሳቡን የመግለፅ ክህሎቶችና ሙያዊ እሴቶችን እንዲጨብጥ በማስቻል ብቁ ባለሙያን ማዘጋጀት ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ተቋም የትምህርት ክፍሎቹ የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃን በተገቢ የምሩቃን ብቃት መመዘኛዎች እንዲመራ ያደርጋል፡፡
3. ተቋማት ወቅታዊ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃን የሚያስጠብቅ ተቋማዊ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ስርዓት ይኖራቸዋል፤ የትምህርት ክፍሎቻቸው ስርዓቱን ስለመተግበራቸውም ያረጋግጣሉ።

4. ከአንድ በላይ ብዛት ላላቸው ተቋማት የጋራ የሆነ ስርዓተ ትምህርት በነዚሁ ተቋማት ተሳትፎ በጋራ ሊቀረፅ ይችላል፤ ስርዓተ ትምህርቱም በሁሉም ፈፃሚ ተቋማት የሚተገበር አነስተኛው መመዘኛ ሆኖ ያገለግላል፡፡
5. ሀገራዊ ጥቅሞችና አግባብነት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም በተቋማት የጋራ ተሳትፎ ሥርዓተ ትምህርቶች ሊዘጋጅላቸው የሚገቡ ፕሮግራሞችንም ጨምሮ ለሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ሥርዓተ ትምህርቶችን የመቅረፅና የመተግበር ነፃነት ይኖረዋል፡፡
6. የስርዓተ ትምህርት አተገባበር በምርምርና ጥናት ላይ የተመሠረተና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፤ የመማር ማስተማር ሂደቱም በዝግጅቱ፣ በአሰጣጡ እና በምዘና ስርዓቱ ሁሊም ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፡፡
7. የእያንዳንዱ ተቋም ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ለመንግስታዊ ተቋማት የጋራ የሆኑ ስርዓተ ትምህርቶች ቀረፃን ሊያስተባብር ይችላል፤ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎችን ለማስፈፀምም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
8. ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሃገራዊ የሥርዓተ ትምህርት ቡድኖች ወይም ምክር ቤቶች ወይም የሥርዓተ ትምህርት ግምገማ፣ ቀረፃና ትግበራን የሚያስተባ ብርና የሚከታተል አካል ሊያቋቁም ይችላል፡፡

22. <u>ስለተቋም ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት</u>

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እና አግባብነት ያላቸው ደንቦችና መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም አስተማማኝ የሆነና በየጊዜው የሚሻሻል የጥራት ማጐልበቻ ሥርአት ይኖረዋል።
2. የማንኛውም ተቋም ውስጣዊ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት የአካዳሚክ ሰራተኞች የሙያ ልማትን፣ የትምህርት ይዘትን፣ የመማር ማስተማሩ ሂደትን፣ የተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥን ያካተተ ግልፅና የተሟላ የጥራት መለኪያን የያዘ መሆን ይኖርበታል፤ በተጨማሪም ተማሪዎች የትምህርት ይዘትን፣ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን፣ የምዘና፣ የፈተናና የውጤት አሰጣጥ ሥርዓቱን የሚገመግሙበት ስርዓት ይኖረዋል።
3. የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓቱ በተቋሙ ለመማር መረጃ ለሚጠይቁ ታሳቢ ተማሪ ዎች ከሚሰጥ መረጃ አንስቶ ተማሪዎች ትምህርቱንና ቆይታቸውን ሲያጠናቅቁ

እስከሚሰጡት ግምገማ ድረስ ባሉት በሁሉም የትምህርት አግባብነትና ጥራትን በማመለከት ሂደት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. ማንኛውም ተቋም የጥራት ደረጃ መመዘኛዎችን ማዘጋጀት፣ በየጊዜው አካዳሚያዊ ኦዲት ማድረግና በኦዲት የተመለከቱ ድክመቶችን መከታተልና ማስተካከል እንዲሁም ግምገማውን፣ የተከናወኑ ተግባራትን እና የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ ተገቢ ሰነዶችን መያዝና ለኤንጀንሲውም መላክ ይኖርበታል።
5. ተቋማት ጥራት ማጎልበትን አስመልክቶ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በኤጀንሲው የሚሰጡ ተገቢነት ያላቸው አስተያየቶችን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው።
6. የተቋም የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓትን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መካተት ይኖርባቸዋል።
7. ሚኒስቴሩ፣ ማዕከሉና ኤጀንሲው የተመራቂዎች ቁልፍ ባህሪያትን ወይም የምሩቃን የብቃት መመዘኛዎችን እንደየነገሩ ሁኔታ በሚወስን ወይም በሚያመላክት ሃገራዊ የምሩቃን ብቃት ማዕቀፍ አማካኝነት ጭምር የተቋማት ጥራትን የማጎልበት ጥረትን እና የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃን አቅጣጫ ያስይዛሉ፡፡

## 23.<u>ስለ አካዳሚክ ምክርና ድጋፍ</u>

1. ማንኛውም ተቋም አግባብነት ባላቸው ክፍሎችና በአካዳሚክ ሰራተኞቹ አማካኝነት በተቋሙ ስለሚሰጡ የትምህርት አይነቶች እና ስለትምህርቱ ይዘት፣ አደረጃጀትና የተማሪዎች ምዘና ስርዓት በተገቢ ተቋማዊ ስርዓት ለተማሪዎቹና ለአመልካቾች መግለፅ ይኖርበታል።
2. ማንኛውም ተቋም በየትምህርት አይነቱ በትምህርት ላይ ቆይታቸው ጊዜ በሙሉ ለተማሪዎች የአካዳሚክ የምክርና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል።
3. የአካዳሚክ ምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ልዩ አካዳሚያዊ ድጋፍ የሚያሻቸው ተማሪዎች መኖራቸውን ከጠቆመ የተቋማት የትምህርት ክፍሎች ድክመቶቹን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተቋማት እንዳስፈላጊነቱ የትምህርት መስኮች ምርጫን አስመልክቶ ለተማሪዎች የቅድመ ቅበላ የማማከር አገልግሎት ሥርዓትን ለመመሥረት የሚያስችላቸው እርምጃን ይወስዳሉ።

## 24. <u>ምርምርና የምርምር አቅጣጫዎች</u>

1. በማንኛውም ተቋም የሚካሄድ ምርምር የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማሳደግ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ባተኮሩ የአገሪቱ የልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ተቋም ከቁልፍ የውስጥና የውጭ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በሀገር ፍላጎት፣ በተቋሙ ተነፃፃሪ ሙያዊ ዓቅም እና ባለው የገንዘብ ሀብት የተወዳዳሪነት ብልጫው ላይ ተመሥርቶ ምርምር የሚደረግባቸው ጉዳዮች ቅደም ተከተልን መለየት ይኖርበታል።
3. ማንኛውም ተቋም የሚያካሂደው ምርምር በተለይ፡-
   ሀ/ በአገሪቱ ቀዳሚ ፍላጎት ላይ በመመስረት በቴክኖሎጂ ሽግግር ችግር ፈቺ የሆነና የማስፈፀም ዓቅምን የሚገነባ፣
   ለ/ አግባብነት ያላቸው ቀጣይ ጥናቶችና ምርምሮችን ለማካሄድ እንዲችሉ ተማሪዎችን በመሠረታዊ የምርምር ዕውቀትና ክህሎት የሚያስታጥቅ፤
   
   መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም ተቋም በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የራሱ ምርምርን ለማካሄድና የምርምር ፕሮጀክቶችን ከሌሎች ሀገራዊና ዓለምአቀፋዊ ተቋማት፣ የምርምር አካላት እና እንዱስትሪዎች በጋራ ለማካሄድ የሚያስችለው ተቋማዊ ስርዓት ይኖረዋል።
5. ምርምር ማካሄድን የሚመለከቱ የአደረጃጀትና የማኔጅመንት ዝርዝር ጉዳዮች በተቋሙ የሚወሰኑ ይሆናሉ፡፡
6. ማንኛውም ተቋም አከራካሪ ጉዳዮችን አብራርቶ በመደንገግ እና ዓቅምና ተፈፃሚነትን ግምት ውስጥ በማስገባት በምርምር አጀንዳውና ዕቅዱ መሰረት አካዳሚክ ሠራተኞቹን በዋናነት በመምህርነት ወይም በተመራማሪነት ወይም ሁለቱንም በማቀናጀት እንዲያካሂዱ አድርጎ የሚያሰማራበት ግልጽነት ያለው ሥርዓት ይኖረዋል።
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተቋም እያንዳንዱ የአካዳሚክ ሠራተኛውን በሥነ-ጽሑፍ ላይ በተመሰረተ ጥናት ወይም በልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ባተኮረ ምርምር ላይ መሠማራቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
8. ማንኛውም ተቋም ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን ጀምሮ ባሉት 300 ቀናት ውስጥ ወይም አዲስ የሚቋቋም ተቋም ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ

በአንድ ዓመት ውስጥ የተቋሙንና የአካዳሚክ ሰራተኞቹን አፈፃፀምን የሚቃኙ የምርምርና የምክር አገልግሎት የብቃት መመዘኛዎች፣ ሙያዊ ስነምግባር እና ሃላፊነትን የደነገጉ መመሪያዎችና ያፈፃፀም ስርዓቶች ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 25. <u>የምርምርና ፈጠራ ፈንድ</u>

1. ማንኛውም ተቋም የምርምርና ፈጠራ ፈንድ ይኖረዋል።
2. ማንኛውም ተቋም በበጀት ምደባና ሌሎች ድጋፎች በተለይ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ማሻሻል ላይ ላተኮረ ምርምር ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተቋም ቅድሚያ የሚሰጠውን የምርምር ስራ መንግስታዊ ካልሆነ ምንጭ በሚያገኘው ገቢ ተጠቅሞ ማካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም ተቋሙ ከመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ካልሆነ ምንጭ በተለይ ለምርምር የተመደበለት ገንዘብ ባግባቡ እና በሙሉ ለምርምር ተግባር መዋሉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
4. ማንኛውም ተቋም ግልፅነት ያለው የምርምር ፈንድ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል።
5. ማንኛውም ተቋም ወይም የተቋሙ አካዳሚክ ሠራተኛ ከሌሎች አካላትና ከውጭ አገር ምንጭ በሚገኝ ገንዘብ የጋራ የምርምር ሥራ ማካሄድ የሚችለው የምርምሩ ሥራ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (8) ሥር በተገለጸው መሰረት በተቋሙ የሥነ-ምግባር ስርዓት ክልል የሚከናወን ከሆነ ነው፡፡

## 26. <u>የምክር አገልግሎት እና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት</u>

1. ተቋማት በብቃታቸው መሰረት የምክር አገልግሎትና ተጓዳኝ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡
2. የመንግስት ተቋማት የአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው የሚካሄዱት የምክር አገልግሎትና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ተቋሙ እንዲያከናውን የተቋቋመባቸው ስራዎች ጥራትና አፈፃፀምን ሳይነኩ መከናወናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
3. የመንግስት ተቋማት በአካዳሚክም ሆነ በሌሎች ሠራተኞቻቸው የሚከናወኑ ተጓዳኝ ተግባራት ተልዕኳቸውን እና የተመሰረቱባቸው ሕጋዊና የስነምግባር መርሆዎችን የማይሸረሽሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
4. ማንኛውም የመንግስት ተቋም ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ተቋሙ አዲስ የተቋቋመ ሲሆን

ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በሠራተኞቹ የሚከናወኑት የምክር አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት የሚመሩበትን መመሪያ ማውጣት ይኖርበታል።

5. ማንኛውም ተቋም ከኢንዱስትሪዎች ጋር ግልፅነት ባለው ድርድርና ስምምነት መሠረት መርህን የጠበቀና የጋራ ጥቅምን የሚያራምድ ግንኙነት የመመስረት ሃላፊነት አለበት፡፡
6. የግለሰቦች አእምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት መብቶችና ውል የተገባበት ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተቋም ለአካዳሚክ አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ ይደረጉ የነበሩትን ዕውቀትና ክህሎት ለሕብረተሰቡ ግልጋሎት እንዲውሉ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡
7. ተቋማት በምክር አገልግሎቶች አማካይነት የሚያገኟቸውን ውጤቶች ለአካዳሚክ አገልግሎቱ ማዳበሪያና ለመማር ማስተማሩ ሂደት ማበልጸጊያ አንድ ምንጭ አድርገው መጠቀም ይኖርባቸዋል።
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተውን መመሪያ ተላልፎ በመገኘቱ አግባብነት ባለው ሃላፊ የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሚ የመተላለፍ ሁኔታ የፈፀመ ሰው በተቋሙ የዲስፕሊን ደንብ መሠረት እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡
9. ማንኛውም የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ጥሰት መኖሩን የተገነዘበ የቅርብ ሃላፊ ወይም የተቋሙ ባለሥልጣን በሕጋዊ ሥርዓት መሠረት ጥሰቱን የማስቆም ሃላፊነት ይኖርበታል፤ ይህን ሃላፊነቱን ካልተወጣ ወይም ችላ ካለ የዲሲፕሲን እርምጃ ይወሰድበታል።

## 27. <u>መረጃ ስለማግኘት</u>

1. ተቋማት ስታቲስቲካዊ መረጃ የሚሰበሰቡበትንና በመካከላቸው ፣ በክፍሎቻቸው መካከልና ከሚኒስቴሩ ጋር መረጃዎችን የሚለዋወጡበት ቀልጣፋ ሥርአት መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተቋማት ትክክለኛ፣ ዝርዝርና የተሟላ አመታዊ የትምህርትና የገንዘብ ገቢና ወጪ ስታቲስቲካዊ መረጃ ማሳተም ይኖርባቸዋል። መረጃን የማሳተሙ ግዴታ ከአቅም በላይ የሆነ ክስተት ካላጋጠመ በስተቀር አንድ የትምህርት ዘመን እንደተጠናቀቀ በአንድ መቶ ሃያ ቀናት ጊዜ ውስጥ መፈፀም ይኖርበታል።

3. በሕግ የተደነገጉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምርምር ለሚያካሂዱ የአካዳሚክ ሰራተኞችና ተማሪዎች መረጃ የመስጠትና የመተባበር ሃላፊነት አለባቸው።

28. <u>የአካዳሚክ ዘመን እና የበጀት ዓመት</u>

1. የማንኛውም ተቋም የመደበኛ ፕሮግራም አንድ የትምህርት ዘመን እኩል በሆኑ ሴሚስተሮች የተከፈሉ 300 ቀናት ይኖሩታል።
2. የማንኛውም ተቋም ሴኔት የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የትምህርት ዘመንን ይወስናል፡፡
3. የመንግሥት ተቋማት የበጀት ዓመት የመንግሥት በጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የተቋማት ሠራተኞች</u>

29. <u>የሠራተኞች ዓይነት</u>

ማንኛውም ተቋም፡-

1. አካዳሚክ ሠራተኞች፣
2. የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣
3. የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣
4. እንደ አግባቡ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ ባለሙያዎች፣

ይኖሩታል።

30. <u>አካዳሚክ ሠራተኞች</u>

1. ማንኛውም ተቋም የሚከተሉት አካዳሚክ ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፦
   ሀ/ ለማስተማርና/ወይም ለምርምር የተቀጠሩ ፕሮፌሰሮች፣ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች፣ ረዳት ፕሮፌሰሮች፣ ሌክቸረሮች ረዳት ሌክቸረሮች እና በሁኔታዎች አስገዳጅነትና ለመሸጋገሪያ ጊዜ የሚቀጠሩ ረዳት ምሩቆች፤
   ለ/ በዓለም ዓቀፍ መልካም ተሞክሮዎችና በተቋሙ ሴኔት ውሳኔና ደንብ መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛነት እውቅና የተሰጣቸው ሌሎች ሠራተኞች፡፡
2. ማንኛውም ተቋም ለአካዳሚክ ሰራተኞች የማዕረግ ዕድገት የሚሰጥበትና አዲስ ቅጥርን የሚፈፅምበት ዓለም አቀፋዊ መልካም ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ የዕድገትና የቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ይኖረዋል።

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም የባችለር ዲግሪ ምሩቃን በመደበኛ አካዳሚክ ሰራተኝነት በመንግስታዊ ተቋማት ሊቀጠሩ የሚችሉትና ማዕረጋቸው የሚወሰነው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
4. ማንኛውም ተቋም በጥራትና በቁጥር በቂ የአካዳሚክ ሠራተኞች እንዳሉት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የአካዳሚክ ሰራተኞች ብዛት በተቋሙ የሚወሰን ሆኖ በተማሪ መምህር ምጣኔና ለምርምር በሚያስፈልግ ተጨማሪ ቁጥር ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡
5. በሁሉም የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ አገራዊ የማስተማርና የምርምር ሥራዎች ጫና መስፈርት ይኖራል፡፡ መስፈርቱ በመንግሥት ተቋማት የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶና በቦርዱ ተደግፎ በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ሚኒስቴሩ መስፈርቱን በግል ተቋማትም ተፈጻሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. ሚኒስቴሩ ማንኛውም ተቋም ማሟላት ያለበትን በትምህርት ደረጃና በማዕረግ አነስተኛው የአካዳሚክ ሰራተኞች ምጣኔን በየጊዜው ያወጣል፡፡
7. በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ዓቅሙ በተሻለ ዕድገት ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ተቋም እንደ አንድ ሀገራዊ ቀዳሚ ተግባሩ ያነሰ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው ልማት ያለ ትምህርት ክፍያ እገዛ ያደርጋል፡፡
8. አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ለአንድ አካዳሚክ ቅጥር ቦታ የሚያመለክት ሰው ሊቀጠር የሚችለው ከቅርብ ጊዜ አሰሪው የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል ብቻ ይሆናል፡፡
9. አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ ተቋም በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት የተባረረ አካዳሚክ ሠራተኛ በሌላ ተቋም መቀጠር የሚችለው የቀድሞ ታሪኩ፣ የተባረረበት ጥፋትና ከተባረረ በኋላ ያለበት ሁኔታ ታይቶና ተገምግሞ በሴኔት ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል፡፡
10. ማንኛውም ተቋም እንደነገሩ ሁኔታ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

31. <u>የአካዳሚክ ሠራተኛ መብት</u>

1. የዚህ አዋጅ ሊሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም የአካዳሚክ ሠራተኛ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ በተቋሙ ተልዕኮ መሠረት የአካዳሚክ ነፃነትን የመጠቀም፤

ለ/ በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ምርምር የማካሄድና ሙያዊ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤ እንዲሁም በተቋሙ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የሳባቲካልና የምርምር ዕረፍቶችን በመውሰድ ለተቋሙና ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ምርምሮችና ጥናቶች የማካሄድ፤

ሐ/ በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያ መሠረት ሙያውን የሚያዳብር ትምህርትና ሥልጠናን የማግኘት፤

መ/ በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያ እንዲሁም እንደአስፈላጊቱ በሚኒስቴሩ በሚወጣ ሀገራዊ መስፈርት መሠረት የሙያ ዕድገትን የማግኘት፤

ሠ/ ግልፅና ፍትሃዊ አስተዳደር የማግኘትና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በሚፈቅደው መሠረት በመንግስት የሚወሰን ወይም በግል ተቋሙ ዓቅም ላይ የተመሠረተ ደሞዝና ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት፤

ረ/ በተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ፣ ዕቅድና የውስጥ ደንብና መመሪያዎች ዝግጅትና የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ላይ እንደአመቺነቱ የመሳተፍና በመማር ማስተማር ሂደት አግባብነትና ጥራት ላይ አስተያየት የማቅረብ፤

ሰ/ ስለ ስራ አፈፃፀሙ የተደረገ ግምገማ ውጤትንና ያለእርሱ ዕውቀት በግል ማህደሩ ውስጥ ስለተቀመጡ መረጃዎች የማወቅ፤ እንዲሁም በማህደሩ ውስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች ለተቋሙ አስተዳደራዊ ጉዳይ ወይም አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር እንዲያዙለት የማድረግ፤

ሸ/ በተቋሙ ግቢ ውስጥ የራሱና የግል ንብረቱ ደህንነት ተጠብቆ ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት፤

ቀ/ ስለተቋሙ ዕቅድ፣ ዕድገት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ ሁኔታና የክንውን ውጤቶች መረጃ የማግኘት፤

በ/ አካዳሚክ ሠራተኛን መምረጥ ተገቢ በሆነበት ሁሉ የመመረጥና የመምረጥ፤

ተ/ በዲስፕሊን ጉዳይ የመስማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳለት የመጠየቅና ፍትህን የማግኘት፡፡

2. ማንኛውም ተቋም አካዳሚክ ሠራተኞቹን በሚመለከቱ የመብት ጉዳዮች ላይ በአሳታፊ ሂደት የውስጥ ደንብና ያፈፃፀም ስርዓትን የመቅረፅና ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡

32. <u>የአካዳሚክ ሠራተኛ ግዴታ</u>

1. የተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ/ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ የማስተማር፣ የአካዳሚክ ምክር አገልግሎትና የሕብረተሰብ አገልግሎት የመስጠት፤

ለ/ በራሱ የሙያ መስክና ብቃት መሰረት ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ችግር ፈቺ ጥናትንና ምርምርን የማካሄድና ዕውቀትና ክህሎትን የማሸጋገር፣ ወይም ቢያንስ የሚያስተምረውን ትምህርት በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የማድረግና በየጊዜው የማሻሻል፤

ሐ/ ሥርዓተ ትምህርትን በመገምገም፣ በመቅረፅና በማጎልበት ሂደት ላይ የመሳተፍና ተገቢውን ሚና የመጫወት እንዲሁም በሥርዓተ ትምህርቱ አተገባበር በተማሪዎች ምዘና፣ ውጤት አሠጣጥ፣ ማማከር፣ የተማሪዎችን ቅሬታዎችና አቤቱታዎችን በማስተናገድና ባጠቃላይ በሙያዊ ሥነ-ምግባር የሚጠበቅበትን ሙያዊ ብቃት የማረጋገጥ፤

መ/ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና ተቋሙ የሚመራባቸውን እሴቶች የማ ክበር፣ የመተግበርና አካዳሚክ ነፃነቱን በሙያዊ ስነምግባር እና አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የመጠቀም፤

ሠ/ ተማሪዎች የተቋሙን ተልዕኮ፣ መሪ እሴቶችና የከፍተኛ ትምህርት ዓላማ ዎችን እንዲያውቁ የመምከር፣ የማገዝና የመርዳት፤

ረ/ ሙሉ የሥራ ጊዜውን ለተቋሙ የማዋል፤

ሰ/ በመማር-ማስተማር ሂደት የራስን ፖለቲካዊ አመለካከት ወይም ሃይማኖት በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ከመጫን የመቆጠብ፤

ሸ/ ከተቋሙ ማሕበረሰብ አባላት በሚኖረው ግንኙት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ መብቶችን ከሚፃረሩ ድርጊቶችና አሰራሮች የመቆጠብ፤

ቀ/ በተቋሙ የማቋቋሚያ ሕግ ወይም መመሥረቻ ሰነድ እና በተቋሙ የሴኔት ደንብ መሠረት የሚሰጡት ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፤

በ/ ከሌላ ተቋም ጋር አስቀድሞ በሚደረግ ስምምነት መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ ስለመቅጠር በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሙሉ ሃይሉን፣ የሥራ ጊዜውንና ትኩረቱን ለተቋሙ የማዋል።

2. አካዳሚክ ሰራተኞች የሆኑ የጤና ባለሙያዎች በተቋሙ የማስተማሪያ ሆስፒታል ውስጥ በሙያቸው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታም ይኖርባቸዋል።

3. ተቋማት በዚህ አንቀጽና አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረተና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ያሳተፈ የአካዳሚክ ሠራተኞች የዲስፕሊን ደንብ አውጥተው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

4. ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ (3) የተመለከተውን ደንብ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ መሆን ከሚጀምርበት ወይም አዲስ ተቋም ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን አንስቶ ባሉት 300 ቀናት ውስጥ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።

## 33. ስለ አካዳሚክ ሠራተኞች ቋሚነትና የጡረታ መውጫ ዕድሜን ስለማራዘም

1. እንደ ልዩ ጥቅምና ለሙያ ልቀት ማበረታቻ እንዲሆን አንድ አካዳሚክ ሠራተኛ ቋሚ ቅጥር ሊደረግ ይችላል። የአካዳሚክ ሠራተኛ ቋሚ ቅጥር የሚሆነው በሰጠው አገልግሎትና ባበረከተው የማስተማር እና/ወይም የምርምር ምሁራዊ አስተዋፅኦ ወይም ባስመዘገበው የተቋም መሪነት ብቃት ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡

2. ቋሚ የሆነ የአካዳሚክ ሠራተኛ የሥራ ዋስትና ይኖረዋል፤ ቋሚ የሆነ የአካዳሚክ ሠራተኛ ከሥራው ሊባረር የሚችለው በመንግስት ተቋሙ የሴኔት ደንብ መሠረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የሚያሟላ ፕሮፌሰር ወይም ተባባሪ ፕሮፌሰር በጡረታ ከተገለለ በኋላም ማዕረጉን እንደያዘ እንዲቀጥል በተቋሙ የሴኔት ደንብ መሠረት ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

4. ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በመንግሥታዊ ተቋም የሚያገለግል አካዳሚክ ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜን ለእያንዳንዱ ጊዜ በሶስት ዓመት የሚታሰብ ሆኖ ለሁለት ጊዜያት እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል፦

   ሀ/ የአካዳሚክ ሠራተኛው የማስትሬት ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ኖሮት መልካም ጤንነት ያለውና ተከታታይና ውጤታማ አገልግሎተ ሲሰጥ የቆየ ከሆነ፣

   ለ/ ተቋሙ በወቅቱና በወደፊት ፍላጎቱ ላይ ተመሥርቶ የጡረታ ዕድሜው መራዘሙ ተገቢ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ፣

ሐ/ የአካዳሚክ ሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜው እንዲራዘምለት ፈቃደኛ ከሆነ፡፡

5. ሚኒስቴሩ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ለማድረግ መመሪያ ያወጣል፡፡

## 34. አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ ስለመቅጠር

1. አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ መቅጠር ተፈጻሚ የሚሆነው የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማረጋገጥ መልካም መፍትሄ ሆኖ ሲገኝ ወይም የአካዳሚክ ሠራተኛ እጥረትን ለመቅረፍ አስፈላጊ ሲሆን ነው፡፡ የጋራ ቅጥር ተግባራዊ ሲደረግ የማስትሬት ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለውን የአካዳሚክ ሠራተኛን የሚመለከት ሆኖ ከኢንዱስትሪ፣ ከንግድ፣ ከምርምር ማዕከሎች ወይም ከሌሎች ድርጅቶች በጋራ ቅጥር በተቋም ለመሰማራት የሚያበቃ ሙያዊ ዓቅም ያለው ባለሙያንም የሚመለከት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ አካዳሚክ ሠራተኛ ወይም የመንግሥት ሰራተኛ ዓቅሙ ካለው በራሱ ፈቃድና በተቋሙ ወይም በመሥሪያ ቤቱ ፈቃድ በጋራ ቅጥር ሊሰማራ ይችላል፡፡ የሰው ሃይል እጥረት ባለባቸው አንዳንድ መስኮች፣ ተቋማትና መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች አካዳሚክ ሠራተኞችን ወይም የመንግሥት ሠራተኞችን በጋራ ለመቅጠር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡
3. የቅጥሩ ሁኔታ፣ ቅጥሩ የሚቆይበት ጊዜ፣ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች፣ እንዲከናወኑ የሚፈለጉ ተግባራትና ጊዜን ማደላደል የመሳሰሉት ለተቀጣሪውና ለአሠሪዎቹ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች የሚመለከተው ሴኔት በሚያወጣው ደንብና ሥርዓት መሠረት በስምምነት ይወሰናሉ።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የመንግስት ተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ ወይም ሌላ የመንግስት ሰራተኛ በግል ተቋም የጋራ ተቀጣሪ ሆኖ የመቀጠር መብት እንደሰጡ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም።
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መመሪያና የሥነ ሥርዓት ደንብ እንዲያወጡ የሚረዳ መመሪያን ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣል፡፡

## 35. የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች

1. የመንግሥት ተቋማት የቴክኒክና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀፅ (3) እና አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (በ) መሠረት ቦርድ በሚያወጣው ፖሊሲና መመሪያ መሠረት ይተዳደራሉ።
2. አካዳሚክ ባለሙያዎች ያልሆኑና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የተቀጠሩ የቴክኒክ ሠራተኞች የሚተዳደሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚወጡት ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ይሆናል፤ ሆኖም የደመወዝ ክፍያቸው በመንግስት የሕዝብ ጤና ጥበቃ ዘርፍ ለተመሳሳይ ባለሙያዎች ተፈጻሚ በሚሆነው መሠረት ይሆናል፡፡
3. መንግሥታዊ ተቋማት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸው ተፈላጊውን የብቃት ደረጃ ያላቸው መሆናቸውንና ቁጥራቸውም ከተፈላጊው ቁጥር ያልበለጠ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርባቸዋል።
4. መንግሥት በጀት ሲመድብ የመንግሥት ተቋማት ተፈላጊውን የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቁጥር ብቻ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸውን መጠን መመደቡን ያረጋግጣል።
5. ማዕከሉ ከመንግስታዊ ተቋማት ጋር በመሆን የሚያስፈልገውን የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ትክክለኛ ቁጥር ለመወሰን የሚረዳ የምጣኔ መስፈርትን ይህ አዋጅ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣል።
6. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎችን ተፈጻሚነት እንዲያገዝ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ተገቢ አደረጃጀትና ጥንቃቄ የተሞላው የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቅጥር አፈጻጸም እንዲኖረው የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
7. የመንግስት ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው የምጣኔ መስፈርት ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸው ምጣኔን ማስተካከል አለባቸው።

36. <u>የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መብትና ግዴታ</u>

1. የመንግስት ተቋማት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች መሠረት መልካም አስተዳደርን የማግኘት መብት ይኖራቸዋል።

2. ማንኛውም የመንግስት ተቋም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአስተዳደር ደንብና መመሪያን ከማውጣትና ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በአሳታፊ ሂደት ግንዛቤና መግባባት እንዲፈጠር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
3. የመንግሥት ተቋም ቦርድ አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች ላይ በመመስረትና የተቋሙን አቅም በማገናዘብ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አስተዳደር ዝርዝር መመሪያን ማውጣት ይችላል፡፡
4. ማንኛውም የተቋም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ አግባብነት ላላቸው ሕጎችና የተቋሙ መመሪያዎች የመገዛትና በተግባርም የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለተቋማት ተማሪዎች

### 37. የተማሪዎች መብት

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የማንኛውም ተቋም ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡-
   ሀ/ በመማርና በምርምር በነፃነት እውነትን የመፈለግና ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ፤
   ለ/ በመማሪያ ክፍል፣ በተቋም ግቢና በሕብረተሰብ ውስጥ ባጠቃላይ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፤
   ሐ/ በተቋም ግቢ ውስጥ ሕገ-መንግስታዊ ሰብአዊ መብታቸውና ደህንነታቸውን ተጠብቆ የመኖርና የግል ንብረታቸውን ደህንነትን የማስጠበቅ፤
   መ/ በተቋም ጉዳዮች ላይ በሕጋዊና ሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነፃነት የማራመድ፤
   ሠ/ ማንኛውም ዓይነት አድልዎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ሕጋዊ ከለላን የማግኘት፤
   ረ/ በማንኛውም የመምህርና ተማሪ ግንኙነት ገጽታዎች የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፤
   ሰ/ ስለ አካዳሚያዊ ብቃታቸው በዚህ አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በተቋሙ አካዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፤ ኢ-ፍትሃዊ ምዘና ሲፈፀም ቅሬታን

በተቋሙ ስርዓት መሰረት በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትህን የማግኘት፤

ሸ/ ግልፅነት ባለው ስርዓት መሠረት በአካዳሚክ ሰራተኞች የስራ አፈፃፀምና በአካዳሚክ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ግምገማ ላይ የመሳተፍ፤

ቀ/ በግል የትምህርት ማሕደር በቋሚነት የሚቀመጡ መረጃዎች በምስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለፁበት ሁኔታ የሚወስን የሚያስተማምን ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፤

በ/ የተማሪው የጋራ ጥቅሞችን በህጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ሕጐች በተቋቋመና የተቋሙን ተማሪዎች በአባልነት በሚያቅፍ የተቋሙ የተማሪዎች ማሕበር አባል የመሆን፤

ተ/ በተቋሙ ደንብና ስርዓት መሠረት በማሕበራቸው አማካይነት በተቋሙ መገልገያዎች የመጠቀም፤

ቸ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና የተቋም ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በማሕበራቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካይነት ተቋሙን በሚያስተዳድሩ አካላት ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤

ኀ/ የሚያስከትሏቸው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በማህበራቸው አመራር ስር ዜና፣ አስተያየትና ርእሰ አንቀፆችን ጨምሮ ሃሳብን በነፃ ለማንሸራሸር በተቋም ውስጥ የመገናኛ ሚዲያን የመጠቀም፤

ነ/ በዚህ አዋጅ መሰረት የወጪ መጋራት ስርዓት ተጠቃሚ የመሆንና የምክር አገልግሎትን የማግኘት፡፡

2. ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን የተማሪዎች መብት ማስከበሪያ የሚሆን መመሪያን የመቅረፅና የመተግበር ግዴታ አለበት፤ መመሪያው በዚህ አዋጅ መሠረት የተቀረፀና የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን ባሳተፈ ሂደት መግባባት የተደረሰበት መሆን ይኖርበታል፡፡

## 38. <u>የተቋም ተማሪዎች ግዴታ</u>

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የተቋም ተማሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ/ በክፍል የመገኘትና ትምህርቱን በሚገባ የመከታተል፣ የማንኛውም አካዳሚክ ሰራተኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣንን የማክበር፤

ለ/ በተመዘገበበት ትምህርት የተተመጡ የብቃት መመዘኛዎችን የማሟላት፤

ሐ/ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች የማወቅና የማራመድ፤

መ/ በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋሙ ግቢ ውስጥ በሕግ የተጠበቀውን የሌሎች ሰዎችን መብት የማክበር፤

ሠ/ አግባብነት ያላቸው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን እንደዚሁም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረቱትን የተቋሙ መመሪያዎችና ደንቦችን የማክበር፤

ረ/ ከተቋሙ አካዳሚክና ሌሎች ሠራተኞች እንዲሁም ከማንኛውም የተቋሙ ተማሪ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ-መንግሥታዊ መብቶቻቸውን የማክበር፤

ሰ/ ከማንኛውም ሕገወጥ ድርጊት እና ከማንኛውም ከሥነምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፤

ሸ/ የግልም ሆነ የጋራ የተማሪ ጥቅሞች አደጋ ላይ በሚወድቁበት ጊዜ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ቅሬታን በማሰማት መፍትሔን የመሻት፤

ቀ/ የተቋሙን ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም፤ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በተቋሙ ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂ የመሆን፤

በ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተቋሙ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መክፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም፡፡

2. ማንኛውም ተቋም የተማሪዎችን የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ተገቢ ሥርዓት የማውጣት ግዴታ አለበት፡፡

## 39. <u>የተማሪዎች ቅበላ</u>

1. በማንኛውም ተቋም በቅድመ ምረቃ ትምህርት ለመመዝገብ የሚችሉ ተማሪዎች የመሰናዶ ትምህርትን ያጠናቀቁና የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናን ያለፉ መሆን ይኖርባቸዋል፤ በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በሚኒስቴሩ የአቻ ግምት የተሰጣቸው ተማሪዎችም የመመዝገብ ዕድሉን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

2. የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናውን የሚያስተዳድረውና የቅበላ መስፈርቱን የሚወስነው ሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽና የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም የሚከተሉትን ተማሪዎች ይቀበላል፡-

   ሀ/ በቅድመ ምረቃ ፕሮግራሙ የመሰናዶ ትምህርትን አጠናቀው የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናን ያለፉና በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በሚኒስቴሩ የአቻ ግምት የተሰጣቸውን፤

   ለ/ ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት የቅደመ-ምረቃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና ተቋሙ ያስቀመጠውን መግቢያ የቅድመ-ምረቃ ውጤት ያላቸውን፤ ወይም ለሶስተኛ ዲግሪ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁና ተቋሙ ያስቀመጠውን መግቢያ አካዳሚክ ውጤት ያላቸውን፤

   ሐ/ ብቃትን መሠረት አድርጎ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተቋሙ የሚያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተናን ያለፉ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ምሩቃንን፡፡

4. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) እና ንዑስ አንቀፅ (3) ተራ ፊደል (ሀ) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ልዩ ድጋፍን ማግኘት ስለሚገባቸው ዜጎች እኛ የቅበላ ሥነ-ሥርዓቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ሆኖ ሚኒስቴሩ ደንቡን ለማስፈጸም በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

5. ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ የመቋቋሚያ ሕግ መሠረት በወጣ ልዩ የቅበላ ሥርዓትና የተቋሙ ሴኔት በሚወስነው አገባብ መሠረት ዓቅሙ ያላቸው ጎልማሶችን በቅድመ ምረቃ ተማሪነት ሊቀበል ይችላል፤ ሚኒስቴሩ ይህን የቅበላ ስርዓት በግል ተቋማትም ሁኔታው ሲፈቅድ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል።

6. የተማከለ የተማሪዎች ምደባ እስከቀጠለ ድረስ ሚኒስቴሩ ተማሪዎችን የሚመድበው የመንግሥት ተቋማትን በማማከር ይሆናል፤ የመንግሥት ተቋማት ራሳቸው በቀጥታ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚችሉበት ጊዜ ሲደርስና ተግባራዊ መደረጉም ሲታመንበት ሚኒስቴሩ የመግቢያ ፈተናውን በማስተዳደር፣ የማለፊያ ነጥብንና መግቢያ ነጥብን በመወሰን፣ ስለ ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚዎች መመሪያን በማውጣት፣

የቅበላ ስርዓትን በመወሰን እና የቅበላው አፈፃፀምን በመከታተልና በማስተካከል ላይ የተገደበ ይሆናል፡፡

40. <u>ስለ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች</u>

1. ተቋማት አገልግሎት መስጫ አውታሮቻቸውና ፕሮግራሞቻቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሆነው እንዲታነጹ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
2. ሁኔታና ዓቅም በፈቀደ መጠን ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎቻቸው ጥቅም ሲሉ የክፍሎቻቸውን አጠቃቀምና አመዳደብ መለወጥ፣ አማራጭ የፈተና ሥርዓቶችን መቀየስና የትምህርት ሂደቱን የሚያመቻቹ ዘዴዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል።
3. የተቋሞች ሕንፃዎች ዲዛይን፣ የግቢዎቻቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ኮምፒውተሮቻቸውና ሌሎች የመገልገያ አውታሮቻቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጐት ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል።
4. አስፈላጊ ሲሆንና አቅም በፈቀደ መጠን ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎቻቸው የቱቶሪያል፣ የፈተና ጊዜያት መራዘምና የማስረከቢያ ጊዜያት መራዘምን ጨምሮ ልዩ አካዳሚክ ዕርዳታዎች ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

41. <u>የመማር-ማስተማር ጥራትና የተማሪዎች ምዘና</u>

1. በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት የትምህርቱ አሰጣጥ በየትኛውም መልኩ ቢሆን አሳታፊ ሆኖ ተማሪን ያማከለና በንቃት መማርን የሚያራምድ መሆን ይኖርበታል።
2. በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታ በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋሙ ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መልካም ድባብ ያለው መሆን ይኖርበታል።
3. የትምህርቱ አቀራረጽና አሰጣጥ የተማሪዎችን ዕውቀትና ክህሎት የሚያበለጽግ፣ መልካም እሴቶችን የሚያስታጥቅና በተማሪዎች አመለካከት ላይ አወንታዊ ለውጥና እድገት የሚያመጣ መሆን ይኖርበታል።
4. ተማሪዎች የሚመዘኑት በመዛኝነቱ አግባብነት ባለው ስርዓትና በተማሩት ላይ ተመሥርቶ መሆን ይኖርበታል፤ የምዘና ውጤት አሰጣጥ ስርዓትም የተረጋገጠውን ዓቅም የሚገልፅ ይሆናል፡፡

5. በተቋም ደረጃ ዕውቅና የተሰጠውና በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል እንደአግባቡ በማጣጣም የሚሠራበት እና እያንዳንዱ የአካዳሚክ ሠራተኛ ሊያከብረው የሚገባ ተማሪዎችም አስቀድመው የሚያውቁት የተማሪዎች ምዘናና ፈተና ስርዓት ይኖራል፡፡
6. በተማሪዎች ምዘናና የምዘና ውጤት ደረጃ አሰጣጥ ረገድ አመራር የሚሰጡ በተገቢ የትምህርት ክፍሎች ደረጃ ብቁ አካላት እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት ይኖራል፡፡
7. ምዘናና የምዘና ውጤቶችን አስመልክተው ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች በተቋምና በአካዳሚክ ክፍሎች ደረጃ ተገቢው ትኩረት ተሠጥቷቸው በጥንቃቄና በአፋጣኝ መታየት ይኖርባቸዋል።
8. አካዳሚክ ሠራተኞች በተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥ የሥራ ላይ ሙያዊ የንድፈ-ሃሳብና የክህሎት ሥልጠና ይሰጣቸዋል፤ የማስተማር ብቃትና የምዘና ክህሎቶችን ጠንቅቆ ማወቅ በአካዳሚክ ሰራተኛነት ለመቀጠልና ዕድገትን ለማግኘት እንደ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ይወሰዳሉ።
9. በተማሪዎች በኩል ምንጭ ሳይጠቅሱ የሌላ ሰው ስራና ሐሳብን እንደ የራስ ስራና ሀሳብ ተጠቅሞ የቤት ወይም የምርምር ስራ መስራትም ሆነ በፈተናዎች ላይ ማጭበርበር፤ በአካዳሚክ ሠራተኞች በኩል ደግሞ በፈተናዎች አስተዳደር፣ በቤት ሥራዎችና በፈተናዎች እርማት እንዲሁም በውጤት አሠጣጥ ላይ በዝምድና ወይም ለማጥቃት ብሎ መስራት ከባድ ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ የዲስፕሊን ጥፋቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡
10. የማስተማር ዘዴዎች፣ የተማሪዎች ምዘና፣ የምዘና ውጤቶችና ደረጃ አሰጣጥን የሚመለከቱ ሥነ-ሥርዓቶች በተቋሙ የሴኔት ደንብ ውስጥ መካተትና በትምህርት ክፍሎች መመሪያዎች ተብራርተው መገለጽ ይኖርባቸዋል።

## ክፍል ሶስት

## የመንግስት ተቋማት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## አስተዳደርና ውስጣዊ አደረጃጀት

### 42. የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ተቋም፡-

ሀ/ የአመራርና አማካሪ አካላት፣

ለ/ የአካዳሚክ ክፍሎች፣

ሐ/ እንደአግባቡ የመማሪያ ሆስፒታል አመራር፣

ሐ/ የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች፣

መ/ ቢሮዎችና ተግባራቱን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችሉ ሌሎች መገልገያዎች፣

ይኖሩታል።

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የአካዳሚክ ክፍሎችን ለመመስረት ሲወሰን ከትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ ከትብብር አሰፈላጊነትና ከውጤታማ የሀብት አጠቃቀም አኳያ እየታየ መሆን ይኖርበታል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተቋቋመ የትምህርት ክፍል በፕሬዚዳንቱ ተዘጋጅቶና በአስተዳደር ካውንስል፣ በዩኒቨርስቲ ካውንስልና በሴኔት የተመከረበትና በቦርዱ የፀደቀ የአስተዳደር ሥርአት ይኖረዋል። የአስተዳደር ሥርዓቱም የአመራርና የአስፈፃሚ አካላትን የያዘና ኃላፊነታቸውን እንዲሁም የአመራርና የአስተዳደር ሥነ-ሥርአቶችን ያካተተ ይሆናል፡፡

4. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም በቦርዱ የማፀደቅና በሚኒስቴሩም የማስፈቀድ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ በአለም አቀፍ መልካም ልምድ ላይ ተመሥርቶ ተልእኮውን ለማሳካት የሚያስችል የተሻለ ውጤታማ ሥራ ለመስራት ብቻ በማሰብ አደረጃጀቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀየር እራሱን እንደገና ሊያደራጅ ይችላል፡፡

5. ሚኒስቴሩ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም መመሪያ ካልሰጠ በስተቀር፣ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት እራሱን እንደገና ለማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተቋሙ ፕሬዚዳንት በአስተዳደር ካውንስል፣ በዩኒቨርሲቲ ካውንስል፣ በሴኔትና በተቋሙ የመምህራንና የተማሪዎች ማሕበራት የተመከረበት የተሟላ የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

## 43. የአመራርና አማካሪ አካላት

1. ማንኛውም የመንግሥት ተቋም እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት የአመራርና አማካሪ አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ቦርድ፤

ለ/ ፕሬዚዳንት፤

ሐ/ ሴኔት፤

መ/ የአስተዳደር ካውንስል፤

ሠ/ የዩኒቨርሲቲ ካውንስል፤

ረ/ የትምህርት ክፍል ካውንስል፤

ሰ/ የትምህርት ክፍል አስተዳደር ካውንስል፤

ሸ/ የዲፓርትመንት ጉባኤ፤

ቀ/ በቦርዱ ወይም በሴኔቱ ወይም በዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ የሚቋቋሙ አስፈላጊ ቁጥርና አይነት ያላቸው አማካሪ ወይም ልዩ ኮሚቴዎች ወይም ካውንስሎች፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት ተቋም የአመራርና የአማካሪ አካላት አደረጃጀትና ስያሜዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ (3)፣ (4) እና (5) መሠረት ፕሬዚዳንቱ በሚሰጠው ምክር ላይ ተመሥርቶ ቦርዱ ሊለውጣቸው ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ተራ ፊደል (ረ) እስከ (ሸ) የተመለከቱት የትምህርት ክፍሎች አመራር አካላት ይዘት፣ አመሰራረት፣ ሃላፊነትና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 42 (3) መሰረት ይወሰናል፡፡

## 44. የቦርድ ኃላፊነት

1. የመንግሥታዊ ተቋም ቦርድ የተቋሙ የበላይ አመራር ሆኖ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ/ ተቋሙ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች መተግበሩንና በተቋሙ ውስጥ መልካም አስተዳደር መስፈኑን መከታተልና ማረጋገጥ፤

ለ/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተቋሙ እቅድ፣ በጀት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ አደረጃጀት፣ የአስተዳደርና አሰራር ሥርዓት፣ የውስጥ

ደንብና የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን በሚመለከት የሚቀርቡለት ሃሳቦችን መርምሮ ማፅደቅና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤

ሐ/ በፕሬዚዳንቱ በሚቀርብ ሃሳብ ላይ በመመሥረት ምክትል ፕሬዚዳንቶችና ሌሎች አካዳሚክ ሃላፊዎች እንዲሁም የሴኔት አባላት እንዳግባቡ የሚታጩበት፣ የሚሾሙበት ወይም የሚመደቡበትና የሚመረጡበትን ሥርዓትና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣት እና በትክክል መተግበራቸውንም መከታተል፤

መ/ ፕሬዚዳንታዊ እጩን ለሹመት እንደአግባብነቱ ለሚኒስትሩ ወይም ለክልሉ አካል ማቅረብ እና ፕሬዚዳንቱ በሚያቀርበው መሠረት ምክትል ፕሬዚዳንቶችን መሾም፤

ሠ/ አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ምክትል ፕሬዚዳንት ኃላፊነቱን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሳየ ከሃላፊነት ማሰናበትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ፤ ፕሬዚዳንቱን የሚመለከት ሲሆን ደግሞ ሚኒስትሩን በማማከር እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ፤

ረ/ የተቋሙን ኦዲተሮች መሾምና ክፍያቸውን መወሰን፤

ሰ/ የተቋሙን የስትራቴጂክ እቅድ፣ አመታዊ እቅድና በጀት ማቅረብና ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን መከታተል የተቋሙን የክንውን ሪፖርትና የፋይናንስ መግለጫን ማፅደቅና ማቅረብ፤

ሸ/ ተቋሙ የዋና ዋናና የጥቃቅን ገቢዎቹን ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ መያዙንና ወጪዎቹ በበጀቱ መሠረት መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፤

ቀ/ የተቋሙ ሌሎች የአመራር አካላት ከባድ የሕግ መጣስ ተግባር በሚፈፅሙበት ጊዜ ወይም ከባድ የሆነ የገንዘብ ብክነት ሰለመከሰቱ ጥርጣሬ ካለ ወይም በርግጥ ተከስቶ ከሆነ በራሱ ስልጣን ክልል ተገቢውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድና ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ፤

በ) በፌደራል መንግስት የሰራተኞች አዋጅና ደንቦች መሠረታዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቅጥር፣ እድገት፣ ዲሲኘሊን፣ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን የሚመለከት ፖሊሲን እንዳስፈላጊነቱ እንዲዘጋጅ ማድረግና ማፅደቅ፤

ተ) ተቋሙን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት እና ለሚኒስቴሩ የሚያስፈልግ ከሆነም ሪፖርት ማድረግ፤

ቸ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤ ለከፍተኛ ትምህርት ዕድገት በሚጠቅሙ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ በአጠቃላይና የተቋም አስተዳደር ላይ በተለይ በተቋም መሪነቱ ከሚያስተውለው ወይም ከሚያውቀው በመነሳት ለሚኒስቴሩ ምክር መስጠት፤

ኀ) በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት፤

ነ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ኀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ ቅሬታዎችን በተፋጠነ መንገድ ተቀብሎ የሚፈታበት የተሟላ ተቋማዊ ሥርአት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

ኘ) የተቋሙን፣ የተቋሙን አካዳሚክ ክፍሎች፣ የመሪዎቹንና የአስተዳደር አካላቱን የስራ አፈፃፀም በፕሬዚዳንቱ ሪፖርት መሰረት ከእቅድ አኳያ መገምገም፤

አ) የሴኔት ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው የአካዳሚክ ሕጎች መፈፀማቸውን መከታተል፤

ከ) በፕሬዚዳንቱ ወይም በሴኔት የተላለፉ ውሳኔዎች የተቋሙን ተልእኮ የሚጎዱ ወይም የመንግስትን ፖሊሲ፣ ይህንን አዋጅ ወይም ሕገ-መንግስቱን የሚቃረኑ ሆነው ሲገኙ ውሳኔዎቹን መሻር፤

ኸ) የራሱን የአሰራር ሥነሥርዓትና የውስጥ አስተዳደር ደንብና አባላቱን የሚመለከት የዲስፕሊን ደንብን ማውጣት፤

ወ) የፕሮፌሰርነት የማዕረግ ዕድገትን ማፅደቅ፤

ዐ) ከፕሬዚዳንቱ በሚቀርብ ምክር ላይ ተመሥርቶ ተቋሙ ለትምህርት የሚያስከፍላቸውን የተለያዩ ክፍያዎች አይነትና መጠን እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት በወሰነው መሠረት የተቋሙን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተከፋይ አበሎችን፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎችንና የመሳሰሉትን መወሰን፤

ዘ) የሴኔቱን፣ የአስተዳደር ካውንስሉንና የዩኒቨርሲቲ ካውንስሉን በትክክል መደራጀትና መሥራት መከታተል፤ አስፈላጊነቱን ሲያምንበት በፕሬዚዳንቱ

ምክር ላይ በመመሥረት ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ወይም ለዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ የሆኑ ልዩ አማካሪ አካላትን ማቋቋም፤

ገቨ) በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና በተቋሙ ሟቋቋሚያ ሕግ የተሰጠው ሌላ ኃላፊነትን መወጣትና ይህን አዋጅ ማክበርና ተቋሙም እንዲያከብረው ማድረግ፡፡

2. የቦርዱ ተጠሪነት እንዳግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም ለተገቢው የክልል መንግስት አካል ይሆናል፡፡

3. የፌደራል መንግስት ተቋም የቦርድ ሰብሳቢ በሚኒስትሩ የሚሾም ሆኖ ቦርዱ የተሰጠውን ሃላፊነት በትክክል መወጣቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

4. የፌደራል መንግስት ተቋም ቦርድ አባላት ጥቅማ ጥቅሞች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑና በተቋሙ የሚሸፈኑ ሆኖ የተቋሙን ዓቅም ግምት ውስጥ ያስገቡ ይሆናሉ።

45. <u>ስለቦርዱ አባላትና ምልአተ ጉባኤ</u>

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮና ዓቅምን መሰረት ያደረገ የሴቶች ተሳትፎ ያለበት ሰባት ድምፅ መስጠት የሚችሉ አባላት ይኖሩታል፡፡

2. ሚኒስትሩ ከቦርዱ ሰብሳቢ በተጨማሪ ሶስት ድምፅ መስጠት የሚችሉ የቦርድ አባላትን መርጦ ይሾማል።

3. ፕሬዚዳንቱ ከአስተዳደር ካውንስሉና ከሴኔቱ ጋር በመመካከር ሌሎች ሶስት እጩዎችን በሚኒስትሩ እንዲሾሙ ያቀርባል፡፡

4. የተቋሙ ፕሬዚዳንት ድምፅ የማይሰጥ የቦርዱ አባልና ፀሃፊ ይሆናል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት የሚሾሙት የቦርድ አባላት በኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉ ወይም ያገለገሉና በተለይ በማስተማር ወይም በምርምርና በግል ስብዕናቸው የታወቁ ግለሰቦች፣ ወይም እውቀታቸው፣ ልምዳቸውና አትኩሮታቸው ለከፍተኛ ትምህርት አላማዎች በአጠቃላይና ለተቋሙ ተልእኮዎች መሳካት በተለይ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችላቸው የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ተወካዮች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

6. ቦርዱ በራሱ ውሳኔ ማንኛውንም ሰው በአስረጂነት በስብሰባዎቹ ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

7. አምስት ድምፅ የሚሰጡ የቦርድ አባላት ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ ሆኖም አምስት የቦርድ አባላት መሳተፍ የማችይሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ከተፈጠረ ቦርዱ

በአራት አባላት ምልአተ ስብሰባዎቹን ያካሂዳል፡፡ ቦርዱ ይህንን ሁኔታ በተመለከተ በአሰራር ሥነ-ሥርአት ደንቡ ላይ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

8. የቦርዱ ሰብሳቢ ጊዜ በተቆረጠለት ስብሰባ ላይ መሳተፍ የማይችል ከሆነ በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላት ያንን ስብሰባ የሚመራ ሰብሳቢ ከመካከላቸው በመምረጥ የስብሰባውን አጀንዳ ይፈጽማሉ፡፡
9. ቦርዱ በጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚያሳልፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡

46. <u>ስለቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በአመት ከሦስት እስከ አራት የሚሆኑ መደበኛ ስብሰባዎችን ያደርጋል፤ ቦርዱ ባጠቃላይ ሃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችልና በተለይ የእቅድና የበጀት ዝግጅቶች እንዲሁም አፈጻጸም ላይ አስተዋፅኦ ለማድረግ እንዲችል መደበኛ ስብሰባዎቹ አመቺ በሆኑ ወቅቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አባላቱ አንድ ሶስተኛው በሚጠይቁበት ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ማድረግ ይችላል፡፡
3. ፕሬዚዳንቱ የቦርዱ ሰብሳቢ ስምምነትን በማግኘት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማድረግ ይችላል፤ ሁሉም የቦርዱ ስብሰባዎች በቂ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ በሰነድ መያዛቸውን፣ ሰነዶቹ በጥንቃቄ መጠበቃቸውን እና ቦርዱ በሚያዘው መሠረት ውሳኔዎቹ በትክክል ለሚመለከታቸው መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

47. <u>የቦርድ አባልነት መቋረጥ</u>

የቦርድ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

1. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፤
2. በፈቃደኝነት ከአባልነት በመልቀቅ፤
3. በሞት፣ በሕመም ወይም በከባድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘት፤
4. በከባድ ጥፋት፣ በችሎታ ማጣት ወይም በስብሰባዎች ላይ ለመገኘት ከባድ የሆነ ድክመት በማሳየት ወይም ባለመቻል፤
5. ሚኒስቴሩ ቦርዱን ሙሉ በሙሉ ለመቀየር ወይም በከፊል ለመለወጥ ውሳኔ ላይ ሲደርስ።

48. <u>ስለቦርድ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ</u>

1. ቦርዱ አመራሩን በቀጣይነት ለማሻሻል የሚረዱ ትምህርቶችን ለማግኘት የራሱን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል።
2. የቦርዱ የአፈፃፀም ግምገማ ፕሬዚዳንቱ ተሳትፎ በሚያደርግበት ድምፅ የመስጠት መብት ባላቸው አባላት በዝግ ስብሰባ ይካሄዳል።
3. የቦርዱ ሰብሳቢ የግምገማውን ውጤቶች በየወቅቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያደርጋል፤ የቦርድ ሰብሳቢዎችና የትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ የጋራ መድረክም በዓመት ሁለት ጊዜ ይኖራል፡፡
4. ቦርዱ ግምገማውን መቼና እንዴት እንደሚያካሂድ ይወስናል፤ ሆኖም በአመት ቢያንስ አንድ የክትትል ግምገማና አንድ የማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል።

49. <u>ስለሴኔት</u>

የቦርዱ ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሴኔት የአካዳሚክ ጉዳዮችን በሚመለከት መሪ አካል በመሆን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. የተቋሙን የትምህርት ዘመን መወሰን፤
2. የተቋሙን አካዳሚክ ፕሮግራሞችንና ስርዓተ ትምህርቶቻቸውን መወሰን፤ የትምህርት ክፍሎች የሚሰጡትን ትምህርት እና የሚያካሂዱትን ምርምር ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ መምራትና አቅጣጫን ማስያዝ፤
3. በዚህ አዋጅ መሠረት የትምህርትና ምርምር ፕሮግራሞችን በሚመለከትና የአካዳሚክ ማሕበረሰቡ የሚተዳደርበትን ደንብ ማውጣትና ስለ መከበሩም መከታተል፤
4. ዲግሪ የሚሰጥበትን ወይም የሚሰረዝበትን ሁኔታዎችን መወሰን፤
5. ተቋም አቀፍ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻና የተማሪዎች ምዘና ስርዓትን ማውጣት፤
6. በአካዳሚክ ሃላፊነት ስለሚሾሙት ጥያቄ ሲቀርብለት ለፕሬዚዳንቱ ምክር መስጠት፤
7. የፕሮፌሰር ማዕረግ ዕድገት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ደግፎ ለቦርዱ ማቅረብና በተባባሪ ፕሮፌሰር ዕድገት ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ መስጠት፤
8. በትምህርት ክፍሎች በሚቀርብ በፕሮፌሰር ደረጃ የሚፈፀም የአዲስ ቅጥር ጥያቄ ላይ መወሰን፤

9. የሴኔት ኮሚቴዎች ብዛት፣ አባልነት፣ ሃላፊነትና አሰራርን መወሰን፤

10. በፕሬዝዳንቱ በሚቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በተቋሙ እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባ ልዩ አስተዋፅኦ ላስመዘገቡ ሰዎች የክብር ዲግሪ ወይም ሌሎች ሽልማቶችን መስጠት፤

11. በተቋሙ ሥር ስላሉት የትምህርት ክፍሎች መክፈት፣ መዝጋት ወይም መዋሃድ በፕሬዝዳንቱ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት መርምሮ ማፅደቅ፤

12. በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የሚሰጠውን ሌላ ሃላፊነት ወይም በፕሬዚዳንቱ የሚመራለትን ጉዳይ ማከናወን፡፡

50.<u>የሴኔት አባላት</u>

1. የሴኔት የአባልነት ሁኔታ፣ የአገልግሎት ዘመን እና የአባላት ቁጥር በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከሴኔቱ አባላት ቢያንስ አብላጫው በፕሬዝዳንቱ የሚመረጡ ሆነው ለሃላፊነቱ የሚመጥኑና በተቋሙ ውስጥ በተነፃፃሪ ረጅም አገልግሎት ያላቸው የአካዳሚክ ሠራተኞች ይሆናሉ።

3. ፕሬዝዳንቱ የተቋሙ የአካዳሚክ ማሕበረሰብ በተገቢ ሁኔታ በሴኔቱ ውስጥ መወከሉን ያረጋግጣል፤ የሴኔቱ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

4. ለአፈፃፀም ውጤታማነት ሲባል በሴኔቱ አባልነትና የአባላት ብዛትን እንዲሁም የስራ ዘመን ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፕሬዚዳንቱ ምክር መሰረት ቦርዱ ማሻሻያ ማድረግ ይችላል፡፡

51. <u>የሴኔት ስብሰባዎች</u>

1. ሴኔት የአባላቱን ዲስፕሊን ጨምሮ የራሱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወስናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ፕሬዝዳንቱ ሲጠይቅ ሴኔቱ ቀጣይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

3. ሴኔቱ ፕሬዚዳንቱ ወይም ቦርዱ ሲጠይቅ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛው ሲጠይቅ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

4. ፕሬዚዳንቱ የሴኔት ስብሰባዎች በበቂ ሁኔታ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ መዘገባቸውንና ቃለ ጉባኤዎቹ መጠበቃቸውን፣ በጉዳዮች ላይ

የሚደረገው ውይይት ሁሉንም የዳሰሰ መሆኑን እና የሴኔት ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው በትክክል መተላለፋቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፡፡

5. ከሴኔት አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤ የሴኔት ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፤ ደምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለም ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
6. ሴኔት በሃላፊነቱ መሰረት የትምህርት ክፍሎችን፣ የኮሚቴዎቹን እና እንደ አካል የራሱን የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፤ የግምገማው ውጤት በፕሬዚዳንቱ አማካኝነት ለቦርዱ ይቀርባል፡፡
7. ሴኔቱ በማንኛውም ስብሰባው ለስራ አስፈላጊ ናቸው ያላቸው የስራ ክፍሎችን ወይም ግለሰቦችን በአስረጂነት ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

52. <u>ስለመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመትና የስራ አፈፃፀም ግምገማ</u>

1. የተቋም ፕሬዚዳንት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) መሠረት ቦርዱ አወዳድሮ ከሚያቀርባቸው እጩዎች መካከል እንደ አግባቡ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ይሾማል፡፡
2. የፕሬዚዳንትነት የሃላፊነት ቦታ በቦርዱ በሚሰየም አካል በይፋ ለተወዳዳሪዎች ይገለጻል፡፡
3. የመንግሥት ተቋም ምክትል ፕሬዚዳንቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሐ) እና (መ) መሠረት በይፋ ተወዳዳሪዎች ተጋብዘው የተሻለ ብቃትና ዝግጁነት ያለው ተመርጦ በቦርድ ይሾማል፡፡
4. የመንግስታዊ ተቋም እጩ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች የአካዳሚክ መሪነት እና የአስተዳደር ክህሎት ያላቸው እንዲሁም ለተቋማዊ ለውጥና እድገት ዝግጁ የሆኑና ሕገ መንግስቱንና የመንግስት ፖሊሲዎችን የተቀበሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውድድርና የምርጫ ሥነ ሥርዓት ዝርዝር መመሪያ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግና በቦርዱ ይወጣል፡፡
6. የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የሥራ ዘመን ስድስት አመት ሲሆን የምክትል ፕሬዚዳንት አራት አመት ይሆናል፤ ሆኖም የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተደጋጋሚ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

7. ቦርዱ የፕሬዚዳንቱንና የምክትል ፕሬዚዳንቶቹን የሥራ አፈፃፀም የክትትል ግምገማ በአመት ሁለት ጊዜ እንዲሁም ጥልቀት ያለው ግምገማ ደግሞ በየሶስት አመቱ ፕሬዚዳንቱንና ምክትል ፕሬዚዳንቶቹ በተገኙበትና ያለ ድምፅ በሚሳተፉበት ሁኔታ ያካሂዳል፡፡
8. ማንኛውም ሰው ከ180 ቀናት በላይ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ወይም ተጠባባቂ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ መቆየት የለበትም፡፡

53. <u>የመንግስት ተቋም ፕሬዚዳንት ኃላፊነት</u>

1. የቦርዱ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት ተቋም ፕሬዚዳንት የተቋሙ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን የሚከተሉት ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ/ ተቋሙ የሥራ ድርሻውንና ተልዕኮውን ለማሳካት ይችል ዘንድ ተቋሙን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
   ለ/ የተቋሙ አካላትና ማሕበረሰብ የከፍተኛ ትምህርት አላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች ማክበራቸውን ያረጋግጣል፤
   ሐ/ የዚህ አዋጅና የሌሎች በተቋሙ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ አግባብነት ያላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
   መ/ ተቋሙ አገሪቱ በምትፈልገው መጠንና አይነት ከፍተኛ ጥራት ወይም ብቃት ያላቸው ምሩቃንን ማፍራቱን ያረጋግጣል፤
   ሠ/ መማር ማስተማርንና ምርምርን የሚያበረታታ አመቺ ተቋማዊ ሁኔታን ይፈጥራል፤ በቀጣይነት ይገነባል፤
   ረ/ የተቋሙ የምርምርና የማማከር ተግባራት ሁሉ ቅድሚያ በሚሰጣቸው አገራዊ ጉዳዮች ላይ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
   ሰ/ ተቋሙ ተልእኮውን ለማሳካት ከአለም አቀፍ እንዲሁም ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት፣ አግባብነት ካላቸው ኤጀንሲዎች እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ድርጅቶችና ማሕበራት ጋር በዘላቂነት ግንኙነት እንዲፈጥር ያደርጋል፤
   ሸ/ ተቋሙ ሁልጊዜም ከሀገራዊና አለም አቀፋዊ እድገቶች ጋር እኩል የሚራመድና በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምርምር፣ በማማከር እና በማሕበረሰብ አገልግሎቶች የአገሪቱን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችለው ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ቀ/ ተቋሙ በሰው ሃይሉ፣ በአደረጃጀቱና አሰራሩ ለተቋሙ ተልዕኮ የሚመጥን ብቃት ያለው የውስጥ አመራርና አስተዳደር ሥርአት እንዲኖረው ያደርጋል፤

በ) የአካዳሚክ ሃላፊዎችና የሴኔት አባላትን የአሰያየምና የሹመት ስርአትን በማዘጋጀትና በቦርዱ በማፀደቅ በተግባር ላይ ያውላል፤

ተ) በትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ በተቋማዊ ነፃነትና ተጠያቂነት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትና በወጪ ቆጣቢነት መርሆች ላይ በመመሥረት የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትን ለሴኔቱና ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፤

ቸ) የቅጥርና ሃላፊነት ቦታዎች በውድድር የሚያዙ መሆኑንና ከሃላፊነት መነሳትም በስራ አፈፃፀም ግምገማ፣ በዲስፕሊን ጉዳይ እና በአገልግሎት ዘመን ማብቃት ብቻ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ኀ) የተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ፣ ደንብና መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርአት አግባብነት ባለው የመንግስት ፖሊሲ፣ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሰረት መቀረጻቸውን ያረጋግጣል፤

ነ) ተቋማዊ የደረጃ መለኪያዎችን ያዘጋጃል፤ የተቋሙ የአካዳሚክና የአስተዳደር ሥራዎች በወጡት መለኪያዎች መሠረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ኘ) የተቋሙን ገቢና ወጪ በትክክል የሚያሳዩ የሂሳብ መዛግብት መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

አ) የቦርድ፣ የሴኔት፣ የአስተዳደር ካውንስል እና የዩኒቨርሲቲ ካውንስል ሰብሰባዎች በበቂ ዝግጅትና ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ከ) በተቋሙ ውስጥ ወይም በተቋሙና በሶስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን የተቋሙን ተልእኮና ጥቅሞች ከማሳካት አኳያ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፤

ኸ) የተቋሙ እንቅስቃሴና መሠረታዊ ግንኙነቶች በተገቢው የመረጃ ስርዓት መመዝገባቸውን፣ መረጃው በአግባቡ መጠበቁንና አግባብነት ላላቸውም ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ወ) የተቋሙን እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፀድቁም ያስፈፅማል፤

ሀ) ቦርዱ ፣ የተቋሙ ማሕበረሰብ ፣ መንግስትና ሕዝብ ስለተቋሙ ሁኔታ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ዘ) በተቋሙ ምድረ ግቢ ህይወትና ንብረትን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ የአደጋ መከላከያና የጥበቃ ሥርአት እንዲገነባ ያደርጋል፤

ዠ) ተቋሙ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸውም ግንኙነት ተቋሙን ይወክላል፤

የ) በተቋሙ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤

ደ) እንዳስፈላጊነቱ ለምክትል ፕሬዚዳንቶች እና አግባብነት ላላቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ሃላፊዎች ሃላፊነቱን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ጀ) የውጪ ጉዞዎቹን በታቀዱና ለተቋሙ ባላቸው ፋይዳ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ጠ) በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ እና በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. ፕሬዚዳንቱ ሙሉ ጊዜውን ለቢሮው ስራዎች ያውላል፤ ለአገልግሎቱ ተገቢውን ደሞዝና ጥቅማጥቅሞች ያገኛል፡፡

3. ፕሬዚዳንቱ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራው ላይ በማይገኝበት ጊዜ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ እሱን ተክቶ እንዲሠራ ይወክላል፤ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱም የማይገኝ ቢሆን ግን ሌላ ምክትል ፕሬዚዳንትን ሊወክል ይችላል፡፡

## 54. የመንግስት ተቋም ምክትል ፕሬዚዳንት ሃላፊነት

1. በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የሚሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግስት ተቋም ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፦

   ሀ/ ፕሬዚዳንቱን ሃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ ማማከርና ማገዝ፤

   ለ/ በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

2. ማንኛውም የመንግስት ተቋም ቦርዱ እንደሁኔታው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር በመመካከር አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚወስነውን ያክል ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይኖሩታል።

3. ምክትል ፕሬዚዳንቶች አብዛኛውን የስራ ጊዜያቸውን ለቢሮው ስራዎች ያውላሉ፤ ለአገልግሎታቸውም ተገቢውን ደሞዝና ጥቅማጥቅሞች ያገኛሉ፡፡

4. በማንኛውም የመንግስት ተቋም ውስጥ ተባባሪ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚባል አይኖርም።

## 55. ስለፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት አገልግሎት መቋረጥ

1. የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ከሃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፡-

   ሀ/ በፈቃዱ ሥራ በመልቀቅ፤

   ለ/ በችሎታ ማጣት፣ በከባድ ጥፋት፣ በሕመም ወይም በሞት ምክንያት የተሰናበተ ከሆነ፤

   ሐ/ በፈቃድ ከ180 ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ከተለየ፤

   መ/ ያለፈቃድ ከ45 ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ከተለየ፤ ወይም

   ሠ/ የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ከቦርድ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ወይም የቦርዱ ሃሳብ ባይቀርብም ተገቢ እርምጃ ነው ብሎ ካመነ እንደአግባቡ ሚኒስትሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ኃላፊ ፕሬዝዳንቱን ከሥራ ማሰናበት ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ቦርዱ ምክትል ፕሬዚዳንትን ከሃላፊነት ሊያሰናብት ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሶስት ተከታታይ የክትትል ወይም በአንድ ጥልቅ የስራ አፈፃፀም ግምገማው የፕሬዚዳንቱ ወይም የምክትል ፕሬዚዳንቱ በሃላፊነት መቀጠል ተቋሙን ይጎዳል ብሎ ቦርዱ ካመነ እንዳግባብነቱ ከሃላፊነቱ እንዲሰናበት እርምጃን ሊያስወስድ ወይም ሊወሰድ ይችላል፡፡

## 56. የአስተዳደር ካውንስል

1. ፕሬዚዳንቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሃላፊዎች ለመጨመር ያለው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶቹ እና የተቋሙ አጠቃላይ ተማሪዎች ጉዳይ ሃላፊ የአስተዳደር ካውንስሉ ዋናዎቹ አባላት ይሆናሉ፤ የአስተዳደር ካውንስሉ ሰብሳቢ ፕሬዚዳንቱ ይሆናል፡፡

2. የአስተዳደር ካውንስሉ በስትራቴጂክ ጉዳዮችና ፕሬዚዳንቱ በጋራ መታየት አለባቸው ብሎ በሚያምንባቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ፕሬዝዳንቱን ያማክራል፤

እንዲሁም የተቋሙን እንቅስቃሴዎች የመከታተያ፣ የማስተባበሪያና የመገምገሚያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡

3. የአስተዳደር ካውንስሉ ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ በመደበኛነት በታወቀ ቀንና ሰዓት መሠረት መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
4. የአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባዎቹን የሚያካሂደው ከመደበኛ አባላቱ መካከል አብዛኛዎቹ በተገኙበት መሆን ይኖርበታል፡፡
5. የአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ፕሬዚዳንቱ በሚመድበው ፀሐፊ መያዝ ይኖርበታል፡፡
6. ፕሬዚዳንቱ በአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባዎች ሃሳብ በግልፅና በነፃ መንሸራሸሩን ያረጋግጣል፤ የሀሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የተፎካካሪ ሀሳቦችን የተቀባይነት ክብደት ለማየት ሲባል ብቻ ፕሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡
7. በፕሬዚዳንቱ ወይም በሱ በተወከለ ሌላ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሌላ አባል ልዩነቶች ሲኖሩ የአስተዳደር ካውንስሉን ውይይትና ውጤት ለሶስተኛ ወገን መግለጽ አይችልም።
8. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በግል ተቋማት ላይም እንዳግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 57. <u>የዩኒቨርሲቲ ካውንስል</u>

1. የዩኒቨርሲቲ ካውንስል በፕሬዚዳንቱ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ፣ አባላቱ የአስተዳደር ካውንስሉ ዋናዎቹ አባላት፣ የአካዳሚክ ክፍሎች ሃላፊዎች፣ የሴኔት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የቤተመጻሕፍት ዋና ሃላፊ፣ ሬጅስትራር፣ ሌሎች ቁልፍ የአካዳሚክ መኮንኖች፣ የአገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ሃላፊዎች እና በፕሬዚዳንቱ ምክር ላይ ተመሥርቶ ቦርዱ በሚወስነው መሠረት የጾታ ተዋጽኦው የጠበቀ የአካዳሚክ ሠራተኞችና የተማሪዎች ተወካዮች ይሆናሉ።
2. የዩኒቨርሲቲ ካውንስል በተቋሙ ረቂቅ እቅድ፣ በጀት፣ አደረጃጀትና መመሪያዎች፣ የትምህርት ፕሮግራሞች ፣ የትብብርና የግንኙነት ስምምነቶች፣ በትምህርት ክፍሎች መከፈል፣ ውህደትና መዘጋት እና በተቋሙ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ሃሳብ በመስጠት ፕሬዚዳንቱን ያማክራል፡፡
3. የዩኒቨርሲቲ ካውንስል መደበኛ የስብሰባ ቀንና ሰዓት ኖሮት ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

4. በዩኒቨርሲቲ ካውንስል ስብሰባ ላይ የአባላቱ መገኘት ግዴታ ነው፤ በፕሬዚዳንቱ ፊቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር አባልነት በውክልና ሊሰጥ አይቻልም፤ ስብሰባዎች ያለምልዓተ ጉባኤ ሊካሄዱ ይችላሉ፡፡
5. ፕሬዚዳንቱ በዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ ስብሰባ ሂደት ሃሳብን በነፃ ለመግለፅ የሚያበረታታ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤ በካውንስሉ ውይይት ሰፊ የሃሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የሃሳቦቹ ክብደትን ለማወቅ ሲባል ፕሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. የአስተዳደር ካውንስሉ ፀሀፊ ድምፅ የማይሰጥና በውይይቱ ላይ የማይሳተፍ ፀሀፊ ሆኖ ለዩኒቨርሲቲ ካውንስሉም ያገለግላል፡፡
7. ፕሬዚዳንቱ ወይም ፕሬዚዳንቱ ከሰየመው ሰው ውጪ ማንኛውም አባል የዩኒቨርሲቲ ካውንስሉ ቃል አቀባይ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፤
8. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዩኒቨርሲቲ ካውንስል የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
9. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንዳግባቡ በግል ተቋማትም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

58. <u>የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ</u>

1. የመንግሥት ተቋማት ጥረቶቻቸውን ለማስተባበር፣ የትምህርት መለኪያዎችንና አሰራሮችን ለማመሳሰል፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እና ሚኒስቴሩን በከፍተኛ ትምህርት ሀገራዊና አለምአቀፋዊ የስትራቴጂ ጉዳዮች፣ እድገትና ሁኔታዎች ላይ ለማማከር በዚህ አዋጅ እውቅና የተሰጠው የምክክር መድረክ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2. የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ በዚህ አዋጅ መሰረት መመስረቱን በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ይፋ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡
3. የመንግስት ተቋማት ፕሬዚዳንቶች ተቋሞቻቸውን በመወከል የምክክር መድረኩ አባላት ይሆናሉ፡፡ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምክክር መድረኩ ስያሜ፣ አላማ፣ ተግባርና ሀላፊነት አመራር፣ አሰራርና የስነስርዓት ደንብ በፕሬዚዳንቶቹ ጉባኤ ሊወሰን ይችላል፡፡
4. የምክክር መድረኩ በፕሬዚዳንቶቹ ጉባኤ ውሳኔ የሚቋቋም ፅህፈት ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

5. የምክክር መድረኩ ቃል አቀባይ በፕሬዚዳንቶች ጉባኤ ደንብ መሰረት በሰብሳቢነት የተመረጠው የመንግስት ዩንቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡
6. የምክክር መድረኩ ስራውን የሚያከናውነው በአባል ተቋማት አመታዊ የአባልነት መዋጮ፣ ስጦታዎችና ከሌሎች በሕግ ከተፈቀዱ ምንጮች በሚያገኘው ገንዘብ ይሆናል፡፡
7. የምክክር መድረኩ በአሰራሩ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጐች ድንጋጌዎችንም ማክበር ይኖርበታል።
8. ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ በከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮች ላይ ከምክክር መድረኩ ጋር ለመምከር ይችላል፡፡
9. በመንግስት ተቋማት የምክክር መድረክና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሰረት በተቋቋመ የግል ተቋማት ማህበር መካከል እንዳስፈላጊነቱ የምክክር ግንኙነት ሊኖር ይችላል፡፡
10. የመንግስት ተቋማት የምክክር መድረክ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ወይም የሌሎች ሕጎችን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ ግድፈቶቹን እስኪያስተካክል ድረስ በሚኒስቴሩ ትዕዛዝ ሊታገድ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለመንግሥት ተቋማት መከፈል፤ መዋሃድ፣ የስም ለውጥና መዘጋት

### 59. የመንግሥት ተቋም መከፈል፤ መዋሃድ ወይም የስም ለውጥ

1. አንድ የመንግስት ተቋም እንደአግባብነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ወይም በሚመለከተው ክልል በሚወጣ ሕግ መሠረት ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የመንግስት ተቋማት ሊከፈል ወይም ከሌላ የመንግስት ተቋም ጋር ሊዋሃድ ወይም ስሙ ሊለወጥ ይችላል፡፡
2. የመንግሥት ተቋማት መከፈል፣ መዋሃድ ወይም ስም መለወጥ የሚከናወነው የዚህ አዋጅና የሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይሆናል፡፡

### 60. የመንግሥት ተቋም መዘጋት

1. እንደአግባብነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ውሳኔ የመንግሥት ተቋም እንዲዘጋ ማድረግ ይቻላል፡፡

2. የመንግሥት ተቋም መዘጋት በተገቢው ሚዲያ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

## 61. ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ

1. የመንግስት ተቋም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የመንግስት ተቋማት የተከፈለ ከሆነ መብቶቹና ግዴታዎቹ ለአዲሶቹ ተቋማት ይተላለፋሉ፡፡ እያንዳንዱ አዲስ ተቋም ከነባሩ ተቋም የሚተላለፍለት መብትና ግዴታ መጠን መከፈሉ በተወሰነበት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ወይም የክልሉ ሕግ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተዋሃዱ ተቋማት መብትና ግዴታ ለአዲሱ ተቋም ይተላለፋሉ፡፡
3. በዚህ አዋጅ መሠረት የተከፈለው ወይም የተዋሃዱት የመንግስት ተቋማት ሕጋዊ ሰውነታቸውን አዲሶቹ ተቋማት በሕግ ከተቋቋሙበት ቀን ጀምሮ ያጣሉ።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ የስም ለውጥ ያደረገ ተቋምን በሚመለከትም ተፈፃሚ ይሆናል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለመንግሥት ተቋም በጀትና የገንዘብ አስተዳዳር

## 62. በጀት

1. የፌዴራል መንግስት ወይም ክልሎች ለመንግስት ተቋማት በጀት የሚመድቡት በስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነት ላይ በተመሠረተ የጥቅል በጀት ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡
2. የመንግሥት ተቋም አስቀድሞ ስምምነት የተደረሰበትን የአምስት ዓመት ጠቋሚ ጥቅል በጀት ይመደብለታል፤ ሆኖም ጥቅል በጀቱ በየዓመቱ እየተገመገመ የሚስተካከል ይሆናል፡፡
3. የመንግስት ተቋም የገንዘብ ፍላጐቱን ለማሟላት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 66 እና 67 በተገለጸው መሠረትና በሕግ ከተፈቀዱ ሌሎች ምንጮች ገቢዎችን ማሰባሰብ ይችላል፡፡
4. እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም በተቋሙ ቦርድ የጸደቀውን የሥራ ዕቅድ፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነትን እንዲሁም የተቋሙን ዝግጁነት እየታየ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ በጥቅል በጀት ሥርዓት መሥራት ይጀምራል።

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የጥቅል በጀት አሠራር ተጠቃሚ ለመሆንና አስተዳደሩንም በአግባቡ ለመምራት ይችሉ ዘንድ የመንግስት ተቋማት የትምህርትና የገንዘብ መረጃዎችን የሚያስተዳድሩበትን አቅም መገንባት ይኖርባቸዋል።
6. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ተቋማት የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፡፡
7. የመንግስት ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ስጦታዎችን መቀበል ይችላል፤ ሆኖም የሚያገኘው ስጦታ በተቋሙ አቋም፣ ተልዕኮና ዓላማ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማይኖረው መሆን ይኖርበታል።
8. ማንኛውም የመንግስት ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ሰለሚያገኘው ገንዘብና ከኢንቨስትመንት ስለሚያገኘው ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

63. <u>የድጎማ በጀት</u>

1. በማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም በአገልግሎት ላይ ያልዋለ የቀዳሚው ዓመት ጥቅል በጀት የተቋሙ ድጎማ በጀት ሆኖ ወደሚቀጥለው የበጀት ዓመት እንዲተላለፍና ለተቋሙ አገልግሎት እንዲውል ሊደረግ ይችላል፡፡
2. ተቋሙ የድጎማ በጀትን በካፒታል በጀት መልክ ብቻ ይጠቀምበታል፡፡
3. የድጎማ በጀት ከዓመቱ ጥቅል በጀትና ከተቋሙ ገቢ ከሚገኘው ገንዘብ ጋር እንደተቋሙ አጠቃላይ ዓመታዊ በጀት በቦርዱ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

64. <u>የገንዘብ አስተዳደር</u>

1. የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የተቋሙን የገንዘብ ጉዳይ በሕግ፣ በቅልጥፍና፣ በውጤታማነት፣ በቁጠባና በግልፅነት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነትና ተጠያቂነት ይኖርበታል።
2. ሕግ በሌላ ሁኔታ ያስቀመጣቸውን ሁኔታዎችና በጀትን አስቀድሞ በቦርድ የማፀደቅ አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ተቋም በጸደቀለት የሥራ ዕቅድ መሠረት ገቢውን በነፃነት የመጠቀም መብት ይኖረዋል።
3. በጀት ባልፀደቀበት ወቅት ቦርዱ በጀቱን እስኪያፀድቀው ድረስ የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የተቋሙ መደበኛ ስራ እንዳይስተጓጎል በቀዳሚው የበጀት ዘመን አሰራርና መጠን መሰረት ወጪ እንዲያደርግ በቦርዱ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

65. <u>የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነት</u>

1. የመንግሥት ተቋም ለአምስት ዓመት የሚቆይ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነት እንዳግባብነቱ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር ያደርጋል፡፡
2. የስትራተጂክ ዕቅዱ ስምምነት በተለይ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-
   - ሀ/ ስትራተጂክ ዓላማዎችን፣ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ የመማር-ማስተማር ውጤቶችንና ተቋማዊና የሰው ሃይል ልማትን፤
   - ለ/ የታቀዱ የምርምር ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን፤
   - ሐ/ የትምህርት ፕሮግራሞችን እና በተከታታይና በርቀት የሚሰጡ ፕሮግራሞችን፤
   - መ/ የተማሪዎችን ብዛትና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ብዛትና የሙያ ብቃት ደረጃን፤
   - ሠ/ የአካዳሚክ ሠራተኞቹን የብሔር ብሔረሰብ ተዋፅኦ ማመጣጠንን እና በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ ማሳደግን፣ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች የሚደረገውን እገዛ ማጠናከርን የሚመለከቱ እርምጃዎችን፤
   - ረ/ ከመንግሥት የሚጠበቀውን ጠቋሚ የጥቅል በጀትና ሊከሠት የሚችለውን የገንዘብ ክፍተት ከሌሎች ምንጮች ለማሟላት በተቋሙ የተገባውን ግዴታ፤
   - ሰ/ ጠቋሚ ጥቅል በጀቱና ተቋሙ ራሱ አሟላለሁ ያለውን ገንዝብ ለእያንዳንዱ የስትራተጂክ ዕቅዱ ዘመን መመደቡን የሚያሳይ ጠቋሚ ክፍፍል፤
   - ሸ/ የስትራተጂክ ዕቅዱ በጀት በቂ ሳይሆን ቢቀር የተቀመጠውን መፍትሄ፤
   - ቀ/ ተገቢ የሒሳብ፣ የክትትል፣ የግምገማና ሪፖርትን የማቅረብ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን፡፡
3. ስትራቴጂክ ዕቅዱ የተመሠረተባቸው ታሳቢዎች ከተለወጡ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡
4. የመንግሥት ተቋማት ቀጣዩን ረቂቅ የስትራቲጂክ ዕቅድ ስምምነታቸውን በወቅቱ የስተራቴጂክ ዕቅድ ዘመን ውስጥ እንደአግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ያፀድቃሉ፡፡

66. <u>ገቢን ስለማስገኘት</u>

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግሥት ተቋም በተቋሙ ፕሬዚዳንት ጥያቄና በቦርዱ ውሳኔ የገቢ ማስገኛ ድርጅትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡
2. ድርጅቱ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ሕጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የሚሠራ ይሆናል፡፡
3. ድርጅቱን ለማቋቋም የሚያስፈልገው የመነሻ ገንዘብ በመንግስት የሚመደብ በጀት ሊሆን ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ሊኖሩት ይችላል፦

   ሀ/ ድርጅቱ ከሚሠጠው አገልግሎት ወይም ከሚያከናውነው ሥራ የሚገኝ ገቢ፤

   ለ/ የተቋሙ ሠራተኞች በፈቃደኝነት ከሚያደርጉት መዋጮ፤

   ሐ/ ለድርጅቱ ከሚሰጡ ሥጦታዎች፤

   መ/ ከሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች፡፡
5. ተቋሙ የድርጅቱን የተጣራ ትርፍ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ለተልዕኮው መሳካት ሊጠቀምበት ይገባል፡፡
6. የድርጅቱ የፋይናንስ መግለጫዎች የበጀት አመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ለቦርዱ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

67. <u>የገቢ ፈንድ</u>

1. በመንግስት ተቋም ውስጥ በቦርድ ተወስኖ እንደ አግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ሲፀድቅ የገቢ ፈንድ ሊቋቋም ይችላል፡፡
2. የፈንዱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

   ሀ/ በተቋሙ የገቢ ማስገኛ ድርጅት የሚደረግለት መዋጮ፤

   ለ/ በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያልዋለ የፈንዱ ገንዘብ፤

   ሐ/ ሥጦታዎች፤

   መ/ ሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች፡፡
3. ፈንዱ ቦርዱ በሚያጸድቀው መሰረት ለተቋሙ ልዩ ልዩ የዓቅም ግንባታ ተግባራት፣ ለሽልማትና ሌሎች ተግባራት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡
4. የፈንዱ አጠቃቀም የበጀት ስርዓትን የተከተለ ይሆናል፡፡

68. <u>ሪፖርት ስለማቅረብና ስለቁጥጥር</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ተቋም:-

ሀ/ በስትራተጂክ ዕቅዱ ላይ የተመሠረተውንና በአግባቡ ተመዝኖ የፀደቀውን ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና በኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትን እንደአግባብነቱ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል ማቅረብና የበጀት ዓመቱ ትምህርታዊና ሌሎች መረጃዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 በተደነገገው መሠረት ማሳተም፤

ለ/ በማናቸውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል የሚጠየቀውን መረጃ መስጠት፣

ይኖርበታል።

2. ማንኛውም የመንግስት ተቋም እንደአግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ሕግንና የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነቱን ማክበሩን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ሊደረግበት ይችላል፡፡

3. እንደአግባብነቱ ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ከሕግ፣ ከመንግስት ፖሊሲ፣ ከተቋሙ ተልዕኮ ወይም ደንቦች ጋር የሚጋጩ የቦርድ፣ የፕሬዚዳንት ወይም የሴኔት ውሳኔዎችን ሊሽር ይችላል፡፡

## 69. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. የመንግሥት ተቋም በፕሬዚዳንቱ ኃላፊነትና አስተዳደር ሥር የሚመራ የተቋሙ ግዴታዎችንም ታሳቢ ያደረገ የገቢና የወጪ ሒሳብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓትን መዘርጋት ይኖርበታል።

2. የመንግስት ተቋም የደብል ኤንትሪ ሂሳብ አያያዝን የመከተል፣ ተቀጽላ የሆኑ ተግባራት ገቢና ወጪዎችን ከሌሎች ገቢዎችና ወጪዎች ለይቶ የመያዝ እና ለሁሉም የገቢና ወጪ ጉዳዮች የሒሳብ አያያዝ አጠቃላይ ሥርዓትን የመከተል ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

3. ሚኒስቴሩ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመማከር የአንድ የመንግስት ተቋም ሀብትንና ዕዳን ለመለካት ቀለል ያለ የመመዘኛና የኦዲት ሥርዓት ለመጠቀም የሚያስችል የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

## 70. <u>ኦዲት</u>

1. በማንኛውም የመንግሥት ተቋም ውስጥ ራሱን የቻለና ለፕሬዚዳንቱ ተጠሪ የሆነ የውስጥ ኦዲት ይቋቋማል፡፡
2. የመንግሥት ተቋም የውስጥ ኦዲት ክፍል ኃላፊ በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በቦርድ ይሾማል፡፡
3. የውስጥ ኦዲት የተቋሙን የአፈፃፀም፣ የፋይናንስና ንብረት ኦዲት አከናውኖ ውጤቱን ለፕሬዚዳንቱና ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
4. እንደአግባብነቱ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም የክልሉ ዋና ኦዲተር ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ተቋም ሂሳብ በቦርዱ በተሰየመ የውጭ ኦዲተር በየአመቱ ተመርምሮ ውጤቱ ለፕሬዚዳንቱ፣ ለቦርዱና እንደአግባብነቱ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለግል ተቋማት

### 71. ተጠያቂነት

1. የግል ተቋም በሚቋቋምበት የመመሥረቻ ሰነድ እና በመተዳደሪያ ደንቡ በተደነገገው መሠረት አግባብነት ላለው አካል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የግል ተቋም በትምህርት አሰጣጥና ምርምር ረገድ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ትክክለኛነት ተጠያቂነቱ ለሚኒስቴሩ ጭምር ይሆናል፡፡

### 72. ስለግል ተቋማት ሃላፊነት

1. ማንኛውም የግል ተቋም የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡-
   ሀ/ በሚኒስቴሩ የሚወጡ የተማሪዎች ቅበላን የሚመለከቱ መመሪያዎችን በጥብቅ የመከተል፤
   ለ/ ትምህርታዊ ይዘትን፣ የማስተማር ዘዴን፣ የተማሪዎች መመዘኛና የፈተናዎች ሥርአትን እና የውጤት ሥርአትን ጨምሮ ቢያንስ ለደረጃው የሚጠበቅበትን አነስተኛው የስርዓተ ትምህርት የጥራት ደረጃዎች የማረጋገጥ፤
   ሐ/ የአካዳሚክና የምርምር ክንውኖቹን አስመልክቶ ዓመታዊ ግለ-ግምገማና የተማሪዎችና የአካዳሚክ ሰራተኞች ግምገማ የማካሄድና ውጤቱን ለተቋሙ ማሕበረሰብ የማሳወቅና ለኤጀንሲውም ሪፖርት የማድረግ፤
   መ/ ከትምህርት ፕሮግራሞቹ መካከል በዲግሪ ለማስተማር ፈቃድ ባገኘባቸው

የትምህርት መስኮች የሚከተለው ስርዓተ ትምህርትን፣ የቅበላ ዓቅምንና ትምህርቱን ለማጠናቀቅ የሚወስደውን መደበኛ ጊዜ በማካተት እውቅና የተሰጣቸው የትምህርት ፕሮግራሞችን ዝርዝር እና የአካዳሚክ ሰራተኞቹን ደረጃና የቅጥር ሁኔታቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን በቀላሉ ተደራሽ በሆነ መልኩ የመያዝና እነዚሁኑ አስመልክቶ ለተማሪዎቹና ለኀብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፤

ሠ/ በአመራርና በአስተዳደር አደረጃጀቱ፣ አሰራሩ፣ በአመራሩና በአስተዳደሩ ሃላፊዎች ብቃት፣ ተቋሙ የሚገኝበት አካባቢ፣ የትምህርት መገልገያዎችን ጨምሮ የካምፓሱ አጠቃላይ አካባቢያዊ ሁኔታ ተቋሙ ለተሰጠው ደረጃና ለሚያካሂዳቸው ስልጠናዎች፣ ላለው የተማሪዎችና የሰራተኞች ብዛትና ለተሰማራበት የትምህርት መስክ የሚመጥን መሆኑን የማረጋገጥ፤

ረ/ የአምስት ዓመት ዝርዝር የትምህርት፣ የምርምርና የሥልጠና እቅድን እንዲሁም በእቅዱ ላይ በየዓመቱ የተደረጉ ማስተካከያዎችን ለኤጀንሲው የማቅረብና እቅዱን ይፋ የማድረግ፤

ሰ/ የትምህርት፣ የምርምርና የሥልጠና ተግባራቱን በተመለከተ ዝርዝር አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት በትምህርት ዓመቱ ማለቂያ ላይ ለኤጀንሲው ማቅረብና የትምህርት ግብአቶቹንና ውጤቶችን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የማሳተም፤

ሸ/ ሚኒስቴሩ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች ያለ ምንም ክፍያ ሚኒስቴሩ በሚፈልግበት አይነትና በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማቅረብ፤

ቀ/ የመክሰር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጥያቄ ከቀረበበት ይህንኑ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

በ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ተግባሩን የማከናወን፡፡

2. የግል ተቋም አመታዊ የአፈዓዐም ሪፖርት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ/ በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን፤

ለ/ የተቋሙን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ውጤት፤

ሐ/ በትምህርት ዘመኑ በተቋሙ ውስጥ የተከሰቱ ሁኔታዎችን፤

መ/ የትምህርቱን ዘመን ማብቃት ተከትሎ በተቋሙ የበላይ የአስተዳደር አካል የተፈረመበት ተቋሙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋምነቱ ያለበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ የግምገማ መግለጫ።

3. አመታዊ የትግበራ ሪፖርት፣ የተቋሙ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እና የትግበራው የግምገማ ውጤት ይፋ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

4. ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ሌሎች ድንጋጌዎችና በመደበኛ የአካዳሚክ ኦዲት አፈፃፀም ሳይገደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም የግል ተቋም ላይ ድንገተኛ የአካዳሚክ ኦዲት ወይም ማጣራት በማድረግ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## 73. <u>የግል ተቋም የውስጥ ደንብ</u>

1. የግል ተቋም የውስጥ ደንብ ስለተቋሙ የአስተዳደር አካላት፣ የተቋሙ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ አሰጣጥ ሥነሥርአት፣ የአካዳሚክና ምርምር ጉዳዮች፣ የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን መብትና ግዴታ እና ስለቅሬታ አፈታት ሥርአት መደንገግ ይኖርበታል ፡፡

2. የግል ተቋም የውስጥ ደንብ የዚህን አዋጅ ወይም የማንኛውንም አግባብነት ያለው ሌላ ሕግ ድንጋጌዎች የማይቃረን መሆን ይኖርበታል፡፡

3. ኤጀንሲው የግል ተቋማት ተገቢው የውስጥ ደንብ ያላቸው ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡

## 74. <u>የእውቅና ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ</u>

1. የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚኒስቴሩ እውቅናን ማግኘት ይኖርበታል።

2. ማንኛውም የግል ተቋም ዲግሪ ለመስጠት የሚችለው በሚኒስቴሩ እውቅና ሲሰጠውና እውቅና ባገኘበት የትምህርት ፕሮግራሞች፣ የትምህርት ዓይነትና በተፈቀደለት የተማሪዎች ብዛት ብቻ ይሆናል፡፡

## 75. <u>የእውቅና ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የእውቅና ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻን ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የተቋሙን ስምና ዋና አድራሻ፣

ለ/ የተቋሙን የፋይናንስ አቅም፤

ሐ/ ስለተቋሙ ተጠያቂ የሆነ አካልን ስምና አድራሻ፤

መ/ የተቋሙን ባለቤቶች ስምና አድራሻ፤

ሠ/ የተቋሙን ራዕይ፣ ተልእኮና ዓላማ፤

ረ/ የትምህርት ፕሮግራሞችንና የትምህርት ደረጃዎችን፤

ሰ/ ደረጃውን የጠበቀ ስርዓተ ትምህርት፣ የተቀጠሩና የሚቀጠሩበትን ጊዜ በመለየት በቅርቡ የሚቀጠሩ የአካዳሚክ ሠራተኞች በሙያ ዓይነትና በትምህርትና በማዕረግ ደረጃ እና የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቁጥርና የትምህርት ደረጃ፤

ሸ/ ተቋሙ ያለውና በቅርቡ የሚኖረው ለትምህርትና ለስልጠና የሚያስፈልጉ እንደ መፃሀፍት፣ ቤተመፃሕፍት፣ ቤተሙከራ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የትምህርትና የምርምር መገልገያዎች ዝርዝር፤

ቀ/ የአዲስ ተማሪዎች ቅበላ መመዘኛ፤

በ/ የተቋሙን ደረጃ፣ የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን መብትና ግዴታ እና የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርአትን የያዘ የውስጥ ደንብ፤

ተ/ የተቋሙ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ስራዎች የሚከናወኑበት የአመራርና የአስተዳደር ሥርአት፤

ቸ/ የተቋሙን የአምስት አመት እቅድ፤

ኀ/ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት የተሰጡ የኢንቨስመንትና ሌሎች አስፈላጊ ፈቃዶችን፡፡

3. ኤጀንሲው የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች ተቋሙ ማሟላቱን ሲያረጋግጥ የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል፤

ለ/ ተቋሙ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች የማያሟላ ሆኖ ሲያገኘው የእውቅና

ፈቃድ ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፡፡

4. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ) መሰረት የእውቅና ፈቃድ ጥያቄን ውድቅ ሲያደርግ ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘባቸውን ምክንያቶች ለአመልካቹ በፅሁፍ መግለፅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ የተከለከለ አመልካች የፈቃድ ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት እንደገና ለማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የእውቅና ፈቃድ በድጋሚ የተከለከለ አመልካች ዳግም ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ሊያመለከት ይችላል፡፡
6. ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ክልከላ ውሳኔውን እንደ ክልከላው ሁኔታ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል።

## 76. የእውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

1. ኤጀንሲው የቀረበለትን የእውቅና ፈቃድ ማመልከቻ መርምሮ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱት መመዘኛዎችን ተቋሙ ማሟላቱን አረጋግጦ በተገቢ ጊዜ ውስጥ የእውቅና ፈቃዱን ይሰጣል፡፡
2. በኤጀንሲው የሚሰጠው የእውቅና ፈቃድ፡-

   ሀ/ የተቋሙን ስምና አድራሻን፤

   ለ/ የተቋሙን ደረጃ፣ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን፤

   ሐ/ የመምህራኑ ብዛትና የትምህርት ደረጃ ስብጥርን፤

   መ/ የተማሪዎች ብዛትና ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታን፤

   ሠ/ የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠበትን ቀንና የሚያገለግልበትን የጊዜ ገደብን፤

   ረ/ የእውቅና ፈቃዱን የሰጠውን ሃላፊ ስምና ፊርማ እና የኤጀንሲውን ማህተም፤

   መያዝ ይኖርበታል።
3. ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ መሰጠቱን አስመልክቶ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## 77. የእውቅና ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 76 መሠረት ለግል ተቋም የተሰጠ የመጀመሪያው የእውቅና ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለ3 ዓመታት ያገለግላል፡፡

2. ለግል ተቋም የተሰጠ የእውቅና ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃና በቀጣይም በየአምስት ዓመቱ አዲስ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት መታደስ ይኖርበታል።

## 78. የእውቅና ፈቃድን ለማሳደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እንዲታደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጥ ወይም ቀደም ሲል እንዲታደስ ሲጠየቅ ለኤጀንሲው ከቀረበው ማመልከቻ ጋር ቀርበው የነበሩትን መረጃዎችና የትምህርት ግብአቶችና መገልገያዎች አሁን ያሉበትን ደረጃ የሚገልፅ ሪፖርትን፤
2. በተቋሙ የጥራት ማጎልበት ስርዓት የተካሄደ የግለ-ግምገማ ውጤት ሪፖርትን፤
3. የተቋሙ የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የድጋፍ ሰጪ ቋሚ ሠራተኞች ዝርዝርን፤
4. በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝርን፤
5. ለትምህርትና ለምርምር እንዲሁም ከትምህርት ጋር ተዛማጅነት ላላቸው ሌሎች ተግባራት ማከናወኛ የተዘጋጁ መገልገያዎችንና የትምህርት መረጃዎች ዝርዝርን፤
6. በኦዲተር የተመረመሩ የመጨረሻዎቹን ሦስት ዓመታት የተቋሙ የሂሳብ ሪፖርቶችን፤
7. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በኤጀንሲው የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን፡፡

## 79. የእውቅና ፈቃድ ለማደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ ውሳኔ አሰጣጥ

1. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 78 መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲቀርብለት በገምጋሚ ኮሚቴው አማካይነት፡-

ሀ/ በተቋሙ የቀረበውን ግለ-ግምገማ፣ ሰነድና ሌሎች ሪፖርቶችን ይመረምራል፤ በነዚሁ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችንና ስታትስቲካዊ መግለጫዎችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤

ለ/ በተቋሙ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን ባገናዘበ መልክ፡-

1) የተቋሙን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ መሠረተ ልማቶች፤
2) ሥርአተ ትምህርትን፣ የመማር ማስተማር ጥራትን፣ የተማሪዎች መረጃዎችን፣ የትምህርት መገልገያዎችን፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ

ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና የመምህራኑ ብቃትን ጨምሮ የተማሪዎች የትምህርቱ ጥራት ግምገማን፤

3) የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ዝርዝርና የትምህርት ደረጃን፤

4) የምርምር ስራዎቹን መጠንና አግባብነት፤

በጥልቀት ይገመግማል፤

2. ኤጀንሲው በገምጋሚ ኮሚቴው ሪፖርት መሠረት፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች በተቋሙ መሟላታቸውን ካረጋገጠ የእውቅና ፈቃዱ እንዲታደስለት ያደርጋል፤ ወይም

ለ/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች በተቋሙ አለመሟላታቸውን ካረጋገጠ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፡፡

3. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን ከወሰነ ተቋሙ ያለበትን ደረጃ መሆን ከሚገባው ደረጃ ጋር በማነፃፀር ከሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ ጋር በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች አመልካቹን በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/(ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም በኤጀንሲው የተገለፁትን የማስተካከያ እርምጃዎች በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በመውሰድ ተፈላጊ መመዘኛዎችን አሟልቶ እንደገና ማመልከት ይችላል፡፡

5. ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄውን ውድቅ ያደረገበትን የመጨረሻ ውሳኔ በተገቢው ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል።

6. የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ተማሪዎችና ሰልጣኞች ቢኖሩ አግባብ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ተዛውረው ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

## 80. <u>የእውቅና ፈቃድ እድሳት</u>

1. የታደሰው እውቅና ፈቃድ፡-

ሀ/ የተቋሙን ስምና አድራሻን፤

ለ/ የተቋሙን ደረጃ፣ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን፤

ሐ/ የመምህራኑ ብዛትና የትምህርት ደረጃ ስብጥርን፤

መ/ የተማሪዎች ብዛትና ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታን፤

ሠ/ የእውቅና ፈቃዱ የታደሰበት ቀንና የሚያገለግልበተ የጊዜ ገደብን፤

ረ/ የእውቅና ፈቃዱን ያደሰውን ሃላፊ ስምና ፊርማ እና የኢጀንሲው ማህተም፤ መያዝ አለበት፡፡

2. ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ መታደሱን አስመልክቶ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል።

## 81. የእውቅና ፈቃድን ስለመሰረዝ

1. ኤጀንሲው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የግል ተቋም የእውቅና ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፡-

   ሀ/ የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ሲረጋገጥ፤

   ለ/ ተቋሙ የሚፈለግበትን ደረጃ ባለመጠበቁ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም የሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጐች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ጥሶ በመገኘቱ በኤጀንሲው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በማስጠንቀቂያው በተገለፀው የጊዜ ገደብ ጉድለቶችን ሳያስተካክል ሲቀር፤

   ሐ/ ተቋሙ ሲፈርስ ወይም ሥራውን ሲያቆም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የሚወሰነው የእውቅና ፈቃድ ስረዛ አዲስ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. የዕውቅና ፈቃዱ የተሠረዘ የግል ተቋም ተማሪዎቹና ሰልጣኞቹ ትምህርታቸውን አግባብነት ባላቸው ሌሎች ተቋማት እንዲፈፅሙ ማድረግ ይኖርበታል።

## 82. አቤቱታ ስለማቅረብ

1. በኤጀንሲው ውሳኔ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም የእውቅና ፈቃድ እንዲታደስለት ያቀረበው ማመልከቻን ውድቅ የተደረገበት ወይም የዕውቅና ፈቃዱ የተሠረዘበት ማንኛውም ተቋም ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ለሚኒስቴሩ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ሚኒስቴሩ አቤቱታውን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የይግባኝ መርማሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

3. ሚኒስቴሩ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አመልካቹ ቀርቦ እንዲሰማ ማድረግ ይኖርበታል።

83. <u>ምትክ የእውቅና ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. የእውቅና ፈቃድ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ማንኛውም የግል ተቋም ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ለኤጀንሲው ለማመልከት ይችላል፡፡

2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት፡-

ሀ/ አመልካቹ የተበላሸውን የዕውቅና ፈቃድ እንዲመልስ፤

ለ/ የዕውቅና ፈቃዱ የጠፋ ከሆነ ስለመጥፋቱ ሕጋዊ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ፣ ካደረገ በኋላ ምትክ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

84. <u>የእውቅና ፈቃድ ስለመመለስ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የእውቅና ፈቃድ የተሰረዘበት ተቋም ፈቃዱ በተሰረዘ በ15 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለኤጀንሲው መመለስ አለበት፡፡

2. አንድ ተቋም ደረጃውን የለወጠ፣ ከሌላ ጋር የተዋሃደ፣ የተከፈለ ወይም ስሙን የለወጠ ከሆነ በዚሁ መሠረት ተገቢውን አዲስ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው የቀድሞውን ፈቃድ ለኤጀንሲው መመለስ ይኖርበታል።

85. <u>ስለ እውቅና ፈቃድ ክፍያ</u>

የእውቅና ፈቃድ ክፍያ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

86. <u>ስለ መንግሥት ድጎማ</u>

1. መንግስት ብቁ የሰው ሃይልን በማፍራት የአገሪቱ የልማት ፍላጎት የሚጠይቀው የማስፈፀም ዓቅም ግንባታን ለማጠናከር የሚሰሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማትን ለማበረታታት የበጀት ድጎማ ወይም የዓቅም ግንባታ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ሚኒስቴሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት፡-

ሀ/ በቅደመ-ምረቃና ድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች በተቋማቱ ውስጥ ተመዝግበው የሚማሩትን መደበኛ ተማሪዎችና ከእነርሱም መካከል በነፃ የሚማሩትን ተማሪዎች ብዛት፤

ለ/ ተቋማቱ የቋሚ ቅጥር ዕድል ያሰገኙላቸውን የአካዳሚክ ሠራተኞች ብዛት፤ ሐ/ የተቋማቱን የትምህርት ጥራት፤

መ/ ተቋማቱ በትምህርትና ምርምር ረገድ ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች፤ እና

ሠ/ ተቋማቱ ራሳቸው አገልግሎቶቻቸውን ለማስፋፋት ያፈሰሱትን ሀብት፤ በማገናዘብ ከመንግስት የበጀት ድጎማ ወይም የዓቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ሊያመለክቱ ስለሚችሉበትና አጠቃቀሙን ስለሚከታተልበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል።

3. ለትርፍ ያልተቋቋመ የግል ተቋማት፡-

ሀ/ በተወሰነ መስክ ወይም ተወራራሽ በሆኑ መስኮች ለሚሰጧቸው የዲግሪ ፕሮግራሞችና ጥናቶች ድጋፍ እንዲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚያካሂዷቸው የዲግሪ ፕሮግራሞች የላቀ ጥራት ያሏቸው ስለመሆናቸው በኤጀንሲው ተረጋግጦ እንዲበረታቱ ለማድረግ፤

አስቀድሞ ለዚሁ ዓላማ ከተያዘው የመንግስት ገንዘብ ላይ ተጨማሪ ድጎማ ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

87. <u>የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት</u>

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለመንግሥት ተቋማት ስለሚሰጥ የዕውቅና ፈቃድም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር</u>

88. <u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከፍተኛ ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ዝግጅትና አተገባበር ከአለም አቀፍ እድገት እና ከአገራዊ ፍላጐትና መመዘኛዎች ጋር የሚመጣጠን መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. በባችለር፣ በማስትሬት፣ በህክምና ስፔሻሊቲ እና በዶክትሬት ፕሮግራሞች ትምህርት ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ መመዘኛዎችን ይወስናል፤
3. የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤
4. በዚህ አዋጅ፣ በመንግስት ፖሊሲና እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚያወጣቸው መሥፈርቶች መሠረት በመንግስታዊ ተቋማት ደረጃና በመንግስታዊ ተቋማት

ውስጥ የሚደረጉት የተማሪዎች ምደባ እና የተማሪዎች ቅበላ ስርዓቱ ባጠቃላይ ፍትሃዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

5. ሃገራዊ አነስተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን፣ የሙያ ስነምግባር ደንቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሰራር ሥነሥርአትን ያወጣል፤
6. መንግስት ለመንግስት ተቋማት ጥቅል በጀት የሚመድብበትን መሥፈርትና ሥርአት ይወስናል፤
7. በተቋማት መካከል ትብብርና የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
8. ለተቋማት የውስጥ የጥራት ማጎልበቻ ሥርአት ድጋፍ ይሰጣል፤
9. የመንግስት ተቋም ስትራቴጂክ እቅድን ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤
10. የአገሪቱ የከፍተኛ ባለሙያ የሰው ሃይል ፍላጎትን ለመለየትና ይህንኑ ለማሟላት ጥናት ያካሂዳል፤
11. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርት መስክ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፤
12. የመንግስት አካላት፣ የሙያ ማሕበራት፣ የንግድ ማሕበራት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰዎች በትምህርት፣ በስልጠና፣ በተግባር ልምምድ፣ በምርምር እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳዮች ላይ ከተቋማት ጋር በጋራ ወይም በትብብር እንዲሰሩ ያበረታታል፤
13. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ያረጋግጣል፡፡

89. <u>የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በግልጽ የሠፈሩ የግምገማና የእውቅና አሰጣጥ መመዘኛዎችንና ሥርአትን በማዘጋጀት በስራ ላይ ያውላል፤
2. በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተቋምን ወይም የተቋምን ክፍሎች ለመክፈት ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ ፕሮጀክትን በመገምገም ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

3. የእውቅና ፈቃድ ወይም እድሳት ለመስጠት የሚያስችል የተቋም ብቃትና የትምህርትና የስልጠና አግባብነትና ጥራት ግምገማን ያካሂዳል፤
4. የተቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ስለመቻሉ ግምገማ ያካሂዳል፤
5. በማንኛውም ተቋም የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፤
6. የግምገማ ኮሚቴዎችን ያደራጃል፤ ሃላፊነታቸውና አሰራራቸውን ይወስናል፤ ስራቸውን ሲያከናውኑ የሚከተሉትን የስነምግባር መመሪያም ያወጣል፤
7. በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለእውቅና ፈቃድና ለእውቅና ፈቃድ እድሳት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይመረምራል፤ይወስናል፤
8. የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለመገምገም ወይም የእውቅና ፈቃድ ወይም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄዎችን ለመመርመር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አግባብነት ካላቸው አካላት መረጃና አስተያየት ይጠይቃል፤
9. በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡትን የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎች መከተላቸውን ለማረጋገጥ ተቋማትን በመገምገም የሚደረሰባቸውን የግምገማ ግኝቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
10. የተቋማትን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችሉ መመዘኛዎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
11. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተቋማትን መዋሃድ፣ መከፈል፣ መዘጋት ወይም የስም ለውጥ አስመልክቶ ለሚኒስቴሩ ምክር ይሰጣል፤
12. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተቋማት ወይም የነሱ ቅርንጫፎች በተቋቋሙባቸው አገሮች እውቅና ያገኙ መሆናቸውንና በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

13. በውጭ ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችና የነዚህኑ ተቋማት ደረጃና አቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤
14. የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃዎች የአቻነት መወሰኛ ሥርአት ያዘጋጃል፣ በውጭ አገር ተቋማት የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎችን የአቻ ግምት ይሰጣል፤
15. እውቅና ያገኙ ተቋማትንና ደረጃቸውን፣ ዋና ዋና ክፍሎቻቸውንና የትኩረት መስኮቻቸውን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ይይዛል፣ አግባብነት ባላቸው የመገናኛ ዘዴዎች መረጃዎቹን በየጊዜው ለሕዝብ ያሰራጫል።

90. <u>የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከፍተኛ ትምህርትንና የተቋማትን እድገት አስመልክቶ አገር አቀፍ ስትራቴጂ ያዘጋጃል ፤
2. በከፍተኛ ትምህርት ሥርአት ውስጥ ትምህርትና ምርምር ስለሚያድጉበት ሁ ኔታ የረጅም ጊዜ አገር አቀፍ እቅድ ያዘጋጃል፤
3. የተቋማትን የትምህርትና ምርምር ጥራትን፣ የአካዳሚክ ሰራተኞችን ብቃት እንዲሁም የትምህርት ፕሮግራሞችን ለማሳደግ የሚያግዙ አገር አቀፍ የመነሻ ሃሳቦችንያቀርባል፤
4. በተቋም ደረጃ የሚወጣ እቅድና ስትራቴጂ በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚወጣ አጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት እቅድና ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለዚህም ከተቋማት ጋር በቅርበት ይሠራል፤ የስትራቴጂክ እቅድ ስምምነት ይመረምራል፤ ሲፀድቅም አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
5. ለእያንዳንዱ የመንግስት ተቋም ስለሚሰጥ የጥቅል በጀት ምደባ ሃሳብን ያመነጫል፤ የጥቅል በጀት ምደባ አፈፃፀምን ይከታተላል፤
6. የተቋማትን ዓመታዊ የትምህርት፣ የምርምር፣ የፋይናንስና ሌሎች ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበሰባል፣ ይተነትናል፤ እንደተገቢነቱም አትሞ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፤
7. ተቋማት የተለያየ መጠን ባለው የልማት በጀት መልክ የማበረታቻ ሽልማት ስለሚያገኙበት መመዘኛና አሰራር ለሚኒስቴሩ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በስራ ላይ ያውላል፤

8. የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑንና በአካሄዱ ከአለም አቀፉ እውነታ ጋር እኩል የሚራመድ መሆኑን ያረጋግጣል፤

9. ቀልጣፋ የከፍተኛ ትምህርት አስተዳደር፣ አመራርና ማኔጅመንት እንዲኖር ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤

10. በወቅታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች፣ አሰራርና ውጤቶች ላይ ምርምርና ጥናት በማድረግ ትክክለኛ የአሠራር አቅጣጫዎችን ይጠቁማል፤ ለማሻሻያ፣ ለለውጥና ለልማት የእውቀት ግብአት ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

11. በአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ማሻሻያና ልማት ስትራቴጂና እቅድ ላይ ሃሳብ ይሰጣል፤

12. በሃላፊነቱ ማዕከልነት በአገራዊ ተቋማት መካከል ትብብርን ያጎለብታል፤ የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮችን ከሚያከናውኑ ተመሳሳይ የውጭ አገር አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፤

13. በማቋቋሚያ ሕጉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 91. የአገልግሎት ክፍያዎች

1. የመንግስት ተቋም ለትምህርት አገልግሎቶች ክፍያ መጠየቅ ይችላል፤ የሚጠይቀው ክፍያ ዓይነት፣ መጠንና የክፍያ አፈፃፀም አግባብ የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ በሚወጣው መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. የግል ተቋም ክፍያ የሚያስከፍልበት የውስጥ ደንብ የሚወሰነው በተቋሙ የመመስረቻ ሰነድ ውስጥ ሥልጣን በተሠጠው አካል ይሆናል፡፡

### 92. ወጪ ስለመጋራት

1. የማንኛውም በመንግሥት ተቋም ተማሪ የሆነና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 91 መሠረት ለትምህርቱ የማይከፍል ኢትዮጵያዊ የትምህርቱን ወጪ በገንዘብ ወይም በአገልግሎት እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ሥርዓት እና ሥርዓቱ በየጊዜው የሚከለስበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይፈጸማል፡፡

93. <u>አገልግሎት በሌሎች ወገኖች እንዲሰጥ ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ተገቢና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ሆኖ ሲያገኘው የድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሰጥ ሊያደረግ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የመንግሥት ተቋም አገልግሎት በሌሎች አቅራቢዎች እንዲሰጥ ሲያደርግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ለዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

94. <u>የመሬት አቅርቦት</u>

መንግስት አግባብነት ባላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች መሠረት ተቋማት ለትምህርት፣ ለምርምርና ለሕብረተሰብ አገልግሎት ተግባራት ማከናወኛ የሚያስፈልጋቸውን መሬት ሊሰጥ ይችላል፡፡

95. <u>ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎችን ተላልፎ ከተገኘ በሕግ መሠረት የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሃላፊነት ይኖርበታል።
2. እውቅና ያለው የትምህርት ማስረጃ ሳይሰጠው እንደተሰጠው አስመስሎ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ወይም ዕውቅና ላልተሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ማስረጃ የሰጠ ወይም የሃሰት የትምህርት ማስረጃ የሰጠ ማንኛውም ሰው በሕግ መሠረት የፍትሐብሄርና የወንጀል ኃላፊነት ይኖርበታል።

96. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. በአዋጅ ቁጥር 351/1995 መሠረት የተሰጡ የቅድመ እውቅናና የእውቅና ፈቃዶች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጡ ተደርገው ይቆጠራሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ የግል ተቋማት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ ለማሟላት የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው።

3. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት መታየት የጀመሩና ያላለቁ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናሉ፡፡

**97. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**98. የተሻሩ ሕጎች**

1. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤ ሆኖም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ እስከሆነ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም የአሰራር ልምዶች በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**99. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 7 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 210/2003 ዓ.ም

## የፌደራል ዩንቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 97(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌደራል ዩንቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀፅ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   3. "ፌደራል ዩንቨርስቲ" ማለት በአዋጁ አንቀፅ 5(1) እና አንቀጽ 9(1) መሰረት የተቋቋመ ዩንቨርሲቲ ነው፤
   4. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል።

3. **የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ዓላማ**

   የአዋጁ አንቀጽ 4 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

   1. ዕውቀትን የማፈላለግ፣ የማበልጸግ፣ የማቀብና የማስተላለፍ፤
   2. በተለያዩ መስኮች የቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞችን የመስጠት፤
   3. ለቴክኖሎጂ ሽግግር ቅድሚያ በመስጠት ምርምርና ጥናቶችን ማከናወንና ውጤቱን የማስረጽ፤
   4. የሕብረተሰብና ሌሎች የማማከር አገልግሎቶችን እንደሁኔታው በነፃ ወይም በክፍያ የመስጠት፡፡

4. **የፌደራል ዩኒቨርሲቲ ኃላፊነት**

   የአዋጁ አንቀጽ 8 እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የትምህርት ክፍሎችን የማቋቋም፣ የማደራጀትና ደረጃቸውን ፣ ተግባራቸውንና ኃላፊነታቸውን የመወሰን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመዝጋት፣
2. በአገሪቱ ፍላጎት መሠረት የቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ የትምህርት ፕሮግራሞችን እና አጫጭር ስልጠናዎችን የመቅረጽና የመስጠት፤
3. የምርምር ውጤቶችን የማሳተምና የማሰረጽ፤ በምርምር ውጤቶች ላይ ለመምከር የውይይት መድረኮችን የማዘጋጀትና የማካሄድ፤
4. የአካዳሚክ መጽሔቶችንና የአካዳሚክ ዜና ማሳወቂያን የማቋቋምና የማስተዳደር፤
5. የዩኒቨርሲቲውን መምህራን የትምህርት ደረጃ የማሳደግ እና የመምህርነት ሙያዊ ብቃታቸውን በቀጣይነት የመገንባት፤
6. የሌሎች መንግሥታዊና ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት የማስፈጸም አቅምን መገንባት ላይ አስተዋፆ የማድረግ፤
7. የምክር አገልግሎቶች ለመንግሥት፣ ለኢንዱስትሪዎችና ለህብረተሰቡ የመስጠት፤
8. ዘመናዊ የቤተመፃህፍት አገልግሎትን በማደራጀት ለተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ፤
9. በትምህርት አግባብነትና ጥራት ጉዳዮች ላይ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር፤
10. አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢ ክፍያን የማስከፈል፤
11. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

5. <u>የተቋም ነፃነትና ተጠያቂነት</u>

1. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በአዋጁ አንቀጽ 17 የተሰጠው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ተጠያቂነት ይኖረዋል፡፡
2. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮውን በሚገባ ስለማሳካቱ በተለይም የሚከተሉትን ስለማረጋገጡ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡-

ሀ/ የሚያካሂዳቸው የትምህርትና የምርምር ፕሮግራሞች አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የሚመሩ መሆናቸውን እና ተገቢውን የጥራት ደረጃዎች የጠበቁ መሆናቸውን፤

ለ/ የትምህርት፣ የስልጠናና የምርምር ፕሮግራሞቹ ትኩረት ለመንግሥት

ፕሮግራሞች ቅድሚያ የሚሰጡ ከሀገራዊ ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን፤

ሐ/ የመማር ማስተማርና የምርምር ሥራዎቹ እና አጠቃላይ አሠራሩ ተቋማዊ ሥርዓት ያላቸውና በመልካም አስተዳደር መርሆዎች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን፤

መ/ አስተማማኝ የገቢ ማመንጨት አቅም መገንባቱንና የበጀትና ሃብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢና ዓላማውንና ኃላፊነቱን በማሳካት ውጤታማ መሆኑን፤

ሠ/ የራሱን አፈጻጸም ባጠቃላይ እና የትምህርት ክፍሎቹንና የአካዳሚክ ሠራተኞቹን አፈጻጸም በተለይ አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ መልካም ልምዶች ላይ በተመሠረቱ መመዘኛዎች ወቅቱን ጠብቆ የሚለካና አፈጻጸሙን በቀጣይነት የሚያሻሽል መሆኑን፤

ረ/ የትምህርት ክፍሎችን አስተዳደራዊ ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር የሚያረጋግጥ አስተማማኝ ተቋማዊ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን፤ እንዲሁም የመላ ዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት የአስተዳደር ነፃነት የተሰጣቸው የአካዳሚክ ክፍሎችን አፈፃፀም ከዩኒቨርሲቲው ዓላማና ሃላፊነት ጋር ስለመጣጣማቸው በሚገባ የሚቆጣጠሩ መሆናቸውን፤

ሰ/ ተቋማዊ ነጻነቱንና የአካዳሚክ ነፃነቱን አግባብ ካልሆነ አጠቃቀም የሚከላከል መሆኑን፤

ሸ/ የጥራት ደረጃውንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት የሚያቀርብ መሆኑን ፡፡

## 6. <u>ስለዩኒቨርሲቲ ሴኔት</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 49 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ሴኔት የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሚያወጣቸውን የአካዳሚክ አጠቃላይ መመሪያዎችን ተግባራዊ የማድረግ፤

ለ/ የተማሪዎች የአካዳሚክና የዲስፕሊን ጉዳዮችን የሚመለከቱ መመሪያዎችን አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የማውጣት፤

ሐ/ የአካዳሚክ ሠራተኞች ጉዳዮች የሚመሩበት መመሪያዎችን አግባብነት

ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የማውጣት፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን የመገምገም፡፡

2. ሴኔቱ ኃላፊነቱን አግባብነት ላላቸው የዩኒቨርሲቲው አካላትና ለሚያቋቁማቸው ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴዎች በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

3. በአዋጁ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌዎች መሠረት ለዩኒቨርሲቲ ቦርድ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ሰኔት በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት፤

   ለ/ የዩኒቨርሲቲው የምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት፤

   ሐ/ የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት፤

   መ/ የዩኒቨርሲቲው የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ወይም የኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ (ትምህርት ቤት) ዲን፤

   ሠ/ የዩኒቨርሲቲው ዋና ሬጂስትራር፤

   ረ/ የዩኒቨርሲቲው የቤተመጻህፍት ኃላፊ፤

   ሰ/ በግል ብቃታቸውና በአካዳሚክ ማዕረጋቸው ቀዳሚነት ላይ ተመሥርቶ የሚመረጡ ከአስራ ሁለት እስከ ሃያ አምስት የሚደርሱ የአካዳሚክ ክፍሎች ኃላፊዎች እና/ወይም መምህራን፤

   ሸ/ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ማኅበር ሁለት ተወካዮች፤

   ቀ/ የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ማኅበር ሁለት ተወካዮች ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ሰ) የተመለከቱት የሴኔቱ አባላት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በሚወስነው አሠራር መሠረት በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ተመርጠው የሚመደቡ ይሆናሉ፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተራ ፊደል (ሰ) እስከ (ቀ) የተመለከቱት የሰኔት አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ እንደአግባብነቱ በድጋሚ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6. የሰኔት አባልነት በተቻለ መጠን ጾታዊ ስብጥርና መመጣጠን እንዲኖረው የሚደረግ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ሸ) እና (ቀ) የተመለከቱት አባላት እኩል የፆታን ተዋጽኦ መሠረት ያደረገ ይሆናል ፡፡

7. ያለ ድምጽ በቋሚነት የሚሳተፉ የሰኔት አባላት ጉዳይ በሰኔቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡

7. <u>ስለዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 52 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትነት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንትነት በዕጩነት የሚቀርብ ተወዳዳሪ፡-

   ሀ/ ኃላፊነቱን ለመቀበል ፈቃደኝነት ያለው፤ እና

   ለ/ በመልካም ሥነምግባሩ የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ እምነት የሚጥልበት፤ መሆን አለበት፡፡

2. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች የውድድርና ምርጫ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

   ሀ/ ተገቢው ሽፋን ያለውና በቂ ጊዜ የሚሰጥ የውድድር ማስታወቂያ ይወጣል፤

   ለ/ የመመዘኛ መሥፈርቱን የሚያሟሉ ቢያንስ ሦስት ዕጩዎችንና የተወዳዳሪዎችን ሙሉ ዝርዝር ያካተተ የውሳኔ ሃሳብ ለፕሬዚዳንትነት ሲሆን ለዚሁ ተግባር በዩኒቨርሲቲው ቦርድ በተሰየመ ኮሚቴ ወይም ለምክትል ፕሬዚዳንትነት ሲሆን በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በተሰየመ ኮሚቴ ለቦርዱ ይቀርባል፤

   ሐ/ ቦርዱ የሌሎች ሁለት ተፎካካሪ ዕጩዎች መረጃንም ጨምሮ ለፕሬዚዳንትነት ይበልጥ እንደሚመጥን ያመነበትን ዕጩ እንዲሾም ለሚኒስትሩ ያቀርባል ፡፡

3. ቦርዱ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች አፈጻጸም ዝርዝር መመሪያ ያወጣል ፡፡

4. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በአዋጁ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ዐ) መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተለይቶ ውክልና ሲሰጠው በዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሚወሰን ይሆናል ፡፡

8. <u>የፕሬዚዳንት ኃላፊነት</u>

የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በአዋጁ አንቀጽ 53 ከተደነገጉት በተጨማሪ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የዩኒቨርሲቲውን የአፈጻጸም ሪፖርቶች በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ጸድቀው ወይም ቦርዱ በሚሰጠው አመራር መሠረት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤

2. የዩኒቨርሲቲውን ቦርድ አጀንዳዎች የቦርዱን ሰብሳቢ በማማከር ያዘጋጃል፣ የቦርዱን ስብሰባዎች የሚያሳልጡ ቅድመ ዝግጅቶችን ያከናውናል፣ የቦርዱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤

3. በአዋጁ አንቀጽ 58 መሠረት የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ እንዲቋቋምና ተልዕኮውን እንዲወጣ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል።

9. <u>የምክትል ፕሬዚዳንት ኃላፊነት</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ማንኛውም የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ በዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት የተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በሥራ ላይ ለማዋል በሥሩ ያሉ ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ/ በሥሩ ያሉ ክፍሎች ዕቅዶች ዝግጅትን ይመራል፣ የዕቅዱን አፈጻጸም በበላይነት ይቆጣጠራል፤

ሐ/ በኃላፊነቱና ተግባሩ መሠረት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮችን ይመሰርታል ፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

መ/ በሥሩ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸምና በጀት አጠቃቀም በተመለከተ ለፕሬዚዳንቱ ሪፖርት ያቀርባል ፡፡

2. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንቶች የውጭ ጉዞ አስቀድሞ በዕቅድ የተያዘ ወይም በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በተለየ ሁኔታ የተፈቀደ ሆኖ የክንውን ሪፖርት የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

10. <u>ልዩ የተማሪ ቅበላ</u>

1. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በአዎጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌዎች መሠረት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዝግጅታቸው፣ በአጠቃላይ ዕውቀታቸውና በሥራው ዓለም ተሞክሮአቸው ለቅድመ ምረቃ ትምህርት ብቁ የሆኑ ጎልማሶችን በልዩ የቅበላ ሥርዓት በተፈቀዱ መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞቹ ሊቀበል ይችላል ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የጎልማሶች ልዩ የቅበላ ሥርዓትን መዘርጋት የሚቻለው የፍላጎት ጥናት በማድረግና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመፈተሽ አስፈላጊነቱንና ሊፈጸም የሚችል መሆኑን ዩኒቨርሲቲው ሲያረጋግጥ ይሆናል፡፡

3. የጎልማሶች ልዩ የቅበላ ሥርዓቱ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ውሳኔና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡
4. ለቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ጎልማሶች የሚመለመሉት የትምህርት መስኩ የሚጠይቀውን ብቃት የሚለካ የመግቢያ ፈተና በመስጠት ይሆናል፡፡
5. በዩኒቨርሲቲው ቦርድ በተወሰነ አሠራር መሠረት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ግለሰቦችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከክፍያ ነፃ ለማድረግ ካልወሰነ በስተቀር በልዩ የቅበላ ሥርዓት የሚስተናገዱ ጎልማሶች የመግቢያ ፈተናን እና የትምህርትን ወጪዎችና ሌሎች ክፍያዎችን በራሳቸው እንዲሸፍኑ ይደረጋል፡፡
6. በዋጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ የተወሰነላቸውን ተማሪዎች የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በዓቅሙ ልክ የመቀበልና ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርበታል።

11. **<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

1. ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በቦርዱ የጸደቀ የራሱ አርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡
3. የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ቦርድ በአዋጁ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ረ) የተሰጠውን ሥልጣን የፌዴራል ዋናው ኦዲተርን ምክር መሠረት አድርጎ ይፈጽማል፡፡

12. **<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 296/2005

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እውቅና፣ የአቻ ግምት፣ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 17(1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እውቅና፣ የአቻ ግምት፣ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 296/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 261/2004 የተቋቋመው የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው፤
   2. "የእውቅና ፈቃድ" ማለት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ለመጀመር በአዋጁ መሰረት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፤
   3. "የእውቅና እድሳት ፈቃድ" ማለት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና እንዲቀጥል ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የፈቃድ እድሳት ነው፤
   4. "አቻ ግምት" ማለት ከውጭ አገር ለተገኘ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃ ከአገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃ ጋር በማነጻጸር ደረጃ መስጠት ነው፤
   5. "የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ" ማለት እውቅና ከተሰጠው የአገር ውስጥ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘን በማናቸውም ሰው የቀረበን የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ ነው፤
   6. "ድንበር ዘለል ድህረ ምረቃ ትምህርት" ማለት በውጭ አገር የሚገኝ አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከአገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት አቅራቢ ጋር በመተባበርም ሆነ ያለትብብር ኢትዮጵያ ውስጥ በድህረ ምረቃ የሚሰጠው ከፍተኛ ትምህርት ነው፤

7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

8. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፤

9. በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

10. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

## 3. <u>ስለ አገልግሎት ክፍያ</u>

1. ለእውቅና ፈቃድ የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ በተመለከተው ተመን መሠረት ይፈፀማል፡፡
2. ለእቻ ግምት የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሁለት በተመለከተው ተመን መሠረት ይፈፀማል፡፡
3. የትምህርት ማስረጃን ለማረጋገጥ የሚፈፀም የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሦስት በተመለከተው ተመን መሠረት ይፈፀማል፡፡

## 4. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ሠንጠረዥ አንድ

### የእውቅና ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን በብር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ዲግሪ | ለማስተርስ | ለፒኤችዲ |
| 1 | የመደበኛና የርቀት የአገር በቀል የቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች | | | |
| 1.1 | እስከ ሁለት መርሃ ግብሮች የእውቅና ፈቃድ | 4,000.00 | 7000.00 | 10,000.00 |
| | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ መርሀ ግብር | 1,000.00 | 3,500.00 | 5,000.00 |
| 1.2 | እስከ ሁለት መርሃ ግብሮች የእውቅና ፈቃድ እድሳት | 5,000.00 | 8,000.00 | 11,000.00 |
| | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ መርሀ ግብር | 2,000.00 | 4,000.00 | 5,500.00 |
| 1.3 | በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ በእያንዳንዱ መርሃ ግብር | 2,000.00 | 3,000.00 | 4,500.00 |
| 1.4 | በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ እድሳት በእያንዳንዱ መርሃ ግብር | 2,500.00 | 3,500.00 | 5,000.00 |
| 1.5 | ስርአተ ትምህርት በድጋሚ ሲገመገም ለእያንዳንዱ መርሃ ግብር | 1,000.00 | 1,750.00 | 2,500.00 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1.6 | የርቀት ትምህርት እውቅናና ድጋሚ እውቅና ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ማእከል | 1,000.00 | 2,500.00 | - |
| 2 | ድንበር ተሻጋሪ የድህረ ምረቃ ትምህርት | | | |
| 2.1 | ለአንድ መርሃ ግብር የእውቅና ፈቃድ | | 10,000.00 | 15,000.00 |
| 2.2 | ለአንድ መርሃ ግብር የእውቅና ፈቃድ እድሳት | | 12,000.00 | 20,000.00 |
| 2.3 | ለአንድ መርሃ ግብር በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ | | 5,000.00 | 7,500.00 |
| 2.4 | ለአንድ መርሃ ግብር በድጋሚ ለሚቀርብ የእውቅና ፈቃድ እድሳት | | 6,000.00 | 10,000.00 |

## ሠንጠረዥ ሁለት

### የአቻ ግምት አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ለኢትዮጵያውያን | ለውጭ ዜጎች |
| 1 | ከውጭ አገር ዲግሪና ከዚያ በላይ ይዘው ለሚመጡ ለአቻ ግመታ አገልግሎት | 225.00 | 450.00 |
| 2 | ምትክ ለሚሰጥ አቻ ግመታ | 100.00 | 200.00 |
| 3 | በጊዜያዊነት ለሚሰጥ አቻ ግመታ | 125.00 | 250.00 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ከውጭ ሀገር የትምህርት ማስረጃ ይዘው መማር ለሚፈልጉ የሚሰጥ ማረጋገጫ | 150.00 | 300 |

ሠንጠረዥ ሦስት

## የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የክፍያ መጠን በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ለኢትዮጵያውያን | ለውጭ ዜጎች |
| 1 | ኦሪጅናል ዶክመንት ለማረጋገጥ | 200.00 | 400.00 |
| 2 | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ኮፒ | 50.00 | 100.00 |
| 3 | ተቋሙ እውቅና ያለው ስለመሆኑ ለሚመለከተው ሁሉ በሚል የሚሰጥ አገልግሎት | 100.00 | 200.00 |
| 4 | ተቋሙ እውቅና ያለው ስለመሆኑና ሌሎች መረጃዎች በውጭ ለሚገኙ ተቋማት በቀጥታ ሲላክ | 170.00 | 340.00 |

# አዋጅ ቁጥር 954/2008 ዓ.ም

# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ

በኢኮኖሚ ረገድ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ክህሎት ያለው፣ በዲሲፕሊን የታነፀ፣ ተነሳሽነት የተላበሰና ከአዳዲስ አሠራሮች ጋር ተዋህዶ ሥራውን የሚያከናውን የሰው ኃይል ማፍራት ያለውን ወሳኝ ድርሻ በመገንዘብ፤

በገበያ ፍላጐት የሚመራ አስፈላጊ የሰው ኃይል ማፍራት የሚቻለው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በኩል መሆኑ በመታመኑና የሃገራችን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂም የሰው ኃይል ግንባታው በዚሁ አቅጣጫ እንዲመራ የተወሰነ በመሆኑ፤

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ አገር አቀፍ የሙያ ደረጃ በማዘጋጀትና የሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓት በማደራጀት በተለያዩ መንገዶች ክህሎት የጨበጡ የማህበረሰብ አባላት ወጥ በሆነ የምዘና ሥርዓት ተመዝነው አገር አቀፍ እውቅና ያለው ማረጋገጫ የሚያገኙበትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆን የሰው ኃይል ማፍራት እንደሚገባ በመታመኑ፤

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በገበያ ተወዳዳሪነት የማረጋገጥ ሚና እንዲጫወት ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ ወጥነት ይኖረው ዘንድ በአንድ በኩል አገር አቀፍ የአስተዳደር ማዕቀፍ በመደንገግ በሌላ በኩል ደግሞ ያልተማከለና አሳታፊ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት በማመቻቸት ባለድርሻ አካላት በንቃት የሚሳተፉበት አሠራር መፍጠር በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና" ማለት በሃገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሠረት በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ደረጃቸው ከከፍተኛ ትምህርት በታች በሆኑ መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓት ሲሆን መደበኛ ባልሆነ መልኩ የተገኘ የሙያ ብቃት የማረጋገጥ ሥርዓትን ይጨምራል፤
2. "የተጠቃለለና የተዋሃደ" ማለት በየዘርፉ ያሉትን ሙያዎች ወጥነት ባለው መንገድና በአንድ የብቃት ማእቀፍ ሥር በተሟላ መልኩ ያዋሃደ የትምህርትና ስልጠና ለማስፈን የተዘረጋ ሥርዓት ነው፤
3. "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/2003 የተቋቋመው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ነው፤
4. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
5. "ባለድርሻ አካላት" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸው እንደ መንግስታዊ አካላት፣ ማሰልጠኛ ተቋሞች፣ የልማት ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ አካላትንና እነዚህ የመሳሰሉ ሌሎች አካላትን ያጠቃልላል፤
6. "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ" ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ሕንጻን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ) ወይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፤

7. “አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ” ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ሕንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 (ሃምሳ ሺ አንድ) እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) ወይም በማኑፋክቸሪንግ እንዱስትሪ ዘርፍ፣ በከተማ ግብርና፣ በባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራና በግንባታ ዘርፍ ከብር 100,000 እስከ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፤

8. “የክልል አግባብነት ያለው አካል” ማለት በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠናን የሚመራና የሚያስተባብር መንግስታዊ አካል ሲሆን የብቃት ማዕከላትንም ይጨምራል፤

9. “የሙያ ደረጃ” ማለት በሥራ ዓለም በሚገኙ ሙያተኞች የሚዘጋጅ የሙያ ደረጃ ሲሆን ሰዎች በሥራ ዓለም ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ሊኖራቸው የሚገባውን ብቃት የሚያመለክት ነው፤

10. “የሙያ ብቃት” ማለት የተወሰነ ሥራ ለማከናወን ለሥራ መደቡ የሚገባውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ይዞ መገኘት እና ተግባራዊ ማድረግ መቻል ነው፤

11. “የብቃት ማዕከል” ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሙያ ብቃት ምዘና ሂደት የማመቻቸትና የማደራጀት ሃላፊነት የተሰጠው መንግስታዊ አካል ነው፤

12. “የሙያ ብቃት ምዘና” ማለት ከተገቢው የሙያ ብቃት ላይ የደረሰ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

13. “የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከል” ማለት የሙያ ብቃት ምዘና ለማከናወን ሲባል በብቃት ማዕከላት እውቅና ተሰጥቶት የሚቋቋም ማዕከል ነው፤

14. “የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት” ማለት በኤጀንሲው ስም በብቃት ማዕከላት የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ሲሆን የሰነዱ ባለቤት በሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓት ተመዝኖ ብቃቱ የተረጋገጠ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ ነው፤

15. “ውጤትን መሠረት ያደረገ ምዘና” ማለት የሙያ ብቃቱ እንዴት፣ መቼና የት እንደተገኘ ግምት ውስጥ ሳይገባ የሙያ ብቃቱ ስለመኖሩ ብቻ የሚመዘንበት አሠራር ነው፤

16. "የትብብር ሥልጠና" ማለት ማሰልጠኛ ተቋሞችና የልማት ድርጅቶች በትብብር የሚሰጡት የስልጠና ዘዴ ነው፤

17. "የሥራ ላይ ስልጠና" ማለት በልማት ድርጅቶች ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙ ሠራተኞችን የሙያ ብቃት ክፍተትን መሠረት አድርጎ በሥራ ቦታ የሚሰጥ ስልጠና ነው፤

18. "የልማት ድርጅት" ማለት በትብብር ሥልጠና ማዕቀፍ የሚሳተፍ ምርት ወይም አገልግሎት ለመስጠት በመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆነ አካል ወይም በግል የተቋቋመ ድርጅት ሆኖ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝንም ይጨምራል፤

19. "የልማት ፕሮግራም ፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች" ማለት የሃገሪቱን የልማት ፕሮግራሞች በበላይነት የሚመሩ አስፈጻሚ አካላት ናቸው፤

20. "አመራር አካላት" ማለት በማሰልጠኛ ተቋሞች የሚሰሩ የሥራ ሃላፊዎች ናቸው፤

21. "አሰልጣኝ" ማለት በማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ በማሰልጠን ሥራ የተሰማራ ሰው ነው፤

22. "ሰልጣኝ" ማለት ሙያ ለመቅሰም እና ያለውን ችሎታ፣ የሙያ ሥነ ምግባር እና አመለካከቱን ለማዳበር ሲባል በትብብር በሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር ውስጥ ስልጠና የሚከታተል ግለሰብ ነው፤

23. "የጋራ ቅጥር ሥርዓት" ማለት ባለሙያው መደበኛ ቅጥሩ በልማት ድርጅት ወይም በአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሆኖ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም ተጨማሪ የማሰልጠን ኃላፊነት የሚወስድበት አሠራር ነው፤

24. "እውቅና" ማለት በማሰልጠኛ ተቋሞች የሚሰጡ የስልጠና መርሃ ግብሮች ከሚኒስቴሩ የእውቅና አሰጣጥ መመሪያ አንጻር ተመዝነውና ተገቢነታቸው ታይቶ የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት ሥርዓት ሲሆን፣ የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ምዘና ለማከናወን ያላቸው ብቃት ተመዝኖ ማረጋገጫ የሚያገኙበት አሠራርንም ይጨምራል፤

25. "እውቅና ሰጪ አካል" ማለት ኤጀንሲው ወይም የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ሥርዓት አስፈጻሚ አግባብነት ያለው አካል ሲሆን የብቃት ማዕከላትንም ይጨምራል፤

26. "ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት" ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ችግር በመለየትና የተሟላ መረጃ በማደራጀት፣ ስልጠናና

ምክር፣ የቴክኖሎጂ ልማትና የገበያ ትስስር እንዲሁም ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍን የሚያካትት ድጋፍ ነው፤

27. "ማሰልጠኛ ተቋም" ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ላይ የተሰማራ የመንግስት፣ የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ነው፤
28. "መንግስታዊ ያልሆኑ ማሰልጠኛ ተቋሞች" ማለት በግል ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ባለቤትነት የተያዙ ማሰልጠኛ ተቋሞችን የሚያጠቃልል ነው፤
29. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርንም ይጨምራል፤
30. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
31. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓቱ ውስጥ በሚሳተፉ፣ በተለይም በማሰልጠኛ ተቋሞች፣ በልማት ድርጅቶች፣ በአሰልጣኞችና ሠልጣኞች እንዲሁም ይህንን አዋጅ እንዲያስፈጽሙ ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ዓላማዎች</u>

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት አጠቃላይ ዓላማ ብቃት ያለው፣ ተነሳሽነት የተላበሰ፣ ለሥራ ፈጠራ የተዘጋጀና ከለውጥ ጋር ራሱን ማስተካከል የሚችል የሰው ኃይል በመፍጠር የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ/ በውጤት ላይ የተመሠረተ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን መፍጠር፣ ማጠናከር እና እየጎለበተ እንዲሄድ ማድረግ፣
   ለ/ ማሰልጠኛ ተቋሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፈልፈያና የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል አቅም መፍጠሪያ እንዲሆኑ ማድረግ፤
   ሐ/ የአቅም ክፍተታቸውን በመለየት የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን

አገልግሎት በመስጠት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ተወዳዳሪ ማድረግ፤

መ/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎች የሚለዩበትን፣ የሚመረጡበትን፣ የሚቀዱበትን፣ የሚፈተኑበትንና የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

ሠ/ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ እና የተቀናጀ የአሰራር ማዕቀፍ መፍጠር፤

ረ/ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ለመፈጸም፣ በብቃት ለመምራትና የጥራት ማኔጅመንት ሥርዓትን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠርና ማጠናከር፤

ሰ/ ለአገር እድገት ቁልፍ ሚና ባላቸው የሥራ መስኮች አግባብነት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚዳረስበትንና የሚሰጥበትን መንገድ ማመቻቸት፤

ሸ/ የልማት ድርጅቶች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ጋር የተቀናጁ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ቀ/ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ዘለቄታ ያለው የፋይናንስ ሥርዓትና የሥራ አመራር መዋቅር መዘርጋት፤

በ/ ሴቶችንና ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ወገኖች እንዲሁም የገጠሩን ማህበረሰብ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ተጠቃሚ በማድረግ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እኩል የተሳትፎ እድል የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

## 5. <u>መርሆዎች</u>

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ማዕቀፍ የልማታዊ መንግሥት እሴቶችን መሰረት በማድረግ የተጠቃለለና የተዋሃደ፣ በገበያ ፍላጐት የሚመራ፣ አሳታፊና ያልተማከለ አሠራር የሚከተል እንዲሁም ተደራሽነትን በማረጋገጥ መርሆዎች መሠረት የሚመራ ይሆናል።

## 6. <u>ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማዕቀፍ</u>

1. የሀገር አቀፍ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማዕቀፍ የተሟላ፣ ለሁሉም ሙያዎች የሚያገለግል እና በየደረጃው ለይቶ ለመመደብ መሟላት የሚጠበቅባቸውን መመዘኛዎች የያዘ ሆኖ እንዲደራጅ ይደረጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደራጅ የብቃት ማዕቀፉ ግልጽነት ለተላበሰና ወጥነት ላለው ሥርዓት መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል።
3. ኤጀንሲው እያንዳንዱ ብቃት ሊኖረው የሚገባውን ዝርዝር ተፈላጊ መመዘኛ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ያወጣል።

7. <u>የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አፈጻጸም</u>

1. የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ አጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን የማስተባበር ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
2. የፌደራል መንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን በተመለከተ ሀገር አቀፍ ደረጃና መለኪያ ያወጣል፡፡

8. <u>የማሰልጠኛ ተቋሞች አመሠራረት</u>

1. በፌደራል መንግሥት በጀት የሚተዳደር ማንኛውም ማሰልጠኛ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይቋቋማል፤ የተቋሙ የስራ አመራር ቦርድ በደንብ ይወስናል፡፡
2. በክልል መንግሥት በጀት የሚተዳደር ማንኛውም ማሰልጠኛ ተቋም በክልሉ መንግሥት ሕግ መሠረት ይቋቋማል፤ የተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት በክልሎች ህግ መሰረት ይወስናል፡፡
3. መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም በግል ባለሀብቶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ሊቋቋም የሚችልበትን ሁኔታ በመመስረቻ እና በመተዳደሪያ ደንቦቻቸው ይወሰናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሙያ ደረጃ ምደባ እና የሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓት</u>

9. <u>የሙያ ደረጃ ምደባ</u>

1. የሙያ ደረጃ ምደባ ዓላማ የሥራ ገበያውን የሰው ኃይል ፍላጐት በመተንተን ተፈላጊውን የሰው ኃይል ለማቅረብና ለማፍራት የሙያ ብቃቱንም ለማረጋገጥ ለሚከናወኑ ቀጣይ ተግባራት መነሻ የሚሆን የሙያ ደረጃ ሰነድ ማዘጋጀት ነው።
2. ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመመካከር የባለድርሻ አካላትንና በሥራ ዓለም ልምድ ያካበቱ ግለሰቦች በአባልነት የተካተቱባቸው የቴክኒክ ቡድኖችን በማዋቀር የሙያ ደረጃ እንዲዘጋጅ በማድረግ በሥራ ላይ ያውላል።
3. ለየሙያው ቅርበትና ልዩ እውቀት ባላቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች መሪነት የሙያ ደረጃ ይዘጋጃል፡፡
4. እያንዳንዱ ሙያ በየደረጃው የሚጠበቅበት የብቃት ደረጃ የሚገለጽባቸው የተጠቃለሉ የሙያ ደረጃ ሰነዶች በየወቅቱ ለሕዝብ ይፋ ይሆናሉ።

10.<u>የብቃት ማዕከላት</u>

የብቃት ማዕከላት፡-

1. የሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓቱን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ለተገቢው የክልል አካላት ተጠሪ ሆነው ይደራጃሉ፤
2. ከሙያ ብቃት በምዘናና ከምዘና ጋር በተያያዙ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ከማናቸውም አካል ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው ሥራቸውን ያከናውናሉ፤
3. ሚኒስቴሩ ከክልል አግባብነት ካለው አካል ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት እውቅና ይሰጣሉ፤
4. ምዘና ለማከናወን ብቃታቸው ለተረጋገጠ መዛኞች የብቃት ምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፡፡

11.<u>የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት</u>

1. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት በብቃት ማዕከላት እውቅና እየተሰጣቸው ይደራጃሉ፡፡
2. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ከየሙያ ደረጃው ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገው በተዘጋጁ የሙያ ብቃት ምዘና መሣሪያዎች መሠረት ምዘናውን ያከናወናሉ፡፡
3. ለተመዛኞች ተደራሽነት ሲባልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተንቀሳቃሽ የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት እንዲደራጁ ሊደረግ ይችላል።

4. ለምዘና የሚያገለግሉ የሙያ ብቃት ምዘና መሣሪያዎችን በማዘጋጀት ረገድና ምዘናውን ለማከናወን በሥራ ዓለም ልምድ ያካበቱ ሙያተኞች ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

12. **<u>የሙያ ብቃት ምዘና</u>**

1. የሙያ ብቃት ምዘና ተመዛኞች በሚመዘኑበት የሙያ ዘርፍ የሚፈለገው ብቃት ያላቸው ስለመሆናቸው ለመወሰን በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ መመሪያ መሠረት የሚከናወን ይሆናል።
2. የሙያ ብቃት ምዘና ሙያው አለኝ ብሎ ለሚቀርብ ለማንኛውም ተመዛኝ ክፍት ይደረጋል።

13. **<u>የሙያ ብቃት ምዘና ወጥነት</u>**

1. የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ በሙያ ብቃት ምዘና በኩል ተመዝኖ ብቃቱ መረጋገጥ ይጠበቅበታል።
2. በማሰልጠኛ ተቋም የሚሰጥ ሥልጠናን በብቃት ያጠናቀቀ ማንኛውም ሰልጣኝ የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ቢፈልግ ብቃቱ በሙያ ብቃት ምዘና መረጋገጥ አለበት፡፡

14. **<u>የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>**

1. በሙያ ምዘናው መሠረት ብቃቱን ያረጋገጠ ማንኛውም ሙያተኛ በኤጀንሲው ስም በብቃት ማዕከላት በኩል የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትና እውቅና ይኖረዋል።

15. **<u>የልማት ፕሮግራም ፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች</u>**

የልማት ፕሮግራሞችን ፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ተገቢ አቅም መገንባታቸውን ኤጀንሲው ሲያረጋግጥ የሙያ ደረጃ ምደባና የሙያ ብቃት ምዘናን በባለቤትነት ወስደው እንዲፈጽሙ እና እንዲያስፈጽሙ እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣን ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የሰው ኃይል እና የማሰልጠኛ ተቋሞች ልማት</u>

## 16.<u>የአሰልጣኞች እና የአመራሮች ምደባ</u>

በሙያው የሰለጠኑ፣ ብቃት ያላቸው፣ የሥራ ልምድ ያዳበሩ እና በጎ ሥነ-ምግባር የተላበሱ ሙያተኞች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኝነት የሥራ መደቦች ወይም ለአመራርነት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚመለመሉ ናቸው።

## 17.<u>የአመራሮች እና የአሠልጣኞች የሙያ ብቃት ደረጃዎች</u>

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመራሮች እና አሠልጣኞች የሙያ ዕድገታቸውን የሚያመለክቱ ደረጃዎች እንዲኖራቸው ይደረጋል።

## 18.<u>የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠና ስለመስጠት</u>

1. በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመራሮችና አሰልጣኞች የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣቸዋል።
2. ሥልጠናዎቹ የሙያ ደረጃንና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራ ኃላፊዎችና አሰልጣኞች የብቃት ማዕቀፍን መሠረት ያደረጉ ይሆናሉ።
3. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አስፈጻሚ አካላት የቴክኒክና ሙያ መምህራንን ለሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስልጠናዎቻቸው ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እቅድ አንጻር ለመቃኘት ይችሉ ዘንድ ስለአዳዲስ የሙያ ደረጃዎች በየወቅቱ መረጃ ሊሰጧቸው ይገባል፡፡
4. የሥራ ላይ ሥልጠና ዕድል በመርህ ደረጃ ለመንግሥት፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እና ለግል የማሠልጠኛ ተቋሞች አመራሮች እና አሰልጣኞች በእኩልነት የሚሰጥ ይሆናል። ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ ከክልል አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 19.<u>የአሠልጣኞችና አመራሮች ብቃት ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት</u>

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰልጣኝ ወይም የአመራር አባል ሆኖ ለማገልገል የሚፈልግ ግለሰብ ለሥራ መደቡ የተዘጋጀውን የሙያ ብቃት ምዘና ወስዶ የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት መያዝ አለበት።

## 20.<u>የጋራ ቅጥር ሥርዓት</u>

1. ማንኛውም የአሰልጣኝነት ሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት የያዘ ሙያተኛ ከመደበኛ ሥራው በተጨማሪ በማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ በጋራ ቅጥር ሥርዓት መሠረት በአሰልጣኝነት ተቀጥሮ መሥራት ይችላል።

2. የጋራ ቅጥር ሥርዓት በባለሙያው ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ቀጣሪው መሥሪያ ቤትና ማሰልጠኛ ተቋሙ በሚያደርጉት ስምምነት የሚወሰን ይሆናል።

3. የጋራ ቅጥሩ ሁኔታ፣ የሚቆይበት ጊዜ፣ ደመወዝና ሌሎች የጊዜ ማደላደልንና የመሳሰሉት ባለሙያውንና ቀጣሪዎቹን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ በእነዚሁ አካላት ስምምነት የሚወሰኑ ይሆናሉ።

21. **<u>ስለማሰልጠኛ ተቋሞች ልማትና የማሰልጠኛ ተቋሞች አመራር ብቃት</u>**

የማሰልጠኛ ተቋሞች ልማት የሚከናወንበትና ደረጃቸው የሚወሰንበት ሁኔታ እንዲሁም አመራር ብቃት የሚመዘንበት አሠራር ይኖራል፡፡

22. **<u>የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምርምር የትኩረት መስኮች</u>**

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዙሪያ የሚደረጉ ምርምሮች ከንድፈ ሃሳብ ትንተና ወጣ ብለው ተግባር ተኮር በሆኑ በሚከተሉት ጉዳዮች እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡-

1. ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ ሃገራዊ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የምርምር አቅም ማደራጀት፤
2. የሰው ኃይል የገበያ ሁኔታውን ማጥናት፤
3. በተለያዩ አካላት የተሰባሰቡ መረጃዎች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በሚጠቅም መንገድ መለየትና መተንተን፤
4. ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ማሸጋገር በሚቻልበት ስልት ዙሪያ ተግባራዊ ምርምር ማካሄድ፡፡

23. **<u>ስለተግባር ተኮር ምርምር</u>**

የማሰልጠኛ ተቋሞች ተግባር ተኮር ምርምርን አጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ሥርዓቱን ከማስፈጸም አኳያ ችግሮችን ለመፍታትና አዳዲስ አሰራሮችን ለመተግበር በቀጣይነት የሚከናወንና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የማይነጠል አካል ማድረግ አለባቸው፡፡

24. **<u>የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት</u>**

1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ችግር በመለየትና በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተሟላ መረጃ በማደራጀት አቅም መገንባትና ድጋፍ መስጠት ሲሆን አፈጻጸሙም፡-

ሀ/ በገበያ ፍላጎት የሚመራ እና የድጋፍ ማዕቀፍን መሠረት ያደረገ አገልግሎት

መስጠት እና

ለ/ ለነባር እና ለሞዴል ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ መስጠት ይሆናል፡፡

2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ዝርዝር አፈጻጸም ኤጀንሲው አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ ተቋማት ጋር በሚያደርገው ምክክር የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የትብብር ስልጠና ማዕቀፍ

### 25. የትብብሩ መሠረት

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በማሰልጠኛ ተቋማትና በልማት ድርጅቶች መካከል በሚፈጠር ትብብር የሚካሄድ ይሆናል።
2. የትብብሩ መሠረት በፈቃደኝነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል።
3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ቢኖርም የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የልማት ፕሮግራሞች በትብብር ሥልጠና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው፡፡

### 26. የትብብር ሥልጠና አፈጻጸም

1. የትብብር ስልጠናው ሰልጣኞች የንድፈ ሃሣብ ዕውቀት እና የተግባር ክህሎት በተመጣጠነ ሁኔታ እንዲገበዩ በሚያስችል ሁኔታ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡
2. የንድፈ ሃሣብና የተግባር ሥልጠና ምጣኔው እንደየሙያው ዓይነትና ደረጃ የሚለያይ ሆኖ በሙያ ደረጃው በተመለከተው መሠረት ይከናወናል፡፡

### 27. ለትብብር ስልጠና ተሳታፊዎች ተገቢ ዕውቅና ስለመስጠት

ኤጀንሲው፣ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ማሰልጠኛ ተቋሞች በትብብር ሥልጠና ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ የልማት ድርጅቶች ስማቸው እና አድራሻቸው በሚያገኙት ዘዴ ሁሉ በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ እና እንዲሠራጭ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## ክፍል አምስት

## የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም እውቅና አሰጣጥ

### 28. የእውቅና ፈቃድ መያዝ ግዴታ ስለመሆኑ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃግብር ለመክፈት ወይም ለማስፋፋት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከእውቅና ሰጪው አካል የእውቅና ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበት።

## 29.<u>የእውቅና አሰጣጥ</u>

1. ሚኒስቴሩ የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ወጥነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡
2. ኤጀንሲው በፌደራል መንግሥት አካላት ለሚቋቋሙ ማሰልጠኛ ተቋሞች፣ በፌደራል ደረጃ በግል ለሚቋቋሙ ማሰልጠኛ ተቋሞች፣ በውጪ ዜጎች ለሚቋቋሙ ማሰልጠኛ ተቋሞች እንዲሁም በሌላ አገር ሕግ በተቋቋሙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሥር ለሚተዳደሩ ማሰልጠኛ ተቋሞች እውቅና ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል አግባብ ያላቸው አካላት በክልላቸው ውስጥ ሥልጠና ለሚሰጡ ማሰልጠኛ ተቋሞች ዕውቅና ይሰጣሉ።
4. እውቅና ለመስጠት የሚደረግ ግምገማ ግልጽነት በተላበሰና አሳታፊ በሆነ ሥርዓት የሚከናወን መሆን አለበት።
5. የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት እውቅና የሚሰጣቸው ተቋሞችን በሚደግፍ፣ በሚያበረታታ እና አቅማቸውን ደረጃ በደረጃ በሚያሳድግ መልኩ መከናወን ይኖርበታል።
6. እውቅና ስለሚታደስበት፣ ስለሚታገድበት፣ ስለሚሠረዝበት እና ስለቅሬታ አቀራረብ እንዲሁም እውቅና የሚሰጣቸው የማሰልጠኛ ተቋሞች ስለሚጠበቅባቸው የአገልግሎት ክፍያና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 30. <u>የማሰልጠኛ ተቋማት እውቅና ያገኙባቸውን የሥልጠና መርሃግብሮች ዝርዝር ስለመያዝና ማሰራጨት</u>

1. እውቅና ሰጪ አካላት እውቅና በሰጡዋቸው ተቋሞች ውስጥ የሚሰጡ የሥልጠና መርሃግብሮችን ዝርዝር በየወቅቱ መመዝገብ እና የተለወጡ ነገሮችም ካሉ ይህንኑ የሥልጠና ተቋማት ማሳወቅ አለባቸው፤ ዝርዝሩም በየወቅቱ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት።
2. ኤጀንሲው ከክልል አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እውቅና የተሰጣቸውን መርሃግብሮችና የሚሰጡባቸውን ማሰልጠኛ ተቋሞች የተጠቃለለ

ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ በመያዝ በየወቅቱ አግባብ ባለው የመገናኛ ዘዴ ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት።

31.<u>የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል</u>

1. በእውቅና ሰጪው አካል የተመደበ ባለሙያ ወይም ቡድን በማሰልጠኛ ተቋሙ ውስጥ በመገኘት ማሰልጠኛ ተቋሙ የሥልጠና መርሃግብሮቹን እውቅና በተሰጠበት መመዘኛና ደረጃ መሠረት ስለማከናወኑ ክትትል የማድረግ ስልጣን አለው፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የቴክኒክ ድጋፍ፣ ምክርና እገዛ መስጠት አለበት።
2. በእውቅና መመዘኛዎቹ መሠረት ሥራን አለማከናወን የእርምት እርምጃ ያስከትላል፡፡
3. ኤጀንሲው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና ስትራተጂ በክልሎች በአግባቡ እንዲፈጸም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የመንግሥት የማሰልጠኛ ተቋሞች የበጀትና የፋይናንስ አስተዳደር</u>

32.<u> የፋይናንስ አስተዳደር ነጻነትና ተጠያቂነት</u>

የአገሪቱ የፋይናንስ ሕጎችና ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም ውስጣዊ የፋይናንስ አጠቃቀም ነፃነት ይኖረዋል።

33.<u>በጀት</u>

1. ተጠሪነታቸው ለፌደራሉ መንግስት የሆኑት የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋሞች ስትራተጂክ ዕቅዳቸው መሠረት ተደርጎ በፌደራሉ መንግሥት በኩል በጀት የሚመደብላቸው ይሆናል።
2. ማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም በሚያቀርበው ስትራቴጂክ ዕቅድና በሚያስመዘግበው ውጤት መሠረት ዓመታዊ በጀት ይመደብለታል።
3. ማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ስጦታዎችን መቀበል ይችላል፤ ሆኖም የሚቀበለው ስጦታ በተቋሙ አቋም፣ ተልእኮ እና ዓላማ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማይኖረው መሆን ይኖርበታል።
4. ማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች የሚያገኘውን ስጦታና በውስጥ እንቅስቃሴው የሚያገኘውን ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

34. <u>ለስልጠና የሚጠየቁ ክፍያዎችን ስለመወሰንና ስለመሰብሰብ</u>

1. ማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም በተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ ስለመጠኑና ስለአከፋፈሉ ሁኔታ በማስጸደቅ ለስልጠና የሚከፈሉ ክፍያዎችን የመሰብሰብና የሰበሰበውን ገቢ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርን መመሪያ መሠረት በማድረግ ለተቋሙ ተልእኮ ማስፈጸሚያ መጠቀም ይችላል።
2. የሥልጠና ክፍያውን መጠን ለመጨመር ወይም የአከፋፈል ሁኔታውን ለማሻሻል የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሥራ አመራር ቦርድ መጽደቅ አለበት።

35.<u>የወጪ መጋራት</u>

1. በማንኛውም የፌደራል መንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም ሥልጠናውን የሚከታተል ሠልጣኝ የሥልጠና፣ የምዘና፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ወጪ እንዲጋራ ሊጠየቅ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የወጪ መጋራት ዝርዝር አፈጻጸም እና በየጊዜው የሚከለስበት ሁኔታ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

36. <u>የውስጥ ገቢን ስለማመንጨትና ስለመጠቀም</u>

1. ማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም በሥራ አመራር ቦርዱና በሚመለከተው አካል አጽድቆ የውስጥ ገቢ የማመንጨትና ይህንኑ ገቢም ለተቋሙ ተልእኮ ማስፈጸሚያ ሊያውለው ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቋሙ ያመነጨውን ገቢ ከበጀት ዓመቱ በኋላ ወደቀጣይ በጀት ዓመት አሸጋግሮ ለመጠቀም ስለሚችልበት ሁኔታ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል።
3. የውስጥ ገቢ የመማንጨት ሥራ የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋሞቹን ዋነኛ ዓላማ በማይጎዳ መልኩና የገበያ ክፍተትን ለመሙላት ብቻ የሚከናወን መሆን ይኖርበታል።

37. <u>የፋይናንስ አስተዳደር</u>

1. የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋሞች ኃላፊዎች የፋይናንስ ጉዳያቸውን በፋይናንስ ሕግ መሠረት በግልጽነት፣ በቅልጥፍና እና በውጤታማነት መርሆዎች ላይ ተመስርተው የማስተዳደርና የመምራት ኃላፊነት አለባቸው።

2. ማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም የተቋሙን የፋይናንስ መግለጫዎች የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. በማንኛውም የፌደራል የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ ራሱን የቻለና ለማሰልጠኛ ተቋሙ ኃላፊ ተጠሪ የሆነ የውስጥ ኦዲት ይደራጃል፡፡

38.<u>ስለ ሂሣብ መዛግብት</u>

1. ማንኛውም የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋም ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዛግብት የመያዝ ግዴታ አለበት።

2. የመንግሥት ማሰልጠኛ ተቋሞች የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

39. <u>መዛግብትና ሰነዶች</u>

ማንኛውም የማሠልጠኛ ተቋም የሥራውን እንቅስቃሴ በተመለከተ፣ የሥራ መሪዎቹን፣ የአሰልጣኞቹን ዝርዝር ከሙያ ብቃት ምስክር ወረቀታቸው ጋር እና የሰልጣኞችን ዝርዝር የሚያሳዩ መዛግብት አደራጅቶ መያዝ ይኖርበታል።

40.<u>መረጃዎችን ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም የማሠልጠኛ ተቋም የሥራውን እንቅስቃሴ በተመለከተ በእውቅና ሰጪው አካል ሲጠየቅ ተገቢና ወቅታዊ መረጃዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት።

2. የማሠልጠኛ ተቋሞች የሰልጣኞቻቸውን ቁጥር፣ የሰልጣኞቻቸውን የሙያ ብቃት ምዘና ውጤት እና የመሳሰሉትን መረጃዎች በስታትስቲክስ አስደግፈው የመያዝ እና ለእውቅና ሰጪው አካል የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

3. እውቅና ሰጪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የቀረቡለትን መረጃዎች በሕግ ወይም በሌላ አኳኋን እንዲገልጽ ካልተገደደ በስተቀር በምስጢር ሊይዛቸው ይገባል።

41.<u>የሥልጠና ዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ</u>

የግል ማሠልጠኛ ተቋሞች የሥልጠና ዋጋ ማስተካካያ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታና አፈጻጸሙን ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር ይወሰናል፡፡

42.<u>ኃላፊነት</u>

ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ተላልፎ ከተገኘ በሕግ መሠረት የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ኃላፊነት ይኖርበታል።

43.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ክልሎች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሕጎችን ሊያወጡ ይችላሉ።
3. ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

44.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. በአዋጅ ቁጥር 391/1996 መሠረት የተሰጡ የእውቅና ፈቃዶች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጡ ተደርገው ይቆጠራሉ።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ማሠልጠኛ ተቋሞች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡት ደንብና መመሪያዎች መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው።
3. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመታየት ላይ የነበሩ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳሉ።
4. የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2003 በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጣ ይቆጠራል።

45.<u> የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ ቁጥር 391/1996 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

46.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት 19 ቀን 2008 ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## ለ/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የስልጠና ማዕከሎችን ማቋቋሚያ ህጎች

### 1/ በትምህርት ሚኒስቴር ስር የሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች

### ደንብ ቁጥር 211/2003 ዓ.ም

### የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 211/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ሠመራ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በሠመራ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

### ደንብ ቁጥር 212/2003 ዓ.ም

### የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 212/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. <u>መቋቋም</u>

   1. አምቦ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ዋና ግቢ</u>

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአምቦ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 213/2003 ዓ.ም

## የቡሌ ሆራ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 213/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በቡሌ ሆራ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 214/2003

## የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 214/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. መቋቋም

   1. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. ዋና ግቢ

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. የተሻረ ደንብ

   የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲን እንደገና ለማደራጀት የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 113/1985 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 215/2003 ዓ.ም

## የአሶሳ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 215/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አሶሳ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአሶሳ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 217/2003

## የወለጋ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 217/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. <u>መቋቋም</u>

   1. ወለጋ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ዋና ግቢ</u>

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በነቀምት ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 218/2003

## የወላይታ ሶዶ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 218/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ወላይታ ሶዶ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 219/2003

## የወልቅጤ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የወልቅጤ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 219/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ወልቅጤ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በወልቅጤ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 220/2003

## የወልዲያ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 220/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በወልዲያ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 221/2003</u>

## <u>የወሎ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የወሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 221/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>መቋቋም</u>

   1. ወሎ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ዋና ግቢ</u>

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በደሴ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 222/2003

## የዋቻሞ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 222/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በሆሳዕና ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 223/2003

## የዓዲግራት ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 223/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በዓዲግራት ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 18 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 224/2003

## የሚዛን ቴፒ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 224/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ሚዛን አማን ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 225/2003

## የአክሱም ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአክሱም ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 225/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አክሱም ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአክሱም ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 226/2003

## የጂግጂጋ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 226/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በጂግጂጋ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 227/2003

## የደብረ ማርቆስ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 227/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>መቋቋም</u>

   1. ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ዋና ግቢ</u>

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ደብረ ማርቆስ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 228/2003

## የደብረ ብርሃን ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 228/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ደብረ ብርሃን ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 229/2003

## የደብረ ታቦር ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 229/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በደብረ ታቦር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# ደንብ ቁጥር 230/2003

## የዲሬዳዋ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዲሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 230/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ዲሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በዲሬዳዋ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 231/2003

## የሀዋሳ ዩንቨርስቲን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 231/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በሀዋሳ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የደቡብ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 62/1992 (በደንብ ቁጥር 127/1999 እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 232/2003 ዓ.ም

## የሀረማያ ዩንቨርስቲን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 232/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በሀረማያ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የአለማያ ግብርና ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 198/1986 (በደንብ ቁጥር 123/1998 እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 233/2003

## የመቐለ ዩንቨርስቲን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመቐለ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 233/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. መቐለ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በመቐለ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የአለማያ ግብርና ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 61/1992 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 234/2003

## የባህር ዳር ዩንቨርስቲን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 234/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በባህር ዳር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የባህር ዳር ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 8/1992 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 235/2003

## የአርባ ምንጭ ዩንቨርስቲን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 235/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ አርባ ምንጭ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የአርባ ምንጭ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 111/1997 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 236/2003

## የመደወላቡ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 236/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ መደወላቡ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 238/2003

## የዲላ ዩንቨርስቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዲላ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 238/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ዲላ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ዲላ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የዲላ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 129/1999 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 239/2003

## የመቱ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የመቱ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 239/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. መቱ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በመቱ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 240/2003

## የጅማ ዩንቨርስቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጅማ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 240/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ጅማ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የጅማ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 63/1992 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 241/2003

## የጎንደር ዩንቨርስቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 241/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ጎንደር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በጎንደር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የጎንደር ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 112/1997 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 317/2003

## የጋምቤላ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 317/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በጋምቤላ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 30 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 322/2006

## የአርሲ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 (በአዋጅ ቁጥር 803/2005 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 5 አንቀጽ 35 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 322/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. የአርሲ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአሰላ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ ከመስከረም 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 349/2008

## ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 349/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በቦንጋ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 350/2008

## የደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 350/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የደባርቅ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በደባርቅ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 351/2008

## የደንቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የደንቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 351/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የደንቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በደንቢ ዶሎ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 352/2008

## የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 352/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በእንጅባራ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 353/2008

## የጅንካ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጅንካ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 353/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የጅንካ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በጅንካ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 354/2008

## የቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 354/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በቀብሪ ደሃር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 355/2008

## የመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 355/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>መቋቋም</u>

   1. የመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ዋና ግቢ</u>

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በቱሉአዋሊያ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# ደንብ ቁጥር 356/2008

## የአዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 356/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የአዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በጭሮ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 357/2008</u>

## <u>የራያ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የራያ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 357/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>መቋቋም</u>

   1. የራያ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. <u>ዋና ግቢ</u>

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በማይጨው ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 358/2008

## የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 358/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የወራቤ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በወራቤ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 359/2008

## የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5 እና 39 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 359/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መቋቋም**

   1. የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
   2. የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡
   3. ዩኒቨርስቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በፍቼ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች</u> <u>ደንብ ቁጥር 200/2003</u>

## የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 200/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፤
   2. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
   3. "ፕሮቮስት" ማለት የማስተማርና የህክምና አገልግሎት በመስጠት ጭምር ኮሌጁን ሊያገለግል የሚችል ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀጽ 11(1) መሠረት የተሾመ የኮሌጁ መሪ ነው፤
   4. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   5. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

   1. ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ "ኮሌጅ" እየተባለ የሚጠራን የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. አግባብነት ባላቸው የአዋጁ አንቀጽ 88 ድንጋጌዎች ለትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ኮሌጁ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡
   3. ኮሌጁ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ይተዳደራል፡፡

4. የኮሌጁ ዋናው ግቢ በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎችና የምርምርና የህብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 4. ዓላማ

የአዋጁ አንቀጽ 4 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ሕብረተሰብ-ተኮር፣ ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተዛመደ እና ጥራቱን የጠበቀ የህክምና አገልግሎት መስጠት፤
2. ከተግባር ጋር የተዋሃደ፣ ችግር ፈቺና ተማሪን ማዕከል ያደረገ ሥርዓተ ትምህርትን በመዘርጋት ጥራት፣ ብቃትና ሥነ ምግባር ያላቸው የጤና ባለሙያዎችን በብዛት ማሰልጠን፤
3. ተገቢውን ተቋማዊ ሥርዓት በመዘርጋት ትኩረት በሚሹ የጤና ጉዳዮች ላይ ችግር ፈቺና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ምርምሮችን ማካሄድና ማስረጽ፤
4. ልዩ የቅበላ ሥርዓት በመዘርጋት የሴቶችንና የታዳጊ ክልሎችን ተሳትፎ ማጎልበት፡፡

## 5. ኃላፊነት

የአዋጁ አንቀጽ 8 እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ኮሌጁ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የህክምና አገልግሎት ለሕብረተሰቡ የመስጠት፤
2. በስሩ የሚገኙ የህክምና መስጫ ተቋማት እና ስፔሻላይዝድ ማዕከላትን የማስተዳደር፣ አዳዲስ የህክምና ዘርፎችን የመክፈት፤
3. ፕሮግራሞች፣ ፋኩልቲዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ተቋማት አቋቁሞ የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የመቀየስ፣ የመተግበርና በአግባቡ የመምራት፤
4. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ከፍተኛ አስተዋፆ ላደረጉ ሰዎች የአካዳሚክ ማዕረግና የሚዳይ ሽልማት የመስጠት፤
5. ቅድሚያ በሚሰጥባቸው የጤና መስኮች ላይ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር የማድረግ፤

6. ለልምምድ ተማሪዎችን ከሚልኩ የግልና የመንግስት ተቋማት በውስጥ ደንቡ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ፤ ሌሎች አገልግሎቶቹን የመሸጥ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎትን የመግዛት፤
7. የህብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ የህክምና አገልግሎቱን ክፍያ የመወሰን፤ የነጻ ህክምና ተጠቃሚዎች መለየት የሚያስችል ወጤታማ አሰራርን የመቀየስ፤
8. መደበኛውን የህክምና ቅብብሎሽ ሥርዓት ሳይከተል ለሚመጣ ታማሚ ልዩ ክፍያ በማስከፈል የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚደረግበትን ሥርዓት የማመቻቸት፤
9. ሠራተኞችና ተማሪዎች ስለሚያገኙት የህክምና አገልግሎት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የመወሰን፤
10. ሴሚናሮች፣ ዓውደ ጥናቶችና ሲምፖዚየሞችን የማዘጋጀት፤
11. በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት የመመስረትና እንደአስፈላጊነቱ ጥምረት የመፍጠር፤
12. የማማከር፣ የሥልጠናና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የመስጠት፤
13. የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦችን ማቋቋምና በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የማሰራጨት፤
14. ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

6. <u>ነፃነትና ተጠያቂነት</u>

1. ኮሌጁ በአዋጁ አንቀጽ 17 የተደነገገው የአስተዳደር ነጻነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከተው ተጠያቂነት ጋር ይኖረዋል።
2. ኮሌጁ ተልዕኮውን በሚገባ ስለማሳካቱ በተለይም የሚከተሉትን ስለማረጋገጡ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡-

   ሀ/ በመማር ማስተማርና የምርምር ሥራዎቹ ለመንግሥት ፕሮግራሞች ቅድሚያ መስጠቱንና ከሃገራዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን፤

   ለ/ አጠቃላይ አሠራሩ በግልጽነትና በአሳታፊነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን፤

   ሐ/ የበጀትና ሃብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢና ለህዝብ ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ መሆኑን፤

   መ/ የመማር ማስተማር፣ የምርምር ሥራዎች እና የህክምና አገልግሎቶች

ተቋማዊ ሆነው በግልጽ የሚከናወኑ መሆኑን፤

ሠ/ ኮሌጁ በሚያስመዘግበው የጥራትና ተገቢነት ውጤት የሚለካ መሆኑን።

## 7. ስለኮሌጁ የአመራር አካላት

ኮሌጁ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል፡-

1. ቦርድ፤
2. ሴኔት፤
3. ፕሮቮስትና ምክትል ፕሮቮስቶች፤
4. የአስተዳደር ካውንስል፤ እና
5. አካዳሚክ ኮሚሽኖች፡፡

## 8. ስለኮሌጁ ቦርድ

1. የኮሌጁ ቦርድ ሰብሳቢና አባላት በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ይሆናሉ።
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) እና በፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001 አንቀጽ 7 የተጠቀሱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
4. ስለመንግሥት ተቋም ቦርድ ስብሰባዎች፣ የአባልነት መቋረጥና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ የተመለከቱት የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለኮሌጁ ቦርድ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## 9. የኮሌጁ ሴኔት

1. የኮሌጁ ሴኔት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የኮሌጁ ፕሮቮስት ...................... ሰብሳቢ

   ለ/ የኮሌጁ ምክትል ፕሮቮስቶች .......... አባላት

   ሐ/ የፕሮግራም ኃላፊዎች ...................... "

   መ/ የቤተ መጻሕፍትና የኢንፎርሜሽን ኃላፊ....አባል

   ሠ/ ሬጅስትራር .......................................... "

   ረ/ የአካዳሚክ ሠራተኞች ሁለት ተወካዮች.........አባላት

   ሰ/ የተማሪዎች ተወካይ ................................. አባል

2. በአዋጁ አንቀጽ 50(4) እና 51 የተደነገገው የሴኔቱን አባላትና ስብሰባዎች በሚመለከት እንደአግባቡ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## 10.<u>የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 49 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በቦርዱ የሚወጡ አጠቃላይ መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የኮሌጁን ፕሮግራሞችና ኢንስቲትዩቶች ሥርዓተ ትምህርቶችን ይቀርጻል፣ መርምሮ ያጸድቃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ ያደርጋል፤
3. በህግና በቦርዱ የሚወጡ ፖሊሲዎችን መሠረት በማድረግ የተማሪዎችን አስተዳደር፣ የኮሌጁን የትምህርት ነክ ጉዳዮች፣ የትምህርት ኃላፊዎችን የምርጫ ሥነ-ሥርዓት እና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲሲፕሊንና ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤
4. የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር መርምሮ ያጸድቃል፤ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለቦርዱ ሃሳብ ያቀርባል፤
5. አዳዲስ የትምህርት መርሃ ግብሮች እንዲጀመሩ ያደርጋል፤ የኮሌጁን ተቋማት ውህደት በተመለከተ የቀረበ ሃሳብን መርምሮ ያጸድቃል፤
6. የተማሪዎች አቀባበልን፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰን፣ የዲሲፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ያወጣል፤ በነዚህ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤
7. አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥና ደረጃዎች አቅጣጫዎችን ይወስናል፤
8. የሴት ተማሪዎችንና የታዳጊ ክልሎች ተማሪዎችን ቅበላና ማቆየትን አስመልክቶ ሥርዓት ይዘረጋል፤
9. ለድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም ልዩ የተማሪዎች አቀባበል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ምረቃን ያጸድቃል፤
10. የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤
11. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተግባሩን ለሌሎች የኮሌጁ አካላትና ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 11. <u>ስለኮሌጁ ፕሮቮስትና ምክትል ፕሮቮስቶች</u>

1. የኮሌጁ ፕሮቮስትና ምክትል ፕሮቮስቶች ሹመትና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ እንደ አግባብነቱ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሰረት ይፈጸማል፡፡

2. ፕሮቮስቱ በአዋጁ ለመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

3. የኮሌጁ ምክትል ፕሮቮስቶች ቁጥር በአዋጁ አንቀጽ 54(2) መሠረት ይወሰናል፡፡

4. ምክትል ፕሮቮስቶች፣

ሀ/ የኮሌጁን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ፕሮቮስቱን ያግዛሉ፤

ለ/ በፕሮቮስቱ ተለይተው የሚሰጧቸውን ሥራዎች ያከናውናሉ፡፡

5. ፕሮቮስቱ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ፕሮቮስት ለፕሮቮስቱ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

## 12. የአስተዳደር ካውንስል

የኮሌጁን የአስተዳደር ካውንስሉ ተግባራት፣ አባላት አሰያየምና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት በሚመለከት የአዋጁ አንቀጽ 56 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 13. የአካዳሚክ ኮሚሽን

1. እያንዳንዱ ፕሮግራም ወይም ኢንስቲትዩት የአካዳሚክ ኮሚሽን ይኖረዋል።

2. የፕሮግራም ወይም የኢንስቲትዩት አካዳሚክ ኮሚሽን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የፕሮግራሙ ወይም ኢንስቲትዩት ኃላፊ.......ሰብሳቢ

ለ/ የፕሮግራሙ ወይም ኢንስቲትዩት ምክትል ኃላፊዎች ካሉ .......... አባላት

ሐ/ የትምህርት ክፍሎች ሀላፊዎች........................................... »

መ/ አንድ የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካይ................................ አባል

ሠ/ አንድ የተማሪዎች ተወካይ ............................................ »

ረ/ በኮሚሽኑ የሚመደቡ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ኃላፊዎች .......... አባላት

3. የኮሌጁ ሴኔት የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የፕሮግራሙን ወይም የኢንስቲትዩቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በጀት በማዘጋጀት ይደለድላል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ለ/ የሥልጠናና የትምህርት መርሃ ግብሮችን፣ ሥርዓተ ትምህርቶችን ወይም ማሻሻያዎችን አዘጋጅቶ ለሴኔቱ ያቀርባል፤

ሐ/ በሴኔቱ መመሪያ መሠረት የተማሪዎችን ትምህርትና ሥነ-ምግባር

የተመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን ይወስናል፤

መ/ ከትምህርት ጋር የተያያዙ ሽልማቶችንና የክብር ዲግሪ እንዲሰጥ ለሴኔቱ ሃሣብ ያቀርባል፤

ሠ/ የሌክቸረር፣ ረዳት ሌክቸረር፣ ረዳት ምሩቅና የቴክኒክ ረዳቶችን ቅጥርና ዕድገት በሴኔቱ መመሪያ መሠረት አጣርቶ ይወስናል፤

ረ/ ማንኛውም የፕሮፌሰርነት ማዕረግ እንዲሰጥ ለሴነቱ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሰ/ የነፃ ትምህርት ዕድልና የምርምርና ሰባቲካል እረፍቶችን ያጸድቃል፤

ሸ/ የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነሥርዓት ደንብ ያወጣል፤

ቀ/ ከሴኔቱና ከፕሮቮስቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

14. <u>የኮሌጁ አካዳሚክ ሠራተኞች</u>

የኮሌጁ አካዳሚክ ሠራተኞች የሥራ ጊዜያቸውን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለህክምና አገልግሎት፣ ለማስተማርና ለምርምር ማዋል አለባቸው።

15. <u>ስለተማሪዎች መቀበያ መመዘኛ</u>

1. የተማሪዎችን ቅበላ የሚመለከቱ የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሌጁ፡-

   ሀ/ የመሰናዶ ትምህርትን አጠናቀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ያለፉና በኮሌጁ የተወሰኑ መመዘኛዎችን ያሟሉ ተማሪዎችን ለቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፤

   ለ/ የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ ትምህርት ያጠናቀቁና በኮሌጁ የተወሰኑ መመዘኛዎችን ያሟሉ ተማሪዎችን ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርት ይቀበላል፤

   ሐ/ ለሴቶችና ለታዳጊ ክልል ተወላጆች የተለየ የተማሪዎች ቅበላ ሥርዓት ሊወስን ይችላል፡፡

2. ኮሌጁ የሚቀበለው ተማሪ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በወጪ መጋራት መርህ ያለበትን ግዴታ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ኮሌጁ የውጪና የሀገር ውስጥ ተማሪዎችን የትምህርት ወጪ ክፍያ በማስከፈል ሊያስተምር ይችላል፡፡

16. <u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001 ድንጋጌዎች ከዚህ ደንብ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ የኮሌጁ ማስተማሪያ ሆስፒታልን በተመለከተ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

17. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

የቅዱስ ጳውሎስ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮሌጁ ተላልፈዋል፡፡

18. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 21 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 3/ በኢትዮጵያ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ስር የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች

### ደንብ ቁጥር 237/2003

### የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 237/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡[3]
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአዳማ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **የተሻረ ደንብ**

   የአዳማ ዩንቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 120/1998 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

5. **ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ**

---

[3] ይህ ንዑስ አንቀፅ በ20/66 (2006) ደ.315 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

በደንብ ቁጥር 120/1998 ተቋቁሞ የነበረው የአዳማ ዩንቨርስቲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለዩንቨርስቲው ተላልፈዋል፡፡

6. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 216/2003 ዓ.ም

## የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩንቨርስቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 216/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   1. አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡[4]
   3. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሠረት ይተዳደራል፡፡

3. **ዋና ግቢ**

   የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

4. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[4] ይህ ንዑስ አንቀፅ በ20/65 (2006) ደ.314 አንቀፅ 2 ተሻሻለ፡፡

## 4/ በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ስር የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች

## ደንብ ቁጥር 121/1998

## የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች

## ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995 አንቀጽ 8(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 121/1998" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995[5] ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለኮሌጁ እንደገና መቋቋም ፣ ዓላማ ፣ ሥልጣንና ተግባር

3. **እንደገና መቋቋም**

   1. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ "ኮሌጅ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
   2. የኮሌጁ ተጠሪነት ለአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ይሆናል፡

4. **ዓላማ**

   ኮሌጁ የሀገሪቱን ሲቪል ሰርቪስ የሙያና የአመራር አቅም ለማሳደግና የሥነ-ምግባር ደረጃ ለማሻሻል የሚረዱ፣

   1. የስልጠናና የትምህርት ፕሮግራሞችን ቀርጾ በተለያዩ የአቅርቦት ዘዴዎች የመስጠት፣

---

[5] በ15/64 (2002) አ. 650 ተሻረ፡፡

2. ምርምሮችን የማካሄድ ፣
3. የምክር አገልግሎቶችን የመስጠት፣
4. የሙያ መለኪያዎችን ማውጣትና የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ዓላማዎች ይኖሩታል።

5. **የኮሌጁ ስልጣንና ተግባር**

የአዋጁ አንቀጽ 14 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሌጁ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችና ልዩ የሆኑ የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ የትምህርት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ይሰጣል ፣
2. ምርምር ያካሂዳል የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
3. [6]
4. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋፅኦ የሚዳይ ሽልማትና ማዕረግ ይሰጣል፤
5. በሥሩ ኢንስቲትዩቶችን፣ ማዕከሎችንና ሌሎች የትምህርት፤ የምርምርና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ያቋቁማል ፣
6. የገቢ ማስገኛ ተቋሞችንና የገቢ ፈንድ ያቋቁማል ፣
7. በሀገሪቱ ውስጥና በሌሎች ሀገሮች ከሚገኙ አቻ ተቋሞችና ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ጋር ግንኙነት ይመሰርታል ፣
8. በኮሌጁ ውስጥ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል ፣
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል ፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
10. ዓላማውን ለማራመድ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኮሌጁ የፖሊሲና የስራ አስፈፃሚ አካላት

6. **ስለኮሌጁ አስተዳደር ቦርድ መቋቋም**

1. ተጠሪነቱ ለአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የሆነና በሚኒስትሩ የሚሾሙ ሰብሳቢና ስድስት ሌሎች አባላት ያሉት የኮሌጁ አስተዳደር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ተቋቁሟል፡፡

---

[6] ይህ ንዑስ አንቀፅ በ21/22(2007) ደ.332 አንቀፅ 33(ሀ) ተሽሯል፡፡

2. ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

7. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 35 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኮሌጁን ተልዕኮዎችና ጥቅሞች ያስጠብቃል፤
2. የኮሌጁን ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሹመት ያቀርባል፤
3. ኮሌጁ በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምርምር፣ በምክር አገልግሎትና በሙያ ሰርተፊኬት አሰጣጥ ረገድ የሚመራባቸውን አጠቃላይ ፖሊሲዎችና የውስጥ ደንቦችን ያወጣል፤
4. የኮሌጁ የሰው ሀይል፣ የቁሳቁስና የገንዘብ ምንጮች የመንግስት ፖሊሲዎችን መሰረት በማድረግ ለኮሌጁ ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፤
5. የኮሌጁን አደረጃጀት ይወሰናል፣
6. የኮሌጁን የገቢ ምንጭ በተመለከተ አጠቃላይ አቅጣጫዎችን ይነድፋል፡፡
7. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የኮሌጁን ኦዲተር ይሰይማል፣ ያገልግሎቱን ክፍያም ይወሰናል፤
8. በኮሌጁ ውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ መኖሩን ያረጋግጣል፤
9. ለኮሌጁ ሠራተኞች የሚሰጡ ከፍተኛ መጠሪያዎችን ወይም ማዕረጎችን በኮሌጁ የውስጥ ደንብ መሠረት ያፀድቃል፤
10. የኮሌጁን ስትራቴጂካዊና ዓመታዊ ዕቅዶችን ያፀድቃል፣ በጀቱን ለመንግሥት ያቀርባል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤
11. የአዋጁ አንቀጽ 35/7/ እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሌጁን የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤
12. የኮሌጁን ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

8. <u>የኮሌጁ ሴኔት መቋቋም</u>

ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ የሆነ የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የኮሌጁ ሴኔት ተቋቁሟል፡-

1. የኮሌጁ ፕሬዚዳንት .......................... ሰብሳቢ
2. የኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች.................... አባላት

3. የተቋማት ፣ የማዕከላት እና የድህረ ምረቃ ትምህርት
   ቤት ዳይሬክተሮች ..............................................አባላት
4. የህዝብ ግንኙነትና የገበያ ጥናት መኮንን ......................አባል
5. የዕቅድና ሥራ አመራር ደጋፊ ክፍል ዳይሬክተር .......... አባል
6. የቤተ መጻሕፍትና የኢንፎርሜሽን ኃላፊ ......................አባል
7. ሬጅስትራር ........................................................... አባል
8. የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር ............................አባል
9. የካሪኩለምና ፔዳጎጂካል ማዕከል ኃላፊ .........................አባል
10. በእያንዳንዱ ተቋም፣ ማዕከል ወይም የድህረ ምረቃ ትምህርት
   ቤት የሚወከሉ አንድ አንድ የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካዮች.......አባላት
11. ሁለት የተማሪዎች ተወካይ ............................................. አባላት
12. የሴቶች የስራ አመራር ማዕከል ኃላፊ .............................. አባል
13. የሰራተኞች ተወካይ ....................................................... አባል

9. <u>ስለኮሌጁ ሴኔት ሥልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 37 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዕቅዶችና በጀት ላይ ውይይት ያደርጋል፣ በፕሬዚዳንቱ አማካኝነት ለቦርዱ ያቀርባል፤
2. የቦርዱ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተማሪዎች አስተዳደር ፣ በትምህርት ፣ በሰው ኃይል ልማትና መሻሻል እንዲሁም ዲሲፕሊንን በሚመለከቱ ጉዳዮች የአካዳሚክ መመሪያዎች ያወጣል፤
3. በኮሌጁ የሚሰጡ የስልጠና፣ የትምህርት፣ የምርምርና የምክር አገልግሎቶች አግባብነትና ጥራት ያላቸው መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
4. በማደግ ላይ ያሉ ክልሎች፣ የሴት፣ የአካል ጉዳተኞች የጎልማሳ ተማሪዎችን ምልመላ፣ ቅበላና ማቆየት የሚመለከቱ የድጋፍ መንገዶችን ያመቻቻል፤
5. ለጎልማሶችና የሙያ ልምድ ላላቸው ተማሪዎች የሚያገለግል ልዩ የቅበላ ሥርዓት ያወጣል፤
6. የቦርዱ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የተማሪዎችን ቅበላ፣ ማቋረጥና መልሶ ቅበላን የሚመለከቱ መመዘኛዎችን ያወጣል፤

7. የትምህርት መለኪያዎችን በተለይም የፈተናዎች ዓይነትና ዘዴዎች መስፍርቶችን ይወስናል፤

8. በትምህርት መለኪያዎቹ መሠረት ዲግሪዎች፣ ዲፕሎማዎችና የምስክር ወረቀቶች እንዲሁም ሌሎች ሽልማቶች የሚሰጡበትን ሁኔታ ይወስናል፤

9. በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሌክቸረር፣ የረዳት ሌክቸረር፣ የረዳት ምሩቅና የቴክኒክ ረዳቶች ዕድገት በአካዳሚክ ኮሚሽኖች ሲቀርብለት ውሳኔ ይሰጣል፤

10. በኮሌጁ ውስጥ ከፍተኛ የማዕረግና የትምህርት እድገት እንዲሁም ሌሎች የኮሌጁ የክብር ማዕረጎች እንዲሰጡ ለቦርዱ ያቀርባል።

11. አዳዲስ የትምህርት መርሃ ግብሮች በኮሌጁ ውስጥ እንዲጀመሩ ያደርጋል፤ የኮሌጁን ተቋማት ውህደት በተመለከተ የቀረበ ሃሣብን መርምሮ ያፀድቃል፤

12. የኮሌጁን ተቋማት፣ የማዕከላትና የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ካሪኩለሞችን መርምሮ ያፀድቃል፤

13. የራሱን የስብሰባ ስርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

10. <u>ስለኮሌጁ ሥራ አስፈጻሚዎች</u>

1. ኮሌጁ አንድ ፕሬዚዳንትና ሁለት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይኖሩታል፡፡
2. ፕሬዚዳንቱ እንዲሁም ምክትል ፕሬዚዳንቶቹ በቦርዱ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማሉ።

11. <u>የፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 40 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፕሬዚዳንቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለኮሌጁ አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፣ ኮሌጁ ቀልጣፋና ውጤታማ እንቅስቃሴ ሊኖረው በሚያስችል መልኩ ስራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. ለኮሌጁ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል፣ የኮሌጁን ጥቅም ያስጠብቃል፤
3. የኮሌጁን የልዩ ልዩ የስራ ዘርፍ ዳይሬክተሮችን፣ ምክትል ዳይሬክተሮችንና ሌሎች ኃላፊዎችን ይመድባል፤
4. የኮሌጁን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

12. <u>የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 41 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኮሌጁ የሥልጠና ፣ የትምህርት ፣ የምርምርና የምክር አገልግሎት ስራዎች አግባብነታቸውንና ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አስፈላጊውን መንገድ ይቀይሳል ፣ ይከታተላል፤
2. የአካዳሚክ ሰራተኞች ሙያቸውን በማሳደግ ልቀው እንዲገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
3. ለኮሌጁ የአካዳሚክ ሰራተኞችና ተማሪዎች በመማር ማስተማር፣ በምርምር እና በምክር አገልግሎት ተግባራት ዙሪያ ምቹ ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤
4. የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር ያፀድቃል፤
5. በኮሌጁ የሚከናወኑ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ስራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤
6. እቅዶችንና የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፣ የእቅዶቹን አፈጻጸም ይከታተላል፡፡

13. <u>የልማትና አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር</u>

የአዋጁ አንቀጽ 41 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የልማትና አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፣

1. የኮሌጁን ተልዕኮና አላማዎች ለማሳካት ቀልጣፋና ዘመናዊ የሆነ አስተዳደራዊ ስራ የሚከናወንበትን ምቹ ሁኔታ ዘላቂ በሆነ መንገድ እንዲፈጠር ያደርጋል፤
2. የኮሌጁ ዓላማ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኮሌጁ የገቢ ምንጭ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን መንገድ ይቀይሳል፤
3. የኮሌጁ የአስተዳደር አገልግሎት አሠጣጥ ደረጃዎችና አሠራሮች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ ያጎለብታል፤
4. የኮሌጁ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የላቀ የሥራ አፈጻጸም እንዲኖራቸው መንገድ ይቀይሳል፤
5. የኮሌጁን የአስተዳደርና ፋይናንስ ጉዳዮችና የኢንፍራስትራክቸር ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
6. እቅዶችንና የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል ፣ የእቅዶቹን አፈጻጸምም ይከታተላል፡፡

## 14. ስለአካዳሚክ ኮሚሽኖች መቋቋም

1. በእያንዳንዱ ኢንስቲትዩት፣ ማዕከል ወይም ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአካዳሚክ ኮሚሽን ይቋቋማል፡፡
2. የአካዳሚክ ኮሚሽኑ ተጠሪነት እንደአግባቡ ለኢንስቲትዩቱ ለማዕከሉ ወይም ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

   ሀ/ የኢንስቲትዩቱ፣ የማዕከሉ ወይም የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ............................................... ሰብሳቢ

   ለ/ ምክትል ዳይሬክተሩ ........................... አባል

   ሐ/ በኢንስቲትዩቱ፣ በማዕከሉ ወይም በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱ የሚገኙ የክፍል ኃላፊዎች ...............................አባላት

   መ/ የአካዳሚክ ሠራተኞች ተወካይ ........... አባል

   ሠ/ የተማሪዎች ተወካይ ........................... አባል

   ረ/ የሴት ተማሪዎች ተወካይ .................... አባል

   ሰ/ የኢንስቲትዩቱ፣ የማዕከሉ ወይም የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱ የተከታታይ ትምህርት አስተባባሪ ...............................አባል

## 15. ስለአካዳሚክ ኮሚሽኖች ሥልጣንና ተግባር

የኮሌጁ ቦርድ፣ ሴኔት፣ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የአካዳሚክ ኮሚሽን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የኢንስቲትዩቱን፣ የማዕከሉን ወይም የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱን እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡
2. የሥልጠናና የትምህርት መርሃ ግብሮችን ሥርዓተ ትምህርቶች ያዘጋጃል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
3. የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር ይመረምራል ፣ እንዲጸድቅም ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት ያቀርባል፡፡
4. በኢንስቲትዩቱ፣ በማዕከሉ ወይም በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱ ሠራተኞችና ተማሪዎች ወስጥ የሙያ ክብርና የሥነ-ምግባር መለኪያዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚያድጉበትን ሁኔታ ያስፋፋል።

5. የመምህራንና የቴክኒክ ረዳቶችን ዕድገትና ማዕረግ ለኮሌጁ ሴኔት አቅርቦ ያስወስናል፡፡
6. በኮሌጁ ዓላማዎች መሠረት የፕሮግራሞችና አገልግሎቶች አግባብነትና ጥራት ቀጣይነት ባለው ሂደት ከፍላጎት ጋር እየተመዛዘነ የሚሄድበትን ሁኔታ ያጎለብታል፡፡
7. በኢንስቲትዩቱ፣ በማዕከሉ ወይም በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ብቃታቸውን ያስመሰከሩ ዕጩዎችን በመለየት ዲግሪ፣ ዲፕሎማ ፣ የምስክር ወረቀት ወይም ሌሎች ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሽልማቶች እንዲያገኙ ለኮሌጁ ሴኔት በማቅረብ ያስጸድቃል፡፡
8. በማደግ ላይ ያሉ ክልሎች ሴቶችና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡
9. ከኮሌጁ ሴኔትና ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡
10. የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

16. <u>ሌሎች የኮሌጁ አካላት</u>

ቦርዱ በዚህ ደንብ ከተመለከቱት ውጭ ያሉ አካላትን ማቋቋም እና ሥልጣንና ተግባራቸውን መወሰን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለገቢ አመንጪ ድርጅትና ስለገቢ ፈንድ
### ንዑስ ክፍል አንድ
### ስለ ገቢ አመንጪ ድርጅት

17. <u>ስለድርጅት መቋቋም</u>

ተጠሪነቱ ለኮሌጁ የልማትና አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት የሆነ የኮሌጁ ገቢ ማስገኛ ሥራዎችን የሚመራ የኮሌጁ አካል (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) ተቋቁሟል፡፡

18. <u>የድርጅቱ ካፒታል</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 49 እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥት የፋይናንስ ሕጎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ቦርዱ የድርጅቱን ካፒታል ሊወስን ይችላል፡፡

2. የአዋጁ አንቀጽ 49 እንደተጠበቀ ሆኖ ከኮሌጁ አካዳሚያዊና አካዳሚያዊ ካልሆኑ አካላት የሚገኙ ገቢዎች የድርጅቱ ገቢዎች ይሆናሉ።

19. <u>የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የኮሌጁ የውስጥ ደንቦች እንደተጠበቁ ሆነው ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የማማከር አገልግሎት መስጠት፤
2. የኢንተርኔት ካፌና የኮምፒውተር አገልግሎት መስጠት፤
3. የመጽሐፍትና የሌሎች ሕትመቶች ሽያጭ አገልግሎት መስጠት፤
4. ያሉትን መሣሪያዎችና መገልገያዎች ማከራየት፤
5. ሌሎች ተመሳሳይ የገቢ ማስገኛ አገልግሎቶችን መስጠት፡፡

20. <u>የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፡-

1. ድርጅቱን ይመራል ፤ያስተዳድራል፤
2. ለድርጅቱ የተመደቡ የኮሌጁን ሠራተኞች በኮሌጁ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ያስተዳድራል፤
3. የድርጅቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ በኮሌጁ ፕሬዝዳንት በኩል ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. በኮሌጁ ስም ለድርጅቱ የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፤
5. የፈንዱ የፋይናንስና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ከአገሪቱ የፋይናንስ ሕጎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፣
6. ከድርጅቱ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

21. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

ሥራ አስኪያጁ የድርጅቱን የፋይናንስ መግለጫና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት የድርጅቱ የበጀት ዓመት ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለኮሌጁ የልማትና አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ማቅረብ አለበት፡፡

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለገቢ ፈንድ</u>

22. <u>መቋቋም</u>

ዓላማውና የገቢ ምንጩ በአዋጁ አንቀጽ ከ53 እስከ 55 በተገለጸው መሠረት የሆነ የኮሌጁ ፈንድ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## 23.የፈንዱ አካላት

1. ፈንዱ፡-

ሀ/ የፈንዱ አስተዳደር ቦርዱ (ከዚህ በኋላ "የፈንዱ ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ)፣ እና

ለ/ ሴክሬታሪያት፣

ይኖረዋል።

2. የፈንዱ ቦርድ ተጠሪነቱ ለኮሌጁ ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡

## 24. የፈንዱ ቦርድ አባላት

1. የፈንዱ ቦርድ በኮሌጁ ፕሬዚዳንት የሚሰየሙ አምስት አባላት ይኖሩታል።
2. የፈንዱ ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡
3. የፈንዱ ቦርድ አባላት በማናቸውም ሁኔታ ሥራቸውን መሥራት ካልቻሉ በምትካቸው አዲስ አባላት ይሰየማሉ።

## 25. የፈንዱ ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የፈንዱ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፈንዱ ዓላማዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣ ለአፈጻጸማቸው አስፈላጊውን መመሪያ ያወጣል፤
2. ከልዩ ልዩ የፈንዱ ምንጮች የተገኙ ገቢዎች በተገቢ ሁኔታ ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ በሴክሬታሪያቱ የሚቀርብለትን ሪፖርት መርምሮ ያጸድቃል፤
3. የፈንዱ ገቢዎች በየጊዜው መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፤
4. ስለሥራው ለኮሌጁ ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤
5. ለፈንዱ ዓላማ መሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 26. የፈንዱ ቦርድ ስብሰባዎች

የፈንዱ ቦርድ ስብሰባዎች የሚካሄዱበት ሁኔታና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ቦርዱ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 27. የሴክሬታሪያቱ ሥልጣንና ተግባር

ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ዓመታዊ በጀት፣ የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ መግለጫ ሪፖርቶችን ለፈንዱ ቦርድ አቅርቦ ያጸድቃል፤

2. በፈንዱ ድጋፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን ይመረምራል፣ በፈንዱ ቦርድ መመሪያ መሠረት የፕሮጀክቶቹን የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ይፈቅዳል።

3. ለፈንዱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ያጠናል፤

4. የፈንዱን ቦርድ የሥራ መዛግብት፣ ዘገባዎችና የስብሰባ ቃለ ጉባዔዎችን ይይዛል፣ የፈንዱ ቦርድ ውሳኔዎች በትክክል መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

5. በፈንዱ ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

28. <u>የሴክሬታሪያቱ ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

የፈንዱ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ፈንዱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለፈንዱ ቦርድ ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀጽ 27 የተመለከቱትን የሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

29. <u>የተሻሩ ሀጎች</u>

1. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 23/1988 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

2. ይህን ደንብ የሚቃረኑ ሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

30. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 5/ በመከላከያ ሚኒስቴር ስር የሚገኝ የትምህርት ተቋም ማቋቋሚያ ህግ

## ደንብ ቁጥር 68/1993

## የሀገር መከላከያ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሀገር መከላከያ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 68/1993" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

   1. "መንግስት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ነው፤
   2. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት የተቋቋመው የዩንቨርስቲ ኮሌጁ ቦርድ ነው፤
   3. "ጉባኤ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 መሠረት የተቋቋመው የዩንቨርስቲ ኮሌጅ ጉባኤ ነው፤
   4. "የአካዳሚክ ሰራተኛ" ማለት በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ ሰራተኛ ነው፤
   5. "ኮማንዳንት" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 መሠረት የሚሾም የዩንቨርስቲ ኮሌጁ የበላይ ሃላፊ ነው፤
   6. "ዩንቨርስቲ ኮሌጅ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመው የመከላከያ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነው፡፡

3. **መቋቋም**

1. የመከላከያ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ወደፊት በቦርዱ የሚቋቋሙ ፋኩልቲዎችና ኮሌጆችን ያካትታል፡፡
3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተጠሪነት ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ዕውቀትን ማዳበር፣ ማስፋፋትና ማስተላለፍ፤
2. ለመከላከያ ሠራዊት ደረጃውን የጠበቀ የምሕንድስና፣ የሕክምና፣ የማኔጅመንት፣ የወታደራዊ ሣይንስና፣ ሌሎች ትምህርት መስጠት፤
3. በልዩ ልዩ ሙያ ላይ ለተሰማሩ የሠራዊቱ አባላት የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መስጠት፤
4. በቴክኒክ በጤናና በአስተዳደር ባለሙያዎችን የሚያሰለጥኑ የመከላከያ የትምህርት ተቋሞች የሚሰጡት ትምህርት ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ሙያዊ እገዛ ማድረግ፤
5. የአገር መከላከያ ሠራዊት የሚታጠቃቸው እና የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎችን በተመለከተ እንዲሁም በመከላከያ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ጥናት ማካሔድና ሃሳብ ማቅረብ፤
6. በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙ የቴክኒክ፣ የጤናና የአስተዳደር ሙያዎችንና ሙያተኞችን የሥራ መደብና ደረጃ መለየት፡፡

5. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥልጣንና ተግባር፤</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. ፋኩልቲዎች፣ ዲፓርትሜንቶችንና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ክፍሎች ወይም ተቋማት ማቋቋምና ማካሄድ፤
2. የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራም መንደፍና ስራ ላይ ማዋል፤
3. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋጽኦ የአካዳሚክ ሜዳልያ ሽልማትና ማዕረግ መስጠት፤
4. ሴሚናሮች፣ ወርክሾፖችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀትና ማካሄድ፤

5. የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

6. በሀገር ውስጥና በሌሎች ሀገሮች ከሚገኙ አቻ የትምህርት ተቋሞች፣ የምርምር ተቋሞችና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ጋር ግንኙነት መመሥረት፤

7. የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦች ማቋቋምና ማሰራጨት፤

8. የንብረት ባለቤት የመሆን፤

9. ውል የመዋዋል፤

10. በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

11. ዓላማውን የሚያራምዱ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለ ዩኒቨርስቲ ኮሌጁ የፖሊሲና የሥራ አስፈፃሚ አካላት**

6. **ስለ ዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ቦርድ መቋቋም**

   1. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በመከላከያ ሚኒስቴር የሚሰየሙ አንድ ሊቀመንበርና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን አባላት የሚገኙበት ቦርድ ይኖረዋል።

   2. ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

7. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

   ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   1. ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በተገናዘበ መልኩ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አጠቃላይ የአካዳሚክና የአስተዳደር ፖሊሲ ያወጣል ያስፈፅማል፤

   2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አደረጃጀት ይወስናል፤

   3. ተባባሪ ፕሮፌሰርና የፕሮፌሰር ማዕረግ ያፀድቃል፤

   4. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን እቅድና በጀት ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር አቅርቦ ያስፀድቃል፤

   5. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ሁኔታ የሚወስን የውስጥ አስተዳደር ደንብ ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በማገናዘብ ያወጣል፤

   6. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች መንግስት ባፀደቀው መመሪያ መሰረት ይወስናል፤

   7. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ከሦስተኛ አካል ጋር የሚያደርገውን ስምምነት ያፀድቃል፤

8. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን በሚመለከት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ወይም ማንኛውም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
9. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓርማ ያፀድቃል፣
10. የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይወስናል፤
11. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

8. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤ መቋቋም</u>

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባኤ ተቋቁሟል፡-
   ሀ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት .................... ሰብሳቢ
   ለ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች..... አባላት
   ሐ/ የየፋኩልቲ ወይም የየኮሌጁ ዲኖች................አባላት
   መ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሬጅስትራር ................. አባል
   ሠ/ የምርምር ዳይሬክተር ................................ አባል
   ረ/ የሚሊተሪ ሳይንስ ፕሮግራም ዳይሬክተር........ አባል
   ሰ/ ከየፋኩልቲው ወይም ከየኮሌጁ የተመረጡ አንዳንድ የመምህራን ተወካይ ......... አባላት
   ሸ/ የተማሪዎች ካውንስል ተወካይ ..................... አባል
2. ጉባኤው የራሱ ፀሀፊ ይኖረዋል፡፡
3. የጉባኤው ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡

9. <u>የጉባኤው ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚያወጣው አጠቀላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጉባኤው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአካዳሚክ ጉዳዮችን እና የሥልጠና ፕሮግራሞችን ይወስናል፤
2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥርዓተ ትምህርት መሻሻልን አስመልክቶ ከዲንስ ካውንስል የሚቀርቡ ሃሳቦችን መርምሮ ያፀድቃል፤
3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የትምህርት ካሌንደር መርምሮ ያፀድቃል፤
4. ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መምህራን በዲንስ ካውንስል ሲቀርብለት እስከ ረዳት ፕሮፌሰር የአካዳሚክ ማዕረግ ይሰጣል፣ ከረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ በላይ መርምሮ የውሣኔ ሃሣብ ለቦርዱ ያቀርባል፤

5. የተማሪዎች አቀባበልን ፣ የትምህርት ደረጃ አወሳሰንን፣ የዲስፕሊን ጉዳዮችንና ምረቃን የሚመለከቱ መመዘኛ መስፈርቶችን ያወጣል፣ በነዚህም ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

6. አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥ አቅጣጫዎችን ይወስናል፤

7. ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመረቁ ተማሪዎች ዝርዝር መርምሮ ያፀድቃል ፣ ሚዳይና ሽልማት የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፤

8. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች እንዲወሰን ለቦርዱ ሃሳብ ያቀርባል፤

9. በየሴሚስተሩ ቢያንስ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ፤

10. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

10. <u>**የአመራር ኮሚቴ መቋቋም**</u>

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አመራር ኮሚቴ ይቋቋማል፡-

ሀ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት ............. ሰብሳቢ

ለ/ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ............. አባል

ሐ/ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት .. አባል

መ/ የኮማንዳንቱ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ............ ፀሐፊ

2. የአመራር ኮሚቴው ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡

11. <u>**የአመራር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር**</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓላማ መሠረት ያደረገ እቅድ ያወጣል፣ በጀት ያዘጋጃል፣ ሥራዎች በእቅዱ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

2. የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር መርምሮ ያፀድቃል፤

3. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚሰጥ ሥልጠናን ለመጠበቅና ለማሳደግ የቲዮሪ እና የተግባርን ውህደትና ሚዛን ያስጠብቃል፣ ሥልጠናው ከመከላከያ ተጨባጭ ፍላጎት እና ከሠራዊቱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እድገት ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፤

4. የመምህራንን ብቃትና ጥራት ያረጋግጣል፣ የትምህርት መረጃዎችን ያሟላል፣ ዙሪያ መለስ ድጋፍ ይሰጣል፤

5. የመከላከያና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች እንዲከበሩና እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ የስልጠና ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ያወጣል፤
6. የጥናት፣ የምርምርና የፈጠራ ሥራዎችን በስፋትና በጥራት ለማካሄድ መምህራን በጋራና በግል እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ አመቺ ሁኔታም ያመቻቻል፤
7. አዲስ ለሚገቡ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎች የሚቀመጡ መመዘኛዎች እንደአስፈላጊነቱ ይመረምራል፣ ያሻሽላል፤
8. የተማሪዎችን የሙያ ምርጫና ምደባ ከወቅቱ የመከላከያ ፍላጎት ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል፤
9. ከመሰል ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነትና የልምድ ልውውጥ ያበረታታል፤
10. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በአወቃቀር፣ በሰው ኃይልና በአሰራር ብቃቱን እያረጋገጠ እንዲሄድ ቀጣይ ጥረት ያደርጋል፡፡

12. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሹመትና ተጠሪነት</u>

1. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት በመንግሥት ይሾማል፤ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡፡
2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ተጠሪነታቸው ለኮማንዳንቱ ሆኖ በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማሉ፡፡

13. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መሪና አስፈፃሚ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የሥራ እቅድ እንዲወጣ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በጀት በወቅቱ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው ባለሥልጣን አቅርቦ ያስፈቅዳል፣ ስለአፈጻጸሙም ክትትል ያደርጋል፤
4. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚሰጡ ትምህርቶች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
5. የምርምር ሥራዎች እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

6. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚደረጉ ምርምሮች በአብዛኛው የሠራዊቱን ተልዕኮ የሚያሳኩ እንዲሆኑ ይጥራል፤
7. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በሰው ኃይልና በማቴሪያል እንዲሟላ ጥረት ያደርጋል፤
8. ወደ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ለሚገቡ ተማሪዎች ተገቢው የመመልመያ መመዘኛዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይቆጣጠራል፤
9. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ስም የሚደረጉ ማናቸውንም ስምምነቶች እና ሰነዶች ይፈርማል፤
10. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ስም የባንክ ሂሣብ እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤
11. የመከላከያ እቅዶችን፣ የመከላከያና የዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ደንቦችና መመሪያዎች በተገቢው መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፤
12. ስለ ዩንቨርስቲ ኮሌጁ የስራ እንቅስቃሴ ለቦርዱ በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል፤
13. ተማሪዎች ትምህርታቸውን በትጋትና በብቃት እንዲከታተሉና ተመርቀውም ለሰራዊቱ ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ሁለገብ የግንባታ ሥራ በብቃት እንዲካሄድ ያደርጋል፤
14. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም በየወቅቱ መገምገሙንና የግምገማው ውጤትም በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፤
15. የአሰተዳደራዊ ጉዳዮችን በመመሪያው መሰረት መፈፀማቸውን ይቆጣጠራል፡፡

14. **<u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአካዳሚኩን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ የዲንስ ካውንስሉን ይሰበስባል፡፡
2. የትምህርቱ፣ የምርምሩና የቴክኒክ አገልግሎቱ በሚገባ እንዲካሄድ ያስተባብራል፣ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ድጋፍ ሰጪ አካላት ለትምህርቱ እንቅስቃሴ ድጋፍ መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥርዓተ ትምህርት ደረጃ መጠበቁን ያረጋግጣል፣ የማሻሻያ ሐሳብ ያቀርባል፣ የመማር ማስተማር ሂደት ጥራት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤
4. መጽሐፍት፣ የማስተማርያ ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች ለትምህርቱ ተግባር መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

5. አዳዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች እንዲጀመሩ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነቱንም ይቆጣጠራል፤

6. የተማሪዎችን የትኩረት መስክ ምርጫ ያስተባብራል፤

7. ፈተናና የፈተና ውጤትን አስመልክቶ በየትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ከየፋኩልቲው የሚቀርቡ ዘገባዎችን እየገመገመ ከአስተያየት ጋር ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት ያቀርባል፤

8. የመምህራን ቅጥርን፣ ኮንትራት ማደስንና የደረጃ ዕድገትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን እየመረመረ ለዩኒቨርስቲው አመራር ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣ የመምህራንን የኮንትራት ቅጥር ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ወክሎ ይፈርማል፤

9. የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ዝግጅትና አቅርቦት፣ የበጀት ፍላጎትና አፈጻጸም እና የሰው ኃይል ፍላጎትን በተመለከተ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት ዘገባ ያቀርባል፤

10. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክ ሕጎችና ደንቦች በተገቢው ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

11. በየፋኩልቲው የሥራ አፈጻጸም ግምገማዎች መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፤

12. በሥሩ የሚገኙ ኃላፊዎችን የሥራ ብቃት ይገመግማል፤

13. በአካዳሚክ ጉዳዮችና ስብሰባዎች ላይ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ኮማንዳንት ያማክራል፣ ይወክላል፤

14. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

15. <u>የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለኮማንዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎችና የሠራዊት አባላት ሕገመንግሥታዊ ግንዛቤያቸው እንዲጐለብትና በፀና እምነት ላይ ተመሥርተው ተልዕኮአቸውን በብቃት እንዲወጡ የሚያስችል የልማት ሥራዎችን ይሠራል፤

2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ማህበረሰብ የዜግነትና የሙያ ግዴታውን በጠንካራ እምነትና ፍላጎት እየተወጣ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ተልዕኮ በብቃት እንዲያሳካ ዙሪያ መለስ አመራር ይሰጣል፣ የቅርብ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይህንን ተልዕኮ ለማገልገል የሚቋቋሙ መዋቅሮች ያጠናክራል፡፡

3. የመከላከያ እና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ደንቦች መመሪያዎችና ፖሊሲዎች በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ማህበረሰብ በተለይም በተማሪዎች እንዲታወቁና እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

4. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የሰው ኃይል ፍላጎት መንግሥት ባፀደቀው አቋም መሠረት መሟላቱን ያረጋግጣል፣ የሠራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ ሹመት፣ ስንብትና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች በደንቦችና በመመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣ ሠራተኞች መብታቸው ተከብሮላቸው ግዴታቸውን እንዲወጡ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

5. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎችና የሠራዊት አባላት የሚሊታሪ ሳይንስና ጥበብ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር፣ የአካልና የሥነልቦና ዝግጁነታቸው እንዲረጋገጥ የተ ገነባውን የካዴት ሥልጠና ፕሮግራም በቅርብ ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፤

6. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ማህበረሰብ በአጠቃላይና በተለይም በተማሪው አካልን የሚገነቡና አእምሮን የሚያዝናኑ ደረጃን የጠበቁ ስፖርታዊ ፕሮግራሞች እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡

7. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁንና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ማህበረሰብ ፀጥታና ደህንነት እንዲሁም ንብረት የሚያስጠብቅ ሥርዓት እንዲኖርና እንዲጎለብት ተገቢውን አመራር ይሰጣል፤

8. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ንብረት በመንግሥት መመሪያ መሠረት ያስተዳድራል፣ ለመማር ማስተማር ሂደት የሚደግፍ የማቴሪያል አቅርቦት መኖሩን ያረጋግጣል፣ የካንፓስ ሕንፃዎች ግንባታና እንክብካቤ ያሰተባብራል፣ የካንፓስ ልማትና ዕድገት ይከታተላል፤

9. ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ማህበረሰብ የሚያስፈልጉ የጤና፣ የተማሪዎች የምግብ ፣ የትራንስፖርት ድጋፍ እንዲሁም ለማህበረሰቡ የሚያስፈልጉ ሌሎች አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

10. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የፋይናንስ አቅም የሚያሳድግና የመንግሥትን መደበኛ ወጭ ሳይጨምር ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል የልዩ ገቢ ምንጭ ያስፋፋል፣ ገቢውን በአግባቡ ያስተዳድራል፤

11. የአስተዳደርና ሪሶርስ በጀትና ዕቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ የዘርፉን የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ግምገማዎች ያካሂዳል፣ ሪፖርት ያቀርባል፤

12. በአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ላይ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ኮማንዳንት ያማክራል፤

13. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ኮማንዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

16. <u>የዲንስ ካውንስል መቋቋም</u>

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የዲንስ ካውንስል ይቋቋማል፡-

   ሀ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት .......... ሰብሳቢ

   ለ/ የፋክልቲ ዲኖች ........................................................አባላት

   ሐ/ ሬጂስትራር ..............................................................አባል

   መ/ የላይብራሪ ኃላፊ .......................................................አባል

2. ካውንስሉ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

3. የዲንስ ካውንስሉ ተጠሪነት ለሴኔት ይሆናል፡፡

17. <u>የዲንስ ካውንስል ሥልጣንና ተግባር</u>

የዲንስ ካውንስል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሥርዓተ ትምህርት መሻሻልን አስመልክቶ ከፋኩልቲዎች የሚቀርቡ ሃሳቦችን ይመረምራል፣ የፕሮግራም ለውጥ የማያስከትሉ የክሬዲት ሰዓቶችና የኮርስ መግለጫዎችን ማሻሻያዎች ያጸድቃል፣ የፕሮግራም ለውጥ የሚያስከትሉ ለውጦችን አስመልክቶ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባዔ ሀሳብ ያቀርባል፤

2. የተማሪዎችን የሙያ ምርጫ እና ምደባ መስፈርት ለዩንቨርሲቲ ኮሌጁ አመራር ኮሚቴ ሃሣብ ያቀርባል፤

3. የዩንቨርሲቲ ኮሌጁ የትምህርትና ምርምር መመሪያዎች እንደአስፈላጊነቱ፣ ያወጣል፣ ለአመራር ኮሚቴ አቅርቦ ያስፀድቃል፣ በትክክል በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

4. ለአካዳሚክ ሠራተኞች የማዕረግ እድገት እንዲሰጥ ለዩንቨርሲቲ ኮሌጁ ጉባዔ ሃሳብ ያቀርባል፤

5. ከየፋኩልቲዎቹ የሚቀርቡ የምርምር ጥያቄዎችን ይመረምራል፣ ለአመራር ኮሚቴው ሃሳብ ያቀርባል፣ በደንቡ መሠረት እንዲፈጸም ይከታተላል፤

6. የፈተና አሰጣጥንና የተማሪዎች የፈተና ውጤትን ለጉባኤው ያሳውቃል፤

7. ለዲንስ ካውንስሉ ውሣኔ የሚረዱ ጥናቶችን ያስጠናል፣ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

8. ማንኛውንም የአካዳሚክ ሠራተኛ በአስረጅነት ይጠራል፤

9. በየወሩ ይሰበሰባል፣ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎች ሊያደርግ ይችላል፡፡

18. <u>የአካዳሚክ ኮሚሽን መቋቋም</u>

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የአካዳሚክ ኮሚሽን በእያንዳንዱ ፋኩልቲ ይቋቋማል፡-

ሀ/ የፋኩልቲው ዲን ...................................... ሰብሳቢ

ለ/ የፋኩልቲው ረዳት ዲን ................................ አባል

ሐ/ የዲፓርትመንት ኃላፊዎች ........................ አባላት

መ/ ከፋኩልቲ የተመረጡ ሶስት ተወካዮች ...... አባላት

ሠ/ ከሦስቱ ተወካይ መምህራን አንዱ አባልና ፀሐፊ

ረ/ ከነዚህ ውጪ እንደ አስፈላጊነቱ በዲኑ ጥሪ ሌሎች የፋኩልቲ አባላት ሊሳተፉ ይችላሉ፣ ሆኖም ድምጽ መስጠት አይችሉም።

2. የአካዳሚክ ኮሚሽኑ ተጠሪነት ለዲንስ ካውንስል ይሆናል።

19. <u>የአካዳሚክ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር</u>

የአካዳሚክ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፋኩልቲውን አካዳሚክ ጉዳዮች በተመለከተ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ላይ ሃሳብ ያቀርባል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ሲፀድቅ ዝርዝር ፕሮግ ራሞች መውጣታቸውንም ያረጋግጣል፣ ተግባራዊ መሆናቸውንም ይከታተላል፤

2. የሥርዓተ ትምህርት መሻሻልን አስመልክቶ ከዲፓርትመንቶች የሚቀርቡ ሃሳቦችን ይመረምራል፣ የውሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የትምህርትና የምርምር ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

4. የመምህራን የአካዳሚክ ማዕረግ እንዲሰጥ ለዲንስ ካውንስል ሃሳብ ያቀርባል፤

5. የምርምር ተግባራት እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ከየዲፓርትመንቱ የሚቀርቡ የምርምር ጥያቄዎችን በመመርመር ለዲንስ ካውንስል ሃሣብ ያቀርባል፤

6. የፈተና አሰጣጥንና የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ይገመግማል፤

7. ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመረቁ ተማሪዎች ዝርዝር መርምሮና አፅድቆ ለዲንስ ካውንስል ያቀርባል፤

8. በፋኩልቲው የሚሰጡ ኮርሶች ትምህርት አሰጣጥ፣ የትምህርት መርጃዎችና መምህራን ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል፤

9. እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ የአካዳሚክ ሥራዎችን የሚሠሩ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤

10. ማንኛውንም የአካዳሚክ ሠራተኛ በአስረጅነት ይጠራል፤

11. በሴሚስተር ሶስት ጊዜ ይሰበሰባል፣ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎች ሊያደርግ ይችላል።

20. <u>የፋኩልቲ ዲኑ ስልጣንና ተግባር፣</u>

የፋኩልቲ ዲኑ ተጠሪነቱ ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዲፓርትመንቱ የሚሰጡ ትምህርቶችና የሚካሄዱ ምርምሮች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
2. በዲፓርትመንቶች መካከል የሥራ ግንኙነት እንዲዳብርና እንዲጠነክር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
3. በዲፓርትመንቶች አዳዲስ ፕሮግራሞች እንዲጀመሩ ተፈላጊውን ጥናት ያደርጋል፤
4. የተማሪዎች የትኩረት መስክ ምርጫ ያስተባብራል፤
5. ዲፓርትመንቶች በጋራና በተናጠል የሚሰጧቸውን ፈተናዎች ደረጃ ይገመግማል፤
6. ከየዲፓርትመንቶች የሚቀርቡ የበጀት ጥያቄዎችን ይመረምራል፣ ከአስተያየት ጋር ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤
7. የዲፓርትመንቶችን ዓመታዊ ዕቅድ ይመረምራል፣ ስለዕቅዱም አፈጻጸም ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤
8. የዲፓርትመንት ኃላፊዎችን የሥራ ብቃት ይገመግማል፣ ተግቢውን የደረጃ እድገትና የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኙ ጥያቄ ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
9. የመምህራን ግምገማ እንዲደረግ ያስተባብራል፣ የግምገማውንም ውጤት ለመምህራን ያሳውቃል፣ ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤
10. የአካዳሚክ ማዕረግ ማግኘት የሚገባቸውን መምህራን ለአካዳሚክ ኮሚሽን እያቀረበ ያስፀድቃል፣ ውጤቱንም ለዲንስ ካውንስል ያቀርባል፤
11. በአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

21. <u>የዲፓርትመንት ካውንስል መቋቋም</u>

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዲፓርትመንት ካውንስል ይቋቋማል፡-

ሀ/ የዲፓርትመንቱ ኃላፊ ..................... ሰብሳቢ

ለ/ የዘርፉ አስተባባሪዎች/ዘርፎች የሌሏቸው የዲፓርትመንት መምህራን በሙሉ..............አባላት

ሐ/ ከአስተባባሪዎቹ (ከመምህራንን) መካከል የሚመረጥ ......... አባልና ፀሐፊ

2. የዲፓርትመንቱ ካውንስል ተጠሪነቱ ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ ይሆናል፡፡

22.<u>የዲፓርትመንት ካውንስል ስልጣንና ተግባር፤</u>

የዲፓርትመንት ካውንስል የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ በዲፓርትመንቱ የሚሰጡ ኮርሶች ደረጃና ብቃት፣ የመምህራን ደረጃና ብቃት፣ በዲፓርትመንቱ የተመደቡ ተማሪዎችን የአካዳሚክ ብቃት ይመረምራል፣ ያረጋግጣል፤
2. በዲፓርትመንቱ የሚሰጡ ኮርሶችን ብቃት ይመረምራል፣ ያረጋግጣል፣ ነባር ኮርሶች የሚገመገሙበትን ሥርዓት ያወጣል ፣ አስፈላጊነታቸውንም ያረጋግጣል፣ መሻሻል የሚገባቸውን በዲፓርትመንቱ ኃላፊ በኩል ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
3. ለመቀጠር የሚፈልጉ መምህራንን የትምህርት ደረጃና የትምህርት ትኩረት መስክ እየመረመረ በዲፓርትመንት፣ ኃላፊው አማካኝነት ለፋኩልቲው ዲን ያቀርባል፤
4. በዲፓርትመንቱ የሚያስተምሩ መምህራን የማዕረግ ዕድገት ጥያቄ ይመረምራል፣ በዲፓርትመንት ኃላፊው አማካኝነት ለፋኩልቲ ዲን ሃሳብ ያቀርባል፤
5. በዲፓርትመንቱ መምህራን የሚዘጋጁ የግማሽ ሴሚስተርና የሴሚስተር ፈተናዎችን የመመዘን ብቃት ይገመግማል፣ ያረጋግጣል፤
6. በየሴሚስተሩ መጨረሻ ለተማሪዎች የሚሰጠውን ማርክ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤
7. በዲፓርትመንቱ መምህራን ምርምር የማድረግ ጥያቄ ሲቀርብ ተገቢነታቸውን ያረጋግጣል፣ እንዲፈቀድም ሃሳብ ያቀርባል፤
8. የዲፓርትመንቱን እቅድ ያወጣል አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤
9. እንደ አስፈላጊነቱ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡
10. በዲፓርትመንቱ የሚሰጥ ትምህርት ደረጃን በተመለከተ በዲፓርትመንቱ ኃላፊ አማካይነት ለአካዳሚክ ኮሚሽን ሪፖርት ያቀርባል፤
11. በየአስራ አምስት ቀናት ይሰበሰባል፡፡

## 23.የዲፓርትመንት ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

የዲፓርትመንት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፋኩልቲ ዲን ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. በዲፓርትመንቱ የሚሰጠው ትምህርት ከሚፈለገው ሳይንሳዊ ይዘትና ከሚሰጥበት ደረጃ ጋር የተመጣጠነና ከተግባር ጋር የተዋሀደ መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. በየርዕሱ የሚዘጋጁትን የትምህርት ፕላን ይመረምራል፣ ብቃታቸውን ያረጋግጣል፤
3. በዲፓርትመንቱ ጥናትና ምርምሮች እንዲካሄድ ያበረታታል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤
4. በዲፓርትመንቱ የሚፈለጉትን የመምህራን ዓይነትና ቁጥር ያጠናል፣ ተፈላጊዎቹ መምህራን እንዲቀጠሩም አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፤
5. በዲፓርትመንቱ የሚያስተምሩ መምህራንን የማዕረግ ዕድገት ጥያቄ ይመረምራል፣ ዕድገት ለሚገባቸው መምህራን ለዲፓርትመንት ካውንስል አቅርቦ ያስወስናል፤
6. የዲፓርትመንቱን ሠራተኞች የሥራ ብቃት ይገመግማል፣ ተገቢውን የደረጃ ዕድገትና የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኙ ጥያቄ ያቀርባል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
7. ለዲፓርትመንቱ የሚመደቡ ተማሪዎችን ይመዘግባል፣ አካዳሚክ አማካሪ ይመድብላቸዋል፣ በየሴሚስተሩ የሚሰጡ ኮርሶችን ለፋኩልቲው ዲን ያሳውቃል፤
8. በዲፓርትመንቱ ለሚማሩ ተማሪዎች አስፈላጊው የመማሪያ ቦታ፣ የትምህርት መረጃዎች፣ ማቴሪያሎችና መፃሕፍት መሟላታቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
9. የፈተናዎችን ደረጃና ተገቢነት የሚያረጋግጥ የፈተና ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፤
10. በዲፓርትመንቱ የሚሰጡ ፈተናዎች ሁሉ በተገቢው መንገድ መከናወናቸውን ይከታተላል፤
11. የዲፓርትመንቱን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
12. የዲፓርትመንቱን ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፣ ስለዕቅዱም አፈጻጸም ለዲኑ በጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባል፤
13. በፋኩልቲው ዲን የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**24.በጀት**

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

1. ከመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤
2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ከሚሰበስባቸው የአገልግሎት ክፍያዎች፣ እና
3. ከሌሎች ምንጮች።

**25. የሒሳብ መዛግብት**

1. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤
2. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**26. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**27. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

**አዲስ አበባ ጥር 9 ቀን 1993 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ**

**6/ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የሚገኝ የስልጠና ማዕከል ማቋቋሚያ ህግ**

# አዋጅ ቁጥር 364/1995

## የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከልን ማቋቋሚያ አዋጅ

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ዳኝነት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን የመጠበቅና የመገንባት የማይተካ ሚና ስለሚጫወትና ከሙያተኞቹ ከፍተኛ ሙያዊ ክህሎትና ሥነ-ምግባር የሚጠይቅ ስለሆነ፣ ለዚህም በበቂ ሁኔታ የሠለጠኑ ሙያተኞችን ማፍራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ዳኞችን፣ ዓቃብያነ ሕግንና ሌሎች ሙያተኞችን ለማብቃት ባለማቋረጥ የሚያድግና ተከታታይነት ያለው የሥልጠና ሥርዓት ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከልን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 364/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   1. "የፍትህ አካላት" ማለት በዋነኛነት ፍርድ ቤቶችንና የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤቶችን ሆኖ እንደአግባብነቱ ከፍትህ ሥራ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚሠሩ ሌሎች አካላትን ሊጨምር ይችላል፡፡
   2. "የፍትህ አካላት ባለሞያዎች" ማለት በዋናነት ዳኞች፣ ዐቃብያን ሕግ፣ ሬጅስትራሮችን፣ ተከላካይ ጠበቆችን ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በፍትህ አካላት ውስጥ የሚሠሩ ሌሎች ሙያተኞችን ሊጨምር ይችላል፡፡

3. **መቋቋም**

   1. የፍትህ አካላት የስልጠና ማዕከል ከዚህ በኋላ ማዕከሉ እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መስሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
   2. የማዕከሉ ተጠሪነት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

   የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

## 5. ዓላማ

የሥልጠና ማዕከሉ ዓላማ

1. የዳኝነት ሥርዓቱ ከፍተኛ ሙያዊ ብቃትና ሥነ-ምግባር እንዲሁም ሕዝባዊ አመኔታና ተቀርቋሪነት ያላቸውና ለሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ መከበር በጽናት በሚቆሙ ሙያተኞች የተገነባ እንዲሆን ማስቻል፤
2. በሕግ የበላይነት፣ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ፣ የተቀናጀና ወጥነት ያለው የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓትን ማምጣት፤
3. ፍትኃዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የፍትህ ሥርዓት ለማስፈን የሚያስችል በቀጣይነት የሚያድግና ተከታታይነት ያለው ሥልጠና ማካሄድ ይሆናል፡፡

## 6. ሥልጣንና ተግባር

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በፌዴራልና በክልል የፍትህ አካላት ውስጥ በዳኝነት፣ በዓቃቤ ሕግነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት ወይም በሬጅስትራርነትና በሌሎች ከፍትህ ሥርዓቱ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ሙያዎች ውስጥ ሥርዓቱን ለሚቀላቀሉ የሕግ ባለሙያዎች ሥልጠናዎችን መስጠት፤
2. በፌዴራልና በክልል የፍትህ አካላት ውስጥ በሥራ ላይ ለሚገኙ ዳኞች፣ ዓቃብያነ ሕግ፣ ተከላካይ ጠበቆች፣ ሬጅስትራር እና ሌሎች በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ለሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ቀጣይነት ያላቸው የሥራ ላይ ሥልጠናዎች መስጠት፤
3. በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የሚታዩ የተዘበራረቁ የፍትህ አሰጣጥ አሠራሮች ተስተካክለው ወጥነት እንዲኖራቸውና ደረጃቸውን የጠበቁ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓቶች በሁሉም ቦታ እውን እንዲሆኑ ተገቢውን ምርምርና ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሃሣብ ማመንጨት፤
4. በራሱ ወይም ከሌሎች የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለፍትህ ሥርዓቱ መጠናከር አስተዋጽኦ በሚኖራቸው የሕግና የፍትህ ጉዳዮች ላይ መምከርና የማሻሻያ ሃሣቦችን ማመንጨት፤
5. አስፈላጊዎቹን የሥልጠና ማቴሪያሎች ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀት፣ ማሠራጨት፤
6. ሌሎች የማዕከሉን ዓላማና ግብ መሠረት ያደረጉ ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን።

7. <u>የማዕከሉ አቋም</u>

ማዕከሉ፡-

1. የሥልጠና ካውንስል
2. አንድ ዳይሬክተር
3. ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች እና
4. ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

8. <u>የሥልጠና ካውንስሉ አካላት</u>

ካውንስሉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ........ ሰብሳቢ
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ........ አባል
3. የፍትህ ሚኒስትር ................................ "
4. የአቅም ግንባታ ሚኒስትር ..................... "
5. የክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ከመካከላቸው የሚወክሏቸው አምስት ፕሬዚዳንቶች............................ "
6. የሥልጠና ማዕከሉ ዳይሬክተር ........... አባልና ጸሐፊ

9. <u>የካውንስሉ ሥልጣንና ተግባር</u>

ካውንስሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የማዕከሉን እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የማዕከሉን ዕቅድና የሥራ መርሐ ግብሮች ይገመግማል፣ ያጸድቃል፣ አስፈላጊ በጀት እንዲፈቀድ ለመንግሥት ያቀርባል፤
3. ሥልጠናን አስመልክቶ በሚቀርቡ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
4. የማዕከሉን ወቅታዊና ዓመታዊ ሪፖርት ያጸድቃል፣
5. የማዕከሉን ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዱ ድጋፎችንና ስጦታዎችን በሚመለከት አጠቃላይ መመሪያዎችን ይሰጣል፤
6. የተቋሙን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሥራ መመሪያና የሠራተኞች የአገልግሎት ሁኔታ ይወሰናል፤
7. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚቀርቡ ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል፡፡

10. <u>የካውንስሉ ስብሰባ</u>

1. ካውንስሉ ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤

2. አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የማዕከሉ ካውንስል ሰብሳቢ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
3. የካውንስሉ ምልዓተ ጉባዔ የሚኖረው ከአባላት ከ50+1 ሲገኙ ብቻ ነው፤
4. ማናቸውም ውሳኔ የሚያልፈው ስብሰባ ላይ ከተገኙ የካውንስሉ አባላት ከግማሽ በላይ ድምፅ ሲደገፍ ብቻ ነው። ሆኖም ድምፅ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

11. <u>**የማዕከሉ ዳይሬክተር አሰያየም፣ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. የማዕከሉ ዳይሬክተር በካውንስሉ ሰብሳቢ አቅራቢነት በካውንስሉ ይሾማል፤
2. ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ኃላፊ በመሆን ከካውንስሉ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ስራ ይመራል፣ ያስተባብራል፤
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ/ የማዕከሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ መርሃ ግብርና በጀት አዘጋጅቶ ለካውንስሉ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
   ለ/ ለማዕከሉ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ ሂሣብ ያንቀሳቅሳል፤
   ሐ/ የማዕከሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለካውንስሉ ያቀርባል፤
   መ/ ለማዕከሉ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፤
   ረ/ የካውንስሉን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤
   ሰ/ ሌሎች በካውንስሉ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል።

12.<u>**የማዕከሉ ም/ዳይሬክተሮች**</u>

1. የማዕከሉ ምክትል ዳይሬክተሮች በዳይሬክተሩ አቅራቢነት በካውንስሉ ይሾማሉ፤
2. ምክትል ዳይሬክተሮች በዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጣቸውን ሥራ ይሠራሉ፤
3. ዳይሬክተሩ በሚሰጠው ውክልና መሠረትም ዳይሬክተሩ ሳይኖር የሱን ሥራ ተክተው ይሠራሉ።

13. <u>**በጀት**</u>

የማዕከሉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-

1. በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤
2. ማዕከሉ ሊያመነጭ ከሚችለው ገቢና፤
3. ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገንዘብ።

14. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. ማዕከሉ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የማዕከሉ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

15. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊዎቹን ደንቦች ለማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

16. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 7/ በፌደራል ፖሊስ ስር የሚገኝ የትምህርት ተቋም ማቋቋሚያ ህግ

## ደንብ ቁጥር 132/1999 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995 አንቀጽ 8(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 132/1999 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 መሠረት የተቋቋመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቦርድ ነው፤
   2. "ሴኔት" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 መሠረት የተቋቋመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኔት ነው፤
   3. "ፕሬዚዳንት" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 መሠረት የተሾመ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት ነው፤
   4. "ዳይሬክተር" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ 3(2) መሰረት በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥር የተቋቋመ ተቋም ዳይሬክተር ነው፤
   5. "የአካዳሚ ሠራተኛ" ማለት በማስተማር ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ነው፤
   6. "ተጠቃሚ ተቋም" ማለት የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ምሩቃን ቀጣሪ የሆነ ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ሲሆን፣ የፌደራልና የክልል ፖሊስ ተቋማትን፣ የማረሚያ ቤት አስተዳደሮችን፣ የጉምሩክ ፖሊስንና የህግ አስፈፃሚነትና የህዝብን ጸጥታና ደህንነት የማረጋገጥ ተልዕኮ ያላቸውን ሌሎች ተቋማት ያጠቃልላል።

3. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በሥሩ የሚከተሉትን ተቋማት አካትቶ ይይዛል፡-

   ሀ/ የፖሊስ እስታፍ ኮሌጅ፤

   ለ/ የፖሊስ መደበኛና ልዩ ሥልጠና አካዳሚ፣

   ሐ/ የፖሊስ ጤና ባለሙያዎች ሥልጠና ኢንስቲትዩት፤

   መ/ የወንጀል ምርመራ እና ፎሬንሲክ ሳይንስ ኢንስቲትዩት፤

   ሠ/ የፖሊስ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት፤

   ሰ/ ወደፊት በቦርዱ የሚቋቋሙ ሌሎች ኮሌጆች፣ ኢንስቲትዩቶችና ትምህርት ቤቶች።
3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተጠሪነት ለፌዴራል ፖሊስ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ለህገ መንግስቱ ታማኝ የሆኑና በፖሊሳዊ ሥራ የዳበረ ብቃት ያላቸው የፖሊስ ባለሙያዎችንና መሪዎችን ማፍራት፤
2. ከፖሊስ ሙያ ጋር የተያያዘ ዕውቀትን ማዳበር፣ ማስፋፋት፣ ማቆየትና ማስተላለፍ፤
3. የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና አቅምን አፈጻጸም ማጠናከርና ማስፋፋት፤
4. የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ጥረቶችን ውጤታማነት ማጠናከር፤
5. የፖሊስ አገልግሎትን የማሻሻልና የማዘመን ሂደት ማፋጠን፤
6. የህብረተሰቡን ከወንጀልና ከአደጋ ተጋላጭነት ራሱን የመከላከል ሂደት ማገዝ፤
7. የፖሊስን ተቋም መልካም እይታ በመገንባት ማገዝ።

5. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. በስሩ ፋኩልቲዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ኢንስቲትዩቶችንና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ክፍሎችን የማቋቋምና የማካሄድ፤
2. በፖሊስ አገልግሎትና በተያያዥ የጸጥታና ደህንነት መስኮች የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን የመስጠት፤

3. በተለያዩ የፖሊስ ሥራ መስኮች የልዩ ሙያና የሙያ ማሻሻያ ኮርሶችን የማዘጋጀት የመስጠት፤
4. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋጽኦ የአካዳሚክ ሜዳል፣ ሽልማትና ማዕረግ የመስጠት፤
5. የሰልጣኞችን ባህሪ የማጥናት፣ የመገምገም፣ የመቆጣጠር፣ መዝግቦ የማቆየትና ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ፤ የምሩቃንን ሁኔታ የመከታተል፤
6. ለሚሰጣቸው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የመግቢያ፣ የመቀጠያና የመመረቂያ መመዘኛዎችን የመወሰን፤
7. ተልዕኮዎቹን ለመወጣት አስፈላጊ የሚሆኑ የውስጥ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈጸም፤
8. ለፖሊስ አገልግሎት ዋና ዋና የሥራ መደቦች የተፈላጊ ችሎታና ብቃት እስታንዳርዶችን የመለየት፤
9. የሥልጠና ፍላጎትና ውጤት ትንተናና ግምገማ የማድረግ፤
10. በፖሊሱ አባላት ዘንድ የመማርና በተማሩት መሰረት የመሥራት ተነሳሽነት ሊሰፋፉ የሚችልበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
11. የፖሊስን ሞያ ለማሳደግ የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን የማድረግና ውጤቱንም የማሰራጨት፤
12. ወንጀልን፣ አደጋንና ግጭትን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማግኘት፣ የማመንጨት፣ የማደራጀትና የማሰራጨት፤
13. ፖሊስ ነክ ህትመቶችንና የማስተማሪያ ጽሑፎችን የማዘጋጀትና የማሰራጨት፤
14. የፌዴራልና የክልል ፖሊስ አመራሮችን የማማከር፤
15. ለሌሎች የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት፤
16. በክፍያ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤
17. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸውና ለተልዕኮው መሳካት እገዛ ሊያደርጉ ከሚችሉ የአገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ጋር ግንኙነት የመመሥረት፤
18. ተልዕኮውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሚሆኑ ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ገንዘባዊ ግብዓቶችን የማግኘትና የማስተዳደር፤
19. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ በስሙ የመዋዋል፣ የመክሰስ እና የመከሰስ፤

20. ዓላማውን የሚያራምዱ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፡፡

6. **ስለተጠቃሚ ተቋማት ተሳትፎ**

1. ተጠቃሚ ተቋማት በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተማሪ ኮታ ድልድል፣ በሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ይዘት፣ በአዳዲስ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች መከፈትና በነበሩ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች መዘጋት ወይም መታጠፍ ጉዳዮች ላይ ከየራሳቸው የሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላጎት አንጻር አስተያየት የማቅረብ መብት ይኖራቸዋል።

2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ቦርድና አመራር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተጠቃሚ ተቋማት አስተያየታቸውን የሚገልፁበትን መንገድ ማመቻቸትና በጉዳዮች ላይ ሲወስኑም አስተያየቶቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የፖሊሲና የሥራ አስፈጻሚ አካላት**

7. **ስለቦርዱ መቋቋም**

1. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በፌዴራል ፖሊስ ኃላፊ የሚሰየሙ አንድ ሊቀመንበርና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን አባላት የሚገኙበት ቦርድ ይኖረዋል።
2. ቦርዱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።
3. የቦርዱ ተጠሪነት ለፌደራል ፖሊስ ኃላፊ ይሆናል፡፡

8. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ይህ ደንብ እንደአስፈላጊነቱ እንዲሻሻል ለመንግሥት ሃሳብ ያቀርባል፤
2. ከመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በተገናዘበ መልኩ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አጠቃላይ የትምህርትና ስልጠና እና የአስተዳደር ፖሊሲ ያወጣል፣ ያስፈፅማል፤
3. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አደረጃጀት ይወስናል፤
4. የተጠቃሚ ተቋማት ተሳትፎን የሚያስችሉ ተገቢ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን ያረጋግጣል፤
5. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ለመንግሥት አቅርቦ ያሾማል፤ የዳይሬክተሮችን ሹመት ያፀድቃል፤
6. የተባባሪ ፕሮፌሰርና የፕሮፌሰር ማዕረግ ያፀድቃል፤

7. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓመታዊ እቅድና የበጀት ጥያቄ ይመረምራል፣ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
8. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክ ሠራተኞች ቅጥር፣ ዕድገት፣ ዲስፕሊን፣ አበልና ጥቅማ ጥቅም የሚወስን የውስጥ አስተዳደር ደንብ አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ያስፈፅማል፤
9. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚያሰከፍላቸውን ክፍያዎች መንግሥት ባፀደቀው መመሪያ መሠረት ይወስናል፤
10. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች ያጸድቃል፤
11. ማንኛውም የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ደረጃውን ጠብቆ የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
12. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን መለያ ምልክት ወይም ዓርማ ይወስናል፤
13. የራሱን የስብሰባና የአሰራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤
14. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

9. <u>ስለፖሊስ ሥልጠና መማክርት መቋቋም</u>

1. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ይዘት፣ አወቃቀርና ሂደት ወጥ የሆነ ስታንዳርድ ያላቸውና አገራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮችን በሚገባ አጣጥመው የሚያስኬዱ እንዲሆኑ ከማስቻል አንጻር የፖሊስ ሥልጠና መማክርት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. መማክርቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት ......... ሰብሳቢ

   ለ/ የምርምር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ........አባል

   ሐ/ የሌሎች የፌዴራልና ክልል ፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋማት መሪዎች...አባላት

   መ/ በቦርዱ የሚሰየሙ ሌሎች አካላት......አባላት
3. የመማክርት ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡
4. መማክርቱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡
5. መማክርቱ ቢያንስ በአንድ በጀት አመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

10. <u>የፖሊስ ሥልጠና መማክርት ዓላማና ተግባሮች</u>

ቦርዱ የሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ መማክርቱ የሚከተሉት ዓላማና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ወጥነትንና ተቀራራቢነትን የሚያረጋግጡ አገር አቀፍ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በሁሉም የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ዘንድ ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
2. በሁሉም የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት መካከል በአገር አቀፍ ደረጃ ጥሩ ቅንጅትና ህብረት እንዲኖር ያደርጋል፤
3. በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጁ የፖሊስ ሥልጠና እቅዶች ላይ በመወያየት ማሻሻያ አስተያየት ይለዋወጣል፤
4. አገር አቀፍ የፖሊስ ሥልጠና ሂደቶችን ይገመግማል፣ ተሞክሮ ይለዋወጣል፤
5. በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

11. <u>የሴኔት መቋቋም</u>

1. የሚከተሉትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሴኒት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡-
   ሀ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ፕሬዚዳንት ........ ሰብሳቢ
   ለ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች............ አባላት
   ሐ/ ዳይሬክተሮች ......................... አባላት
   መ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሬጅስትራር........አባል
   ሠ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ............ አባል
   ረ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መምህራን ጉዳይ ኃላፊ.............. አባል
   ሰ/ ከየትምህርትና የሥልጠና ተቋማቱ የተወከሉ አንዳንድ መምህራን....አባላት
   ሸ/ የተማሪዎች ካውንስል ሁለት ተወካዮች..... አባላት
   ቀ/ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሴቶች ጉዳይ ተወካይ...... አባል
   በ/ በቦርዱ የሚሰየሙ ሌሎች ሰዎች ........ አባላት
2. ሴኒቱ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።
3. የሴኔቱ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡

12. <u>የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ሴኔቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፕሮግራሞችና ኮርሶች መከፈትን፣ መሻሻልንና መዘጋትን ያጸድቃል፤

2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የትምህርት ካሌንደር መርምሮ ያፀድቃል፤
3. ከዳይሬክተርና ሙሉ ፕሮፌሰር በታች ያሉ የአካዳሚክ ሠራተኞች ምደባዎችንና ማዕረጎችን ያጸድቃል፤
4. የዳይሬክተሮችንና ፕሮፌሰሮችን ሹመትና ማዕረግ መርምሮ ለቦርዱ ያቀርባል፤
5. ቦርዱ ያወጣቸውን ፖሊሲዎች መሠረት በማድረግ የአካዳሚክ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ያፀድቃል፤
6. ዲግሪዎች፣ ዲፕሎማዎች፣ የምስክር ወረቀቶች፣ ሜዳይና ሌሎች የአካዳሚክ ሽልማቶች እንዲሰጡ ይወስናል፤
7. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

13. <u>የፕሬዚዳንቱና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሹመትና ተጠሪነት</u>

1. ፕሬዚዳንቱ በቦርዱና በፌዴራል ፖሊስ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል፣ ተጠሪነቱም ለቦርዱ ይሆናል፡፡
2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ምክትል ፕሬዚዳንቶች በቦርዱ አቅራቢነት በፌዴራል ፖሊስ ይሾማሉ፤ ተጠሪነታቸውም ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል፡፡

14. <u>የፕሬዚዳንቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ፕሬዚዳንቱ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መሪና ዋና አስፈፃሚ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክና አስተዳደራዊ ሥራዎች በዋና ኃላፊነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የፖሊስ ሥልጠና መማክርትን ይሰበስባል፤ የውሳኔዎቹንም ተፈጻሚነት ይከታተላል፤
3. በቦርዱና በሴኔቱ የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
4. የተጠቃሚ ተቋማትን ፍላጎቶች ለማካተት የሚያስችሉ ሥርዓቶች መበጀታቸውን ያረጋግጣል፤
5. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ስትራቴጂክና ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲጸድቁም ተፈፃሚነታቸውን ያረጋግጣል፤
6. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን አጠቃላይ ተቋማዊ የሥራ አፈጻጸም ደረጃ ይከታተላል፣ ያሻሽላል፤
7. አግባብነት ያላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

8. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን በመወከል ስምምነቶችንና ውሎችን ይፈርማል፤

9. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ይወክላል፤

10. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ስም የባንክ ሒሳብ እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤

11. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የየሩብ ዓመትና ዓመታዊ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ዘገባዎች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

12. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

15. <u>የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. በአካዳሚክ ጉዳዮች ፕሬዚዳንቱን ያግዛል፣ ያማክራል፤

2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአካዳሚክ ሥራዎች ይመራል፣ ያስተባብራል፤

3. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሚሰጡ ትምህርትና ሥልጠናዎች ሕገመንግሥታዊ ግንዛቤን፣ ፖሊሳዊ ሰብዕናን እና ሙያዊ ብቃት ከመገንባት አንጻር ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

4. በሚሰጡ ፕሮግራሞች አዘገጃጀት፣ ይዘትና አሰጣጥ ተሳታፊዎቹ የሚሰማሩባቸው ሥራዎች ልዩ ሁኔታና የተጠቃሚ ተቋማት ፍላጎት የተጤነበት መሆኑን ያረጋግጣል፤

5. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ዝግጅትን፣ የፕሮግራሞች አፈጻጸም ሂደት አመራርንና የጥናትና ምክር አገልግሎት ሥራዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ስታንዳርዶችና ሥርዓቶች መዘጋጀታቸውንና መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

6. የፖሊስ ጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲስፋፉና የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች የፖሊሱን አገልግሎት ለማሻሻል እንዲበቁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

7. አካዳሚክ ካውንስሉን ይሰበስባል፤ የሴኔቱ፣ የአመራር ኮሚቴውና የአካዳሚክ ካውንስሉ ውሳኔዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

8. የዳይሬክተሮችን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤ የሌሎች የአካዳሚክ ሠራተኞችን የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ሁኔታን ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤

9. የአካዳሚክ ዘርፉን ዓመታዊ እቅድና የበጀት ፍላጎት ያዘጋጃል፤

10. የአጫጭር ኮርሶችን፣ ወርክሾፖችን፣ ሴሚናሮችንና ኮንፈረንሶችን ዝግጅትና አፈጻጸም ይከታተላል፤

11. የጥናትና ምርምር፣ የካሪክለም ቀረጻና ማሻሻያ እንዲሁም የማስተማሪያ ጽሁፍ ዝግጅት ሥራዎችን ይከታተላል፤
12. የአካዳሚክ ዘርፉን ሪፖርት እንደየአስፈላጊነቱ እያዘጋጀ ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
13. የአካዳሚክ ሠራተኞችን የቅጥርና የውል ዕደሳ ጥያቄዎችን ተቀብሎ በመመርመር ለአመራር ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
14. ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ወክሎ የአካዳሚክ ሠራተኞችን የቅጥር ውል ይፈራረማል፤
15. ፕሬዚዳንቱ በሌለበት ተክቶት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ይመራል፤
16. በፕሬዚዳንቱና በሴኔቱ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል።

16. <u>የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. በአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ፕሬዚዳንቱን ያግዛል፣ ያማክራል፤
2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአስተዳደርና ልማት ሥራዎች ይመራል፣ ያስተባብራል፤
3. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሠራተኞችና ተማሪዎች ዘንድ ስለህገ መንግስቱ፣ ስለአገራዊ ፖሊሲዎችና የትኩረት ጉዳዮች፣ ስለፖሊስ ደንቦችና መመሪያዎች፣ ስለተፈላጊ የፖሊስ ሰብዕናዎችና ባህሪያት ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባሮችን ያስፈጽማል፤
4. የድጋፍ ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገትና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ይቆጣጠራል፤
5. የዩነቨርሲቲ ኮሌጁን የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ ሪፖርት እንደየአስፈላጊነቱ እያዘጋጀ ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
6. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የሰው ኃይል ፍላጎት መሟላቱንና የሠራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ ዕድገት፣ ስንብትና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤ ሠራተኞች መብታቸው ተከብሮላቸው ግዴታቸውን እንዲወጡ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፤
7. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን ንብረት አግባብ ባላቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ያስተዳድራል፤ ለመማር ማስተማር ሂደት የማያስፈልጉ ቁሳዊ አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

8. ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎችና ማህበረሰብ የሚያስፈልጉ የጤና፣ የምግብና መኝታ፣ የትራንስፖርት፣ የጥበቃና የመሳሰሉ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መመሪያ የተወሰኑ አገልግሎቶችና አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

9. ከመንግሥት መደበኛ በጀት በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የፋይናንስ አቅም ለማጠናከር የሚያስችሉ የገቢ ምንጮችን ያስፋፋል፣ ገቢውን በአግባቡ ያስተዳድራል፤

10. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ አመታዊ በጀትና ዕቅድ አዘጋጅቶ፣ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተፈጻሚ ያደርጋል፤

11. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## 17. <u>የምርምር ተቋም ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

የጥናትና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የጥናትና ምርምር እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱን ያግዛል፣ ያማክራል፤

2. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የጥናትና የምርምር እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች ይመራል፣ ያስተባብራል፤

3. የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲስፋፉና የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች የፖሊሱን አገልግሎት ለማሻሻል እንዲበቁ ያደርጋል፤

4. የጥናትና ምርምር ፍላጎቶችን ይለያል፤ የጥናት ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፤ የጥናት ፕሮጀክት ወጪ መሸፈኛ አማራጮችን ይፈልጋል፤ የጸደቁ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን አፈጻጸምና ውጤት ይከታተላል፤

5. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤

6. የሥልጠና ፍላጎትና ውጤት ግምገማ በየወቅቱ መደረጉንና የሚያስፈልጉ የፕሮግራም ማስተካከያዎች መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

7. የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ህትመትና ሥርጭት ያመቻቻል፤

8. በጥናትና ምርምር ጉዳዮች ላይ ሥልጠናዎችን፣ ወርክሾፖችን፣ ሴሚናሮችንና ሲምፖዚየሞችን አዘጋጅቶ ይሰጣል፤

9. በሌሎች የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ተቋማት የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ጥረቶችን ያግዛል፣ ያበረታታል፤

10. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ተማሪዎች ለመመረቂያ ማሟያ የሚያደርጉዋቸውን ጥናቶች ሂደት ያስተባብራል፤

11. ለጥናትና ምርምሩ ተቋም አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችና ሥርዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

12. መምህራንና ተማሪዎች በጥናትና ምርምሩ ሥራ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

13. የጥናትና ምርምሩን ተቋም ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤

14. የተቋሙን ሠራተኞችና የአጥኚዎችን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤

15. ለጥናትና ምርምሩ ሥራ አስፈላጊ የሚሆኑ የአሰራርና አፈጻጸም መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ተፈጻሚነታቸውን ያረጋግጣል፤

16. የተቋሙን የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ሪፖርቶች እያዘጋጀ ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤

17. በጥናትና ምርምር ጉዳዮች ላይ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

18. <u>**የትምህርትና የሥልጠና ተቋም ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**</u>

የማንኛውም የትምህርትና የሥልጠና ተቋም ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የተቋሙን አካዳሚክና አስተዳደራዊ ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ፤ የወርክሾፖችና የሲምፖዚየሞች ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደቶችን ይመራል፤
3. የተቋሙን አካዳሚክ ኮሚሽን ይሰበስባል፤
4. ለተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችና ሥርዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
5. በተቋሙ ውስጥ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በሙሉ ተገቢ ስታንዳርዶችን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
6. የህገ መንግስታዊ መርሆዎች ማስረጽና የፖሊሳዊ ስብዕና ግንባታ ስትራቴጂዎች ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
7. የተቋሙን የአካዳሚክና የድጋፍ ሠራተኞች አፈጻጸም ይገመግማል፤
8. ለተቋሙ ሠራተኞችና ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ መመሪያ መሰረት ሊቀርቡ የሚገቡ አቅርቦቶችና አገልግሎቶች ተሟልተው መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

9. የተቋሙን ዓመታዊ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤
10. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች አፈጻጸምንና የሰልጣኞችን ሁኔታ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
11. በትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ላይ አስፈላጊ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ አስተያየት ያቀርባል፤
12. የተቋሙን የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ሪፖርቶች እያዘጋጀ ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤
13. በትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች ላይ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

19. <u>የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሌሎች አካላት</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ሌሎች የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ክፍሎች አመሰራረትና አሰራር እንዲሁም የአመራር አካላቱ አሰያየም በቦርዱ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

20. <u>በጀት</u>

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

1. በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤
2. ከሚሰበስባቸው የአገልግሎት ክፍያዎች፤ እና
3. ከሌሎች ምንጮች።

21.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኮሌጁ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

22. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረኑ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

23. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዝያ 19 ቀን 1999 ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

# ክፍል አስራ ስድስት

## ጤና

## ደንብ ቁጥር 167/2001

## የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 (በአዋጅ ቁጥር 603/2001 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 እና 34 መሠረት ይህን ደንብ አጽድቋል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 167/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

   1. "የፌዴራል ሆስፒታል" ማለት ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሆነ ሆስፒታል ወይም በዩኒቨርሲቲ ስር የሚተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫና የጤና ሙያ ማስተማሪያ ሆስፒታል ነው፤
   2. "የግል ሕክምና መስጫ ክፍል" ማለት በፌዴራል ሆስፒታል ውስጥ የጤና ባለሙያዎች የህክምናና የምርመራ አገልግሎት በመስጠት ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ነው፤
   3. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
   4. "ዩኒቨርሰቲ" ማለት የጤና ሙያ ማስተማሪያና የጤና አገልግሎት መስጫ ሆስፒታልን የሚያስተዳድር የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ ደንብ በማንኛውም የፌዴራል ሆስፒታል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. **የፌዴራል ሆስፒታል ሥልጣንና ተግባር**

   የፌዴራል ሆስፒታል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

   1. የመደበኛና ድንገተኛ ምርመራና ህክምና አገልግሎት ይሰጣል፤
   2. የሪፈራል አገልግሎት ይሰጣል፤

3. የህክምናና የምርመራ አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የምርምር ተግባራትን ያከናውናል፤
4. የማስተማሪያ ሆስፒታል ሲሆን፣ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ወይም ስልጠና የጤና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዳ መሆኑን ያረጋግጣል፤
5. የማህበራዊና የማገገሚያ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
6. ለተመላላሽና ተኝተው ለሚታከሙ ተገልጋዮች የበሽታን መከላከልና የጤና ማጎልበት ተግባር ያከናውናል፤
7. የህብረተሰቡን ጤና እና ጤና-ነክ ችግሮችን በመፈተሽና በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል፤
8. ለሌሎች የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የአቅም ግንባታና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
9. የሚያከናውናቸውን የጤና አገልግሎቶች በተመለከተ መረጃ ይሰበስባል፣ አግባብ ላለው አካልም ያስተላልፋል፤
10. ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤
11. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

5. <u>የፌዴራል ሆስፒታል አቋም</u>
   1. የአመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፤
   2. በቦርዱ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚሾም ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ እና
   3. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

   ይኖሩታል።

6. <u>ስለቦርድ አባላት</u>
   1. ቦርዱ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚሰየሙ ከአካባቢው መስተዳደር፣ ከሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ ከትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ከሲቪክ ማህበራትና ከታዋቂ ሰዎች የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል።
   2. የቦርዱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ይወሰናል፡፡

3. ለቦርድ አባላት የሚከፈለዉ አበል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በሚኒስትሩ ይወሰናል፡፡

7. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል ሆስፒታል ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

1. ሆስፒታሉን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የሆስፒታሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት መርምሮ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
3. ሆስፒታሉ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን የክፍያ ተመን አስመልክቶ የሚያቀርበውን የማሻሻያ ሀሳብ በመመርመር አስተያየቱን ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤
4. የሆስፒታሉን የውስጥ አሰራር መመሪያዎች ያፀድቃል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤
5. የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውንም ይመራል፤
6. የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ከሆስፒታሉ ተጠንቶ የቀረበለትን ጥናት በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤
7. በሆስፒታሉ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ተገቢውንም ውሳኔ ይሰጣል፤
8. የሆስፒታሉ የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ከመቅረቡ በፊት መርምሮ ያጸድቃል፡፡

8. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ አንድ ሦስተኛው ስብሰባ እንዲካሄድ ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

1. የአንድ የቦርድ አባል የሥራ ዘመን ለሶስት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ እንደገና እንዲያገለግል ሊደረግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ባላቸው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት የቦርድ አባል የሆኑትን ሰዎች የአገልግሎት የሥራ ዘመን አይመለከታቸውም፡፡
3. ማንኛውም የቦርድ አባል የአገልግሎት ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ከአባልነት መሰናበት ቢፈልግ ይህንኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሲጠናቀቅ የነባሩ ቦርድ ሰብሳቢ ከስድስት ወራት ለማይበልጥ ጊዜ በቀጣዩ ቦርድ ውስጥ በአባልነት እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

10. ከቦርድ አባልነት ስለመነሳትና የጎደሉትን ስለመተካት

1. አንድ የቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊነሳ ይችላል፡-
   ሀ/ በቦርድ አባሉና በሆስፒታሉ መካከል የጥቅም ግጭት ሲያጋጥም፤
   ለ/ የጤና እክል ወይም የስነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም፤
   ሐ/ በወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት፤
   መ/ ያለምንም ፈቃድ ወይም አስቀድሞ ባለማሳወቅ ለሦስት ተከታታይ ጊዜ የቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ ቀሪ ሲሆንና በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳያሻሽል ሲቀር፡፡
2. አንድ የቦርድ አባል ከአባልነት ሲነሳ ሚኒስትሩ ወይም ፕሬዝዳንቱ አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል።

11. የዋና የስራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

1. የፌዴራል ሆስፒታል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የሆስፒታሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈፃሚው፡-

ሀ/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የሆስፒታሉን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የሆስፒታሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፤

ሐ/ የሆስፒታሉን ዓመታዊ የሥራ ፕሮራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለሆስፒታሉ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ሆስፒታሉ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችለው ተገቢውን የሰው ሀይልና ሌሎች ግብዓቶችን ያሟላል፤

ረ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ሥራቸውን ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ሰ/ የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል እንዲረዳ ህክምናና ህክምና ነክ ያልሆኑ ሥራዎች በሦስተኛ ወገኖች ስለሚሰጡበት ሁኔታ በማጥናት ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሸ/ በሆስፒታሉ ውስጥ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ እያጠና ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ቀ/ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤

በ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሆስፒታሉን ይወክላል፤

ተ/ የሆስፒታሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቸ/ ከቦርዱ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

3. ዋና ሥራ አስፈጻሚው ለሆስፒታሉ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገዉ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 12. <u>ስለግል ህክምና መስጫ ክፍሎች</u>

1. እያንዳንዱ የፌዴራል ሆስፒታል በዉስጡ የግል የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ያቋቁማል፡፡

2. በግል የሕክምና መስጫ ክፍል የሚሰጠው አገልግሎት ሆስፒታሉ በመደበኛ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል የሚሰጠውን አገልግሎት የማያስተጓጉል መሆን አለበት፡፡

3. በመደበኛውና በግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጠው ባለሙያ በሚሰጠዉ የሕክምናና የምርመራ አገልግሎት በተጠቃሚዎች መካከል ልዩነት መፍጠር የለበትም፡፡

4. ለግል የህክምና መስጫ አገልግሎት የሚያስፈልገው የሥራ ክፍል ብዛት እንደሁኔታው እየታየ በቦርዱ ይወሰናል፡፡

13. <u>በጀት</u>

የፌዴራል ሆስፒታል በጀት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በመንግሥት ይመደባል።

14. <u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ማንኛውም የፌዴራል ሆስፒታል የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የፌዴራል ሆስፒታል የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይመረመራል፡፡

15. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

16. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

17. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

# <u>አዋጅ ቁጥር 661/2002</u>

## <u>የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ</u>

የሕብረተሰቡ ጤና ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ካልተረጋገጠ ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ መድኃኒት መጠበቅ ያለበት በመሆኑ፤

ደህንነቱና ጥራቱ ባልተጠበቀ ምግብ ምክንያት በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ደረጃውን ባልጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሁም ብቃትና ሙያዊ ሥነ-ምግባር በጎደለው የጤና ባለሙያ፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለትና በተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር ጉድለት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር መግታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችንና እነዚህኑ ለማምረት የሚያገለግሉ ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ሕገወጥ ምርት፣ ሥርጭትና አጠቃቀም መከላከልና መግታት በማስፈለጉ፤

በጤናው ዘርፍ ሰፍኖ የቆየውን የተበታተነና ጥራት የጎደለውን የአስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ አዲስና የተቀናጀ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ምግብ" ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ውኃ ወይም ሌላ መጠጥ፣ የሚታኘክ ማስቲካ፣ ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከምና ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትንባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን አይጨምርም፤

2. "የምግብ ንግድ" ማለት ምግብና የምግብ ጥሬ ዕቃዎችን ለንግድ ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ማጭረር፣ ማሸግ፣ መላክ፣ ማስመጣት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ፣ በጅምላና በችርቻሮ መሸጥና የምግብ ጥራት ላቦራቶሪ ሥራን ይጨምራል፤

3. "መከለስ" ማለት ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት በሚቀርብ ምግብ ወይም መድኃኒት ይዘት ላይ ሌላ ነገር በመጨመር ወይም ይዘቱን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሌላ ነገር በመተካት ወይም በተገቢው መንገድ በንጽህና ባለመመረቱና ባለመያዙ ከባዕድ ነገር ጋር እንዲነካካ ማድረግ ነው፤

4. "የምግብ ጭማሪዎች" ማለት እንደ ምግብ አካል ተቆጥሮ ምግብን ለማጣፈጥ፣ ለማቅለም፣ ሳይበላሽ ለማቆየት ወይም ለማሳመር የሚረዳ በምግብ ላይ የሚጨመር ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

5. "ንጥረ ምግብ" ማለት ማንኛውንም ምግብ በተለይ የሰውነት ጤንነትን ለማጎልበት ወይም በተመጣጠነ የምግብ እጥረት ምክንያት የሚከሰት የጤና ችግርን ለመከላከል በሚገቡ የፕሮቲን፣ የቫይታሚን፣ ማዕድንና በመሳሰሉት የዳበረ ወይም የበለጸገ ምግብ ነው፤

6. "መድኃኒት" ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን፣ ፕሪከርሰር ኬሚካሎች፣ የባህል መድኃኒቶች፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒቶች፣ መርዞች፣ ደምና የደም ተዋጽኦዎች፣ ቫክሲኖች፣ ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶች፣ ኮስሞቲኮች፣ የሳኒተሪ ዝግጅቶች እና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤

7. "ፋርማኮፒያ" ማለት በአገሪቱ የተዘጋጀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ ስለመድኃኒት ዝግጅቶች፣ መድኃኒትነት ይዘት ያላቸው እና የሌላቸው ንጥረ ነገሮች

ፊዚካላዊ ባህሪይ፣ የዝግጅት ምንነት፣ ይዘት፣ ጥራት፣ ጥንካሬ እና እነዚህን ባህሪያት በተመለከተ ማሟላት ያለባቸው መመዘኛዎች ወይም ደረጃዎች ያካተተ ህጋዊ ተፈጻሚነት ያለው ሰነድ ነው፤

8. “የናርኮቲክ መድኃኒቶች ወይም ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች” ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለችው የተባበሩት መንግሥታት የናርኮቲክ መድኃኒቶች ወይም የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ስምምነት መሠረት ዓለም አቀፍ ቁጥጥር የሚካሄድበት መድኃኒት ሲሆን አስፈጻሚ አካሉ የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፒክ መድኃኒት ብሎ የሚሰይመውንም ይጨምራል፤

9. “ፕሪከርሰር ኬሚካል” ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለችው የተባበሩት መንግሥታት የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ህገ ወጥ ዝውውር የሚገታ ስምምነት መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች፣ ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን አስፈጻሚ አካሉ ፕሪከርሰር ኬሚካል ብሎ የሚሰይመውንም ይጨምራል፤

10. “የትምባሆ ዝግጅት” ማለት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ከትምባሆ ቅጠል የተዘጋጀ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ ወይም በማሽተት የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

11. “መርዝ” ማለት በአነስተኛ መጠንም ሲወሰድ በሰው፣ በእንስሳት፣ በዕጽዋት ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

12. “የሳኒተሪ ዝግጅት” ማለት የሰው ወይም የቤት ውስጥ ንጽህናን ለመጠበቂያ የሚያገለግል ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን ፓዶችን፣ ታምፖችን፣ የጥርስ ንጽሕና መጠበቂያ ዝግጅቶችን፣ የላብ መምጠሚያዎችን እና ዲተርጀንቶችን ይጨምራል፤

13. “ፀረ-ተባይ” ማለት ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለእጽዋት ጤና አጠባበቅ ሲባል ተባይን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር ወይም ለማጥፋት የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገር ውህድ ነው፤

14. “የሕክምና መሣሪያ” ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ አካል ላይ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ህክምና፣ የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎች እና የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ ሲሪንጆችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻ፣ ጎዝ፣

ጥጥና መሰል ዝግጅቶችን፣ ሰው ሰራሽ ጥርሶችን፣ ኬሚካሎችን፣ የጨረራ ፊልሞችንና ሌሎች መሰል መሳሪያዎችና መገልገያዎችን ይጨምራል፤

15. "ባህላዊ መድኃኒት" ማለት የእጽዋት፣ የእንስሳት ወይም የማዕድን ተዋጽኦ ሆኖ በነጠላም ሆነ በመቀላቀል ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት የሚውል ዝግጅት ነው፤

16. "ኮስሜቲክ" ማለት ሰውነትን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደምግባት ለመጨመር ወይም የአካልን ቅርጽና አሠራሩን ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር በገላ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን የቆዳ ቅባቶችን፣ ሎሽኖችን፣ ሽቶዎችን፣ የከንፈር ቀለሞችን፣ የጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ፣ የዓይንና የፊት ማስዋቢያ፣ የጸጉር ማቅለሚያዎችን፣ የጠረን መቀየሪያ ዝግጅቶችን፣ ሜዲኬትድ ሳሙናዎችን እና ለእነዚህ ዝግጅቶች መሥሪያ የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤

17. "የመድኃኒት ንግድ ሥራ" ማለት መድኃኒቶችን ለትርፍ አላማ ማምረት፣ እንደገና ማሸግ፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ በጅምላ ማከፋፈል ወይም በችርቻሮ ማደል ሲሆን ጥራት መመርመርን፣ ሳይንሳዊ ቢሮ ማቋቋምና ምርምር ማካሄድን እና በንግድ ወኪልነት መሥራትን ይጨምራል፤

18. "የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት" ማለት ፈቃድ ባለዉ የሕክምና ባለሙያ ተጽፎ ለሕሙማን የሚሰጥ የመድኃኒት ዕደላ ትዕዛዝ ነው፤

19. "የሕክምና ሙከራ" ማለት የአንድን መድኃኒት ወይም የሕክምና ዘዴ ፈዋሽነትና ደህንነት ለማረጋገጥ በእንስሳት ወይም በሰዎች ላይ የሚደረግ ሙከራ ነው፤

20. "ጨረራ አፍላቂ መድኃኒት" ማለት የሰውን ወይም የእንስሳትን በሽታ ለመመርመር፣ ለመከላከል ወይም ለማከም አገልግሎት የሚውል አንድ ወይም ከአንድ የበለጠ ሬድዮ ኒዩክላይድ ጨረራ አፍላቂ ንጥረ ነገር የያዘ መድኃኒት ነው፤

21. "ማሸጊያ" ማለት ምግብን ወይም መድኃኒትን በውስጡ ለመሙላት ወይም ለመክተት ወይም ለመጠቅለል የሚያገለግል ማንኛውም መያዣ ሲሆን ከምግቡ ወይም ከመድኃኒቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን መያዣዎችንና ለመጠቅለያ የሚያገለግሉ ሌሎች ዕቃዎችን ይጨምራል፤

22. "ገላጭ ጽሁፍ" ማለት ስለ አንድ ምግብ ወይም መድኃኒት አስፈላጊውን መረጃ የሚገልጽ በማሸጊያው ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ጽሁፍ ሲሆን በማሸጊያው ውስጥ በአባሪነት የሚከተተውን ጽሁፍ ይጨምራል፤

23. “እንደገና ማሸግ” ማለት የምርት ሂደቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ምግብን ወይም መድኃኒትን በሌላ አምራች ድርጅት መልሶ የማሸግ ሥራ ነው፤

24. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በወጣው የጤና ቁጥጥር ደረጃ መስፈርት መሰረት በምግብ፣ በመድኃኒት ወይም በጤና ወይም በጤና ነክ አገልግሎት ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነው፤

25. “አስመስሎ ማቅረብ” ማለት የምግብ ወይም የመድኃኒት ማሸጊያ፣ መለያ፣ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም ወይም ማንኛውንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም ምግቡ ወይም መድኃኒቱ በእውነተኛው አምራች እንደተመረተ በማስመሰል ወይም የምግብነት ወይም የመድኃኒትነት ይዘትና ባህርይ ለውጦ በማቅረብ በሰው ጤና ላይ ጉዳት ማስከተል ነው፤

26. “ተቆጣጣሪ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን በአስፈጻሚ አካል ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ባለሙያ ነው፤

27. “የተጠረጠረ ሰው” ማለት አግባብ ባለው አካል ተገምግሞ ለተላላፊ በሽታ እንደተጋለጠ የሚቆጠርና ያለበትን በሽታ ማስተላለፍ የሚችል ሰው ነው፤

28. “ቆሻሻ” ማለት ከኢንዱስትሪዎች፣ ከእርሻ ቦታዎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከመኖሪያ ቤቶች፣ ከንግድ ስፍራዎች፣ ከጤናና ምርምር ተቋማት፣ ከመጸዳጃ ቤት ወይም ከሌሎች መሰል ተቋሞች የሚወጣና በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ፈሳሽ፣ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ሌላ ቆሻሻ ነው፤

29. “የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለት” ማለት ሰው በሚኖርበት አካባቢ የሚገኝ በአካላዊ እድገት፣ በጤና ወይም በአኗኗር ዘይቤ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ሁኔታ ነው፤

30. “የጤና ባለሙያ” ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት አግባብ ባለው አካል እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፤

31. “የሕክምና ባለሙያ” ማለት ሕመምተኛውን በመመርመር የበሽታውን ዓይነት የሚለይና በመድኃኒት ወይም አካልን በመቅደድ የሚያክም የሰው ሐኪም ወይም እነዚህኑ ተግባራት እንዲያከናውን በአስፈጻሚው አካል የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ነው፤

32. “የመድኃኒት ባለሙያ” ማለት አግባብ ባለው አካል የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ፋርማሲስት፣ ድራጊስት ወይም ፋርማሲ ቴክኒሻን ነው፤

33. "ባህላዊ ሕክምና" ማለት አገር በቀል የሆነና በልምድ የካበተ እንዲሁም በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያገኘ ዕውቀት ሆኖ የዕጽዋትን ወይም የእንስሳትን ተዋጽኦ፣ የማዕድናት ወይም የእጅ ጥበብ በመጠቀም የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ነው፤

34. "የባህላዊ ሕክምና አዋቂ" ማለት ባህላዊ ሕክምና ለመስጠት አግባብ ባለው አካል የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

35. "ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና" ማለት ሀገር በቀል የባህላዊ ሕክምና ያልሆነና ከዘመናዊ የጤና ስርዓት ጋር ያልተጣመረ ሕክምና ሲሆን በተደጋጋፊነት ወይም በአማራጭነት እንዲሰጥ የተፈቀደ አገልግሎት ነው፤

36. "የተደጋጋፊ ወይም የአማራጭ ሕክምና ባለሙያ" ማለት ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና ለመስጠት በአስፈጻሚ አካሉ የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ነው፤

37. "የሙያ ሥራ ፈቃድ" ማለት የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

38. "የጤና ተቋም" ማለት የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ወይም የመድኃኒት ንግድ ሥራን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፤

39. "ልዩ የጤና ተቋም" ማለት ማንኛውም ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ስፔሻላይዝድ የጤና ማዕከል ወይም ሀኪሞችንና ከዚያ በላይ የሙያ ደረጃ ያላቸውን ባለሙያዎች የሚያሰለጥንና የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤

40. "ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም" ማለት ማንኛውም የኅብረተሰብ መገልገያ ተቋም ሲሆን፣ ትምህርት ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማዕከላት፣ የአሳዳጊ አልባ ህፃናት ማዕከላት፣ መዋዕለ ህፃናት፣ የገበያ ቦታዎች፣ የስፖርት ቦታዎች፣ የመታሻ ማዕከላት፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የጸጉር ቤቶችና የውበት ሳሎኖችን ይጨምራል፤

41. "ሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ" ማለት በሥራ አካባቢ የሚከሰቱ ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ኬሚካላዊ፣ ፊዚካላዊና ሥነ ሕይወታዊ ጎጂ ንጥረ ነገሮች በመከላከልና በመቆጣጠር ሠራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ ሳይንሳዊ፣

ቴክኖሎጂያዊና አስተዳደራዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የሠራተኞችን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሳይንስ ነው፤

42. "ባዮኢኩቫለንስ ማእከል" ማለት ሁለት ዓይነት የመድኃኒት ዝግጅቶች በፍቱንነታቸውና ደህንነታቸው የሚመሳሰሉ መሆናቸው በጥናት የሚረጋገጥበት ማእከል ነው፤
43. "አስፈጻሚ አካል" ማለት በፌዴራል ደረጃ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም አካል ነው፤
44. "አግባብ ያለው አካል" ማለት እንደአግባቡ አስፈጻሚ አካሉ ወይም የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ተግባራትን በክልል ደረጃ የማከናወን ሥልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ወይም በህግ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ አካል ነው፤
45. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስ ቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
46. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
47. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
48. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በምግብ፣ በመድኃኒት፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ በጤና ባለሙያዎች እና በጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ላይ በመላው አገሪቱ በሚካሄዱ የቁጥጥር ተግባሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል ደረጃ የዚህ አዋጅ ተፈጻሚነት የሚከተሉትን በሚመለከት ይሆናል፦
   ሀ/ በአገር አቀፍ ደረጃ የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች፣ የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ደረጃ ማውጣትን፤

ለ/ ለክልል ተሻጋሪ የምግብና የመድኃኒት ማምረት፣ ምግብና መድኃኒት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለማከፋፈል፣ ለማስተዋወቅና ለማከማቸት እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎች ፈቃድ መስጠትንና መቆጣጠርን፤

ሐ/ በበቂ መጠን የማይገኙ የጤና ባለሙያዎችን መመዝገብና የሙያ ፈቃድ መስጠትን፤

መ/ ከውጭ ሀገር አገልግሎት ለመስጠት የሚመጡ የጤና ባለሙያዎችን መመዝገብንና የሙያ ፈቃድ መስጠትን፤

ሠ/ ለልዩ የጤና ተቋማት ፈቃድ መስጠትንና መቆጣጠርን፤

ረ/ ከአንድ ክልል በላይ የሚነኩ የአካባቢ ጤና አገልግሎቶችን መከታተልንና መቆጣጠርን፤

ሰ/ በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ የሚካሄድ የኳራንቲን ቁጥጥር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማካሄድን፤ እና

ሸ/ ሌሎች ክልል ተሻጋሪ የምግብ፣ የመድኃኒት፣ ጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት አገልግሎቶችንና ተቋማትን የሚመለከቱ የቁጥጥር ሥራዎችን።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ለአስፈጻሚ አካሉ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉት የቁጥጥር ተግባራት በክልል መንግሥታት ተቆጣጣሪ አካላት የሚፈጸሙ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## ስለ አስፈጻሚ አካልና ተቆጣጣሪዎች

4. **የአስፈጻሚ አካሉ ሥልጣንና ተግባር**

አስፈጻሚ አካሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም የሕክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሠራር፣ የሀይ-ጅንና የአካባቢ ጤናን እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን የቁጥጥር ደረጃዎች አዘጋጅቶ አግባብ ላለው አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውንና መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
2. ለልዩ የጤና ተቋማት፣ ለመድኃኒት አምራች ድርጅቶች፣ ለጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪዎች፣ ለባዮኢኩቫለንስ ማእከላት፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና

ለአከፋፋይ ድርጅቶች እና ለክልል ተሻጋሪ የጤና አገልግሎት ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

3. የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተቋማት ጥራትና ብቃት የሚጠናከርበትንና የሚስፋፋበትን የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፣ ረቂቅ ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ለመንግሥት ውሳኔም ያቀርባል፤
4. የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን በሚመለከት የመረጃዎች ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
5. በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
6. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎችን ያደራጃል፤
7. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ምግቦች፣ መድኃኒቶች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶችና የአስከሬን ቁጥጥር ያካሂዳል፣ የመግቢያና የመውጫ ፍቃዶች ይሰጣል፤
8. የሀገሪቱን የመድኃኒት መዘርዝር ያዘጋጃል፣ በመዘርዝሩ የተካተቱትን መድኃኒቶች፣ በደረጃ ይመድባል፣ መዘርዝሩን እንደአስፈላጊነቱ ይከልሳል፤
9. የምዝገባ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ መድኃኒቶችን ይገመግማል፣ ይመዘግባል፣ ምዝገባውን ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
10. የምግቦችን ደህንነት፣ ጥራት እና የመድኃኒቶችን ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸውን ገበያ ላይ ከዋሉ በኋላ ለማረጋገጥ የድህረ ገበያ ቅኝት በማካሄድ ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ ያካሂዳል አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፤
11. የሕክምና ሙከራ ጥያቄዎችን እየመረመረ ይፈቅዳል፣ ሂደቱ በመልካም የሕክምና ስርዓት መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፣ ውጤቱንም ይገመግማል፣ ለሀገሪቱ በሚጠቅም ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፣ አስፈላጊ ሲሆንም የሕክምና ሙከራውን ያግዳል ወይም ያስቆማል፤
12. የናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች እና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ማምረትን፣ ማስመጣትን፣ መላክን፣ ማከፋፈልን፣ ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣

አጠቃቀምን፣ መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይቆጣጠራል፣ አለአግባብ መጠቀምን ይከላከላል፣ ለዓለም አቀፍ ናርኮቲክ ቁጥጥር ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፤

13. ትምባሆ ማስመጣትን፣ ስርጭትን፣ ሽያጭን፣ አጠቃቀምን፣ አስተሻሸግና መለያ አሰጣጥን፣ ማስተዋወቅንና አወጋገድን ይቆጣጠራል፤

14. ወደ አገር በሚገቡ አውሮፕላኖች ላይ ከጤና አጠባበቅና ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር ጋር ተያያዥነት ያለው ኢንስፔክሽን ያካሂዳል፣ እንዲሁም ከአገር በሚወጡ አውሮፕላኖች ላይ ርጭት ያካሂዳል ሰርተፊኬትም ይሰጣል፤

15. በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ወይም በሚወጡ አለም አቀፍ መንገደኞች ላይ ተላላፊ በሽታዎችን በተመለከተ ቁጥጥር ያካሂዳል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ፣ ከአገር እንዳይወጡ ወይም እንዲገለሉ ያደርጋል፤ ከአንድ ክልል በላይ የሆነ የወረርሽኝ በሽታ ሲከሰት አስፈላጊ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

16. በበቂ መጠን የማይገኙ የጤና ባለሙያዎች፣ ለአማራጭና ተደጋጋፊ ህክምና ባለሙያዎች እና በግልም ሆነ በቡድን ከውጭ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ለሚመጡ የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

17. የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎቻቸው በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤

18. ከተለያዩ ተቋማት የሚወጡ ክልል ተሻጋሪ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በሕዝብ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

19. ሕገወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችና የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

20. ከአንድ ክልል በላይ ለህብረተሰቡ ለመጠጥ የሚቀርብ ውኃ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

21. በፌዴራል መንግሥት ስር ያሉ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

22. በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

5. ስለተቆጣጣሪዎች

1. አስፈጻሚው አካል የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ላይ የወጡ ሌሎች ህጎችንና መመሪያዎችን ለማስፈጸም ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተመደበ ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ/ የምግብና የመድኃኒት አስመጪ፣ ላኪ፣ አምራች፣ አከፋፋይና አጓጓዥ ድርጅቶችንና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን በማናቸውም ክፍት በሆኑበት ሰዓት በመግባት የመቆጣጠር፤
   ለ/ በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ምግቦችን፣ መድኃኒቶችን፣ የመንገደኞች ክትባት ሰርተፊኬቶችን፣ አስክሬኖችን፣ አውሮፕላኖችንና በሌሎች ጤና ነክ ጉዳዮች ላይ የቁጥጥር ሥራዎችን የማከናወን፤
   ሐ/ ጤናን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖረው ወደ ማንኛውም ግቢ ወይም ሕንፃ በመግባት ፍተሻ የማካሄድ፤
   መ/ ምርመራ ለማድረግ ወይም መረጃ ለማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የምግቦችንና መድኃኒቶችን ናሙናዎችን የመውሰድ፣ ልኮችን የመውሰድ፣ ፎቶግራፎችን የማንሳትና መረጃዎችን ፎቶኮፒ የማድረግ፤
   ሠ/ የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣ የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦችና መድኃኒቶች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ የማድረግና ውጤቱ እስከሚታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ የማድረግ፤
   ረ/ ፍተሻ በሚካሄድበት ግቢ ወይም ሕንጻ ውስጥ የሚያገኝ ማንኛውም ዕቃ ወይም ማቴሪያል በጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ነው የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖረው የፍተሻው ውጤት እስከሚታወቅ ዕቃው ወይም ማቴሪያሉ ተለይቶ እንዲቀመጥ የማዘዝ፤
   ሰ/ ምግቦችና መድኃኒቶች የአገልግሎት ዘመናቸው ሲያበቃ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሲወሰን በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን የመቆጣጠር።

## ክፍል ሦስት

## የምግብ ደህንነትና ጥራት አስተዳደርና ቁጥጥር

6. **ስለምዝገባና ፈቃድ**

   1. ማንኛውም ምግብ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ መመረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት፣ መላክ፣ መዘጋጀት፣ መከማቸት፣ መከፋፈል፣ መጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ወይም ለህብረተሰቡ ሊቀርብ አይችልም።
   2. ማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት ከአስፈጻሚ አካሉ ፈቃድ ሳያገኝና ሳያስመዘግብ በምግብ ማምረቻ ተቋሙ የምርት አይነትና ሂደት ላይ ለውጥ ማድረግ አይችልም።

7. **የምግብ ደህንነትና ጥራት አጠባበቅ**

   1. ማንኛውም ምግብ ወይም የምግቡ ጥሬ እቃ፣ ጭማሪ ወይም ማሸጊያ ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟላ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ለአገልግሎት ሊውል አይችልም።
   2. ማንኛውም ምግብ አግባብ ያለው አካል ያወጣውን ወይም የተቀበለውን መሥፈርት ተከትሎ ጤናማ አጠባበቅ ሊደረግለት ይገባል።
   3. ማንኛውም ሰው የምግብ ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያቋቁመው ላቦራቶሪ ከአስፈጻሚ አካሉ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።
   4. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው የምግብ አገልግሎት ተቋም ሊያካሂድ አይችልም።
   5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
   6. ማንኛውም ምግብን በማምረት፣ በማዘጋጀት፣ በማከማቸት፣ ማከፋፈልና ማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም በተላላፊ በሽታ የተያዙ ከምርቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሠራተኞች ቀጥሮ ማሰራት የተከለከለ ነው፡፡

8. **ስለምግብ ማሸጊያዎችና ገላጭ ጽሑፍ**

   1. ማንኛውም የታሸገ ምግብ አምራች፣ አስመጭ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ምግቡ በአግባቡ ካልታሸገና ገላጭ ጽሁፍ ካልተደረገበት በስተቀር ለገበያ ሊያቀርበው ወይም በማናቸውም አኳኋን ሊያሰራጨው አይችልም።
   2. የማንኛውም የታሸገ ምግብ ገላጭ ጽሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ ሊሆን ይገባል፡፡

9. <u>ንጥረ ምግብ</u>

1. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የወጣውን ደረጃ ካላሟላ በስተቀር በንጥረ ምግብ ምርት ስራ ላይ መሰማራት አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው በአስፈጻሚ አካሉ ካልተፈቀደ በስተቀር የሚያመርታቸው የምግብ ምርቶች በንጥረ ምግብ የዳበሩ እንደሆኑ አድርጎ መግለጽ አይችልም።
3. ማንኛውንም በንጥረ ምግብ የዳበሩ የምግብ ምርት ማሸጊያ ላይ የንጥረ ምግቡ ዓይነትና ይዘት፣ የአጠቃቀም መመሪያና የአገልግሎት ጊዜ ማብቅያ በቀላሉ በማይለቅና በግልጽ መገለጽ ይኖርበታል።
4. ማንኛውም ሰው በሚያመርተው ወይም በሚያከፋፍለው የምግብ ጨው ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ አዮዲን ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

10. <u>ምግብን ወደ ሀገር ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለመላክ</u>

1. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የምግብ ምርት በሚመለከተው የላኪው ሀገር የመንግሥት አካል የተረጋገጠ የጥራትና የጤናማነት ሰርተፊኬት አብሮት ማምጣት ይኖርበታል።
2. ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የጤናማነት ሰርተፊኬት ለሚያስፈልጋቸው ምግቦች አስፈጻሚ አካሉ የጤናማነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፡

11. <u>ምግብን ማጭረር</u>

ምግብን በጨረራ የማከም ተግባር ሊካሄድ የሚችለው ይኸው ተግባር የሚጠይቀውን የደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥርዓት በአስተማማኝ ሁኔታ ማሟላቱ በአስፈጻሚ አካሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡

12. <u>ስለመጠጥ ውኃ ጥራት አጠባበቅ</u>

1. አግባብ ባለው አካል ጥራቱ ካልተረጋገጠ በስተቀር የምንጭ፣ የጉድጓድ ወይንም የቧንቧ ውኃ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው ከአስፈጻሚ አካሉ ፈቃድ ሳያገኝ የማዕድን ውኃም ሆነ የታሸገ ውኃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ወይም በአገር ውስጥ በማምረት ለሕብረተሰቡ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለመድኃኒቶች አስተዳደርና ቁጥጥር</u>

13. ስለመድኃኒት ምዝገባ

1. ማንኛውም መድኃኒት ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ በአስፈጻሚ አካሉ ሳይመዘገብ በአገር ውስጥ ተመርቶም ሆነ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም አስፈጻሚ አካሉ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ያልተመዘገቡ መድኃኒቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. የመድኃኒት ምዝገባ የምስክር ወረቀት መድኃኒቱ የምዝገባ መስፈርቶችን አሟልቶ እስከቀጠለ ድረስ በየአራት ዓመቱ ይታደሳል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከቱት አስገዳጅ ሁኔታዎች ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

14. የመድኃኒት ጥራት ደረጃና አግባባዊ አጠቃቀም

1. ማንኛውም መድኃኒት ወይም የመድኃኒቱ ጥሬ ዕቃ ወይም ማሸጊያ አግባብ ያለው አካል ባወጣው ወይም በተቀበለው ፋርማኮፒያ የተካተቱ ወይም በእንዲህ ዓይነቱ ፋርማኮፒያ ውስጥ ያልተካተተ ሲሆን በአምራች ፋብሪካዎች የወጡና ዓለም አቀፍ ወይም አግባብ ባለው አካል ዕውቅና ያገኙ የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።
2. ማንኛውም መድኃኒት ጥቅም ላይ እንዲውል ሲፈቀድ የነበረውን የደኅንነት፣ የፈዋሽነት ወይም የጥራት ባህሪ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ወይም የሚያስከትለው ጉዳት ከሚሰጠው ጥቅም አመዝኖ ሲገኝ መድኃኒቱ በጥቅም ላይ እንዳይውል ታግዶ ምዝገባው እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡
3. ማንኛውም መድኃኒት ጥቅም ላይ የሚውለው አስፈፃሚው አካል አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ በሚያወጣው ደረጃዎችና የአሰራር መመሪያዎች መሠረት መሆን አለበት።

15. ስለህክምና ሙከራ

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሕክምና ሙከራ በሰው ላይ ለማድረግ የሚቻለው በአስፈጻሚ አካሉ ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡
2. በሰዉ ላይ የሚደረግ የሕክምና ሙከራ የሚከናወነው ሰውየው በራሱ ላይ ሙከራው እንዲካሄድበት በጽሁፍ ከተስማማ ነዉ፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም በአጥቢና ነፍሰጡር እናቶች፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ሰዎች፣ በህግ ታራሚዎች፣ በአዕምሮ ሕመምተኞች ላይ የሕክምና ሙከራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአስፈላጊ ሁኔታዎች ምክንያት በአጥቢና ነፍሰጡር እናቶች፣ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ሰዎች፣ በሕግ ታራሚዎች፣ በአዕምሮ ሕመምተኞች እና በሙከራ አድራጊው ባለሙያ ወይም ድርጅት ሥር ባሉ ሰዎች ላይ የሕክምና ሙከራ ማድረግ የሚቻለው ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሠረት ከአስፈፃሚ አካል ልዩ ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነው።
5. የሕክምና ሙከራ እንዲያካሂድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የደረሰበትን ውጤት ለአስፈጻሚ አካሉ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡
6. የሕክምና ሙከራ አድራጊው ባከናወነው የሕክምና ሙከራ ጉዳት ለደረሰበት ሰው በደረሰበት የጉዳት መጠን ልክ ተገቢውን ካሳ መክፈል አለበት፡፡

16. <u>ስለመድኃኒት ማሸጊያዎችና ገላጭ ጽሑፍ</u>

1. ማንኛውም የመድኃኒት አምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ወይም የጤና ተቋም መድኃኒቱ በአግባቡ ካልታሸገና ገላጭ ጽሑፍ ካልደተረገበት በስተቀር ለገበያ ሊያቀርበው ወይም በማናቸውም አኳኋን ሊያሰራጨው አይችልም።
2. የማንኛውም መድኃኒት ገላጭ ጽሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ ሊሆን ይገባል፡፡

17. <u>መርዞች፣ ጨረራ አፍላቂ መድሃኒቶች እና ፀረ-ተባዮች</u>

1. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያገኝ መርዞችን ወይም ጨረራ አፍላቂ መድሃኒቶችን ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ አይችልም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ያመረታቸውን፣ ያስመጣቸውን፣ ያከፋፈላቸውን ወይም የሸጣቸውን መርዞች ወይም ጨረራ አፍላቂ መድሃኒቶች በተመለከተ ሪከርድ መያዝና አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

3. ፀረ-ተባዮች፣ መርዞችና ጨረራ አፍላቂ መድሃኒቶች የሚታሸጉት፣ የሚጓጓዙት፣ የሚከማቹትና የሚሰራጩት በሰዎች፣ በእንሰሳትና በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን አደጋ መቀነስ በሚያስችል ሁኔታ መሆን አለበት፡፡
4. አስፈጻሚው አካል ፀረ-ተባዮችን ማምረት፣ ማጓጓዝ፣ ማከማቸት፣ አጠቃቀምና አወጋገድ አስመልክቶ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ አግባብ ካለው አካል ጋር በጋራ ይሰራል።

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሣይኮትሮፒክ ንጥረ</u>

<u>ነገሮችና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች</u>

18. <u>ልዩ ፈቃድ ስለማስፈለጉ</u>

1. ማንኛውም ሰው ናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም ፕሪክ-ርሰር ኬሚካሎችን ለማስመጣት፣ ለመላክ፣ ለማምረት፣ ለማከፋፈል፣ ለማከማቸት ወይም ለመያዝ ከአስፈጻሚ አካሉ ልዩ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ልዩ ፈቃድ የሚሰጠው መድኃኒት ማስመጣትን፣ መላክን፣ ማምረትን፣ ማከፋፈልን ወይም ማከማቸትን ወይም የጤና አገልግሎት መስጠትን በሚመለከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላለው ሰው ብቻ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች መሠረት የናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን ወይም ፕሪክርሰር ኬሚካሎችን ለማስመጣት ወይም ለመላክ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ የሚያገለግለው ክተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ አንድ ጊዜ ለማስመጣት ወይም ለመላክ ብቻ ይሆናል፡፡
4. ናርኮቲክ መድኃኒቶችን፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን ወይም ፕሪክርሰር ኬሚካሎችን፡-

ሀ/ በፖስታ ቤት ወይም በመርከብ ማስመጣት ወይም መላክ፣ ወይም

ለ/ ከሌሎች መድኃኒቶች ወይም ዕቃዎች ጋር አሽጎ ማስመጣት ወይም መላክ፤

አይፈቀድም።

19. <u>ስለ መድኃኒት አስተዛዘዝ ሥርዓት</u>

1. የናርኮቲክ መድኃኒቶችንና የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን ማዘዝ የሚችለው ልዩ ፈቃድ የተሰጠው የሕክምና ባለሙያ እንዲሰራ በተፈቀደለት ጤና ተቋም ብቻ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የሕክምና ባለሙያ የናርኮቲክ መድኃኒቶችንና ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን ለራሱ ማዘዝ አይችልም።
3. ናርኮቲክ መድኃኒት ወይም ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገር የሚታዘዘው በልዩ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ብቻ ይሆናል፡፡

20. <u>ስለአያያዝና ሪፖርት አቀራረብ</u>

1. የናርኮቲክ መድኃኒቶችና ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች የእነዚሁ ኢንቮይሶች፣ መዝገቦችና የማዘዣ ወረቀቶች ቁልፍ ባለው የብረት ሳጥን ውስጥ ወይም በተለየ ክፍል ውስጥ መቀመጥና ቁልፉም በተፈቀደለት የመድኃኒት ባለሙያ እጅ መያዝ አለበት።
2. ማንኛውም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ስለናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎች አስፈጻሚ አካሉ ባወጣው መመሪያ መሠረት ሪከርድ መያዝና ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

21. <u>ስለአወጋገድና ሥራ ስለማቋረጥ</u>

1. ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የተበላሹ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ወይም በሕገወጥነት የተያዙ ናርኮቲክ መኃኒቶችን፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችን ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን በተለየ ቦታ ይይዛል፣ አስፈጻሚ አካሉ በሚያወጣው መመሪያ መሠረትም እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡
2. ማንኛውም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራውን ሲያቋርጥ በእጁ ስለሚገኙ ናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎችና ስለነዚሁ ኢንቮይሶች፣ መዝገቦችና ማዘዣ ወረቀቶች አስፈጻሚ አካሉ ባወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መፈጸም አለበት።

22. <u>ስለትንባሆ ቁጥጥር</u>

1. ማንኛውም ሰው ትምባሆ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ለማከፋፈል ከአስፈጻሚው አካል ልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. የትምባሆ ማስመጣት፣ ማከፋፈል፣ ሽያጭ፣ አጠቃቀም፣ አስተሻሸግና ገላጭ ጽሁፍ፣ የማስተዋወቅና የአወጋገድ ተግባራት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## የሀይጅን፣ አካባቢ ጤና አጠባበቅና ተላላፊ
## በሽታዎች ቁጥጥር

### 23. ስለሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት

1. ማንኛውም ቀጣሪ የሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች ለሰራተኞቹ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. አስፈጻሚ አካሉ ስለሥራ ነክ ጤና አጠባበቅና ስለ መሳሪያ አጠቃቀም ተገቢውን መመሪያ ያወጣል።

### 24. ስለአደገኛ ኬሚካሎች

1. ማንኛውንም ኬሚካል ከምግብ ጋር ወይም አካባቢን በሚበክልና በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ ማጓጓዝ ወይም ማከማቸት የተከለከለ ነው።
2. አደገኛ ኬሚካሎችን በማዘጋጀት፣ በማጓጓዝና በማከማቸት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው አካባቢን እንዳይበክልና በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈጻሚ አካሉ የሚያወጣውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

### 25. ስለግንባታ ሥራዎች

ለማንኛውም አገልግሎት የሚውል ግንባታ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው አስፈጻሚ አካሉ ከሕዝብ ጤና አጠባበቅ አንጻር የሚያወጣቸውን መስፈርቶች ማክበር አለበት፡፡

### 26. በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ስለሚደረግ የጤና አጠባበቅ ቁጥጥር

1. ማንኛውም ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣ መንገደኛ ሀገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የጤና አጠባበቅ መስፈርቶች መሠረት ለዓለም አቀፍ መንገደኞች የሚጠየቀውን ክትባት የመውሰድ፣ በመግቢያና መውጫ ኬላ ላይ ሲጠየቅ የክትባት ደብተሩን ለሚመለከተው የጤና ኃላፊ የማሳየትና በተላላፊ በሽታ ሲጠረጠርም ለምርመራ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. አግባብነት ያለው የጤና ማስረጃ ያልያዘ ወይም በህብረተሰቡ ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ወረርሽኝ ካለበት ቦታ የመጣ ሰው ወደ ሀገር እንዳይገባ ሊታገድ ይችላል፡፡
3. በመግቢያ ወይም በመውጫ ኬላ ላይ የተጠረጠረ ሰው ሲያጋጥም የሚመለከተው ኃላፊ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኘው የጤና ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

4. የጤና የምስክር ወረቀት ሳይያዝና መከላከያ ሳይደረግ እንስሳትን ከመንገደኞች ጋር ማጓጓዝ የተከለከለ ነው።

## 27. ስለተላላፊ በሽታዎች

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በአቅራቢያዉ የተላላፊ በሽታን መኖር ባወቀ ጊዜ ይህንኑ ወዲያውኑ በቅርቡ ላለው የጤና አገልግሎት ተቋም የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ የጤና ተቋሙም አስፈላጊውን እርምጃ እየወሰደ ለህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አግባብ ያለው የጤና ባለሙያ በወረርሽኝ ተላላፊ በሽታ የተያዘን ወይም የተጠረጠረን ማንኛውም ሰው ለተወሰነ ጊዜ ተገልሎ እንዲቆይ ማድረግ አለበት፡፡
3. በወረርሽኝ ተላላፊ በሽታ የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ለምርመራ፣ ለሕክምና ወይም ለክትባት ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡
4. ቤተሰቦች ወይም አሳዳጊዎች ህጻናትን ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል የማስከተብ ግዴታ አለባቸዉ።

## 28. ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች

1. ማንኛውም ሰው በወረርሽኝ መልኩ ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች የተጠቃ ከሆነ ወይም በዚሁ በሽታ መያዙ ከተጠረጠረ ወይም በሽታው ከተከሰተበት አካባቢ ከመጣ በሽታውን ለመከላከል ሲባል ለሚደረግ ቁጥጥር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና አገልግሎት ተቋም ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች በደረጃው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠትና ከአቅሙ በላይ ከሆነ ህክምና ማግኘት ወደሚችልበት ጤና ተቋም በወቅቱ የመላክ ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የጤና አገልግሎት ተቋም ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን አስመልክቶ በየጊዜዉ የሚወጡ የመከላከልና የመቆጣጠሪያ መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

## 29. የአስከሬን አያያዝና ዝውውር

1. በአስፈጻሚ አካሉ ካልተፈቀደ በስተቀር አስክሬንን ወይም አጽምን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ከሀገር እንዲወጣ ማድረግ የተከለከለ ነው።
2. ማንኛውም ሰው አስከሬንን ወይም አጽምን ለመቅበር፣ ቆፍሮ ለማውጣት፣ ለማዘዋወር አስፈጻሚ አካሉ ያወጣውን የጤና አጠባበቅ መስፈርት ማሟላት አለበት።

30. <u>ስለቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ</u>

1. ማንኛውም ሰው ደረቅ፣ ፍሳሽ ወይም ሌሎች ቆሻሻዎችን አካባቢን በሚበክልና በጤንነት ላይ ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ማከማቸት ወይም ማስወገድ የለበትም፡፡
2. ከጤና ወይም ምርምር ተቋም የሚወጣ ደረቅ፣ ፍሳሽ ወይም ሌላ ቆሻሻ በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ አለበት፣ አወጋገዱም አስፈጻሚ ያወጣቸውን ደረጃዎች ማሟላት አለበት።
3. ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች፣ ከማስረጊያዎችና ከኢንዱስትሪ የሚወጣውን ጤና የሚበክል ያልታከመ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ አካባቢ፣ ወደ ውኃ አካላት ወይም ወደ ውኃ አካላት መገናኛዎች መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡

31. <u>የመጸዳጃ ቤት እንዲኖር ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ንጽህናው የተጠበቀ በቂ የመጸዳጃ ቤት የማዘጋጀትና ለደንበኞች ክፍት የማድረግ ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም የከተማ ወይም የገጠር አስተዳደር የሕዝብ መጸዳጃ ቤት እንዲኖርና ንጽህናዉም ሁልጊዜ የተጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

32. <u>የመታጠቢያ ስፍራዎችንና የመዋኛ ገንዳዎችን ስለመቆጣጠር</u>

1. የሕዝብ መታጠቢያ ስፍራ፣ መዋኛ ገንዳ፣ የተፈጥሮ እንፋሎት ወይም የፍል ውኃ መታጠቢያ አዘጋጅቶ ለሕዝብ አገልግሎት የሚያቀርብ ማንኛውም ድርጅት አስፈጻሚ አካሉ ያወጣውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡
2. የሕዝብ መታጠቢያ ወይም የመዋኛ ቦታ አዘጋጅቶ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው አገልግሎቱን የማይታይ ወይም ግልጽ የሆነ የቆዳ ሕመም ወይም ቁስል ላለባቸው ሰዎች መፍቀድ የለበትም።

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ስለጤና ባለሙያዎች</u>

33. <u>የሙያ ፈቃድ አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛውም ሰው እንደ ጤና ባለሙያ ለመስራት አግባብ ካለው አካል የሙያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ለማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠ የሙያ ሥራ ፈቃድ በየአምስት ዓመቱ የሙያ ሥነ-ምግባርና ሙያዊ ብቃቱ ተገምግሞ መታደስ አለበት።

3. የሙያ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት የጤና ባለሙያ በጤና ባለሙያነቱ ሊሰራ አይችልም።
4. የሙያ ፈቃዳቸው የታገደባቸውና የተሰረዘባቸውን ባለሙያዎች በተመለከተ አግባብ ያለው አካል ለሕዝብ መረጃ ማድረስ አለበት።

34. <u>የአገልግሎት ደረጃና ወሰን</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ በአስፈጻሚ አካሉ በተቀመጠው የአገልግሎት ደረጃና በተወሰነው የሙያ ወሰን መሠረት መሥራት አለበት።

35. <u>ሥነ-ምግባር</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ አግባብ ባለው የሙያ ሥነ-ምግባር መሠረት ግዴታውን መወጣት አለበት።
2. የጤና ባለሙያዎች አጠቃላይ የሥነ-ምግባር ሁኔታ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ የጤና ባለሙያዎች የሥነ-ምግባር ደንብ ይወሰናል፡፡

36. <u>ሪፖርት ስለማድረግ</u>

1. ሙያዊ ስህተት መፈጸሙን ያወቀ የጤና ባለሙያ ወይም ማንኛውም ሰው አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሪፖርት መደረግ አለባቸው ተብለው በህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል የተለዩ ተላላፊ በሽታዎች መኖራቸውን ባወቀ ወይም በጠረጠረ ጊዜ ባፋጣኝ ለህብረተሰብ ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

37. <u>የታካሚዎች መረጃ እና የጤና ተቋማት ግዴታዎች</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በጤና ተቋም ዉስጥ ከታካሚ ጋር በተደረገ በእያንዳንዱ ግንኙነት የተገኙ የግል ጤና መረጃዎችን አሟልቶ መመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና አገልግሎት ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተመዘገቡ የታካሚዎች የግል ጤና መረጃዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡
3. ህጋዊ በሆነ ምክንያት ካልተጠየቀ በስተቀር ማንኛዉም የታካሚ የግል ጤና መረጃ በምስጢር መጠበቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ መሠረት የተገኘና የተያዘ የታካሚዎች የጤና መረጃ በወቅቱ ተጠናቅሮ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

38. <u>የድንገተኛ ሕክምናና ሪፈራል</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ደረጃው በሚፈቅደው መሠረት የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት የመስጠት ሀላፊነት አለበት፡፡
2. የጤና ባለሙያው በሚሰራበት የጤና ተቋም ደረጃ መሠረት ተገቢውን የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት መስጠት ያልቻለ እንደሆነ ታካሚውን ተፈላጊውን አገልግሎት ሊያገኝ ወደሚችልበት አግባብ ያለው የጤና ተቋም ሪፈራል ስርአቱን በመከተል ወዲያውኑ ሪፈር ማድረግ አለበት፡፡

39. <u>መድኃኒት ስለማዘዝና ማደል</u>

1. መድኃኒቶችን ማዘዝ የሚችለው አግባብ ባለው አካል የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው የሕክምና ባለሙያ ብቻ ይሆናል።
2. ማንኛውም የህክምና ባለሙያ መድኃኒት የሚያዘው የመድኃኒት አስተዛዘዝ ሥርዓትን በመከተልና ደረጃዉን ጠብቆ በተዘጋጀ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ላይ ይሆናል፡፡
3. መድኃኒቶች የሚታደሉት በመድኃኒት ባለሙያ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጤና ኢክስቴንሽን ባለሙያዎችና በአስገዳጅ ሁኔታዎች በሌሎች የጤና ባለሙያዎች መድኃኒቶች ስለሚታደሉበት ሁኔታ አስፈፃሚ አካሉ በሚያወጣው መመሪያ ሊፈቀድ ይችላል፡፡
5. ማንኛውም መድኃኒት ለማደል ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ የመድኃኒት እደላ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ በቂ መረጃና ግንዛቤ በመስጠት በጥንቃቄ ማደል አለበት፡፡
6. በመድኃኒት አስተዛዘዝ ስርዓት መሠረት ያለሀኪም ትዕዛዝ ከሚሰጡ መድኃኒቶች በስተቀር ማንኛዉም በመድኃኒት ማደል ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት መድኃኒቶችን ማደል አይችልም።

40. <u>ቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪዎች</u>

1. ማንኛውም የጤና ተቋም የቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በተግባር እንዲለማመዱ ሲፈቀድ የጤና ተቋሙና ትምህርት ቤቱ ልምምዳቸውን የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም የቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪ በታካሚ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

<u>ክፍል ስምንት</u>

## ስለጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት

### 41. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

1. የጤና ተቋምን ለማቋቋም ወይም የመድኃኒት ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለዉ አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

### 42. የጤና አገልግሎት ተቋም ደረጃ

አስፈጻሚ አካሉ የጤና ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት ዓይነትና ደረጃ ይወስናል።

### 43. ሥራ ስለማቋረጥ

ማንኛውም የጤና ተቋም ወይም የመድኃኒት ንግድ ድርጅት ሥራውን ሲያቋርጥ በይዞታው ስለሚገኙ መድኃኒቶችና ስለእነዚሁ ኢንቮይሶች፣ መዝገቦችና ማዘዣ ወረቀቶች አስፈጻሚ አካሉ ባወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መፈጸም አለበት፡፡

### 44. ስለ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም

ማንኛውም ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም በአስፈጻሚ አካሉ የወጡ የጤና አጠባበቅ ደረጃዎችን ማሟላት አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለባህላዊና ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና

### 45. ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት

ማንኛውም በአገር ውስጥ የሚመረት ወይም ከውጭ የሚመጣ ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት በአስፈጻሚ አካሉ ተገምግሞ ሳይመዘገብ አገልግሎት ላይ ሊውል አይችልም።

### 46. የባህላዊ፣ የተደጋጋፊ ወይም የአማራጭ ሕክምና ባለሙያ

1. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል የሙያ ፈቃድ ሳያገኝ በባህላዊ፣ በተደጋጋፊ ወይም በአማራጭ ሕክምና ሊሰማራ አይችልም።
2. የባህላዊ፣ የተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና የሙያ ፈቃድ በየአምስት ዓመቱ የባለፈቃዱ የሙያ ሥነ-ምግባርና ብቃት እየተገመገመ መታደስ አለበት፡፡
3. ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት የባህላዊ፣ የተደጋጋፊ ወይም የአማራጭ ሕክምና ባለሙያ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም።

47. <u>ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ</u>

1. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል ከተፈቀደለት ቦታ ዉጭ የባህላዊ፣ የተደጋጋፊ ወይም የአማራጭ ሕክምና አገልግሎት መስጠት አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ አይችልም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

<u>ክፍል አስር</u>

<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና የቅሬታ አቀራረብ</u>

48. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

1. አግባብ ባለዉ አካል የብቃት ማረጋገጥ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ወይም ለአዋጁ አፈጻጸም የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ የተሰጠው የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
2. አግባብ ያለው አካል ማንኛውም መድኃኒት ወይም ምግብ ለአገልግሎት ብቁ አለመሆኑን ሲያረጋግጥ መድኃኒቱን ወይም ምግቡን ለመያዝና በባለቤቱ ወይም በባለይዞታው ወጪ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረዉ በጤና አገልግሎት ወይም በመድኃኒት ንግድ ሥራ ተሰማርቶ ከተገኘ አግባብ ያለው አካል ተቋሙን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

49. <u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ የተከለከለ የምስክር ወረቀቱ ወይም ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው ቅሬታውን እርምጃው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ አግባብ ያለው አካል ላቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ቅሬታ የቀረበለት አካል በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 50. ስለንግድ ማስታወቂያዎች

1. የምግብ፣ የመድኃኒት ወይም የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በማናቸውም መንገድ የሚተላለፍበት ሁኔታ አስፈጻሚ አካሉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን ወይም ማስታወቂያ አስተላላፊ አካል አስፈጻሚ አካሉ ያወጣውን መመሪያ አክብሮ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡
3. አስፈጻሚ አካሉ የምግብ፣ የመድኃኒት ወይም የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያ አስመልክቶ የሚወጣው መመሪያ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

### 51. መረጃ ስለመስጠት

1. የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞች አግባብ ያለው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ስለሥራቸዉ መረጃ የማቅረብ ግዴታ ይኖርባቸዋል።
2. የክልል ተቆጣጣሪ ወይም ውክልና የተሰጣቸው አካላት ስለሰጡት፣ ስላገዱት እና ስለሰረዙት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የሙያ ፈቃድ ለአስፈጻሚ አካሉ መረጃ የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው።

### 52. የመተባበር ግዴታ

አስፈጻሚ አካሉ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ።

### 53. ቅጣት

1. በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፤

   ሀ/ ማንኛውም የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ሰዉ፡-

   1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ /2/ /ሀ/ መሠረት ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ተግባሩን እንዳያከናውን እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከብር 10,000 በማያንስና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

2. አግባብ ያለውን አካል ሳያስፈቅድ ፈቃዱን በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ካስተላለፈ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

ለ/ ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው የመድኃኒት አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ካከፋፈለ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

ሐ/ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው በመድኃኒት ንግድ ወይም ጤና አገልግሎት ከተሰማራ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

መ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 15 በመጻረር የሕክምና ሙከራ ያካሄደ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማያንስና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

ሠ/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 ወይም 50 በመጻረር የንግድ ማስታወቂያዎችን ያስተላለፈ ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ረ/ ማንኛውም ሰው የናርኮቲክ መድኃኒቶች ወይም ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ሕገ-ወጥ አጠቃቀም ለመገፋፋት በማናቸውም መንገድ ካስተዋወቀ ወይም ሌሎች እንዲያስተዋውቁ ካደረገ ወይም ከፈቀደ ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ከሚኖራቸው አግባብነት ያለው ጠቀሜታ ውጭ በሆነ ሁኔታና ለሕገ-ወጥ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ማምረት ተግባር ያዋለ እንደሆነ ከሰባት ዓመት በማያንስና ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 30,000 በማያንስና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

ሰ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ስለምግብ ደህንነትና ጥራት ወይም አንቀጽ 8 ስለምግብ ማሸጊያዎችና ገላጭ ጽሁፍ የተደነገገውን

የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 20,000 በማያንስና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

ሸ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 6 ስለምግብ ምዝገባና ፈቃድ፣ አንቀጽ 9 ስለንጥረ ምግብ ደረጃና ገላጭ ጽሑፍ ወይንም አንቀጽ 11 ምግብን ስለማጭረር ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 10,000 በማያንስና ከብር 20,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ቀ/ የዚህን አዋጅ፣

1) አንቀፅ 12 ስለመጠጥ ውኃ ጥራት አጠባበቅ ድንጋጌን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 20,000 በማያንስና ከብር 40,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤
2) አንቀጽ 24 ስለአደገኛ ኬሚካሎች ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

በ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ /1/ ስለሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 20,000 በማያንስና ከብር 40,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ተ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 25 ስለግንባታ ሥራ መስፈርቶች ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከሦስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ቸ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 31 መጸዳጃ ቤት ስለማዘጋጀት ወይም አንቀጽ 32 ስለመታጠቢያ ስፍራዎችና መዋኛ ገንዳዎች ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 3,000 በማያንስና ከብር 5,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፤

ኀ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 33 ስለሙያ ፈቃድ ወይም አንቀጽ 34 ስለአገልግሎት ደረጃና ወሰን ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤

ነ/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ፣

1) አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ /1/ ተላላፊ በሽታን ስለማሳወቅ ወይም /2/ በወረርሽኝ ተላላፊ በሽታ የተያዘ ወይም የተጠረጠረን ሰው ስለመለየት ድንጋጌ ከተላለፈ ከስድስት ወር በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 3,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤
2) አንቀጽ 36 ሪፖርት ስለማድረግ ድንጋጌ ከተላለፈ ከስድስት ወር በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤
3) አንቀጽ 37 ስለታካሚዎች መረጃ እና የጤና ተቋማት ግዴታዎች ድንጋጌ ከተላለፈ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

ኘ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 ስለባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት ምዝገባ፣ አንቀጽ 46 ስለባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ባለሙያ ፈቃድ ወይም አንቀጽ 47 ስለባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

2 ማንኛውም አግባብ ያለው አካል ሠራተኛ ወይም ኃላፊ መደለያ በመቀበል ወይም በዝምድና ወይም አግባብ ባልሆነ ሌላ ግንኙነት በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ከተደነገገው ውጭ፤

ሀ/ መድኃኒትን፣ ምግብን ወይም የጤና ወይም ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም አገልግሎትን በሚመለከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያደሰ ወይም እንዲሰጥ ወይም እንዲታደስ ያደረገ፣ ወይም

ለ/ የመድኃኒት ወይም ምግብ ምርት ወይም መድኃኒት ወይም ምግብ ለማምረት የሚያገለግል ጥሬ ዕቃ ተገቢውን የደህንነት፣ የፈዋሽነትና የጥራት ደረጃ ግምገማ ሳያደርግ አገልግሎት ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም እንዲፈቀድ ያደረገ፣

እንደሆነ በወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከሰባት ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 30,000 በማያንስና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው ቅጣት መደለያ በሰጠው ባለጉዳይ ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተውን ጥፋት በመፈጸም ተግባር የተሳተፈና ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ጥፋትና ስለተባባሪዎቹ ማና በቂ መረጃ የሰጠን ሰው የፍትህ ሚኒስቴር በዚህ ሕግ መሠረት ክስ እንዳይመሠረትበት ሊያደርግ ይችላል።

54. <u>ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ/ የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 176/1991፣ እና

ለ/ የሕዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 200/1992፡፡

2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

55. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

2. ክልሎች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ።

3. አስፈጻሚ አካሉ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

56. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም**
**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 204/2003

## የምግብ ጨው አዮዲን እንዲኖረዉ ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 9(4) መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የምግብ ጨው አዮዲን እንዲኖረው ለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 204/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

   1. "አዮዲን ያለዉ ጨው" ማለት ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲሆን አግባብ ባለው አካል በሚወሰነው መመዘኛ መሠረት ጨው ከአዮዲን በመደባለቅ የተዘጋጀ ጨው ነው፤
   2. "አዮዲን የሌለዉ ጨው" ማለት ለሰው ምግብ አገልግሎት የማይውሉ ምርቶችን ለማዘጋጀት ወይም ለማምረት የሚያገለግል ጨው ነዉ፤
   3. "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤
   4. "ማሸጊያ" እና "ገላጭ ጽሑፍ" በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (21) እና (22) የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤
   5. "ተቆጣጣሪ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመደበ ተቆጣጣሪ ነው፤
   6. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፤
   7. "አግባብ ያለዉ አካል" ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ነው፤
   8. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

9. ማንኛውም ከወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በማናቸውም ሁኔታ ለሰው ምግብነት አገልግሎት በሚውል ጨው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ለምግብነት የሚውል ጨዉ አዮዲን እንዲኖረዉ ስለማስፈለጉ</u>

ማንኛውም ሰው አዮዲን የሌለው ጨው ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲውል ማዘጋጀት፣ ወደ ሀገር ዉስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ ወይም መሸጥ አይችልም።

5. <u>አዮዲን ያለዉ ጨው ደረጃ</u>

1. ማንኛውም ለሰው ምግብነት የሚውል አዮዲን ያለው ጨው አግባብ ባለው አካል በሚያወጣው የጨው ደረጃዎች መሰረት የጥራት ደረጃና መመዘኛ ማሟላት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው ወደ ሃገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ የጤናማነት ምስክር ወረቀት ማምጣት ይኖርበታል።

6. <u>አዮዲን ያለው ጨው አስተሻሸግና ገላጭ ጽሑፍ</u>

1. አዮዲን ያለው ጨው ማሸጊያ በጨው ውስጥ ያለው አዮዲን ሳይባክን እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችል የጥራት ደረጃ ያለው መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም አዮዲን ያለው ጨው የሚከተሉት ገላጭ ጽሑፎች በእሽጉ ላይ በግልጽ ሰፍረው ሊታዩበት ይገባል፡-

   ሀ/ የታሸገው ጨው አዮዲን ያለው መሆኑን፣

   ለ/ የአዘጋጁን ስምና ሙሉ አድራሻ፤

   ሐ/ የጨውን የተጣራ ክብደት፤

   መ/ ጨዉ የተዘጋጀበትና የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃበትን ወርና ዓመት ምህረት፤

   ሠ/ የእሽጉን የመለያ ቁጥር፤ እና

   ረ/ ጨው በቀዝቀዛ፣ ንጹህና ደረቅ ሥፍራ ላይ መከማቸት ያለበት መሆኑን።

7. <u>ስለቁጥጥር</u>

1. ማንኛውም ተቆጣጣሪ በማንኛዉም የጨዉ ማዘጋጃ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣ ወይም መሸጫ ቦታ በመገኘት ለሰው ምግብነት የሚውል ጨው አዮዲን ያለበት መሆኑን ለመመርመርና ለማረጋገጥ ይችላል፡፡
2. ተቆጣጣሪዉ ተግባሩን በሚያከናወንበት ወቅት በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

8. <u>አዮዲን ስለሌለው ጨው</u>

አዮዲን የሌለው ጨው ለኢንዱስትሪ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ስለሚዘጋጅበት፣ ወደ ሀገር ዉስጥ ስለሚገባበት፣ ስለሚከማችበት፣ ስለሚከፋፈልበት፣ ለሽያጭና ለአገልግሎት ስለሚውልበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመምክር መመሪያ ሊያወጣና አፈጻጸሙን ለመከታተል ይችላል፡፡

9. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>ቅጣት</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የወጡትን መመሪያዎች ተላልፎ ቢገኝ አግባብ ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

12. <u>ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በደንቡ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

13. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 16 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ደንብ ቁጥር 299/2006

## የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 55/1/ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤
   2. "ምግብ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(1) መሰረት የተሰጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ በምግብ አምራች ድርጅት ተመርቶ ከአንድ ክልል በላይ ወይም ለውጭ አገር ገበያ ሽያጭ የተዘጋጀ ምርት ነው፤
   3. "የምግብ አምራች" ማለት ምግብ በማምረት ከአንድ ክልል በላይ ወይም ለውጭ አገር ገበያ ሽያጭ የሚቀርብ ምግብ የሚያመርት ተቋም ነው፤ ሆኖም ባህላዊ ምግቦችን የሚያዘጋጁ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን አይጨምርም፤
   4. "የምግብ ደህንነት" ማለት ምግብን በተገቢው መንገድ በማምረት፣ በማዘጋጀት፣ በመያዝ፣ በማከማቸትና በማጓጓዝ ለተጠቃሚ በማቅረብ ሂደት ምግብ ለጤና ተስማሚ ስለመሆኑ ማረጋገጥና መቆጣጠር ነው፤
   5. "ምግብን ማጭረር" ማለት ምግብን ለጨረራ ሀይል በማጋለጥ ጎጂ ባክቴሪያዎችንና ሌሎች ተዋህስያንን በመግደል የቆይታ ጊዜውን ለማራዘም የሚከናወን ሂደት ነው፤
   6. "ለብክለት ተጋላጭ ምግብ" ማለት ለበሽታ አምጪ ጥቃቅን ሕዋሳት ዕድገት ወይም ለመርዞች መመረት የተመቻቸ ወይም የተጋለጠ ምግብ ነው፤

7. "በቅድሚያ የታሸጉ ምግቦች" ማለት ሻጩ ጋር ከመድረሱ በፊት በአምራቹ የታሸገ ምግብ ነው፤

8. "ተጨማሪ ምግብ" ማለት ማንኛውም የመደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ የንጥረ ምግብ ወይም ፊዚዮሎጂካል ጥቅም ያላቸው የቫይታሚን ወይም የማዕድን ወይም የሌሎች ንጥረ ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበት በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ በካፕሱል፣ በእንክብል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በጠብታ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ነው፤

9. "የጨቅላ ሕጻን ምግብ" ማለት ከእንስሳ ወይም አትክልት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ አግባብ ባለው የጨቅላ ሕጻን ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀና ከውልደት እስከ መጀመሪያዎቹ ስድስት ወር እድሜ ውስጥ ላለ የጨቅላ ሕጻን የንጥረ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት የተዘጋጀ ምግብ ነው፤

10. "የሕጻን ምግብ" ማለት ከእንስሳ ወይም አትክልት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ አግባብ ባለው የሕጻን ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀና ጨቅላ ሕጻንና ከስድስት ወር እድሜ በላይ የሆነን ሕጻንን ለመመገብ ተስማሚ እንደሆነ የተገለፀ ወይም በሌላ መልኩ ገበያ ላይ የዋለ ምግብ ነው፤

11. "ማሟያ ምግብ" ማለት የእናት ጡት ወተት፣ የጨቅላ ሕጻን ወይም የሕጻን ምግብ ለሕጻኑ የምግብ ፍላጎት በቂ ሳይሆን ሲቀር ለምግቦቹ ማሟያነት ተስማሚ ሆኖ በፋብሪካ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፤

12. "ልውጥ ሕያው ምግብ" ማለት በዘረመል ምህንድስና የተለወጠ የስጋ ወይም ለምግብነት ሊውል የሚችል የእፅዋት ተዋፆ ነው፤

13. "የአልኮል መጠጥ" ማለት በማንኛውም መጠን የአልኮል ይዘት ያለው መጠጥ ነው፤

14. "መሸጥ" ማለት ለንግድ ዓላማ ምግብን፣ መድኃኒትን ወይም የትምባሆ ምርትን ለሽያጭ ማቅረብ፣ ማስተዋወቅ፣ መያዝ፣ ማከማቸት፣ ለዕይታ ማቅረብ፣ ማስተላለፍ ወይም መለወጥን ይጨምራል፤

15. "ፋርማሲዮቲካል ምርት ሰርተፍኬት" ማለት አንድ መድኃኒት ፈቃድ ባለው አምራች የተመረተ መሆኑን የሚያረጋግጥ በባለሥልጣኑ ወይም በሚመረትበት አገር ተቆጣጣሪ አካል የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

16. "የመልካም አመራረት አሰራር" ማለት ማንኛውም የምግብ ወይም የመድኃኒት አምራች ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ ምግብ ወይም ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ

የተረጋገጠ መድኃኒት ማምረት እንዲችል በማምረት ሂደት ወጥነት ባለው ሁኔታ ሊከተለው የሚገባው መሠረታዊ አሰራር ነው፤

17. "ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት" ማለት አገር በቀል የባህል መድኃኒት ያልሆነ እና ከዘመናዊ መድኃኒት ጋር ያልተጣመረ በጥሬነቱ ያለ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ የተቀመመ ምርት ነው፤
18. "አደገኛ ኬሚካል" ማለት በጥንቃቄ ካልተያዘ ወይም አገልግሎት ላይ ካልዋለ በሰው ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል በባለሥልጣኑ አደገኛ በሚል ተለይቶ የተመደበ ኬሚካል ነው፤
19. "መርዛማ ቆሻሻ" ማለት ማንኛውም ታክሞ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ለሰው ልጅ ጤና ጎጂ የሆነ ቆሻሻ ነው፤
20. "እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ" ማለት የሰውን ጤና እንዳይጎዳ ታክሞ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ፈሳሽ ቆሻሻ ወይም በተለያየ ሂደት ውስጥ በማለፍ ወደ ሌላ ጠቃሚ ነገር ሊለወጥ የሚችል ቆሻሻ ነው፤
21. "የመግቢያና መውጫ ኬላ" ማለት ዓለም አቀፍ ኤርፖርት፣ በድንበር የሚገኝ መቆጣጠሪያ ኬላ ወይም ሥልጣን ባለው አካል የተሰየመ ደረቅ ወደብ ነው፤
22. "ተላላፊ በሽታ" ማለት በፍጥነት በመዛመት አደገኛ ወረርሽኝ የሚያስከትል በሽታ ነው፤
23. "ኳራንታይን" ማለት ለድንገተኛ ተላላፊ በሽታ ተጋልጠዋል ወይም በበሽታው ተይዘዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎችን እስኪረጋገጥ ድረስ በተለየ ቦታ እንዲቆዩ ማድረግ ነው፤
24. "ለይቶ ማቆየት" ማለት በተላላፊ በሽታ የተያዘ ሰው በሽታውን ወደሌሎች ሰዎች እንዳያስተላልፍ ለተወሰነ ጊዜ ለብቻው ተለይቶ እንዲቆይ ማድረግ ነው፤
25. "የማጓጓዣ አንቀሳቃሽ" ማለት የአውሮፕላን ወይም የባቡር ካፒቴን ወይም የሌላ ማናቸውም ማጓጓዣ አንቀሳቃሽ ነው፤
26. "የጤና ባለሙያ" ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት አግባብ ባለው አካል እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ሲሆን የተደጋጋፊ ወይም አማራጭ የህክምና ባለሙያን ይጨምራል፤
27. "የጤና አገልግሎት" ማለት የጤና ባለሙያው በህግ በተፈቀደለትና የጤና ሙያ ተግባር አይነትና ወሰን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

28.“በበቂ መጠን በገበያ ላይ የማይገኙ የጤና ባለሙያዎች” ማለት አገራዊ ፍላጎትን ማሟላት ሳይቻል ሲቀር በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እጥረት እንዳለባቸው የሚቆጠሩ የጤና ባለሙያዎች ናቸው፤

29.“እክል” ማለት አንድ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራዉን ሲያከናውን ብቃቱን ወይም ሚዛናዊነቱን የሚያዛባ የአዕምሮ ወይም አካላዊ ሁኔታ ነው፤

30.“የአዕምሮ ህመም” ማለት በአስተሳሰብ፣ በግንዛቤ፣ በስሜት ወይም በባህሪ ጽኑ መታወክ ምክንያት የአንድን ሰው የማመዛዘን፣ እውነታን የማገናዘብ ችሎታ ወይም ከሌሎች ጋር የመግባባት ወይም የዘወትር ህይወት የሚጠይቀውን ማሟላት የማይችል በመሆኑ ምክንያት የህክምና እርዳታ የሚያስፈልገው የጤና ችግር ነው፤

31.“ሙያዊ ያልሆነ ተግባር” ማለት በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ ወይም ደረጃዎች የተደነገገ የጤና ባለሙያ ሙያዊ ግዴታን ወይም ሥነ ምግባርን የሚቃረን ተግባር ነው፤

32.“ተገልጋይ” ማለት ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን የጤና አገልግሎት ለማግኘት ሲል በውል ወይም በሌላ መልኩ ከጤና ባለሙያ ጋር ግንኙነት የሚፈጥር ታካሚ ወይም ደንበኛ ነው፤

33.“ተቋም” ማለት የጤና ወይም የተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ህክምና አገልግሎት መስጫ ወይም የምግብ ተቋም ነው፤

34.“የምግብ ተቋም” ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(2) መሠረት የምግብ ንግድን የሚያከናውን ተቋም ሆኖ የምግብ ችርቻሮን አይጨምርም፤

35.“ምግብ አዘጋጅ” ማለት ማንኛዉም ምግብን በማምረት፣ በማስመጣት ወይም በመላክ ንግድ ስራ ውስጥ ከምግቡ ጋር ንክኪ ያለው ሰው ነው፤

36.“ምግብ ማበልጸግ” ማለት በማህበረሰቡ ወይም በማህበረሰቡ የተወሰነ ክፍል የሚታይን የአንድ ወይም የብዙ ንጥረ ምግቦች እጥረትን ለመከላከል ወይም ለማስወገድ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ንጥረ ነገሮችን በምግብ ውስጥ መጨመር ነው፤

37.“ጤና” ማለት በበሽታ አለመያዝ ወይም አካል ጉዳተኛ ያለመሆን ብቻ ሳይሆን የተሟላ የአካል፣ የአዕምሮና የማህበራዊ ደህንነት ነው፤

38.“የህይወት አድን ድንገተኛ ህክምና” ማለት ሕይወትን አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ወይም ጉዳት ላጋጠመው ህመምተኛ መደበኛ የህክምና አገልግሎት እስኪያገኝ ድረስ

በማንኛውም ሰው ወይም መሰረታዊ የሕይወት አድን ድንገተኛ ሕክምና በሰለጠነ ሰው የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

39. “የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት” ማለት አጣዳፊ እና ሕይወትን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም ዘላቂ የጤና ችግር የሚያመጣ በሽታ ወይም ጉዳት ላጋጠመው ህመምተኛ በጤና ተቋማት ውስጥ በጤና ባለሙያ የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ነው፤

40. “ሕብረ-ኅዋስ” ማለት የተዋልዶ አካላት የሆኑትን አባላዘር፣ ሴቴ ዘር፣ የሴቴና የወንዴ ዘር ማመንጫዎችን፣ ሽል እንዲሁም በደም ልገሳ ወቅት የሚወሰዱ ደምንና የደም ተዋፆዎችን ሳይጨምር ከሰውነት የአካል ክፍሎች የሚወሰዱ በቅርጽ፣ በይዘትና በተግባር ተመሳሳይ የሆኑ የህዋስ ስብስብ ነው፤

41. “ንቅለ ተከላ” ማለት በቀዶ ጥገና የሕክምና ዘዴ በሕይወት ካለ ወይም ሕይወቱ ካለፈ ሰው የተለገሰን የአካል ክፍል ወይም ሕብረ-ኅዋስ በመውሰድ የታካሚን በበሽታ የተጠቃ ወይም በአግባቡ መደበኛ ተግባሩን የማያከናውን የአካል ክፍል ወይም ሕብረ-ኅዋስ መተካት ነው፤

42. “ሰው ሰራሽ የተዋልዶ ህክምና” ማለት የወንድን የዘር ፍሬ በተፈጥሮ ከሚታወቀው ዘዴ በተለየ መልኩ ወደ ሴቷ ውስጣዊ የመራቢያ አካላት ለወሊድ ዓላማ ማስተላለፍ ሲሆን በተጨማሪም የወንድ እና የሴት ዘር ጥምረት ውጤትን ዘሯ ከተወሰደው ማሕጸን ውስጥ ለማስተላለፍ ከሰውነት አካል ውጪ የወንድ እና የሴት ዘርን ማቀላቀልን ይጨምራል፣

43. “አከፋፋይ” ማለት ምግብ ወይም መድሃኒትን ከአንድ ክልል በላይ በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው ነው፤

44. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፤

45. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የምግብና የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር

## ምዕራፍ አንድ

## የምግብ ደህንነትና ጥራት

### 3. አጠቃላይ

ማንኛውም ለጤና ተስማሚ ያልሆነ ወይም ተገቢውን የደህንነትና ጥራት ደረጃ ያልጠበቀ ምግብ ሊመረት፣ ወደ አገር ውስጥ ሊገባ፣ ወደ ውጭ አገር ሊላክ፣ ሊከማች፣ ሊከፋፈል፣ ሊጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ወይም ለህብረተሰቡ ጥቅም ሊውል አይችልም።

4. <u>ምግብን ስለማምረት</u>

1. ምግብን ከአንድ ክልል በላይ ወይም ለውጪ አገር ገበያ ሽያጭ የሚያቀርብ አምራች በባለሥልጣኑ ሳያስመዘግብና ፈቃድ ሳያገኝ ያመረተውን ምግብ ለሽያጭ ማቅረብ ወይም የምርት፣ የዓይነትና የሂደት ለውጥ ማድረግ አይችልም።
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚመዘግበው ወይም ፈቃድ የሚሰጠው የመልካም የአመራረት አሰራር፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት ላብራቶሪ ምርመራ እና ሌሎችም አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ መመዝገብ ያለባቸውን የምግብ አይነቶች በመመሪያ ይወስናል።

5. <u>ምግብን ስለመከለስና አስመስሎ ስለማቅረብ</u>

1. በማንኛውም ምግብ ላይ መጠኑን ወይም ክብደቱን ለመጨመር፣ መልኩን ለማሳመር ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ሲባል ባዕድ ነገር መጨመር ወይም መቀላቀል የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውንም ምግብ ከማንኛውም የሰውን ጤና ሊጎዳ ከሚችል ወይም የምግቡን ጥራትና ደህንነት ሊያጓድል ከሚችል ነገር ጋር በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ መደባለቅ የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውንም የምግብ ማሸጊያ፣ መለያ፣ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም ወይም ማንኛውንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም ምግቡ በእውነተኛው አምራች እንደተመረተ በማስመሰል ወይም የምግቡን ጥራትና ደህንነት አጓድሎ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

6. <u>ምግብን ማከማቸት፣ ማጓጓዝና ለዕይታ ማቅረብ</u>

1. ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ በሚያቀርብበት፣ በሚያሸግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ውስጥ መሆን አለበት፡፡

2. ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ምግብን ማጓጓዝ የሚችለው ከምግቡ ጋር ንክኪ የሚኖረው የማጓጓዣ ክፍል ንፁህ ሆኖ ምግቡን ለማንኛውም ኬሚካላዊ፣ አካላዊ ወይም ማይክሮ ባዮሎጂካል ብክለት በማያጋልጥ መልኩ መሆን አለበት፡፡

3. ማንኛውንም ምግብ ከተበከለ ምግብ፣ ከምግብ ትርፍራፊ፣ ከመርዝ፣ ጎጂ ከሆኑ ነገሮች፣ ከእንስሳት ወይም ከሌሎች በካይ ነገሮች ጋር ማከማቸት፣ መጫን ወይም ማጓጓዝ ክልክል ነው፡፡

7. <u>ምግብን ስለማበልጸግ</u>

1. ባለሥልጣኑ የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ የምግብ አምራች ድርጅት የሚያመርተውን ምግብ በተለያዩ ማዕድናትና ቫይታሚኖች እንዲበለጽግ ማዘዝ ይችላል፡፡

2. ማንኛውም የምግብ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንዲበለጽግ የተለየ ምግብን ማምረት፣ ማስመጣት፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ የሚችለው ባለስልጣኑ ባወጣው መስፈርት መሰረት የበለጸገ ሲሆን ነው፡፡

3. የበለጸገ ምግብ ገላጭ ጽሁፍ ምግቡ የበለጸገበትን ማዕድን ወይም ቫይታሚን የሚገልፅ ሀረግ ሊኖረው ይገባል፡፡

8. <u>ምግብን ማጭረር</u>

1. ምግብ የሚያጨር ተቋም ተገቢውን የደህንነትና የሀይጂን መስፈርቶችን በሚያሟላ መልኩ ዲዛይን መደረግ ይኖርበታል።

2. በማንኛውም ምግብ ሲኖር የሚገባው የራዲዮ ኒውኩላይ ቅሪት ተቀባይነት ካለው መጠን መብለጥ የለበትም፡፡

9. <u>ምግብ ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለመላክ</u>

1. ማንኛውም ሰው ለህብረተሰብ አገልግሎት የሚውል ምግብን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው ባለሥልጣኑ የምግቡን ደህንነትና ጥራት በማረጋገጥ ሲፈቅድ ይሆናል፡፡

2. ባለሥልጣኑ ከውጭ አገር የገባ ምግብ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑን ካረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ያስደርጋል፡፡

3. ባለሥልጣኑ በምግብ ላኪው ተቋም ሲጠየቅ የምርቱን የላብራቶሪ ምርመራ የምስክር ወረቀት፣ በአገር ውስጥ ገበያ ላይ እንዲውል የተፈቀደ ስለመሆኑ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ወይም የጤና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

10. <u>ስለተጨማሪ እና ልውጥ ህያው ምግቦች</u>

1. ማንኛውም ሰው ተጨማሪ ምግቦችን ለሽያጭ ማቅረብ የሚችለው ተጨማሪ ምግቡ በባለሥልጣኑ ተመዝግቦ ሲፈቀድ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የታሸገ እና "ተጨማሪ ምግብ" የሚል ገላጭ ጽሁፍ ሳይኖረው ማንኛውንም ተጨማሪ ምግብ መሸጥ አይችልም።
3. ማንኛውም የተጨማሪ ምግብ ገላጭ ጽሁፍ፣ አቀራረብ ወይም ማስታወቂያ የተመጣጠነና የተለያየ አመጋገብ ተገቢውን የንጥረ ምግብ መጠን እንደማያስገኝ ወይም ተጨማሪ ምግቡ የሰውን በሽታ እንደሚከላከል ወይም እንደሚያድን የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡
4. ማንኛውንም ልውጥ ሕያው ምግብ ለማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ወይም ለማከፋፈል ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡
5. ማንኛውም ሰው ልውጥ ሕያው ምግብን በቅድሚያ የታሸገ ሳይሆንና "ልውጥ ሕያው" የሚል ገላጭ ጽሁፍ ሳይኖረው መሸጥ አይችልም።

11. <u>የጨቅላና የሕጻናት ምግቦችና ማሟያ ምግቦች</u>

1. ማንኛውንም የጨቅላና ህጻናት ምግቦችን ወይም ማሟያ ምግቦችን ለማምረት፣ ወደ አገር ወስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ወይም ለማከፋፈል ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የእናት ጡት ወተት ምትክ ግብይትን የሚመለከት ዝርዝር መስፈርቶችን ያወጣል።

12. <u>ክልል ተሻጋሪ የውሃ አቅርቦት</u>

ማንኛውም ሰው ክልል ተሻጋሪ የውሃ አቅርቦት አገልግሎት መስጠት የሚችለው ስለ ውሃው ደህንነትና ጥራት ከባለሥልጣኑ ማረጋገጫ ሲሰጠው ብቻ ነው፡፡

13. <u>ስለአልኮል ሽያጭ</u>

1. ማንኛውም በፋብሪካ ደረጃ ተመርቶ ከአንድ ክልል በላይ የሚሰራጭ፣ ለውጭ አገር ገበያ ለሽያጭ የሚቀርብ ወይም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ የአልኮል መጠጥ አግባብ ያለው አካል ያወጣውን ደረጃ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሽያጭ የሚቀርብ የአልኮል መጠኑ ከአስር በመቶ በታች የሆነ ማንኛውም መጠጥ ገላጭ ጽሑፍ የአገልግሎት ጊዜን መግለጽ ይኖርበታል።

3. ባለሥልጣኑ የአልኮል መጠጥ ቁጥጥርን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር

### 14. አጠቃላይ

ማንኛውም ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ ያልተረጋገጠ መድኃኒት ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር መላክ፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ወይም ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

### 15. ስለመድኃኒት ማምረትና ምዝገባ ምስክር ወረቀት

1. ማንኛውም የመድኃኒት አምራች ወይም ወኪል ማምረት ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው በብሔራዊ መድኃኒት መዘርዝር ውስጥ የተካተተን መድኃኒት ነው፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የአገር ውስጥ የመድኃኒት አምራች ድርጅት በብሔራዊ መድኃኒት መዘርዝር ውስጥ ያልተካተተ መድኃኒትን አምርቶ እና በልዩ ሁኔታ አስመዝግቦ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም በብሔራዊ መድኃኒት መዘርዝር ውስጥ ያልተካተተና የመድኃኒት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የሌለው መድኃኒት ገበያ ላይ ሊውል አይችልም።

4. ባለሥልጣኑ መድኃኒት ገበያ ላይ እንዲውል የመድኃኒት ምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው፡-

    ሀ/ የመድኃኒት አምራቹ ፋብሪካ የመልካም አመራረት አሰራርን የተከተለ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

    ለ/ ስለመድኃኒቱ ደህንነት፣ ጥራትና ፈዋሽነት የሚያረጋግጡ ሰነዶች ተገምግመው መስፈርቶችን ያሟላ ከሆነ፤ እና

    ሐ/ መድኃኒቱ የላብራቶሪ ጥራት ምርመራ መስፈርቶችን ያሟላ ከሆነ፤

    ይሆናል፡፡

5. ማንኛውም የመድኃኒት አምራች የመድኃኒት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ከተሰጠው በኋላ በምዝገባ ወቅት በሰጠው መረጃ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ለውጥ ሊያደርግ የሚችለው ይህንኑ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ በማሳወቅና ተቀባይነት ሲያገኝ ይሆናል፡፡
6. ማንኛውም መድኃኒት ያስመዘገበ አምራች የመድኃኒት ምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ በአዋጁ አንቀጽ 13(3) የተመለከተው ጊዜ ከማብቃቱ ከስድስት ወራት በፊት ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

16. <u>መድኃኒትን ማከማቸት፣ ማጓጓዝና ማከፋፈል</u>

1. ማንኛውም የመድኃኒት አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ መድኃኒትን በሚያከማችበት፣ በሚያጓጉዝበት እና በሚያከፋፍልበት ጊዜ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ውስጥ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም የመድኃኒት አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ መድኃኒትን ማጓጓዝ የሚችለው ከመድኃኒቱ ጋር ንክኪ የሚኖረው የማጓጓዣ ክፍል ንፁህ ሆኖ መድኃኒቱን ለማንኛውም ኬሚካላዊ፣ አካላዊ ወይም ማይክሮ ባዮሎጂካል ብክለት በማያጋልጥ መልኩ መሆን አለበት፡፡

17. <u>መድኃኒትን ስለመከለስ እና አስመስሎ ስለማቅረብ</u>

1. በማንኛውም መድኃኒት ላይ መጠኑን፣ ይዘቱን ወይም ክብደቱን ለመቀየር፣ መልኩን ለማሳመር ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ሲባል ባዕድ ነገር መጨመር ወይም መቀላቀል የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውንም መድኃኒት ከማንኛውም የሰውን ጤና ሊጎዳ ከሚችል ወይም የመድኃኒቱን ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነት ሊያጓድል ከሚችል ነገር ጋር በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ መደባለቅ የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውንም የመድኃኒት ማሸጊያ፣ መለያ፣ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም ወይም ማንኛውንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም መድኃኒቱ በእውነተኛው አምራች እንደተመረተ በማስመሰል ወይም የመድኃኒትነት ይዘትና ባህሪ ለውጦ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

18. <u>መድኃኒት ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባት</u>

1. ማንኛውም ሰው መድኃኒት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ሲሰጠውና በመግቢያ ኬላ ላይ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

2. ባለሥልጣኑ ከውጪ አገር የመጣ መድኃኒት ደህንነቱ፣ ጥራቱ ወይም ፈዋሽነቱ ያልጠበቀ ከሆነ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ያስደርጋል፡፡

3. ባለሥልጣኑ ስለተወገደው መድኃኒት በመድኃኒት አስገቢው ሲጠየቅ አግባብ ያለውን ማስረጃ ይሰጣል፡፡

19. <u>ስለመድኃኒት ጥሬ እቃ እና ማሸጊያ</u>

1. ማንኛውም ሰው የመድኃኒት ጥሬ እቃና ማሸጊያ ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ ማከፋፈል ወይም ማከማቸት የሚችለው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

2. ባለሥልጣኑ የመድኃኒት ጥሬ እቃና ማሸጊያ በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

20. <u>ያልተመዘገበ መድኃኒት ወደ አገር ውስጥ ሊገባ ስለሚችልበት ሁኔታ</u>

ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሌለው መድኃኒት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ልዩ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፦

1. ለሕክምና ሙከራ ወይም ለሌላ ሳይንሳዊ ምርምር፤
2. በሐኪም የታዘዘበት የማዘዣ ወረቀት ላለው ተጠቃሚ ግለሰብ፣
3. ለምዝገባ ዓላማ የላብራቶሪ ጥራት ምርመራ ለማካሄድ፣
4. ለተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ወይም ለተመሳሳይ አስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ፤
5. ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች አገልግሎት፣ ወይም
6. በአስመጪዎች ትኩረት የማይሰጣቸው መድኃኒቶችን ወይም በቂ ትኩረት ላላገኙ በሽታዎች ሕክምና የሚውሉ መድኃኒቶችን ለማስገባት፡፡

21. <u>ስለመርዞችና ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶች</u>

ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ መርዞችን ወይም ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶችን ማምረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ መላክ፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት ወይም መያዝ አይችልም።

22. <u>ስለሕክምና ሙከራ</u>

1. ማንኛውም በሰው ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ በባለሥልጣኑ የሚፈቀደው የምርምሩ ፕሮፖዛል ከሳይንስ፣ ከሕግና ከሥነ-ምግባር አንጻር ተገምግሞ ተቀባይነት ሲያገኝ ይሆናል፡፡

2. ማንኛውም ተመራማሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ፈቃድ ለማግኘት ሲጠይቅ ለባለሥልጣኑ የምርምሩን ፕሮፖዛል፣ ስለራሱና ተባባሪ ስለሆኑት

ባለሙያዎች ተፈላጊ መረጃ፣ የሕክምና ሙከራ የሚደረግበት መድኃኒት፣ ከሕክምና ሙከራ የሥነ-ምግባር ኮሚቴ የተሰጠ ፈቃድ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን ማቅረብ አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ ፈቃድ የሰጠውን የሕክምና ሙከራ በየጊዜው በመልካም የሕክምና ስርዓት መሠረት መፈፀሙን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥናቱ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም ያደርጋል፣ የጥናት ውጤቱን ይገመግማል እንዲሁም ለኅብረተሰቡ በሚጠቅም ሁኔታ አገልግሎት ላይ እንዲውል ይፈቅዳል።

23. <u>የሕክምና ሙከራ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ተቆጣጣሪ አካል</u>

1. ባለሥልጣኑ የሕክምና ሙከራ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ተቆጣጣሪ አካል ያቋቁማል፡፡
2. የሕክምና ሙከራ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ተቆጣጣሪ አካል በየደረጃው የሚቋቋሙ የሕክምና ሙከራ ሥነ-ምግባር ኮሚቴዎችን እውቅና ይሰጣል፣ ይከታተላል፤ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡
3. የሕክምና ሙከራ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ተቆጣጣሪ አካል ሰብሳቢ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ይሆናል፡፡
4. የሕክምና ሙከራ ሥነ-ምግባር ኮሚቴ ተቆጣጣሪ አካል ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

24. <u>የሕክምና ሙከራ አድራጊው ግዴታዎች</u>

1. የሕክምና ሙከራ አድራጊው የምርምር ውጤቱን በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ሳያሳውቅና በባለሥልጣኑ ሳይጸድቅ ማሰራጨት አይችልም።
2. የሕክምና ሙከራ አድራጊው ባለሥልጣኑ በሙከራው ላይ ለሚያደርገው ክትትል የሙከራውን ቦታና ሰነዶች የማስጐብኘትና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
3. ከሕክምና ሙከራ ጋር በተያያዘ ከሚወጣ ተመጣጣኝ ወጪ በስተቀር የሕክምና ሙከራ አድራጊው የሕክምና ሙከራ ለሚደረግበት ሰው በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ክፍያ መፈጸም አይችልም።

25. <u>በነፍሰጡሮች፣ በአጥቢዎች፣ ለአካለ መጠን ባልደረሰ ሰው ወይም በማህፀን ውስጥ ባለ ጽንስ ላይ የሚደረግ የሕክምና ሙከራ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 15(4) መሰረት በነፍሰጡሮች፣ በአጥቢዎች፣ ለአካለ መጠን ባልደረሰ ሰው ወይም ማህጸን ውስጥ ባለ ጽንስ ላይ የሕክምና ሙከራ ሊከናወን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፡-

1. መድኃኒቱ በሕክምናው ዘርፍ የነፍሰጡሮችን፣ የአጥቢ እናቶችን፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሰዎችን ወይም ማህጸን ውስጥ ያለ ጽንስን ጤና ለመመርመር፣ በሽታን ለመከላከል ወይም ለማከም የሚረዳ ስለመሆኑ ሳይንሳዊ መረጃ መቅረቡ፤
2. የሕክምና ሙከራው ከነፍሰጡሮች፣ ከአጥቢ እናቶች፣ ለአካለ መጠን ካልደረሱ ሰዎች ወይም ማህጸን ውስጥ ካለ ጽንስ ውጪ ባሉ ሰዎች ላይ ቢካሄድ የሚጠበቀውን አጥጋቢ ውጤት ማምጣት እንደማይቻል ሳይንሳዊ ወይም የሕክምና መረጃ መኖሩ፤
3. በአጥቢ እናት ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ ሲሆን በጡት ወተት አማካኝነት ወደ ህጻኑ የሚተላለፈው የመድኃኒት መጠን በህጻኑ ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑ፤
4. በነፍሰጡር ወይም በአጥቢ እናት ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ ሲሆን ስለሕክምና ሙከራው ገለጻ ተደርጎላት ከጽንሱ ወይም ከህጻኑ አባት ጋር የጋራ ስምምነት ወይም የጽንሱ ወይም የህጻኑ አባት በሌለበት ሁኔታ የነፍሰጡሯ ወይም የአጥቢ እናቷ ስምምነት መገኘቱ፤
5. ለአካለ መጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ ለሚደረግ የሕክምና ሙከራ ሲሆን የልጁ ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ የእናትና አባቱ ወይም እናቱ ወይም አባቱ በማይኖርበት ሁኔታ የአንዳቸው ስምምነት ወይም ወላጅ ያጣ ሕፃን ከሆነ የአሳዳሪው ስምምነት መገኘቱ፤
6. በማህጸን ውስጥ ባለ ጽንስ ላይ የሚካሄድ የሕክምና ሙከራ ሲሆን በጽንሱ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑና የእናትና አባቱ ወይም አባቱ በማይኖሩበት ሁኔታ የእናቱ ስምምነት መገኘቱ፡፡

## 26. <u>በአእምሮ ሕመምተኞች ላይ ስለሚደረግ የሕክምና ሙከራ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 15(4) መሠረት በአእምሮ ሕሙምተኞች ላይ የሕክምና ሙከራ የሚከናወነው የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፦

1. የሕክምና ሙከራው ዓላማ መድኃኒቱ የአእምሮ ሕመምን ለመመርመር፣ ለመከላከል ወይም ለማከም የሚውል መሆኑ፤
2. የሕክምና ሙከራው ከአእምሮ ሕመምተኞች ውጭ ባሉ ሰዎች ላይ ቢካሄድ የሚፈለገውን የሙከራ ውጤት ማምጣት እንደማይቻል ሳይንሳዊ ወይም የሕክምና መረጃ መቅረቡ፤ እና
3. የአእምሮ ሕመምተኛው ፈቃዱን ለመግለጽ የሚችል ከሆነ የሕክምና ሙከራው ተገልጾለት ስምምነቱ መገኘቱ ወይም ፈቃዱን ለመግለጽ ብቁ ሳይሆን ሲቀር የአሳዳሪው ስምምነት መገኘቱ፡፡

27. <u>በህግ ታራሚዎች ላይ ስለሚደረግ የህክምና ሙከራ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 15(4) መሠረት በሕግ ታራሚ ላይ የሕክምና ሙከራ የሚከናወነው የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፡-

ሀ/ የሕክምና ሙከራው በተለይ ከእስራት ጋር በተያያዘ በሕግ ታራሚዎች ላይ የሚከሰት ህመምን ለመመርመር፣ ለመከላከል ወይም ለማከም የተፈለገ ከሆነ፤ እና

ለ/ በሕክምና ሙከራው ላይ የሚሳተፈው ታራሚ ለመሳተፍ በሙሉ ነጻነት ከወሰነ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሕግ ታራሚ ላይ የሕክምና ሙከራ ሲከናወን የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አስተዳደር እንዲያውቀው የመደረግ መብት ኖሮት አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

28. <u>የሕክምና ሙከራን ስለማቋረጥ</u>

የሕክምና ሙከራ እንዲካሄድበት የተስማማ ሰው በማናቸውም ጊዜ ሙከራውን ማቋረጥ ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>
## <u>የባህላዊና ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ህክምና</u>
## <u>መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር</u>

29. <u>ስለባህላዊ መድኃኒት ምዝገባ</u>

1. ማንኛውም ሰው የባህል መድኃኒትን ለማስመዝገብ ስለመድኃኒቱ ምንጭ፣ የአጠቃቀም ሁኔታና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የባህል መድኃኒቱን ፈዋሽነት፣ ደህንነትና ጥራት ሲያረጋግጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርቡትን መረጃዎች ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

30. <u>የተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና መድሀኒት ምዝገባ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 15(2) ስለመድኃኒት ምዝገባ የተደነገገው እንደአግባብነቱ የተደጋጋፊ ወይም አማራጭ ሕክምና መድኃኒትን ለማስመዝገብ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>
## <u>ድህረ ገበያ ቅኝትና የምግብና መድኃኒት አያያዝና አወጋገድ</u>

31. <u>ስለድህረ ገበያ ቅኝት</u>

1. ባለሥልጣኑ ለሽያጭ በቀረበ ምግብ ወይም መድኃኒት ላይ ድህረ ገበያ ቅኝት ያካሂዳል፤ በተገኘው ውጤት መስረትም ተገቢውን መስፈርት የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ እርምጃ ይወስዳል።
2. ማንኛውም የምግብ ተቋም፦

   ሀ/ በምግብ ደህንነትና ጥራት ላይ ያልተጠበቀ ችግር ሲኖር ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፤

   ለ/ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ ማንኛውንም ምግብ ከማሰራጨት የመቆጠብ፤ እና

   ሐ/ ለሽያጭ ያቀረበው ማንኛውም ምግብ ደህንነቱና ጥራቱ ያልጠበቀ ከሆነ በመሰብሰብ ባለሥልጣኑ ባወጣው መመሪያ መሰረት የማስወገድ፤

   ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የጤና ተቋም፡-

   ሀ/ በመድኃኒት ጥራት፣ ፈዋሽነትና ደህንነት ረገድ የሚያጋጥመውን ማንኛውንም ቀድሞ የማይታወቅ ችግር፣ ወቅታዊ የመድኃኒት መረጃዎችን ወይም ከተገልጋይ የሚቀርብ ቅሬታ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ፤ እና

   ለ/ ባለሥልጣኑ መድኃኒቱ የደህንነት፣ የፈዋሽነት ወይም የጥራት ችግር አለው ብሎ ሲያሳውቅ የመድኃኒቱን ስርጭት የማቆም፤

   ግዴታ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የምግብ ወይም የጤና ተቋም ባለሥልጣኑ ለሚያካሂደው የድህረ ገበያ ቅኝት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ) መሰረት የአንድን መድኃኒት ሥርጭት ሲያግድ የመድኃኒቱ አምራች ወይም ወኪል የተሰራጩትን መድኃኒቶች የመሰብሰብና የማስወገድ ኃላፊነት አለበት፡፡
6. ማንኛውም የመድኃኒት አምራች፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት የገበያ ፈቃድ ባገኘበት መድኃኒት ላይ ተከታታይ የመድኃኒት ደህንነት ክትትል የማድረግ እና ችግር ሲከሰትም አስፈላጊውን እርምት ለማድረግ የሚያስችለውን የፋርማኮቪጂላንስ ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
7. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሚያጋጥመውን የመድኃኒት ጐጂ ባህሪያት እንዲሁም የመድኃኒት ፈዋሽነትን ወይም ጥራትን አስመልክቶ የሚያጋጥመውን ችግር ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

32. <u>ምግብን ወይም መድኃኒትን ስለመያዝና ማስወገድ</u>

1. አግባብ ያለው አካል፡-

ሀ/ ገበያ ላይ እንዲውል ያልተፈቀደ፤

ለ/ አስመስሎ የቀረበ፤

ሐ/ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈ፤

መ/ የጥራት ደረጃውን የማያሟላ፤

ሠ/ በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሌለው ሰው የተከማቸ፣ የተከፋፈለ፣ ለዕደላ የቀረበ ወይም የታደለ፤ ወይም

ረ/ ላልተፈቀደ የሕክምና ሙከራ የዋለ፤

መድኃኒትን ወይም ምግብን በመያዝ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለተወገደው ምግብ ወይም መድኃኒት በምግቡ ወይም በመድኃኒቱ ባለቤት ወይም ባለይዞታ ሲጠየቅ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የትምባሆ ዝግጅት ቁጥጥር</u>

### 33. <u>ፈቃድ ስለማስፈለጉ</u>

ማንኛውንም የትምባሆ ዝግጅት ማስመጣት፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ የሚቻለው ዝግጅቱ መስፈርቶችን ማሟላቱ ተረጋግጦ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ያገኘ ሲሆን ነው፡፡

### 34. <u>ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ከትምባሆ ዝግጅት ስለመጠበቅ</u>

ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርቶችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ አካለ መጠን ላልደረሰ ሰው እንዲጠቀም መሸጥ ወይም መገፋፋት የተከለከለ ነው፡፡

### 35. <u>ስለትምባሆ ዝግጅት ማሸጊያና ገላጭ ጽሁፍ</u>

1. ማንኛውም የትምባሆ ዝግጅት ምርት ገላጭ ጽሁፍ የትምባሆ ዝግጅት ምርት ባህሪን፣ የጤና ችግር ማስከተሉን እና አደገኝነቱን የሚገልጽ ሆኖ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የአንዱ የትምባሆ ዝግጅት ምርት ጉዳት ከሌላ የትምባሆ ዝግጅት ጉዳት ያነሰ መሆኑን የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የትምባሆ ዝግጅት ነጠላ ፓኬት፣ ጥቅል ማሸጊያና የውጭ ማሸጊያ ገላጭ ጽሁፍ፡-

ሀ/ ስለትምባሆ የጤና አስከፊነት የጤና ማስጠንቀቂያ የያዘና ይህም የማሸጊያውን ገጽ 30 በመቶ ወይም ከዛ በላይ የሚሸፍን፤

ለ/ የጤና ማስጠንቀቂያው በጽሁፍ ወይም በስዕል ማጨስ ካንሰር፣ የልብ ወይም ብሮንካይትስ ህመም ያመጣል ወይም ካለዕድሜ ይገድላል ወይም ሌሎች ትምባሆን በመጠቀም የሚመጡ ከፍተኛ የጤና ችግሮችን የሚገልጽ፤

ሐ/ በትልቁና ግልጽ ሆኖ የሚታይና የሚነበብ እና የማይለቅ ሆኖ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተጻፈ፣ እና

መ/ ትምባሆ የያዘውን ንጥረ ነገርና በጪሱ ውስጥ የሚገኘውን ዋና ዋና ጎጅ ንጥረ ነገር የሚገልጽ፤

መሆን አለበት፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የውጭ ማሸጊያ" ማለት የትምባሆ ዝግጅት ምርት ለችርቻሮ የሚቀርብበት ማንኛውም ማሸጊያ ነው፡፡

36. <u>ማጨስ የሚከለከልባቸው ቦታዎች</u>

1. ትምባሆን በማንኛውም ሕዝብ በሚሰበሰብበት ወይም በሚገለገልበት ቦታ ማጨስ ክልክል ነው፡፡

2. ሕዝብ የሚሰበሰብበት ወይም የሚገለገልበት ቦታ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ በጤና ተቋማት ክፍል ውስጥ፤

ለ/ በትምህርት ተቋማት ክፍል ውስጥ፤

ሐ/ በህዝብ ማጓጓዣዎች ውስጥ፤

መ/ እንደ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች ባሉ የመመገቢያ ቦታዎች፤ እና

ሠ/ አግባብ ያለው አካል እንዳይጨስባቸው የሚወስናቸው ሌሎች ቦታዎች፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በባለሥልጣኑ የሚለዩ ሕዝብ የሚሰበሰብባቸው ወይም የሚገለገልባቸው ተቋማት ውስጥ ትምባሆን ማጨስ የሚቻለው ለዚሁ ዓላማ በተለየ የማጨሻ ቦታ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>የሃይጂን፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅና</u>
## <u>የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር</u>

37. <u>ስለአደገኛ ኬሚካል</u>

1. ማንኛውም አደገኛ ኬሚካል ሲመረት፣ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ፣ ሲከማች፣ ሲጓጓዝ፣ ሲከፋፈል፣ ለሽያጭ ሲቀርብ ወይም አገልግሎት ላይ ሲውል በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጣው መስፈርት ተጥሶ ሲገኝ አግባብ ያለው አካል አደገኛ ኬሚካሉን የመያዝ ወይም ከገበያ እንዲሰበሰብ እና እንዲወገድ ወይም ወደመጣበት አገር እንዲመለስ ማድረግ እና ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፡፡

38. <u>የአስከሬን አጓጓዝና አወጋገድ</u>

1. ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው መስፈርቶች መሰረት ካልተፈቀደ በስተቀር አስከሬን ወይም አጽም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ከአገር ለማስወጣት አይቻልም።

2. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የመቃብሩ ቦታ ለሕዝብ ጥቅም ሲፈለግ ካልሆነ በስተቀር አስከሬንን ከተቀበረበት ጊዜ ጀምሮ ሰባት ዓመት ሳይቆይ ከተቀበረበት ሊወጣ አይችልም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ለአርኪዮሎጂ ወይም ለቱሪዝም የሚደረግ የአጽም ማጓጓዝን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

39. <u>የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ</u>

1. አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ መርዛማ የሆኑ ወይም በሽታ ሊያስተላልፉ የሚችሉ ቆሻሻዎችን ማቃጠል ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ማስወገድ አይቻልም።

2. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የወጡ መስፈርቶችን በማሟላት አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ መርዛማ ወይም በሽታ ሊያስተላልፍ የሚችል ቆሻሻን እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ወይም በማስወገድ ስራ ሊሰማራ አይችልም።

3. አግባብ ያለው አካል ቆሻሻ ማስወገጃ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ስራ የሚሰራበተ ቦታን ከመሰየሙ በፊት የቆሻሻው በቦታው መወገድ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል መደረግ በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት እንደማያደርስ ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. ማንኛውም ፈሳሽ ቆሻሻ ወደ አካባቢ ሊለቀቅ የሚችለው አግባብ ያለው አካል የሚያወጣውን ደረጃ ሲያሟላ ይሆናል፡፡

40. <u>የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት</u>

አግባብ ያለው አካል ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ተገቢውን የሃይጂንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

41. <u>የድምጽና የአየር ብክለት</u>

ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ የህብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅ ሲል የድምጽና የአየር ብክለትን ለመከላከል የሚያወጣቸውን መስፈርቶች ማክበር አለበት፡፡

42. <u>የሕዝብ መገልገያ መጸዳጃ ቤት</u>

ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ መጸዳጃ ቤት ባለሥልጣኑ ያወጣቸውን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

43. <u>የዓለም አቀፍ መንገደኞች ክትባት</u>

1. የዓለም አቀፍ መንገደኞች ክትባቶች የሚሰጡት ባለሥልጣኑ በሚሰይማቸው የጤና ተቋማት ይሆናል፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 26(2) መሰረት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የሚታገድ ሰውን ያመጣ ማንኛውም አጓጓዥ የታገደውን ሰው የቆይታውን ወጪ በመሸፈን ወደ መጣበት አገር የመመለስ ግዴታ ይኖርበታል።

44. <u>በመግቢያና መውጫ ኬላ የማጓጓዣዎችና ጭነቶች ቁጥጥር</u>

1. ማንኛውም ከውጭ ወደ አገር የሚገባ ወይም በአገር ውስጥ አቋርጦ የሚያልፍ ማጓጓዣ በኢትዮጵያ ድንበር ክልል ውስጥ ማንኛውንም ቆሻሻ ወይም የቆሻሻ ዝቃጭ ከሚፈቀድለት አሰራር ውጪ ማስገባት ወይም መጣል የለበትም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሰው እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ወይም ተረፈ ምርትን ባለሥልጣኑን በማስፈቀድ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ተላላፊ በሽታ ያስተላልፋል ተብሎ የሚጠረጠር ገቢ ወይም ወጪ ማጓጓዣ ወይም ጭነት ወደ አገር የሚገባው ወይም ከአገር የሚወጣው ርጭትን ጨምሮ ተገቢው የጤና አጠባበቅ ቁጥጥር ተደርጎበት በባለሥልጣኑ ፈቃድ ሲያገኝ ይሆናል፡፡
4. ደም፣ የደም ውጤቶች፣ የሰው አካላቶች፣ ሽንት ወይም ዓይነ ምድር ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ከአገር ማስወጣት የሚቻለው በባለሥልጣኑ ሲፈቀድ ነው፡፡

5. ማንኛውም ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የታገደን ጭነት ወይም ቆሻሻ ወደ አገር ያስገባ የማጓጓዣ አንቀሳቃሽ በራሱና በባለንብረቱ ወጪ ወደ መጣበት አገር የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

45. <u>ድንበርን በእግር ስለሚያቋርጡ ግለሰቦች</u>

ወረርሽኝና ድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ በእግር ድንበር አቋርጦ የሚወጣ ወይም የሚገባ ማንኛውም ሰው በመግቢያና መውጫ ኬላ ላይ የጤና አጠባበቅ ቁጥጥር ሳይደረግበትና ሳይፈቀድለት መግባት ወይም መውጣት አይችልም።

46. <u>ስለተጠረጠረ ሰው እና ሪፖርት ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም ወደ አገር የሚገባ ዓለም አቀፍ መንገደኛ የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ሲባል ለኳራንቲን ቁጥጥር በቃል ወይም በጽሁፍ የሚቀርብለትን ጥያቄ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡
2. በጉዞ ወቅት ማንኛውም ተላላፊ በሽታ አለበት ተብሎ የሚጠረጠር መንገደኛ ሲኖር የማጓጓዣ አንቀሳቃሹ በአቅራቢያው ላለው ወይም ለሚያርፍበት የመግቢያና መውጫ ኬላ ኃላፊ የበሽታውን ዓይነትና ዋና ዋና ምልክቶች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ማሳወቅ ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት መረጃ የደረሰው የመግቢያና መውጫ ኬላ ኃላፊ በኬላው ለሚገኝ ተቆጣጣሪ መረጃውን ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የመግቢያና መውጫ ኬላ ኃላፊ" ማለት የኬላው ኦፕሬሽን ወይም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጣቢያ ኃላፊ ነው፡፡

47. <u>ኳራንቲን ስለማድረግና ለይቶ ስለማቆየት</u>

1. ማንኛውም የተጠረጠረ ሰው ወዲያውኑ ኳራንቲን መደረግ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ የተጠረጠረ ሰውን ኳራንቲን እንዲያደርገው ለህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል ወዲያውኑ ያስተላልፋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ማንኛውም ኳራንቲን የተደረገ ሰው በተላላፊ በሽታ መያዙ ሲረጋገጥ ወደ ጤና ተቋም ለይቶ ማቆያ ክፍል መዛወሩንና አስፈላጊውን የፈውስና የተሃድሶ ሕክምና መሰጠቱን ያረጋግጣል።

3. የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል በዋና ዋና መግቢያና መውጫ በሮች የኳራንቲን አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማደራጀት ወይም በአካባቢው የሚገኝ ጤና ተቋምን ለይቶ ማቆያ ማዕከል አድርጎ መሰየም አለበት፡፡

48. <u>ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. ባለሥልጣኑ ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር፡-

ሀ/ ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ሕዝብ የሚሰበሰብባቸውን ተቋማት ለተወሰነ ጊዜ ሊዘጋ፤

ለ/ ጊዜያዊ የቁጥጥር ጣቢያዎችን በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ሊያቋቁም፤ እና

ሐ/ ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን ሊወስድ፤

ይችላል፡፡

2. የሚመለከታቸው አካላት በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ ባለሥልጣኑ ለሚያደርገው የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የጤና ክብካቤ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>ስለጤና ክብካቤ አገልግሎት</u>

49. <u>ስለማስከተብ ግዴታዎችና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክር አገልግሎት</u>

1. ማንኛውም የጤና ተቋምና በተቋሙ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ የጤና ባለሙያ የሕክምና ደረጃውን እና የሚሰጠውን አገልግሎት መሠረት በማድረግ ለነፍሰ ጡር ሴቶች እና ለእናቶች የመከላከያ ክትባቶችን እንዲወሰዱ እና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ጥረት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

2. ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣው መመሪያ መሰረት ሕፃናትን የማስከተብ ኃላፊነት አለባቸው።

50. <u>የጤና አጠባበቅ ትምህርት</u>

ማንኛውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት መሰረት በማድረግ የጤና አጠባበቅ ትምህርቶችና ወቅታዊ መረጃዎች ለተገልጋዮች የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

51. <u>የፈውስና የተሃድሶ ሕክምና አገልግሎት</u>

1. ማንኛውም የመንግስት የጤና ተቋም የሕክምና አገልግሎት መስጠት የሚችለው የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓቱንና የተቋሙን አቅም ባገናዘበ መልኩ ይሆናል፡፡

2. የሕክምና አገልግሎት አግባብ ያለው አካል በሚያወጣው ደረጃ መሰረት በጤና ተቋም፣ በሥራ ቦታ፣ በታካሚው መኖሪያ ቤት፣ አደጋ በተከሰተበት ሥፍራ፣ በአምቡላንስ ውስጥ ወይም በሌሎች መሰል ቦታዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

52. <u>የታካሚውን ሙሉ ፈቃድ ስለማግኘት</u>

1. የታካሚው በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ሳይገኝ የሕክምና አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በሚከተሉት ሁኔታዎች የታካሚው ፈቃድ ሳይገኝ የሕክምና አገልግሎት መስጠት ይቻላል፦
   ሀ/ ታካሚው ፈቃድ መስጠት የማይችል ሲሆንና ፈቃዱ ከሚከተሉት በአንዱ የተሰጠ ሲሆን፦
      1) ታካሚው በጽሁፍ ፈቃዱን እንዲሰጥለት በወከለው ሰው፤
      2) ፈቃድ ለመስጠት ውክልና የተሰጠው ሰው ከሌለ በታካሚው የትዳር ጓደኛ፣ ልጅ፣ ወላጅ፣ ወንድም ወይም እህት፤ ወይም
      3) በህግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፈቃድ እንዲሰጥ ስልጣን በተሰጠው ሰው፤
   ለ/ ለታካሚው ሕክምና አለመስጠት ከፍተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋ የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ፤
   ሐ/ ታካሚው በግልጽ ወይም በማንኛውም መልኩ የሕክምና አገልግሎቱን እንደማ ይፈልግ ካላሳወቀና ሕክምናውን ማዘግየት በታካሚው ጤንነት ላይ ዘላቂ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን።
3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የታካሚውን በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡
4. ፈቃዱን ተጠይቆ ሕክምናውን አለመፈለጉን ለገለፀ ታካሚ የጤና ባለሙያው እምቢታው በጤናው ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት ገልጾለት ይህንኑ በፅሁፍ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት በታካሚው ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን የሚሰጥ ፈቃድ ተገኘ ሊባል የሚችለው የተወሰኑ የሕክምና ዓይነቶችን በሚመለከት በቃል ወይም በድርጊት እንዲሰጥ በመመሪያ ካልተፈቀደ በስተቀር በጽሑፍ የተገለጸ ሲሆን ነው፡፡

53. <u>የድንገተኛ ሕክምና</u>

1. ማንኛውም የጤና ተቋም የህይወት አድን ድንገተኛ የሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ተቋም በጤና ተቋማት ደረጃ መሰረት የሚጠበቅበትን የድንገተኛ የሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።
3. የድንገተኛ ሕክምና እርዳታ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን አደጋና ወረርሽኝ በተከሰተበት ቦታ ሁሉ መስጠት ይቻላል።

54. <u>የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት</u>

1. ማንኛውም የጤና ተቋም አግባብ ያለው አካል በሚያወጣው የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ የሚጠበቅበትን የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ተቋም ለታካሚው ተገቢውን ምርመራና ሕክምና ማድረግ የማይችል ሲሆን የሕክምና ቅብብሎሽ ሥርዓቱን ተከትሎ ታካሚውን ተገቢውን አገልግሎት ወደሚሰጠው አግባብ ያለው የጤና ተቋም ማስተላለፍ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የጤና ተቋም የሕክምና ቅብብሎሽ ሥርዓቱን ተከትሎ የመጣለትን ታካሚ የመቀበልና ለላኪው የጤና ተቋም ግብረ መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የጤና ተቋም ለድንገተኛ ሕክምና ታካሚን ወደ ሌላ ጤና ተቋም ከመላኩ በፊት ተቀባዩ የጤና ተቋም ታካሚውን መቀበል ስለመቻሉ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡
5. ማንኛውም ሰው የሕክምና ቅብብሎሽ ሥርዓት አተገባበር መመሪያን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

55. <u>ስለህልፈተ ሕይወትና የአስከሬን ምርመራ</u>

1. ህልፈተ ሕይወት የሚረጋገጠው የሰው የአንጎል፣ የልብና የመተንፈሻ አካላቶች የአሰራር ስርዓት መሰረት ባደረገ ምርመራ በሕይወት እንደሚገኝ ምንም ዓይነት ምልክቶች እንደማይታይበት ብቃት ባለው የጤና ባለሙያ ሲረጋገጥ ነው፡፡
2. የአስከሬን ምርመራ የሚከናወነው የሟች የትዳር ጓደኛ፣ ለአካለ መጠን የደረሰ ልጅ፣ ወላጅ፣ ሞግዚት ወይም አሳዳጊው ወይም አግባብ ያለው አካል የሞቱን ምክንያት ለማወቅ ሲጠይቅ ይሆናል።
3. የህልፈተ ሕይወት መንስዔ ለማወቅ የሚደረግ ምርመራ ብቃት ባለው የጤና ተቋም ሊከናወን ይችላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ሟች በሕይወት እያለ ፈቃዱን በጽሁፍ ከሰጠ ወይም ሟች በህይወት ዘመኑ ክልከላ ካላደረገና የሟች ቤተሰብ ፈቃድ ከተገኘ ለትምህርት ወይም ለምርምር ዓላማ የአስከሬን ምርመራ ማድረግ ይቻላል፡፡

56. <u>የሕክምና ምስክር ወረቀት</u>

ማንኛውም የጤና ተቋም የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የሕክምና ምስክር ወረቀት ለታካሚ ሊሰጥ ይገባ፡-

1. የታካሚዉን ስም፣ ዕድሜና አድራሻ፣
2. የምርመራዉን ዉጤትና ለታካሚዉ የተደረገለትን ሕክምና እና እንደ ሁኔታው የተሰጠዉን ዕረፍትና የቦርድ ውሳኔ፣
3. የሕክምና ማስረጃው የተሰጠበትን ቀን፤
4. ተከታታይ ሕክምና ስለማስፈለጉና የታካሚውን ወቅታዊ የጤና ሁኔታ፤ እና
5. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን፡፡

57. <u>ስለሰው ሰራሽ ተዋልዶ የሕክምና</u>

1. አግባብ ያለው አካል ፈቃድ በሚሰጠው የጤና ተቋም እና ጤና ባለሙያ ሰው ሰራሽ የተዋልዶ ሕክምና መስጠት ይቻላል፡፡
2. ሰው ሰራሽ ተዋልዶ ለማካሄድ ማህፀን ማከራየትም ሆነ መከራየት የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው ወይም የምርምር ተቋም ሰውን በክሎኒንግ ቴክኖሎጂ መፍጠር አይችልም።

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>
## <u>ስለደምና የደም ተዋፆ እና የአካል ክፍሎችና</u>
## <u>የህብረ-ህዋሳት ልገሳና ንቅለ ተከላ</u>

58. <u>ስለደምና የደም ተዋፆ ልገሳ</u>

1. የደምና የደም ተዋፅኦ ልገሳ፣ ማሰባሰብና የሥርጭት ሥራዎች በሰብዓዊነት መርሆዎች ላይ ተመስርተው መከናወን አለባቸው።
2. የሰው ህይወትን ለማዳን አገልግሎት ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር የሚውል ደም ወይም የደም ተዋፆ ለለጋሹም ሆነ ተቀባዩ የገንዘብ ጥቅም የሚያስገኝ መሆን የለበትም፡፡
3. ማንኛውንም የደምና የደም ተዋፆ ለተቀባዩ ሊሰጥ የሚችለው ደህንነቱና ጥራቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡

59. <u>ስለአካል ክፍሎችና የህብረ-ህዋሳት ልገሳና ንቅለ ተከላ መርሆዎች</u>

1. የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳት ንቅለ ተከላ ማከናወን የሚቻለው የተቀባዩን ህይወት ለማቆየት ወይም የሰውነት አቋሙን ለማስተካከል ሌላ የተሻለ አማራጭ መንገድ የማይገኝ መሆኑ በሕክምና ቦርድ ሲረጋገጥ ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በህይወት ዘመኑ ወይም ህይወቱ ካለፈ በኋላ የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳትን ለመለገስ ወይም በምንም ዓይነት ሁኔታ እንዳይወሰዱ ለመከልከል ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ሰው በህይወት ሳለሁ ወይም ከሞትኩ በኋላ የአካል ክፍሎቼን ወይም ህብረ-ህዋሳቶቼን ለግሻለሁ ብሎ የገባውን ቃል በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ሊሽር ይችላል፡፡
4. የአካል ክፍል ወይም ህብረ-ህዋሳት ለጋሹ በክፉ ልቦና ተነሳስቶ የገባውን ቃል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የሻረ እንደሆነ ተለጋሹ በተሰጠው ተስፋ መሠረት ላደረገው ወጪ ሁሉ ካሣ እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል፡፡
5. የሚከተሉትን መፈጸም የተከለከለ ይሆናል፡-

ሀ/ የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳት ንግድ ማካሄድ፤

ለ/ የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳት ለመለገስ የገንዘብም ሆነ ገንዘብ ነክ ያልሆነ ክፍያ መቀበል፣ መስጠት ወይም ለመስጠት ቃል መግባት፤

ሐ/ የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳትን ፍላጎት ወይም አቅርቦት ማስተዋወቅ፤

መ/ የእንስሳትን የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳት ለሰው ንቅለ ተከላ ማዋል፡፡

60. <u>ህይወቱ ካለፈ ሰው የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳትን ስለመሰብሰብ</u>

1. አንድ ሰው በህይወት በነበረበት ወቅት የአካል ክፍሎቹንና ህብረ-ህዋሳቱን ለመለገስ ከተስማማ የሰውየው ህይወት ሲያልፍ ለንቅለ ተከላ የሚውሉ የአካል ክፍሎቹንና ህብረ-ህዋሳቱን መሰብሰብ ይቻላል፡፡
2. ማንኛውም የጤና ተቋም ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የአካል ክፍሎችን እና ህብረ ህዋሳትን መሰብሰብ አይችልም።
3. አንድ ሰው በህይወት እያለ ማንኛውንም ዓይነት ልገሳ የሚቃወም ግልጽ ክልከላ እንዳደረገ የሚያሳይ የጽሁፍ መረጃ ካልተገኘና የሟች የትዳር ጓደኛና ልጆች ወይም እናትና አባት ወይም ወንድሞችና እህቶች እንደቅደም ተከተላቸው በልገሳው ከተስማሙ ከሟች አስከሬን ለንቅለ ተከላ የሚውሉ የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳትን መሰብሰብ ይቻላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ውስጥ የተዘረዘሩት ግለሰቦች ለሟቹ ሞት ምክንያት በወንጀል የተጠረጠሩ ከሆነ ከሟች አስከሬን ለንቅለ ተከላ የሚውሉ የአካል ክፍሎችና ህብረ-ህዋሳት ልገሳን መፍቀድ አይችሉም።

5. ለጋሹ የንቅለ ተከላ ድንጋጌዎችን ተከትሎ አንድ የታወቀ ተቀባይ የልገሳው ተጠቃሚ እንዲሆን ካላዘዘ በስተቀር የአካል ክፍሎችና ሀብረ-ሀዋሳት ተቀባዮች ድልደላ የሚወሰነው በሕክምናው አስገዳጅ ሁኔታዎች እንዲሁም በፍትሀና ርትዕ መርሆዎች ላይ በመመስረት መሆን አለበት፡፡

6. የለጋሹን ህልፈተ ህይወት የሚያረጋግጡት የጤና ባለሙያዎች ከሁለት ያላነሱ መሆን እና ንቅለ-ተከላውን ከሚያካሄዱት የጤና ባለሙያዎች የተለዩና የጥቅም ግንኙነት የሌላቸው መሆን አለባቸው።

## 61. በሀይወት ካለ ሰው የአካል ክፍሎችና ሀብረ-ህዋሳትን ስለመሰብሰብ

1. በሀይወት ካለ ሰው የአካል ክፍሎችና ኀብረ-ህዋሳትን መውሰድ የሚቻለው በለጋሹ ጤንነትና ሀይወት ላይ የከፋና ዘላቂ አደጋ የማይፈጥር መሆኑ ብቃት ባላቸው የጤና ባለሙያዎች ሲታመንበትና የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፦

   ሀ/ ለጋሹ በሕግ ፊት ችሎታ ያለው ሆኖ በግንዛቤ ላይ በተመሰረተ ፈቃድ መስማማቱን ሁለት ምስክሮች ባሉበት በጽሁፍ ካረጋገጠ፤ እና

   ለ/ ለጋሹ፡-

      1. ከተቀባዩ ጋር የትዳር ግንኙነት ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ፤ ወይም
      2. ከተቀባዩ ጋር የትዳር ግንኙነት ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌለው ሲሆን በሁለቱ መካከል ምንም ዓይነት የጥቅም ግንኙነት አለመኖሩ፤

   በዚህ ደንብ አንቀጽ 62 በተጠቀሰው ብሔራዊ የአካል ንቅለ ተከላ ኮሚቴ ከተረጋገጠ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም ለአካለ መጠን ካልደረሰ ሰው በአሳዳጊዉ ፈቃድ የፍልቂ አጥንት ሀብረ ህዋስን መሰብሰብ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም የጤና ተቋም ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ አንቀፅ መሠረት የአካል ክፍሎችን እና ሀብረ ህዋሳት ሀብረ ህዋሳትን መሰብሰብ አይችልም፡፡

## 62. ስለንቅለ ተከላ

1. ማንኛውም የጤና ተቋም ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳያገኝ የአካል ክፍሎች እና ሀብረ ህዋሳት ንቅለ ተከላ ሕክምና አገልግሎትን መስጠት አይችልም።

2. ባለሥልጣኑ የአካል ክፍሎችን እና ህብረ ህዋሳትን መሰብሰብና ንቅለ ተከላ ሕክምናን በተመለከተ ሙያዊ ሥነ ምግባሩን ተከትሎ ስለመከናወኑ የሚያረጋግጥ ብሔራዊ የአካል ንቅለ ተከላ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

3. ብሔራዊ የአካል ንቅለ ተከላ ኮሚቴው እያንዳንዱን የንቅለ ተከላ ጥያቄ ሳያጸድቅ የንቅለ ተከላ ሕክምና አገልግሎት ማካሄድ አይቻልም። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብሔራዊ ኮሚቴው በክልል ደረጃ ለሚቋቋም የአካል ንቅለ ተከላ ኮሚቴ የሥልጣን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለጤና ባለሙያዎች

## ምዕራፍ አንድ

## ስለሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር

### 63. የጤና ሙያዎችን ስለመሰየምና ስለሙያ ሥራ ፈቃድ አስፈላጊነት

1. ባለሥልጣኑ የጤና ባለሙያዎችን ስያሜ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ የሙያ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሙያ ሥራ ወሰን ይወስናል፡፡

2. ማንኛውም የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው የጤና ባለሙያ በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ አግባብ ያለው አካል በሚሰጠው ልዩ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ከሙያው የስራ ወሰን ውጭ ማንኛውንም ዓይነት የጤና አገልግሎት መስጠት አይችልም።

3. ከአንድ በላይ የሆነ የጤና ሙያ ያለው ሰው አስፈላጊውን መስፈርት እስካሟላ ድረስ የጤና ባለሙያ በሆነባቸው ሙያዎች ሁሉ መስራት የሚያስችለው የሙያ ሥራ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡

### 64. ስለጤና ባለሙያዎች መዝገብ

1. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ የሚገኝ ማንኛውንም የጤና ባለሙያ ስም፣ ዜግነት መደበኛ የመኖሪያና የሥራ አድራሻ እና ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎችን የሚይዝ መዝገብ ይኖረዋል።

2. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በጤና ሙያ ዘርፍ በየጊዜው የሚያስመርቃቸውን ምሩቃን ዝርዝር ለባለሥልጣኑ እና አግባብ ላለው አካል መላክ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚያዝ መዝገብ እንደአስፈላጊነቱ ለሕዝብ ግልጽ መደረግ አለበት፡፡

65. <u>የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ባለሥልጣኑ ለጤና ሙያ ስራ ፈቃድ ያወጣቸውን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ የጤና ሙያ ሥራ ፈቃድ ይሰጠዋል።
2. አግባብ ያለው አካል እክል ለገጠመው የጤና ባለሙያ እንደ አግባብነቱ ገደብ የተደረገበት የጤና ሙያ ሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በማንኛውም መልኩ የሙያ ስራ ፈቃዱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊያስተላልፍ ወይም ሊያከራይ አይችልም።

66. <u>የሙያ ስራ ፈቃድ ስለማሳደስ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 33(2) መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ሥራ ፈቃዱን ለማሳደስ ሲቀርብ፡-
   ሀ/ በሙያ ዘርፉ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መውሰዱን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፤ እና
   ለ/ ሙያውን ለማከናወን የሚያስችል የጤና ሁኔታ እንዳለው የሚያረጋግጥ የሕክምና ምስክር ወረቀት፤

   ማቅረብ ይኖርበታል።
2. ለዚህ አንቀጽ ሲባል "ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ" ማለት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሙያ በሥራ ላይ እያለ በሙያው ያገኘውን እውቀትና ክህሎት ጠብቆ እንዲቆይ እና የሙያ ብቃቱን ለማጎልበት በየጊዜው የሚወስደው ሥልጠና ነው፡፡

67. <u>የተሰጠ የሙያ ስራ ፈቃድ የማይሰራበት ጊዜ</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሁለት ዓመት በላይ በማንኛውም ምክንያት በሙያው ሳይሰራ ከቆየ ወደሙያ ሥራው ከመመለሱ በፊት አግባብ ላለው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ባለሙያ እንደ አግባብነቱ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ፣ ስልጠና እንዲወስድ ወይም በሌላ ባለሥልጣኑ በሚመርጠው የጤና ተቋም ውስጥ በሚገኝ የጤና ባለሙያ ሥር ለተወሰነ ጊዜ በክትትል እንዲሰራ በማድረግ በሙያው እንዲሰራ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

3. ባለሙያው ከሁለት ዓመት በላይ በሙያው ሳይሰራ ቆይቶ አግባብ ላለው አካል ሳያሳውቅ ድንገት በሙያው ሲሰራ ቢገኝ ያለሙያ ስራ ፈቃድ እንደሰራ ይቆጠራል።

68. <u>በውጭ ሀገር የሰለጠነ የጤና ባለሙያ</u>

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 65(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እውቅና ባለው የውጭ አገር ተቋም ስልጠና ወስዶ ለሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው፡-
   ሀ/ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የትምህርት ማስረጃ አቻ ግምት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤
   ለ/ በማንኛውም ውጭ አገር በሙያው ለመስራት ፈቃድ አውጥቶ ከሁለት ዓመት በላይ ያልሰራ ከሆነ አግባብ ያለው አካል በሚመድበው የጤና ተቋም ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማጠናቀቅ ይኖርበታል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ከሁለት ዓመት በላይ በውጭ አገር ያገለገለ የጤና ባለሙያ የተማረበት ወይም የሰራበት አገር የበሽታ ሥርጭት ከኢትዮጵያ የበሽታ ሥርጭት ጋር የማይጣጣም ከሆነ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሰረት የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማጠናቀቅ ይኖርበታል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ባለሥልጣኑ ከውጭ አገር ለአጭር ጊዜ በሚቆይ የእርዳታ ስራ፣ ለአደጋ ጊዜ የሰብዓዊ እርዳታ ወይም በባለሥልጣኑ በሚወሰኑ ለሌሎች የጤና አገልግሎቶች ለሚመጡ ባለሙያዎች ጊዜያዊ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. የጤና ባለሙያውን በጊዜያዊነት ያስመጣው ተቋም፡-
   ሀ/ ባለሙያው ተልዕኮውን ሲያጠናቅቅ ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅና ፈቃዱ እንዲመለስ ማድረግ አለበት፤
   ለ/ ባለሙያው በሚሰጠው የጤና አገልግሎት ለሚደርስ ጉዳት የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት ይኖርበታል።

69. <u>የሙያ ሥራ ፈቃድን ስለመመለስ</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠው የሙያ ስራ ፈቃድ ሲታገድ ወይም ሲሰረዝ ወይም የመጣበትን ተልዕኮ ሲያጠናቅቅ ወይም የሙያ ስራውን ሲተው የሙያ ስራ ፈቃዱን ለባለሥልጣኑ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የጤና ባለሙያ ሥነ ምግባር

### 70. አጠቃላይ መርሆዎች

ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-

1. አዋጁን፣ ይህን ደንብ ወይም አግባብ ያለውን ማንኛውንም ህግ በሚጥስ መልኩ ሥራውን ማከናወን የለበትም፤
2. ያለምንም አድልዎ የጤና አገልግሎትን ለተገልጋይ መስጠት አለበት፤
3. ለተገልጋይ ጤንነትና ፍላጎት ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

### 71. የጤና ሙያ ሥነ ምግባር ኮሚቴ

1. የጤና ሙያ ሥነ ምግባር ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት አግባብነት ካላቸው ተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎች ሆነው በሚኒስትሩ ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

### 72. የኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት

1. ደረጃውን ባልጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሁም ብቃትና ሙያዊ ሥነ-ምግባር በጎደለው የጤና ባለሙያ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ያጣራል፣ ይመረምራል ሊወሰድ ስለሚገባው አስተዳደራዊ እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፤
2. የቀረበለትን ክስ ለማየት የሚበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ የጤና ባለሙያው ወይም ተቋሙ መልሱን በ30 ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ በመጥሪያው ላይ በመግለጽ ቅሬታዉ ለቀረበበት አካል ይልካል፤
3. የቀረበውን ቅሬታ ለማጣራት እንደአስፈላጊነቱ ከባለሥልጣኑ ጋር በመማከር ገለልተኛ አጣሪ አካል እንዲያጣራለት ሊሰይም ይችላል፤
4. ተገቢው ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ የሙያ ስራ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲታገድ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ ይችላል፤
5. በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን መንስዔዎች በማጥናት ችግሮቹ በዘላቂነት ስለሚፈቱበት ሁኔታ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፤
6. ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

### 73. የኮሚቴዉ ስብሰባዎች

1. ኮሚቴው ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል፡፡

2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3. የኮሚቴው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

74. <u>የጤና ባለሙያ ዋና ዋና ሃላፊነቶች</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-

1. እንደስራ ድርሻው በሚሰጠው የጤና አገልግሎትና በሚወስነው ውሳኔ ተጠያቂነት አለበት፤

2. አግባብ ባለው ህግ መሰረት የጤና አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የተገልጋዩን ሙሉ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

3. ከሙያ አጋሩም ሆነ ከተገልጋይ ጋር በሚያደርገው ሙያዊ ግንኙነት እውነተኛና በቂ መረጃ መስጠት አለበት፤

4. የተገልጋዩን ሚስጥር፣ የግል ሕይወት፣ ምርጫና ክብር መጠበቅ አለበት፤

5. ዘላቂ መልካም ሥነ ምግባርና ስብዕና ሊኖረው ይገባል፤

6. በቡድን ስራ ውስጥ የሌላውን ባለሙያ አስተዋፆ በማክበር የሚጠበቅበትን ሙያዊ ሃላፊነት መወጣት አለበት፤

7. ተገቢውን የምክር አገልግሎት ለተገልጋዩ መስጠት አለበት፤

8. በየጊዜው በሚወጡ አዳዲስ የሕክምና ቴክኖሎጂዎች እና ግኝቶች ሙያዊ እውቀቱንና ክህሎቱን ማሳደግ ይኖርበታል፤

9. ከታካሚውና ከሌሎች የጤና ባለሙያዎች ጋር አግባባዊና ፍሬያማ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፤

10. የታካሚውን ትክክለኛ የሕክምና መረጃ መዝግቦ ማስቀመጥ አለበት፤

11. በተመደበበት ቦታና የስራ ሰዓት በስራ ገበታው ላይ በመገኘት ሙያዊ አገልግሎት መስጠት አለበት፤

12. የህብረተሰብ ጤና ፕሮግራሞችን በሚቀርጽበትና በሚተገብርበት ጊዜ የህብረተሰቡን ተሳታፊነትና ፈቃደኝነት ማረጋገጥ አለበት፤

13. ሙያውን በሚመለከት ጉዳይ አግባብ ያለው አካል የሚሰጠውን ህጋዊ ትዕዛዝና የሚያወጣውን የአሠራር ሥርዓት ማክበር አለበት፡፡

## 75. ስለአገልግሎት ክፍያና ኮሚሽን

ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-

1. ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚጠይቀው የአገልግሎት ክፍያ ውጪ ከማንኛውም ሰው ወይም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም ኮሚሽን ወይም ማናቸውንም ጥቅም መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም፤
2. ተገልጋይ እንዲላክለት ሲል ለማንኛዉም ሰው ኮሚሽን መክፈል ወይም ማናቸውንም ጥቅም መስጠት የለበትም፤
3. ሙያው ከሚፈቅደው ውጪ እንዲያከናውን ወይም ሙያው የሚጠይቀውን እንዳያከናውን ተፅኖ ለማሳደር ወይም ታካሚው መክፈል ከሚገባው በላይ ክፍያ እንዲከፍል ለማድረግ ምንም ዓይነት ክፍያ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትም ሆነ መቀበል የለበትም፤
4. በራሱ ወይም በቀጠረው ወይም አብሮት በሚሰራው ወይም በምትክነት በመደበው ባለሙያ ለተሰጠ የጤና አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር ክፍያ ማስከፈል ወይም መቀበል የለበትም፤
5. ተገልጋይን ለሕክምና ወይም ለሕክምና ሙከራ ወይም ለምርምር ወደ ሌላ ጤና ባለሙያ በማስተላለፉ ለዚሁ አገልግሎቱ ክፍያ ማስከፈል ወይም ሌላ ጥቅም መቀበል የለበትም፤
6. ለጥቅም ሲል የታካሚውን የጤና ችግር የማይፈታ የጤና አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡

## 76. ከሌላ የጤና ባለሙያ ጋር ስለመሥራት

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሌላ የጤና ባለሙያ ቀጥሮ ማሰራት የሚችለው ተቀጣሪው የጤና ባለሙያው አግባብ ባለዉ አካል ፈቃድ የተሰጠው ከሆነ ነው፡፡
2. ለትምህርትና ሥልጠና ካልሆነ በስተቀር አንድ የጤና ባለሙያ አግባብ ባለው አካል የሙያ ፈቃድ ካልተሠጠው ሌላ የጤና ባለሙያ ጋር አብሮ መስራት ወይም ለዚሁ ባለሙያ ማንኛውንም ዓይነት ሙያዊ ድጋፍ መስጠት የለበትም፡፡

## 77. የሙያ ሚስጥር ስለመጠበቅ

1. አግባብ ባለው አካል ለህብረተሰቡ ጤና ጉጂነቱ የታመነበት ጉዳይ ካልሆነ፣ በፍርድ ቤት ካልታዘዘ፣ የታካሚዉን ስምምነት ካላገኘ ወይም በህግ የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የጤና ባለሙያ ታካሚውን የሚመለከት ማንኛዉንም መረጃ በቃል ወይም በጽሁፍ መግለጽ ወይም መስጠት አይችልም።
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ታካሚዎችን የሚመለከት መረጃን ለሳይንሳዊ ምርምር ወይም ጥናት ዓላማ መግለጽ ወይም ማስተላለፍ የሚችለዉ የማንኛውንም ታካሚ ማንነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማያሳዉቅ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡
3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ተላላፊ በሽታ ያለበት ታካሚን ህመሙን ሊያስተላልፍባቸው ለሚችላቸው ሰዎች እንዲያሳውቅ ማበረታታት አለበት፡፡

78. <u>የአገልግሎት መድልዎና ታካሚዎች ስለመላክ</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በመደበኛና በትርፍ ጊዜ ስራ ለተገልጋይ የሚሰጠው ክብካቤ ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በአንድ በሚሰራበት የጤና ተቋም የተመሠረተ ግንኙነትን ምክንያት በማድረግ በሌላ ተቋም ለታካሚው ከሌሎች አስበልጦ የሙያ አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡
3. አገልግሎቱ በጤና ተቋሙ የማይገኝ እስካልሆነና ያለውን የጥቅምና የሥራ ግንኙነት ግልጽ አድርጐ ለታካሚው እስካልገለጸ ድረስ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከአንድ የጤና ተቋም ወደ ሌላ የሚሰራበት የጤና ተቋም ታካሚውን መላክ አይችልም።
4. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም “መደበኛ ስራ” ማለት የጤና ባለሙያው በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ሲሆን፣ “የትርፍ ጊዜ ስራ” ማለት ደግሞ ባለሙያው ከመደበኛ ስራ ውጪ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ነው፡፡

79. <u>ሚስጥራዊ ሕክምና ስለመከልከሉ</u>

1. ማንኛውም የሕክምና ባለሙያ ሚስጥራዊ ሕክምና ሊሰጥ አይችልም።
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የጤና አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሚገለገልበት መሳሪያ፣ ቴክኖሎጂ ወይም ሕክምና መፍትሄ ሊሰጥ እንደሚችል በጥናትና በምርምር የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ሚስጥራዊ ህክምና” ማለት ሆን ተብሎ ከሌሎች ሰዎች የሚደበቅና በጥቂት ሰዎች ወይም ባለሙያዎች ብቻ የሚታወቅ በሽታን ለማዳን

ወይም የጤና ችግርን ለመቅረፍ ወይም ህመምን ለማስታገስ የሚውል መድኃኒት ወይም ሕክምና ነው፡፡

## 80. ሙያ እና አገልግሎትን ስለማስተዋወቅ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-
   ሀ/ አገልግሎቱን የሚመለከት ሙያዊ ያልሆነ፣ ሃሰተኛ ወይም አሳሳች የሆነ የማስተዋወቅ ተግባር መፈጸም የለበትም፤
   ለ/ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር የሚሰጠውን አገልግሎት ማስተዋወቅ አይችልም፤
   ሐ/ የሙያ አገልግሎቱን ሲያስተዋውቅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አላስፈላጊ የሆነ የተገልጋይን ተነሳሽነት በሚፈጥር ሁኔታ መሆን የለበትም፤
   መ/ አገልግሎቱን ሲያስተዋውቅ ሌሎች የጤና ባለሙያዎችን በሚጐዳ ወይም አገልግሎታቸውን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ መሆን የለበትም፤
   ሠ/ የሚያደርገው የሙያ ማስተዋወቅ ተግባር በራሱ የተሻለ የሙያ ብቃትና የዕውቀት የበላይነት ላይ ልዩ ትኩረት የሚያሰጥ መሆን የለበትም፤
   ረ/ ስለሚሰጠው አገልግሎት የሚያደርገው የማስተዋወቅ ተግባር ለተገልጋዩ ስጦታ፣ የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌላ ማበረታቻ የሚያስገኝ መሆኑን በመግለጽ መሆን የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ የወጣ የጤና ባለሙያ የጤና ተቋሙ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ማክበሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 81. መድኃኒትንና የሕክምና መሳሪያን ስለማተዋወቅ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከአምራቹ ወይም ከአከፋፋዩ ጋር የቅጥር ግንኙነት ሳይኖረውና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ፈቃድ ሳይሰጠው ማንኛውንም መድኃኒት ወይም የሕክምና መሣሪያ ሊያስተዋውቅ አይችልም።
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሊያገኘው የሚችለውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ለታካሚው በዋጋ ወይም በፈዋሽነት አግባብነት የሌለውን መድኃኒት ወይም የሕክምና መሳሪያ የበለጠ ጠቀሜታ አጉልቶ ማሳየት የለበትም፡፡

## 82. በምርምር ስለመሳተፍ

ማንኛውም የጤና ባለሙያ በሰው ላይ በሚደረግ ጥናታዊ ሥራ ውስጥ ሊሳተፍ የሚችለው ጥናቱ ተገቢውን የሥነ ምግባር ግምገማ በማለፍ የጽሁፍ ፈቃድ ያገኘና አሠራሩም ተቀባይነት ያገኘዉን የጥናት ፕሮቶኮል የጠበቀ ከሆነ ይሆናል፡፡

83. <u>የሙያ ድጋፍ ወይም ምክር ስለመጠየቅና ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ለተገልጋዩ ጥቅም ሲል አጠራጣሪ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ በመሆኑ ተጨማሪ ወይም ከፍተኛ እርዳታ ሲፈልግ ከማንኛውም የሙያ ባልደረባው ምክር ወይም ድጋፍ መጠየቅ አለበት፡፡
2. በስራ ባልደረባው ምክር የተጠየቀ ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተጠየቀውን ሙያዊ ምክርና አገልግሎት የሙያው ደረጃ በሚፈቅደው መሰረት መስጠት አለበት፡፡

84. <u>የግል እምነትና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የግል እምነቱን ምክንያት በማድረግ እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያ፣ ህጋዊ ውርጃና ደም ማስተላለፍ የመሰለ የሕክምና አገልግሎት አልሰጥም ማለት አይችልም።

85. <u>ህጋዊ መረጃዎችን ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ተገልጋዩን የሚመለከቱ የላብራቶሪና የሌላ ምርመራ ማዘዣና ውጤት፣ የመድኃኒት ማዘዣ፣ የምስክር ወረቀት፣ የደንበኛውን ማህደር፣ የሆስፒታል ወይም ሌላ ሪፖርቶችን ሲሰጥ ሙሉ ስሙንና ፊርማውን ማስፈር አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሟላና እውነተኛ የህመም ፈቃድ ወይም የሕክምና ምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

86. <u>ስለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀትና እደላ</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ስለይዘቱና በሰው አካል ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት የማያውቀውን መድኃኒት ወይም የተቀመመ የመድኃኒት ዝግጅቶችን ማዘዝ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ መድኃኒትን የሚያዝበት የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት በተቋሙ ደረጃና በሙያው አይነት መሠረት የተዘጋጀና ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

3. ማንኛውም የጤና ባለሙያ አስገዳጅ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሚያዘው መድኃኒት በብሔራዊ የመድኃኒት መዘርዝር ውስጥ የተመዘገበ መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም መድኃኒት ለማደል ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ማንኛውንም በሕጋዊ መንገድ ያልተገኘ መድኃኒትን ማደል ወይም መያዝ የለበትም፡፡

87. <u>ስለቆሻሻ አወጋገድና በሽታን መከላከል</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ መወገድ ያለበትን ከጤና አገልግሎት የሚወጣ ቆሻሻ ለራሱ፣ ለተገልጋዩና ለህብረተሰቡ ጤና ሲባል ተገቢ በሆነ መልኩ ማስወገድ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከራሱ ወደ ተገልጋይ፣ ከተገልጋይ ወደ ተገልጋይ ወይም ከተገልጋይ ወደ ጤና ባለሙያ በሽታ እንዳይተላለፍ የሚቀመጡ የደህንነት ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት፡፡

88. <u>በሽታ የሚያስከትለው ሁኔታ ስለመግለጽ</u>

1. የጤና ባለሙያው በሞት አፋፍ ላይ ያለና ሊድን በማይችል ወይም በከባድ በሽታ የተያዘ ታካሚን የህመም ሁኔታና በሽታው የሚያስከትለውን ውጤት ለታካሚው ወይም ታካሚው ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ወይም የአእምሮ ሕመምተኛ ከሆነ ለአሳዳሪው ሊገልጽለት ይገባል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የጤና ባለሙያው በሞት አፋፍ ላይ ያለና ሊድን በማይችል ወይም በከባድ በሽታ የተያዘን ሰው የበሽታ ሁኔታና በሽታው የሚያስከትለውን ውጤት ለታካሚው መንገር በመንፈስ አለመረጋጋት ታካሚው ራሱን ይጎዳል ብሎ ካመነ ይህንን መረጃ ለታካሚው ቤተሰብ አባላት ብቻ ሊናገር ይችላል፡፡

89. <u>እክልን እና ሙያዊ ያልሆነ ተግባርን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሚከተሉትን አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡-

1. እክል ገጥሞታል ብሎ ያመነበትን የሌላ የጤና ባለሙያን እክል፤
2. የሚያውቀው ወይም በይፋ እንዲያውቅ የተደረገ ከሆነ ወይም በተጠረጠረው እክሉ ምክንያት በሥራ ባልደረቦቹ ተገቢውን ድጋፍ እንዲጠይቅ ምክር የተለገሰው ከሆነ የራሱን እክል፤
3. የሙያ ፈቃድ የሌለው ወይም የሙያ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው የጤና አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን፤ እና
4. የሌላ ባለሙያን ማንኛውም ሙያዊ ያልሆነ ሥነ ምግባርን፡፡

<u>**ክፍል ሰባት**</u>

## ስለተቋማት

### 90. ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

1. ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አግባብ ካለው አካል ሳያገኝ ተቋም አቋቁሞ ስራ ላይ መስማራት አይችልም።
2. ለማንኛውም ተቋም የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በወሰደበት መስፈርት መሰረት ስራውን ማከናወን ይኖርበታል።
4. አግባብ ያለው አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚሰጥበት ወይም በሚያድስበት ጊዜ የምርቱን ወይም የአገልግሎቱን ዓይነት፣ አመራረት፣ አዘገጃጀት፣ አከመቻቸት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ከምርቱ ወይም ከአገልግሎቱ ጥራትና ደህንነት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ዓይነት ሁኔታዎችን እንደ ተቋሙ ግዴታ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡
5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ውጪ በማንኛውም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

### 91. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ስለመመለስ

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት፣ የተሠረዘበት ወይም እድሣት የተከለከለበት ወይም ሥራውን ያቋረጠ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን አግባብ ላለው አካል መመለስ አለበት፡፡

### 92. ስለባለሙያዎች የጤና ምርመራ

1. ማንኛውም ተቋም ከተገልጋይ ጋር ግንኙነት ያለው የጤና ባለሙያን ወይም ምግብ አዘጋጅን በተቋም ውስጥ ከመቀጠሩ በፊት እንዲሁም በየዓመቱ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በስተቀር የጤና ምርመራ እንዲያደርግ ማድረግ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለራሱ የጤና ምርመራ ማድረግ አይችልም።
3. ማንኛውም ምግብ አዘጋጅ በምግብ በሚተላለፍ በሽታ በሚያዝበት ጊዜ ለተቋሙ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4. ማንኛውም የምግብ ተቋም በምግብ በሚተላለፍ በሽታ የተያዘ መሆኑ የታወቀን የምግብ አዘጋጅ በሽታው የማይተላለፍበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ከምግብ ጋር ንክኪ ካላቸው ስራዎች እንዲገለል ማድረግ አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ ከተገሌጋይ ጋር ግንኙነት ያለውን የጤና ባለሙያ ወይም የምግብ አዘጋጅ ምርመራ ሊያደርግበት ስለሚገባው የበሽታ አይነት በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

93. <u>ስለተቋም መስፈርቶችና ክልከላዎች</u>

1. ማንኛውም ተቋም የሚለቃቸውን ጐጂ ንጥረ ነገሮችና ቆሻሻዎች ለመቆጣጠር ውስጣዊ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡
2. ማንኛውም ተቋም ከውጭ አገር ምግብን ወይም መድኃኒትን በማስመጣት በቀጥታ ወደ ሌላ አገር ለመላክ ከባለሥልጣኑ ልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
3. ማንኛውም ተቋም የተከለከለ ወይም የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበት ምግብን ወይም መድኃኒትን ማስመጣት፣ መያዝ ወይም ማሰራጨት አይችልም፡፡
4. ማንኛውም አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለሌለው ሰው ምግብን ወይም መድኃኒትን ማከፋፈል አይችልም።
5. ማንኛውም የተግባር ልምምድ ለሚያደርግ ተማሪ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ የፈቀደ የጤና ተቋም ተማሪው በታካሚው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ይኖርበታል።

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

94. <u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ አግባብ ባለው አካል በማናቸውም ጊዜ የሙያ ስራ ፈቃዱን እንዲያሳይ ወይም የራሱን ወይም የሌላ ባለሙያ ሙያዊ እንቅስቃሴ የሚያሳይ መረጃ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ያገኘውን መረጃ በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር በሚስጥር መጠበቅ አለበት፡፡

95. <u>ሪፖርት የማድረግ ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ሰው አንድ የጤና ባለሙያ የጤና ሁኔታው ብቁ የሚያደርገው አለመሆኑን ወይም ሙያዊ ያልሆነ ሥነ ምግባር መፈጸሙን ካመነበት አግባብ ላለው አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አግባብ ላለው አካል በቅን ልቦና መረጃ የሰጠ ሰው በህግ ተጠያቂ አይሆንም።

96. <u>ስለአገልግሎት ክፍያ</u>

ማንኛውም ሰው የሙያ ስራ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ለማሳደስ፣ መድኃኒትን ለማስመዝገብ ወይም ሌሎች ምስክር ወረቀቶችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት በመንግሥት በጸደቀ ተመን መሰረት አግባብ ላለው አካል የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

97. <u>ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

1. የሚከተሉት በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡-

    ሀ/ የጤና አገልግሎት ተቋም ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 174/1986፤ እና

    ለ/ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባዔ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/1994፡፡

2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

98. <u>መመሪያ የማዉጣት ስልጣን</u>

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

99. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 370/2008

## የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት ክፍያ ተመንን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5፣ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 17(1) እንዲሁም በምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 55(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የምግብ፣ መድኃኒት፣ የጤና ተቋማትና የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ የአገልግሎት ክፍያ ተመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 370/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው፤
   2. "ደንብ" ማለት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 299/2006 ነው፤
   3. በአዋጁ እና በደንቡ የተጠቀሱ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. **ስለ አገልግሎት ክፍያ**

   1. የምግብ፣ የመድኃኒትና የኮስሞቲክስ አምራቾች አዲስ ፈቃድ ለማግኘት፣ በየጊዜው እድሳት ለማካሄድ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት፤ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን፣ አዲስ የምርት መስመር ለማስፈቀድ፣ የአድራሻ ለውጥ የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ ሲኖርና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 እና 2 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡
   2. የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች፣ የኮስሞቲክስና የትምባሆ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይነት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

ለማግኘት፣ በየጊዜው እድሳት ለማካሄድ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት፣ ሁለተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽንና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ፣ ተጨማሪ መጋዘን ለማስፈቀድ፣ የአድራሻ ለውጥ፣ የባለሙያ ወይም የድርጅት ስም ለውጥ ሲኖርና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ፣ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 3 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

3. የጤና ተቋማት የመድኃኒት መግዣ ፈቃድ ለማግኘት፣ ለእድሳት እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 4 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡
4. ለጤና ባለሙያዎች የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬት ለማግኘትና ለእድሳት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 5 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡
5. ከውጭ አገር በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት ለሚመጡና ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ሄደው ለመሥራት ለሚፈልጉ የጤና ባለሞያዎች የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ሰርተፍኬትና በሥራ ላይ ያላቸውን አፈፃፀም መግለጫ ማስረጃ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 6 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡
6. የጤና ተቋማት አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት፣ ለእድሳት፣ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ለማግኘት፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን፣ አዲስ የአገልግሎት ዘርፍ ለመጨመር፣ የአድራሻ የባለሙያና የድርጅት ስም ለውጥ ለማድረግና አዲስ ተቋም በተጨማሪነት ለማስፈቀድ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 7 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡
7. በመግቢያና መውጫ በር ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ወይንም ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ ምግብ ለቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 8 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልገሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡
8. በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ ለሚካሄድ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ፣ ኮስሞቲክስና የኮስሞቲክስ ጥሬ ዕቃዎች፣ ትምባሆ ቁጥጥር፣ ለአስክሬን ቁጥጥር፣ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ ለሚበር

አውሮፐላን ርጭት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 9 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልገሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

9. በመውጫ በሮች ላይ ለማካሄድ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ መድኃኒትና የመድኃኒት ጥሬ ዕቃዎች፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ፣ ኮስሞቲክስና የኮስሞቲክስ ጥሬ ዕቃዎች እና የትምባሆ ቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 10 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልገሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

10. በውጭ ሀገር የሚገኝ የምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ እና ኮስሞቲክስ አምራች ወኪል ለመሆን ፈቃድ ለማግኘት፣ የወኪል ለውጥ፣ ተጨማሪ ወኪል ለማስመዝገብ ለእድሳት እንዲሁም ሲጠፉ ምትክ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 11 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

11. ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ለማስመዝገብ ለሰነድ ቅድመ ግምገማ ሥራ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዙር ቅድመ ማጣሪያ ሰነድ ግምገማ ስራ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 12 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልገሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

12. ለምግብ፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያ መሳሪያና ኮስሞቲክስ ለማስመዝገብ ወይም ለዳግም ምዝገባ ለሰነድ ግምገማ ሥራ፣ ለዋና እና አነስተኛ ልዩነት ምዝገባ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 13 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

13. ለሚወገዱ ግብዓቶች ወይም ምርቶች በቦታው በመገኘት በአግባቡ መወገዱን ለማረጋገጥና ለሰርተፊኬት ዝግጅት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 14 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

14. የመድኃኒት ምርት ሰርተፊኬት፣ ለሕክምና መገልገያዎች የተሰጠ የገበያ ፈቃድ ወይም ሰርተፊኬት እንዲሁም ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር የምግብ፣ መድኃኒትና ኮስሞቲክስ አምራቾች የመልካም አመራረት ስርዓትን ተከትለው ስለማምረታቸው የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማግኘት ወይም ሰርቲፍኬት ለማሳደስ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 15 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

15.በውጭ ሀገር የሚገኙ የመድኃኒት አምራቾች በአገር ውስጥ ለሚከፍቱት ወኪል ቢሮዎች እውቅና ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 16 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

16.ባለስልጣኑ ቁጥጥር በሚያካሂድባቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ወይም ፈቃድ ለማሳደስ እንዲሁም ሲጠፋ ምትክ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 17 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

17.መድኃኒትን በአገር ውስጥ ለማስመዝገብና ለማስመጣት በውጭ ሀገር የሚካሄድ የመልካም አመራረት ቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 18 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

18.የሕክምና ሙከራ ቁጥጥር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 19 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

19.ለመድኃኒት ምዝገባ፣ ዳግም ምዝገባና ለውጥ የላቦራቶሪ ምርመራ ስራ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 20 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

20.የባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ለሚሰጣቸው የመድኃኒት ምርመራ ስራዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 21 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

21.የባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ለሚሰጣቸው የምግብ ምርመራ ስራዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 22 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

22.የባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ለሚሰጣቸው የቶክሲኮሎጂ ምርመራ ስራዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 23 በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 2 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**ሰንጠረዥ አለው**

## ክፍል አስራ ሰባት

## ባህል፣ቱሪዝምና ስፖርት

### ሀ/ ባህልና ቅርስ

## አዋጅ ቁጥር 179/1991

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አዋጅ

በሀገሪቱ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍትን በተቀናጀ ሁኔታ መምራት፣ የሀገሪቱን የመዛግብት፣ የመጻሕፍትና መሰል ጽሑፎችን፣ ቀረጸ ድምጽና ምስል ማሰባሰብ፣ የዶክሜንቴሽን አገልግሎትን በዘመናዊ መልክ በአንድ ማዕከል ማደራጀትና የሀገሪቱን የመረጃ አገልግሎት ማዳበር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አዋጅ ቁጥር 179/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **የተፈጻሚነት ወሰን**

   1. ይህ አዋጅ መዛግብትን በተመለከተ እንደ አግባቡ በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።
   2. ሕትመትን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ በማንኛውም እትም ወይም ከፊል እትም፣ ደራሲ፣ አታሚ፣ አሳታሚ፣ አባገር፣ አከፋፋይና ወኪል ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

3. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ድርጅት” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ድርጅት ነው፤[7]
2. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነዉ፤[8]
3. “መዛግብት” ማለት ቅርፁንና መልዕክቱ የተላለፈበትን ሁኔታ ሳይለይ መንግሥታዊ መ/ቤቶች እንዲሁም ግለሰቦች የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የተፈጠረና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴው ካበቃ በኋላ በመረጃ ፋይዳነቱ ቋሚ ጥበቃ እንዲደረግለት የተመረጠ ማናቸውም በኦርጂናልም ሆነ በቅጅ መልክ የሚገኝ ጽሑፍ፣ ወይም በካርታ፣ በግራፍ የተገለጸ ወይም በድምጽና በሥዕል፣ በፎቶግራፍ ወይም በመሳሰለ ሠነድ ያለ ሪኮርድ ነው፤
4. “የሕዝብ ቤተመጻሕፍት” ማለት በክልል አስተዳደር ወይም በከተማ አስተዳደር ሥር ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ቤተ መጻሕፍት ነው፤
5. “ሪኮርድ” ማለት መልዕክቱ የተላለፈበትን ቅርጽና የመልዕክቱን ዓይነት (ይዘት) ሳይለይ በአመንጪው ተቋም ወይም ግለሰብ ለሥራ ሂደት የተፈጠረና ለተፈጠረበት ጊዜና ቦታ በመረጃነት ሊቀርብ የሚችል ነገር ግን በመረጃ ፋይዳው ተመዝኖና ተመርጦ ወደ ብሔራዊ ቤተመዘግብትና ቤተ መጻሕፍት ያልተዛወረ ወይም ለመዛወር በሂደት ላይ የሚገኝ ማናቸውም ደብዳቤ፣ ማስታወሻ፣ ብትን ጽሑፍ፣ ጥራዝ፣ መጽሐፍ፣ ዕቅድ፣ ካርታ፣ ንድፍ፣ ቅርጽ፣ ሥዕላዊ ወይም ግራፊክ፣ ፎቶግራፍ፣ ፊልም፣ ማይክሮ ፊልምና ማይክሮፊሽ፣ የድምጽ ሪኮርድ፣ ቪዲዮ ቴፕ ወይም በኤሌክትሮኒክ የተመዘገበ መረጃ ነው፤
6. “የታተመ ጽሑፍ” ማለት በማናቸውም መካኒካዊ ወይም ኤሌክትሮኒካዊ ዘዴ የታተመ መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ክፍል፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ በራሪ ወረቀት፣ ካርታ፣ ዕቅድ፣ ሰሌዳ፣ ብትን እትም፣ ሠንጠረዥና ሌላ ተመሳሳይ ሠነድ ነው፤
7. “በከፊል የታተመ (ረግሬይ ሊትሬቸር)” ማለት ልባሱ ብቻ በማተሚያ ቤት ታትም የውስጥ ጽሑፉ በታይፕ ወይም በኮምፒውተር ወይም በስቴንስል ተቀርጾ የተባዛ የመረጃ ፋይዳ ያለው ሰነድ ነው፣

[7] በ12/1 (1998) አ. 471 አንቀፅ 33/2 መሰረት “ድርጅት” የሚለው ስያሜ “ኤጀንሲ” በሚል ስለተቀየረ በዚሁ መሠረት ይነበብ፡፡
[8] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9 (23) የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

8. "የተባዛ ጽሑፍ" ማለት በማተሚያ ቤት ሳይሆን በታይፕ ወይም በኮምፒውተር በወረቀት ላይ የተመታ ወይም በስቴንስል የተመትቶ የተባዛና የዶክሜንት ዋጋ ያለው ጽሑፍ ነዉ፤

9. "ማኑስክሪፕት" ማለት በባሕላዊ ዘዴ የተዘጋጀ ታሪካዊ፣ ባሕላዊ ወይም ሥነጥበባዊ ይዘት ያለው ጽሑፍ ነው፤

10. "ቀረጸ ድምጽ" ማለት በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ አማካኝነት በድምጽ ተቀርጾ የሚተላለፍ መረጃ ነው፤

11. "ቀረጸ ምስል" ማለት በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ አማካኝነት በምስል ተቀርጾ የሚተላለፍ መረጃ ነው፤

12. "ቀረጸ ምሥልና ድምጽ" ማለት በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ አማካኝነት ድምጽና ምሥልን በማጣመር የሚተላለፍ መረጃ ነው፤

13. "ትውፊት" ማለት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ በቃል የተላለፈና የሚተላለፍ የአንድ ሕዝብ ወይም አካባቢ ባህል፣ ወግ፣ እምነት፣ ታሪክና ሌሎች ማህበራዊ ዕሴቶችን በዘፈን፣ በዝማሬ፣ በተረትና ምሣሌ እና በሌሎች መንገዶች አማካኝነት የሚገልጽ ሥነ ቃል ነዉ፤

14. "የቃል ታሪክ" ማለት በቃል ምልልስ ከሰው የተገኘና በካሴት የተቀረጸ ወይም በጽሑፍ ተገልብጦ የሚገኝ የታሪክ መረጃ ነዉ፤

15. "የመረጃ አመንጭ" ማለት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የተፈጠረ የመረጃ ክምችት ያለው ሰው ነው፤

16. "አሳታሚ ድርጅት" ማለት በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም አሳታሚ ድርጅት ነው፤

17. "አታሚ" ማለት በመካኒካል ኃይል በመንቀሳቀስ ጽሑፎች፣ ቀረጸ ድምጽና ቀረጸ ምስል የሚያትም ወይም የሚያራባ ሰው ነው፤

18. "ማተሚያ ቤት" ማለት በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የሕትመት ሥራን የሚያከናውን ድርጅት ነው፤

19. "መጽሐፍ" ማለት የወቅታዊ ዜና ጽሑፍ ያልሆነና ቢያንስ አርባ ዘጠኝ እና ከዚያም በላይ ገጾች ያሉት የታተመ ጽሑፍ ነው፤

20. "የዶክሜንት ቅርስ" ማለት ጥንታዊ የብራና ጽሑፎች፣ ጥንታዊ ሕትመቶች፣ ማናቸውም ዓይነት እትምና እትም ያልሆነ እንዲሁም በከፊል የታተሙ ጽሑፎች፣ በዲጂታል ኤሌክትሮኒክስ ፎርም የተቀረጸ ቀረጸ ድምጽ፣ ቀረጸ ምስል፣ ቀረጸ ድምጽና

ምስል ሌሎችም በመረጃ ፋይሎች በትርስነት ተጠብቀው ለትውልድ የሚተላለፉ ሠነዶችን የሚያጠቃልል ነው፤

21.“ሲዲ” ማለት ኮምፓክት ወይም አፕቲካል ዲስክ የሆነ እና በኮምፒውተር እና ሌላ ተመሳሳይ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ጽሑፍና ዳታ ድምጽና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በተናጠል ወይም በማዋሀድ ለማከማቸት እንዲሁም መረጃን ለማሠራጨት ወይም ለማስተላለፍ አገልግሎት የሚውል ነው፤

22.“ሕትመት” ማለት የታተመ ጽሑፍን፣ በከፊል የታተመ ጽሑፍን (ግሬይ ሊትሬቸርን)፣ ቀረጸ ድምጽን፣ ቀረጸ ምስልን፣ ቀረጸ ድምጽና ምስልን፣ እና በማግኔቲክ ዲስክ (ኮምፓክት ዲስክ) የተቀረጹ ሕትመቶችን ያጠቃልላል፤

23.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ድርጅት

4. **መቋቋም**

   1. ኢትዮጵያ ብሔራዊ በተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ድርጅት (ከዚህ በኋላ “ድርጅቱ” እየተባለ የሚጠራን) የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለየብቻ ራሳቸውን ችለው ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡
   2. ድርጅቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

5. **ዋናው መሥሪያ ቤት**

   የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ማቋቋም ይችላል፡፡

6. **የድርጅቱ አቋም**

   ድርጅቱ፡-

   1. አንድ የመማክርት ጉባዔ፤
   2. አንድ ዋና ዲሬክተር፤ እና
   3. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

   ይኖሩታል፡፡

7. **የድርጅቱ ዓላማ**

የድርጅቱ ዓላማ የሀገሪቱን የመረጃ ሀብቶች እያሰባሰበ፣ እያደራጀና እየተንከባከበ በመጠበቅ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለማገናዘቢያ (ሪፈረንስ) አገልግሎት ማቅረብ ይሆናል፡፡

8. <u>የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ድርጅቱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሀገሪቱ ከሚገኝ ማንኛውም ተቋም የመነጩ ሪኮርዶች ወደ ድርጅቱ ከመዛወራቸዉ በፊት በያሉበት ተቋም በበቂ ቦታና አስተማማኝ ሁኔታ እንዲያዙ ያደርጋል፤
2. የታተሙ ጽሑፎች፣ በከፊል የታተሙ ጽሑፎች (ግሬይ ሊትሬቸ)፣ ያልታተሙ ጽሑፎች፣ የማኑስክሪፕት፣ የታሪካዊ መዛግብትና የሪኮርዶች እንዲሁም የትውፊታዊም ሆነ የቃል ታሪኮች፣ የቀረጸ ድምጽ፣ የቅረጸ ምስል፣ የቅረጸ ምስልና ድምጽ በአጠቃላይም የመረጃ ቅርሶች ብሔራዊ የክምችት ማዕከል ሆኖ ይሠራል፡ ክምችቶቹን በሳይንሳዊና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለጥናትና ምርምር እንዲውሉና ረዥም ዕድሜ እንዲኖራቸው ጥበቃ ያደርጋል፤
3. በውጭ ሀገር ያሉትን የኢትዮጵያ የስነጽሑፍ ቅርሶች ወደ ሀገር ለማስመለስ ወይም ቅጂውን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል፤
4. ተግባራቸውን ያቋረጡ መሥሪያ ቤቶችን ሪኮርዶችና ባለቤት የሌላቸውን መዛግብት ወደ ድርጅቱ እንዲዛወሩ ያደርጋል፤ ይንከባከባል፤
5. ሪኮርዶች ከየአመንጪ ድርጅቶች ተሰባስበው በአስተማማኝ ሁኔታ በጊዜያዊነት የሚከማቹበት፣ ፋይዳ ያላቸው የሚመረጡበትና ወደ ብሔራዊ በተመዛግብት የሚተላለፉበት፣ ያልተመረጡት የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚጠሰንበት የሪኮርድ ማዕከል ያቋቁማል፤
6. በአገሪቱ ከሚገኙ በተመዛግብት፣ ቤተመጻሕፍት፣ የዶክሚንቴሽን ማዕከላትና በሌሎች መረጃ ሰጪ አካላት መካከል የጋራ ትብብር በመፍጠር የሀገሪቱን ብሔራዊ የመረጃ ሀብት ወጥነት ባለው ሁኔታ በጋራ ያደራጃል፣ የመረጃ ባንክ (ዳታ ቤዝ) ይፈጥራል፣ በአግባቡና በተቀላጠፈ ዘዴ ለመጠቀም የሚያስችል ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፤
7. ብሔራዊ ቤተመዛግብትን፡ በተመጻሕፍትንና ሪኮርድ ማዕከልን እንዲሁም የሪኮርድ አመንጪ ተቋማት የሪኮርዶች አያያዝና ደኅንነትን በተመለከተ ደንብና መመሪያ እንዲወጣ ሃሳብ ያቀርባል፤ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

8. ለመንግሥት ወይም ለሕዝብ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውና በግለሰቦች እጅ የሚገኙ መዛግብት ለሰው ሠራሽ ወይም ለተፈጥሮዊ አደጋ የተጋለጡ ሆነው ሲገኙ ለመንግሥትና ለሕዝብ ጠቀሜታ ሲባል ካሣ በመክፈል ወደ ድርጅቱ እንዲዛወሩ ያደርጋል፤

9. ዋና (ኦርጂናል) መዛግብትና የዶክመንት ቅርሶች በቋሚነት ከአገር እንዳይወጡ ቁጥጥር ያደርጋል፤ የቅጂዎችን ይዘት በመመርመር ከሀገር እንዲወጡ ፈቃድ ይሰጣል፤

10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝገበ መጻሕፍትንና መዝገበ መጽሔትን ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤

11. የሀገሪቱ ዓለም አቀፍ እስታንዳርድ የመጻሕፍትና የመጽሔት መለያ ሰጪ አካል ሆኖ ይሠራል፤

12. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) እና (11) በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ሀገሪቱን ይወክላል፤

13. በሀገሪቱ ውስጥ ተዘጋጅተው ለሚታተሙ ወይም ከሀገር ውጪ ተዘጋጅተው በሀገር ውስጥ ለሚታተሙ በፊልም፣ በማግኔቲክ ቴፕ ወይም ማግኔቲክ ዲስክ የተቀረጹ የሥነጽሑፍ፣ የታሪክ፣ የሣይንስና ለሌሎች ተመሳሳይ የጽሑፍ ሥራዎች፣ የቀረጻ ድምጽ፣ ቀረጻ ምሥልና ድምጽ እንዲሁም የሲዲ ሥራዎች ባለቤትነት መብት መዝጋቢ አካል ሆኖ ይሠራል። ይህንኑ በተመለከተም በዓለም አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ ማዕከል በመሆን ሀገሪቱን ይወክላል፤[9]

14. በሀገሪቱ የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም በግለሰቦች እጅ የሚገኙትን ዉድና ብርቅ የሆኑትን ጥንታዊ ጽሁፎችና ሌሎች ሥዕሎች ከተቋማቱ እና ከግለሰቦቹ ጋር በሚደረግ ስምምነት በማዕከል ያሰባስባል፣ ማሰባሰብ በማይቻልበት ሁኔታ በማይክሮ ፊልምና በማይክሮፊሽ በመቅረጽ ይይዛል እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ለተጠቃሚዎች በአመቺ ሁኔታ ያቀርባል፤

15. በይነ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ተቋማት እንዲሁም የታወቁ የጥናትና ምርምር ተቋማት ለሚያወጡአቸው እትሞች አከማች ይሆናል፤

16. በመንግሥት ዉሳኔ ምስጢራዊ የሆኑ መዛግብት ምስጢር መጠበቱን ያረጋግጣል፤

[9] ይህ ስልጣን በ9/40 (1995) ኢ 320 አንቀፅ 16/3 መሰረት ለኢትዮጵያ የአህምሮአዊ ንብረት ፅህፈት ቤት ተላልፏል፡፡

17. በክልል መስተዳድሮች ከተቋቋሙና ከሚቋቋሙ ቤተ መዛግብትና ቤተመጻሕፍት እንዲሁም የሕዝብ አብያተመጻሕፍት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
18. ድርጅቱ ለተቋቋመበት ዓላማ የሥልጠና ማዕከል ሆኖ ይሰራል፤
19. ከሀገር አቀፍና ዓለምአቀፍ አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ የቤተመጻሕፍትና የቤተመዛግብት ሙያ እንዲያድግና እንዲስፋፋ ጥረት ያደርጋል፤
20. ለሚሰጠው አገልግሎት እንደአስፈላጊነቱ ዋጋ ያስከፍላል፤
21. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

## 9. <u>የመማክርት ጉባዔ አባላት</u>

1. የመማክርት ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የሚኒስቴሩ ተወካይ ............................. ሰብሳቢ

ለ/ የገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ[10] ...................... አባል

ሐ/ የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ .................... "

መ/ የፍትሕ ሚኒስቴር ተወካይ[11] ........................ "

ሠ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ .................. "

ረ/ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን [12]ተወካይ ........... "

ሰ/ የዩኒቨርስቲዎች ተወካይ ............................. "

ሸ/ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ሰብሳቢ ............ "

ቀ/ የሥነጥበባት ማኅበሮች ሰብሳቢ .................... "

በ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ........ "

ተ/ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ ተወካይ............ "

ቸ/ የኢትዮጵያ ካርታ ሥራዎች ባለሥልጣን ተወካይ............... "

ኀ/ የኢሚግሬሽን፣ የደህንነትና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን[13] ተወካይ...... "

ነ/ የድርጅቱ ዋና ዲሬክተር .............. አባልና ፀሐፊ

2. ከላይ የተደነገገው ቢኖርም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሌሎች አካላትም በአባልነት ሊወከሉ ይችላሉ።

## 10. <u>የመማክርት ጉባዔው ሥልጣንና ተግባራት</u>

---

[10] በ22/12(2008) አ.916 አንቀፅ 9(6) መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለሆነ በዚሁ መሠረት ይነበብ፡፡
[11] በ22/ 62 (2008) አ.943 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ኢቃቤ ህግ ተብሎ ይነበብ፡፡
[12] በ22/12 (2008) አ.916 አንቀፅ 9(11) መሠረት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ስለሆነ በዚሁ መሠረት ይነበብ፡፡
[13] በ19/55 (2005) አ.804 መሠረት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ስለሆነ በዚሁ መሠረት ይነቡበ፡፡

የመማክርት ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. ድርጅቱ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል ምክር ይሰጣል፣
2. ብሔራዊ የሪከርዶች አስወጋጅ ኮሚቴን ይሰይማል።

11. <u>**የመማክርት ጉባዔው ስብሰባ**</u>

1. ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤
2. አባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልአተ ጉባዔ ይኖራል፤
3. የጉባዔዉ ውሳኔ በአብዛኛው ድምጽ ይወሰናል፤ ድምጽም ለሁለት በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4. የመማክርት ጉባዔ አባላት በአባልነት የሚቆዩት ለአምስት ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

12. <u>**ስለድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር**</u>

1. ዋናው ዳይሬክተር በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል፡፡
2. ዋናው ዳይሬክተር የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስትሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሥራ ይመራል፤ ያስተዳድራል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋናው ዳይሬክተር፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ለድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የድርጅቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   ሐ/ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ለድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት የገንዘብ ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

   መ/ የድርጅቱን የሥራ ክንውን የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

   ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል፡፡
4. ዋናው ዳይሬክተር ለድርጅቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለድርጅቱ ሌሎች ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱን ተክቶ የሚሠራው ሰው ውክልና ከሰላሳ ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ ከሆነ ውክልናው ለሚኒስትሩ ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

<u>**ክፍል ሦስት**</u>

<u>**የብሔራዊ መዛግብት አስተዳደር**</u>

13. <u>የሪኮርድ አመንጪ ግዴታ</u>

ማንኛውም የሪኮርድ አመንጪ መሥሪያ ቤት፡-

1. በተገቢው የተደራጀ የሪኮርድና የማኅደር አገልግሎት ዘርፍ ይኖረዋል፤
2. በየዓመቱ መጨረሻ 25 ዓመት የሚሞላቸውንና የማይንቀሳቀሱ ሪኮርዶችን ወደ ድርጅቱ የሪኮርድ ማዕከል ያዘዋውራል፤
3. ከመሥሪያ ቤቱ ተሰርቀው ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚጠፉ ሪኮርዶችን በሚመለከት መሰረቃቸው ወይም መጠፋታቸው የታወቀ፣ የመረጃን ይዘት ለመለወጥ የተፋቁ ወይም የተደለዙ ሪኮርዶችን በተመለከተ ይህ ሁኔታ በተረጋገጠ በአንድ ወር ውስጥ ለድርጅቱ ሪፖርት ያደርጋል።
4. በመሥሪያ ቤቱ ይዞታ ስር ያሉ ሪኮርዶች ከመሥሪያ ቤቱ ውጪ በዘላቂነት የሚዛወሩበት ሁኔታ ሲፈጠር ዝውውሩ ከመከናወኑ በፊት ሁኔታውን ለድርጅቱ ማሳወቅ አለበት፤
5. ኤክስፐርትና ከዚያም በላይ ማዕረግ ካላቸው አባላት የተውጣጣና መወገድ የሚገባቸውን ሪኮርዶች ዝርዝር የሚያዘጋጅ ኮሚቴ ያቋቁማል፤
6. የሪኮርድና ማህደር ሥራን ዘመናዊ ለማድረግ የሚወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. መሥሪያ ቤቱ በሚፈርስበት ጊዜ ሪኮርዶቹን ወደ ድርጅቱ ማዛወር አለበት፡፡

14. <u>ሪኮርዶችን ስለማስወገድ</u>

1. ማንኛውም የሪኮርድ አመንጪ መሥሪያ ቤት ሪኮርዶችን ማስወገድ አይችልም፡፡
2. ከ1928 ዓ.ም በፊት የተፈጠሩ ማናቸውም መዛግብት አይወገዱም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናንኛውም ሪኮርድ የሚወገደው በድርጅቱ ብቻ ይሆናል፡፡

15. <u>የድርጅቱ ግዴታ</u>

ድርጅቱ፡-

1. ከመረጃ አመንጪዎች የተላኩለትን ሪኮርዶች ከ5 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አደራጅቶ ለጥናትና ምርምር ሥራ ያቀርባል፤
2. አመንጪዎች መዛግብታቸዉን በጠየቁ ጊዜ ሁሉ በውሰት ያቀርባል፡፡

16. <u>ስለተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሀገሪቱ ሰው መዛግብትን ለጥናትና ለምርምር የመጠቀም መብት አለው፡፡ አፈፃፀሙ ድርጅቱ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

17. <u>በመዛግብት መጠቀም ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>

1. ከላይ በአንቀጽ 16 የተደነገገው ቢኖርም፡-

   ሀ/ መዝገቡ ወደ ድርጅቱ ከመዛወሩ በፊት በአመንጪውና ድርጅት መካከል በተደረገ ስምምነት ወይም በመንግሥት በተወሰነው መሠረት የመዝገቡ የምስጢራዊነት ዘመን ያላለቀ ከሆነ፤

   ለ/ መዝገቡ የያዘው ምስጢር ይፋ መውጣት በሀገርና በሕዝብ ደህንነት ላይ አደጋ የሚያደርስ መሆኑን ድርጅቱ በእርግጠኝነት ሲያምንበት፤

   ሐ/ የግል መዛግብትን በተመለከተ፣ በአስረካቢውና በደርጅቱ መካከል በተደረገዉ ስምምነት መሠረት ጥያቄዉ ሊስተናገድ የማይችል ሰሆን፤

   በመዛግብት ለመጠቀም የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አያገኝም።

2. ድርጅቱ ጥያቄውን ያልተቀበለበትን ምክንያት ጥያቄው በቀረበ በአንድ ሳምንት ጊዜ ዉስጥ በጽሁፍ መግለጽ አለበት፡፡

18. <u>መዛግብትን ስለማስተላለፍና ባለቤትነትን ስለማዛወር</u>

1. መንግሥታዊ መዛግብትን በንግድ መልክ መግዛት፣ መሸጥ፣ በስጦታ ወይም በውርስ እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

2. በግል ባለቤትነት ስር የሚገኙ መዛግብትን በውርስ፣ በስጦታ ወይም በግዢ ወደ ድርጅቱ ማዛወር ይቻላል።

3. ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም በይዞታው ስር የሚገኙ መዛግብትን በውርስ፡ በስጦታ፡ ወይም በሽያጭ መልክ ሲያስተላልፍ ለድርጅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት አስተዳደር</u>

19. <u>ሕትመቶችን በድርጅቱ የማኖር ግዴታ</u>

1. ማንኛውም አታሚ ወይም አሳታሚ ያተመውን ወይም ያሳተመውን ማንኛውም ዓይነት ህትመት ቅጂ በድርጅቱ የማኖር ግዴታ አለበት።
2. ውጪ ሀገር ተዘጋጅተዉ ኢትዮጵያ ውስጥ የተባዙ ሥራዎች አዘጋጅ ወይም አከፋፋይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የማክበር ግዴታ አለበት።
3. ማንኛውም አሳታሚ ወይም ደራሲ በሙሉም ሆነ በከፊል ኢትዮጵያ ውስጥ ተዘጋጅተው ውጪ ሀገር የታተሙ ህትሙሶችን 3 ቅጂ የማኖር ግዴታ አለበት።

## 20. <u>ህትመቶችን የማኖሪያ ጊዜና ሁኔታ</u>

ህትመቶችን የማኖር ግዴታ የተጣለበት ማንኛውም አታሚያ፣ አሳታሚ፣ ደራሲ፣ አባገር ወይም አከፋፋይ ህትመቶችን ህትመቱ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በአደራ ፖስታ ወይም በልዩ መልክተኛ ለድርጅቱ ቤተ መጻሕፍት ማስረከብ አለበት፡፡

## 21. <u>የዶክመንት ቅርሶችን ስለማስተላለፍና ባለቤትነትን ስለማዛወር</u>

1. ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም በይዞታው ስር የሚገኙ የዶክመንት ቅርሶችን በውርስ፡ በስጦታ፡ ወይም በሽያጭ መልክ ለሌላ ሰው ሲያስተላልፍ ለድርጅቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. የዶክመንት ቅርሶችን በዚህ ሕግ ከተደነገገው ውጪ ከሀገር ማስወጣት የተከለከለ ነው፡፡

# <u>ክፍል አምስት</u>

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## 22. <u>ደንብና መመሪያ ስለማዉጣት</u>

1. ሚኒስትሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያዎችን ያመጣል።
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ ደንብ ያወጣል፡፡

## 23. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት እንዲሁም ግለሰብ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 24. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

1. አዋጅ ቁጥር 50/1968 እና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 40/1968 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን የማንኛውም ሕግ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 25. ቅጣት

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከበድ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፡-

1. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 13(2) የጣሰ እንደሆነ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራትና እስከ 2,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይችላል፡፡
2. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 14(1) የጣሰ እንደሆነ ከአንድ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት እና ከ2,000 እስከ 20,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይችላል፡፡
3. ህገጠዋ በሆነ ሁኔታ መዛግብትን፣ መጻሕፍትንና የዶክመንት ቅርሶችን ከሀገር ያስወጣ እንደሆነ ከሦስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከ5,000 እስከ 20,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይችላል፡፡
4. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 18(1) የጣሰ እንደሆነ ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከ10,000 እስከ 20,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይችላል፡፡
5. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 19 የጣሰ እንደሆነ እስከ 2,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
6. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 22(1) የጣሰ እንደሆነ እስከ 2,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 26. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣ ሰኔ 24 ቀን 1991 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 378/2008

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የአገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 5፣ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 17(1) እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 179/1999 አንቀጽ 8(20) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የአገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 378/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ነው፤
   2. "ተገልጋይ" ማለት ድርጅቱ በሚሰጣቸው አልግሎቶች የሚጠቀም ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፤
   3. "የመረጃ ሀብቶች" ማለት ባላቸው የመረጃ ፋይዳ ምክንያት በኤጀንሲው ቋሚ ጥበቃ ሥር የሚገኙ የመዛግብት፣ መጻሕፍት፣ መጽሄቶች፣ ጋዜጦች፣ መቅረፀ-ድምጾች፣ መቅረፀ-ድምጽና ምስሎች፣ ጥንታዊ ጽሁፎች የታተሙ፣ በከፊል የታተሙ፣ ወይም ያልታተሙ ሥራዎች ወይም የሌሎች ሪከርዶች ክምችት ነው፤
   4. "የማይክሮ ፊልም ህትመት" ማለት በማይክሮ ፊልም ተቀርፀው የሚገኙ የመረጃ ሀብቶች የወረቀት ቅጂ ነው፤
   5. "ዲጂታል ቅጂ" ማለት በተገልጋዮች ከኤጀንሲው ድረ-ገፅ ላይ ሊወሰድ የሚችል ወይም ፍላሽ ዲስክን፣ ሲዲን ወይም ካሜራን በመሳሰሉ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ የመረጃ ተሸካሚ ቁሳቁሶች አማካኝነት ለተገልጋዮች የሚቀርብ ዲጂታይዝ ተደርጎ ወደ ኮምፒውተር የገባ መረጃ ቅጂ ነው፤

6. "ጥንታዊ ጽሁፎች" ማለት ባላቸው ልዩ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነ-ጽሁፋዊ ወይም ሥነ-ጥበባዊ ፋይዳ ምክንያት እንደ ቅርስ የሚታዩ መተኪያ የሌላቸው ጥንታዊ ሰነዶች ወይም መጽሐፍት ናቸው፤

7. "ሥልጠና" ማለት በቤተመጽሐፍት ወይም በሪከርድ ሥራ አመራር ዙሪያ በኤጀንሲው ባለሙያዎች ለሠልጣኞች የሚሰጥ ሥልጠና ነው፤

8. "ፈተና" ማለት በመንግሥት ወይም በግል ተቋማት ጥያቄ የላይብረሪ ሳይንስ ወይም የሪከርድ ማኔጅመንት ባለሙያዎችን ለቅጥር ለመመልመል ወይም ለሌላ ዓላማ በኤጀንሲው የሚሰጥ ፈተና ነው፤

9. "የማይክሮ ፊልም ፎቶግራፍ ቅጂ" ማለት ከማይክሮ ፊልም ላይ በፎቶ ካሜራ የሚወሰድ የመረጃ ሀብት ቅጂ ነው፤

10. "ዓለም አቀፍ የመጻሕፍት መለያ መደብ (አይኤስቢኤን)"ማለት ከዓለም አቀፍ የቤተመጻሕፍት ድርጅት የሚሰጥ የመጻሕፍት መለያ መደብ ማለት ነው፤

11. "የውሰት አገልግሎት" ማለት በኤጀንሲው ክምችት ውስጥ ያሉ መጻሕፍትን ወይም ዲቪዲዎችን ለተገልጋዩ ማዋስ ነው፤

12. "የመጽሐፍት ድጋፍ" ማለት ኤጀንሲው አብያተ መጻሕፍትንና ሌሎች የመረጃ ተቋማትን ለማጠናከር የሚያደርገው የመጽሐፍት ስጦታ ነው፤

13. "የዲቪዲ አገልግሎት" ማለት በኤጀንሲው ክምችት ውስጥ ያሉ ዲቪዲዎችን ለተገልጋዩ ማሳየት ነው፤

14. "የመረጃ ሀብቶች የፎቶግራፍ ቅጂ" ማለት በኤጀንሲው ክምችት ውስጥ ያሉ በፎቶ ካሜራ የተቀረጹ የመረጃ ሀብቶች ቅጂ ነው።

3. <u>የኤጀንሲው አገልግሎት ዋጋ</u>

ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 179/1999 አንቀጽ 8(20) መሠረት የሚያስከፍለው ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

4. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ፣ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## <u>የአገልግሎት ዋጋ ተመን ሠንጠረዥ</u>

| ተ.ቁ | አገልግሎት | ብዛት/ዓይነት | የአገልግሎት ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ብር | ሳንቲም |
| 1 | የመጽሐፍ ድጋፍ | በአንድ መጽሐፍ | 1 | 00 |
| 2 | ፎቶ ኮፒ | አንድ ገጽ ለኢትዮጵያዊ | 1 | 00 |
| | | አንድ ገጽ ለውጭ ሀገር ዜጋ | 2 | 00 |
| 3 | የፎቶግራፍ የመረጃ ሀብቶች ቅጂ | አንድ ፎቶግራፍ | 10 | 00 |
| 4 | ከኮምፒውተር ላይ ሕትመት | አንድ ገጽ ለኢትዮጵያዊ | 2 | 00 |
| | | አንድ ገጽ ለውጭ ሀገር ዜጋ | 4 | 00 |
| 5 | ከማይክሮ ፊልም ስብስብ ላይ ቅጅ | አንድ ገጽ | 4 | 00 |
| 6 | ከማይክሮ ፊልም ስብስብ ላይ በካሜራ ቅጅ | አንድ ገጽ | 4 | 00 |
| 7 | በዲጂታል መልክ ከሚገኙ ጥንታዊ መጻሕፍት ቅጂ በራስ ሲዲ | በአንድ ገጽ | 1 | 50 |
| 8 | በዲጂታል መልክ ከሚገኙ መዛግብት/ማኑስክሪፕት ቅጂ በራስ ሲዲ | በአንድ ገጽ | 1 | 50 |
| 9 | በዲጂታል መልክ ከሚገኙ መዛግብት ቅጂ በዲጂታል/በቪዲዮ ካሜራ | አንድ ገጽ ለኢትዮጵያዊ | 1 | 00 |
| | | አንድ ገጽ ለውጭ ሀገር ዜጋ | 2 | 00 |
| 10 | የዲቪዲ ፊልም አገልግሎት | አንድ ሙሉ ዲቪዲ | 3 | 00 |
| 11 | የኢንተርኔት አገልግሎት | አንድ ሰዓት | 3 | 00 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 12 | አለም አቀፍ የመጻሕፍት መለያ መደብ(አይ.ኤስ.ቢ.ኤን)መመዝገቢያ | አንድ ጊዜ መመዝገቢያ | 20 | 00 |
| 13 | የውሰት አገልግሎት (መጻህፍት) | ለተቋማት የዓመት አባልነት | 1500 | 00 |
| | | በስራ አመራር ላይ የተዘጋጁ መፃሕፍት የዓመት ክፍያ | 250 | 00 |
| | | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መፃሕፍት የዓመት ክፍያ | 100 | 00 |
| | | አይ.ቲእና የትምህርት መፃህፍት የአመት ክፍያ | 70 | 00 |
| 14 | የፊልም የውሰት አገልግሎ(ዲቨ.ዲ) | የአመት አባልነት ክፍያ | 300 | 00 |
| 15 | ዓለም አቀፍ የመፃህፍት መለያ መደብ (አይ.ኤስ.ቢ ኤን) ቁጥር አገልግሎት | ለአንድ እርእስ | 150 | 00 |
| | | ለ10 እርእስ | 1000 | 00 |
| | | ለ100 እርእስ | 6000 | 00 |
| | | ለ1000 እርእስ | 20,000 | 00 |
| 16 | በጥያቄ የሚሰጥ ስልጠና (በኤጀንሲው አዳራሽ) | ለ20 ቀናት በአንድ ሰው | 800 | 00 |
| | | ለ10 ቀናት በአንድ ሰው | 400 | 00 |
| 17 | በጥያቄ የሚሰጥ ስልጠና (በጠያቂው ተቋም አዳራሽ ከአዲስ አበባ ውጭ) | ለ20 ቀናት በአንድ ሰው | 115 | 00 |
| | | ለ10 ቀናት በአንድ ሰው | 60 | 00 |
| | በጥያቄ የሚሰጥ ስልጠና (በጠያቂው ተቋም አዳራሽ በአዲስ አበባ ውስጥ) | ለ20 ቀናት በአንድ ሰው | 80 | 00 |
| | | ለ10 ቀናት በአንድ ሰው | 40 | 00 |
| 18 | ፈተና ማዘጋጀትና መፈተን | ለመንግስት ተቋም በአንድ ሰው | 500 | 00 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መንግስታዊ ላልሆነ ተቋም በአንድ ሰው | 1000 | 00 |

## <u>አዋጅ ቁጥር 209/1992</u>

## <u>ስለ ቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣ አዋጅ</u>

ቅርስ የአንድ ሕዝብ የዘመናት የኑሮ እንቅስቃሴ፣ የሥራ እና የፈጠራ ክንዉን መዘክር ስለሆነ፤

ስለሰዉ፣ ስለሌላዉ ምድራዊ ሕይወት ዝርያ አመጣጥ፣ እንዲሁም ስለተጓዘበት የለውጥና የእድገት ሂደት በማጤን ተፈጥሮንና አካባቢን ይበልጥ ለመረዳት ለሚደረግ ጥናትና ምርምር ቅርሶች ምትክ የሌላቸው የመረጃ ምንጮች ስለሆኑ፤

ቅርስ ለሳይንስ እድገትና እንዲሁም በጠቅላላ የሰውን ዘር በሚመለከት እዉቀት ላይ ያለው ድርሻ የጎላና ዓለም አቀፋዊ ስለሆነ፤

ኢትዮጵያ የየራሳቸው ታሪክና ባህል ያላቸው ብዙ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የሚገኙባት፤ ሕዝቦቿም ባሳለፉት የረጅም ዘመን ታሪክ በዓለም የባህል ቅርስነት የተመዘገቡትን ጨምሮ የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ለመሆን የቻሉ ስለሆኑ፤

ተተኪው ትዉልድ ስለ ማንነቱ መገለጫ ለሆነው ታሪኩና ባህሉ ጥልቅና ሰፊ ግንዛቤ ይበልጥ እንዲኖር ቅርስ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት ቅርስን መንከባከብና መጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ፣ የኅብረተሰቡና የመንግስት ግዴታ በመሆኑ፤

ለቅርስ የሚያስፈልገዉ እንክብካቤና ጥበቃ የሚሟላበትን መንገድ መቀየስ እና በነዚሁ ላይ በማንኛዉም ደረጃ የሚደረግ የጥናትና የምርምር ሥራ ሥርዓት በያዘና የሀገሪቷንና የዜጎቿን መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልክ እንዲከናወን ማድረግ ስለሚገባ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

   ይህ አዋጅ "ስለ ቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 209/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**መቋቋም**</u>

   1. የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን (በዚህ በኋላ "ባለሥልጣኑ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለማስታወቂያና ባህል ሚኒስትር[14] ይሆናል፡፡

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ሚኒስትር” ማለት የማስታወቂያና ባህል ሚኒስትር ነዉ፡፡[15]
2. “ባለሥልጣን” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 የተቋቋመው የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፡፡
3. “መማክርት ጉባኤ” ማለት በዚ.ህ አዋጅ አንቀጽ 8 የተመለከተው የቅርስ መማክርት ጉባኤ ነው፡፡
4. “ቅርስ” ማለት በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የሥራ እንቅስቃሴ ዉጤት የሆነ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልጽና የሚመሰክር በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በሥነጥበብና በዕደጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያለው ማንቸዉም ግዙፍነት ያለውና ግዙፍነት የሌለው ነገር ነው፡፡
5. “ግዙፍነት የሌለዉ ቅርስ” ማለት በእጅ ለመዳሰስ የሚያዳግት ነገር ግን በዓይን ለማየት፣ በጆሮ ለመስማት የሚችል ቅርስ ሲሆን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ልዩ ልዩ ትርዒትና ጨዋታ፣ ሥነቃል፣ የሃይማኖት፣ የእምነት፣ የጋብቻ፣ የሐዘን ሥነ ሥርዓት ሙዚቃ፣ ድራማና ሌሎች ተመሳሳይ ባህላዊ ዕሴቶች፣ ወግና ልማድን ይጨምራል፡፡
6. “ግዙፍነት ያለዉ ቅርስ” ማለት በእጅ የሚዳሰሱ፣ በዓይን የሚታዩ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ባህላዊና ታሪካዊ ወይም ሰዉ ሰራሽ ቅርሶችን ይጨምራል፡፡
7. “የማይንቀሳቀስ ቅርስ” ማለት ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ የማይቻሉ፣ በመሠረት ተገንብተው ቋሚ ከሆኑ ነገሮች ጋር የተያያዙና ከቦታ ወደ ቦታ ለማዛወር የሚቻለውም በማፍረስ ብቻ ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

    ሀ/ መካነ ቅርሶች የተገኙባቸዉ ቦታዎች፣ የፖሊዬንቶሎጂ ታሪክ፣ የቅድመ ታሪክና የአርኪዎሎጂ ሥፍራዎች፣

    ለ/ ሀንፃ፣ የመታሰቢያ ቦታ፣ ሐዉልት፣ ቤተመንግስት፣

    ሐ/ የጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ፣ ጥንታዊ የመቃብር ቦታ፣ የዋሻ ሥዕሎችና ጽሑፎች

    መ/ ቤተክርስቲያን፣ ገዳም፣ መስጊድ ወይም ማንኛዉም የማምለኪያ ሥፍራ፣

[14] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9 (23) መሠረት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኗል፡፡
[15] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9 (23) መሠረት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

8. "የሚንቀሳቀስ ቅርስ" ማለት ከቋሚ ነገሮች ጋር በመሠረት ያልተገነቡና ከቦታ ወደ ቦታ ያለምንም ችግር በቀላሉ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ከትውልድ ተላልፈው የደረሱን ቅርሶች ሲሆኑ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ/ የብራና ጽሁፍ፣ የድንጋይ ላይ ጽሁፎችና ሥዕሎች የድንጋይ መሳሪያዎች፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ ወይም ከብረት ወይም ከመዳብ ከሌሎች ንጥረ ነገሮች ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከቆዳ፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከቀንድ፣ ከአጥንትና ከአፈር ወይም ከሌሎች ነገሮች የተሰሩ ቅርጾችና ምስሎች እንዲሁም የአርኪዎሎጂና የፖሊዮንቶሎጂ ቅሪቶች፣

ለ/ ጽሁፍና የግራፊክ ዶክመንት ወይም የሲኒማቶግራፊና የፎቶግራፍ ዶክመንት፣ የድምጽ ወይም የቪዲዮ ቅጅ ዶክመንት፤

ሐ/ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሐስ፣ ከመዳብ ወይም ከሌሎች ነገሮች የተሰራ ገንዘብ፣

መ/ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መገልገያ ጌጥ ወይም ባህላዊ ዕቃ፤

9. "የቅርስ ምዝገባ" ማለት ቅርስን ለመለየት፣ ለመቆጣጠር፣ ለማጥናት ለመንከባከብና ለመጠገን፣ ለትምህርትና ለመዝናኛነት አገልግሎት የሚውሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ስለ ቅርሱ ሰፊ መረጃ ለማሰባሰብ በተዘጋጀ ቅጽ መመዝገብና እንደ አመቺነቱ በፊልምና በቪዲዮ መቅረጽንም ይጨምራል፡፡

10. "ጥገና" ማለት ጥንታዊ ይዘቱ ሳይለወጥ ለቅርሶች የሚደረግ አጠቃላይ እንክብካቤና ጥበቃ ነው፡፡

11. "ቁፋሮ" ማለት ማንኛውም ከምድር በታች የሚገኝን ቅርስ ለማውጣትና ለማጥናት በሰው ሀይል ወይም በመሳሪያ መቆፈር ነው፡፡

12. "ሙዝዬም" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ያልሆነ ቅርሶችን የሚሰበስብ የሚጠብቅና የሚጠግን፣ ለምርምር ለጥናት፣ ለማስተማሪያና ለመዝናኛነት ስብስቦችን በሚገባ አዘጋጅቶ ለኀብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነዉ፡፡

13. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠዉ አካል ነው፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ቅርሶች በታሪክ ምስክርነታቸዉ ከትውልድ ወደ ትዉልድ እንዲተላለፉ ሳይንሳዊ ምዝገባና ቁጥጥር ማከናወን፤
2. ቅርሶችን ከሰው ሰራሽና ከተፈጥሮ አደጋዎች መከላከል፤

3. ከቅርሶች የሚገኙ ጥቅሞች ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማቶች እገዛ እንዲያደርጉ ማስቻል፤ እና
4. ቅርሶችን ማግኘትና ማጥናት፡፡

5. ***ዋና መሥሪያ ቤት***

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በማናቸውም ቦታ ለማቋቋም ይችላል።

6. ***የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር***

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር ቅርሶችን ይመዘግባል፤
2. ቅርሶችን ይንከባከባል ያቆጣጠራል፣ እንዲሁም ስለቅርሶች መረጃ ይሰበስባል፤ ቅርስ መሆን ያለመሆኑን ይለያል፣ ደረጃም ያወጣል፤
3. ስለቅርስ ምንነት፣ ጥቅምና አጠባበቅ አስፈላጊውን ትምህርትና ምክር ይሰጣል፤
4. ቅርሶችን በሙዝዬም በማሰባሰብ ለጎብኝዎችና ለተመራማሪዎች ያቀርባል፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት እንዲታይ ያደርጋል፤
5. በቅርሶች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ እንዲካሄድም ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤
6. ሙዝዬም ለሚያቋቁም ሰው የሙያና የብቃት እንዲሁም የቅርስ ምዝገባ የምሥክር ወረቀት ይሰጣል፤
7. ለቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራዎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤
8. ቅርሶች ከአገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤ በልዩ ልዩ ሕገ ወጥ በሆኑ መንገዶች ተወስደዉ በውጭ ሀገር የሚገኙ ቅርሶች ወደ ሀገር የሚመለሱበትን መንገድ ያመቻቻል፤
9. በስጦታ ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ዕቃዎች ቅርስ አለመሆናቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለጥናትና ለምርምር ወደ ውጭ ለሚላኩ የአርኪዎሎጂ ናሙናዎች፣ ካስቶች ፈቃድ ይሰጣል፤ ለንግድ አላማም እንዳይውሉ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፤
10. በየክልል መስተዳድሮች ለሚካሄዱ የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም ጥናትና ምርምር ሥራዎች የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

11.ባለሥልጣኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም ባለሙያዎች በየመስኩ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤

12.ቅርሶችን በተመለከተ አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ያደርጋል፤

13.በዓለም አቀፍ፣ በአገርና በክልል ደረጃ ኢትዮጵያን በተመለከት የሚቀርቡ ቅርስ ነክ የሆኑ ኤግዚቢሽኖችን ደረጃ ያወጣል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤

14.በታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ስያሜና ምስል የሚወጡ የንግድና ሌላም ምልክቶች የቅርስን ታሪካዊ እሴት የማይጎዱ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤

15.ለሚሰጠው ፈቃድና አገልግሎት ያስከፍላል፤

16.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

17.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተግባሮችን ያከናዉናል፡፡

7. <u>**የባለሥልጣኑ አቋም**</u>

ባለሥልጣኑ፡-

1. የመማክርት ጉባኤ፣
2. ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ እና
3. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

8. <u>**የመማክርት ጉባኤ**</u>

1. ባለሥልጣኑ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየሙ 13 አባላት የሚገኙበት የመማክርት ጉባኤ ይኖረዋል፡፡
2. የመማክርት ጉባኤ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል።

9. <u>**የመማክርት ጉባኤው ሥልጣንና ተግባራት**</u>

የመማክርት ጉባኤዉ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር የሚሻሻልበትን ሁኔታ አጥንቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤
2. ባለሥልጣኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤
3. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ የሥራ ክንውን በየጊዜው ይገመግማል፡
4. በባለሥልጣኑ የሚከናወኑትን የቅርስ ጥበቃ ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ይመረምራል፤ ምክርም ይሰጣል፡፡

10. <u>የመማክርት ጉባኤው ስብሰባዎች</u>

1. ጉባኤው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም በሰብሳቢው ወይም በአንድ ሶስተኛ አባላት ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. በስብሰባው ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
3. የጉባኤው ውሳኔ በአብዛኛው ድምፅ ይወሰናል፤ ድምፁ ለሁለት በዕኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤
4. ጉኤዉ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡

11. <u>ስለ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋነው ሥራ አስኪያጅ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት ይሾማል።
2. ዋናው ሥራ አስኪያጅ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ባለሥልጣኑን ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስኪያጁ፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ለባለሥልጣኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራም እንዲሁም ዓመታዊ ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

   ሐ/ በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   መ/ የባለሥልጣኑን የሥራ መግለጫና አጠቃላይ የሥራ ሪፖርት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡

   ሠ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደ በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፡፡

   ረ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤
4. ዋናዉ ሥራ አስኪያጅ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገዉ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

12. <u>የባለሥልጣኑ በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል።

ሀ/ በመንግስት የሚመደብለት በጀት፤

ለ/ ከአገልግሎትና ከፈቃድ ከሚሰበሰብ ገቢ፤ እና

ሐ/ ከሌሎች ምንጮች።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ይይዛል።
2. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብት ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረምራል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለቅርስ አስተዳደር</u>

14. <u>ስለቅርስ ባለቤትነት</u>

1. ቅርሶች በመንግሥት ወይም በማናቸውም ሰው ባለቤትነት ሊያዙ ይችላሉ፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት ድንጋጌ መሰረት የተገኙ ቅርሶች በባለቤትነት ሊያዝ የሚችሉት በመንግሥት ብቻ ነው።

15. <u>ሙዚዬም ስለማቋቋም</u>

የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከባለሥልጣኑ ያገኘ ማንኛውም ሰው ሙዚየም ሊያቋቁም ይችላል፤ አፈፃፀሙም በሚወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

16. <u>ቅርሶችን በደረጃ ስለመመደብ</u>

ቅርሶችን በብሔራዊና በክልል ደረጃ መመደብ በሕግ ይወሰናል፡፡

17. <u>ስለቅርሶች ምዝገባ</u>

1. ማንኛውም ሰው በባለቤትነት የያዘውን ቅርስ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ ለአያያዛቸውና ለአጠባበቃቸው የሚያመች መለያ በመስጠት ቅርሶችን ይመዘግባል፡፡
3. ማንኛውም ሰው ላስመዘገበው ቅርስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
4. በዚህ አዋጅ መሰረት ለቅርሶች ምዝገባ የሚደረገውን ማናቸውንም ወጭ ባለሥልጣኑ ይሸፍናል፡፡

18. <u>የቅርስ ባለይዞታ የሆነው ሰው ግዴታዎች</u>

ማናቸውንም ቅርስ በባለቤትነት የያዘ ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡

1. በራሱ ወጭ ለቅርሱ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ፤

2. ቅርሱን ለኤግዚቢሽን ወይም በሌላ ሁኔታ ለሕዝብ እንዲታይ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ መፍቀድ፤

3. ስለቅርሱ አያያዝና አጠቃቀም የሚመለከቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማክበር አለበት፡፡

## 19. ስለቅርስ ጥገናና እንክብካቤ

1. ማናቸውንም የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ሥራ ለማከናወን በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

2. ጥገናና እንክብካቤዉ ከባለቤቱ አቅም በላይ የሆነ ወጭ የሚያስከትል ሲሆን ወጭውን በከፊል ለመሸፈን መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 20. በይዞታ ለመጠቀም በተሰጠ መሬት ላይ ስለሚገኝ ቅርስ ጥበቃ

ማንኛውም ሰው በይዞታ እንዲጠቀምበት በተሰጠው መሬት ላይ የሚገኝ ቅርስ በሚገባ መጠበቁን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 21. ቅርሶችን ስለማንቀሳቀስ

1. ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር የማይንቀሳቀስ ቅርስን መጀመሪያ ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ አይቻልም።

2. የተመዘገበ የሚንቀሳቀስ ቅርስን መጀመሪያ ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማንቀሳቀስ በቅድሚያ ባለሥልጣኑን ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

## 22. የቅርሶች አጠቃቀም

1. ቅርሶች ለሣይንስ፣ ለትምህርት፣ ለባህልና ለሥነ ጥበብ ዕድገት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ተግበሮች ጥቅም ላይ ይዉላሉ፡፡

2. ቅርሶችን ለኢኮኖሚያዊና ለሌሎች ተግባሮች መጠቀም የሚቻለው አጠቃቀሙ ለአጠባበቃቸው እንቅፋት የማይፈጥር ሲሆንና ታሪካዊ፣ ሣይንሳዊ፣ ባህላዊና ሥነ ጥበባዊ ዋጋቸውን የማይቀንስ ሲሆን ብቻ ነው።

3. ቅርሶች በጥቅም ላይ የሚውሉት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣዉ መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

## 23. የቅርሶችን ባለቤትነት ስለማስተላለፍ

1. ማንኛውም ሰው የያዘውን ቅርስ በማናቸውም ሁኔታ ለሌላ ሰው ሲያስተላልፍ ሁለቱም ወገኖች በቅድሚያ ባለሥልጣኑን በጽሑፍ ማሳወቅ አለባቸው።

2. ባለሥልጣኑ ለሽያጭ የቀረቡ ቅርሶችን የመግዛት ቅድሚያ መብት ይኖረዋል።

24. <u>በቅርሶች ስለመነገድ</u>

1. ማንኛውም ሰው ቅርሶችን ለንግድ ዓላማ መግዛትና መሸጥ አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው ቅርሶችን ለንግድ ሥራ በፊልም ወይም በማናቸውም ሁኔታ መቅረጽ ወይም መቅዳት የሚችለው በሚወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት ነው፡፡

25. <u>ቅርሶችን ስለመውረስ</u>

ማንኛውም ቅርስ፡-

1. በዚህ አዋጅና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተገቢው ጥበቃ፣ ጥገናና ዕድሳት ያልተደረገለት ወይም ለብልሽት የተጋለጠ፣ ወይም በአንቀጽ 22(3) ከተመለከተው ውጭ ጥቅም ላይ በማዋል ለጥፋት ወይም ለብልሽት የተጋለጠ፤ ወይም
2. በቤተ መዘክር የመጠበቁ አስፈላጊነትና የተገቢው ካሣ ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲወሰን፤ ወይም
3. ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ወደ ውጭ አገር ሊወጣ ሲል የተያዘን ቅርስ ባለሥልጣኑ ሊወርስ ይችላል፡፡

26. <u>በሌላ አገር ስለሚገኝ ቅርስ</u>

1. በሕገ ወጥ መንገድ በሌላ አገር የሚገኝ ቅርስ ወደ አገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡
2. በተለያየ ሁኔታ ውጭ አገር የሚገኝ ቅርስ መረጃ ይሰበሰባል፤ ሕዝብም እንዲያውቀው ይደረጋል።

27. <u>ቅርስን ከሀገር ስለማውጣት</u>

ቅርስን ከሀገር ማስወጣት አይቻልም፤ ሆኖም ሚኒስትሩ ሲፈቅድ ለሣይንሳዊ ጥናት፣ ለባሕል ልውውጥ ወይም ለኤግዚቪሽን ቅርስን በጊዜያዊነት ከሀገር ለማውጣት ይቻላል፡፡

28. <u>ወደ ሀገር ስለገባ የሌላ ሀገር ቅርስ</u>

ለባሕል ልዉዉዉጥ ወይም ለኤግዚቢሽን ወይም በሌላ ምክንያት በጊዚያዊነት ሀገር ውስጥ የገባ የሌላ ሀገር ቅርስ እንደአስፈላጊነቱ መንግሥታዊ ጥበቃ ይደረግለታል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለቅርሶች ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት</u>

29. <u>ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት</u>

የቅርስ ፍለጋ ግኝትና ጥናት የሚደረገው በፖሊዮንቶሎጂ፣ በአርኪዮዎሎጂ፣ በአንትሮፖሎጂና በተዛማጅ የጥናት መስኮች ላይ ነዉ፡፡

30. ፈቃድ ስለማስፈለጉ

1. ማንኛውም ሰው አስቀድሞ ከባለሥልጣኑ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ለማካሄድ አይችልም።
2. ባለሥልጣኑ የቅርስ ፍለጋ ግኝትና ጥናት ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚጠይቀው የሙያ ብቃትና አስፈላጊዉ የገንዘብ አቅም ያለዉ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

31. ስለ ማመልከቻ ይዘት

የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ለማካሄድ ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ይዘት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

32. ስለ ፈቃዱ ይዘት

የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ለማካሄድ የሚሰጥ ፈቃድ የሚይዛቸዉ ዝርዝሮች ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣዉ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

33. ፈቃዱ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1. የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ የሚሰጠዉ ከሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል፡፡
2. የፍለጋ ግኝትና ጥናት ሥራዉ ከመጠናቀቁ በፊት የፈቃድ ጊዜዉ ካለቀ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያድስ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተሰጡት ጊዜያቶች በላይ ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገ በአዲስ መልክ ማመልከቻ ቀርቦ እንደአስፈላጊነቱ በባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

34. የፈቃድ ማዉጫና ማሳደሻ ክፍያ

የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ ለማዉጣትና ለማሳደስ የሚደረገዉ ክፍያ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣዉ ደንብ ይወሰናል።

35. ፈቃድ የተሰጠው ሰዉ ግዴታዎች

የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ የተሰጠው ሰዉ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. ስለ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ስለ ሥራዉ አካሄድ በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ዘገባና ሪፖርት የማቅረብ፤
2. ስለ እያንዳንዱ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት የተሟላ መግለጫ የያዘ ልዩ መዝገብ የመያዝ፤
3. ማንኛዉም ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት በሚገባ ጠብቆ ለባለሥልጣኑ የማስረከብ፤ ለጥናትና ምርምር በሚያመች መንገድ የማስቀመጥ፤
4. ከባለሥልጣኑ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት በምሥጢር የመጠበቅ፤
5. እንዲያጠና ወይም እንዲፈልግ ከተፈቀደለት የጥናት ዓይነትና የጥናት ቦታ ዉጭ ያለማከናወን፤
6. ጥናቱ የሚካሄድበትን አካባቢ ሕዝቦች ባህል፣ እምነትና ሥነ ልቦና በማይጎዳ መልክ የማጥናት፤
7. የፍለጋ ሥፍራዉ ከተጠናቀቀ በኃላ ፍለጋዉ የተካሄደበትን ቦታ ቀድሞ እንደነበር የማድረግ፣
8. በቅርሶች ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ሥራ ኢትዮጵያዉያንን የማሳተፍና የማሰልጠን፣
9. የጥናቱ ተሳታፊ ለሆኑ ኢትዮጵያዉያን የመድን ዋስትና መግባት፤
10. የሙያዉ ዲስፕሊን የሚጠይቃቸዉን ግዴታዎች የማክበር፤ እና
11. ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ደንብና መመሪያ የማክበርና የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

## 36. <u>ፈቃድን ስለማገድና ስለመሠረዝ</u>

1. የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 35 ከጣሰ ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ፈቃዱን ሊያግድበት ይችላል፡፡
2. የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች ካላከበረ ወይም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ በማንኛዉም ጊዜ ፈቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል።
3. የቅርስ ፍለጋ ጥናት ግኝትና ፈቃድ የተሰረዘበት ሰው ቅሬታዉን ዉሳኔ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ሊያቀርብ ይችላል፤ የሚኒስትሩ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 37. <u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

1. ባለሥልጣኑ የቅርስ ፍለጋዉን ፕሮጀክት በሚመለከቱ ጉዳዮች የሚወክለዉ ኃላፊ ይመድባል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረተ የተመደበ ኃላፊ የቅርስ ፍለጋዉ፣ ግኝቱና ጥናቱ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሰረት መከናወኑን ይቆጣጠራል፡፡

38. <u>ግኝትን ስለማሳወቅ</u>

ማንኛዉም ከመስክ የተገኘ ግኝት በቅድሚያ በአገር ዉስጥ መገናኛ ብዙሃን በባለሥልጣኑ አመካይነት መገለፅ አለበት፡፡

39. <u>ዘገባዎችንና የጥናት ዉጤቶችን ስለማሳተም</u>

1. የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት የመስክ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለዉ የአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፍለጋውን ዘገባዎችና የጥናቱን ለማሳተም ፈቃድ የተሰጠው ሰዉ ብቸኛ ባለመብት ይሆናል፤ ሆኖም እነዚህኑ ከማሳተሙ አስቀድሞ ባለሥልጣኑን ያሳዉቃል፡፡
2. የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከእያንዳንዱ እትም አምስት ቅጂ ለባለሥልጣኑ ይሰጣል፡፡
3. የቅርስ ፍለጋ፣ ግኝትና ጥናት ፈቃድ የተሰጠው ሰዉ የፍለጋዉን ዘገባዎችና የጥናት ዉጤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ካላሳተመ ባለሥልጣኑ እነዚህኑ በሙሉ ወይም በከፊል ራሱ ለማሳተም ወይም ሌላ ሰው እንዲያሳትማቸዉ ለመፍቀድ ይችላል፡፡

40. <u>በጥናቱ ዉጤቶች ላይ ስለሚኖር ባለሀብትነት</u>

የዚህ አዋጅ አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅርስ ፍለጋ ግኝትና ጥናት ፈቃደ የተሰጠው ሰው ያካሄደዉ ጥናት ዉጤት የሆነ ማንኛዉንም ጽሑፍ በሚመለከት የባለሀብትነት መብቱ በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት የተጠበቀ ነዉ፡፡

41. <u>በአጋጣሚ ስለተገኙ ቅርሶች</u>

1. ማንኛዉም ሰዉ የማዕድን ሥራ፣ ህንፃ፣ የመንገድ፣ ወይም ተመሳሳይ ሥራ ለማካሄድ ባደረገዉ ቁፋሮ ወይም በማናቸዉም አጋጣሚ ሁኔታ ቅርሶችን ሲያገኝ ወዲያዉኑ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግና ባለሥልጣኑ ቅርሶቹን እስኪረከባቸዉ ድረስ በተገኙበት ሁኔታ እንዲቆዩ ተገቢዉን ጥበቃ ማድረግ አለበት፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ሪፖርት እንደደረሰዉ የተገኘዉን ቅርስ ለመመርመር፣ ለመረከብና ለመመዝገብ ተገቢዉን እርምጃ መዉሰድ አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት እርምጃ ካልወሰደ ቅርሱን ያገኘዉ ሰዉ በክልሉ ለሚገኝ የመንግስት ባለሥልጣን ዝርዝር ሁኔታዎችን በፅሁፍ በማሳወቅ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን ይችላል፡፡

4. ባለሥልጣኑ በአጋጣሚ የተገኘን ቅርስ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት ላስረከበ ሰዉ ተገቢዉ ሽልማት እንዲሰጠዉ ያደርጋል፣ እንዲሁም ቅርሱን ያገኘዉ ሰዉ በዚህ አንቀፅ መሰረት ግዴታዉን ለመወጣት ያወጣዉ ወጪ ካለ ባለሥልጣኑ ይተካል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

42. **ስለተከለለ ሥፍራ**

1. በሚኒስትሩ አሳሳቢነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ክምችት ያለበትን ቦታ ከመሬት በታች ተቀብረዉ የሚገኙ ቅርሶችን ክምችት አለበት ተብሎ የተገመተን አካባቢ በተከለለ ሥፍራነት መሰየምና በነጋሪት ጋዜጣ ማሳወቅ ይችላል፡፡

2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት በተለይ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር፣ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት በተከለለ ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የሕንፃ፣ የመንገድ ወይም ማንኛዉንም ዓይነት የቁፋሮ ሥራ የመሬት ንቅናቄ ሊያስከትል የሚችል ማንኛዉም ተግባር ማከናወን አይችልም፡፡

3. ማንኛዉም ሰዉ የተከለለ ሥፍራ አስፈቅዶ ማንኛዉም ዓይነት የግንባታ ሥራ ሲያከናዉን ቅርስ ካገኘ ሥራዉን አቁሞ ሁኔታዉን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

43. **ስለ ቁጥጥር**

1. ከባለሥልጣኑ ሥልጣን የተሰጠዉ ተቆጣጣሪ ሚኒስተሩ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ማንቸዉም ቅርስ በሚገኝበት ቦታ በተገቢዉ ሰዓት ለመግባትና ቅርሱ ተገቢዉን እያያዝና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ለመቆጣጠር ይችላል፡፡

2. ማናቸውም የቅርስ ባለቤት፣ ተገቢውን የመታወቂያ ወረቀት የያዘ የባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀፅ (1) መሠረት ቅርሱ ወደሚገኝበት ቦታ ለመግባትና ለመቆጣጠር እንዲችል የመተባባር ግዴታ አለበት፡፡

44. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰዉ ይህን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን በማስፈፀም ረገድ የመተባባር ግዴታ አለበት፡፡

45. <u>ቅጣት</u>

1. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከበድ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፡-
   ሀ/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 18፣ 20፣ 23(1)፣ ወይም 44(2) ድንጋጌ የተላለፈ እንደሆነ እስከ 6 ወር በሚደርስ እሥራት ወይም እስከ ብር 1500 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
   ለ/ የዚህን አዋጀ አንቀጽ 19(1)፣ 21፣ 22(2) ወይም 35 ድንጋጌ የተላለፈ እንደሆነ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም እስከ ብር 3,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
   ሐ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 24፣ አንቀጽ 27 ወይም አንቀጽ 30(1)፡ 42(1) ወይም 43(2) ድንጋጌ የተላለፈ እንደሆነ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ወይም ከብር አሥር ሺ እስከ ብር አሥራ አምስት ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
2. በወንጀለኛ መቅጫ ህግ[16] ከበድ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛዉም ሰው፡
   ሀ/ በቅርስ ላይ የስርቆት ወንጀል ከፈፀመ ከሰባት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
   ለ/ ሆነ ብሎ በቅርስ ላይ የማፍረስ ወይም ጉዳት የማድረስ ወንጀል ከፈፀመ ከአስር ዓመት በማያንስ ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡
   ሐ/ በሥራ ኃላፊነታቸዉ አጋጣሚ ያገኘውን ቅርስ የሚሰርቅ ወይም የሚያሰርቅ ወይም ጉዳት እንዲደርስ የሚያደርግ ከአስራ አምስት ዓመት በማያንስ ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

[16] የ1996ቱ የወንጀል ህግ የ1949ኙን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የተካ በመሆኑ የወንጀል ህግ በሚል ይነበባል፡፡

46. <u>ደንብና መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ የማዉጣት ሥልጣን አለው፡፡
2. ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

47. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1. የቅርሶች ጥናትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 36/1982 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ማንኛውም ሕግ ወይም የተለምዶ አሠራር ሁሉ ይህን አዋጅ የሚቃረን ከሆነ ይህን አዋጅ በሚመለከት ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

48. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 20 ቀን 1992 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ሰኔ 20 ቀን 1992 ዓ/ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 839/2006

## ቅርሶችን በብሔራዊ እና በክልል ቅርስነት መመደቢያ አዋጅ

ቅርስ የሰው ልጅ የዕድገት ሂደት፣ ባህልና ታሪክ መገለጫ ስለሆነ ለዘላቂነቱ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያደርግለትን አካል በህግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኅብረተሰቡን አሳታፊ ያደረገ የቅርስ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ቅርሶች ላሉበት አካባቢ ኅብረተሰብ ብሎም ለሀገር አቀፍ ዘላቂ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሀገሪቱን ቅርሶች በዓለም ቅርስ መዝገብ ዝርዝር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችሉ የዝግጅት ሥራዎችን ለማከናወን በቅድሚያ ቅርሶችን በደረጃ በማስፈለጉ፤

የቅርሶች አስተዳደርን በሚመለከት የሥራ መደራረብና የሃብት ብክነት እንዳይፈጠር በፌደራልና በክልሎች መካከል የሚኖረውን የኃላፊነት ድርሻ መለየት እና ቀልጣፋ የአስተዳደርና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 16 ላይም ቅርሶች በብሔራዊና በክልል ደረጃ የሚመደቡበት አግባብ የተደነገገ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "ቅርሶችን በብሔራዊ እና በክልል ቅርስነት መመደቢያ አዋጅ ቁጥር 839/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡

   1. "ቅርስ" ማለት በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የሥራ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚገልጽና የሚመሰክር በሳይንስ፣ በታሪክ፣ በባህሪ፣ በሥነጥበብና በዕደ ጥበብ ይዘቱ ከፍተኛ ተፈላጊነትና ዋጋ ያለው ማናቸውም ግዙፍነት ያለውና የሌለው ነገር ነው።

2. "አፋዊ ትውፊት" ማለት ከሰዉ ወደሰው እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፊያ መንገዱ አፋዊ ክዋኔ የሆነና የፈጠረውን ማኅበረሰብ ባህል፣ ታሪክ፣ ለዓለም ያለ አተያይ፣ የሕይወት ፍልስፍና እና ማንነት የሚገልጽ እንደ ትረካ፣ ድርደራ ወይም ዘፈን የመሰለ ትውፊታዊ ዕውቀት ነው፤

3. "ትጢን ጥበብ" ማለት ባህላዊ አጋጣሚዎችን ምክንያት በማድረግ የሚከወን ባህላዊ ጭፈራ፣ ድራማ ወይም ዘፈን ነው፤

4. "የማኅበራዊ ክንዋኔ ሥነ-ሥርዓት ወይም ፌስቲቫል" ማለት ትውፊታዊ ሥነ-ሥርዓቶችን፣ ፌስቲቫሎችን ወይም የዐውደ ዓመት በዓላትን ምክንያት በማድረግ የሰው ልጅ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ፍላጐቱን ለማሟላት እንደየሁኔታው በግል ወይም በጋራ የሚያከናውነውና የፈጠረውን ማኅበረሰብ ባህል የሚያንፀባርቅ የማኅበራዊ ክንዋኔ ሥነ-ሥርዓት ወይም ፌስቲቫል ነው፤

5. "ፌስቲቫል" ማለት ህዝባዊ በዓላት ወይም ክብረበዓላት ናቸው፤

6. "የተፈጥሮ ዕውቀትና ትግበራት" ማለት ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር ውስጥ የሚፈጥሩት፣ የሚጋሩትና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፉት ሀገር በቀል ዕውቀትና ክህሎት ነው፤

7. "ትዉፊታዊ የዕደጥበብ ዕውቀትና ክህሎት" ማለት የፈጠረውን ማኅበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች ለማሟላት ባህላዊ ቁሳቁሶችና መገልገያ መሣሪያዎችን በመጠቀም ሂደት የተገኘ አገር በቀል የዕደ ጥበብ ዕውቀትና ክህሎት ነው፤

8. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬደዋ ከተማ መስተዳድሮችን ይጨምራል፣

9. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

10. "ባለሥልጣን" ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

11. "ፓሊዮንቶሎጂ" ማለት በሥነ-ህይወት ዘርፍ የሚደረግ የጥናትና ምርምር ዘርፍ ነው፤

12. "አርኪዎሎጂ" ማለት የሰውን ልጅ የቅድመ ታሪክና የታሪክ ዘመን የሚያጠና ዘርፍ ነው፤

13. "መካነ ቅርስ" ማለት አንድ ቅርስ ወይም የቅርስ ክምችት የተገኘበት ወይም ያለበት ቦታ ነው፤

14.“ግኝት” ማለት ከሰው ልጅ ጋር ተያያዥነት ያለው የቅድመ ሰው ወይም የሰው ወይም የእንስሳት ወይም የመገልገያ መሣሪያ ወይም ግብረ ሕንፃ ወይም ሌላ ግንባታ ቅሬት ነው፤

15.“የመታሰቢያ ሐውልት” ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ወይም ህዝብ ወይም ሁነት ለማሰብ ወይም ለመዘከር ወይም ለማስታወስ የተዘጋጀ ወይም የቆመ ወይም የተተከለ ቁስ ነው፤

16.“ግብረ ህንፃ” ማለት ማንኛውም በሰው ሆን ተብሎ የተገነባ ህንፃ ወይም የህንፃ ክፍል ወይም ግንብ ወይም የግንብ ክፍል ወይም መሠረት ነው፤

17.“አደጋ ላይ ያለ ልዩ ቅርስ” ማለት በተፈጥሯዊ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች የተነሳ የመጥፋት አደጋ ያንዣበበበት ወይም ለአደጋ የተጋለጠ ወይም የተመናመነ ቅርስ ነው፤

18.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

19.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የቅርሶች ምደባ</u>

1. ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሚያሟላ ቅርስ በብሔራዊ ቅርስነት ይመደባል፡-

ሀ/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በዓለም ቅርስ መዝገብ ውስጥ የገባ እና ወደፊት በዓለም የቅርስ መዝገብ ውስጥ የሚመዘገብ ማንኛውም ቅርስ፣

ለ/ የሰው ዘር አመጣጥ ወይም የአኗኗር ሁኔታዎች ወይም የመገልገያ መሣሪያዎች ሂደትን የሚወክል የፓሊዮንቶሎጅና የአርኪዮሎጅ መካነ ቅርስ ወይም ግኝት፣

ሐ/ የሰው ወይም የሰውና የተፈጥሮ መስተጋብር ውጤት የሆኑ መረጃዎችን የያዘ ሆኖ ለትምህርት፣ ለታሪክ፣ ለቱሪዝም ወይም ለሳይንስ ምርምር ጠቀሜታ ያለውና ከፍተኛ ሀገር አቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ እሴትነት ያለው የአርኪዮሎጂ መካነቅርስ ወይም ግኝት፤

መ/ የኢትዮጵያውያን የጋራ ባህልና ታሪክ መገለጫ ሆኖ ለሣይንስ፣ ለቴክኖሎጂ፣ ለሥነ-ጽሑፍ ወይም ለሥነ ጥበብ ዕድገት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ተንቀሳቃሽ ቅርስ፤

ሠ/ የኢትዮጵያውያን የጋራ የታሪክ ወይም የባህል አሻራ ከሆነ ሁነት ጋር የተያያዘ ቦታ፣ የመታሰቢያ ሐውልት፣ ግብረ ሕንፃ ወይም ሌላ ግንባታ፣

ረ/ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ላቅ ያለ ድርሻ ካለው ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ተቋም ታሪክ ጋር የተያያዘ ቅርስ፣

ሰ/ በመልክዓ ምድር አቀማመጡ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ክልሎች ውስጥ የሚገኝ የቅርስ ቦታ፣

ሸ/ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የጋራ የባህል አሻራ የሚያንጸባርቅ አፋዊ ትውፊት፣ ትውን ጥበብ፣ የማኅበራዊ ክንዋኔ ሥነ-ሥርዓትና ፌስቲቫል፣ የተፈጥሮ ዕውቀትና ትግበራ ወይም ትውፊታዊ የዕደ ጥበብ ክህሎት እና የእነዚሁ መገለጫ፣

ቀ/ እያንዳንዱን ብሔረሰብ የሚወክልና ብዝሀ ባህልን የሚያንጸባርቅ አፋዊ ትውፊት፣ ትውን ጥበብ፣ የማኅበራዊ ክንዋኔ ሥነ-ሥርዓትና ፌስቲቫል፣ የተፈጥሮ ዕውቀትና ትግበራ ወይም ትውፊታዊ የዕደ ጥበብ ክህሎት እና የእነዚሁ መገለጫ፣

በ/ በአደጋ ላይ ያለ ልዩ የሆነ ቅርስ፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በብሔራዊ ቅርስነት ደረጃ ያልተመደበ የክልል ቅርስነት ደረጃ ይኖረዋል።

3. ውጪ አገር የሚገኙ ቅርሶች ወደ ሀገር ሲመለሱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 መሠረት ደረጃቸው ይመደባል፡፡

4. <u>የቅርሶች አመዳደብ ሥርዓት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ የሚሸፈን ቅርስ ያለምንም ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት በብሔራዊ ቅርስነት ይመዘገባል።

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 በንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (ለ) እስከ (በ) ከተደነገጉት መሥፈርቶች መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን የሚያሟላ ቅርስን በሚመለከት ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት ወይም በሚመለከተው የክልል አካል፣ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም ወይም ግለሰብ የሚቀርብለትን ሃሳብ መሠረት በማድረግ አጥንቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ለተቋቋመው የቅርሶች ምደባ ምክር ቤት የጥናት ሪፖርቱን ያቀርባል።

3. የቅርሶች ምደባ ምክር ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በባለሥልጣኑ የቀረበለትን የጥናት ሪፖርት መርምሮ ቅርሱ በብሔራዊ ቅርስነት መመደብ ይገባዋል ብሎ ካመነ የውሳኔ ሃሳቡን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

4. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሲያጸድቀው ቅርሱ በብሔራዊ ቅርስነት በባለሥልጣኑ ይመዘገባል፡፡

5. **የብሔራዊና የክልል ቅርሶች አስተዳደር**

1. ባለሥልጣኑ:-

ሀ/ በብሔራዊ ቅርስነት የተመዘገቡ ቅርሶችን በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 ድንጋጌዎች መሰረት ያስተዳድራል፣

ለ/ እንዳስፈላጊነቱ ብሔራዊ ቅርሶች በሚገኙበት ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሊከፍት ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል የሥልጣን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ሐ/ በዓለም የቅርስ መዝገብ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ በብሔራዊ ቅርስነት የተመዘገቡ ቅርሶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እያጠና ለዓለም የቅርስ ኮሚቴ በማቅረብ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤

መ/ የክልል ቅርሶች ጥናትና አጠባበቅን በሚመለከት እንዳስፈላጊነቱ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

2. በክልል ቅርስነት ደረጃ የሚመደቡ ቅርሶች አግባብ ባላቸው የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 ድንጋጌዎች በሚመለከታቸዉ የክልል አካላት ይተዳደራሉ፡፡ ክልሎችም የየራሳቸው የክልል ቅርስ ምደባ ምክር ቤት ማቋቋም ይችላሉ።

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ አፈጻጸም፣ በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 ድንጋጌዎች ለባለሥልጣኑ፣ ለሚኒስቴሩ እና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባሮች በክልል ቅርስነት የሚመደቡ ቅርሶችን በሚመለከት በየደረጃው ለየሚመለከታቸው የክልል መንግሥት አካላት እንደተሰጡ ይቆጠራል፡፡

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሲከፍት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በብሔራዊ ቅርሱ አስተዳደር የሚሳተፍ ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላትና የሕዝብ አደረጃጀቶች የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት ኮሚቴ ያደራጃል፡፡

6. **ብሔራዊ የቅርሶች ምደባ ምክር ቤት መቋቋም**

1. በብሔራዊ ቅርስነት ስለሚመደቡ ቅርሶች የሚቀርቡ ሃሳቦችን እየመረመረ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ኃላፊነት የሚኖረው ብሔራዊ የቅርሶች ምደባ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2. ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

## 7. የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተወካያ -------- ሰብሳቢ፣
2. በእያንዳንዱ ክልል የቅርሶች አስተዳደርን በሚመለከት ሥልጣን የተሰጠው አካል ተወካያ-----------አባል፣
3. የቅርስ ማህበራት ተወካይ ---------------------- አባል፣
4. በአጀንዳ የተያዘው ቅርስ ባለይዞታ ----------- አባል፣
5. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ------- አባልና ፀሐፊ፡፡

## 8. የምክር ቤቱ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

የምክርቤቱ አባላት የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

1. በምክር ቤቱ ስብሰባዎች የመገኘት፣
2. የምክር ቤቱን ዓላማ ለማሳካት ተገቢውን ጥረት የማድረግ፣
3. በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተመለከቱ ሌሎች ተግባርና ሃላፊነቶችን የመፈፀም።

## 9. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች

1. ምክር ቤቱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል፡፡
2. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤቱ ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 10. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማስፈፀም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 11. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

13. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 15 ቀን 2006 ዓ/ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

ለ/ ቱሪዝም

<u>ደንብ ቁጥር 66/1992</u>

<u>የወጪ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ፊልም ስለሚያነሱበት ሁኔታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀፅ 5 መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ፊልም ስለሚያነሱበት ሁኔታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 66/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ሚኒስቴር" ማለት የማስታወቂያና ባሕል ሚኒስቴር ነዉ፤[17]
2. "ፊልም" ማለት በሴሉሎስ ወይም በማግኔቲክ ቴፕ የሚቀረፅ ተንቀሳቃሽ ሥዕል ነው፤
3. "ተራኪ ፊልም" ማለት በልቦለድ ድርሰት ላይ ተመስርቶ ተዋንያንን በማሳተፍ የሚቀረፅ ፊልም ነው፤
4. "ዘጋቢ ፊልም" ማለት ተፈጥሮን፣ ባህልን፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን እና የመሳሰሉትን ነገሮች በቴሌቪዥን፣ በሲኒማ፣ ወይም በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ስክሪን ማስተላለፊያዎች ለማሰራጨት ዓላማ የሚቀረፅ ፊልም ነው፤
5. "የፊልም ማንሳት ፈቃድ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በተወሰነ ጊዜና ቦታ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት ብቻ ለሚመጡ የውጭ ዜጎች በሚኒስቴሩ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች፦

1. ኢትዮጵያ ውስጥ የፊልም ተቋም እንዲያቋቁሙ ቋሚ ፈቃድ ከተሰጣቸው ሰዎች በስተቀር ዓላማቸው ትርፍ የሆነ ወይም ያልሆነ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት በሚመጡ ዜጎች ላይ፤

---

[17] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9(23) መሠረት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

2. በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች፤

ተፈጻሚ ይሆናሉ።

4. ዓላማ

የደንቡ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በውጭ ዜጎች የሚካሔደው የፊልም ማንሳት ሥራ የሀገሪቱን ታሪክ፣ ባህል፣ የተፈጥሮ ውበት፣ ሀብት፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ሁኔታ እና የመሳሰሉትን ለውጭው ዓለም በማስተዋወቅ ጉልህ ሚና የሚጫወት ስለሆነ ሥራው የሚመራበትን ሥርዓት ግልጽና ቀልጣፋ በማድረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
2. የሀገሪቱ ዜጎችና ድርጅቶች ከሚነሳው ፊልም ማግኘት የሚገባቸውን መብትና ጥቅም ማስከበር፤
3. የፊልም ማንሳቱ ሥራ የሀገሪቱን ሕጎች እና የሕዝቦቿን ባህል በማክበር እንዲካሔድ ማድረግ።

5. ፈቃድ ስለማስፈለጉ

ኢትዮጵያ ውስጥ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት የሚፈልግ ማንኛውም የውጭ ዜጋ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

6. ፊልም ለማንሳት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም ለማንሳት የሚፈልግ የውጭ ዜጋ ሥራው ከሚጀምርበት ከ10 ቀን በፊት ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል።
2. ማመልከቻው በተለይም የፊልሙን ዓላማና ርዕስ፣ ፊልም ማንሳቱ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ፊልም ማንሳቱ የሚካሔድበትን ትክክለኛ ሥፍራ እና ለፊልሙ ሥራ የሚውለውን ጠቅላላ ወጪ እንዲሁም ከጠቅላላው ወጪ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ የሚውለውን ገንዘብ መግለጽ ይኖርበታል።
3. አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር፡-

    ሀ/ ተራኪ ፊልም ከሆነ የፊልሙን ስክሪፕት አንድ ቅጂ ከነአጭር መግለጫው ወይም ዘጋቢ ፊልም ከሆነ አጭር መግለጫውን፤

    ለ/ በፊልሙ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ገጸ ባህርይ የሚካተት ከሆነ ግለሰቡ ወይም ሕጋዊ ወራሾቹ የማይቃወሙ መሆኑን የሚያመለክት ውሎችንና ሰነዶችን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ፤

ሐ/ በኢትዮጵያዊና በውጭ ዜጋ በጋራ የሚሰራ ፊልም ሲሆን የእያንዳንዱን ወገን ግዴታና ኃላፊነት የሚያመለክት በሁለቱ መካከል የተደረገ ስምምነት፤ እና

መ/ በፊልም ሥራው ላይ የሚሰማሩትን ሰዎች ዜግነት፣ የፓስፖርቱን ቁጥር፣ ፓስፖርቱን የሰጠው አገር፣ ቋሚና ጊዜያዊ አድራሻ፣ እንዲሁም ሌሎች በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ መረጃዎችን፤

አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 6 የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተዉ መቅረባቸውንና በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 ውስጥ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ መፈጸሙን በማረጋገጥ ማመልከቻው በቀረበለት በ3 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በተሰጠ ፈቃድ ላይ ከተገለጹ ቦታዎች መካከል ፊልም ለማንሳት የተከለከሉ ቦታዎች ካሉ ለመከልከል ሥልጣን ያለው አካል መብት የተጠበቀ ነው፡፡

8. <u>ስለ በረራ ፈቃድ</u>

1. አመልካቹ ለፊልም ማንሳቱ ሥራ አይሮፕላን መጠቀም ከፈለገ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የበረራ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።
2. አመልካቹ ከፈለገ የበረራ ፈቃድ ማመልከቻውን በሚኒስቴሩ አማካኝነት ሊያቀርብ ይችላል፤
3. ለፊልሙ ሥራ አይሮፕላን ለመጠቀም የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ማመልከቻ በቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ የበረራ ፈቃድ መስጠት አለበት፤ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው ከሆነም ባለሥልጣኑ ውሳኔውን ለአመልካቹ ወይም ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ያስታውቃል።

9. <u>የአመልካቹ ግዴታ</u>

አመልካቹ ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. የተሰራውን ፊልም ሁለት የቪ.ኤች.ኤስ. ቪዲዮ ካሴት የእንግሊዝኛ ቅጂ ለሚኒስቴሩ የማስረከብ፤
2. በግንባር በመቅረብ በፈቃድ ግዴታው መሠረት ለመሥራትና የአገሪቱን ሕግ ለማክበር ግዴታ የመግባት፡፡

10. <u>ፈቃድን ስለመሰረዝ</u>

በዚህ ደንብ በአንቀጽ 9(2) በተመለከተው መሠረት ባለፊቃዱ የገባውን ግዴታ ያላከበረ እንደሆነ ሚኒስቴሩ ፊቃዱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

11. <u>የቀረጥ ነጻ መብት</u>

1. አመልካቹ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ይዟቸው የሚመጣውን ለፊልሙ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ዝርዝር ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡
2. አመልካቹ በዝርዝሩ የተመለከቱትን እቃዎች ከአገር እንደሚያስወጣ ግዴታ ሲገባም እነዚህ መሣሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፊልባቸው እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

12. <u>ስለ ፈቃድ ክፍያ</u>

1. ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም ለማንሳት የሚፈልግ የውጭ ዜጋ ከዚህ የተመለከተውን የፊቃድ ክፍያ ለሚኒስቴሩ ይከፍላል፡-
   ሀ/ ለፊልሙ ሥራ ከሚወጣው ወጪ ለመጀመሪያ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/፣ ብር 1ሺ /አንድ ሺህ/ እና
   ለ/ ከብር 100,000 /አንደ መቶ ሺህ ብር/ በላይ ለሆነው ለተጨማሪው የፊልም ሥራ ወጪ ደግሞ ተጨማሪ 0.2 በመቶ (ዜሮ ነጥብ ሁለት ፐርሰንትን)፡፡
2. የፊልም ማንሳቱ ሥራ የሚካሄደው ፊልም ለማንሳት ክፍያ በሚያስከፍል ቦታ የሆነ እንደሆነ በሚመለከተው አካል የሚጠየቀውን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

13. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

ሚኒስቴሩ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

14. <u>ዉክልና ስለመስጠት</u>

ሚኒስቴሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማናቸውም የፊልም ማንሳት ፈቃድ የተሰጠባቸው ግዴታዎች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዲችሉ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

15. <u>ቅጣት</u>

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ሰው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

16. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት 19 ቀን 1992 ዓ/ም
መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## ደንብ ቁጥር 173/2002

## የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

1. "የቱሪለት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት ሆቴል፣ ሞቴል፣ ሎጅ፣ ፔንሲዮን ወይም ሬስቶራንት ነዉ፤
2. "ቱሪስት" ማለት በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሌላ አካባቢ በመጓዝ በደረሰበት አካባቢ በማንኛውም ዓይነት ክፍያ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ሳይሰማራ ከ24 ሰዓት ላላነሰና ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው፤
3. "የደረጃ ምደባ" ማለት ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ፔንሲዮኖችና ሬስቶራንቶች የአገልግሎት ጥራት ደረጃቸውን ለመጠበቅ ይዘታቸዉን ማሻሻል እንዲችሉ የሚመዘኑበት ሥርዓት ነው፤
4. "ሆቴል" ማለት የመኝታ፣ የምግብ፣ የመጠጥና እንደ አስፈላጊነቱም የመዝናኛ፣ የስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነዉ፤
5. "ሞቴል" ማለት የመኝታ፣ የምኪና ማቆሚያና እንደ አስፈላጊነቱ የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን በከተማ፣ ከከተማ ውጭና በአውራ ጎዳና ዳር ላይ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነዉ፡፡
6. "ሎጅ" ማለት የመኝታ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን እንደአስፈላጊነቱም የመዝናኛና የስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን በተፈጥሮ አከባቢ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅቶ ነው፤

7. “ፔንሲዮን” ማለት መኝታና የቁርስ አገልግሎት ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤
8. “ሬስቶራንት” ማለት የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅቶ ነው፤
9. “የምስክር ወረቀት” ማለት ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሥራ ላይ ለተሠማራ ድርጅት የሚሰጥ የደረጃ መለያ ማስረጃ ነዉ፡፡
10. “ዓርማ” ማለት ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሚደረግ የደረጃ ምደባ መሰረት የሚሰጥ መለያ ነዉ፡፡
11. “አገልግሎት” ማለት ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለተጠቃሚዎች በክፍያ የሚሰጥ መስተንግዶ ነዉ፡፡
12. “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅድም ተከተሉ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነዉ፣
13. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ፣
14. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸዉ አነጋገር ሴቶንም ይጨምራል።

3. **ዓላማ**

የዚህ ደንብ ዓላማ የቱሪስት አገልሎት ሰጪ ድርጅቶች የአገልግሎት ጥራት እንዲያሻሽሉና ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲኖራቸዉ ለማስቻል ማገዝና መቆጣጠር ይሆናል፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኙና ደረጃ ሊመደብላቸዉ በሚገባ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. **የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃዎች**

1. የተወሰነዉን መሥፈርት የሚያሟሉ ሆቴሎች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-
   ሀ/ ባለ አምስት ኮከብ + ዴሉክስ ሆቴል፣
   ለ/ ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል፣
   ሐ/ ባለ አራት ኮከብ ሆቴል፣
   መ/ ባለ ሦስት ኮከብ ሆቴል፣
   ሠ/ ባለ ሁለት ኮከብ ሆቴል፣
   ረ/ ባለ አንድ ኮከብ ሆቴል፣
   ሰ/ ተመራጭ ሆቴል፡፡

2. የተወሰነዉን መሥፈርት የሚያሟሉ ሎጆች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-

ሀ/ ባለ አምስት ኮከብ ሎጅ፤

ለ/ ባለ አራት ኮከብ ሎጅ፤

ሐ/ ባለ ሦስት ኮከብ ሎጅ፤

መ/ ባለ ሁለት ኮከብ ሎጅ፤

ሠ/ ባለ አንድ ኮከብ ሎጅ፤

ረ/ ተመራጭ ሎጅ፡፡

3. የተወሰነዉን መሥፈርት የሚያሟሉ ሞቴሎች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-

ሀ/ ባለ አምስት ኮከብ ሞቴል፤

ለ/ ባለ አራት ኮከብ ሞቴል፤

ሐ/ ባለ ሦስት ኮከብ ሞቴል፤

መ/ ባለ ሁለት ኮከብ ሞቴል፤

ሠ/ ባለ አንድ ኮከብ ሞቴል፤

ረ/ ተመራጭ ሞቴል፡፡

4. የተወሰነዉን መሥፈርት የሚያሟሉ ፔንሲዮን "ሬኮሜንድድ ፔንሲዮን" ተብሎ ይመደባል፡፡

5. የተወሰነዉን መሥፈርት የሚያሟሉ ሬስቶራንቶች በሚከተሉት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-

ሀ/ ባለ አምስት ኮከብ ሬስቶራንት፤

ለ/ ባለ አራት ኮከብ ሬስቶራንት፤

ሐ/ ባለ ሦስት ኮከብ ሬስቶራንት፤

መ/ ባለ ሁለት ኮከብ ሬስቶራንት፤

ሠ/ ባለ አንድ ኮከብ ሬስቶራንት፤

ረ/ ተመራጭ ሬስቶራንት፡፡

6. ሚኒስትሩ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በመዉሰድ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለመመደብ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

7. ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ያወጣዉ መመሪያ በተጠቃሚዎችና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ በሰፊዉ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መዉሰድ አለበት፡፡

6. <u>ደረጃን የማስመደብ ግዴታ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ከተዘረዘሩት ደረጃዎች በአንዱ ሊመደብ የሚችለዉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው የድርጅቱን ደረጃ የማስመደብ ግዴታ አለበት፡፡

7. <u>ማመልከቻ ስለማቅረብ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተደነገገዉ ግዴታ የሚመለከተዉ ሰዉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ሥራ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ የደረጃዉ ምደባ እንዲደረግለት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የምስክር ወረቀትና ዓርማ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠዉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የደረጃ ለዉጥ ወይም የንግድ ድርጅት ስያሜ ለውጥ ሲያደርግ የእንደገና ምደባ እንዲደረግለትና የምስክር ወረቀትና ዓርማ በምትክነት እንዲሰጠዉ ለሚኒስቴሩ ማመለከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተመለከተዉ ጥያቄ ሲቀርብለት በ30 ቀናት ዉስጥ ምላሹን ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

8. <u>የምስክር ወረቅትና ዓርማ እንዲታይ ስለማድረግ</u>

ማንኛዉም በደረጃ የተመደበ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሚኒስቴሩ የተሰጠዉን የምስክር ወረቀትና ዓርማ በድርጅቱ ዋና መግቢያ ጎልቶ ሊታይ በሚችልበት ሥፍራ ማስቀመጥ አለበት፡፡

9. <u>የደረጃ ምደባ እንደገና ስለማከናወን</u>

1. ሚኒስቴሩ ደረጃ ለተመደበላቸዉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በየሦስት አመቱ በአዲስ መልክ የደረጃ ምደባ ያከናዉናል፡፡
2. የእንደገና ምደባዉ ተግባር ለድርጅቱ ሥራና ለተጠቃሚዉ አመቺ በሆነ ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ የድርጅርቱ ባለቤት ወይም ወኪሉ ለሚቀርብለት ጥያቄ ተገቢዉን መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

10. <u>የደረጃ ምብባ መዝገብ</u>

1. ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን የደረጃ ምደባ መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
2. ማንኛዉም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የንግድ ስሙ ወይም የደረጃ ምደባዉ ሲለወጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የተደረገዉ ምዝገባ መስተካከል አለበት፡፡

3. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የደረጃ ምደባ መዝገብ ለሕዝብ ተደራሽ ይደረጋል፡፡

11. <u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተመደበለትን ደረጃ ጠብቆ የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ያካሂዳል፡፡
2. የቁጥጥር ተግባሩ ለድርጅቱ ሥራና ለተጠቃሚዉ አመቺ በሆነ ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ወኪል ለሚቀርብለት ጥያቄ ተገቢዉን መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀፅ መሠረት ቁጥጥር የሚያደርገዉ በራሱ አነሳሽነት ወይም የተገልጋዮችን ቅሬታ ወይም አስተያየት መነሻ በማድረግ ይሆናል፡፡
4. ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የተገልጋዮችን ቅሬታና አስተያየት ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

12. <u>የምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ</u>

1. ምደባ የተደረገለት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በምስክር ወረቀቱ ላይ ለተመለከተዉ ምደባ የተቀመጠዉን የደረጃ መስፈርት ያልጠበቀ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ በሚወስነዉ ተገቢ የሆነ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ጉድለቶቹን እንዲያስተካክል በጽሑፍ ትዕዛዝ ይሰጠዋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የተሰጠዉን ትዕዛዝ አክብሮ ያልፈፀመ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተሰጠዉን በምስክር ወረቀት ይሰረዛል፡፡ የስረዛዉ ዉሳኔም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ በጽሑፍ እንዲደርሰዉ ይደረጋል፡፡
3. የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ዉሳኔ የተሰጠዉ ድርጅት ባለቤት ወይም ወኪሉ የምስክር ወረቀቱ ሊሰረዝ አይገባም የሚል ከሆነ ቅሬታዉን በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 መሠረት ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የድርጅት ባለቤት ወይም ወኪሉ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት ቅሬታዉን ካላቀረበ ወይም ያቀረበዉ ቅሬታ ተመርምሮ ዉድቅ ከተደረገ የምስክር ወረቀቱ መሠረዝ ይጸናል፡፡
5. ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የምስክር ወረቀት መሠረዙን አመቺ በሆነ የመገናኛ ዘዴ ለሕዝብ ያሳዉቃል፡፡

13. <u>የምስክር ወረቀትና ዓርማን ስለመመለስ</u>

በዚህ ደንብ አንቀፅ 12 መሠረት የምስክር ወረቀት የተሠረዘበት ወይም ሥራዉን ያቆመ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የምስክር ወረቀቱንና ዓርማዉን ለሚኒስቴሩ መመለስ አለበት፡፡

14. <u>ምትክ የምስክር ወረቀትና ዓርማን ስለመስጠት</u>

ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የተሰጠዉን የምስክር ወረቀት ወይም ዓርማ ከተበላሸ ወይም ከጠፋና ስለመጥፋቱ ድርጅቱ ማረጋገጫ ለሚኒስቴሩ ካቀረበ ምትክ ይሰጠዋል፡፡

15. <u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የደረጃ ምደባና እንደገና ምደባ እና የምስክር ወረቀትና ዓርማ ለመስጠትና ለመተካት ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘዉ ሠንጠረዥ በተመለከተዉ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይፈፀማል፡፡

16. <u>ግዴታዎችን ስለመፈፀም</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 5 ከተዘረዘሩት ደረጃዎች በአንዱ ሊመደብ የሚችል ማንኛዉም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በዚህ ደንብ አንቀፅ 6፣ 8፣ 9(2)፣ 11(2) እና 15 የተጠቀሱትን ግዴታዎች መፈፀም አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ ከሌሎች አግባብነት ካላቸዉ አስፈፃሚ አካላት ጋር በመተባበር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሱት ግዴታዎች መፈፀማቸዉን ያረጋግጣል፡፡

17. <u>ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ</u>

1. ሚኒስቴሩ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የደረጃ ምደባና እንደገና ምደባን እና የምስክር ወረቀትን ስረዛን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምር ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
2. ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በተሰጠ የደረጃ ምደባና እንደገና ምደባ ዉሳኔ ወይም በምስክር ወረቀት መሰረዝ ቅር የተሰኘ ማንኛዉም ሰዉ ቅሬታዉን በ30 ቀናት ዉስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለተቋቋመዉ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ኮሚቴዉ የቀረበለትን ቅሬታ በ45 ቀናት ዉስጥ መርምሮ የዉሳኔ ሃሳቡን ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡

18. <u>መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈል መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

19. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 209/1987 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

20. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በዚህ ደንብ አንቀፅ 19 በተሻረዉ ደንብ መሰረት ተመድበዉ የነበሩት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ይህ ደንብ እንደፀና እንደገና ይመደባሉ፡፡

21. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክርሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**የአገልግሎት ክፍያዎች ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ዓይነት | መደባ ወይም እንደገና ምደባ | ዓርማ (ሰሰፐ/ሲተካ) | የምስክር ወረቀት (ሲሰጥ/ሰተካ) |
|---|---|---|---|---|
| | | (ብር) | (ብር) | (ብር) |
| 1 | ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆችና ፔንሲዮኖች | | | |
| 1.1 | እስከ 25 ክፍሎች | 1000 | 1200 | 50 |
| 1.2 | ከ26 እስከ 50 ክፍሎች | 1500 | 1200 | 50 |
| 1.3 | ከ51 እስከ 100 ክፍሎች | 1750 | 1200 | 50 |
| 1.4 | ከ101 እስከ 200 ክፍሎች | 2000 | 1200 | 50 |
| 1.5 | ከ200 እስከ 400 ክፍሎች | 2500 | 1200 | 50 |
| 1.6 | ከ400 ክፍሎች በላይ | 2750 | 1200 | 50 |
| 2 | ሬስቶራንት | 500 | 1200 | 50 |

ሐ/ ፓርኮች

## ደንብ ቁጥር 329/2007

## የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ ደንብ "የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 329/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ድንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተከል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤
   4. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
   5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክን መሰየም

   የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ (ከዚህ በኋላ "ፓርክ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተሰይሟል።

4. የፓርኩ ዳር ድንበር

   ፓርኩ በኦሮሚያና በአፋር ብሔርዊ ክልሎች ዉስጥ 590 ካሬ ኪ.ሜ ስፋት ቦታ የሚሸፍን ሆኖ በሚከተሉት አዋሳኝ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፦

   1. ከአዋሽ ሰባት ኪሎ ከተማ በስተደቡብ በ08 ዲግሪ 58 ደቂቃ 34 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 09 ደቂቃ 50 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ ከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 1 በመነሳት፤

2. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 58 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 08 ደቂቃ 18 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 2 ይዞ፣ ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ዱዱብ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 59 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 07 ደቂቃ 29 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉን ጉልት ቁጥር 3 ይዞ፣ በዚያ አቅጣጫ በ09 ዲግሪ 00 ደቂቃ 41 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 05 ደቂቃ 42 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 4 ድረስ፤
3. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ በ09 ዲግሪ 04 ደቂቃ 37 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 04 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉን ጉልት ቁጥር 5 ይዞ ፣ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ አሰዳ ሐይቅ አጠገብ በ09 ዲግሪ 08 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 05 ደቂቃ 03 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 6 ይዞ፣ ደሆ በተባለ አከባቢ በ09 ዲግሪ 08 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 04 ደቂቃ 18 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 7 ድረስ፤
4. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ሳቡሬ በተባለ አከባቢ በ09 ዲግሪ 07 ደቂቃ 36 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 59 ደቂቃ 52 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 8 ድረስ፤
5. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ከሳቡሬ አከባቢ ወደ ፍል ዉሃ በሚወስደዉ መንገድ ላይ በ09 ዲግሪ 06 ደቂቃ 08 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 59 ደቂቃ 56 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 9 ድረስ፤
6. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ በ09 ዲግሪ 06 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 58 ደቂቃ 30 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 10 ድረስ፤
7. ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ በ09 ዲግሪ 05 ደቂቃ 10 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 55 ደቂቃ 43 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 11 ይዞ፣ በዚያዉ አቅጣጫ ሃሮ ቀርሳ በተባለ አከባቢ በመተሐራ ሳቡሬ መንገድ ዳር ላይ በ09 ዲግሪ 04 ደቂቃ 08 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 52 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉን ጉልት ቁጥር 12 ይዞ፣ በ09 ዲግሪ 00 ደቂቃ 58 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39

ዲግሪ 51 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 13 ድረስ፤

8. ከዚያም ደቢቲ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 59 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 51 ደቂቃ 02 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 14 ድረስ፤
9. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ በመታጠፍ ዲጋኤዱ በተባለ አካባቢ በ08 ዲግሪ 56 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 55 ደቂቃ 19 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉን ጉልት ቁጥር 15 ይዞ፣ ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ ቆቦ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 56 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 56 ደቂቃ 50 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 16 ድረስ፤
10. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ በመታጠፍ ቆቦ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 56 ደቂቃ 58 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 58 ደቂቃ 00 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 17 ድረስ፤
11. ከዚያም ወደ ምስራቅ በመታጠፍ ቆቦ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 56 ደቂቃ 51 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ39 ዲግሪ 58 ደቂቃ 42 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 18 ይዞ፣ ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ በንቲ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 56 ደቂቃ 11 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 02 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 19 ድረስ፤
12. ከዚያም ወደ ደቡብ የመታጠፍ በንቲ በተባለ አከባቢ በ08 ዲግሪ 55 ደቂቃ 00 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 01 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 20 ይዞ፤
13. ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ በመታጠፍ ገልቻ በተባለ አከባቢ በአዋሽ ወንዝ አፋፍ በ08 ዲግሪ 51 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ40 ዲግሪ 00 ደቂቃ 09 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተመለከተዉ ጉልት ቁጥር 21 ድረስ፤
14. ከዚያም ወደ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመነሳ በአዋሽ ወንዝ ተከትሎ በአዋሽ ሰባት ኪሎ ከተማ በስተደቡብ ከተመለከተዉ መነሻ ጉልት ቁጥር 1 ይገጥማል፡፡

## 5. <u>የፓርኩ አስተዳደር</u>

1. ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 አንቀጽ 4 መሠረት ጎቱ ውስጥ በሚያደራጀው የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ") በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

6. <u>የኮሚቴ አባላት</u>

ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር)......... ሰብሳቢ፤
2. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር).......... አባላት፤
3. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ተወካዮች....አባላት፤
4. የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች ...................................... አባላት፤
5. የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌዎች ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች......አባላት፤
6. ለፓርኩ ጉብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት አንድ ተወካይ......አባል፤
7. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ............................አባልና ፀሐፊ።

7. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤
2. በፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
3. ከፓርኩ ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን የፓርኩን ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፤ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፡፡

8. <u>የኮሚቴዉ ስብሰባ</u>

1. ኮሚቴው በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤
2. ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት የተጠቀሙባቸውን ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤
3. የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፡፡

10. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንሰሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል።
2. ባለሥልጣኑ በፓርኩ ከሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል የሚገቡ የቤት እንስሳትን በሚመለከት ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የሚጣል አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከባለስልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. <u>የተሻሩ ህጎች</u>

የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ማቋቋሚያ ትዕዛዝ ቁጥር 54/1961 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

13. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 30 ቀን 2007 ዓ/ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

አባሪ የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ካርታ



## ደንብ ቁጥር 333/2007

## የአልጣሽ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በመጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአልጣሽ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 333/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተከል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤
   4. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
   5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. **የአልጣሽ ብሔራዊ ፓርክን መሰየም**

   በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት "አላጣሽ ብሔራዊ ፓርክ" ተብሎ ሲጠራ የነበረው ፓርክ "አልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ" ተብሎ (ከዚህ በኋላ "ፓርክ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተሰይሟል።

4. **የፓርኩ ዳር ድንበር**

   ፓርኩ በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር ዞን በቋራ ወረዳ አስተዳደር የሚገኝና በጠቅላላው 266,570 ሄክታር ቦታ የሚሸፍን ሆኖ በደቡብ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ በሰሜን ከመሐዲድ ቀበሌ አስተዳደር፣ በምስራቅ ከባምባሆና ገለጎ ቀበሌ አስተዳደሮች እንዲሁም

በምዕራብ ከሱዳን ጋር የሚዋሰን ሆኖ በሚከተሉት አዋሳኝ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፡-

1. ፓርኩን በምስራቅ በኩል ከሚያዋስነውና በገለጎ ቀበሌ ከሚገኘው የአልቢድ ወንዝ ላይ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አልቢድ ኮረብታ አጠገብ ከወንዙ ዳርቻ ላይ በ12 ዲግሪ 29 ደቂቃ 17 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 48 ደቂቃ 33 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 1 መነሻ በማድረግ፣ በዚያዉ አቅጣጫ በ12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 29 ስከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 48 ደቂቃ 33 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የሚገኘዉን ጉልት ቁጥር 2በመትከል፣ ከዚያም በ12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 35 ሰከንድ ስሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 47 ደቂቃ 28 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ ደርሃሰን አፋፍ ጠርዝ ሾላ ዉሃ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 3 ድረስ፣
2. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የደርሃሰን ተራራን አፋፍ ለአፋፉ ተከትሎ ሄዶ እስከ ገለጎ ቀበሌ መጨረሻ አልዋሾ ተራራ ድረስ በመሄድ ከመሀዲድ ቀበሌ ከአልዋሾ ተራራ ሥር የሚነሳዉን  የአልዋሾን ሸለቆ ተከትሎ ሸለቆዉንና የአልጣሽ የበጋ የመኪና መንገድ መገናኛ ላይ በ12 ዲግሪ 15 ደቂቃ 07 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 15 ደቂቃ 14 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የሚገኘዉን ጉልት 4 ይዞ፣ ከዚያም ሸለቆዉን በመከተል ሸለቆዉ ከበርሚል ወንዝ የሚገናኝበት ቦታ ላይ በ12 ዲግሪ 16 ደቂቃ 10 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 43 ደቂቃ 16 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 5 ድረስ፤
3. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ የበርሚል ወንዝን በመከተል በአምራኩባ ተራራ ትክክል በወንዙ ጠርዝ ላይ በ12 ዲግሪ 18 ደቂቃ 43 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 43 ደቂቃ 32 ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ የሚገኘው ጉልት ቁጥር 6 ድረስ፣
4. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ የአምራኩባ ተራራን ትይዩ በመከተል በአምራኩባ ተራራና በበርሚል ወንዝ መካከል በ12 ዲግሪ 21 ደቂቃ 45 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 02 ደቂቃ 39 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 7 ድረስ፤

5. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በአምራኩባ ተራራ ትይዩ ደናር ወንዝ ዳር ላይ በ12 ዲግሪ 22 ደቂቃ 33 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 42 ደቂቃ 43 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 8 ድረስ፤
6. ከዚያም የአምራኩባ ተራራን ወደ ፓርኩ ክልል በማስገባት ከተራራው ግርጌ በ12 ዲግሪ 23 ደቂቃ 53 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 43 ደቂቃ 07 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 9 ድረስ፤
7. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ፦
   ሀ/ በ12 ዲግሪ 24 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 41 ደቂቃ 28 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 10 ድረስ፤
   ለ/ በ12 ዲግሪ 24 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 41 ደቂቃ 10 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 11 ድረስ፤
   ሐ/ በ12 ዲግሪ 25 ደቂቃ 09 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 40 ደቂቃ 54 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 12 ድረስ፤
   መ/ በ12 ዲግሪ 24 ደቂቃ 54 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 40 ደቂቃ 30 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 13 ድረስ፤
   ሠ/ በ12 ዲግሪ 25 ደቂቃ 10 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 39 ደቂቃ 52 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከተተከለው ጉልት ቁጥር 14 ድረስ፤
   ረ/ በ12 ዲግሪ 25 ደቂቃ 24 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 43 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚኘው ጉልት ቁጥር 15 ድረስ፤
   ሰ/ በ12 ዲግሪ 26 ደቂቃ 03 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 38 ደቂቃ 43 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 16 ድረስ፤
   ሸ/ በ12 ዲግሪ 27 ደቂቃ 07 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 38 ደቂቃ 19 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 17 ድረስ፤
   ቀ/ በ12 ዲግሪ 28 ደቂቃ 47 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 17 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 18 ድረስ፤
   በ/ በ12 ዲግሪ 27 ደቂቃ 50 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 48 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር 19 ድረስ፤

8. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ለበጎ ወንዝ ጥግ ልዩ ስሙ አምጃሌ ከተባለው ቦታ ላይ በ12 ዲግሪ 30 ደቂቃ 27 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ35 ዲግሪ 37 ደቂቃ 14 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር 20 ድረስ፤
9. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍና የገለጎ ወንዝን ድንበር በማድረግ እስከ ኢትዮጵያና ሱዳን ዓለም-አቀፋዊ ድንበር ድረስ፤
10. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ በምዕራብ በኩል የኢትዮጵያና ሱዳን ዓለም-አቀፋዊ ወሰንን ተከትሎ የአይማ /ዲንደር/ ወንዝ ከኢትዮጵያ እስከሚ ወጣበት ቦታ ድረስ፤
11. ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በደቡብ በኩል የአማራንና የቤንሻንጉል ጉምዝን ብሄራዊ ክልሎች የሚያዋስነውን የአይማ /ዲንደር/ ወንዝ ተከትሎ በመሄድ እስከ አይማና አልቢድ ወንዞች መገናኛ ድረስ፤
12. ከዚያም የአልቢድ ወንዝን ተከትሎ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ወንዙን ተከትሎ ይሄድና አልቢድ ኮረብታ ጥግ ከወንዙ ዳርቻ ላይ እስከሚገኘዉ መነሻ ጉልት ቁጥር አንድ ድረስ።

5. <u>የፓርኩ አስተዳደር</u>

1. ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 አንቀጽ 4 መሠረት ገለጉ ወረዳ ውስጥ በሚያደራጀዉ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴው" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

6. <u>የኮሚቴ አባላት</u>

ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላቶች ይኖሩታል፦

1. የቋራ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ................................................ ሰብሳቢ፤
2. የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ................................. አባል፤
3. የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች ................................... አባላት፤
4. የገለጉ ወረዳ ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች .................አባላት፤
5. የገለጉ ወረዳ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንድ ተወካይ............አባል፤
6. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ...........................አባልና ፀሐፊ።

7. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤
2. በፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
3. ከፓርኩ ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን የፓርኩን ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፤ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፡፡

8. <u>የኮሚቴዉ ስብሰባ</u>

1. ኮሚቴው በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤
3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በዱር እንሰሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤
2. ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤
3. የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፡፡

10. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንስሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል።

2. ባለሥልጣኑ ፓርኩ በሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል የሚገቡ የቤት እንስሳትን በሚመለከት የሚጣል ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የፓርኩን ዳር ድንበር ለማስከበር በሚደረገው እንቅስቃሴ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 8 ቀን 2006 ዓ/ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አባሪ

## አልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ ካርታ



## ደንብ ቁጥር 334/2007

## የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህ ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 334/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ድንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተከል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤
   4. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
   5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **የጋምቤል ብሔራዊ ፓርክን መሰየም**

   የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ (ከዚህ በኋላ "ፓርክ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተሰይሟል።

4. **የፓርኩ ዳር ድንበር**

   ፓርኩ በጋምቤላ ክልል ዉስጥ 4575 ካሬ ኪ.ሜ ስፋት ቦታ የሚሸፍን ሆኖ በሚከተሉት አዋሳኝ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፦

   1. ከሸንተዋ ከተማ በስተ ሰሜን ምስራቅ በ07 ዲግሪ 50 ደቂቃ 23 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ በ34 ዲግሪ 01 ደቂቃ 12 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አንድ በመነሳት፤

2. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ በመታጠፍ በፑኪዲ አካባቢ በ07 ዲግሪ 52 ደቂቃ 10 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ34 ዲግሪ 09 ደቂቃ 32 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር ሁለት ድረስ፤

3. ከዚያም ወደ ሰሜን በመታጠፍ በ07 ዲግሪ 55 ደቂቃ 58 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ34 ዲግሪ 09 ደቂቃ 44 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሦስት ድረስ፣

4. ከዚያም አቅጣጫ በ07 ዲግሪ 55 ደቂቃ 58 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ34 ዲግሪ 09 ደቂቃ 44 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አራት ድረስ፤

5. ከዚያም ወደ ምስራቅ በመታጠፍ በ07 ዲግሪ 58 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ34 ዲግሪ 12 ደቂቃ 54 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምስት ድረስ፤

6. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 01 ደቂቃ 18 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ34 ዲግሪ 13 ደቂቃ 36 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስድስት ድረስ፤

7. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 02 ደቂቃ 07 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ34 ዲግሪ 12 ደቂቃ 40 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሰባት ድረስ፤

8. ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ በ08 ዲግሪ 04 ደቂቃ 02 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ34 ዲግሪ 10 ደቂቃ 36 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስምንት ድረስ፤

9. ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ በ07 ዲግሪ 05 ደቂቃ 06 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ34 ዲግሪ 08 ደቂቃ 08 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ዘጠኝ ድረስ፤

10. ከዚያም ወደ ምዕራብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 05 ደቂቃ 52 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 52 ደቂቃ 47 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስር ድረስ፤

11. ከዚያም ወደ ሰሜን በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 14 ደቂቃ 33 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና እና በ33 ዲግሪ 54 ደቂቃ 56 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ አንድ ድረስ፤

12. ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን ተከትሎ በ08 ዲግሪ 15 ደቂቃ 58 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 55 ደቂቃ 13 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት ድረስ፤

13.ከዚያም ወደ ምዕራብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 16 ደቂቃ 08 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 52 ደቂቃ 48 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አሥራ ሥስት ድረስ፤

14. ከዚያም ወደ ደቡብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 12 ደቂቃ 27 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 51 ደቂቃ 29 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ አራት ድረስ፡

15. ከዚያም ተመሣሣይ አቅጣጫ ተከትሎ በ08 ዲግሪ 09 ደቂቃ 03 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 50 ደቂቃ 35 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት ድረስ፡

16. ከዚያም ወደ ምዕራብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 11 ደቂቃ 02 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 43 ደቂቃ 46 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት ድረስ፤

17.ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 14 ደቂቃ 34 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 38 ደቂቃ 48 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት ድረስ፤

18.ከዚያም ወደ ምዕራብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 12 ደቂቃ 53 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 23 ደቂቃ 58 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ስምንት ድረስ፤

19.ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ በመታጠፍ በ08 ዲግሪ 18 ደቂቃ 18 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 20 ደቂቃ 13 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ ድረስ፤

20. ከዚያም ወደ ምዕራብ በመታጠፍ ወደ ጊሎ ወንዝ የሚገባዉ ገባር ወንዝና የኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን ዓለም አቀፍ ድንበርን ተከትሎ በ08 ዲግሪ 20 ደቂቃ 31 ሰከንድ

ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 12 ደቂቃ 56 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ድረስ፤

21.ከዚያም የኢትዮጵያ እና የደቡብ ሱዳን ዓለም አቀፍ ድንበርን ተከትሎ ፒቦር ወንዝ ዳር ላይ በ08 ዲግሪ 08 ደቂቃ 26 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 11 ደቂቃ 28 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አንድ ድረስ፤

22.ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ በመታጠፍ በጊሎ ወንዝ ዳር ላይ በ08 ዲግሪ 01 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ33 ዲግሪ 14 ደቂቃ 43 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሁለት ድረስ፤

23.ከዚያም ወደ ደቡብ በመታጠፍ በአኮቦ ወንዝ ዳር ላይ የኢትዮጵያ እና የደቡብ ሱዳን ዓለም አቀፍ ድንበርን ተከትሎ በ07 ዲግሪ 47 ደቂቃ 38 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 09 ደቂቃ 32 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሥስት ድረስ፤

24.ከዚያም ወደ ምስራቅ በመታጠፍ በአኮቦ ወንዝ ዳር ላይ የኢትዮጵያ እና የደቡብ ሱዳን ዓለም አቀፍ ድንበርን ተከትሎ በ07 ዲግሪ 38 ደቂቃ 17 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 44 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አራት ድረስ፤

25. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ በመታጠፍ በጊሎ ወንዝ ዳር ላይ በ07 ዲግሪ 46 ደቂቃ 49 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 51 ደቂቃ 25 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አምስት ድረስ፤

26. ከዚያም ወደ ምዕራብ በመታጠፍ ጊሎ ወንዝ ዳር ላይ በ07 ዲግሪ 51 ደቂቃ 59 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 26 ደቂቃ 50 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ስድስት ድረስ፤

27. ከዚያም ወደ ሰሜን በመታጠፍ በ07 ዲግሪ 59 ደቂቃ 42 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 27 ደቂቃ 47 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሰባት ድረስ፤

28. ከዚያም ወደ ምስራቅ በመታጠፍ በ07 ዲግሪ 56 ደቂቃ 55 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ33 ዲግሪ 50 ደቂቃ 42 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ስምንት በመድረስ ከሸንተዋ ከተማ በስተሰሜን ምስራቅ ከሚገኘዉ መነሻ ጉልት ቁጥር አንድ ጋር ይገጥማል፡፡

5. <u>የፓርኩ አስተዳደር</u>

1. ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 አንቀጽ 4 መሠረት ጋምቤላ ከተማ ውስጥ በሚያደራጀዉ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

6. <u>የኮሚቴ አባላት</u>

ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላቶች ይኖሩታል፦

1. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር) ......... ሰብሳቢ፤
2. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር)............ አባላት፤
3. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተወካዮች .......አባላት፤
4. የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች ............................................ አባላት፤
5. የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌዎች ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች ..................አባላት፤
6. ለፓርኩ ጉብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት አንድ ተወካይ........አባል፤
7. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ...........................................................አባልና ፀሐፊ።

7. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤
2. በፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ የኀብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
3. ከፓርኩ ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን የፓርኩን ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፤ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፡፡

8. <u>የኮሚቴዉ ስብሰባ</u>

1. ኮሚቴው በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በዱር እንሰሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤
2. ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤
3. የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፡፡

10. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንሰሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል።
2. ባለሥልጣኑ ፓርኩ በሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል የሚገቡ የቤት እንስሳትን ስከት የሚጣል ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከባለስሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## አባሪ

## የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ካርታ



## ደንብ ቁጥር 335/2007

## የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች

## ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የየቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 335/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1998 ነው፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ድንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
3. "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተከል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤
4. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የቃፍታ ሽራሮ</u> <u>ብሔራዊ ፓርክን መሰየም</u>

የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ (ከዚህ በኋላ "ፓርክ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተሰይሟል።

4. <u>የፓርኩ ዳር ድንበር</u>

ፓርኩ በትግራይ ክልል ዉስጥ በሚከተሉት አዋሳኝ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፦

1. ከተከዜ ወንዝ በመነሳት ሕለጊን ተራራ ሰሜናዊ ጫፍ ላይ በ14 ዲግሪ 17 ደቂቃ 33 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ በ36 ዲግሪ 41 ደቂቃ 46 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ የሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አንድ በመነሳት፤

2. ከዚያም ሐለጊን ተራራ ደቡባዊ ጫፍ ላይ በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 58 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 42 ደቂቃ 22 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሁለት ድረስ፤
3. ከዚያም በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 07 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 43 ደቂቃ 02 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሦስት ድረስ፣
4. ከዚያም ሽሮና ጫፍ ላይ በ14 ዲግሪ 14 ደቂቃ 06 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 44 ደቂቃ 20 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አራት ድረስ፤
5. ከዚያም በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 49 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 45 ደቂቃ 51 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምስት ድረስ፤
6. ከዚያም በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 27 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 46 ደቂቃ 24 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስድስት ድረስ፤
7. ከዚያም እንደፊትአዉራሪ አካባቢ በ14 ዲግሪ 14 ደቂቃ 53 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 46 ደቂቃ 33 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሰባት ድረስ፤
8. ከዚያም በ14 ዲግሪ 14 ደቂቃ 02 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 49 ደቂቃ 32 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስምንት ድረስ፤
9. ከዚያም በ14 ዲግሪ 13 ደቂቃ 39 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 50 ደቂቃ 38 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ዘጠኝ ድረስ፤
10. ከዚያም በ14 ዲግሪ 11 ደቂቃ 57 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 51 ደቂቃ 28 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስር ድረስ፤
11. ከዚያም በ14 ዲግሪ 11 ደቂቃ 31 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና እና በ36 ዲግሪ 50 ደቂቃ 55 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከተተከለው ጉልት ቁጥር አስራ አንድ ድረስ፤
12. ከዚያም በጎብለል ስካዉት ማረፊያ ቤት አከባቢ በ14 ዲግሪ 10 ደቂቃ 32 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 52 ደቂቃ 31 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚኘው ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት ድረስ፤

13.ከዚያም እንዳጭዑ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 58 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 54 ደቂቃ 13 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አሥራ ሶስት ድረስ፤

14. ከዚያም ሀገረሰላም አከባቢ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 43 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 55 ደቂቃ 12 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ አራት ድረስ፡

15. ከዚያም ዓዕሚ ሓርማዝ በሚባል ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 25 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 55 ደቂቃ 19 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት ድረስ፡

16. ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 38 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 56 ደቂቃ 12 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት ድረስ፤

17.ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 02 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት ድረስ፤

18.ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 14 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ስምንት ድረስ፤

19.ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 41 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 28 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ ድረስ፤

20. ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 16 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 33 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ድረስ፤

21.ከዚያም ሸንተረር ሚዓም ጤል በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 15 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 34 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አንድ ድረስ፤

22.ከዚያም በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 02 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ36 ዲግሪ 59 ደቂቃ 30 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሁለት ድረስ፤

23.ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫን በመከተል ሚዓምጤል ጋራ ስር በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 37 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 59 ደቂቃ 46 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሦስት ድረስ፤

24.ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን በመከተል በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 27 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 59 ደቂቃ 03 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አራት ድረስ፤

25. ከዚያም ኩይሳ ዋርካ ተፋሰስ ራስጌ ላይ በ14 ዲግሪ 04 ደቂቃ 48 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 01 ደቂቃ 21 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አምስት ድረስ፤

26. ከዚያም በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 01 ደቂቃ 16 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ስድስት ድረስ፤

27. ከዚያም በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 18 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 01 ደቂቃ 31 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሰባት ድረስ፤

28. ከዚያም ዉሀደት ብሎክ አከባቢ በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 07 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 03 ደቂቃ 42 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ስምንት ድረስ፤

29.ከዚያም በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 14 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 03 ደቂቃ 52 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ዘጠኝ ድረስ፤

30.ከዚያም በአከባቢዉ ያለዉን ተረተር ተከትሎ በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 56 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 05 ደቂቃ 00 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ድረስ፤

31.ከዚያም በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 02 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 08 ደቂቃ 12 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ አንድ ድረስ፤

32.ከዚያም ማይወይኒ አከባቢ በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 15 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 11 ደቂቃ 41 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ድረስ፤

33.ከዚያም ማይጨዉ አከባቢ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 51 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 13 ደቂቃ 05 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ሶስት ድረስ፤

34.ከዚያም አገልግል በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 26 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 12 ደቂቃ 44 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ አራት ድረስ፤

35.ከዚያም መትረቤል ወንዝ አጠገብ ዲማዛፍ ጋራ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 15 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 14 ደቂቃ 24 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ አምስት ድረስ፤

36.ከዚያም ማይ ቆለንቋል በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 11 ደቂቃ 26 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 15 ደቂቃ 55 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ስድስት ድረስ፤

37.ከዚያም አዲጎሹ አከባቢ በ14 ዲግሪ 12 ደቂቃ 44 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 17 ደቂቃ 22 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ሰባት ድረስ፤

38. ከዚያም እንግርብ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 10 ደቂቃ 47 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 21 ደቂቃ 48 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ስምንት ድረስ፤

39.ከዚያም እንደርታይ ጋራ ጫፍ ላይ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 45 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 23 ደቂቃ 45 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ዘጠኝ ድረስ፤

40.ከዚያም ጥቁር አፈር በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 35 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 22 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ድረስ፤

41.ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 30 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 29 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ አንድ ድረስ፤

42.ከዚያም በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 12 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 22 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ሁለት ድረስ፤

43.ከዚያም ቀልቀል ማይ ዓጋዜን በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 47 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 29 ደቂቃ 17 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ሦስት ድረስ፤

44.ከዚያም እንደቦ በሚባለዉ ቦታ በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 56 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 29 ደቂቃ 35 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ አራት ድረስ፤

45.ከዚያም ሙሚት ቡል እንደርታይ አከባቢ በ14 ዲግሪ 03 ደቂቃ 33 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 31 ደቂቃ 26 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ አምስት ድረስ፤

46.ከዚያም በሰሜን አቅጣጫ ተከዜ ወንዝን ተከትሎ ከሱር ወንዝ ጋር በሚገናኙበት ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 11 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 39 ደቂቃ 25 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ስድስት ድረስ፤

47.ከዚያም በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 03 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 40 ደቂቃ 15 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ሰባት ድረስ፤

48.ከዚያም በእንዳጉሬዛ ላይኛዉ ጫፍ እንደዝባ አጠገብ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 17 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 40 ደቂቃ 29 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ስምንት ድረስ፤

49.ከዚያም ዓድዋ ወንዝ ካምፕ አጠገብ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 55 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 39 ደቂቃ 23 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ዘጠኝ ድረስ፤

50.ከዚያም እንደርታ ተራራ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 37 ደቂቃ 59 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ድረስ፤

51.ከዚያም ምቅልቃል እንዳ ገብረሳሙኤል በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 08 ደቂቃ 52 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 36 ደቂቃ 03 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ አንድ ድረስ፤

52.ከዚያም አትካሮ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 08 ደቂቃ 52 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 35 ደቂቃ 01 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ሁለት ድረስ፤

53.ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 38 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 33 ደቂቃ 31 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ሦስት ድረስ፤

54.ከዚያም ዝባን ማይ መፃዕ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 10 ደቂቃ 31 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 33 ደቂቃ 03 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ አራት ድረስ፤

55.ከዚያም ጨረር ቦዘይ በሚባለዉ ቦታ በ14 ዲግሪ 12 ደቂቃ 57 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 32 ደቂቃ 39 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ አምስት ድረስ፤

56.ከዚያም ጅጉሪ በሚባለዉ ላይ በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 22 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 33 ደቂቃ 01 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ስድስት ድረስ፤

57.ከዚያም በ14 ዲግሪ 18 ደቂቃ 00 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 32 ደቂቃ 50 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ሰባት ድረስ፤

58.ከዚያም ፀቢብ በሚለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 20 ደቂቃ 22 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 31 ደቂቃ 03 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ስምንት ድረስ፤

59.ከዚያም በ14 ዲግሪ 21 ደቂቃ 55 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 27 ደቂቃ 35 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ዘጠኝ ድረስ፤

60.ከዚያም ትክል ድንጋይ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 24 ደቂቃ 22 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 26 ደቂቃ 14 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስልሳ ድረስ፤

61.ከዚያም ታሒታይ ሙራጉዞ በሚባለዉ ላይ በ14 ዲግሪ 25 ደቂቃ 15 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 28 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስልሳ አንድ ድረስ፤

62.ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመጎዝ ጉልጉላ ወንዝን ተከትሎ ከተከዜ ወንዝ ጋር በመገናኘት፣ የተከዜ ወንዝን ተከትሎ በሕለጊን ሰሜንዊ ጫፍ ካለዉ ጉልት ቁጥር አንድ ጋር ይገጥማል፡፡

5. **<u>የፓርኩ አስተዳደር</u>**

1. ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 አንቀጽ 4 መሠረት ቃፍታ ሁመራ ወረዳ ውስጥ በሚያደራጀዉ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

6. **<u>የኮሚቴ አባላት</u>**

ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላቶች ይኖሩታል፡-

1. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር) ..... ሰብሳቢ፤
2. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር).......... አባላት፤
3. የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተወካዮች .......አባላት፤
4. የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች ............................................ አባላት፤
5. የፓርኩ አዋሳኝ ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች ..................አባላት፤
6. የፓርኩ ጎብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት አንድ ተወካይ......አባል፤
7. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ........................................................አባልና ፀሐፊ።

7. **<u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፓርኩ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤
2. በፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
3. ከፓርኩ ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን የፓርኩን ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፤ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፡፡

8. **<u>የኮሚቴዉ ስብሰባ</u>**

1. ኮሚቴው በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. **<u>የተከለከሉ ተግባራት</u>**

በዱር እንሰሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፦

1. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤
2. ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤
3. የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፡፡

10.<u>**አስተዳደራዊ ቅጣት**</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንሰሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል።
2. ባለሥልጣኑ ፓርኩ በሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል የሚገቡ የቤት እንስሳትን ስከት የሚጣል ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11.<u>**የመተባበር ግዴታ**</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አባሪ

## የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ ካርታ




**<u>ደንብ ቁጥር 336/2007</u>**

**<u>የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የስንቅሌ ቅርኬዎች መጠለያን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 336/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤
2. አዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ድንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
3. "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተክል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤
4. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ መሰየም**

የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ (ከዚህ በኋላ "መጠለያ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተሰይሟል።

4. **የመጠለያው ዳር ድንበር**

መጠለያ በምዕራብ አርሲ ዞን ሲራሮ ወረዳ እና በሲዳማ ዞን ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ዉስጥ በሚከተሉት አዋሳኝ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፦

1. በምዕራብ አርሲ ዞን ሲራሮ ወረዳ ዉስጥ፣

   ሀ/ በቂጤ ቱሲሳ አካባቢ ልዩ ስሙ ኦዳ ሰደን በሚባለዉ ቦታ ላይ በ07 ዲግሪ 12 ደቂቃ 24 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ በ38 ዲግሪ 18 ደቂቃ 40 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ የሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አንድ በመነሳት፤

ለ/ ከዚያም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የሚወስደዉ መንገድ በመከተል በቂጤ ቴሲሳ አከባቢ በ07 ዲግሪ 12 ደቂቃ 42 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 17 ደቂቃ 36 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር ሁለት ድረስ፤

ሐ/ ከዚያም በቂጤ ቴሲሳ እና በሰንበቴ ለንጮ መካከል በ07 ዲግሪ 12 ደቂቃ 20 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 03 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሦስት ድረስ፣

መ/ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ በሰንበቴ ለንጮ አካባቢ በ07 ዲግሪ 11 ደቂቃ 33 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 19 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አራት ድረስ፤

ሠ/ ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በታጠፍ በሎቄ ሲፎ አከባቢ በ07 ዲግሪ 11 ደቂቃ 23 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 19 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምስት ድረስ፤

ረ/ ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ በሎቄ ሲፎ አከባቢ በ07 ዲግሪ 09 ደቂቃ 18 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 32 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስድስት ድረስ፤

ሰ/ ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በቀላ ላሊማ አካባቢ በ07 ዲግሪ 08 ደቂቃ 50 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 24 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሰባት ድረስ፤

ሸ/ ከዚያም ከበከላ ካምፕ በስተጀርባ በ07 ዲግሪ 08 ደቂቃ 23 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 31 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስምንት ድረስ፤

ቀ/ ከዚያም በቀላ ላሊሞ አካባቢ በ07 ዲግሪ 08 ደቂቃ 12 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 17 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ዘጠኝ ድረስ፤

2. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ በሲዳማ ዞን በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ፡-

ሀ/ በሻመና ሰፈር እና በኬ ላሊማ ድንበር መካከል በ07 ዲግሪ 07 ደቂቃ 22 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 17 ደቂቃ 02 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስር ድረስ፤

ለ/ ከዚያም ልዩ ስሙ ሀዴሶ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ07 ዲግሪ 07 ደቂቃ 43 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና እና በ38 ዲግሪ 19 ደቂቃ 31 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከተተከለው ጉልት ቁጥር አስራ አንድ ድረስ፤

3. ከዚያም የጣጤሳን ሜዳ ወደ ዉ'ዮ በመተዉ በአኖሌና በሜጢ በማለፍ የጎዳ ሃሬን የገደል ጠርዝ በመከተል ከመነሻ ጉልት ቁጥር አንድ ጋር ይገጥማል፡፡

5. <u>የመጠለያዉ አስተዳደር</u>

1. ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 575/2000 አንቀጽ 4 መሠረት ሲራሮ ከተማ ውስጥ በሚያደራጀዉ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

6. <u>የኮሚቴ አባላት</u>

ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላቶች ይኖሩታል፡-

1. የመጠለያዉ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች(በየዓመቱ በመቀያየር) ..... ሰብሳቢ፤
2. የመጠለያዉ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች(በየዓመቱ በመቀያየር)..........አባላት፤
3. የመጠለያዉ አዋሳኝ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተወካዮች...አባላት፤
4. የመጠለያዉ አዋሳኝ ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች ................................... አባላት፤
5. የመጠለያዉ አዋሳኝ ወረዳ ሀገር ሽማግሌዎች.......................................አባላት፤
6. የመጠለያዉ አዋሳኝ ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች ............አባላት፤
7. የመጠለያዉ ጉብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት አንድ ተወካይ ............... አባል፤
8. የመጠለያዉ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ............................አባልና ፀሐፊ።

7. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የመጠለያዉ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤
2. የመጠለያዉ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
3. ከመጠለያዉ ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን የፓርኩን ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፤ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል፡፡

8. <u>የኮሚቴዉ ስብሰባ</u>

1. ኮሚቴው በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በዱር እንሰሳት ልማት፡ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፦

1. መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤
2. ለምግብ መያዣና ለመሳሰሉት ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤
3. የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፡፡

10. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 5(1) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንሰሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል።
2. ባለሥልጣኑ መጠለያዉ በሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል የሚገቡ የቤት እንስሳትን ስከት የሚጣል ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን 2007 ዓ/ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አባሪ የስንቅሌ ቆርኬዎች መጠለያ ካርታ



## ደንብ ቁጥር 337/2007

## የስሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ መሰየሚያ ደንብ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 4(2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የስሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 337/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ድንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
3. "ጉልት" ማለት ከጠንካራ ነገሮች ተሠርቶ የትሪጎኖሜትሪክ ነጥቦች የቅየሳ ዘዴ በድንበር ላይ የሚተክል ቋሚ የቅየሳ ምልክት ነው፤
4. "ባለስልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 575/2000 የተቋቋመው የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
5. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

3. **የስሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክን መሰየም**

በዱር እንስሳት ልመት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት "ሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ" ተብሎ ሲጠራ የነበረው ፓርክ ስሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ" ተብሎ (ከዚህ በኋላ "ፓርክ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተሰይሟል።

4. **የፓርኩ ዳር ድንበር**

ፓርኩ በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ዉስጥ በደባርቅ፣ በጃናሞራ፣ በአዲአርቃይ፣ በበየዳና በጠለምት ወረዳዎች ዉስጥ 412.0885 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት የሚሸፍን ሆኖ በሚከተሉት አዋሳኝ ሥፍራዎች ውስጥ ይገኛል፦

1. ከፓርኩ የመግቢያ በር ከሚገኘዉ ልዩ ስሙ ደጃች ኃይሉ በሚባለዉ ቦታ በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 29 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ በ37 ዲግሪ 58 ደቂቃ 24 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አንድ በመነሳት፤
2. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ጠፍር ማልፊያ በሚባለዉ ቦታ በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 11 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 59 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር ሁለት ድረስ፤
3. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በ13 ዲግሪ 11 ደቂቃ 57 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ37 ዲግሪ 59 ደቂቃ 30 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሦስት ድረስ፣
4. ከዚያም ልዩ ስሙ አማን አምባ በሚባለዉ በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 10 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 59 ደቂቃ 44 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አራት ድረስ፤
5. ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 29 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 00 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምስት ድረስ፤
6. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ምንጭ ብኝ በሚባለው በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 45 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 00 ደቂቃ 30 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስድስት ድረስ፤
7. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ አንጎባ ወንዝ ዳር በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 42 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 00 ደቂቃ 47 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሰባት ድረስ፤
8. ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ከአዲስጌ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ወረድ ብሎ በ13 ዲግሪ 11 ደቂቃ 08 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 01 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስምንት ድረስ፤
9. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ልዩ ስሙ ጥቁር ዉሃ በሚባለዉ ገደል አፋፍ ላይ በ13 ዲግሪ 11 ደቂቃ 51 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 02 ደቂቃ 09 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ዘጠኝ ድረስ፤

10. ከዚያም ልዩ ስሙ መጨቃ መንደሩን ወደዉጭ በመተዉ በ13 ዲግሪ 12 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 03 ደቂቃ 05 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስር ድረስ፤

11. ከዚያም ልዩ ስሙ መጨቃ በሚባለዉ ሥፍራ በ13 ዲግሪ 13 ደቂቃ 06 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና እና በ38 ዲግሪ 03 ደቂቃ 05 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ አንድ ድረስ፤

12. ከዚያም ልዩ ስሙ ድንጉሩ በሚባለዉ ሥፍራ በ13 ዲግሪ 13 ደቂቃ 26 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 03 ደቂቃ 34 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት ድረስ፤

13. ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ወደ ግጭ መገንጠያ ላይ በ13 ዲግሪ 13 ደቂቃ 45 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 04 ደቂቃ 02 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አሥራ ሦስት ድረስ፤

14. ከዚያም ልዩ ስሙ ቃባራስ በሚባለዉ ሥፍራ በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 08 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 04 ደቂቃ 44 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ አራት ድረስ፡

15. ከዚያም ለዉጤ መቀመጫ በሚባል ቦታ በ13 ዲግሪ 13 ደቂቃ 46 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 05 ደቂቃ 26 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት ድረስ፡

16. ከዚያም አይና ሜዳ ካምፕ አከባቢ በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 27 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 07 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘዉ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት ድረስ፤

17. ከዚያም በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 22 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 05 ደቂቃ 08 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት ድረስ፤

18. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የመኪና መንገድን ተከትሎ በመሄድ በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 43 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 01 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ስምንት ድረስ፤

19. ከዚያም የአርግንን አካባቢ በከፊል የፓርኩ አካል በማድረግ በ13 ዲግሪ 15 ደቂቃ 03 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 37 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ ድረስ፤

20.ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የከበሮ ምድርን በከፊልና ኪዳኔ ባዶን ሙሉ በሙሉ የፓርኩ አካል በማድረግ በለገዝ ራስ ላይ በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 53 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 50 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ድረስ፤

21.ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አቢድ ሠቃዉ አከባቢ በጥቁር ገደል ከበሮ ምድር ራስ ላይ በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 20 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 40 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አንድ ድረስ፤

22.ከዚያም ገጣቢት መንደርን የፓርኩ አካል በማድረግ ቅልጥም ሰባሪ በሚባለዉ አካባቢ አቢድ ሰቃዉ ላይ በ13 ዲግሪ 14 ደቂቃ 00 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድና በ38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 36 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሁለት ድረስ፤

23.ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫን በመታጠፍ የደባርቅና የጃናሞራ ወረዳዎች ድንበር ላይ ልዩ ስሙ ጭንቀት በተባለዉ ስፍራ በ13 ዲግሪ 13 ደቂቃ 23 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 09 ደቂቃ 04 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሦስት ድረስ፤

24.ከዚያም ልዩ ስሙ ቅልጥም ሰባሪት በሚባለዉ ሥፍራ የሽክታቴን ሜዳ አቋርጦ ብትኳ መንደር ላይ በ13 ዲግሪ 13 ደቂቃ 12 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 09 ደቂቃ 24 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አራት ድረስ፤

25. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የጥምርቅ መንደርን ወደ ዉጭ በመተዉ ልዩ ስሙ ነጋዴ ዋሻ በሚባለዉ ቦታ ላይ በ13 ዲግሪ 11 ደቂቃ 44 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 38 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አምስት ድረስ፤

26. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የደባርቅና የጃናሞራ ወረዳዎች የሚገናኙበትን ጥርጊያ መንገድ በማቋረጥ ልዩ ስሙ ጥምርቅ ራስ በሚባለዉ ቦታ በ13 ዲግሪ 10 ደቂቃ 55 ሰከንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 36 ሰከንድ ምስራቅ ሎንግቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ስድስት ድረስ፤

6. በ12° 36' 44.68" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 28' 52.03" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 36' 43.6" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 28' 51.31" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 36' 42.98" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 28' 50.05" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 36' 43.34" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 28' 48.4" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
10. በ12° 36' 43.99" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 28' 47.93" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

ሰ/ የመጥምቁ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን እምብርት ዞን ስፋቱ 0.29 ሄክታር ሆኖ፣

1. በ12° 36' 30.82" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 16.99" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 36' 30.6" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 17.4" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 36' 30.71" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 18.04" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

4. በ12° 36' 31.5" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 18.61" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 36' 32.33" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 16.99." ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 36' 32.69" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 17.71" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 36' 32.58" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 16.9" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
8. በ12° 36' 30.67" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 17.17" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

ሸ/ የዶሮ ቤት እምብርት ዞን ስፋቱ 0.29 ሄክታር ሆኖ፤

1. በ12° 37' 12.86" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 37' 12.25" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.78" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 37' 11.96" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.28" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 37' 11.93" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.88" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 37' 12.04" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.57" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 37' 11.93" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.41" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 37' 11.35" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.2" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 37' 10.24" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.77" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 37' 10.52" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.74" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
10. በ12° 37' 10.02" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.56" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
11. በ12° 37' 10.02" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.46" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
12. በ12° 37' 9.88" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.42" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
13. በ12° 37' 9.88" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.66" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
14. በ12° 37' 9.23" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.3" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
15. በ12° 37' 9.41" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.02" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
16. በ12° 37' 9.77" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.03" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
17. በ12° 37' 10.16" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.3" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
18. በ12° 37' 10.92" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.2" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
19. በ12° 37' 11.75" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.09" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
20. በ12° 37' 12.22" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.63" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
21. በ12° 37' 12.94" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.52" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

22.በ12° 37' 13.15" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.77" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
23.በ12° 37' 12.29" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 21.71" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
24.በ12° 37' 9.05" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.2" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
25.በ12° 37' 8.65" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 20.05" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
26.በ12° 37' 9.26" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 19.94" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
27.በ12° 37' 9.77" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 19.15" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
28.በ12° 37' 9.48" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 18.58" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

ቀ/ የፋሲለደስ መዋኛ እምብርት ዞን ስፋቱ 5.16 ሄክታር ሆኖ፡

1. በ12° 36' 59.04" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 24.23." ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 37' 1.49" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 23.04" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 37' 3.32" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 22.79" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 37' 7.75" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 23.58" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 37' 6.42" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 25.2" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 37' 7.03" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 30.28" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 37' 1.49" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 31.32" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 37' 0.52" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 30.89" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
9. በ12° 37' 59.33" ሰሜን ላቲትዩድ እና 37° 27' 27.11" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

5. <u>የቅርስ ቦታዎቹ ደጀን ዞኖች</u>

ሀ/ የአፄ ፋሲል ግቢና ራስ ግንብ ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (1) እና (2) የተመለከቱት እምብርት ዞኖች ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፦

1. በ12° 36' 53.53" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 18.19" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 36' 53.14" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 19.49" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 36' 52.96" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 19.96" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 36' 51.48" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 25.32" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 36' 49.25" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 24.53" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 36' 50.04" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 23.05" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

7. በ12° 36’ 48.82" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 21.79" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 36’ 44.71" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 20.93" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 36’ 43.99" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 20.17" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
10. በ12° 36’ 40.43" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 19.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
11. በ12° 36’ 37.58" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 18.55" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
12. በ12° 36’ 36.86" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 18.62" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
13. በ12° 36’ 34.34" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 18.26" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
14. በ12° 36’ 32.11" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 19.45" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
15. በ12° 36’ 28.01" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 19.24" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
16. በ12° 36’ 21.31" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 17.36" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
17. በ12° 36’ 16.63" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 14.7" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
18. በ12° 36’ 20.66" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 3.68" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
19. በ12° 36’ 23.65" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 4.44" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
20. በ12° 36’ 23.98" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 2.14" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
21. በ12° 36’ 26.46" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 3.79" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
22. በ12° 36’ 30.38" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 58.5" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
23. በ12° 36’ 40.18" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 5.7" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
24. በ12° 36’ 39.74" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 11.68" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
25. በ12° 36’ 42.84" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 42.84" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
26. በ12° 36’ 47.63" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 12.5" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
27. በ12° 36’ 51.66" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 15.35" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
28. በ12° 36’ 53.9" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28’ 16.79" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

ለ/ የቁስቋም ቤተመንግሥትና ቤተክርስቲያን ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (1) የተመለከተውን የእምብርት ዞን ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ

1. በ12° 37’ 14.54" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26’ 49.85" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 37’ 18.8" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 47.22" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 37’ 19.99" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 46.28" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

4. በ12° 37' 22.37" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 45.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 37' 23.92" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 45.17" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 37' 25.25" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 46.64" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 37' 25.61" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 50.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 37' 24.92" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 51.94" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 37' 24.46" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 52.94" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
10. በ12° 37' 22.87" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 52.94" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
11. በ12° 37' 22.87" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 53.41" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
12. በ12° 37' 20.6" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 54.53" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
13. በ12° 37' 19.45" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 55" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
14. በ12° 37' 17.4" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 55.18" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
15. በ12° 37' 16.72" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 26' 52.19" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ያሀፍራ ያካትታል፤

ሐ/ የጉዛራ ቤተመንግሥት ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (4) የተመለከተው እምብርት ዞን ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፦

1. በ12° 13' 59.09" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 54.3" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 13' 7.87" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 57.43" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 13' 9.1" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 59.7" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 13' 10.36" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 2.9" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 13' 5.64" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 8.99" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 13' 59.56" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 12.8" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 13' 58.22" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 5.64" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 13' 0.89" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 7.04" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 13' 0.89" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 4.78" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
10. በ12° 13' 53.58" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 37' 56.5" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለወዐን ሥፍራ ያካትታል።

መ/ የአጼ ሱሰንዮስ ቤተ መንግሥት ፍርስራሽና ማርያም ግቢ ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (5) በተመለከተው እምብርት ዞን ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፤፦

1. በ12° 11' 44.77" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 46.04" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 11' 44.81" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 46.08" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 11' 55.46" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 43.31" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 11' 57.8" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 39.35" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 11' 59.93" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 34.81" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 11' 38.8" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 47.12" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 11' 36.96" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 47.09" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 11' 35.12" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 46.26" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 11' 33.14" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 43.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
10. በ12° 11' 32.39" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 43.09" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
11. በ12° 11' 31.88" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 39.85" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
12. በ12° 11' 32.06" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 35.64" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
13. በ12° 11' 35.09" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 30.78" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
14. በ12° 11' 38.81" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 30.06" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
15. በ12° 11' 37.61" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 28.26" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
16. በ12° 11' 39.95" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 24.77" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
17. በ12° 11' 40.31" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 24.52" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
18. በ12° 11' 41.5" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 23.33" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
19. በ12° 11' 44.99" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 21.17" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
20. በ12° 11' 46.75" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 17.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
21. በ12° 11' 50.71" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 17.78" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
22. በ12° 11' 52.69" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 17.06" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
23. በ12° 11' 53.59" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 16.56" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
24. በ12° 11' 54.06" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 16.24" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
25. በ12° 11' 55.86" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 16.7" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
26. በ12° 11' 57.26" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 18" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
27. በ12° 11' 57.98" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 19.55" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
28. በ12° 11' 58.67" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 24.41" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
29. በ12° 11' 58.74" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 28.62" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

30.በ12° 11' 59.03" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 32.04" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
31.በ12° 11' 0.14" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 12' 34.31" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
መካከል ያለውን ስፍራ ያካትታል፡፡

ሠ/ ደብረብርሃን ሥላሴ ቤተክርስቲያን ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (6) በተመለከተው እምብርት ዞን ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፡-

1. በ12° 36' 46.4" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 47.39" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 36' 47.77" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 47.75" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 36' 48.74" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 48.72" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 36' 46.69" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 56.21" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 36' 36.97" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 51.42" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 36' 40.64" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 48.65" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 36' 48.74" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 47.86" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 36' 40.93" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 47.5" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
9. በ12° 36' 46.06" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 28' 47.1" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካልላል።

ረ. የመጥምቁ ዮሃንስ ቤተክርስቲያን ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (7) በተመለከተው እምብርት ዞን ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፣

1. በ12° 36' 29.48" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 16.52" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 36' 27.61" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 17.03" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 36' 28.87" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 20.09" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 36' 31.97" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 19.69" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 36' 33.66" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 19.55" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 36' 34.09" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 17.24" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 36' 34.74" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 15.44" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤እና
8. በ12° 36' 31.61" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27' 15.91" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

ሰ. የዶሮ ቤት የጋራ እና የፋሲል መዋኛ የጋራ ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 (8) እና (9) በተመለከቱት እምብርት ዞኖች ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፡-

1. በ12° 36’ 58.07" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 22.36" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
2. በ12° 36’ 54.14" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 22.75" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
3. በ12° 36’ 53.1" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 23.08" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
4. በ12° 36’ 48.13" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 26.03" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
5. በ12° 36’ 48.64" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 30.89" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
6. በ12° 36’ 45.72" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 34.78" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
7. በ12° 36’ 51.12" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 39.67" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
8. በ12° 37’ 0.37" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 32.18" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
9. በ12° 37’ 6.17" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 30.74" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
10. በ12° 37’ 6.96" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 30.6" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
11. በ12° 37’ 10.74" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 31.82" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
12. በ12° 37’ 11.68" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 31.61" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
13. በ12° 37’ 11.64" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 27.54" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
14. በ12° 37’ 9.08" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 23.94" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
15. በ12° 37’ 11.6" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 22.36" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
16. በ12° 37’ 13.04" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 21.74" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
17. በ12° 37’ 14.77" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 21.67" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
18. በ12° 37’ 14.84" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 21.56" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
19. በ12° 37’ 14.66" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 20.45" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
20. በ12° 37’ 12.65" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 19.8" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
21. በ12° 37’ 10.42" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 19.37" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤
22. በ12° 37’ 9.37" ሰሜን ላቲትዩድና 37° 27’ 18.07" ምሥራቅ ሎንግትዩድ፤

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

## ክፍል ሶስት

## ስለ ጎንደር አብያተ መንግሥታትና አብያተ ክርስትያናት ዓለም አቀፍ ቅርሶች ክልል ስፍራ አስተዳደር

6. <u>ስለ ክልል ስፍራው አስተዳደር</u>

1. ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 5 መሠረት በጎንደር ከተማ ውስጥ በሚያደራጀው የመካነ ቅርስ ጽሕፈት ቤት አማካይነት ክልል ሥፍራውን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጎንደር ዓለም አቀፍ ቅርሶች የክለላ ሥፍራ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

7. <u>የኮሚቴው አባላት</u>

1. ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

    ሀ. የጎንደር ከተማ ከንቲባ ............... ሰብሳቢ

    ለ. የጎንደር ዙሪያ ወረዳ አስተዳዳሪ ...... አባል

    ሐ. የሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር....... ተወካይ አባል

    መ. የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ...................... አባል

    ሠ. የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ኃላፊ ....................... አባል

    ረ. በጎንደር ከተማ የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች ....................አባላት

    ሰ. የጎንደር አካባቢ የሀገር ሽማግሌዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ሁለት ተወካዮች ...... አባላት

    ሸ. የጎንደር ከተማ የቤቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች ...........አባል

    ቀ. የጎንደር ከተማ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማህበር አንድ.... ተወካይ አባል

    በ. የመካነ ቅርሱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ...................................... አባልና ፀሐፊ

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች አካላትንም በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

8. <u>የኮሚቴው ስልጣንና ተግባሮች</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. በጎንደር ዓለም አቀፍ ቅርሶች አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በቅርስ አጠባበቅ ላይ የጐላ ተሳትፎ ስለሚያደርጉበትና ከአካባቢው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅትና ትስስር ስለሚፈጠርበት አግባብ ያመቻቻል፤

2. የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ እቅድ እና የእቅድ ክንውን በጋራ ያወጣል፣ ይገመንማል፣ ለባለስልጣኑ ከመቅረቡ በፊት መርምሮ የማሻሻያ አስተያየት ይሰጣል፤

3. ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችሉት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

9. <u>የኮሚቴው ስብሰባ</u>

1. ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው ውሳኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10. <u>ክልከላ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 42 (2) የተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፤ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 በተመለከቱት እምብርት ዞኖች ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፦
   ሀ/ በቅርሶቹ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካሎችንና ከፍተኛ ጨረር አመንጪ መሣሪያዎችን መጠቀም፣
   ለ/ ጥናትና ምርምርን ጨምሮ ማንኛውንም በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ሥራ ማከናወን፣
2. በአዋጁ አንቀጽ 42 (2) የተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 በተመለከቱት ደጀን ዞኖች ውስጥ በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን የተከለከለ ነው፦
   ሀ/ የቅርሱን የእይታ ትስስር እና የላቀ ሁለንተናዊ እሴት የሚጎዳ የህንፃ ግንባታ
   ለ/ ከፍተኛ ኃይል ተሸካሚና አስተላላፊ የኤሌክትሪክና የስልክ ምሰሶዎች ተከላ፣
   ሐ/ የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች ግንባታ፤
   መ/ የማዕድን ማውጣትና ቁፋሮዎች፤
   ሠ/ በቅርሶቹ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ዛፎችን መትከል።

11.<u>የባለስልጣኑን ፈቃድ ስለማግኘት</u>

በደጀን ዞኖች ውስጥ የሚፈቀዱ ተግባራትን ለማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑን ማማከርና ይሁንታ ማግኘት አለበት፡፡

12.<u>አስተዳደራዊ መቀጫ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በቅርሶችና በቅርስ ክለላ ስፍራዎች ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በደረሰው ጉዳት ልክ አስተዳደራዊ መቀጫ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

13.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከጽህፈት ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

14.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**



የጎንደር አብያተ • መንግስታትና አብያተ - ክርስትያናት ዓለም - አቀፍ ቅርስ
THE GONDAR CASTLES AND CHURCHES WORLD HERITAGE SITE
Lay Armachiho
Wegera
Denbia
Gonder Zuria
Legend
GONDAR CASTLES AND CHURCHES
GONDER TOWN
WORLD HERITAGE SITE
አማራ ክልል
AMHARA REGION
Legend
MAP OF ETHIOPIA
AMHARA REGION



FASIL GHEBBI, RAS GINB AND DEBRE BERHAN SELASSIE CHURCH HERITAGE SITE
RAS GINB HERITAGE SITE
DEBRE BERHAN SELASSIE CHURCH HERITAGE SITE
FASIL GHEBBI HERITAGE SITE
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
ጎንደር ከተማ
GONDAR TOWN
Legend
GONDAR_TOWN


QUSQUAM,DORO BIET AND FASILEDES SWIMMING POOL HERITAGE SITE
QUSQUAM HERITAGE SITE
DORO BIET HERITAGE SITE
FASILEDES SWIMMING POOL HERITAGE SITE
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
GONDAR TOWN
Legend
GONDAR_TOWN


የጉዛራ ቤተ-መንግሥት
መካነ-ቅርስ
THE CASTLE OF GUZARA
HERITAGE SITE
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
ደበሳን ጠቅራ ወረዳ
DEBSAN TIKIRA WEREDA
Debsan tikara



አፄ ሱስኒዮስ ቤተ-መንግሥት ፍርስራሽና
ማርያም ግቢ መካነ - ቅርስ
THE RUINED CASTLE OF EMPEROR
SUSENYOS & MARIAM GHEBBI
HERITAGE SITE
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
Meters
Lay Armachew
Wegera
Chilga
Gondar Town
Merab Belesa
Demba
Gondar Z
Libokemkem
Takusa
Mange
Alefa


የመጥምቁ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን
መካነ -ቅርስ
JOHN THE BAPTIST CHURCH
HERITAGE SITE
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
332000
332200
1394400
1394300
ጎንደር ከተማ
GONDAR TOWN
Legend
GONDAR_TOWN
314000
318000
322000
326000
330000
334000
338000
342000
346000
350000
354000

መ/ ስፖርት

# አዋጅ ቁጥር 729/2004 ዓ.ም

# የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር አዋጅ

ህብረተሰቡ በሚኖርበት፣ በሚማርበትና በሚሰማራበት አካባቢ በስፖርት እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለዚህም አላማ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉ እና እንዲጠበቁ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የስፖርት ማዘውተሪያ በየአካባቢው በብዛት እና በጥራት መኖር የህብረተሰቡን በተለይም የወጣቱን ጤንነት ለመጠበቅ፣ አካል ለመገንባት፣ አዕምሮ ለማበልፀግ እና ለሀገር እድገት አስተዋፆ እንዲይበረክቱ የሚያስችል በመሆኑ፤

ስፖርት ለታሰበለት ዓላማና ግብ እንዲውል ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚቋቋሙበት፣ የሚተዳደሩበትን፣ ቁጥጥር የሚደረግበትን እና ሕጋዊ ጥበቃ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 729/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ስፖርት" ማለት ማንኛውም ሰው ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ ለመዝናናት፣ አካሉን ለመገንባትና አዕምሮውን ለማበልፀግ እንዲሁም አቅምና ችሎታውን ለመመዘን በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ ሁኔታ የሚያከናውነውን ማናቸውንም የአካል እንቅስቃሴ ያጠቃልላል፤
   2. "የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ" ማለት ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ ሥልጠና፣ ውድድር፣ መዝናኛ ወይም ለስፖርታዊ በዓል ማከናወኛነት እንዲውል የተዘጋጀ ማንኛውም ሥፍራ ነው፤
   3. "የመሰናዶ ሥራ" ማለት ማንኛውም ሰው ለደንበኞች አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የሚያከናውነው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን የመገንባት

ወይም ሌላ ግንባታን ወደ ስፖርት ማዘውተርያ ስፍራነት መለወጥ እና አስፈላጊ የስፖርት ጥቆችንና መሣሪያዎችን የማሟላት ሂደት ነው፤

4. "ኮሚሽን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 692/2003 የተቋቋመው የስፖርት ኮሚሽን ነው፤[18]
5. "አግባብ ያለው አካል" ማለት እንደ አግባቡ ኮሚሽኑ ወይም የስፖርት ጉዳይን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤
6. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
7. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
8. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በማንኛውም ግለሰብ መኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኙ ለንግድ ዓላማ በማይውሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 4. <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች</u>

1. ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለታቀደለት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉትን መሠረታዊ መሥፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡
2. የስፖርት ውድድሮችን የሚያስተናግዱ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት ይመደባሉ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን መሥፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የሚሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በደረጃ አንድ ይመደባሉ።

[18] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9 (25) መሠረት የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ስለሆነ በዚህ አዋጅ ዉስጥ በዚሁ መሠረት ይነበብ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን መሥፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ አገር አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የሚሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በደረጃ ሁለት ይመደባሉ።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን መሥፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ ክልል አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የሚሆኑ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በደረጃ ሦስት ይመደባሉ።

6. የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እንደየደረጃቸው ማሟላት ያለባቸው ዝርዝር መሥፈርቶች ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

## 5. ፍቃድ ስለማስፈለጉ

1. የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ የመሰናዶ ሥራ ለማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ/ በደረጃ አንድ ወይም ሁለት ለሚመደብ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ከኮሚሽኑ፤ ወይም

   ለ/ ከደረጃ አንድ ወይም ሁለት በስተቀር ለሌሎች የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች አግባብ ካለው የክልል አካል፤

   ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2. ማንኛውም ሰው እንደሁኔታው ከኮሚሽኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው የመሰናዶ ሥራው የተጠናቀቀለትን የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር አይችልም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን ለንግድ ዓላማ ማዋል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል የንግድ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

## 6. ስለማመልከቻ አቀራረብ

1. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ማቋቋምና አገልገሎት መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የመሰናዶ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ፈቃድ እንዲሰጠው አግባብ ላለው አካል ማመልከት አለበት፡፡

2. አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራውን ፕላንና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

3. አመልካቹ የመሰናዶ ስራውን ሲያጠናቅቅ ስለሥራው አፈፃፀም አግባብ ላለው አካል በጽሑፍ ሪፖርት በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት አለበት፡፡

7. **<u>ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

1. አግባብ ያለው አካል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ሲያምንበት ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የመሰናዶ ሥራ ለመጀመር የሚያስችል ፈቃድ ይሰጠዋል፤

ለ/ አመልካቹ የመሰናዶ ሥራውን ሲያጠናቅቅ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራው በፕላኑ መሠረት ደረጃውን ጠብቆ የተሰናዳ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) መሠረት በኮሚሽኑ ለሚሰጥ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው የአገልግገሎት ክፍያ መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) እና (ለ) መሠረት አግባብ ባለው የክልል አካል ለሚሰጥ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በክልሉ ይወሰናል፡፡

8. **<u>ስለስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች አጠቃቀም</u>**

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በትርጉሙ ለተመለከቱት ዓላማዎች፣ ለማኅበራዊ ፌስቲቫሎች እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ለሚዘረዘሩ ሌሎች ተዛማጅ ዓላማዎች ብቻ የሚውሉ ይሆናል፡፡

9. **<u>የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከልሎ ስለመያዝ</u>**

1. ማንኛውም የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ለስፖርት ማዘውተሪያነት የሚውሉ ስፍራዎችን በገጠሩ እንደ ህዝቡ አሰፋፈር ወይም በከተማ በማስተር ፕላን መሠረት ከልሎ መያዝ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የትምህርት ተቋም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የተመለከተውን ደረጃ የሚያሟላ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

3. ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆን አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሲከለሉ፣ በፕላን ውስጥ ሲካተቱ እና ሲቋቋሙ ኮሚሽኑ አስፈላጊውን የቴክኒክ ምክር ይሰጣል፡፡

10.<u>ስለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሕጋዊ ጥበቃ</u>

1. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለሕዝብ ጥምቅ ሲባል በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊወሰዱ አይችሉም።

2. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ በቅድሚያ ለባለንብረቱ ተመጣጣኝ ካሣ መከፈል እና በተወሰደው ቦታ ምትክ ሌላ ቦታ መሰጠት አለበት፡፡

11.<u>ቅጣት</u>

በወንጀል የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር።

1. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን ያለፈቃድ የሚያቋቁም ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖር አገልግሎት የሚሰጥ ወይም ከተፈቀዱ ዓላማዎች ውጭ የሚጠቀም ማንኛውም ሰው ከአንድ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 25,000 እስከ ብር 50,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

2. በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ውስጥ ሁከት ሊያስነሳ የሚችል ድርጊት የሚፈጽም ማንኛውም ሰው ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 25,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

3. በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ውስጥ፡-

ሀ/ የአልኮል መጠጥ የሚጠቀም፤

ለ/ ሲጋራ ወይም ሲጋራ ነክ የሆኑ ነነገሮችን፣ የአልኮል መጠናቸው ከ12 በመቶ በላይ የሆኑ መጠጦችን ወይም ለመልካም ሥነ-ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ወይም በሕግ የተከለከሉ ሌሎች ነገሮችን የሚያስተዋውቅ፤ ወይም

ሐ/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚከለከሉ ሌሎች ድርጊቶችን የሚፈጽም፤ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር 5,000 እስከ ብር 10,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

12.<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጸ 11 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በሚተላለፉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የማገድና የመዝጋት አተዳደራዊ እርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ መውሰድ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ምክንያት የሚሆኑ ዝርዝር ሁኔታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ።

13.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋመ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አግባብ ያለው አካል በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

14.<u>ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

15.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ኮሚሽኑ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

16.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# ክፍል አስራ ስምንት

## መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት

### ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት

## አዋጅ ቁጥር 621/2001

## የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት የተረጋገጠውን የዜጎች የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁለንተናዊ ዕድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፤

   1. "የበጀት አመት" ማለት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ወይም በግሪጎሪያን አቆጣጠር ከጀንዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 31 ያለው ጊዜ ነው፤
   2. "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማህበር" ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረተ የተመሰረተ፣ ሁሉም አባላቱ ኢትዮጵያውያን የሆኑ፣ የገቢ ምንጩ ከኢትዮጵያ የሆነና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት ነው። ነገር ግን የገቢያቸውን ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀሙ ከሆነ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሆነው ሊቆጠሩ ይችላሉ፤

3. “የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት” ወይም “የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር” ማለት ሁሉም አባላቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ፣ ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀም እና በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤

4. “የዉጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት” ማለት በውጭ ሕግ መሰረት የተቋቋመ ወይም የውጭ ዜጎች በአባልነት ያሉበት ወይም ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ የሚጠቀም ወይም የውጭ ዜጎች የሚቆጣጠሩት የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፤

5. “የብዙሃን ማህበራት” ማለት የሙያ ማህበራትን፣ የሴቶች ማህበራትን፣ የወጣት ማህበራትንና ሌሎች ተመሳሳይ የኢትዮጵያ ማህበራትን ያካትታል፡፡

6. “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትሕ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤[19]

7. “የሥራ መሪ” ማለት ኦዲተርን ሳያካትት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የእለት ተእለት አስተዳደር በአጠቃላይ የሚቆጣጠር እና የሚመራ ሰው ነው፤

8. “ሰዉ” ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

9. “የሥራ ቦታ” ማለት የአንድ ሰው ሠነዶችና የሂሣብ መዛግብት የሚቀመጡበት ወይም አንድ ሰው ሥራውን የሚያካሂድበት ቦታ ነው፤

10. “ሕዝባዊ መዋጮ” ማለት በሕዝባዊ ወይም በሥራ ወይም በመኖሪያ ቦታዎች በመሄድ የሚገኘውን ገቢ ለበጎ አድራጎት ተግባሮች እንዲያውለው ገልጾ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት በዋጋ ወይም በነጻ ለማሰባሰብ የሚደረግ ጥሪ ማለት ሲሆን ለሀይማኖት ወይም ለቀብር አገልግሎት በዋለ መሬት ወይም ሕንግ ወይም አጠገባቸው ባለ መሬት ላይ የሚደረግ ጥሪን አያጠቃልልም፤

11. “መተዳደሪያ ደንብ” ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የተቋቋመባቸዉን ወይም ሲያራምዳቸው የሚችሉ ዓላማዎች ወይም ሀብቱን በሥራ ላይ የሚያውልባቸዉ መንገዶችን፣ የአባልነት እና የአመራር ቦታዎችን ለማግኘት የሚያበቁ መመዘኛዎችን፣ የአመራር ቦታ በሹመት ወይም በምርጫ የሚሰጥበት

[19] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 38(3)(ሐ) መሠረት የፌደራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ስለሆነ በዚህ አዋጅ ዉስጥ በዚሁ መሰረት ይነበብ ::

መንገድ፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚተዳደርበት እንዲሁም ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚሻሻሉበት መንገድና ሁኔታን ያጠቃልላል፤

12. “የዘርፍ አስተዳዳሪ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 የተሰየመ የፌዴራል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ነው፤

13. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲምክራስያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ነው፤

14. “አስተዳደራዊ ወጪ” ማለት ለደመወዝ፣ ለአበል፣ ለጥቅማ ጥቅም፣ ለዕቃዎችና ለአገልግሎቶች ግዥ፣ ለጉዞ እና ለመስተንግዶ የሚወጡ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ለማህበሩ አስተዳደራዊ ሥራዎች አስፈላጊ የሆነ ወጪ ነው፡፡

15. “ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ” ማለት ከውጭ አገር የሚደረግ የማንኛውም ዕቃ ወይም ገንዘብ ወይም ዋስትና ስጦታ፣ ክፍያ ወይም ማስተላለፍ ነው፡፡ የውጭ ምንጭ ማንኛውንም የውጭ አገር መንግሥት፣ ኤጀንሲ ወይም ካምፓኒ፣ ዓለም አቀፍ ኢጀንሲ ወይም ማንኛውንም በውጭ አገር ያለ ሰው ያካትታል።

16. “የሃይማኖት ድርጅት” ማለት የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት እና ለማስፋፋት የሚያቋቁሙት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ትርጓሜ የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ለማሳካት የተቋቋሙ ድርጅቶችን ወይም የሃይማኖት ድርጅቱ የሚያቋቁማቸው የበጎ አድራጎ ድርጅቶችን አያጠቃልልም።

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

ሀ/ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ወይም የአባላት ጥንቅራቸው ከአንድ ክልል በላይ በሆኑ ማህበራት፣

ለ/ በአንድ ክልል ብቻ የሚሠሩ ቢሆንም በውጭ አገር በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፣

ሐ/ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፡፡

2. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚነት አይሆንም፤

ሀ/ በሃይማኖት ድርጅቶች፤

ለ/ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍና የውጭ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት፤

ሐ/ በዕድር፣ በዕቁብ እና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ማሕበራት፤ እና

መ/ በሌላ ሕግ በሚሸፈኑ ማህበራት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የበጎ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ኤጀንሲ

4. መቋቋም

1. የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

5. የኤጀንሲዉ አላማዎች

ኤጀንሲዉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲስፋፉና ተልዕኳቸውን በሕግ መሠረት እንዲወጡ ማስቻልና ማበረታታት፤
2. የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሲሆን የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር፤
3. የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በሕግ መሠረት መስራታቸውን ማረጋገጥ።

6. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት

1. ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

   ሀ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ፈቃድ መስጠት፣ መመዝገብና መቆጣጠር፤

   ለ/ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የተሻለ አሠራር እንዲኖራቸው ማበረታታት፣

   ሐ/ ከሥልጣንና ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ ማሰራጨት፤

መ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ምዝገባ በሚመለከት መረጃ በጋዜጣ ማሳተምና ማሰራጨት፤

ሠ/ የመንግሥት አካላት እና የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት የሚሳተፉባቸውን የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፤

ረ/ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችል የዉሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

ሰ/ ለምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርቡ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ጉዳይ ከሚመለከተው ዘርፍ አስተዳዳሪ ጋር በመመካከር መርምሮ መወሰን፤

ሸ/ በአዋጅ ቁጥር 334/1995 (እንደተሻሻለዉ) ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዘለቄታ በጎ አድራጎት እና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሰነዶችን ማረጋገጥና መመዝገብ፤

ቀ/ ለሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች በመንግሥት በሚጸድቀው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፤

በ/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

ተ/ አስፈላጊ ሆኖ ሊያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በውክልና መስጠት፤ እና

ቸ/ ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሸ) የተመለከተው ቢኖርም ሚኒስትሩ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽህፈት ቤት በኤጀንሲው ቅጥር ግቢ ቅርንጫፍ እንዲከፍት ወይም ሠራተኞቹን እንዲመድብ ሊያዝ ይችላል፡፡

## 7. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፣

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ (በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤
2. በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣ እና
3. አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

## 8. <u>የቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከሚሰየሙ የቦርድ አባላት መካከል ሁለቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ከማህበራት የተውጣጡ ይሆናሉ።

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
2. የበጐ አድራጐት ድርጅቶች እና ማህበራት አስተዳደርን በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል፤

3/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞችን መርምሮ ይወስናል፤

4/ በዚህ አዋጅ መሠረት በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፤

5/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡለትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መርምሮ ይወሰናል፡፡

10. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በቦርዱ ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል፡፡
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተሰጡትን ሥልጣንና በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሰረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ ደንብ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የኤንጀሲውን የሥራ መርሐ ግብርና በጀት ያዘጋጃል በሚኒስቴሩ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ መርሐ ግብር መሠረት ገንዘብ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚደረጉ ማናቸውንም ግንኙነቶች በተመለከተ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

3. ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

12. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

13. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየመቱ ይመረመራሉ፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶች</u>

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

14.<u>ትርጓሜ</u>

1. "የበጐ አድራጐት ድርጅት" ማለት ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ የተቋቋመና ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡
2. "የበጎ አድራጎት ዓላማ" የሚከተሉተን ያካትታል፤

ሀ/ ድህነትን ወይም አደጋን መከላከል፣ መቀነስ ወይም ማስወገድ፤

ለ/ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት እና የአካባቢ ጥበቃን ወይም ማሻሻልን ማፋጠን፤

ሐ/ የእንስሳት ደሕንነትን ማስፋፋት፤

መ/ ትምህርትን ማስፋፋት፤

ሠ/ ጤንነትን ወይም ሕይወት ማዳንን ማራመድ፤

ረ/ ጥበብን፣ ባሕልን፣ ቅርስን ወይም ሣይንስን ማዳበር፤

ሰ/ አማተር ስፖርትንና የወጣቶችን ደህንነት ማስፋፋት፤

ሸ/ በዕድሜ፣ በአካል እና በአዕምሮ ጉዳት፣ በገንዘብ ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተቸገሩትን መታደግ፤

ቀ/ የአገሪቱን የረጅም ጊዜ የልማት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማበረታታት፤

በ/ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፤

ተ/ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የሃይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፤

ቸ/ የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፤

ኀ/ የግጭት አፈታትን ወይም ዕርቅን ማስፋፋት፤

ነ/ የፍትህና የህግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር፤

ኘ/ ሌሎች ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገጉ ዓላማዎች፤

3. ሕዝባዊ ጥቅም ይኖራል ተብሎ የሚቆጠረው፡-

ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማዎች አንድ ተለይቶ የሚታወቅ ጥቅም ለሕዝቡ የሚያስገኙ ሲሆን፣

ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማዎች ሲጠቀሙ የሚገባቸውን ሰዎች የማያገሉ ሲሆን፣ እና

ሐ/ ለግለሰቦች ወይም ለድርጅቶች የሚያስገኘው የግል ጥቅም የድርጅቱ ዋና የሥራ ዓላማ በመሆኑ ሣይሆን በአጋጣሚ እና ድርጅቱ ዓላማውን በሚያሳካበት ጊዜ በተቀፅላነት የተገኘ ሲሆን፣

ብቻ ነው፡፡

4. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ዓላማዎችንና የህዝብ ጥቅምን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (በ)፣ (ተ)፣ (ቸ)፣ (ኘ)፣ እና (ነ) በተመለከቱት የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ላይ መሰማራት የሚችሉት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ብቻ ይሆናሉ።

15. <u>የበጐ አድራጐት ድርጅት ዓይነቶች</u>

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት፣

ሀ/ የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት፤

ለ/ የበጐ አድራጐት ተቋም፣

ሐ/ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት፣ ወይም

መ/ የበጐ አድራጐት ማህበር፣

ሆኖ ሲመሰረት ይችላል፡፡

2. በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አምስት ስለበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ሥራ ለመሠማራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አንዱን መመሥረትና በቅድሚያ የፈቃድና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሥራቸውን የሚያስተባብር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ ኤጀንሲው በሚያወጣው ዝርዝር መሰረት ይወሰናል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የዘለቄታ በጐ አድራጐት ድርጅት</u>

16. <u>ትርጓሜ</u>

"የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት አንድ የተለየ ንብረት በስጦታ ወይም በኑዛዜ ወይም በኤጀንሲዉ ትዕዛዝ በዘላቂነትና በማይመለስ ሁኔታ ለበጐ አድራጐት ዓላማ ብቻ የሚዉልበት ነው፡፡

17. ለ<u>ምዝገባ ስለማመልከት</u>

1. መሥራቹ በሕይወት ያለ ከሆነ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባ የሚጠየቀው በመሥራቹ በራሱ ወይም ለዚህ ጉዳይ በወከለው ሰው ብቻ ነው፡፡

2. መሥራቹ ከሞተ በኋላ ጥያቄው የሚቀርበዉ መሥራቹ አደራ በሰጠዉና ይህን በተቀበለው ሰው ወይም የመሥራቹን ኑዛዜ በሚያስፈጽሙ ሰዎች ነው፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱት ሰዎች በማይኖሩበት ጊዜ ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ውል ያዘጋጁ፣ ምስክር የሆኑ ወይም ውሉን በአደራ ያስቀመጡ ሰዎች የምዝገባ ጥያቄ ያቀርባሉ።
4. በዚህ አንቀጽ መሠረት ምዝገባ የመጠየቅ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ምዝገባውን ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ መሥራቹ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በማንኛውም ይመለከተኛል በሚል ሰው አመልካችነት ወይም በኤጀንሲው አነሳሽነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡
5. ኤጀንሲው የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከፈለጉ ሊጠቀሙ የሚችሉባቸውን ሞዴል መተዳደርያ ደንቦችን ያዘጋጃል።

18. ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባርን መሻር

1. ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባር በኤጀንሲው ከመመዝገቡ በፊት መሥራቹ ሊሽረው ይችላል፡፡
2. የመሥራቹ ወራሾች የመሻር መብታቸውን ሊጠቀሙ የሚችሉት የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ እንዲመዘገብ ለኤጀንሲው ጥያቄ በቀረበ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ሳይመዘገብ ከቀረ ነው፡፡

19. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች አደረጃጀት

ማናቸውም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች ይኖረዋል፡፡

20. የሥራ አመራር ቦርድ ጥንቅር

1. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በመሥራቹ ወይም እርሱ በወከለው ሰው ካልተሾሙ ኤጀንሲው የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡
2. የቦርዱ አባል በማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል።
3. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር በምንም ዓይነት ሁኔታ ከሦስት በታች ሊሆን አይችልም።

21.የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ አካል ይሆናል፤

2. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን የሚመራ ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ያሰናብታል፤ እና

3. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ያስተዳድራል።

22. የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎች

1. የሥራ አመራር ቦርዱ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ይሰበሰባል፡፡

2. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ውሣኔዎችን የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡

23. ለቦርዱ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች

1. በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ወይም በማናቸውም ሕግ ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የቦርድ አባል ምንም ክፍያ አያገኝም።

2. በቦርድ ስብሰባ ላይ ለመገኘት አንድ አባል ያወጣውን ለመሸፈን የሚደረግ የወጪ ማካካሻ እንደ ክፍያ አይቆጠርም፡፡

24. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባራ

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣

1. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሥራ ይመራል፣ ድርጅቱን በመተዳደርያ ደንቡ መሠረት ያስተዳድራል፤

2. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤

3. የሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

4. የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራና የሂሣብ ሪፖርቶችን ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፤

5. የድርጅቱን ገቢ የሚያሳድጉ ሁኔታዎችን ያጠናል፣ በሥራ አመራር ቦርዱ ሲጸድቁ ተግባራዊ ያደርጋል፤

6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ ስም በተከፈቱ የባንክ ሂሣቦች ላይ ይፈርማል፤

7. ሌሎች በስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ተያያዥ ተግባራት ያከናውናል።

25. የኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት

ኦዲተሩ፣

1. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤
2. የድርጅቱን የጡስጥ ኦዲት ሪፖርት በኢትዮጵያ ተቀባይነትን ባገኘ መመዘኛ መሠረት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።
3. በዚህ አዋጅ የውጭ ኦዲተርን በተመለከተ የተደነገገው ቢኖርም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በማናቸውም ጊዜ የውጭ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል፡፡

26. <u>ተጠቃሚዎችን ስለመወሰን</u>

መሥራቹ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ ቦርዱ ከመሥራቹ ሃሣብ ጋር ይስማማል ብሎ በሚገምተጡ መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስን ይችላል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

## <u>የበጎ አድራጎት ተቋማት</u>

27. <u>የበጎ አድራጎት ተቋም</u>

1. የበጎ አድራጎት ተቋም ቁጥራቸው ቢያንስ ሶስት በሚደርሱ ሰዎች ለበጎ አድራጎት ተግባራት ብቻ የሚቋቋም የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፡፡
2. የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅትን አደረጃጀት የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ከአስፈላጊ ማስተካከያ ጋር ለበጎ አድራጎት ተቋም አደረጃጅትም ተፈጸሚ ይሆናሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ የበጎ አድራጎት ተቋሙ አደረጃጀት በዚህ አዋጅ ክፍል አራት ስለማህበር አደረጃጀት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት እንዲመራ ሲደነግግ ይችላል፡፡

28.<u>የአባላት ሃላፊነቶች እና ግዴታዎች</u>

1. እያንዳንዱ የበጎ አድራጎት ተቋም አባል ወይም አዲስ አባል ድርጅቱ እርሱ አባል በነበረበት ጊዜ ወይም አባልነቱ ካበቃ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሲፈርስ አባልነቱ ከማብቃቱ በፊት ለነበሩት የድርጅቱ ዕዳዎች እና ሃላፊነቶች እንዲሁም ድርጅቱን ለማፍረስ የሚያስፈልጉ የአገልግሎት ዋጋዎችንና ወጭዎችን ለመሸፈን ከተወሰነ ጣሪያ በላይ ያልሆነ ዋስትና መግባት ይኖርበታል፡፡
2. ኤጀንሲው የበጎ አድራገዐት ተቋማት ለምዝገባ በሚቀርቡበት ወቅት ዋስትና ሊሰጡ የሚገባቸውን አነስተኛ የገንዘብ መጠን በመመሪያ መወሰን ይችላል፡፡

29.<u>ለምዝገባ ስለማመልከት</u>

የበጐ አድራጎት ተቋም የማቋቋም ዓላማ ያላቸው ሰዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68 በተደነገገው መሠረት ለመመዝገብ ለኤጀንሲው ማመልከት አለባቸው።

## ንዑስ ክፍል

## የአደራ በጐ አድራጎት ድርጅቶች

### 30. ትርጓሜ

"የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በሚያቋቁመው ሠነድ መሠረት አንድ የተለየ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ እንዲውል በአደራ ጠባቂዎች የሚተዳደር ድርጅት ነው፡፡

### 31. አመሰራረት

1. የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት በስጦታ ወይም በኑዛዜ ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ ሊቋቋም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ስጦታ ወይም ኑዛዜ አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል፡፡
3. በስጦታ ወይም ኑዛዜ ውስጥ የሚገኙ በተዘዋዋሪ አመልካች አንቀጾች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ለማቋቋም በቂ ይሆናሉ።

### 32. የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት ቀጣይነት

1. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ለተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፡፡ ሆኖም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢ ከሚያስገኙ ሥራዎች ከሕዝባዊ መዋጮ ወይም ከማናቸውም ምንጭ ያገኛቸው ሃብት ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አይወጣም።
2. ላልተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ዘላቂና የማይሻር ይሆናል፡፡
3. የአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ገቢ ከሚያስገኙ ሥራዎች፣ ከሕዝባዊ መዋጮ ወይም ከማናቸውም ምንጭ ያገኛቸውን ሃብት በተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

### 33. በአደራ ጠባቂዎቹ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ

1. የአደራ በጐ አድራጎት ድርጅት መስራች የሆነው ሰው አደራ ጠባቂዎቹን መሾም አለበት፡፡ እነዚህ አደራ ጠባቂዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 በተደነገገው መሠረት የፈቃድና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለኤጀንሲው የምዝገባ ጥያቂ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2. አደራ ጠባቂዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት በተቋቋመ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ጥያቂ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

3. አደራ ጠባቂዎቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም ኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትት ማናቸውንም ድርጊት መፈፀም አይችሉም፡፡

34. <u>የአደራ ጠባቂዎች ብዛት</u>

1. የአደራ ጠባቂዎች ብዛት በማናቸውም ምክንያት ከ2 ያነሰ እና ከ5 የበለጠ ሊሆን አይችልም፡፡ ከ3 ያነሱ ሰዎች ተጠቅሰው ከሆነ ይህን መመዘኛ ለማሟላት ኤጀንሲው ቀሪዎቹ የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

2. ከ5 በላይ አደራ ጠባቂዎች ተጠቅሰው ከሆነ መሥራት የሚችሉና ፈቃደኝነት ያላቸው በቅድሚያ የተጠቀሱት 5 ሰዎች ብቻ አደራ ጠባቂ ይሆናሉ። ቀሪዎቹ ሰዎች ክፍት ቦታዎች ተፈጥረው ካልተሾሙ በስተቀር አደራ ጠባቂ ሊሆኑ አይችሉም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት አደራ ጠባቂዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ከሆኑ የአደራ ጠባቂዎች ብዛት ከሦስት በታች እንዲሆን አጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሚሾሙት አደራ ጠባቂዎቹ ቢያንስ አንዱ መደበኛ ቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ መሆን አለበት፡፡

35. <u>**የአደራ ጠባቂዎች አሿሿም**</u>

1. አደራ ጠባቂውን የሚሾመው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ያቋቋመው ሰው ወይም እርሱ የወከለው ሰው ነው። እነዚህ ሰዎች ከሌሉ ኤጀንሲው አደራ ጠባቂው የሚሾምበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

2. የተሾመው አደራ ጠባቂ ውክልናውን አልቀበልም ካለ ወይም በማናቸውም ምክንያት አደራ ጠባቂነቱን ማከናወን ካልቻለ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት አዲስ አደራ ጠባቂ ይሾማል፡፡

36. <u>**የበጎ አድራጎት ድርጅትን በአደራ በጠባቂነት መሾም**</u>

1. የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅት የሚያቋቁም ሰው የበጐ አድራጐት ድርጅትን በአደራ ጠባቂነት ከሾመ የተሾመው ድርጅት ስራ መሪዎች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ያስተዳድራሉ፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የበጐ አድራጐት ድርጅት የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን በኑዛዜው፣ በስጦታው ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ በተወሰነው መሠረት ከሌሎች ስጦታዎች ወይም ዓላማውን ለማሳካት ከሚጠቀምበት ገቢ ለይቶ በመያዝ ያስተዳድራል።

37. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደረጃጀት</u>

1. የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅትን የሚያቋቁም ሰው አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ያዥ እና ኦዲተር ካልሾመ ወይም እነዚህኑ የሚሾም ሰው ካልወከለ አደራ ጠባቂዎቹ ከራሣቸው መካከል እነዚህን ይመርጣሉ።
2. አደራ ጠባቂዎቹ ይህን ምርጫ ያላደረጉ ከሆነ ወይም መወሰን ካልቻሉ ኤጀንሲው ይሾማል፡፡
3. ከሦስት በላይ የሆኑ አደራ ጠባቂዎች ሲኖሩ ያልተሾሙት አደራ ጠባቂዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የተሾሙት አደራ ጠባቂዎች በተሾሙበት ቦታ ያሉባቸው ሃላፊነቶች ውጭ ሌሎች አደራ ጠባቂዎች ያሏቸው መብቶችና ሃላፊነቶች ይኖሯቸዋል።
4. አደራ ጠባቂዎቹ ስብሰባቸውን የሚመራ ሊቀመንበር ከመካከላቸው ይመርጣሉ።

38. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር</u>

1. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር በተመለከተ ከአደራ ጠባቂዎቹ ቢያንስ አንዱ በጽሑፍ እስካልተቃወመ ድረስ የአደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ የሌሎች አደራ ጠባቂዎች ስምምነት ሳያስፈልገው የማስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፡፡
2. ከማስተዳደር ሥራዎች ውጭ ያሉ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቃውሞ የቀረበባቸው ውሣኔዎች ከአደራ ጠባቂዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱ በተገኙበት ስብሰባ በድምጽ ብልጫ ይወሰናሉ።
3. የተለያዩ ሃሣቦች ከአደራ ጠባቂዎች ውስጥ እኩል ድጋፍ ያላቸው ሲሆኑ የመጨረሻው ውሣኔ የስብሰባው ሊቀመንበር በሚሰጠው ድምጽ ይወሰናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት በተሰጡ ውሳኔዎች የማይስማሙ አደራ ጠባቂዎች የልዩነት ሃሣባቸው በቃለ ጉባኤ ላይ እንዲመዘገብላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
5. አደራ ጠባቂዎቹ በአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ስራ መሪነታቸው ለፈጸሟቸው ከሥልጣን በላይ ለሆኑ ድርጊቶች በግል ሃላፊ ናቸው፡፡

39. የአደራ ጠባቂዎች ሥልጣን

1. አደራ ጠባቂዎቹ በአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ላይ ያላቸው ሥልጣን የአንድ ባለንብረተ ሥልጣን ነው፡፡
2. የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር አደራ ጠባቂዎቹ አስቀድመው ለኤጄንሲው ሳያስታዉቁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለሌላ ሰው ሊያስተላለፉ አይችሉም።
3. አነስተኛ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አደራ ጠባቂዎች የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ንብረት ያለ ዋጋ ለሌላ ሊያስተላልፉ አይችሉም፡፡

40. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ስለመወከል

1. አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱን ይወክላል፡፡ አደራ ጠባቂ ሥራ አስኪያጁ በእርሱ ምትክ ድርጅቱን የሚወክለውን አደራ ጠባቂ ይመርጣል፤ እንዲሁም ማናቸውም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ጉዳዮች የሚከታተል ጠበቃ መወከል ይችላል፡፡
2. አደራ ጠባቂዎቹ ከሥልጣን ወሰናቸው ሣያልፉ ለፈጸሟቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ተጠያቂ የሚሆነው የአደራ በጐ አድራጐት ድርጅቱ ነው፡፡

41. ለአደራ ጠባቂዎች የሚፈፀም ክፍያ

1. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ወይም በማናቸውም ሌላ ሕግ ክፍያን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ከሌለ በቀር አደራ ጠባቂ ክፍያ የማግኘት መብት አይኖረውም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ሁሉም አደራ ጠባቂዎች ክፍያ ሲፈጸም እንደሚገባ በጽሁፍ ሲስማሙ እና ኤጀንሲው ሲያፀድቅ በባለሙያነት የሠራ አንድ አደራ ጠባቂ ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለሰጠው ወይም የአደራ በጎ አድራጎት

ድርጅቱን በመወከል ለፈጸማቸው ድርጊቶች ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሀብት ተመጣጣኝ ክፍያ ያገኛል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም አንድ አደራ ጠባቂ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ በግሉ ያወጣቸው ወጭ እና ሃላፊነቶች እንዲተኩለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

42. <u>የአደራ ጠባቂዎች ኃላፊነት</u>

አደራ ጠባቂዎች በውክልና ድንጋጌዎች መሠረት ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችና እንደ ነገሩ ሁኔታ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ሲቀር ንብረቱን መቀበል ለሚገባቸው ሰዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን መልካም አስተዳደር በሚመለከት ሃላፊ ይሆናሉ።

43. <u>የአደራ ጠባቂዎች ሥራ መልቀቅ</u>

1. የአደራ ጠባቂው ሥራ የመልቀቅ ሃሣብ ካለው ስራውን ከመልቀቁ ከሁለት ወር በፊት ለሌሎች አደራ ጠባቂዎች እና ለኤጀንሲው ሳያስታውቅ ቢቀር ከዚህ የተነሣ በአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. አደራ ጠባቂው ሥልጣኑን ለሌላ አደራ ጠባቂ እስከሚያስተላልፍ ድረስ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፡፡
3. አንድ አደራ ጠባቂ የሥራ መልቀቂያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከማለፉ 1 ወር አስቀድሞ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ባቋቋመው ሰው ወይም ይህን ለመፈጸም ሥልጣን በተሰጠው ሰው፤ እነዚህ ባይኖሩ በኤጀንሲው አዲስ አደራ ጠባቂ ይሾማል፡፡

44. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ማስያዝ</u>

1. የተጠቃሚዎች አበዳሪ የሆኑ ሰዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማናቸውንም ተጠቃሚው ሲያገኝ የሚገባውን አበል በማናቸውም ሁኔታ ማስያዝ አይችሉም፡፡
2. ለተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲፈርስ ንብረቱን ለመውሰድ መብት ያላቸው ሰዎች አበዳሪዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ማስያዝ ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በሚቀርበት ጊዜ ባለዕዳወን መተካት ይችላሉ፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከገቢ ማስገኛ ሥራዎች፣ ከሕዝባዊ መዋጮ ወይም ከማናቸውም ምንጭ በተገኙ ንብረቶች ላይ አበዳሪዎች መብት አይኖራቸውም።

45. <u>የተጠቃሚዎች መብቶች</u>

1. ተጠቃሚዎች በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ሠነድ መሠረት የሚገባቸው ጥቅም እንዲሰጣቸው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠቃሚዎቹ መብቶቻቸዉን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጠር አደራ ጠባቂዉ እንዲሻር ወይም ተገቢ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ኤጀንሲወን መጠየቅ ይችላሉ፡፡
3. ተጠቃሚዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ አካል በሆኑ ንብረቶች ላይ የማዘዝ ወይም የማስተዳደር አንዳች መብት የላቸውም።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም እነዚህን ንብረቶች በሚመለከት የይርጋ ዘመን እንዲቋረጥ ማድረግን በመሳሰለው ሥራ መብቶቻቸውን የመጠበቅ ሥራዎችን ብቻ መፈጸም ይችላሉ፡፡
5. ተጠቃሚዎች ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት አንድን ንብረት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ንብረት አካል መሆኑን በማስታወቂያ መግለጽ ይችላሉ፡፡
6. መሥራቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚዎችን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ አደራ ጠባቂዎቹ ከመሥራቹ ሃሣብ ጋር ይስማማል ብለው በሚገምቱት መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል አምስት</u>

## <u>የበጎ አድራጎት ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች</u>

46. <u>ትርጓሜ</u>

1. "የበጎ አድራጎት ማህበር" ማለት ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተቋቋመ ማህበር ነው፤
2. "የበጎ አድራጎት ኮሚቴ" ማለት ቁጥራቸው 5 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ከሕዝብ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ለመሰብሰብ ሃሣብ ያላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡

47. <u>የበጎ አድራጎት ማህበር</u>

1. አግባብነት ያላቸው የማህበር አደረጃጀትንና አሰራርን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ለበጐ አድራጐት ማህበራት ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ ስለ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተቀመጡት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ለበጎ አድራጎት ማህበራት ተፈግሚ ይሆናሉ።

48.<u>የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ስለማጽደቅ</u>

1. የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች በኤጀንሲው ሳይፀድቁ ገንዘብ ወይም ንብረት ማሰባሰብ ወይም ማናቸውንም ድርጊት መፈጸም አይችሉም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኮሚቴውን ለማቋቋም በሚደረጉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።
3. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ሲያጸድቅ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 69 እና 70 ድንጋጌዎች በማገናዘብ መወሰን አለበት፡፡

49.<u>የሂሣብ መግለጫ</u>

1. የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡
2. የበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተቋቋመው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ይህ ጊዜ እንዳለቀ የሂሣብ መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

50.<u>የበጎ አድራጎት ኮሚቴ አደረጃጀት</u>

1. የበጎ አድራጎት ኮሚቴን የማፅደቅ ውሣኔ መስራች አባላት እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ዝርዝር ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል፡፡
2. ውሣኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ዓላማዎች እና ዓላማዎቹን የሚያሳካበትን ጊዜ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው መወሰን እና በኮሚቴው የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት መጠንና አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

51.<u>የአባላት ሃላፊነት</u>

1. ከበጎ አድራጎት ኮሚቴው እንቅስቃሴ ለሚመነጩ ግዴታዎችና ዕዳዎች አባላት ወይም የስራ መሪዎች በአንድነትና በነጠላ ሃላፊ ይሆናሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን በተመለከተ ማናቸውም ለጋሽ፣ አባል፣ ተጠቃሚ፣ ኤጀንሲው ወይም የዘርፍ አስተዳዳሪ ክስ የማቅረብ መብት አለው፡፡

52.<u>በቂ ያልሆነ ገንዘብና ንብረት</u>

1. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት በኮሚቴው የተሰበሰበውን ዓላማ ለማሣካት በቂ ካልሆነ ወይም ዓላማውን ማሳካት የማይቻል ከሆነ ይህ ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት ውሣኔ መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፡፡
2. በውሳኔው ውስጥ ይህን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ በኤጀንሲው ቁጥጥር ሥር ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተመሣሣይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ይውላል፡፡
3. ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው ገንዘቡን ወይም ንብረቱን የሰጡ ሰዎች መልሰው ሲወስዱት አይችሉም።

53.<u>ቀሪ ገንዘብና ንብረት</u>

1. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ዓላማውን ለማሣካት አስፈላጊ ከሆነው በላይ ከሆነ ቀሪው ገንዘብ ወይም ንብረት ኮሚቴውን ባፀደቀው የኤጀንሲው ውሣኔ መሠረት ሥራ ላይ ይውላል፡፡
2. በውሳኔው ውስጥ ይህን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ኤጀንሲው የሚያዝበት ሆኖ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተመሣሣይ የበጎ አድራጐተ ዓላማ ይውላል፡፡
3. ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው ገንዘቡን ወይም ንብረቱን የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት አይችሉም።

54.<u>ወደ ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ስለመለወጥ</u>

1. የበጎ አድራጎት ኮሚቴው በፀደቀበት ውሣኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአንድ ለተወሰነ ዘላቂ ዓላማ የሚውል ከሆነ ይህንኑ ዓላማ ለማሣካት ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይቋቋማል፡፡

2. በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት የታቀደውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው እጅግ የበዛ ከሆነ የኮሚቴው አባላት በዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ለመመዝገብ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ኤጀንሲውን ሲጠይቁና ሲፈቀድላቸው ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ማህበራት

### 55.ትርጓሜ

1. "ማህበር" ማለት ዓላማው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እና ተመሳሳይ ሕጋዊ ዓላማዎችን ለማከናወን እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ለመተባበር በአባላቱ ስምምነት የተመሠረተ የሰዎች ስብስብ ነው፡፡
2. ማህበራት ሥራዎቻቸውን የሚያስተባብር የማህበራት ሕብረት ማቋቋም ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

### 56.የማህበራት ሕጋዊ ሰውነት

1. ማህበራት በኤጀንሲው እንደተመዘገቡ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛሉ።
2. የማህበር አባልነት ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፎ አይሰጥም ወይም አይተላለፍም፡፡

### 57.የማህበራት መብቶችና ግዴታዎች

1. ማንኛውም ማህበር የማህበሩን መስፈርት ለሚያሟላ አዲስ አባል ክፍት መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ማህበር የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ነው፡፡
3. ማንኛውም የማህበር አባል አንድና እኩል ድምጽ አለው፡፡
4. ማንኛውም ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም።
5. አባልነቱ እንዲቋረጥ የሚደረግ ማንኛውም የማህበር አባል የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በሥራ አስፈጻሚው የመሰማት መብት አለው፡፡
6. ማህበሩ የፌዴራል ባህሪ እና ስያሜ ያለው ከሆነ የሥራው ቦታ ወይም የአባላት ጥንቅር ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና ያለው መሆን አለበት፡፡

7. ኢትዮጵያውያን ብዙሃን ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በምርጫ ሂደት በተለይም ትምህርታዊ ሴሚናሮችን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት፣ የተወዳዳሪዎችን ፕሮግራም በመረዳት፣ የምርጫ ሂደቶችን በመታዘብና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር ረገድ በንቃት መሳተፍ ይችላሉ፡፡
8. የማንኛውም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በአባላቱ አብላዕጫ ድምጽ የሚሻሻል መሆን አለበት፡፡
9. ማንኛውም ማህበር አባላቱ በጠየቁ ጊዜ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ የሚገልፁ ሰነዶችን የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

## 58.የማህበራት አደረጃጀት

1. የማንኛውም ማህበር አደረጃጀት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ማንኛውም ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ አስፈላጊ የሥራ መሪዎች እና የውስጥ ኦዲተር የያዘ መሆን አለበት፡፡
3. የውስጥ ኦዲተሩ በማህበሩ የስራ መሪነት ቦታ ሊይዝ አይችልም።

## 59.የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ሆኖ፡-

1. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፤
2. የማህበሩን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤
3. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፤ ክፍያውን ይወስናል፤
4. በማህበሩ የፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
5. በማህበሩ ሌሎች አካላት ሥልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
6. የማህበሩን መፍረስ ይወስናል፤
7. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

## 60.ከጠቅላላ ጉባው ውሣኔዎች መለየት

1. የተለየ ሃሳብ ያለው የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል፡፡

2. ማንኛውም የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ይጥላል ብሎ ሲያምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት ይችላል፡፡

## 61.<u>የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች</u>

1. የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተደነገገው መሠረት ይካሄዳሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ መደበኛ ስብሰባ በ30 ቀናት ውስጥ ያልተጠራ ከሆነ ኤጀንሲዉ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አባላት ጠያቂነት በሰብሳቢው አማካይነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤጡን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከሆነ ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. የማህበሩ ምልዐተ ጉባኤ በመተዳደሪያ ደንቡ በተወሰነው መሠረተ ይሆናል፡፡ ይህን የሚመለከት ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የስብሰባው አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል፡፡ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በሚቀጥለው ሦስተኛ ስብሰባ ከአባላቱ ሃምሳ በመቶ ባይገኙም በኤጀንሲው ውሳኔ ምልዓት ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡
5. የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢዉ ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡ የማህበሩ የስብሰባ ሥነሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ሲሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተመረኮዘ መሆን አለበት፡፡
6. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ዉሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 62.<u>የኦዲተሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኦዲተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አለው፤

1. የማህበሩን ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል።
2. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት የማህበሩን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል።

3. በዚህ አዋጅ ስለ ውስጥ ኦዲት የተደነገጉት ቢኖሩም ማህበሩ በማንኛውም ጊዜ በውጪ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል፡፡

63.<u>አባላትን የሚመለከቱ መረጃዎች</u>

1. የማህበሩ የሥራ መሪዎች የአባላቱን ዝርዝር ጉዳዮች ይመዘግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ሲጠየቁ ለኤጀንሲው ያቀርባሉ።
2. ከማህበራት የሚፈለጉ መረጃዎች ዝርዝር ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አመሰራረት፣ ፍቃድ አሰጣጥና ምዝገባ</u>

## <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

## <u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አመሰራረት</u>

64.<u>አመሰራረት</u>

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ እንደተመሰረቱ ይቆጠራል።
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በተመሠረተ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለምዝገባ ማመልከት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በቂ ክንያት መኖሩን ካሳየ የጊዜ ገደብ ቢያልፍም ለምዝገባ እንዲያመልከት ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

65.<u>የመመስረት ውጤት</u>

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በመመስረታቸው ብቻ ሕጋዊ ሰውነት አይኖራቸውም፡፡
2. የተመሰረተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሲመዘገብና ሕጋዊ ሰውነት ሲያገኝ መብቶቹና ግዴታዎቹ ወደ ተመዘገበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይተላለፋሉ፡፡
3. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከመመዝገቡ በፊት የሚያሰባስበው ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር ሃምሳ ሺህ ብር በላይ ሊሆን አይችልም።

4. በሕግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ያልተመዘገበ የተመሠረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንዲቋረጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

66. <u>የዘርፍ አስተዳዳሪዎች</u>

1. አግባብነት ያላቸው የፌዴራል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የዘርፍ አስተዳዳሪ ሆነው በሚኒስትሩ ይሰየማሉ።
2. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአንድ የተወሰነ የዘርፍ አስተዳዳሪ የማይሸፈን ወይም ከአንድ በላይ የዘርፍ አስተዳዳሪን የሚመለከት ከሆነ ኤጀንሲው የዘርፍ አስተዳዳሪ ይሆናል፡፡
3. ማናቸውም የዘርፍ አስተዳዳሪ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባር ተጠሪ ለሆኑለት የፌዴራል መንግስት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

67.<u>የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንና ተግባር</u>

የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፤

1. በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ ሂደት ለኤጀንሲው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
2. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚገመግሙና አስተያየት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይመድባል፤
3. በማቋቋሚያ ሕጉ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እና ከበጎ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በሚገቡት ስምምነት መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
4. የዘርፍ አስተዳዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የወሰደውን እርምጃ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ያሳውቃል፤
5. ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ሥራዎች ህብረተሰቡ የላቀ ተጠቃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው ሊከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶችን ያወጣል፤
6. የበጎ አድራጐት ድርጅቶችንና የዘርፍ አስተዳዳሪዉን የጋራ ግቦች ለማሣካት የበጎ አድራጐተ ድርጅቶች ተቀናጅተው የሚሰሩበተን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ምዝገባ</u>

68.<u>ምዝገባ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው ማመልከቻ ሲቀርብለት በ30 ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካቾቹን በበጐ አድራጐት ድርጅትነት ወይም በማህበርነት በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኤጀንሲው የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ካላሳወቀ አመልካቹ በንዑስ አንቀጹ ከተቀመጠው የመጨረሻ ቀን በ15 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ፎርም መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቱን የማህበሩን ግብ፣ አላማና ሥራ የሚመለከቱ መግለጫዎችን የያዘ ሆኖ ከሚከተለት ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

   ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና እንደ አስፈላጊነቱ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያቋቋመው ሠነድ ቅጂ፤

   ለ/ እንዳስፈላጊነቱ ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ሌሎች ሠነዶች፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች በተጨማሪ ውጪ አገር የተመሰረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፣

   ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መቋቋሙን የሚያሳይ ከተቋቋመበት አገር የተሰጠውን የተረጋገጠ ሰነድ፤

   ለ/ ሥልጣን ያለው የድርጅቱ አካል ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠራ ያሳለፈው የተረጋገጠ ውሣኔ፤

   ሐ/ ኢትዮጵያ ከሚገኝ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተቋቋመበት አገር ኤምባሲ ወይም ኤምባሲ ከሌለ ከተቋቋመበት አገር ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

   መ/ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

   ሠ/ የአገር ውስጥ ተወካዩ የተሰጠው የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የምዝገባ ማመልከቻ ሲቀርብ ተገቢው የምዝገባ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

## 69. የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል

ኤጀንሲው ከሚከተሉት አንዱ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን አይመዘግብም፤

1. ሊቋቋም የታሰበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፤
2. ሊቋቋም የታሰበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሕገወጥ ለሆነ ዓላማ፣ የሕዝብን ሠላም ለሚያደፈርስ ተግባር ወይም የኢትዮጵያን ደህንነትና መረጋጋት ለመጉዳት መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖር፤
3. የምዝገባ ማመልከቻው የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ድንጋጌዎች የማያሟላ ሲሆን፤
4. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚመዘገብበት ስም ከሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ከማንኛውም ሌላ ተቋም ስም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ወይም የሕዝብን ሞራል ወይም ሕግን የሚቃረን ሲሆን፤
5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ስያሜ አገር አቀፋዊ ወይም ፌዴራላዊ ሆኖ የአባላት ጥንቅር ወይም የሥራ ቦታው ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና የሌለው ከሆነ፡፡

## 70. በሥራ መሪነት መሥራት የማይችሉ ሰዎች

ማንኛውም ሰው በአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም በእነዚሁ ቅርንጫፎች በሥራ መሪነት መሥራት የማይችለው፤

1. በማጭበርበር ወይም ታማኝነትን በማጓደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ከሆነ፤
2. በማናቸውም ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሲቪል መብቱን የተገፈፈና መብቶቹ ያልተመለሱለት ከሆነ፤
3. በሕግ መሠረት ከችሎታ ማጣት የተነሳ መሥራት የማይችል ከሆነ፤
4. በፍርድ ክልከላ የተደረገበት ከሆነ፤
5. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሌለና አለመኖሩ ለበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ትክክለኛ አስተዳዳር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ፡፡

## 71. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ

1. ኤጀንሲው ማንኛውንም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርን በሚመለከት በየጊዜው የሚወስናቸው ዝርዝሮች የሚመዘገቡበት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ ይይዛል፡፡
2. የዚሁ ዓይነት ሠነድ ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ በኤጀንሲው ዳይሬክተር ትክክለኛ ቅጂ ለመሆኑ የተመሠከረ ከሆነና የኤጀንሲው ማሕተም ከተደረገበት በማናቸውም የክርክር ሂደቶች በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል።
3. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ በኤሌክትሮኒክ መልክ ጨምሮ ኤጀንሲው አግባብ ነው ብሎ በሚገምተው መንገድ ተዘጋጅቶ ይቀመጣል።
4. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡትን፣ የታገዱትንና ከመዝገብ የተሰረዙትን የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ዝርዝር በጋዜጣ ያወጣል።

72.<u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቅርንጫፍ</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አስቀድሞ ኤጅንሲወን በማሳወቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚከፈት ቅርንጫፍ የሚሰጠወ ሥልጣን ራሱን የቻለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚያደርገው ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በቂ ቁጥጥር እንዳያደርግበት የሚያደርገው ሊሆን አይችልም፡፡

73.<u>ስያሜ፣ የሥራ ቦታ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ስለመለወጥ</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሜውን ወይም የሥራ ቦታውን ከለወጠ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ካሻሻለ ለውጡን ወይም ማሻሻያውን ለኢጀንሲው አቅርቦ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68 መሠረት ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከተመዘገበ በኋላ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (3)፣ (4) ወይም (5) የተደነነገገው በማናቸውም ምክንያት ሳይከበር መታለፉ ከተረጋገጠ አጅንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል ወይም ጉድለቱ እንዲታረም ሊያዝ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተፈጸመ የስም ለውጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ማናቸውንም መብቶች ወይም ግዴታዎች አይነካም፡፡ በቀድሞ ስሙ ተጀምረው የነበሩ ክርክሮች በአዲሱ ስም ይቀጥላሉ።

74.<u>በምልክቶች ስለመጠቀም</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በኤጀንሲው ሳያስመዘግብ ማናቸውንም ምልክት መጠቀም አይችልም።

2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለትን ዓርማ ለመመዝገብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 69 የተደነገጉትን የምዝገባ መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል።

75.<u>የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለማሣየትና ስለማስታወቂያ ሰሌዳ</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን በዋናው መሥሪያ ቤትና ግልባጩን በየቅርንጫፎቹ ለማናቸውም ጐብኚ ሊታይ በሚችል ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

2. አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የማስታወቂያ ሠሌዳ የሚጠቀም ከሆነ ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸውን ዝርዝሮች በሰሌዳው ላይ መለጠፍ ይኖርበታል።

76.<u>ፈቃድን ስለማሳደስ</u>

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 78 እና 80 መሠረት አመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎችን ለኤጀንሲው የማቅረብ ግዴታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃዳቸውን በየሦስተ ዓመቱ ማሳደስ አለባቸው።

2. ፈቃድ የሚታደሰው በፈቃድና ምዝገባ ሰርተፊኬቱ ላይ የተገለፀው ጊዜ የሚያገለግልበት የመጨረሻ ቀን ካለፈ በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ነው፡፡

3. ኤጀንሲው፣

ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የስራ አፈጻፀምና የኦዲት ሪፖርቶች የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን፣ እና

ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወይም በኤጀንሲው የተሰጡ ተሰዛዞችን ወይም የራሱን መተዳደሪያ ደንብ ያል ጣሰ መሆኑን፣

ሲያረጋግጥና አስፈላጊው የማሳደሻ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ፈቃዱን ያድሳል፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ስለ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ሂሣብ እና ሪፖርቶች</u>

77. <u>የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ</u>

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የስራ መሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴዎች የሚያብራራ እና በማናቸውም ጊዜ ሊያሣይ የሚችል የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው።
2. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሂሣብ ሰነዶች የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የተቀበለውን ጠቅላላ ገንዘብና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪዉን ምክንያት፣ ሀብትና ዕዳ ያካተቱ መሆን አለባቸው።
3. የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማሕበራት ስሙ ካልተገለፀ ሰው ልገሳ መቀበል አይችሉም፡፡ በማናቸውም ጊዜ የለጋሹን ማንነት በግልጽ የሚያመለክቱ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው።
4. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጁ የሂሳብ ሰነዶችን ሰነዶቹ የተዘጋጁበት የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ የሂሣብ ዓመት ካለቀ በኋላ ቢያንስ ለ5 ዓመታት ጠብቀው ማቆየት አለባቸው፡፡
5. ኤጀንሲው ሰነዶቹ እንዲወድሙ ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገዱ በጽሁፍ ካልፈቀደ በስተቀር ከሂሳብ ሰነድ ጋር በተያያዘ በንዑስ አንቀጽ (4) የተገለጸው አምስት ዓመት ከማለቁ በፊት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕልውና ካከተመ የሂሳብ ሰነዶቹን ጠብቆ የማቆየት ግዴታ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ቀሪ የስራ መሪዎች ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል።

78.<u>ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ተቀባይነተ ባላቸው መመዘኛዎች መሰረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለኤጀንሲው በአድራሻ መላክ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ የማይበልጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ገቢን፣ ወጪን፣ ሃብትንና ዕዳን የሚያመለክት መግለጫ ብቻ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
3. የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የተዘጋጀ የሂሣብ መግለጫና ተያያዥ ሰነድ የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ጠብቀው ያቆያሉ፡፡

79.<u>ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ ስለማድረግ</u>

1. የማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሂሣብ በየዓመቱ በተመሰከረለት ኦዲተር ወይም የውስጥ ኦዲተር ወይም ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር መመርመር አለበት፡፡
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በውጭ ኦዲተር የመመርመር ግዴታ የሚኖርበት አግባብነት ባለው የበጀት ዓመት ቀድሞ ያለው የበጀት ዓመት ሂሳብ ከብር 100,000 /አንድ መቶ ሺ.ህ/ የሚበልጥ ሲሆን ነው፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም ዓይነት የሂሳብ ምርመራ በማንኛውም ጊዜ በውጭ ወይም በውስጥ ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር ሊመረመር ይችላል፡፡
4. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ሂሣብ ዓመቱ ባለቀ አምስት ወራት ዉስጥ ካልተመረመረ ወይም በውጭ ኦዲተር ማስመርመር የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው ኦዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በኤጀንሲው በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማናቸውም የኦዲት ሥራዎች ወጭ የሚከፍለው የሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ጥፋተኛ ሆነዉ ሲገኙ የስራ መሪዎቹ ይሆናሉ።

80.<u>ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት</u>

1. የሥራ መሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበርን የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች ሪፖርትና አስፈላጊ መረጃ በማዘጋጀት ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ሪፖርት የሂሣብ ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም ኤጀንሲው በማናቸውም ልዩ ምክንያት በሚጠይቀው ጊዜ ውስጥ የሥራ መሪዎቹ በኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው።
3. ማንኛውም የሥራ ክንውን ሪፖርት ለኤጀንሲው ሲደርሰዉ የሂሣብ መግለጫ አብሮ መያያዝ አለበት፡፡

81.<u>ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ</u>

በኤጀንሲው ዘንድ የሚገኝ ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የዓመት ሪፖርት ወይም ሌላ ሠነድ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ወይም በኤጀንሲው

ወይም በሚመለከተው የዘርፍ አስተዳዳሪ ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቱ እና ማህበሩ ውሳኔ በማናቸውም አመቺ ጊዜ ለሕዝብ ክፍት ሊደረግ ይችላል፡፡

82. <u>ለሌሎች ሰዎች ሪፖርት ስለማድረግ</u>

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የማህበሩ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ በዚህ ክፍል ከተጠቀሱት አካላት በተጨማሪ ለሌሎች ሰዎች ወይም ድርጅቶች የሂሳብ መዛግብት፣ የኦዲት ሪፖርቶች እና ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብን አይከለክልም፡፡

83. <u>የባንክ ሂሳብ ስለማሳወቅ</u>

የበጎ አድራት ድርጅት ወይም የማህበር መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የባንክ ሂሳብ ከሚፈለገጡ ዝርዝር ጋር ለኤጀንሲው በየአመቱና በተጠየቁ ጊዜ ማሳወቅ አለባቸው።

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>የበጐ አድራጐት ድርጅቶችንና ማሕበራትን ስለመቆጣጠር</u>

84. <u>ምርመራ የማድረግ ሥልጣን</u>

1. ኤጀንሲው በየጊዜው ለአጠቃላይ ወይም ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ የበጐ  አድራጐት ድርጅቶችን ወይም ማሕበራትን ወይም የተወሰኑ ወይም አንድ ዘርፍ የሆኑ የበጉጋ አድራጐት ድርጅቶችን ወይም ማሕበራትን የተመለከተ ምርመራ ሲያካሂድ ይችላል፡፡
2. ለእንዲህ ዓይነት ምርመራ ጉዳይ ኤጀንሲው ማናቸውንም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ፡-

   ሀ/ የሚያውቀወን ወይም መረጃ ሲያገኝ የሚያስችለው ምክንያታዊ ግምት ኖሮ ምርመራው የሚካሄድበትን ጉዳይ በተመለከተ ሂሣብና መግለጫ በጽሁፍ እንዲሰጥ፣ ጉዳዩን በተመለከተ ለቀረበለት ጥያቄ ወይም ምርመራ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጥ፤

   ለ/ በምርመራዉ ሂደት መመርመር ያለበትን ማናቸውንም ጉዳይ በተመለከተ በእጁ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን ሠነዶች ቅጂ እንዲሰጥ፤

   ሐ/ በተወሰነ ጊዜና ቦታ በመገኘት ማስረጃ ወይም ሠነዶችን እንዲያቀርብ፣

   ሊያዝ ይችላል፡፡
3. ኤጀንሲው ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ከሕዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን፣ ከመንግሥት አካላት የሚቀርቡ ሪፖርቶችን እና ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችና

ከማሕበራት ከራሣቸው የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ጨምሮ ማናቸውንም የመረጃ ምንጭ ሲጠቀም ይችላል፡፡

85. <u>ሠነዶች እንዲቀርቡ የማዘዝና ሪከርዶች ኢንዲመረመሩ የማድረግ ሥልጣን</u>

1. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል ከአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ወይም የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ፤

ሀ/ አንድን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር የሚመለከት በይዞታው ሥር ያለ ማንኛውንም መረጃ በጽሁፍ ወይም በቃል ለኤጀንሲጡ እንዲሰጥ፣ ወይም

ለ/ የሠነዱን ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ ለኤጀንሲወ እንዲሰጥ፤ ወይም

ሐ/ ሠነዱ የአንድ ፍርድ ቤት ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሪከርድ ወይም ሠነዶች አካል ካልሆነ በስተቀር ሠነዱን ራሱን ለምርመራ ለኤጀንሲዉ እንዲሰጥ፣

በትዕዛዝ ሲጠይቅ ይችላል፡፡

2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማናቸውንም ግልባጭ ወይም የሠነድ ክፍል ያለ ክፍያ የማግኘት ሥልጣን አለው፡፡

86. <u>ስብሰባዎችን ስለማስታወቀ</u>

ማንኛውም ማሕበር የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከሰባት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የስብሰባዉን ጊዜና ቦታ ለኡጀንሲጡ በጽሑፍ አለበት፡፡

87. <u>መረጃ ስለመግለጽ</u>

በሌሎች ሕጎች በግልጽ የተደነገጉት ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው ወይም የዘርፍ አስተዳዳሪው ሥራዎቹን በሚገባ እንዲከናወን ለማስቻል ወይም ለመርዳት ማንኛውም ሰው ያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃ ለኤጀንሲው ወይም ለዘርፍ አስተዳዳሪው መግለጽ ይችላል፡፡

88. <u>የአስተዳደራዊና የዓላማ ማስፈጸሚያ ወጪዎች</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጣው ከ70 በመቶ የማያንሰውን ዓላማውን ለማስፈጸም እና ከ30 በመቶ የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ሥራ ማዋል አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም ከጠቅላላ ገቢው ከ80 በመቶ በላይ ለዓላማው ማስፈጸሚያ ለሚያወል ወይም የላቀ የሥራ አፈጻጸም ላሳየ የበን

አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መንግሥት የተለያዩ ማበረታቻዎችን ሲያደርግ ይችላል፡፡

89. <u>የውጭ ዜጎችን መቅጠር</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠውን የውጪ ዜጋ መቅጠር አይችልም።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የውጭ የበጐ አድራጐት ድርጅት የውጭ ዜጋን የሀገር ዉስጥ ተወካይ አድርጎ ለመመደብ ገደብ አይኖርበተም፡፡

90. <u>የንብረት ጥበቃ</u>

1. ኤጀንሲዉ ማንኛውንም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር በተመለከተ በሚያደርገዉ ክትትል ወይም ምርመራ ተገቢ ያልሆነ የሥራ አመራር ወይም ድርጊት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ንብረት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የሚከተሉትን እርምጃዎች መወሰድ ይችላል፤

   ሀ/ ተገቢ ላልሆነው የሥራ አመራር ወይም ድርጊት ሃላፊ የሆነውን የሥራ መሪ ማገድና ሥልጣን ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ተተኪ እንዲመድብ ያዛል፤

   ለ/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩየአሠራር ሥርዓቱን እንዲያሻሽል ያዛል፤

2. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ እስከሚያደርግ ድረስ፣

   ሀ/ ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን የተወሰኑ ግዴታዎች ውስጥ የሚያስገቡ ውሎች እንዳይደረገዝ ወይም የተወሰኑ ዓይነት ክፍያዎች እንዳይፈጸሙ ያግዳል፤

   ለ/ የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም የማሕበሩ ንብረት በይዞታው ስር ያለን ሰው ወይም ባለዕዳን ያለ ኤጀንሲው ፈቃድ ንብረቱን እንዳይመለስ ወይም ዕዳውን እንዳይከፍል ያግዳል ወይም ኤጀንሲው በሚወስነው ቦታ ወይም ባንክ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

91. <u>የስራ መሪዎችን ስለ ማንሳትና መተካት</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የማህበር መሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንዱን ያጓደለ እንደሆነ ሥልጣን ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አካል እንዲነሳና በሌላ እንዲተካ እንዲደረግ ኤጀንሲው ያዛል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የሥራ መሪ በሌላ እስኪተካ ድረስ ከሃላፊነት እንዲታገድ ኤጀንሲው ሊያዝ ይችላል፡፡

92. <u>ፈቃድ ለማገድና ለመሰረዝ</u>

1. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፡-

ሀ/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 73(2) መሰረት የተላለፈዉ የኤጀንሲዉን ትዕዛዝ በተወሰነ ግዜ ገደብ ዉስጥ ሳይፈፅም ከቀረ፣

ለ/ ያቀረበዉ ሪፖርት ሐሰተኛ ከሆነ፣

ሐ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ወይም በኤጀንሲው የተሰጡ ትዕዛዞችን ወይም የራሱን መተዳደሪያ ደንብ የጣሰ እንደሆነ፣

መ/ በዚህ አዋጅ መሰረት ለኤጀንሲዉ ማቅረብ ሚገባዉን ማስረጃ በወቅቱ ያለቀረበ እንደሆነ፣

ጉድለቶቹን እስከሚያስተካክል ድረስ ፈቃዱ በኤጀንሲዉ ሊታገድ ይችላል፡፡

2. ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፤

ሀ/ የተመዘገበው በማታለል ወይም በማጭበርበር ከሆነ፣ ወይም

ለ/ ሕገ ወጥ ለሆነ ዓላማ፣ ወይም የሕዝብን ሠላምና የአገርን ደህንነት ለሚጎዱ ዓላማዎች ውሎ ከሆነ፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለዕግድ ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ፣ ወይም

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 76 መሠረት ፈቃዱን ካላሳደሰ፣

ሠ/ የወንጀል ሕጉን ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ የወንጀል ድርጊት ከፈጸመ፤

ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

93. <u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መፍረስ</u>

1. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች በኤጀንሲው ሊፈርስ ይችላል፤

ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሥልጣን ያለው አካል በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት እንዲፈርስ ሲወስን፤

ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 92 መሠረት በኤጀንሲው ሲሠረዝ፤ ወይም

ሐ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ለዳውን የመክፈል ችሎታ የሌለው ሲሆን።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የሚፈርሱት በፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ነው።

94. <u>የመፍረስ ውጤት</u>

1. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር እንዲፈርስ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ፤

ሀ/ ንብረቱ ወዲያውኑ የማፍረሱ ውሳኔ በተሰጠበት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የማፍረስ ሂደቱን እንዲያከናውን በተሾመው ሂሣብ አጣሪ ኃላፊነት ስር ይሆናል፤

ለ/ ሂሣብ አጣሪው የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማሕበሩን እዳዎችና ኃላፊነቶች እንዲሁም የማፍረስ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀጡ ከተከፈሉ በኋላ የበጎ አድራጎተ ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረተ ካለ ተመሣሣይ ዓላማ ላለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ለማንኛውም የበጎ አድራጎተ ድርጅት ወይም ማህበር እንዲተላለፍ ኤጀንሲው ትዕዛዝ ይሰጣል፤

2. የፈረሰ የበጎ አድራጎት ድርጅትን ወይም ማሕበርን የሂሣብ አጣሪ መሾም በተመለከተ ኤጀንሲው ወይም ፍርድ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ የሥራ መሪዎችን ወይም ማኛጡንም ሰው ሊሾም ይችላል፡፡

3. ሂሳቡ በመጣራት ላይ ያለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከዓላማው ጋር የተያያዙና ሲቋረጡ የማይችሉ ሥራዎችን ኤጀንሲውን በማስፈቀድ ለማጠናቀቅ ካልሆነ በስተቀር ከሂሳብ ማጣራቱ ውጭ ሌላ ተግባር ማከናወን አይችልም።

4. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሂሳብ ማጣራት ሥራዎች ተጠናቀው ምዝገባው እስከሚሰረዝ ድረስ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቆያል፡፡

<u>ክፍል ስምንት</u>

## ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል

### 95. ንብረትን ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል ስለሚፈፀምባቸው ሁኔታዎች

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የመጀመሪያ ዓላማ ሊለወጥ የሚችልባቸውና የተሰጠው ሙሉ ንብረት ወይም ከፊሉ ለሌላ ተቀራራቢ ዓላማ እንዲውል በሚከተሉት ሁኔታዎች ይፈጸማል፤

   ሀ/ የመጀመሪያው ዓላማ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሳካ ወይም የማይሳካ ወይም ሊሳካ የማይችል ሲሆን፤

   ለ/ ድርጅቱ ለመጀመሪያው ዓላማ ካለው ንብረት ከፊሉ ብቻ በጥቅም ላይ እንዲውል የሚያመለክት ሲሆን፤

   ሐ/ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ የተሰጠ ስጦታ መንፈስ ሳይነካ በስጦታው መሠረት ያለው ንብረት እና ለተመሣሣይ ዓላማ የሚውል ሌላ ንብረት እና ቢቀናጁ አመቺ በሆነ ሁኔታ የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለጋራ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሲሆን፡፡

2. የዘለቄታ በጐ አድራጐት ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ማቋቋሚያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የሥራ መሪዎች ላይ ሁኔታው በሚያስገድድበት ጊዜ ንብረቱ ወይም ከፊሉ ለተቀራራቢ ዓላማ ማዋል እንዲፈጸምበት ተገቢ እርምጃዎችን መወሰድ አለባቸው።

3. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሱትን ተግባራት ሊፈፅሙ የሚችሉት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ዉሳኔ ሲያስተላልፉ ብቻ ነው፡፡

4. ንብረቱ የተሰጠው ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ቢሆንም ይህ አንቀጽ ለበጐ አድራጐት ዓለማዎች በተሰጠ ንብረት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲው ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡

### 96. የማቋቋሚያ ሰነድ ወይም ትዕዛዝ መመሪያዎች

1. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂ ወይም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ቦርድ ድርጅቱን ካቋቋመው ሰነድ ወይም ትእዛዝ የተቀበላቸውን ግልጽ የሆኑ መመርያዎችን መከተል አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በአደራ ወይም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ተጠቃሚ ለሆነው ሰው ጥቅም የሚያስፈልግ ሆኖ የታየ እንደሆነ ከተባሉት መመሪያዎች ውጭ ለመስራት አደራ ጠባቂው ወይም ቦርዱ ከኤጀንሲው ፈቃድ መጠየቅ ይችላል፡፡

## 97. የአነስተኛ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ልዩ ድጋጌዎች

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ በመጨረሻው የሒሣብ ዓመቱ ጠቅላላ ገቢው ከ50,000 ብር /ከሃምሳ ሺ ብር/ በላይ ካልሆነና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ካልሆነ በስተቀር የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ አካል የሚከተሉትን ሊፈጽም ይችላል፤

   ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሁሉም ንብረቶች ለሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲተላለፍ ወይም እንዲከፋፈል፤

   ለ/ የመተዳደሪያ ደንቡ ሁሉንም ወይም ማናቸውንም የበጎ አድራጎተ ድርጅቱን ዓላማዎች በጎ አድራጎት ወደሆኑ ሌሎች አላማዎች በመለወጥ እንዲሻሻል ማድረግ፤

   ሐ/ የስራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በማስተዳደር ረገድ ሲከተሏቸው የሚገቡ ስነ-ሥርዓቶችን በተመለከተ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ማድረግ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማንኛውም ውሣኔ የሚተላለፈው በአደራ ጠባቂዎች ወይም በቦርዱ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ብቻ ነው፤

3. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲዉ ሲፈቅድ ብቻ ነው፤

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ በንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ)-(ሐ) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲፈጽሙ ዉሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ሕዝባዊ መዋጮ

## 98. ለሕዝባዊ መዋጮ ስለማመልከት

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ሕዝባዊ መዋጮ ማካሄድ የሚችለው በኤጀንሲዉ ሲፈቀድለት ብቻ ነው፡፡

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ የሕዝባዊ መዋጮዉን ዓላማ፣ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ቦታውንና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወስኑትን መመዘኛዎች መያዝ አለበት፡፡

3. ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉን ተላልፎ የተሰበሰበው ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት በኤጀንሲው ተወርሶ ለተመሳሳይ የበጐ አድራጐት ወይም ማህበር ዓላማ እንዲውል ይደረጋል፡፡

99. **በማመልከቻ ላይ ስለመወሰን**

1. ሕዝባዊ መዋጮ ለመሰብሰብ ማመልከቻ ሲቀርብ ኤጀንሲዉ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ፈቃዱን በገደብ ወይም ያለገደብ መስጠት ወይም ዉድቅ ማድረግ ይችላል፡፡

2. ኤጀንሲዉ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ወይም በፈቃዱ ላይ ማናቸውንም ገደብ ሲያደርግ ለማመልከቻ አቅራቢዉ ዉሳኔዉን ከነምክንያቱ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

100. **የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች**

ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ ሲከለክል ይችላል፤

1. ሕዝባዊ መዋጮው ለበጐ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ለማህበሩ ዓላማ የሚውል ካልሆነ፤
2. በአመልካቹ የቀረበው መረጃ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች ከሆነ፤
3. ሕዝባዊ መዋጮውን የሚያከናውኑት ሰዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 የተደነገጉት መመዘኛዎች የማያሟሉ ከሆነ፡፡

101. **ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድን ስለመሠረዝ**

1. ኤጀንሲዉ በሚከተሉት ምክንያቶች ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድን ሲሰርዝ ይችላል፤

   ሀ/ ፈቃዱ ከተሰጠ በኋላ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 98 ድንጋጌዎች እንዳልተሟሉ ሲረጋገጥ፤

   ለ/ ሕዝባዊ መዋጮው ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ እንዲተዳደር የተደረገ ሲሆን፤

   ሐ/ ፈቃዱ ሲሰጥ በኤጀንሲጡ የተጣለው ገደብ የተጣሰ ሲሆን።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሕዝባዊ መዋጮ የመሰብሰብ ፈቃድ ሲሰረዝ የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት በኤጀንሲው ተወስዶ ለበጎ አድራጎት አላማ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

102. **ቅጣት**

1. ማንኛውም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የጣሰ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣

ሀ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 77 በመጣስ የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፤ የተቀበለውን ገንዘብ፣ የገንዘቡን ምንጭና ወጭ ያልመዘገበ፤ የሂሳብ ሰነዶቹን የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ጠብቆ ያላቆየ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከብር 20,000 /ሃያ ሺ. ብር/ በማያንስና ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺ. ብር/ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ለ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 78 በመጣስ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃዎች መሰረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለኤጀንሲዉ ያልላከ ወይም ገቢው ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺ. ብር/ በታች ሲሆን ገቢን፣ ወጪንና ሃብትን ዝርዝር ለኤጀንሲዉ ያላቀረበ ወይም የሂሳብ መግለጫውንና ተያያዥ ሰነድ ለአምስት ዓመት ጠብቆ ያላቀየ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከብር 10,000 /አስር ሺ. ብር/ በማያንስና ከብር 20,000 /ሃያ ሺ. ብር/ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሐ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 83 በመጣስ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የባንክ ሂሳብ ከሚፈለገው ዝርዝር ጋር በየዓመቱ እና በተጠየቀ ጊዜ ለኢጄንሲው ያላቀረበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺ.ብ/ በማያንስና 100,000 /አንድ መቶ ሺ. ብር/ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 88 በመጣስ የየበጀት ዓመት አስተዳደራዊ ወጪውን ከበጀቱ 30 በመቶ በላይ ያወጣ ወይም የዓላማ ማስፈጸሚያ ወጪውን ከ70 በመቶ በታች ያደረገ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር 5,000

/አምስት ሺ. ብር/ በማያንስና ከብር 10,000 /አስር ሺ. ብር/ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተዉ ወንጀል ተሳታፊ የሆነ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የተመለከተዉ የእስራት ቅጣት ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ 10,000 /የአሥር ሺ. ብር/ በማያንስና ከብር 20,000 /የሃያ ሺ. ብር/ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 103. የገቢ ማስገኛ ስራዎች

1. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከኤጀንሲው በጽሁፍ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አባላት ወይም ተጠቃሚዎች ሊከፋፈል የማይችል እና ገቢው ለዓላማው ማስፈጸሚያ የሚውል ከአላማው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ገቢ የማመንጨት ሥራዎች ሲያከናውን ይችላል፡፡
2. ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎቹን በተመለከተ የተለዩ የሂሣብ መዛግብት መያዝ አለበት፡፡
3. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ትርፉን ለአባላቱ አከፋፍሎ ወይም የተለየ የሂሣብ መዛግብት ሳይዝ ቢገኝ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 92 መሰረት አግባብነት ያለውን እርምጃ ይወስዳል።
4. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሌሎች ሕጎች ንግድን፣ ኢንቨስትመንትን እና ሌሎች ትርፍ ለማግኘት የሚሰሩ ሥራዎችን ምዝገባና ፈቃድ በሚመለከት የተደነገጉትን መስፈርቶች እና ሥነ-ሥርዓቶች አያስቀሩም፡፡

## 104. አቤቱታ እና ይግባኝ

1. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በኤጀንሲው አሰራር ላይ ተገቢውን የአስተዳደር እርከኖች ተከትሎ የሚቀርብለትን ማንኛውንም አቤቱታ ተቀብሎ በ15 ቀን ውስጥ መወሰን አለበት፤
2. በማንኛውም ዋና ዳይሬክተሩ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቢኖርም የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ቦርዱ ውሳኔ በሰጠ 15 ቀን ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ መሰረት በይግባኝ ሂደት ላይ የሚገኝ የምዝገባ ወይም የስረዛ ጉዳይ ከሆነ የሚመለከተው አካል የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ እንዳልተመዘገበ ወይም እንዳልተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

105. <u>ወንጀልን ስለመመርመርና ክስ ስለማቅረብ</u>

1. በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦች የተደነገገውን ማናቸውንም ወንጀል በተመለከተ የሚካሄድ የምርመራ ወይም የክስ ማቅረብ ሂደት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ይመራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ኤጀንሲው ለወንጀል ክስ የሚረዱ ማናቸውንም ማስረጃ በማደራጀት ክስ የመመስረት ሥልጣን ላለው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

106. <u>መዋሐድ</u>

1. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት አግባብነት ባላቸው ሕጐችና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሃዱት በአንዱ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ስም ሊዋሐዱ ይችላሉ፡፡ ውህደቱ ሲፈጸም የቀድሞ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት መብትና ግዴታ ወደ ተዋሃደው ድርጅት ይተላለፋል፡፡
2. የተዋሃደው አዲስ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር በዚህ አዋጅ መሠረተ መመዝገብ አለበት፡፡

107. <u>መከፋፈል</u>

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር መተዳደርያ ደንቡ የሚፈቅድ ከሆነ እና አግባብነት ያለው አካል ከፈቀደ በሕግ መሰረት ሊከፋፈል ይችላል፡፡
2. የተከፋፈለው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ስልጣን ያለው አካል ተቃራኒ ውሳኔ እስካልሰጠ ድረስ የተከፈለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የቀድሞ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ላለበት ግዴታና መብት እኩል ተካፋይ ነው፡፡

3. የቀድሞው የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ሕልውና የሚያበቃው ለአዲሶቹ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት የምዝገባና ፈቃድ የምስክር ወረቀት ሲሰጥና የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡

4. በሁሉም አዲሶቹ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወይም ማሕበራት ስምምነት ከነሱ አንዱ የቀድሞውን የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማሕበር ስም ይዞ እንዲቆይ ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል፡

108. <u>ስለ መቀየር/መለወጥ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 95 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የበጐ አድራጐት ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሣኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3) ወይም (4) ከተጠቀሱት የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ወደ አንዱ ሊቀየርና በኤጀንሲው ሊመዘገብ ይችላል፡፡

2. ማንኛውም ማህበር በዚህ አዋጅ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዓይነት ወደ አንዱ ሊቀየርና በኤጀንሲው ሊመዘገብ ይችላል፡፡

109. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

110. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልምዳዊ አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

111. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ ይህን አዋጅ እስካልተቃረነ ድረስ ይቀጥላል፡፡

2. ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡

112. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ/ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## ደንብ ቁጥር 168/2001

## ስለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5 እና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 109 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. "አዋጅ" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 ነው፤
2. "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፤
3. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህም ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤
5. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው፤
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

### ክፍል ሁለት

### ስለምዝገባ

3. **ለመደበኛ ምዝገባ ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

1. የምዝገባ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሊሰራ ያሰበባቸውን ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ዝርዝር ወይም ማህበሩ ሊሰራ ያሰበባቸውን ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ዝርዝር እና የማህበሩ መሥራች አባላት መኖሪያ አድራሻ፤

ለ/ ኤጀንሲው ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ለመመራት የተሰጠ ስምምነት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መስራቾች የተፈረመ መተዳደሪያ ደንብ፤

ሐ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የገንዘብ ምንጭን ከመቶው ምን ያህሉ ከኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ ወይም እንደማይሆን፤

መ/ እንደነገሩ ሁኔታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የሥራ መሪዎች፤ መስራቾችና አባላት ስም፣ አድራሻ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ዜግነት፤

ሠ/ ሊቋቋም የታሰበውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ዓይነት፣

ረ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሊጠቀምበት የሚፈልገው ምልክት ካለ ይህንኑ፤ እና

ሰ/ በኤጀንሲው የሚጠየቁ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ እንደነገሩ ሁኔታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መሥራቾች፣ ባለአደራዎች ወይም ተወካዮች የፈረሙበትና ማመልከቻው ውስጥ የተመለከቱት መረጃዎች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል።

3. ኤጀንሲው የፈቃድና ምዝገባ ጥያቄውን ዉድቅ ካደረገ ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻዉ ዉድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል። ማመልከቻው ውድቅ መደረጉ አመልካቹ በዚህ ደንብ መሠረት የከፈለዉ የአገልግሎት ክፍያ እንዲመለስለት አያደርግም፡፡

4. ኤጀንሲው ምዝገባ የሚያካሂደው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን አግባብነት ያለው ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

4. <u>የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ (4) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የምዝገባ ማመልከቻ የሚከተሉትን ሊያካትት ይጋባል፡-

   ሀ/ ድርጅቱ ለትግበራ ያዘጋጀው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፤

   ለ/ የድርጅቱ የሀገር ውስጥ ተወካይ ዝርዝር የግል መረጃ፣ እና

   ሐ/ ሌሎች ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸው መረጃዎች፡፡

2. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት የድጋፍ ደብዳቤ ለመስጠት ሊከተላቸው የሚገባውን ዝርዝር መስፈርቶች ከኤጀንሲው ጋር በመመካከር ያወጣል።

3. ኤጀንሲው የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባን የሚያካሂደው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

5. <u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ስያሜ</u>

የአመልካችን ወይም የተመዘገበን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሚ፡-

1. ከሌላ አስቀድሞ ከተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ሲሆን፤

2. በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ከሰፈሩት እውነተኛ ዓላማዎቹና ሥራዎቹ አንጻር ህብረተሰቡን ሊያሳስት የሚችል ሲሆን፤

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ምንም ግንኙነት ሳይኖረው በሆነ መልኩ ከመንግሥት ወይም ከማንኛውም የመንግስት አካል ወይም ከማናቸውም የስዎች ስብስብ ወይም ግለሰብ ወይም የንግድ ድርጅት ጋር ግንኙነት አለው የሚያሰኝ ግምት የሚፈጥር ሲሆን፤

   ኤጀንሲው ስያሜው እንዲቀየር ያደርጋል፡፡

6. <u>መተዳደሪያ ደንብ ስለሚይዛቸው ዝርዝሮች</u>

1. የማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

   ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ስያሜ፣ አድራሻና ዓላማ፤

   ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን አደረጃጀት፤

   ሐ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የበጀት ዓመት፤

   መ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፤

ሠ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች የሚመረጡበት ወይም የሚቀጠሩበት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የሥራ ዘመናቸው፤

ረ/ አባላት ወይም የሥራ መሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አባልነታቸው ወይም የሥራ መሪዎች ስለሚቀርበት ሁኔታ፤

ሰ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ የበላይ አካልና አመራር አካላት የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት፤

ሸ/ ማህበር ከሆነ አባላትን የሚቀበልበትና የሚያሰናብትበት ሥርዓት እና ስለ አባላቱ መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚያደርጉት መዋጮ፤

ቀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለሚሻሻልበት ሥነ-ሥርዓት፤

በ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የገቢ ምንጮች፣

ተ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አርማ ወይም ምልክት ካለው ይህንኑ፤

ቸ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሲፈርስ ተፈጻሚ ስለሚሆነው ሥነ-ሥርዓት፣ እና

ኀ/ ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ባህሪ አንጻር አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች፡፡

2. ኤጀንሲው ባዘጋጀው ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ሳይሆን የራሱን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ የሚቀርብ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለምዝገባ ከሚጠየቀዉ ክፍያ በተጨማሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘወዉ ሠንጠረዥ የተመለከተውን መተዳደሪያ ደንብ ማስገምገሚያ ክፍያ ይከፍላል።

## 7. ወዲያው ስለሚፈፀም ምዝገባ

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የኤጀንሲውን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ለመጠቀም ፈቃደኛ የሆነ፣ የፕሮጀክት መግለጫ ማቅረብ የማይጠበቅበትና ሕብረት ያልሆነ የኢትዮጵያ ማህበር ወዲያዉኑ ይመዘገባል፡፡

2. ወዲያውኑ መመዝገብ የሚችሉ የኢትዮጵያ ማህበራት የሚገለገሉበትን ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን ኤጀንሲው ያዘጋጃል።

3. ወዲያውኑ የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መልኩ መመዝገብ ያልነበረበት ሆኖ ሲገኝ፡-

   ሀ/ መደበኛ ምዝገባ ለማድረግ የሚጠየቀዉ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ከተደረገ በኋላ የተመዘገበበት ቀን ሳይቀየር በአዋጁ አንቀጽ 68 መሠረት እንደተመዘገበ ይቆጠራል፤

   ለ/ ለመደበኛ ምዝገባ የሚያስፈልገውን ቀሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ቢኖርም ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ 92 ሥልጣን በተጠቀሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ላይ ከመፈጸም አያግደውም፡፡

5. ኤጀንሲው ወዲያውኑ ስለሚመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. <u>ህብረት ስለመመስረት</u>

1. ማናቸውም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የጋራ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚፈጠር ህብረት እንደ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መመዝገብ አለበት፡፡

2. ሕብረት ለመመስረት የሚፈልጉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት የእያንዳንዱ ድርጅት ወይም ማህበር የበላይ አካል ወይም በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ስልጣን የተሰጠው አካል ውሳኔውን ያስተላለፈበትን ቃለ-ጉባኤ ማቅረብና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ለመደበኛ ምዝገባ የተመለከተውን ክፍያ መክፈል ይኖርባቸዋል።

9. <u>ምዝገባን በማስመልከት የሚቀርቡ ተቃውሞዎች</u>

ማንኛውም ሰው አንድ አመልካች በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት መመዝገቡ ወይም የለም፣ አርማ ወይም ምልክቶች ለውጥ ማድረጉ የሚጎዳው ሲሆን ምዝገባውን ወይም በመዝገብ ውስጥ የሚሰፍረውን ማናቸውንም ዝርዝር ሊቃወም ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ተቃውሞ የሚቀርበውና የሚወሰነው ኤጀንሲው በሚዘረጋው ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

10. <u>በድጋሚ ስለሚደረግ ምዝገባ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ያለምንም ክፍያ ኤጀንሲው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በድጋሚ ይመዘገባሉ። ድጋሚ ምዝገባ የሚካሄድበት ዝርዝር በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡
2. የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ድጋሚ ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

11. <u>ምልክቶችን ስለማስመዝገብ</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊጠቀምበት የወሰነውን አርማ ወይም ምልክት በጥቅም ላይ ከማዋሉ በፊት ለኤጀንሲው ማቅረብና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. አርማ ወይም ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርበው ማመልከቻ የአርማውን ወይም የምልክቱን ቅጂ እንዲሁም አላማ፣ ቅርጽ፣ ይዘት፣ ቀለምና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
3. ለምዝገባ የቀረበው አርማ ወይም ምልክት ተቀባይነት ያለው ከሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ እንዲገባ ይደረጋል፡፡
4. የአርማ ወይም ምልክት ምዝገባ ጥያቄውን ኤጀንሲው ካልተቀበለው ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ተቀባይነት አለማግኘቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 የተደነገገው ከአስፈላጊ ማስተካከያ ጋር ለአርማና ምልክቶች ማሻሻልና መለወጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

12. <u>የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂዎች</u>

1. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት እንደተመሰረተ የሚቆጠረው የድርጅቱ መሥራች ወይም እርሱ የወከለዉ ሰው ወይም ኤጀንሲው በአዋጁ መሰረት የአደራ ጠባቂ በሚሾምበት እና የተሾመው አደራ ጠባቂ በተሹሙቱ ተስማምቶ በተቀበለበት ቀን ነው፡፡
2. የአዋጁ አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአደራ ጠባቂዎቹ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ

ድርጅቱን ለማስመዝገብ የምዝገባ ጥያቄ ሳያቀርቡ ከቀሩ ኤጀንሲው ከአደራ ጠባቂነት እንዲነሱና በሌላ እንዲተኩ ያደርጋል፡

3. ኤጀንሲው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላ ባለው ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የአደራ ጠባቂዎቹ የምዝገባ ማመልከቻ ያላቀረቡበት ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን መስራች ወይም የሚመለከተውን የዘርፍ አስተዳዳሪ ሊያማክር ይችላል፡፡

13. <u>ስለአደራ ጠባቂዎችና ሦስተኛ ወገኖች ግንኙነት</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደራ ጠባቂዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም ኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትቱ ማናቸውንም ሕጋዊ ድርጊቶች ማከናወን አይችሉም።
2. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተላለፉ የአደራ ጠባቂዎች ከአደራ ጠባቂነት እንዲነሱና በሌላ እንዲተኩ ይደረጋል፡፡
3. የአደራ ጠባቂዎቹ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተላልፈው የፈጸሙት ድርጊት በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በአንድነት እና በነጠላ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የአደራ ጠባቂዎች ለሚፈጽሙት ድርጊት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡

14. <u>ፈቃድ ስለማሳደስ</u>

1. ፈቃድለማሳደስ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የኦዲት ሪፖርቶች ጋር የሚቀርብ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 76 የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

   ሀ/ የሦስት ቀጣይ ዓመታት የበጀት ዕቀድ፤

   ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከሚመለከተው የመንግሥት አስፈፃሚ አካል ጋር የገባዉ የፕሮጀክት ስምምነት ካለ ይህንኑ፤

   ሐ/ ሌሎች ኤጀንሲው የሚጠይቃቸዉ ሰነዶች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሥራ መሪ የተፈረመና ማመልከቻው ውስጥ የተመለከቱት መረጃዎች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የተሰጠበት መሆን ይኖርበታል። ለዕድሳት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡፡

3. ኤጀንሲው የዕድሳት ጥያቄን ውድቅ ካደረገ ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ኤጀንሲው የዕድሳት ጥያቄውን አስመልክቶ በመፍቀድም ሆነ በመከልከል የሚሰጠው ውሳኔ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል።

## 15. <u>ሕዝባዊ መዋጮ እና የበጎ አድራጎት ኮሚቴ</u>

1. በአዋጁ መሰረት ሕዝባዊ መዋጮ ለማካሄድ ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴን ለማፀደቅ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይገባዋል፡-
   ሀ/ ሕዝባዊ መዋጮ የሚደረግለት ወይም ኮሚቴ የሚቋቋምለት የበጎ አድራጎት ዓላማ፣
   ለ/ ህዝባዊ መዋጮው የሚካሄድበት ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራውን የሚሰራበት ቦታ ወይም የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ቀን፣
   ሐ/ ሕዝባዊ መዋጮው የሚካሄድበት ወይም የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራውን የሚያካሂድበት ዘዴ፤
   መ/ ሕዝባዊ መዋጮውን በበላይነት የሚመራዉ የሥራ መሪ ወይም ግለሰብ የሚመለከት መረጃ፣ ወይም የኮሚቴው የስራ መሪዎችና አባላት ዝርዝር መረጃ፣
   ሠ/ ኤጀንሲው በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች፡፡
2. በህዝባዊው መዋጮ ወይም በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የሚሰበሰበው ሀብት ከአገር ውጭ ላለ የበጎ አድራጎት ተግባር ሊውል የሚችልበት ሁኔታ ሲኖር ሕዝባዊ መዋጮው ወይም በጎ አድራጎት ኮሚቴው ያለ ኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ይሁንታ ሊፈቀድ አይችልም።

## 16. <u>ስያሜን፣ የሥራ ቦታን ወይም መተዳደሪያ ደንብን ስለመለወጥ ወይም ስለማሻሻል</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ 73 መሠረት ከለወጠ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ካሻሻለ ለዉጡን ወይም ማሻሻያውን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለኤጀንሲው ማቅረብና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በአዋጁ አንቀጽ 73 መሠረት የሥራ ቦታውን ከለወጠ ለውጡን በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው በጽሑፍ በማቅረብ ማስመዝገብ ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለማስመዝገብ የሚቀርበው ጥያቄ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን የበላይ አካል ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል የተፈለገው ስያሜ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ቅጂ መያዝ ይኖርበታል።
4. የስያሜን ወይም የመተዳደሪያ ደንብን ማሻሻያ በኤጀንሲው ለማስመዝገብ የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር ሠንጠረዥ የተመለከተው ይሆናል፡፡
5. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዲመዘገብለት የጠየቀው የስያሜ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ ያልተከለከለ ከሆነ ለውጡ ማሻሻያው ተመዝግቦ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መዝገብ እንዲሰፍር ይደረጋል።
6. ኤጀንሲው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያን ሲመዘግብ የተሻሻለውን ደንብ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ይሰጣል፡፡
7. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዲመዘገብለት ያቀረበውን የስያሜ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ጥያቄ ካልተቀበለው ምክንያቶችን ጨምሮ ማመልከቻው ተቀባይነት አለ ማግኘቱን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 17. <u>ስለመዋሐድና መከፋፈል</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለመዋሀድ ወይም ለመከፋፈል ሲወስን ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ጉዳዩን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ/ አግባብነት ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አካል የመዋሐድ ወይም የመከፋፈል ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ መስረጃ፤

ለ/ የተከፋፈሉትን ወይም የተዋሃዱትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ዝርዝር፤

ሐ/ ስለሚተላለፉት መብትና ግዴታዎች መጠን አግባብነት ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም የማህበሩ አካል የተደረገ ስምምነት፤

መ/ ውሳኔው መከፋፈል ከሆነ የንብረት ክፍፍሉ አፈጻፀም፤ እና

ሠ/ ሌሎች ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ዝርዝሮች፡፡

2. ኤጀንሲው መዋሐድና መከፋፈልን በሚመለከት ቀደም ሲል ተደርጎ የነበረው ምዝገባ በአዲሱ ሁኔታ መሠረት እንዲስተካከልና በጋዜጣ እንዲታተም የሚደርገዉ የመዋሐድና የመከፋፈል ንደትና ውሳኔ ተገቢነት ባላቸው ሕግጋትና መተዳደሪያ ደንቦች መከናወናቸውን አረጋግጦና ከዘህ ደንብ ጋር በትያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የመደበኛ ምዝገባ ክፍያ በማስከፈል ይሆናል።

18. ስለመቀየር

1. ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጁ መሠረት ፈቃድ አግኝቶ የተመዘገበ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበላይ አካሉ ውሣኔ ወደ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ደርጅትነት ወይም ማህበርነት ለቀየርና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለያገኝ ይችላል፡፡

2. ማንኛውም የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርነት ሲለወጥ በባለቤትነቱ ስር ያለን ከዉጥ ምንጭ የተገኘን ሀብት ለወጠዉ የበጎ አድራጎት ድርጀት ወይም ማህበር ሊያስተላልፍ አይችልም።

3. በዚሀ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተዉ መሰረት ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎ ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ለመለወጥ ያመለከተ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የነበረዉ ከዉጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት በድርጅቱ የበላይ አካል ወይም በኤጀንሲው ውሳኔ ተመሳሳይ ዓላማ ላለው የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይተላለፋል፡፡

4. ማናቸውም በክልል የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅትወይም ማህበር ከተመዘገበበት ክልል በተጨማሪ በሌላ ክልልዉስጥ መስራት ወይም አባላት

ማስመዝገብ ከፈለገ ለኤጀንሲዉ በማመልከት በዚህ ደንብ መሠረት መመዝገብ ይችላል፡፡

19. <u>በጋዜጣ ስለማሳተም</u>

1. ኤጀንሲዉ የተመዘገቡ፣ የታገዱ፣ የተሰረዙ እና የፈረሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ በጋዜጣ ያወጣል።
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ለኤጅንሲው አቅርቦ የሚያስመዘግበዉን ስም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ኤጀንሲው ለውጡ ወይም ማሻሻያዉ በተመዘገበበት ወቅት በጋዜጣ ማውጣት አለበት፡፡
3. ማንኛወም ለምዝገባ ያመለከተ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከምዝገባ ክፍያ በተጨማሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት በጋዜጣ ለማውጣት አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘወ ሠንጠረዥ የተመለከተዉን ክፍያ ይከፍላል።
5. የታገዱ፣ የተሰረዙ እና የፈረሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራትን ዝርዝር በጋዜጣ ለማውጣት የሚያስፈለውን የማሳተሚያ ወጪ ኤጀንሲው ይሸፍናል።
6. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ጉዳዮች ኤጀንሲው በሚወስነው ማንኛውም ጋዜጣ ያወጣል ወይም እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ሪፖርቶችና መረጃዎች</u>

20. <u>ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 78 መሰረት የሚዘጋጅ ዓመታ የሃሳብ መግለጫ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊይዝ ያገባል፡-

   ሀ/ በበጀት ዓመቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ የገቢና ወጪ ሂሳብ፤

   ለ/ የገቢ ምንጭ በተለያም ከውጭ የተገኘ ገቢ እና የአስተዳያርና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ድርሻ ማብረሪያ፤

   ሐ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በአመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን አጠቃላይ ሀብት፣ እዳ እና ካፒታል የሚያሳይ የሂብት ሚዛን መግለጫ፤

መ/ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋለውን የሂሳብ አሰራር መግለጫ፤ እና

ሠ/ ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝሮች፡፡

2. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከማናቸውም ምንጭ የሚያገኙትን ገቢ እና የአስተዳደርና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ማስላትን የሚመለከቱ ዝርዝር መስፈርቶችን ያወጣል።

3. ኤጀንሲው የአስተዳደራዊ ስራዎችን ለመለየት የሚያስችል መመሪያ ያወጣል።

4. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሕዝባዊ መዋጮ ካካሄደ የሂሳብ መግለጫው ሕዝባዊ መዋጮውን በሚመለከት ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

## 21. ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራ

1. በአዋጁ አንቀጽ 79 መሰረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊጠቅስ ይገባል፡-

   ሀ/ የሂሳብ መዛንብቱና መግለጫው የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ እና ያሉበትን ሁኔታ በሚገባ የሚያሳይ መሆኑን፤

   ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩን አጠቃላይ ሃብት መዛግብትን ጨምሮ የሂሳብና ሌሎች መዛግብትን በአግባቡ መያዙን፤

   ሐ/ የሂሳብ መዛግብቱና መግለጫው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከውጭ የሚያገኘውን ገቢ ለይቶ በሚያሳይ መልኩ መቀመጡን፤

   መ/ ኦዲተሩ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ዝርዝሮች፤ እና

   ሠ/ ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝሮች፡፡

2. በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕዝባዊ መዋጮ ያካሄደ ከሆነ የኦዲት ሪፖርቱ በመዋጮው የተሰበሰበውን ገንዘብ በተገቢወ የሂሳብ አያያዝ መያዙን ወይም መጠበቁን የሚ፤ያመላክት ዝርዝር ሊያካትት ይገባል።

## 22. ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

1. በአዋጁ አንቀጽ 80 መሰረት የሚዘጋጅ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት የሚከተሉትን ዝርዝሮች ሊይዝ ይገባል፡-

   ሀ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማውን ለማሳካት የቀረባቸው የረጅምና አጭር ጊዜ እንዲሁም ሲኖረው ዓመታዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ፤

ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸው ተግባራት ማጠቃለያና አጠቃላይ ግምገማ፤

ሐ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚፈፅማቸው ያልተጠናቀቀ ፕሮጀክቶች ዝርዝር፤

መ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በወቅቱ ያለውን ሃብት ሊያውል ያቀደበት ዓላማ ማብራሪያና የአጭርና ረጅም ጊዜ ዕቅዱ፤

ሠ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሕዝባዊ መዋጮና ገቢ ማስገኛ ስራዎችን ካከናወነ ይህን የሚያብራራ ራሱን የቻለ መግለጫ፤ እና

ረ/ ሌሎች በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝሮች፡፡

2. የኢትዮጵያ ሴቶች፣ ወጣቶች እና መሰል ብዙሃን ማህበራት የሥራ ክንውን ሪፖርት ለኢጀንሲው ለማቅረብ አይገደዱም፡፡

3. በኤጀንሲው ግምት አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር በጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማውን የመፈፀም ተግባር በዓመቱ ምንም ያላከናወነ ከሆነ በኤጀንሲው የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ሆኖም በቀጣዩ ዓመትም ምንም ተግባር ካላከናወነ ፈቃዱ በኤጀንሲው ይሰረዛል፡፡

23. ገቢ ስለሚያስገኝ ሥራ

1. በአዋጁ አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚያዝ የሂሳብ መዝገብ የሚዘጋጀው የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ግብር ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ በሆነ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ ደረጃ መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡

2. የአዋጁ አንቀጽ 92 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማንኛውም የበጎ አድራጎተ ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኝ ሥራዎቹን በተመለከተ የተለየ የሂሣብ መዛግብትን ያልያዘ እንደሆነ ወይም የሂሳብ መዝገበን በተገቢዉ ሁኔታ ያልያዘ እንደሆነ ኤጀንሲው ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ለመሰማራት የተሰጠውን ፈቃድ ሊያግድበት ወይም ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርቶ ያገኘውን ገቢ ከዓላማዉ ውጭ አውሎ የተገኘ እንደሆነ ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ 92 የተመለከተውን አግባብ ያለው እርምጃ ይወስዳል።

24. ስብሰባን አለማሳወቅ

1. የአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 86 መሠረት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ ከሰባት የሥራ ቀናት አስቀድሞ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ ሳያሳውቅ የቀረ ማንኛውም ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም።

25.<u>የባንክ ሂሣብን ስለመክፈትና ስለማሣወቅ</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ለኤጀንሲው ማሳወቅና የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ያሉትን የባንክ ሂሳቦች በአዋጁ አንቀጽ 83 መሠረት ከሚከተሉት ዝርዝሮች ጋር ለኢጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ/ ያሉትን የባንክ ሂሳቦች ብዛት፣ ዓይነት እና የተከፈቱበት ባንክና የቅርንጫፍ ባንኩ ስም እና የባንክ ሂሳቦቹ መለያ ቁጥር፤

ለ/ የባንክ ሂሳቡ በማን እንደሚንቀሳቀስ፤

ሐ/ በየጊዜው የሚቀርብ የሂሳብ መግለጫ፤

መ/ ኤጀንሲዉ በመመሪያ የሚጠይቃቸዉ ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ መረጃዎች፡፡

3. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ ሂሳብ ሊከፍት የሚችለው በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም በማህበሩ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ባንክ ብቻ መሆን አለበት፡፡
4. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የባንክ የሂሳቡን ከዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርቱ ጋር ወይም ኤጀንሲው በጽሁፍ በሚጠይቀው በማናቸውም ጊዜ በኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡

26. <u>አባላትንና የሥራ መሪዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች</u>

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንደ ሁኔታው አባላቱንና የሥራ መሪዎቹን ዝርዝር መረጃዎች መመዝገብና መጠበቅ እንዲሁም ለኤጀንሲው ማስተላለፍ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያዘው መረጃ የሚከተሉትን ዝርዝሮች
ማካተት ይኖርበታል፡-
ሀ/ የአባላት፣ የሥራ መሪዎችንና የበላይ አካል አባላትን ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ዜግነት፤ የመኖሪያ አድራሻና የትምህርት ደረጃ፤
ለ/ የሥራ መሪዎችና የበላይ አካል አባላት የኃላፊነት ደረጃ ፣ ተግባርና ኃላፊነት እና የሥራ ቦታ፤ እና
ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ በኤጀንሲው የሚወሰኑ መረጃዎች፡፡
3. ማንኛውም የበጎ አድጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) ስር የተጠቀሱትን መረጃዎች እና እንደአግባብነቱ የአባላቱን ስም፣ ዕድሜና ፆታ ከዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት ጋር እንዲሁም ኤጀንሲው በሚጠይቅበት በማንኛውም ጊዜ ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም የኢትዮጵያ ብዙሃን ማህበራት የአባላታቸውን ብዛት ከማሳወቅ በስተቀር የአባላትን ዝርዝር መረጃዎች ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡
5. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ ወይም የበላይ አካል አባል ሲለውጥ ለውጡ በተደረገ በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡
6. ኤጀንሲው ከማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር አባላቱን ወይም የሥራ መሪዎችን በሚመለከት የሚፈልገዉን ዝርዝር መረጃ ሲጠይቅ በጽሁፍ መሆን አለበት።
7. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በኤጀንሲው የተፈለገውን ዝርዝር መረጃ ኤጀንሲው በሚያስቀምጠው አግባብነት ባለው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡
8. በአዋጁ አንቀጽ 92 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ያላሟላን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በጊዜ ገደብ የተወሰነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት መረጃውን እንዲያሟላ ሲያደርግ ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ አይችልም፡፡

27. <u>የጥቅም ግጭት</u>

1. የበጎ አድራጎት ድርጅትን ወይም ማህበርን ወክሎ ከሦስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት በሚፈፀምበት ጊዜ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እና በእርሱ መካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱን ያወቀ የሥራ መሪ ወይም ተወካይ ለበጎ አድራጎት ማህበሩ የበላይ አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ወይም ኤጀንሲው በበጎ አድራት ድርጅት ወይም ማህበር እና የሥራ መሪ ወይም ተወካይ መካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱን ካወቀ ለበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡
3. የጥቅም ግጭት ስለመከሰቱ መረጃ የደረሰው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚመለከተው አካል ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ጥቅም አንፃር ግጭት የተከሰተበት ግንኙነት የመቀጠል ወይም የአለመቀጠል ጉዳይ ላይ ይወሰናል፡፡ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ጋር የጥቅም ግጭት ውስጥ የገባው የሥራ መሪ ወይም ተወካይ በዚህ ውሳኔ አሰጣጥ ሲሳተፍ አይችልም።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተሰጠ ውሳኔዎች ተመዝግበዉ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በሚያቀርብበት ጊዜ ለኤጀንሲው መቅረብ አለባቸው።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት የጥቅም ግጭት መፈጠሩን ያላሳወቀ የሥራ መሪ ወይም ተወካይ አንቀጽ 90 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

28. <u>የምዝገባ የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለማሳየትና ስለማስታወቂያ ሰሌዳ</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 75 ድንጋጌን ያላከበረ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሚፈለገዉን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ዉስጥ እንዲፈጸም ኤጀንሲው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚሰጥ ማስጠንቀቀያ ከአንድ ጊዜ በላይ ሲሰጥ አይችልም፡፡

## 29. ስለኤጀንሲው ትዕዛዞች

1. በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም በማህበር በኤጀንሲው የሚሰጥ ማናቸዉም ትእዛዝ በጽሑፍ ሆኖ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መፈፀም እንዳለበት መገለጽ ይኖርበታል።
2. በኤጀንሲው ትእዛዝ የተሰጠዉ የበጎ አድረጎ ድርጅት ወይም ማህበር በትእዛዙ መሠረት ስለመፈፀሙ የተፈፀመበትን ቀን ለኤጀንሲው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።
3. የማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የሥራ መሪ የአዋጁን፤ የዚህን ደንብ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች በሚጥስበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ጥፋቱን እስኪያርም ወይም በወንጀል ተከሶ ፍርድ እስኪያገኝ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በሌላ እስኪተካ ድረስ በኤጀንሲው ከኃላፊነት ታገድ ይችላል፡፡
4. ኤጀንሲው በአዎጁ መሠረት ዕገዳ የተጣለበት የሥራ መሪ ወይም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የዕገዳዉ ምክንያት የሆኑ ጥፋቶችን በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማስተካከል እንደሚገባው በመግለጽ በጽሑፍ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

## 30. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ቦርድ

1. በአዋጁ አንቀጽ 7(1) የተመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ቦርድ አባል የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ እንደገና ለመሰየምም ገደብ አይኖርበትም፡፡
2. የቦርድ አባል ሲሞት፣ ሲለቅ ወይም ከኃላፊነት ሲነሳ የሥራ ዘመኑ እስከሚያበቃ ድረስ ተተክቶ የሚሠራ አዲስ አባል ይሰየማል።
3. ቦርዱ ከቦርዱ አባላት ውጭ የሆነ በኤጀንሲው የሚመደብና የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን ፀሐፊ ይኖረዋል፡-

ሀ/ የቦርዱን የውስጥ ጉዳዮች ይመራል፤

ለ/ ለቦርዱ የሚቀርቡትን ማመልከቻዎች ይቀበላል፤

ሐ/ የቦርዱን ውሳኔ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

መ/ የቦርዱን ሰነዶች ይይዛል፤

ሠ/ ሌሎች በቦርድ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

## 31.ቅጾችና ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦች

ኤጀንሲዉ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች አስፈላጊ የሆኑ ቅፆችን እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን ያዘጋጃል።

32. <u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

1. ኤጀንሲዉ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡
2. የፍትህ ሚንስትሩ[20] አግባብ ሆኖ ሲያገኘዉ ለማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ ደንብ መሠረት ለምዝንባ ወይም ለሌላ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን በከፊል ወይም በሙሉ ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

33. <u>ውክልና ስለመስጠት</u>

የፍትህ ሚኒስቴር[21] በአዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (8) የተሰጠውን የሃይማኖት ድርጅቶችን የመመዝገብ ሥልጣን በውክልና ለኤጀንሲው ሊሰጥ ይችላል፡፡

34.<u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ኤጀንሲው ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

35. <u>ፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈግሚነት አይኖረውም፡፡

36. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ/ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

---

[20] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 38(3)(ሐ) የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ሆኖል፡፡
[21] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 38(3)(ሐ) የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ሆኖል፡፡

## ሠንጠረዥ

## የአገልግሎቶች ክፍያዎች

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ዩ.ኤስ.ዲ |
| 1 | መ□በኛ ምዝ□ባ | 500.00 | |
| 2 | የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ምዝገባ | | 300.00 |
| 3 | ወዲያውኑ ምዝገባ | 400.00 | |
| 4 | የአርማና ምልክት ምዝገባ | 100.00 | |
| 5 | የሥያሜና መተዳደሪያ ደንብ ለውጥና መሻሻል ምዝገባ | 100.00 | |
| 6 | ዕድሳት | 400.00 | |
| 7 | የተፈረሙና የተረጋገጡ የመተዳደሪያ ደንቦች | 100.00 | |
| 8 | ቆሚ □ሚ□ስቶች ሥራ□ችና ሕ□ባዊ መኸ□ ማስ□ቀት | 150.00 | |
| 9 | የደንበኞች መመሪያ | 20.00 | |
| 10 | የማመልከቻ ቅጽ | 5.00 | |
| 11 | የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ማና□ቅ | 200.00 | |
| 12 | የሰነድ ትክክለኛ ቅፀ በ□ | 5.00 | |
| 13 | የመተዳደሪያ ደንብ ማስገምገምያ | 200.00 | |
| 14 | □□□ ማሳተሚ□፤<br>ሀ) በምዝ□ባ ወቅት | □□ቅቱ □ማሳተሚ□ ኻ□ □ማሽ | |
| | ለ) በስ□ሜ ለውጥ ወቅት | □□ቅቱ □ማሳተሚ□ ኻ□ | |

ለ/ በህግ የተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት

## አዋጅ ቁጥር 153/1991

## የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የተሻሻለው ቻርተር አዋጅ

ቀይ መስቀል በዘር፡ በቀለም ፡ በዜግነት፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በማንኛዉም ሌላ ሁኔታ ልዩነት ሳያደርግ በጦር ሜዳ ለሚቆስሉና ለሚጎዱ በአጠቃላይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ለሚጠቁ ሰዎች ተፈላጊውን ሰብአዊ ዕርዳታ በፍጥነት የሚሰጥና በሰዎች ዘንደ መግባባት፡ መተባበር ወዳጅነትና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የሚጥር ዓለምአቀፍ እንቅስቃሴ በመሆኑ፡

የዚህ እንቅስቃሴ አካል የሆነውና በ1927 ዓ/ም የተመሠረተዉ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በመንግሥትና በኅብረተሰቡ በተለይም በአባላቱ ጠንካራ ድጋፍ በመዋቅር ስፋትም ሆነ በአገልግሎት አቅርቦት እያደገ መምጣቱን በመገንዘብ፣

ማኅበሩ በአደጋዎች ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ ከማቅረቡም በተጨማሪ በሃገሪቱ የልማት ሥራዎች ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሚያደርገው ተሳትፎ እንዲሁም ዝቅተኛ የሆነውን የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ በአነስተኛና በመሠረታዊ መመዘኛዎች ተቀባይነት ወደ አለው ደረጃ ለማሸጋገር ለሚደረገው ጥረት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ፤

ከአካባቢያዊ አየር ማዛን መናጋትና ከተፈጥሮ ሃብቶች መራቆት ጋር በተዛመደ መልክ የሚከሰቱትን የድርቅና የረሃብ አደጋዎች በመከላከሉ ጥረት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ተገቢና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

ማኅበሩ ዓላማውንና ተልዕኮውን ለማሳካትና ዓለምአቀፍ ግዴታውን በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ለመወጣት እንዲችል አደረጃጀቱን ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አደረጃጀት አንጻር እንደገና በማዋቀር በየክልሉ እንዲደራጅ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 21/1982 ተሻሽሎ የነበረው የማኅበሩ ቻርተር እንደገና እንዲሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የተሻሻለው ቻርተር አዋጅ ቁጥር 153/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ቻርተር ውስጥ፡-

1. "ክልል" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 47 (1) እንደተመለከተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞችን ይጨምራል፤
2. "ቀበሌ" ማለት የገጠር ወይም የከተማ ቀበሌ መስተዳድር የተቋቋመበት አካባቢ ነው፤
3. "የቀይ መስቀል ወጣት" ማለት ከ14–30 ዓመት ባለው ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር አባል ነው፤
4. "የጀኔቫ ስምምነቶች" ማለት ለጦር ጉዳተኞች ሊሰጥ የሚገባውን ከለላ በሚመለከት እ.ኤ.አ ኦገስት 12 ቀን 1948 የተፈረሙት የጀኔቫ የቀይ መስቀል ስምምነቶችና እ.ኤ.አ በ1977 የተፈረሙት ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ናቸው፡፡

3. **የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር**

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር (ከዚህ በኋላ "ማኅበሩ" እየተባለ የሚጠራ) በህግ የሰውነት መብት ያለው ሀገር አቀፍ ማኅበር ሆኖ የተቋቋመበትን ተግባር በዚህ ቻርተር መሠረት ማከናወኑን ይቀጥላል፡፡

4. **የማኅበሩ ዓርማ**

1. የማኅበሩ ዓርማ በነጭ መደብ ላይ በጉልህ የሚታይ ቀይ መስቀል ነው፡፡
2. የዓርማው ቅርጽና አጠቃቀም በጀኔቫ ስምምነቶችና ብሔራዊ ማኅበራት በአርማው የሚጠቀሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በተደነገገው ደንብ መሠረት የተወሰነ ይሆናል፡፡

5. <u>መሠረታዊ መርሆዎች</u>

የማኀበሩ መሠረታዊ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ሰብአዊነት፤
2. አለማዳላት፤
3. ገለልተኝነት፤
4. የአሠራር ነጻነት፤
5. የበጐ ፈቃድ አገልጋይነት፤
6. አንድነት፤
7. ዓለምአቀፋዊነት፡፡

6. <u>ዓላማ</u>

የማኀበሩ ዓላማ የጀኔቫ ስምምነቶችንና በአንቀጽ 5 የተመለከቱትን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል የሰውን ልጅ ሰቃይና መከራ መከላከልና ማቃለል እንዲሁም ለሰው ልጅ ሰላም፣ ደህንነትና እድገት መሥራት ይሆናል፡፡

7. <u>ተግባራትና ችሎታ</u>

ማኀበሩ የሚከተሉት ተግባራትና ችሎታ ይኖሩታል፡-

1. ከባድ ችግር ወይም ድንገተኛ አደጋ በደረሰ ጊዜ የተጐዱ ሰዎች ተፈላጊውን ዕርዳታ በፍጥነትና በሚገባ እንዲያገኙ ማድረግ፤
2. በጦርነት ጊዜ ለተጐዱ የጦር አባላትም ሆነ ሰላማዊ ህዝብ በጀኔቫ ሰምምነቶችና በመሠረታዊ መርሆዎቹ መሠረት ዕርዳታ ማድረግ፤ ለዚህም በሰላም ጊዜ ተዘጋጅቶ መገኘት፤
3. በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉትን መልሶ ማቋቋምና በልማት ተግባር ላይ ተሰማርተው ራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
4. በሽታዎችን ለመከላከል፣ ለህዝብ የጤና አገልግሎት ለማዳረስ፣ የጤና ባለሙያዎችን ለማሰልጠን በአጠቃላይ የጤንነት ሁኔታን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት መተባበርና መርዳት የመሠረተ ጤና ክብካቤ ተግባራት የሚስፋፉበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር መቀየስና መተግበር፤

5. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በደን ልማት፣ በንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ እና በመሳሰሉት የአካባቢና የኅብረተሰብ ልማት ተግባራት በመሳተፍ ተገቢውን አስተዋጽኦ ማድረግ፣
6. በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለአደጋ በቀላሉ የሚጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ በተለይም የሴቶችንና ሕጻናትን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ከተጠቂነት ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት ማገዝ፣
7. በሰዎች ሁሉና በሃገሮች መካከል የመግባባትና የመተባበር መንፈስ እንዲዳብር ለማገዝ ለሰብአዊ አገልግሎቶች መሠረት የሆኑት የጀኔቫ ስምምነቶች በኅብረተሰቡ ዘንድ በስፋት እንዲታወቁ ማድረግ፣
8. የዓለምአቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ መሠረታዊ መርሆዎች በሕዝብ ዘንድ በይበልጥ እንዲታወቀ ጥረት ማድረግ፣
9. አባላትንና የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎችን ማበራከት፣
10. የቀይ መስቀል ወጣቶች እንቅስቃሴ በወጣቶችና በሌላውም ኅብረተሰብ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲስፋፋ ማድረግ፣
11. በአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ለመስጠት የሚዘጋጁትን፣ ለኅብረተሰቡ ደኅንነት አገልግሎት የሚያበረክቱትንና ሌሎችም የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎችን በማኅበሩ ሥራ እንዲሰለጥኑና እንዲያገለግሉ ማድረግ፤
12. ከቀይ መስቀልና ከቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካላትና ከሌሎችም ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በማስፋፋትና በማጠናከር በዓለም ላይ መግባባትና ሰላም እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ፣
13. ከዓላማውና ተግባሩ ጋር በማይቃረን ሁኔታ ለማኅበሩ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ቋሚ ገቢ የሚያስገኙ ልዩ ልዩ ዕቅዶችን መተለም፣ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ ራስን ለመቻል የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር፣
14. የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን፣
15. ውል መዋዋል፣
16. በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣
17. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ አባልነት

### 8. አባል ስለመሆን

የማኅበሩን መርሆዎች በሥራ ለመተርጎም ፈቃደኛ የሆነ ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በዜግነት፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግበት አባል ሊሆን ይችላል፡፡

### 9. የአባልነት ዓይነቶች

የአባልነት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፣

1. መደበኛ አባልነት፣
2. የዕድሜ ልክ አባልነት፣
3. የክብር አባልነት፣
4. የድርጅት አባልነት፣
5. የቀይ መስቀል ወጣት አባልነት፡፡

### 10. ለአባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደተጠበቁ ሆነው ለአባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡

   ሀ/ ሀገራዊ ጠቅላላ ጉባዔው በሚወስነው መሠረት የዓመቱን የአባልነት ክፍያ መክፈል፤

   ለ/ ከአባልነት ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት ለማኅበሩ ማበርከት፤ ወይም

   ሐ/ ማኅበሩ የሚፈልገውን ዓይነት አገልግሎት በነፃ መስጠት፡፡

2. ማንኛውም ግለሰብ የዕድሜ ልክ አባል ለመሆን የሚችለው በሀገሪቱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት ለዕድሜ ልክ አባልነት የሚከፈለውን ገንዘብ በአንድ ጊዜ በመክፈል ወይም ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት በስጦታ መልክ በማበርከት ወይም ከክፍያው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ነፃ አገልግሎት በመስጠት ነው፡፡

3. የክብር አባል ለመሆን የሚቻለው ከማኅበሩ መርሆዎች ጋር በተዛመደ ሁኔታ ከፍተኛ ሰብአዊ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በማበርከት ሲሆን፤ የሚፈቀደውም በሀገራዊው ጠቅላላ ጉባዔ ነው።

### 11. የአባልነት መብቶች

1. ማንኛውም መደበኛ ወይም የዕድሜ ልክ አባል እንዲሁም ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው የቀይ መስቀል ወጣት አባል፡

ሀ/ በማኅበሩ የቀበሌና ቅርንጫፉን ወክሎ በሚገኝባቸው የማኅበሩ ስብሰባዎች ላይ ለመገኘትና ድምፅ ለመስጠት፡ እና

ለ/ በማናቸውም ደረጃ ከማኅበሩ መሪዎች አንዱ ሆኖ ለመመረጥ፡ ይችላል፡፡

2. የድርጅት አባልነትን ወክሎ በማኅበሩ ጠቅላላ ስብስባዎች የሚገኝ ሰው ድምጽ ለመስጠት ይችላል፤ ሆኖም ለመመረጥ አይችልም።

3. የክብር አባል በማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባዎች በመገኘት ሃሣብ ለመስጠት ይችላል፣ ሆኖም ድምጽ ለመስጠትም ሆነ ለመመረጥ አይችልም፡፡

4. በየደረጃው በሚገኙ ቦርዶች በአባልነት የሚመረጡ የማኅበሩ አባሎች የአገልግሎት ዘመናቸው ሲያልቅ እንደገና ለመመረጥ ይችላሉ። ሆኖም አንድ አባል ከሁለት የምርጫ ዘመናት በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም።

12. <u>አባልነት የሚሠረዝበትና የሚታደስበት ሁኔታ</u>

1. አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሠረዝ ይችላል፤

ሀ/ የየንመቱ የአባልነት ክፍያ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲቋረጥ፣

ለ/ አባልነቱ የተገኘው ለማኅበሩ ነፃ አገልግሎት በመስጠት ከሆነ ይኸው አገልግሎት ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲቋረጥ፣ ወይም

ሐ/ የማኅበሩ መሠረታዊ መርሆዎች በአባሉ መጣሳቸው ሲረጋገጥ፡፡

2. የዘመኑን መዋጮ በመክፈል ወይም የተቋረጠውን አገልግሎት እንደገና በመቀጠል ወይም ከክፍያው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት በመስጠት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የተሠረዘ አባልነትን ማደስ ይቻላል።

3. አባልነት የሚሠረዘው እንደአግባቡ በወረዳ፣ በዞን ወይም በክልል ወይም በብሔራዊ ቦርድ ሲሆን ውሳኔውን ለማስለወጥ የሚቀርብ ይግባኝ የሚታይበት ሥርዓት በማኅበሩ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የማኅበሩ አደረጃጀት</u>

13. <u>የበላይ ጠባቂ</u>

የማህበሩ የበላይ ጠባቂ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ወይም ማኅበሩ ዓላማውን ከግቡ እንዲያደርስ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ የሚሰጥና

በሕዝብ የበለጠ እንዲታቀፍ የሚያበረታታና አገልግሎቱ እንዲስፋፋ የሚረዳ በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሰየም ሰው ይሆናል፡፡

14. **የማኅበሩ አወቃቀር**

1. የማኅበሩ አደረጃጀት በአገር አቀፍ ደረጃ አንድነትን የሚያሳይ ሆኖ፣ ከህዝብ ጋር ይበልጥ ተቀራርቦ መሥራት እንዲችል በሀገሪቷ ፌዴራላዊና ክልላዊ አደረጃጀት መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተመለከተው መሠረት ተዋቅሯል።

2. ማህበሩ፤

ሀ/ በአገር አቀፍ ደረጃ፣

1. ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. ቦርድ፣
3. ዋና ጽሕፈት ቤት፣

ለ/ በክልል ደረጃ፣

1. ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. ቦርድ፣
3. ጽሕፈት ቤት፣

ሐ/ በዞን ደረጃ፣

1. ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. ቦርድ፣
3. ጽሕፈት ቤት፣

መ/ በወረዳ ደረጃ፣

1. ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. ቦርድ፣
3. ጽሕፈት ቤት፣

ይኖሩታል፡፡

3. ማኅበሩ በቀበሌ ደረጃም እንደአስፈላጊነቱ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ሊኖረው ይችላል።

15. **የማኅበሩ አገር አቀፍ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት**

አገር አቀፍ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1. የአገር አቀፍ ቦርድ አባላት፣
2. ከእያንዳንዱ ክልል በምርጫ የሚወከሉ አምስት አምስት አባላት፣
3. ከሚከተሉት መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች አንዳንድ ተወካይ፣

ሀ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

ለ/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣

ሐ/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣

መ/ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን፣

ሠ/ የደኅንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን።

4. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ተወካይ፣
5. የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ተወካይ፣
6. የቀይ መስቀል ሠራተኞች ማኅበር ተወካይ፣
7. በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሠረት የሚጨመሩ ሌሎች አባላት፡፡

16. <u>የአገር አቀፉ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

የአገር አቅፍ ጠቅላላ ገባዔው ማኅበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ የማኅበሩ ከፍተኛ አካል ሲሆን የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. ከአባላቱ መካከል መርጦ በሚያቋቁመው አስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት ዕጩ ሆነው ከሚቀርቡ በአንቀጽ 11(1) ከተመለከቱት አባላት መካከል የቦርድ አባላትን በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት መምረጥ፣
2. ለቦርዱ አስፈላጊውን አጠቃላይ የፖሊሲ መመሪያ መስጠትና አፈጻጸሙንም መከታተል፣
3. ቦርዱ የሚያቀርበውን የማኅበሩን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድና በጀት ማፅደቅ፣
4. የቦርዱንና የኦዲተሮችን ዘገባ መርምሮ ማጽደቅ፣
5. በቦርዱ የተወሰኑ በበጀት ያልተመለከቱ ከፍተኛና አስቸኳይ የድንገተኛ አደጋ ወጭዎች ካሉ መርምሮ ማጽደቅ፣
6. ቦርዱ በሚያቀርበው ሃሣብ መሠረት የአባልነት ክፍያንና የክልል ጽ/ቤቶች ለማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት የሚያደርጉትን የመዋጮ መጠን መወሰን፣
7. ቦርዱ በሚያቀርበው ሃሣብ መሰረት ከማኅበሩ መርሆዎች ጋር በተዛመደ መልኩ ከፍተኛ ሰብአዊ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ለአበረከቱ የክብር አባልነትን እንዲሁም የማኅበሩን ከፍተኛ ሜዳይና ሽልማት ሊያገኙ የሚገባቸውን ተሸላሚዎች መወሰን፤
8. ለሁለት ዓመታት የሚያገለግል የማኅበሩን ኦዲተር መሰየም፣

9. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ የማኅበሩን ቻርተር ማሻሻልና እንዲጸድቅ ለመንግሥት ከመቅረቡ በፊት የብሔራዊ ማኅበራት ቻርተሮችን ለመመርመር ከቀይ መስቀል ኢንተርናሽናል ኮሚቴና ከፌዴሬሽኑ ተውጣጥቶ ለተቋቋመው ጥምር ኮሚሽን ማቅረብ፤

10. የማኅበሩን አካላትና ጽ/ቤቶች አወቃቀር ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ በዚህ ቻርተር ላይ ተመስርቶና የክልሎችን ሃሣብ በማካተት ተዘጋጅቶ ከቦርዱ የሚቀርብለትን ደንብ ማጽደቅ።

17. <u>የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች</u>

1. የአገር አቀፍ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በየሁለት ዓመት የማኅበሩ የበጀት ዓመት በተፈጸመ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።
2. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ የጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡
3. ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ ሊጠራ የሚችለው፡-

   ሀ/ በቦርዱ ውሳኔ፡ ወይም

   ለ/ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል በአንድ ሦስተኛው ድምጽ ሲጠየቅ ነው።
4. የጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ የሚደረግ መሆኑን የሚያመለክት ማናቸውም ማስታወቂያ፣ የቦርዱና የኦዲተሮች ዘገባዎች እንዲሁም ጉባዔው የሚነጋገርባቸው ሌሎች ጉዳዮች ዝርዝር ስብሰባው ከሚጀመርበት አንድ ወር አስቀድሞ ለጉባዔው አባላት መላክ ይኖርባቸዋል።
5. የጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ስብሰባ የሚነጋገርባቸው ጉዳዮች ዝርዝር ስብሰባው ከሚጀመርበት ጊዜ አሥራ አምስት ቀን አስቀድሞ ለገባዔዉ አባላት እንዲላክ ይደረጋል።

18. <u>የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሥነ ሥርዓት</u>

1. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በማኅበሩ ፕሬዚዳንት ይመራል።
2. በዚህ ቻርተር አንቅጽ 30 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

   ሀ/ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡

   ለ/ ማናቸውንም ወሳኔ ማሳለፍ የሚቻለው በድምጽ ብልጫ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) ምልዓተ ጉባዔ ያልተገኘ እንደሆነ ጉባዔው በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ወስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ይጠራል፡፡ በሁለተኛ ጥሪ

የተሰበሰበው ጉባዔ በተገኙ አባላት የድምጽ ብልጫ ወሳኔዎችን ሊያሳልፍ ይችላል።

4. እያንዳንዱ የጠቅላላ ጉባዔ አባል አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፡፡
5. የጉባዔው ውይይቶችና ወባኔዎች ጉባዔው በመረጠው ዘጋቢ ተይዘው በፕሬዚዳንቱና በዘጋቢው ይፈረማሉ።

19. <u>የአገር አቀፍ ቦርድ አባላት</u>

1. የማኅበሩ አገር አቀፍ በርድ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል።
2. የማኅበሩ ዋና ጸሐፊ ድምጽ የማይሰጥ አባልና ጸሐፊ ይሆናል።

20. <u>የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

በአንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ (4) የተገለፀዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ለአራት ዓመታት ይሆናል፡፡

21. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የማኅበሩን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚያስችለው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል። ይህም የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ይሆናል፡-

1. ከአባላቱ መካከል፣

   ሀ/ የማኅበሩን ፕሬዚዳንት፣

   ለ/ የማኅበሩን ምክትል ፕሬዚዳንት፣

   ሐ/ የማኅበሩን ዓቃቤ ንዋይ፣

   መ/ የአማካሪ ኮሚቴዎችን ሰብሳቢዎች፣

   መምረጥ።
2. በዚህ ቻርተር አንቅጽ 7 የተመለከተው የማኅበሩ ተግባር በሚገባ መከናወኑን ማረጋገጥ፣
3. የማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት ሥራ በሚገባ መከናወኑን መከታተልና መቆጣጠር፣
4. የማኅበሩን ዋና ጸሐፊ መምረጥና መመደብ ኃላፊነቱን የማይወጣ ሆኖ ሲገኝ ከሥራ ማሰናበት፤
5. በማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት በቀጥታ ለዋናው ጸሐፊ ተጠሪ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ ማጽደቅ፤
6. በተሰየመው ኦዲተር የተመረመረዉን የሂሳብ ሪፖርት በየሁለት ዓመት ለጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ፤

7. የማኅበሩን የሁለት ዓመታት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርትና የተከታዩን የሁለት ዓመታት የሥራ ዕቅድና በጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ማስጸደቅ፣

8. የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በማይደረግበት ጊዜ የጉባዔውን ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ መስጠትና በሚቀጥለው ስብሰባ አቅርቦ ማስጸደቅ፤

9. ከማኅበሩ የፋይናንስና ንብረት አማካሪ ኮሚቴ በሚቀርበው ሃሣብ መሠረት የማኅበሩን የመጠባበቂያና ሌሎች ልዩ ልዩ ሂሣቦች ማቋቋምና አጠቃቀማቸውንም መወሰን፤

10.የማኅበሩ መሠረታዊ መርሆዎች በየደረጃው በሚገባ መከበራቸውንና በሥራ መተርጐማቸውን ማረጋገጥ፤

11.የአባልነትን ክፍያ መጠን እንዲሁም ክልሎች ለዋናው ጽ/ቤት ስለሚያደርጉት የመዋጮ መጠን ለጠቅላላ ጉባዔው ሃሣብ ማቅረብ፤

12.ስለውጭ እርዳታ አስፈላጊነትና አጠቃቀም መወሰን፤

13.የቀይ መስቀልና የቀይ ጨረቃ ዓለምአቀፍ ድርጅቶችና እህት ማኅበራት አስፈላጊ ሲሆን ከማኅበሩ ጋር በኅብረት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠሩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመነጋገር ፈቃድ መስጠት፣

14.የክብር አባልነት የሚሰጣቸው ሰዎችን ለጠቅላላ ጉባዔው ማቅረብና ማስጸደቅ፣

15.ከቦርድ አባላት መካከል አንዳንዶቹ በአባልነት ሊቀጥሉ ያልቻሉ እንደሆነ እስከ ተከታዩ ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ ድረስ የሚያገለግሉ ሌሎች አባላት መርጦ መተካት።

16.ጊዜያዊ ወይም ቋሚ አማካሪ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማቋቋም፣ ተግባራቸውንም መወሰን፤

17.የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ ጊዜን፣ ቦታና አጀንዳ መወሰን፤

18.ማኅበሩን በመወከል የውጭ ግንኙነት ማድረግ፤

19.የራሱን የውስጥ ደንብና የአሠራር መመሪያ ማውጣት፤

20.በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን።

## ክፍል አራት

## የማኅበሩ የሥራ መሪዎች ሥልጣንና ተግባር

22. <u>ጠቅላላ</u>

የማኅበሩ የሥራ መሪዎች ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በዚህ ቻርተርና በማኅበሩ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

23. <u>የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፡

1. የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርድ ስብሰባዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል፡
2. የጠቅላላ ጉባዔውና የቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡
3. ቦርዱ ሊሰበሰብ በማይችልበት ጊዜ ከዋናው ጽ/ቤት በሚቀርቡ አስቸኳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሳኔዎቹንም በተከታዩ የቦርዱ ስብሰባ አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡

24. <u>የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት፡

1. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሠራል፤
2. ቦርዱ በተለይ የሚሰጠውን ተግባር ያከናውናል።

25. <u>የማኅበሩ ዓቃቤ ንዋይ ሥልጣንና ተግባር</u>

የማኅበሩ ዓቃቤ ንዋይ፡

1. የማኅበሩን የፋይናንስና ንብረት አማካሪ ኮሚቴ በሊቀመንበርነት ይመራል፡
2. የማኅበሩን የንብረትና የገንዘብ አስተዳደር ሁኔታ በተመለከተ በየወቅቱ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል።

26. <u>የማኅበሩ ዋና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የማኅበሩ ዋና ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ፤

1. የማኅበሩን ዋና ጽ/ቤት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡ ይቆጣጠራል፡
2. በዚህ ቻርተርና በማኅበሩ የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የማኅበሩ ልዩ ልዩ ተግባሮች በሚገባ መከናወናቸዉን የረጋግጣል፣
3. የማኅበሩን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ከሌሎች የቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካላት ጋር እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሀገራዊና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ ከነዚሁ ጋር ውሎችን ከመፈረሙና ማኅበሩ ላይ ሕጋዊ ግዴታዎችን የሚያስከትሉ ተግባራትን ከመፈጸሙ በፊት ቦርዱን ያስፈቅዳል፡

4. ለሥራ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል፤
5. የማኅበሩን የሥራ ዕቅድና ፕሮግራም እንደዚሁም በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፡ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡
6. የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርዱን ውሳኔዎች ሥራ ላይ ያዉላል፡
7. በየዓመቱና እንደአስፈላጊነቱ በየወቅቱ የማኅበሩን የሂሣብ መግለጫዎች ለቦርዱ ያቀርባል፤
8. ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር የቦርድ ስብሰባዎችን አጀንዳ አዘጋጅቶ ከአስፈላጊው ሠነዶችና መረጃዎች ጋር ለእያንዳንዱ አባል ይልካል፡
9. ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለዋና ጸሐፊው በሆኑ የማኅበሩ ዋና ጽጤት የሥራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን ኃላፊዎች በመምረጥ ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤
10.በማኅበሩ አማካሪ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ይሳተፋል ወይም ሌላ ሰው ይወክላል፤
11.የማኅበሩ ዋና ጽ/ቤትን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡ ያሰናብታል፡
12.ለዚህ ቻርተር አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑትን የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎች ለቦርዱ በማቅረብ ያስጸድቃል በሥራ ላይ ያውላል፡
13.ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ማኅበሩን ይወክላል፤
14.ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## ክፍል አምስት

## ስለማኅበሩ ገቢና የሂሣብ መግለጫዎች

### 27. የማህበሩ የገቢ ምንጮች

ማኅበሩ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፤

1. ከአባልነት ክፍያ፤
2. ከውርስ፡ ከስጦታ እና ከዕርዳታ ከሚገኝ ገንዘብና ንብረት፡
3. ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች
4. ከመንግሥት ከሚስጥ ጠቅላላ ወይም የፕሮግራም ድጎማ፡
5. ከአምቡላንስና ከሌሎች አገልግሎቶች፤
6. ከሌሎች የገቢ ምንጮች፡

28. <u>የማኅበሩ የበጀት ዓመት</u>

የማኅበሩ የበጀት ዓመት ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ቀን ይሆናል፡፡

29. <u>ስለዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ አቀራረብ</u>

1. የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እስከ 6 ወር ድረስ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሣብ ሪፖርት ለቦርዱ ይቀርባል፡፡
2. በየሁለት ዓመቱ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሣብ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ይቀርባል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

30. <u>የቻርተሩ መሻሻል</u>

ይህ ቻርተር ከሀገራዊ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት ሁለት ሦስተኛው ተገኝተው ከዚህ ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የተስማሙበት ሃሣብ ለመንግሥት ቀርቦ ሲፈቀድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

31. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በዚህ ቻርተር መሠረት ምርጫና የሥራ ድልድል እስከሚደረግ ድረስ በሥራ ላይ ያሉ የማኅበሩ ተመራጮች ሥራቸውን ይቀጥላሉ።

32. <u>የውስጥ ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

በዚህ ቻርተር በሌሎች አንቀጾች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ለዚህ ቻርተር አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑትን የውስጥ ደንቦች ለማውጣት ይችላል፡፡

33. <u>የተሻረ ሕግ</u>

በመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ ቁጥር 21/1982 የተሻሻለው የማኅበሩ ቻርተር ተሽሮ በዚህ ቻርተር ተተክቷል።

34. <u>ቻርተሩ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ቻርተር ከየካቲት 2 ቀን 1991 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲትቀን 1991 ዓ/ም
ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## አዋጅ ቁጥር 341/1995

## የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ማቋቋሚያ

የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ሀገሪቱ ከምትከተለዉ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር እንደገና ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

በሀገሪቱ ንግድ፣ እንዱስትሪና እንቨስትመንት እንዲስፋፋ ለማደረግ ምክር ቤቶች ጉልህ ሚና ሊኖራቸዉ እንደሚችል ስለታመነበት፣

የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የንግዱ ኅብረተሰብ አባላት ስለትስማሩበት ሥራና በአጠቃላይ ስለአገሪቱ ኢኮኖሚ ልማት የሚወያዩበትና ለመንግሥት ሃሳብ የሚያቀርቡበት መድረክ ሁኖ እንዲያገለግሉ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጸ 55 (1) መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡—

   1. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው።[22]
   2. "ምክር ቤት" ወይም "ምክር ቤቶች" ማለት እንደ አግባቡ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቋቋም የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ወይም የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ነው።
   3. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴምክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከቱትን ክልሎች ማለት ሲሆን አዲስ አበባን እና ድሬዳዋን ይጨምራል፡፡

[22] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9 (10) መሠረት የንግድ ሚኒስቴር ስለሆነ በዚህ አዋጅ በዚሁ መሠረት ይነበብ፡፡

4. "የዘርፍ ማኅበር" ማለት አምራች ድርጅቶች በየተሰማሩበት መስክ የጋራ ጥቅማቸዉን ለማስጠበቅ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 404 መሠረት ያቋቋሙት ሕጋዊ ማኅበር ነው፡፡

5. "ነጋዴ" ወይም "የንግድ ስራ" የተባሉት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1990[23] አንቀጽ 2(2) እና 2(3) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛል፡፡

## 3. ዓላማ

ምክር ቤቶች የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖራቸዋል፡-

1. ለንግዱ ኅብረተሰብ የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት፤
2. የአባሎቻቸዉን መብትና ጥቅም ማስከበር፤
3. የሀገሪቱን ምርቶችና አገልግሎቶች እንዲታዉቁ ገበያ እንዲያገኙ ማደረግ፤
4. የሀገሪቱን ንግድና ኢንቨስትመንት ማሳደግ፤
5. በመንግስትና በንግዱ ማህበረሰብ መካከል እንደአገናኝ ደልድይ ሆኖ ማገልገል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

## 4. የኢትዮጵያ ንግድ እና የዘርፍ ማኅበሪት ምክር ቤት መቋቋም

የሕግ ሰዉነት ያለውና ዋና ጽሕፈት ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሆነ የኢትዮጵያ ንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

## 5. ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ምክር ቤቶች በየደረጃው እንዲቋቋሙ ማበረታት፣ ከተቋቋመም በኋላ ደጋፍና እገዛ ማድረግ፣
2. ለምርቶችና አገልግሎቶች የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ መፈለግ፣
3. ለውጭ ገበያ ተፈላጊነት ያላቸዉን ምርቶች በመለየት፣ መጠንና ጥራታቸዉን በማሻሻል እና በንግድ ሥራ ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ በመፈለግ ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተሳትፎ ማድረግ፣

---

[23] በ22/ነ01 (2008) ሉ. 980 ተሸሯል፡፡

4. ከውጭ አገር ንግድ ምክር ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ የልምድና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣
5. የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የንግድ ትርዒት ማዘጋጀት ወይም መሳተፍ፣
6. በንግዱ ማኅበረሰብ አባላት መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠርና ባለጉዳዮቹ ሲጠይቁ በግልግል አይቶ መወሰን፣
7. ከመንግሥት ውክልና ሲሰጥ የአምራች አገር የምስክር ወረቀትና የምርቶች ዋጋ ማረጋገጫ መስጠት፣
8. የንግድ ጋዜጣ፤ መጽሔትና ሪፖርት ማዘጋጀት እንዲሁም ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ማጠናቀር እና የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠት፣
9. ንግድ ነክ የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለአባሎቻቸው ማሳወቅ፣ መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች መሳተፍ፣
10. ከአባላቱ የሚደረግለትን መዋጮ መወሰን፣
11. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣
12. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣
13. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

6. <u>**አደረጃጀት**</u>

1. የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፦

   ሀ/ አንድ ጉባዔ፤

   ለ/ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ አንድ የሥራ አመራር ቦርድ፣

   ሐ/ አንድ ፕሬዚዳንት፣ አንድ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ አንድ ዋና ፀሐፊ እና አስፈላጊው ሠራተኞች፣

   ይኖሩታል።

7. <u>**አባላት**</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24(2) መሠረት በሚኒስቴሩ የሚወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሚከተሉት አበላት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የክልል የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ተዋካዮች፣

ለ/ የአገር አቀፍ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተወካዮች፣

ሐ/ የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ተወካዮች፣

2. አባላቱ የምክር ቤቱን ጉባዔ ይመሰርታሉ፤
3. የምክር ቤቱ የተወካይ አባላት ብዛት በጉባዔው ይወሰናል፤
4. በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች የሚቋቋሙ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች በቀጥታ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባል ይሆናሉ፡፡
5. በአንድ ክልል ከአንድ በላይ የከተማ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች በሚኖሩ ጊዜ ምክር ቤቶቹ በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ውስጥ የሚወከሉት በክልሉ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አማካኝነት ብቻ ይሆናል፣
6. የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የጉባዔ አባላት የድምጽ ውክልና፦

   ሀ/ የክልል የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱን የመሠረቱትን የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን አባላት ብዛት፣

   ለ/ የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱን አባላት ብዛት፣

   ሐ/ አገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱን የመሠረቱትን የክልል ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አበላት ብዛት መሠረት በማድረግ በጉባዔው ይወሰናል፡፡
7. ጉባዔው ከአባላቱ መካከል ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፣ ተመራጮችም የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ይሆናሉ።

8. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

   ሀ/ የምክር ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ መርሃ ግብር ያፀድቃል፣

   ለ/ የምክር ቤቱን የቦርድ አባላት ይመርጣል፤

   ሐ/ የምክር ቤቱን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች የሚመረምር ኦዲተር ይመድባል፣

መ/ ከዋና ፀሐፊውና ከሂሣብ መርማሪው የሚቀርቡትን ሪፖርቶች ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣

ሠ/ የምክር ቤቱን ውስጠ ደንብ ያፀድቃል፣ ምክር ቤቱን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. ጉባዔው እንደአግባቡ ሥልጣኑንና ተግባሩን ለቦርዱ ፣ ለፕሬዚዳንቱ ፣ ለምክትል ፕሬዚዳንቱ ወይም ለዋና ፀሐፊው በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

9. <u>ስብሰባ</u>

1. ጉባዔው በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. ከጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣
3. ጉባዔው ውሣኔ የሚሰጠው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ድምጹ ዕኩል ለዕኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

10. <u>ስለቦርድ አባላት</u>

1. ጉባዔው ከአባላቱ ውስጥ ፕሬዚዳንቱንና ምክትሉን ጨምሮ ከ11 የማይበልጡ ተወካዮችን በቦርድ አባልነት ይመርጣል፤
2. ፕሬዚዳንቱ የቦርዱ ሰብሳቢ ይሆናል፣
3. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፤
4. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡–

1. የጉባዔው ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
2. የምክር ቤቱን ዋና ፀሐፊ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣
3. ከዋና ፀሐፊው በሚቀርብለት የምክር ቤቱ የመምሪያና አገልግሎት ኃላፊዎች ቅጥርና ስንብት ላይ ውሣኔ ይሰጣል፣
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ወይም ከጉባዔው አባላት አንድ ሦስተኛው ሲጠይቁ የጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዚዳንቱ አማካኝነት እንዲጠራ ያደርጋል፣
5. የምክር ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ለጉባዔው ያቀርባል፤
6. ከዋና ፀሐፊው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፣
7. ቦርዱን የሚረዱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡

8. ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊ የሆነ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## 12. የፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር

1. የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት፡-

   ሀ/ የጉባዔውንና የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፣

   ለ/ የጉባዔውን አስቸኳይ እና መደበኛ ስብሰባ ይጠራል፡፡

2. የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣

3. የፕሬዚዳንቱና የምክትል ፕሬዚዳንቱ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

## 13. የዋና ፀሐፊው ሥልጣንና ተግባር

1. የዋና ፀሐፊው ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡ ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ምክር ቤቱን ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን ዋና ፀሐፊው፡-

   ሀ/ ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የምክር ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣

   ለ/ የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፣ ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፡ ደመወዝና አበላቸውን ይወስናል፣

   ሐ/ ለመምሪያና አገልግሎት ኃላፊነት የሚመርጣቸውን ዕጩዎች ለቦርዱ ያቀርባል፣

   መ/ ለምክር ቤቱ አባልነት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መርምሮ ይወስናል፣

   ሠ/ የምክር ቤቱ ገቢ መሰብሰቡን ያረጋግጣል፣

   ረ/ በቦርዱ የተቋቋሙትን ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሥራ ይረዳል ፣ ሥራቸውንም ያስተባብራል፣

   ሰ/ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የምክር ቤቱን የባንክ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

ሸ/ የምክር ቤቱ የበጀት ዓመት ከመጀመሩ ከሦስት ወራት በፊት ዓመታዊ በጀትና የሥራ መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ቀ/ ስለምክር ቤቱ የገንዘብ አቋምና የሥራ አፈፃፀም ሁኔታ ሪፖርት እያዘጋጀ የበጀት ዓመቱ በተፈፀመ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ያቀርባል፣

በ/ የምክር ቤቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ሦስት

## ስለክልል የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች

14. መቋቋም

1. በማንኛውም ክልል የተቋቋሙ የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች እና የክልል ወይም የወረዳ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የክልላቸውን የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሊያቋቁሙ ይችላሉ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች ዋና መሥሪያ ቤት በክልሉ ዋና ከተማ ይሆናል፣
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች በዚህ አዋጅ መሠረት የየራሳቸው የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል።

15. ሥልጣንና ተግባር

የክልል የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል ፡-

1. የከተማ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን፣ የክልል እና የወረዳ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ተግባራት ማስተባበር፡
2. ለምርቶችና አገልግሎቶች የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ መፈለግ፡
3. በንግዱ ማኅበረሰብ አባላት መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠርና ባለጉዳዮቹ ሲጠይቁ በግልግል አይቶ መወሰን፣
4. በክልሉ ውስጥ ምክር ቤቶች ባልተቋቋሙባቸው ከተሞች ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ድጋፍና እገዛ ማድረግ፣
5. ከከተማ ንግድ ምክር ቤቶች ጋር በመሆን በፌዴራልም ሆኑ በክልል መንግሥታት የሚወጡትን ንግድ ነክ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና

መመሪያዎች ለክልሉ ንግድ ኅብረተሰብ ማሳወቅ፣ መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች መሳተፍ፣

6. አባላት የሚያደርጉላቸውን መዋጮ መወሰን፣
7. የክልሉን የንግድ ጋዜጣ፣ መጽሔትና ሪፖርት ማዘጋጀት፣ እንዲሁም የክልሉን ስታቲካዊ መረጃዎችን ማጠናቀር እና የተለያዩ ሥልጠናዎችን መስጠት፣
8. በንግድ ሥራ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን በማጥናት ከሚመለከታቸው የክልል አካላት እና ከኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ጋር በመወያየት መፍትሔ መፈለግ፣
9. ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ንግድ ምክር ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የልምድና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣
10. የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የንግድ ትርዒት ማዘጋጀት ወይም መሳተፍ፣
11. ከመንግሥት ውክልና ሲሰጥ የአምራች አገር የምሥክር ወረቀት መስጠት
12. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣
13. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣
14. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

16. <u>አባላት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24(2) መሠረት በሚኒስቴሩ የሚወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሚከተሉት አባላት ይኖሯቸዋል፡-

   ሀ/ የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ተወካዮች፣

   ለ/ የክልል ዘርፍ ማኅበራት ተወካዮች፣

   ሐ/ የወረዳ የዘርፍ ማኅበራት ተወካዮች፣
2. አባላቱ የምክር ቤቱን ጉባዔ ይመሰርታሉ፣
3. የተወካይ አባላት ብዛት በጉባዔው ይወሰናል፣
4. የክልል የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የጉባዔ አባላት የድምጽ ውክልና፡-

ሀ/ የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱን የመሠረቱትን አባላት ብዛት፣

ለ/ የክልል ዘርፍ ማኅበሩን የመሠረቱትን የወረዳ ዘርፍ ማኅበራት አባላት ብዛት፣

ሐ/ የወረዳ ዘርፍ ማኅበሩን የመሠረቱትን አባላት ብዛት፣ መሠረት በማድረግ በጉባዔው ይወሰናል፡፡

5. ጉባዔው ከአበላቱ መካከል ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፣ ተመራጮችም የክልል ንግድ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ይሆናሉ።

## 17. ተፈፃሚነት ስላላቸው ድንጋጌዎች

የዚህ አዋጅ አንቀጽ (6)፤ (8)፣ (9)፣ (10)፤ (11)፣ (12) እና (13) እንደ አግባቡ በክልል የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤቶች

## 18. መቋቋም

1. የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤቶች በክልል ወይም በመስተዳድር ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ሊቋቋሙ ይችላሉ፤

2. በአንድ ከተማ አንድ የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤት ብቻ ይቋቋማል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች በዚህ አዋጅ መሠረት የየራሳቸው የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል፣

4. ምክር ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ባሉበት ከተማ ውስጥ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን ማቋቋም ይችላሉ።

## 19. ሥልጣንና ተግባር

የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤቶች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፣

1. ለምርቶችና አገልግሎቶች የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ መፈለግ፣

2. ለውጭ ገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በመለየት፣ መጠንና ጥራታቸውን በማሻሻል እና በንግድ ሥራ ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ በመፈለግ ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተሳትፎ ማድረግ፣
3. በንግዱ ማኅበረሰብ አባላት መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠር እና አባላት ሲጠይቁ በግልግል አይቶ መወሰን፤
4. አባላቱ የሚያደርጉለትን መዋጮ መወሰን፣
5. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዋጋ ማስከፈል፣
6. ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ንግድ ምክር ቤቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር የልምድና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣
7. የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የንግድ ትርኢት ማዘጋጀት ወይም መሳተፍ፣
8. ከመንግሥት ውክልና ሲሰጥ የአምራች አገር የምሥክር ወረቀት መስጠት፣
9. የንግድ ጋዜጣ፤ መጽሔትና ሪፖርት ማዘጋጀት፤ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ማጠናቀር እና የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠት፣
10. ንግድ ነክ የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለአባሎች ማሳወቅ፣ መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች መሳተፍ፣
11. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣
12. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

20. <u>አባላት</u>

1. ቋሚ የንግድ ቦታቸው ምክር ቤቱ ባለበት ከተማ የሆነና ሕጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24(2) መሠረት በሚኒስቴሩ መመሪያ የሚገለጹት የዘርፍ ማኅበራት የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባል ለመሆን ይችላል፣
2. የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባልነት በፈቃደኝነት ይሆናል፣
3. የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱ አባላት ጉባዔውን ይመሠርታሉ፣
4. ምክር ቤቱ ባልተቋቋሙባቸው ከተሞች የሚገኙ ነጋዴዎች የከተማቸውን ምክር ቤት እስኪያቋቁሙ ድረስ በአጎራባች ከተማ በሚገኝ ምክር ቤት አባል ለመሆን ይችላሉ፣

5. የወረዳ ዘርፍ ማኅበራት አባላት የሆኑ አምራቾች የከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤት አባል ለመሆን ይችላሉ፣
6. እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል በጉባዔው ስብሰባ እኩል ድምፅ ይኖረዋል፤
7. የከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አባላት የሆኑ የወረዳ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የድምጽ ውክልና በአባሎቻቸው ብዛት ይሆናል፡፡

21. <u>ስለ ቦርድ አባላት</u>

1. ጉባዔው ከአባላቱ ዉስጥ ፕሬዚዳንቱንና ምክትሉን ጨምሮ ከ11 የማይበልጡ አባላትን በቦርድ አባልነት ይመርጣል፤
2. ፕሬዚዳንቱ የቦርዱ ሰብሳቢ ይሆናል፤
3. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፤
4. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

22. <u>ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ (6)፣ (8)፣ (9)፣ (11)፣ (12) እና (13) እንደ አግባቡ በከተማ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች</u>

23. <u>ስለዘርፍ ማኅበራት አመሠራረት</u>

የዘርፍ ማኅበራት የሚመሰረቱት በየዘርፉ በአምራችነት በተሠማሩ ድርጅቶች ባለቤቶች ይሆናል፡፡

24. <u>ስለዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አደረጃጀት</u>

1. በየዘርፉ የተመሠረቱ፡ የአምራቾች ዘርፍ ማኅበራት፣ የአምራቾች የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶቻቸውን በወረዳ ወይም በክልል ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፣
   ሀ/ የአምራች ድርጅቶች ባለቤቶች በየዘርፉ የመሠረቷቸው የዘርፍ ማኅበራት የየወረዳውን የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ያደራጃሉ፣
   ለ/ በየወረዳዎች የተቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የየክልሉን የዘርፍና ማኅበራት ምክር ቤቶች ያደራጃሉ፣

ሐ/ የክልል ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አንድ የአገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያደራጃሉ።

2. ሚኒስቴሩ፣-

ሀ/ ከወረዳ ወይም ከክልል ደረጃ ጀምረው ወይም ከመነሻው በአገር አቀፍ ደረጃ ብቻ ሊደራጁ የሚገባቸው የዘርፍ ማኅበራት እነማን እንደሆኑ፣

ለ/ የትኞቹ የዘርፍ ማኅበራት በንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ውስጥ ለመወከል እንደሚችሉ፣ እና

ሐ/ በንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ውስጥ የሚወከሉት የዘርፍ ማኅበራት ሊያሟሉት የሚገባውን መሥፈርት በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

25. <u>ዓላማ</u>

በየደረጃቸው የሚቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖራቸዋል።

1. አምራቾች በየሥራ ዘርፋቸው የሚደራጁበትንና የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
2. በገጠርና በከተማ ዕደ ጥበባት አምራቾችን ማበረታታት፣
3. የአገሪቱ ምርቶች የጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣
4. የምርት መረጃዎችን ማጠናቀርና ማሠራጨት፣
5. አባላት ዕውቀታቸውን፣ ሀብታቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
6. አባላት ጥቅማቸውን በጋራ ለማስጠበቅ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
7. አባላት በየዘርፋቸው ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ አስመልክቶ መረጃዎችን የሚለዋወጡበትን መድረክ መፍጠር፣
8. የዘርፍ ማኅበራት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ከመንግሥት ጋር የጋራ ውይይት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

26. <u>ስለዘርፍ ማኅበራት መቋቋም</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 እና 24 መሠረት ተመስርተው የተደራጁ የወረዳ የክልል እና አገር አቀፍ ዘርፍ ማኅበራት በዚህ አዋጅ መሠረት የየራሳቸው የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል፣

2. የወረዳ እና የክልል ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ዋና መሥሪያ ቤታቸው በወረዳው ወይም በክልሉ ዋና ከተማ ሲሆን፤ የአገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል።

27. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

1. አገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

   ሀ/ የክልል ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ተግባራት ማስተባበር፣

   ለ/ አምራቾች በሥራ ሂደታቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እያጠኑ ለሚመለከተው የፌዴራል የመንግሥት አካል የመፍትሔ ሃሣብ ማቅረብ፤

   ሐ/ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የምርት ትርዒት ማዘጋጀት ወይም መሳተፍ፣

   መ/ በጋራ የማምረትና የግብይት አቅማቸውን ለማሳደግ በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ መምከር እና መተግበር፣

   ሠ/ በንግዱ ማህበረሰብ አባላት መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠርና ባለጉዳዮች ሲጠይቁ በግልግል አይቶ መወሰን፣

   ረ/ የምርት ጋዜጣ፣ መጽሔትና ሪፖርት ማዘጋጀት፤ የቴክኖሎጂና የገበያ መረጃዎችን ለአባሎቻቸው ማሰራጨት፣

   ሰ/ ለአባሎቻቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠት፣

   ሸ/ የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለአባሎቻቸው ማሳወቅ፤ መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች መሳተፍ፣

   ቀ/ ከአባላቱ የሚደረግላቸውን መዋጮ መወሰን፣

   በ/ ለሚሰጡት አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣

   ተ/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስማቸው መክሰስና መከሰስ፣

   ቸ/ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

2. የክልል ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል።

   ሀ/ የወረዳ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን ተግባራት ማስተባበር፣

ለ/ አምራቾች በሥራ ሂደታቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እያጠኑ ለሚመለከተው የክልል የመንግሥት አካል የመፍትሔ ሃሣብ ማቅረብ፤

ሐ/ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የምርት ትርዒት ማዘጋጀት ወይም መሳተፍ፣

መ/ የክልሉን አምራቾች በጋራ የማምረትና የግብይት አቅማቸውን ለማሳደግ በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ መምከር እና መተግበር፣

ሠ/ በንግዱ ማህበረሰብ አባላት መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠርና ባለጉዳዮች ሲጠይቁ በግልግል አይቶ መወሰን፣

ረ/ የምርት ጋዜጣ፣ መጽሔትና ሪፖርት ማዘጋጀት፤ የቴክኖሎጂና የገበያ መረጃዎችን ለአባሎቻቸው ማሰራጨት፣

ሰ/ ለአባሎቻቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠት፣

ሸ/ የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን ደንቦችንና መመሪያዎችን ለአባሎቻቸው ማሳወቅ፤ መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች መሳተፍ፣

ቀ/ ከአባላቱ የሚደረግላቸውን መዋጮ መወሰን፣

በ/ ለሚሰጡት አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣

ተ/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስማቸው መክሰስና መከሰስ፣

ቸ/ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

3. የወረዳ ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል።

ሀ/ አባሎቻቸው በሥራ ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እያጠኑ ለሚመለከተው የወረዳ የመንግሥት አካል የመፍትሔ ሃሣብ ማቅረብ፣

ለ/ የአባሎቻቸውን የማምረትና የግብይት አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

ሐ/ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የምርት ትርኢት ማዘጋጀት ወይም መሳተፍ፣

መ/ በንግዱ ማህበረሰብ አባላት መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠርና ባለጉዳዮች ሲጠይቁ በግልግል አይቶ መወሰን፣

ሠ/ የምርት ጋዜጣ፣ መጽሔትና ሪፖርት ማዘጋጀት፤ የቴክኖሎጂና የገበያ መረጃዎችን ለአባሎቻቸው ማሰራጨት፣

ረ/ ለአባሎቻቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠት፣

ሰ/ የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን ደንቦችንና መመሪያዎችን ለአባሎቻቸው ማሳወቅ፤ መንግሥት በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች መሳተፍ፣

ሸ/ ከአባላቱ የሚደረግላቸውን መዋጮ መወሰን፣

ቀ/ ለሚሰጡት አገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፣

በ/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስማቸው መክሰስና መከሰስ፣

ተ/ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

28. <u>ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ (6)፣ (8)፡ (9)፣ (11)፣ (12) እና (13) እንደ አግባቡ በአገር አቀፍ፣ በክልልና በወረዳ ደረጃ በሚቋቋሙ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

29. <u>ስለ ምክር ቤቶች ምዝገባ</u>

1. የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤ በክልል፣ በወረዳ እና በከተማ ደረጃ የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች ደግሞ በክልል በሚመለከታቸዉ ቢሮዎች አማካኝነት ምዝገባ በማድረግ ወረቀት ማግኘት አለባቸው፡፡
2. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የክልል የሚመለከታቸው ቢሮዎች የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችን የመመዝገብና የምስክር ወረቀት የመስጠት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል፡፡
3. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም የክልል የሚመለከታቸው ቢሮዎች የምዝገባ ጥያቄ በቀረበላቸው በ30 ቀናት ውስጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት መስጠት ወይም ጥያቄዉን ያልተቀበሉበትን ምክኒያት በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

4. በክልል፣ በወረዳ እና በከተማ ደረጃ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች ያገኙትን የምዝገባ ሠርተፊኬት ትክክለኛ ኮፒ በኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበር ምክር ቤት እንዲቀመጥ ያደርጋሉ፡፡

30. <u>የምክር ቤቶች የገቢ ምንጭ</u>

በየደረጃው የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፣

1. ከአባላት ከሚገኝ መዋጮ፣
2. ከአገልግሎት ክፍያ ከሚገኝ ገቢ፣
3. ከእርዳታና ድጋፍ ከሚገኝ ገቢ፡፡

31. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በሥራ ላይ ያሉ የንግድ ምክር ቤቶች አቋማቸውን በዚህ አዋጅ መሠረት ያስተካክላሉ፣
2. በአዋጅ ቁጥር 148/1970 መሠረት ተቋቁመው የነበሩት የንግድ ምክር ቤቶች መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ መሠረት አቋማቸውን ለሚያስተካክሉት ምክር ቤቶች ተላልፏል፣
3. ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች የሕግ ሰውነት የሚኖራቸው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 29 መሠረት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ካገኙበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል፡፡

32. <u>ኦዲተር</u>

1. የማናቸውም ምክር ቤት የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በውጭ ኦዲተሮች መመርመር አለበት፤
2. የምርመራ ውጤቱ ትክክለኛ ኮፒ እንደአግባቡ ለጉባዔው፣ ለቦርዱና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለሰጠው አካል የበጀት ዓመቱ ባለቀ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ መሰጠት አለበት።

33. <u>የበጀት ዓመት</u>

የምክር ቤቶች የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል፡፡

34. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያቋጣ ይችለል፡፡

35. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

36. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

1. ስለንግድ ምክር ቤቶች የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 148/1970 ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛዉም አይነት ዓይነት ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

37. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ/ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 781/2005

## የመለስ ፋውንዴሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነት፣ በመፈቃቀድና በአንድነት የሚኖሩባት አገር እንድትሆን ከልጅነት እስከ ሕልፈተ ህይወታቸው የከፈሉትን ከፍተኛ መስዋዕትነት መዘከር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ከለጋ ዕድሜያቸው ጀምሮ በአገራችን ሰላም፣ ልማት፣ መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ለማድረግ በሰጡት በሳል አመራር ከፍተኛ ውጤቶች የተመዘገቡ መሆኑን በመረዳት፤

ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የገበያ አክራሪነት በዓለም በተለይም በታዳጊ አገሮች ያስከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በመተንተን እና የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ እንዲሁም የአረንጓዴ ልማት አስተሳሰብ አማራጭ በማቅረብ በዓለም አቀፍ ደረጃ አወንታዊ ተጽዕኖ ለመፍጠር የቻሉ እንዲሁም በአፍሪካ አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ከፍተኛ አርአያነት ያለው ተግባር ያበረከቱ መሆኑን በመገንዘብ፤

ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የአገራችንን እና የሕዝባችንን ደህንነትና ዕድገት ለማረጋገጥ በሕይወት ዘመናቸው ለፈፀሙት መስዋዕትነትና ጥረት ዘላቂ መታሰቢያ የሚሆን ፋውንዴሽን ማቋቋም ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት፤

ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት አስተሳሰብ በማመንጨት፣ በመተንተን፣ በማስረጽና በመተግበር እንዲሁም በህዝብ አገልጋይነታቸውም ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ መሆናቸውን ለአሁኑና ለቀጣዩ ትውልድ ትምህርትነትና ልምድ የማስተላለፍ አስፈላጊነትን በመገንዘብ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመለስ ፋውንዴሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 781/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ምስል" ማለት በልዩ ልዩ ወረቀት፣ ሸራ፣ ወይም ሌላ የታተመ ወይም በማንኛውም ሁኔታ የተቀረፀ ወይም የተነሳ ወይም የተዘጋጀ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊን ፎቶግራፍ፣ ቅርፃቅርጽ፣ የኤሌክትሮኒክስ ቅጂ እና የመሳሰሉትን ያካትታል፤
2. "ስያሜ" ማለት የክቡር አቶ መለስ ዜናዊን ስም፣ ቅርጽ ወይም ድምጽ (ንግግር) እና የመሳሰሉትን ለመታሰቢያነት፣ ለመጠሪያነት፣ ለማስታወቂያነት ወይም ለሌሎች ማናቸውም አገልግሎቶች ማዋልን ያካትታል፤
3. "ስም" ወይም "ስብዕና" ማለት ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት አስተሳሰብን በማመንጨት፣ በመተንተን፣ በማስረጽና በመተግበር የነበራቸው ግንባር ቀደም ሚና ነው፤
4. "አግባብነት ያለው ስፍራ" ማለት አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የክቡር አቶ መለስ ዜናዊን ስም ወይም ምስል በመጠቀም ለእርሳቸው መታሰቢያ ለመስራት ወይም ሥራዎቻቸውን ለማስተዋወቅ ወይም ለማስተማሪያነት የሚሰየም ቦታን ያጠቃልላል፤
5. "ግንባታ" ማለት የመልካም ስም ማስታወሻ፣ ቅርጻቅርጽ፣ ሃውልት፣ተቋም እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤
6. "ጠቅላላ ጉባዔ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7(1) እና አንቀጽ 8(1) የተመለከተው የፋውንዴሽኑ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፤
7. "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7(2) እና አንቀጽ 12(1) የተመለከተው የፋውንዴሽኑ ቦርድ ነው፤
8. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>መቋቋም</u>

የመለስ ፋውንዴሽን (ከዚህ በኋላ "ፋውንዴሽን" እየተባለ የሚጠራ) በሕግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የፋውንዴሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ በሌሎች ስፍራዎች እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

5. <u>ዓላማ</u>

የፋውንዴሽኑ ዓላማ ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ በሕይወት ዘመናቸው ሲታገሉለት የነበሩትን የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት፣ የሰዎች ዲሞክራሲያዊ ግንኙነት፣ እኩልነት፣ ክብርና ብልፅግና እንዲረጋገጥ፣ የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ሚዛናዊ እንዲሆን የሚያደርግ የህብረተሰባዊ ለውጥ አስተሳሰብ እና የሰላም ፈለግ ማስቀጠል እና መርሆዎቻቸውን ማስፋፋት ይሆናል፡፡

6. <u>ተግባራትና የሕግ ችሎታ</u>

ፋውንዴሽኑ የሚከተሉት ተግባራትና የሕግ ችሎታ ይኖሩታል፡-

1. የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ አስከሬን የሚያርፍበትና በሕዝብ የሚጎበኝ መናፈሻ መገንባትና ማስተዳደር፤
2. ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የፃፏቸው መፃሕፍቶችና የተለያዩ ጽሑፎች፣ እርሳቸውን የሚመለከቱ ጥናታዊ ፊልሞች፣ የምስል፣ የድምፅና የመሳሰሉት መረጃዎች እንዲሁም ሌሎች ለምርምር የሚያግዙ መፃሕፍት ተደራጅተው የሚቀመጡበት እና በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውሉበት ቤተ መፃሕፍት ማቋቋም፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የሚቋቋሙ የህዝብ መናፈሻና ቤተመፃሕፍት ለህዝቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤
4. በሕዝቦች ሁሉና በአገሮች መካከል የመግባባትና የመተባበር መንፈስ እንዲዳብር በተለያዩ መንገዶች ትምህርት መስጠት፣ እገዛ ማድረግ፤

5. በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት፣በዲሞክራሲ፣ በሰላም፣ በህብረተሰባዊ ለውጥ አስተሳሰብ እና ተዛማጅ መስኮች ምርምር ለሚያደርጉ ሁሉ ለጥናትና ለምርምር አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

6. በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን ለመከታተል ለማይችሉ ዜጎች በተለይም ለሴቶች የነፃ የትምህርት ዕድል መስጠት፤ አቅም በፈቀደ መጠን ለውጭ አገር ዜጎችም የነፃ የትምህርት ዕድል መስጠት፤ ዓላማውን በማሳካት ረገድ ከትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ተባብሮ መሥራት፤

7. የአረንጓዴ ልማት አስተሳሰብ መስፋፋትንና መተግበርን መደገፍ፤

8. በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በሰላምና በዲሞክራሲ አስተሳሰብና ተግባር የላቀ አስተዋፆ ላበረከቱ ሰዎች ሽልማት መስጠት፤

9. ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ያጠናቀቋቸውንና የጀመሯቸውን የምርምር ጽሑፎች ማሳተምና እንዲሰራጩ ማድረግ፤ ሆኖም ከመንግሥትና ከፓርቲ ሰነዶች ውጪ የሆኑትን በሚመለከት በቅድሚያ የቤተሰቡን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፤

10. የክቡር አቶ መለስ ዜናዊን አስተሳሰብ ማስቀጠል፣ ማስፋፋትና ማዳበር፤

11. የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ስም፣ ምስል፣ ስራዎችና መታሰቢያዎች አጠቃቀም የሚመራበትን መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤ ሆኖም ከመንግሥትና ከፓርቲ ሥራዎች ጋር ያልተያያዘ ስም ወይም ምስል በመጠቀም ረገድ በቅድሚያ የቤተሰቡን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፤

12. የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል እና በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

13. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፋውንዴሽኑ አመራር

### 7. የአመራር አካላትና ሠራተኞች

ፋውንዴሽኑ፡-

1. ጠቅላላ ጉባዔ፤
2. ቦርድ፤
3. ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት፤
4. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር፤ እና

5. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

8. <u>የጠቅላላ ጉባዔው አባላት</u>

1. ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ቤተሰብ አራት ተወካዮች፤

ለ/ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ሦስት ተወካዮች፤

ሐ/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[24] ተወካይ፤

መ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ፤

ሠ/ የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ፤

ረ/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ፤

ሰ/ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ተወካይ፤

ሸ/ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ተወካይ፤

ቀ/ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሦስት ተወካዮች፤

በ/ የእያንዳንዱ ክልል አምስት አምስት ተወካዮች፤

ተ/ የወጣቶች ማህበራት ተወካይ፤

ቸ/ የሴቶች ማህበራት ተወካይ፤

ኀ/ በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሰረት የሚጨመሩ ሌሎች አባላት፡፡

2. የፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር የጠቅላላ ጉባዔው ፀሐፊ ይሆናል፡፡

9. <u>የጠቅላላ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ጠቅላላ ጉባዔው ፋውንዴሽኑን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል ይሆናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ከአባላቱ መካከል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(1) (ለ) የተመለከቱትን የቦርድ አባላት መምረጥ፤

ለ/ ለቦርዱ አጠቃላይ የፖሊሲ መመሪያ መስጠትና አፈፃፀሙን መከታተል፤

---

[24] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀፅ 9(6) መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

ሐ/ ቦርዱ የሚያቀርበውን የፋውንዴሽኑን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የስራ ዕቅድና በጀት ማጽደቅ፤

መ/ የቦርዱንና የፋውንዴሽኑን የውጭ ኦዲተር ሪፖርቶች መርምሮ ማጽደቅ፤

ሠ/ ለሁለት ዓመታት የሚያገለግል የፋውንዴሽኑን የውጭ ኦዲተር መሰየም፤

ረ/ በቦርዱ አቅራቢነት ሽልማቶችን በዚህ አዋጅ መሠረት መስጠት፤

ሰ/ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 6(11) መሠረት መመሪያ ማውጣት፡፡

10. <u>የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች</u>

1. የጠቅላላ ጉባዔው መደበኛ ስብሰባ በየዓመቱ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ የጠቅላላ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡
2. የጠቅላላ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ የሚችለው፡-

ሀ/ በፋውንዴሽኑ ፕሬዚዳንት ውሳኔ፤

ለ/ በቦርዱ ውሳኔ፤ ወይም

ሐ/ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል በአንድ ሦስተኛ ድምጽ ሲጠየቅ፤

ይሆናል፡፡

11. <u>የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ ሥነ ሥርዓት</u>

1. የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ በፋውንዴሽኑ ፕሬዚዳንት ይመራል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ/ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

ለ/ ማንኛውንም ውሳኔ ማሳለፍ የሚቻለው በስብሰባው ከተገኙት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ድምጽ ሲገኝ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሀ) መሰረት ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ ጉባዔው በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ይጠራል፡፡ በሁለተኛ ጥሪ የተሰበሰበው ጉባዔ በተገኙ አባላት የድምጽ ብልጫ ውሳኔዎችን ሊያሳልፍ ይችላል፡፡
4. እያንዳንዱ የጠቅላላ ጉባዔ አባል አንድ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
5. የጠቅላላ ጉባዔው ውይይቶችና ውሳኔዎች ቃለ ጉባዔዎች በፋውንዴሽኑ ፕሬዚዳንትና በሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተሩ ይፈረማሉ፡፡

12. <u>የቦርዱ አባላት</u>

1. ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ቤተሰብ አራት ተወካዮች፤ እና

ለ/ በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ ዘጠኝ አባላት፡፡

2. የፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ድምጽ የማይሰጥ አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

13. <u>የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(1)(ለ) የተመለከቱት የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ለአራት አመታት ይሆናል፤ ሆኖም አባላቱ ለቀጣይ የአገልግሎት ዘመናት እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

14. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የፋውንዴሽኑን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስችለው ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን ቦርዱ፡-

1. ከአባላቱ መካከል የፋውንዴሽኑን ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ይመርጣል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተደነገገው የፋውንዴሽኑ ተግባር በሚገባ መከናወኑን ያረጋግጣል፤
3. የፋውንዴሽኑን የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ይመለምላል፣ ይሾማል፤ ሃላፊነቱን የማይወጣ ሆኖ ሲገኝ ያሰናብታል፤
4. በቀጥታ ለፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ተጠሪ በሆኑ የስራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን የስራ ሃላፊዎች ምደባ ያፀድቃል፤
5. የፋውንዴሽኑን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ያስፀድቃል፤
6. በፋውንዴሽኑ የውጭ ኦዲተር የተመረመረውን የሂሳብ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፤
7. የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በማይደረግበት ጊዜ የጉባዔውን ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በመስጠት በሚቀጥለው ስብሰባ አቅርቦ ያስፀድቃል፤
8. ለፋውንዴሽኑ ስራ ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ የሚሰበሰብበትን ስልት ይቀይሳል፣ አጠቃቀሙን ይወስናል፤
9. አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባራቸውንም ይወስናል፤
10. የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ ጊዜ፣ ቦታና አጀንዳ ይወስናል፤
11. ፋውንዴሽኑን በመወከል በአገር ውስጥና በውጭ አገር ግንኙነት ያደርጋል፤
12. የፋውንዴሽኑን የውስጥ ደንብና የራሱን የአሰራር መመሪያ ያወጣል፤

13.በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

15. **የፋውንዴሽኑ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር**

የፋውንዴሽኑ ፕሬዚዳንት፡-

1. የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርዱን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል፤
2. የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፤ ከፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ጋር በመመካከር የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ አጀንዳ ይቀርፃል፤
3. የጠቅላላ ጉባዔውና የቦርዱ ውሳኔዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
4. ቦርዱ ሊሰበሰብ በማይችልበት ጊዜ በፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር በሚቀርቡ አስቸኳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔዎቹንም ለተከታዩ የቦርዱ ስብሰባ አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡

16. **የፋውንዴሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር**

የፋውንዴሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

1. የፋውንዴሽኑ ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
2. በቦርዱ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

17. **የፋውንዴሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

የፋውንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ፡-

1. የፋውንዴሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የፋውንዴሽኑን የሥራ ዕቅድና ፕሮግራም እንዲሁም በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
3. የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርዱን ውሳኔዎች ሥራ ላይ ያውላል፤
4. በየዓመቱ እና እንደአስፈላጊነቱ በየወቅቱ የፋውንዴሽኑን የሂሳብ መግለጫዎች ለቦርዱ ያቀርባል፤
5. ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለራሱ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን ሃላፊዎች በመምረጥ ለቦርዱ አቅርቦ ያስጸድቃል፤
6. የፋውንዴሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
7. የፋውንዴሽኑን የውስጥ ደንቦች ለቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል፤
8. ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ፋውንዴሽኑን ይወክላል፤
9. የፋውንዴሽኑን ዓላማዎች ያስተዋውቃል፤

10.በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለፋውንዴሽኑ ገቢና የሂሳብ መግለጫዎች

### 18. የፋውንዴሽኑ የገቢ ምንጮች

ፋውንዴሽኑ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-

1. ከውርስ፣ ከስጦታ እና ከዕርዳታ ከሚገኝ ገንዘብና ንብረት፤
2. ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች፤
3. ከመንግስት ከሚሰጥ ጠቅላላ ወይም የፕሮግራም ድጎማ፤
4. ከሌሎች የገቢ ምንጮች፡፡

### 19.የፋውንዴሽኑ የበጀት ዓመት

የፋውንዴሽኑ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን እስከሚቀጥለው ሰኔ 30 ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

### 20. ስለዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ አቀራረብ

1. የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እስከ 4 ወር ባለው ጊዜ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት ለቦርዱ ይቀርባል፡፡
2. በየዓመቱ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ይቀርባል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለመሆን

ፋውንዴሽኑ ለስራ ማስፈፀሚያ ወደአገር የሚያስገባቸው ዕቃዎች፣ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ፡፡

### 22. አዋጁን ስለማሻሻል

ይህ አዋጅ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት ሁለት ሦስተኛው ተገኝተው ከዚህ ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የተስማሙበት የማሻሻያ ሀሳብ ለመንግስት ቀርቦ ሲፈቀድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 23. የውስጥ ደንቦችን የማውጣት ስልጣን

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ የፋውንዴሽኑን የውስጥ ደንቦች ማውጣት ይችላል፡፡

### 24.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር 17 ቀን 2005 ዓ/ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## አዋጅ ቁጥር 783/2005

## የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚን ማቋቋሚያ አዋጅ

የማላመድና ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማስፋፋት ለአገሪቱ ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ፤

ቴክኖሎጂን በመማርና በማላመድ ላይ የሚካሄዱ የጥናትና የምርምር ስራዎች የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓትን በመደገፍ የአገሪቱን ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያግዙ በመሆኑ፤

ሳይንስና ሳይንሳዊ አሠራር የአገሪቷን የወደፊት አቅጣጫ በሚመለከቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ጥራትና ብቃት ላይ ከፍተኛ አስተዋፆ የሚኖረው በመሆኑ፤

ትክክለኛ የመንግስት ፖሊሲ ዝግጅትና የአፈፃፀም ሂደትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚካሄዱ ጥናትና ምርምሮች በቂ የሆነ ሳይንሳዊ መረጃ በያዙ እጪቅ ባለሙያዎች መደገፉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በብሔራዊ የኢኖቬሽን ሥርዓት ውስጥ በባለድርሻ አካላት መካከል በሚደረገው ግንኙነት በሚካሄደው ጥናትና ምርምር እና በሚሰጠው በመረጃ ላይ የተመሰረተ ሙያዊ እገዛ ለቴክኖሎጂ ሽግግር የራሱን ሚና የሚጫወት አገር አቀፍ የሳይንስ አካዳሚን ማቋቋም የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 783/2005” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ሳይንስ” ማለት የተፈጥሮ ሳይንስ፣ የሂሣብ፣ የጤና፣ የግብርና፣ የምሕንድስና እና የማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፎችን የሚያካትት ሲሆን የሰብዓዊና የሥነ ጥበብ ዘርፎችንም ይጨምራል፤

2. “ሳይንቲስት” ማለት በሳይንስ ምርምርና ጥናት ሥራዎች የተሰማራ ምሁር ወይም ባለሙያ ነው፤
3. “ጠቅላላ ጉባዔ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 (1) የተመለከተው የአካዳሚው ጠቅላላ ጉባዔ ነው፤
4. “ቦርድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 (2) የተመለከተው የአካዳሚው ቦርድ ነው፤
5. “የአገልግሎት ክፍያ” ማለት አካዳሚው ለሚሰጠው በእውቀት ላይ የተመሠረተ የማማከርና ሌሎች አገልግሎቶች የሚያስከፍለው ክፍያ ነው፤
6. “ፋውንዴሽን” ማለት አካዳሚው ከመንግስት ይሁን ከሌላ አካል በአንድ ጊዜ ወይም በተለያየ ጊዜ የሚያገኘውና በቀጣይነት ገቢ የሚያስገኝ ሃብት ነው፤
7. “ሚኒስቴር” ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤
8. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. **መቋቋም**

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ (ከዚህ በኋላ “አካዳሚ” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የአካዳሚው ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ በሌሎች ስፍራዎች እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

5. **ዓላማዎች**

አካዳሚው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ቴክኖሎጂን በመማር እና በማላመድ ላይ ያተኮረ ምርምርን መደገፍና ማበረታታት፤
2. የሰውን የኑሮ ደረጃና አኗኗር ማሻሻል የሚያስችሉ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች፣ ተግባራዊ የሳይንስ ዕውቀት፣ አገር በቀል ቴክኖሎጂዎች እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ ማበረታታት፤
3. ሳይንስን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች በተለይም በሳይንስ ትምህርትና ምርምር ጥራትና አግባብነት ላይ መንግሥትን ማማከር፤
4. በአገሪቱ የሚካሄዱ ሳይንሳዊ ምርምሮች ችግር ፈቺና ለአገሪቱ ልዩ ጠቀሜታ ባላቸው ዘርፎችና ጉዳዮች ዙሪያ እንዲከናወኑ ማበረታታት፤

5. በኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች የሚከናወኑትን ችግር ፈቺና ብቃት ያላቸው የሳይንስ ምርምር ሥራዎች ማበረታታትና መደገፍ፤
6. ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች የሚኖራቸውን የእርስ በርስና ከዓለም አቀፍ የሳይንስ ማኅበረሰብ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ማጠናከር፤
7. በኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች የተካሄዱ ሳይንሳዊ ምርምሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖራቸውን ተቀባይነትና ሚና ማጠናከር፤
8. ዋና ዋና የሳይንስ ግኝቶችን በሰፊው እንዲታወቁ ለማድረግ የሚያስችሉ ህዝባዊ መድረኮችንና አግባብ ያላቸዉን ሌሎች መርሀ-ግብሮችን ማደራጀት፡፡

## 6. ተግባራትና ችሎታ

አካዳሚው የሚከተሉት ተግባራትና ችሎታ ይኖሩታል፡-

1. በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ሳይንቲስቶች በጋራ ጉዳዮች ላይ መምከር ይችሉ ዘንድ አስፈላጊ የውይይትና የምክክር መድረኮች እንዲኖሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
2. በአገር አቀፍ፣ በአካባቢያዊ እና በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የኢትዮጵያ የሳይንስ ማህበረሰብን ጥቅሞች ማራመድ፤
3. የጋራ ዓላማ ካላቸው አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የግንኙነት መረብ እና ትብብር እንዲፈጠር ማድረግ፤
4. አገራዊ ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሳይንሳዊ ጥናት ማካሄድና የጥናት ግኝቶቹን የሚመለከቱ ሪፖርቶችን ለሕትመት ማብቃት፤
5. አገራዊ ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ምርምር ለሚያካሂዱ ሳይንቲስቶች አቅም በፈቀደ መጠን የገንዘብ ድጋፍ መስጠት፤
6. በተሰማሩባቸው መስኮች ወይም የአካዳሚውን ዓላማዎች በሚያራምዱ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ሥራዎች ለሠሩ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች ሽልማቶችን መስጠት፤
7. ለሳይንስ ማህበረሰቡና ለጠቅላላው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚውሉ የራሱን የምርምር መጽሔቶች፣ ሌሎች በየጊዜው የሚወጡ ፅሁፎች እና መፃሕፍት ማሳተም፤
8. በዓለም አቀፍ የሳይንስ አካዳሚዎች መድረኮች መሳተፍ፤
9. የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚያግዙ ስብሰባዎችን፣ ዐውደ-ጥናቶችን እና የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት እና መርሃ-ግብሮችን መቅረፅና መተግበር፤

10.የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

11.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

7. <u>ከመንግሥት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት</u>

1. አካዳሚው፡-

ሀ/ በሚኒስቴሩ አማካኝነት ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ይኖረዋል፤

ለ/ ከሚኒስቴሩና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሳይንሳዊ ምክር ይሰጣል፤

ሐ/ ከዓላማዎቹና ተግባሮቹ ጋር የተያያዙ ሌሎች አገልግሎቶችን ለመንግስት ይሰጣል፡፡

2. መንግሥት በፋይናንስና አግባብነት ባላቸው ሌሎች መንገዶች አካዳሚውን ይደግፋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>አባልነት</u>

8. <u>የአባልነት አይነቶች</u>

አካዳሚው የሚከተሉት የአባልነት ዓይነቶች ይኖሩታል፡-

1. መደበኛ አባል፤
2. ተባባሪ አባል፤ እና
3. የክብር አባል፡፡

9. <u>ለአባልነት ስለሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

1. ማንኛውም፡-

ሀ/ በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

ለ/ በኢትዮጵያ ዉስጥ ነዋሪ የሆነ፤ እና

ሐ/ በተሰማራበት መስክ የላቀ አስተዋፆ ያበረከተ፤

ሳይንቲስት የአካዳሚው መደበኛ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

2. የኢትዮጵያ ዜግነት የሌለው ሳይንቲስት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ለኢትዮጵያ ሳይንስ ዕድገት ጉልህ አስተዋፆ ያበረከተ ከሆነ የአካዳሚው ተባባሪ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

3. ለአካዳሚው ዓላማዎች መሳካት የላቀ አስተዋፆ ያደረገ ማንኛውም ሰው የአካዳሚው የክብር አባል ሊሆን ይችላል፡፡

10.<u>አባልነትን ስለመፍቀድ</u>

1. አካዳሚው በየዓመቱ አዲስ አባላትን ይቀበላል፡፡ በየዓመቱ የሚቀበለው የተጨማሪ አባላት ቁጥር በአካዳሚው ውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡
2. ለአካዳሚው አባልነት የሚደረግ ዕጩ ጥቆማ ቢያንስ በሁለት የአካዳሚው መደበኛ አባላት በጽሁፍ መቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶችን የሚያሟላ ማንኛውም ሳይንቲስት አባልነት እንዲፈቀድለት በጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሰረት የሚቀርብ የዕጩ ጥቆማ ወይም ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-
   ሀ/ ዕጩው ወይም አመልካቹ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ መሆኑንና ለዚህም ብቁ ያደርገዋል የተባለውን ዋናውን ሥራውን የሚያሳይ መግለጫ፤
   ለ/ ከተለያየ የዕውቀት ዘርፍ በተውጣጡ አምስት ሰዎች ስለዕጩው ወይም አመልካቹ በጽሑፍ የተሰጠ ምስክርነት፤
   ሐ/ የዕጩውን ወይም የአመልካቹን አጭር የሕይወት ታሪክና ዋና ዋና ናቸው የሚባሉትን ሕትመቶቹንና ሙያዊ ሥራዎቹን የሚያሳይ ዝርዝር፡፡
5. ቦርዱ የዕጩ ጥቆማዎችንና ማመልከቻዎችን መርምሮ የተሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የዕጩ አባላትን ዝርዝር ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡
6. ጠቅላላ ጉባዔው አባላትን በሚፈቅድበት ጊዜ የእያንዳንዱን ዕጩ አባል የግል ብቃት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሳይንስ ዘርፎች፣ በዕድሜ እና በፆታዎች መካከል የሚኖረውን የአባላት ስብጥር ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
7. የአካዳሚው መደበኛ አባላትና ሠራተኞች በስራቸው አጋጣሚ ያገኟቸውን የአካዳሚውን ዕጩ አባላትና አባላት መረጃዎች በሚስጥር መጠበቅ አለባቸው፡፡

11.<u>የአባላት መብትና ግዴታ</u>

1. ማንኛውም የአካዳሚው መደበኛ አባል፡-
   ሀ/ በአካዳሚው ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች የመሳተፍና በውሳኔዎች አሰጣጥ ላይ ድምፅ የመስጠት፤ እና
   ለ/ ለማንኛውም የአካዳሚው አመራር አባልነት የመምረጥና የመመረጥ፤
   
   መብት ይኖረዋል፡፡

2. ማንኛውም የአካዳሚው መደበኛ አባል፡-

ሀ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና የአካዳሚውን የውስጥ ደንቦችና ውሳኔዎች የማክበር፤

ለ/ ለአካዳሚው ዓላማ መሳካት አስፈላጊውን አስተዋፆ የማድረግ፤ እና

ሐ/ የአባልነት መዋጮ የመክፈል፤

ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

3. የአካዳሚው ተባባሪ እና የክብር አባላት መብቶችና ግዴታዎች በአካዳሚው የውስጥ ደንቦች ይወሰናሉ፡፡

12. <u>ስለአባልነት መቋረጥ</u>

1. አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣል፡-

ሀ/ አባሉ በራሱ ፈቃድ አባልነቱን ሲተው፤

ለ/ አባሉ ይህን አዋጅ ወይም የአካዳሚውን የውስጥ ደንቦች ወይም ውሳኔዎች ሲጥስ፤

ሐ/ አባሉ የሳይንስ ሥነ-ምግባር ደንብን ሲጥስ፤

መ/አባሉ የአባልነት ግዴታዉን ባለመወጣቱ፤ ወይም

ሠ/ አባሉ በማናቸውም ሁኔታ የአካዳሚውን መልካም ስም የሚያጎድፍ ወይም የአካዳሚውን ጥቅም የሚፃረር ሥራ ሲሰራ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አባልነት የማቋረጥ ውሳኔ የሚሰጠው ቦርዱ በሚያቀርበዉ የዉሳኔ ሀሳብ መሠረት በጠቅላላ ጉባዔው ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተራ ፊደል (ለ) እስከ (ሠ) አባልነት ማቋረጥን በተመለከተ በውስጠ ደንብ ይዘረዘራል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የአካዳሚው አመራር</u>

13.<u>የአመራር አካላትና ሠራተኞች</u>

አካዳሚው፡-

1. ጠቅላላ ጉባዔ፤
2. ቦርድ፤
3. ስራ አስፈፃሚ፤
4. የስራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተር፤ እና
5. አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

14. **ጠቅላላ ጉባዔው**

1. ጠቅላላ ጉባዔው የአካዳሚው መደበኛ አባላት በሙሉ የሚገኙበት ይሆናል፤ ሆኖም የአካዳሚው ተባባሪ እና የክብር አባላት ያለ ድምጽ በጉባዔው ስብሰባዎች ይሳተፋሉ፡፡
2. ጠቅላላ ጉባዔው አካዳሚውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የአካዳሚውን የውስጥ ደንቦች ያጸድቃል፤

   ለ/ የአካዳሚውን ፕሬዚዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዐቃቤ ንዋይ እና ሌሎች የአካዳሚውን ቦርድ እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፣ ያሰናብታል፤

   ሐ/ አካዳሚው አዲስ አባላት እንዲቀበል ይፈቅዳል፤

   መ/ የአካዳሚውን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፤

   ሠ/ የአካዳሚውን ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርቶች ያፀድቃል፤

   ረ/ የአካዳሚውን ኦዲተሮች ይሰይማል፤

   ሰ/ በቦርዱ አቅራቢነት ሽልማቶችን ይሰጣል፤

   ሸ/ በሞት፣ የመስራት ችሎታ በማጣት ወይም በአባልነት መቋረጥ ምክንያት አገልግሎቱ የተቋረጠ የቦርድ አባልን ለመተካት አዲስ የቦርድ አባል ይመርጣል፤

   ቀ/ የአካዳሚውን መደበኛ አባላት የሳይንስ መስኮቻቸውን መሠረት በማድረግ ሊሳተፉ በሚችሉባቸው ልዩ ልዩ ዘርፎች ይመድባል፤

   በ/ እንደአስፈላጊነቱ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

15. **የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ**

1. ጠቅላላ ጉባዔው ቢያንስ በዓመት አንድ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡
2. በፕሬዚዳንቱ ወይም በቦርዱ ውሳኔ ወይም ከአካዳሚው መደበኛ አባላት ቢያንስ በአንድ አምስተኛው ሲጠየቅ በማንኛዉም ጊዜ የጠቅላላ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፡፡
3. ከአካዳሚው መደበኛ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

4. የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ፕሬዚዳንቱ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
5. ጠቅላላ ጉባዔው በሚስጥር ድምፅ እንዲሰጥ ካልተወሰነ በስተቀር በስብሰባ ላይ ድምፅ የሚሰጠው እጅ በማውጣት ይሆናል፡፡
6. መደበኛ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሚካሄድበት ስፍራና ጊዜ በጠቅላላ ጉባዔው ይወሰናል፡፡ ሆኖም የጠቅላላ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ የሚካሄድበት ስፍራና ጊዜ በቦርዱ ይወሰናል፡፡
7. የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የሚጠራው በጽሁፍ ሆኖ ጥሪው ከስብሰባው አጀንዳ ጋር ከስብሰባው እለት 21 ቀን በፊት ለሁሉም የአካዳሚው አባላት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡
8. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 16.<u>የቦርድ አባላት</u>

1. ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

    ሀ/ የአካዳሚው ፕሬዚዳንት ....... ሰብሳቢ፤

    ለ/ የአካዳሚው ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ...... አባላት፤

    ሐ/ የአካዳሚው ዐቃቤ ንዋይ ............ አባል፤

    መ/ በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ አራት የአካዳሚው መደበኛ አባላት......አባላት፤

    ሠ/ የሚኒስቴሩ አንድ ተወካይ .........አባል፤

    ረ/ ከመንግሥታዊ የምርምር ተቋማት በመንግሥት የሚመደቡ ሁለት ተመራማሪዎች........አባላት፤

    ሰ/ የአካዳሚው ሥራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተር .........ፀሐፊ (ያለድምፅ)፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተመለከቱት የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ለሦስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና መመረጥ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 14 (3) (ሸ) መሠረት በምትክነት የተመረጠ አባል ለቀጣይ ሁለት የሥራ ዘመናት መመረጥ ይችላል፡፡

## 17.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአካዳሚውን የውስጥ ደንቦች ማዘጋጀትና በጠቅላላ ጉባዔው ሲጸድቁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ፤
2. የአካዳሚውን ሥራዎች በአግባቡ ለመምራት የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ማውጣት፤
3. የአካዳሚውን ሥራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተርና ለርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን መቅጠር እና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ሳይችሉ ሲቀር ማሰናበት፤
4. የአካዳሚውን ገንዘብና ንብረት አያያዝ ጨምሮ ማናቸውንም አካዳሚውን የሚመለከቱ ጉዳዮች አመራር በበላይነት መቆጣጠር፤
5. የአካዳሚውን ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀት እና የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርቶችን በመመርመር በጠቅላላ ጉባዔው እንዲጸድቁ ማቅረብ፤
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 (6) መሠረት የሚሰጡ ሽልማቶችን በሚመለከት የውሳኔ ሃሳቦችን ለጠቅላላ ጉባዔው ማቅረብ፤
7. በአካዳሚው ውስጥ እየተካሄዱ ስላሉ ዋና ዋና ጉዳዮችና ውሳኔዎች ሁሉም አባላት በየወቅቱ እንዲያውቁ ማድረግ፤
8. የጠቅላላ ጉባዔውን አጀንዳዎች ማዘጋጀትና ስብሰባዎችን መጥራት፤
9. በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

18.<u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ስድስት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የቦርዱ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የድምፅ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ፕሬዚዳንቱ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

19.<u>የፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር</u>

የአካዳሚው ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፤
2. የጠቅላላ ጉበዔውና የቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
3. አካዳሚውን ከመንግሥትና ከተባባሪ አካላት ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ይወክላል፤

4. በጠቅላላ ጉባዔውና በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 20.የተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር

1. የአካዳሚው ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት በቦርዱ ተለይቶ በሚወሰነው ዘርፍ ፕሬዚዳንቱን ይረዳሉ፡፡
2. ፕሬዚዳንቱ በማይገኝበት ጊዜ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሰራል፡፡ ሁለቱም በማይገኙበት ጊዜ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሰራል፡፡

## 21. የዐቃቤ-ንዋይ ስልጣንና ተግባር

የአካዳሚው ዐቃቤ-ንዋይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአካዳሚውን የፋይናንስ ሪከርድ ኢያያዝና የገንዘብና የሃብት አጠቃቀምን በተመለከተ የበላይ ኃላፊ ይሆናል፤
2. በየዓመቱና እንደ አስፈላጊነቱ በየሩብ ዓመቱ የአካዳሚውን የፋይናንስ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

## 22.የሥራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

1. የአካዳሚው ሥራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተር በቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአካዳሚውን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተሩ፡-

   ሀ/ የአካዳሚውን የሥራ ክፍሎች አደረጃጀትና የሰው ሃይል ፍላጎት አጥንቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

   ለ/ በጸደቀው አደረጃጀትና የሰው ሃይል ፍላጎት መሠረት የአካዳሚውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

   ሐ/ የአካዳሚውን መርሃ-ግብሮችና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

   መ/ በጸደቀው የአካዳሚው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (3) ከተመለከቱት በስተቀር አካዳሚው ከሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ አካዳሚውን ይወክላል፤

   ረ/ የአካዳሚውን የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሰ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3/ የሥራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት ዳይሬክተሩ የአካዳሚውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ በሆነ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች የአካዳሚው የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የአካዳሚው በጀትና ፋይናንስ

23. በጀት

1. የአካዳሚው በጀት ከሚከተሉት ምንጮች በሚገኝ ገንዘብ የሚሸፈን ይሆናል፡-

ሀ/ ከመንግስት በሚሰጥ የበጀት ድጋፍ፤

ለ/ ከአገልግሎት ክፍያ፤

ሐ/ ከአባላት መዋጮ፤ እና

መ/ ከሌሎች ምንጮች፡፡

2. አካዳሚው ዘላቂ የሆነ የፋይናንስ ምንጭ ለመፍጠር እንዲያስችለው የገቢ ማስገኛ ፋውንዴሽን ማቋቋም ይችላል፡፡

3. የአካዳሚው የበጀት ዓመት የፌደራሉ መንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

24. የሂሳብ መዛግብት

1. አካዳሚው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የአካዳሚው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በጠቅላላ ጉባዔው በሚሰየም የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

25. ይፋዊ መግለጫዎች

1. የአካዳሚውን አቋም የሚያንፀባርቁ ይፋዊ መግለጫዎች ሊሰራጩ የሚችሉት በቦርዱ ከጸደቁ በኋላ ነው፡፡

2. ፕሬዚዳንቱ አካዳሚውን አስመልክቶ የሚዘጋጁ ይፋዊ መግለጫዎችን በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

3. ፕሬዚዳንቱ ይፋዊ መግለጫው የተሟላ መሆኑን ሲያምን ስለመግለጫው አሰጣጥና ስለ ስርጭት ዘዴው ለቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

26. የአካዳሚውን የውስጥ ደንቦች የማውጣት ሥልጣን

1. ጠቅላላ ጉባዔው ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የአካዳሚውን የውስጥ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ የውስጥ ደንቦች በሚኒስቴሩና ቦርዱ በጋራ ተዘጋጅተው በጠቅላላ ጉባዔው መፅደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

27.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ሚኒስቴሩ የአካዳሚውን መሥራች አባላት የያዘ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚካሄደው ጠቅላላ ጉባዔ የአካዳሚውን የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዐቃቤ-ንዋይ እና ሌሎች የቦርድ አባላት ይመርጣል፡፡

28.<u>የአዋጁ መሻሻል</u>

ከአካዳሚው መደበኛ አባላት ቢያንስ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት በተገኙበት ጠቅላላ ስብሰባ ቢያንስ ሁለት ሶስተኛ በሆነ ድምጽ ሲወሰንና ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ሲፀድቅ ይህ አዋጅ ሊሻሻል ይችላል፡፡

29.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 17 ቀን 2005 ዓ/ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**